ተስፋ እንዳትቆርጥ የሚያስፈልግህ ኀይል

# ጽናት

## ጆን ቢቨሬ

የሰይጣን ሽንገላ የተሰኘው ከፍተኛ ተነባቢ መጽሐፍ ደራሲ




የዚህ ጽናት የተሰኘው መጽሐፍ ማጥኛ ዲቪዲ ተካትቶአል፡፡

ተስፋ እንዳትቆርጥ የሚያስፈልግህ ኀይል

# ጽ ና ት

## ጆን ቢቨሬ

**የሰይጣን ሽንገላ** የተሰኘው ከፍተኛ ተነባቢ መጽሐፍ ደራሲ

ትርጒም፡- በተስፋዬ መስፍን

ተስፋ እንዳትቆርጥ የሚያስፈልግህ ኃይል - ጽናት

በጆን ቢቨሬ John Bevere

© 2014 Messenger International

www.Messegerinternational.org

Originally Published in English

ከ www.cloudlibrary.org በነጻ ለመውሰድ በአማርኛ ያሉ ተጨማሪ መጻሕፍት፡- የሰይጣን ሽንገላ - በጆን ቢቨሬ፤ የጽናት መጽሐፍ የጥናት መመሪያና በጽሞና ማሰላሰያ - በጆን ቢቨሬ - እንስት አንበሶቹ ይነሣሉ - በሊዛ ቢቨሬ እንዲሁም የ30 ደቂቃ መልእክቶች የያዙ 12 ቪድዮና ኦዲዮ ሲዲዎች፡፡

ለማባዛት፣ በኢንተርኔት ለማሰራጨት፣ ጠቃሚ ሐሳቦችን ለመጠቀም ወይም ይህን የአማርኛ መልእክት ከሌሎች ጋር ለመከፋፈል ትበረታታላችሁ፡፡

የመጽሐፉን ደራሲ ለማግኘት - JohnBevere@ymail.com

Translated to Amharic by – Tesfaye Mesfin

Computer Setting by – Betelhem Minas

## ማውጫ


መግቢያ ............................................................................ 1

1. ጽናት - የአንድ ነገር ፍጻሜ ከጅማሬው ይሻላል..................... 4
2. በሕይወት መንገሥ.................................................... 16
3. የኃይሉ ምንጭ ........................................................ 29
4. ኢየሱስ የተመላለሰው እንዴት እንደ ነበር ........................... 40
5. ራስን መለየት፣ ልቆ መገኘት ......................................... 52
6. ማየት ወይስ መግባት .................................................. 74
7. ከመከራው በስተ ጀርባ ያለው ማነው? .............................. 94
8. ታጥቃችሁ ተነሡ ...................................................... 115
9. በጸጋው በርቱ ......................................................... 132
10. የትሕትና መሣሪያ .................................................... 139
11. ሽክምን እንጣል ....................................................... 154
12. ራሳችን ግዙ፤ ንቁ ...................................................... 173
13. ዲያቢሎስን ተቃወሙት ................................................. 187
14. ላቅ ያለ የመቃወም መንገድ ........................................... 204
15. ጽናት ያለው ጸሎት ..................................................... 219
16. ሽልማት እንደሚቀበል ሩጡ ............................................ 235
17. ወደ ንጉሡ መቅረብ ..................................................... 250
18. ተስፋ አትቁረጡ! ....................................................... 258

ተጨማሪ - ሀ

የእግዚአብሔር ልጅ ለመሆን ጸሎት .................................. 268

ተጨማሪ - ለ

የተለያዩ የመጽሐፍ ቅዱስ ትርጉሞች የተጠቀምኩበት ምክንያት... 271

ለማስታወስና ለውይይት ................................................ 272

## መግቢያ

ይህን መጽሐፍ ማዘጋጀት ከመጀመሬ ጥቂት ቀደም ሲል የጽናትን አስፈላጊነት በሚገባ የሚያሳይ አንድ ፊልም ዐይቼ ነበር፡፡ ፊልሙ በሚካኤል ዳግላስ እና በቫል ኪልመር መሪ ተዋናይነት የተሠራ *The Ghost and the Darkness* የተሰኘ ሲሆን ታሪኩ በ1800ዎቹ ማለቂያ የሆነ ጉዳይ ላይ የተመሠረተ ነበር፡፡

በፊልሙ መሠረት ብሪቲሾች የምሥራቅ አፍሪካን የባቡር መስመር ዝርጋታ ለማፋጠን የዩጋንዳን ሳቮ ወንዝ አልፎ የሚሄድ የባቡር መስመር ሥራ ግንባታ እንዲቆጣጠር አንድ ፓተርሰን (ቫል ኪልመር) የሚሉት ባለ ብሩህ አእምሮ ወታደራዊ መሐንዲስ ተቀጥሮ ነበር፡፡ ፓተርሰን ወደ ቦታው በሄደ ጊዜ እንኳ ፕሮጀክቱ በጣም ወደ ኋላ ተጓትቶ ነበር፡፡

ምክንያቱን ለማወቅ ጊዜ አልወሰደበትም፡፡ በየጊዜው ሠራተኞች እየጠፉ ነበር፡፡ ጨለማን ተገን በማድረግ ድጋሚ እዚያ ቦታ ላለመገኘት ይሰወሩ ነበር፡፡ ለዚህ ምክንያቱ ደግሞ ሰዎች እየበሉ የነበሩ ሁለት አንበሶች መሆናቸውን ፓተርሰን ወዲያውኑ ተረዳ፡፡ እነርሱን በመግደል ሰዎች ላይ የሚያደርሱትን ጥቃት ለማስቆም ወጥመድ አደረገ፤ የተለያዩ ዘዴዎችን ሞከረ፤ ሆኖም ሁለቱ አንበሶች የፓተርሰንን እንቅስቃሴ አስቀድመው ያወቁ ይመስል ወጥመዱ እንዳይዛቸው ጥንቃቄ ያደርጉ ነበር፡፡

የሞቱት ሰዎች ቁጥር ሰላሣ ሲደርስ የባቡር መሥመሩ ሥራ ኃላፊዎቹ ቻርለስ ሬሚንግተን (ሚካኤል ዳግላስ) የሚባል አሜሪካዊ አዳኝ ቀጠሩ፡፡ ይህ ሰው በአደን ሙያው የታወቀ ቢሆንም፣ አንበሶቹ ግን ማጥቃታቸውን እንደ ቀጠሉ ነበር፡፡ በየሌሊቱ ሰዎች ይበሉ ነበር፤ በኋላም ሠራተኞቹ፣ ‹‹እነዚህ አንበሶች ክፉ መናፍስት ናቸው፤ ማንም ሊያስቆማቸው አይችልም›› የሚል መደምደሚያ ላይ ደረሱ፡፡ የሞቱት ሰዎች ቁጥር 130 ሲደርስ የሥራው ካምፕ ሰዎች በጣም ተሸበሩ፤ በጣም ግራ ተጋቡ፤ ፓተርሰንና ሬሚንግተንም ጠቅላላ ሠራተኞች በሳቮ በሚያልፍ ባቡር ላይ እየተንጠለጠሉ ሲሸሹ ተስፋ ቆርጠው ከማየት በቀር ምንም ማድረግ አልቻሉም፡፡

እኔንም ያነሣሣኝ ይህ የሕይወትን ሐቅ የሚያሳይ ሁኔታ ነበር፡፡ መስመሮቹ በግልጽ ተሰምረዋል፡፡ በአንድ በኩል ለመፈጸም የተስማሙትን ሥራ ጥለው እንዲሄዱ የሠራተኞቹን ፍርሃት እያባባሰ ያለ ተቆጣጣሪው አለ፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ ሬሚንግተንን፣ ፓተርሰንን እና የፓተርሰን ረዳትን

የመሳሰሉ ከተግባራቸው ወደ ኃላ የማይሉና ፍርሃት እጅ እንዲሰጡ ያላደረጋቸው ሦስት ሰዎች አሉ፡፡

አሁን አደገኞቹን ጠላቶች ለመጋፈጥ ሦስቱ ሰዎች ብቻ ቀርተዋል፡፡ ብዙ ጊዜ ሊገድሏቸው እየሞከሩ ሳይሆንላቸው ቀርቷል፡፡ ፊት ለፊታቸው ያለው ግዳጅ አሰልቺና እጅግ ሲበዛ አደገኛ ነበር፡፡ ከዚያም በላይ ሕይወታቸውን እንኳ ሊያሳጣቸው ይችላል፤ ያም ሆኖ ግን ችግሩን ለማስቆምና ድልድዩን ለማስጨረስ ቆርጠዋል፡፡ በዘመኑ አሉ የተባሉ መሣሪያዎች ይዘዋል፡፡ በጥበብ፣ በንቃት፣ በቆራጥነት ከተንቀሳቀሱ እና ተስፋ ካልቆረጡ መጨረሻ ላይ እንደሚያሸንፉ ሬሚንግተንና ፓተርሰን እርግጠኞች ነበሩ፡፡

እዚህ ላይ ብዙ ዝርዝር ነገር ለማቅረብ ቦታውም ጊዜውም አይበቃም፣ ግን ይህን በሚገባ ማወቅ አለባችሁ - በመጨረሻ ሰው በላ አንበሶቹ ጥቃታቸውን ያቆማሉ፡፡ ሆኖም፣ ያ ድል የሚገኘው ትልቅ ዋጋ ተከፍሎ ነው፡፡

አሁን ችግሩ መፍትሔ ስላገኘ ሠራተኞቹ ወደ ሥራ ቦታቸው መመለስ ጀመሩ፣ አሁን የፕሮጀክቱ መሐንዲስ ፓተርሰንን የሚያዩት በጣም በተለየ ሁኔታ ሆኗል፡፡ ሞትን ፊት ለፊት በመጋፈጥ ለሁኔታው አስቸጋሪነት እጅ ያልሰጠ እርሱ ነበር፡፡ ሰዎቹ ለእርሱ እጅግ ከፍ ያለ ከበሬታ ስለ ነበራቸው የማይቻል የሚመስል ነገር እንኳ ለመፈጸም ከኃላው ለመሰለፍ ፈቃደኞች ሆነዋል፡፡ የድልድዩም ሥራ በተወሰነለት ጊዜ ተጠናቀቀ!

እንደ የእግዚአብሔር እንደራሴዎች (አምባሳደሮች) እኛም ድልድይ እየሠራን ነው፡፡ የእኛ ድልድይ ወንዞች የሚያሻግር ሳይሆን፣ በሰማይና በምድር መካከል የተዘረጋ ነው፡፡ እኛም እንዲሁ ተቃውሞ አለብን፤ መጽሐፍ ቅዱስ ጠላታችንን–የሚያገኘውን ሁሉ መዋጥ እንደሚፈልግ አንበሳ ብሎታል፡፡ ሆኖም እንደ እነዚያ አንበሶች ሁሉ ጠላታችን መሣሪያ የለውም… እኛ ግን አለን፡፡ እርሱ ተጥቅ እንዲፈታ ተደርጓል፤ እኛ ግን የሰው ልጅ ሊኖረው ከሚችለው ሁሉ የበለጠ ብርቱ መሣሪያ አለን፡፡

ማሸነፍ ያለብን ጦርነቶች አሉ፤ መቆጣጠር ያለብን ምሽጎች አሉ፡፡ ብዙ ጊዜ እነዚህ ነገሮች የአእምሮ ዝንባሌዎችን፣ የአሠራር መንገዶችን፣ ሥረ መሠረት ያደረጉና ጠላት በዚህ ዓለም ሰዎች አስተሳሰብ ውስጥ የነዛቸው አመለካከቶች ናቸው፡፡ የሚገጥመን ተቃውሞ እጅግ ከባድ ነው፤ ይሁን እንጂ፣ ‹‹በክርስቶስ›› እኛ ከዚያ ሁሉ በላይ ብርቱዎች ነን፡፡

ስለዚህ ፊት ለፊታችን በጣም አስፈላጊ ጥያቄ ተቀምጧል - *ሕይወታቸውን ለማዳን ከዚያ አስቸጋሪ ሁኔታ እንደ ሸሹ ሠራተኞች ነን ወይስ የተሰጠንን ሰማያዊ ኃላፊነት በጽናት የምንፈጽም?* በዚህ አሁን በማቀርበው መልእክት ውስጥ በሕይወታችሁ ጽናት እንዲጐለብት የሚያደርጉ እውነቶች እንዳሉ አምናለሁ፡፡ እነዚህ እውነቶች እንድትጎብዙና እንድትበረቱ ማድረግ ብቻ ሳይሆን፣ ለማሸነፍና ቀና ለውጥ ለማምጣት በሚያስችላችሁም ኃይል ያስታጥቋችኋል፡፡

በዚህ ዕውቀት መመሥረታችሁ እጅግ አስፈላጊ ነው፡፡ ምክንያቱም ባለ ማወቅ የእግዚአብሔር ሕዝብ ረጅም ዘመን ምርኮ ውስጥ ኖረዋል፤ ይህን በማጣትም ጠፍተዋል (ኢሳይያስ 5፥13፤ ሆሴዕ 4፥6 ይመ)፡፡ ትክክለኛ ዕውቀት የእምነት መሠረትን ይገነባል፤ እምነት ደግሞ በጠፋውና በጨለመው ዓለም ውስጥ ለውጥ ማምጣት ያስችለናል፡፡

የተፈጠራችሁት በዙሪያችሁ ባለው ዓለም ቀና ለውጥ እንድታመጡ ነው፡፡ ተስፋ እንዳንቆርጥ የሚረዳንን የጽናት ኃይል ለማወቅ በምናደርገው ጥረት በጸሎት መንፈስ ተግዳሮቱን እንቀበል!

# 1

# ጽናት

*የአንድ ነገር ፍጻሜ ከጅማሬው ይሻላል።*

*መክብብ 7፥8*

አንድን ነገር፣ ‹‹*የምንፈጽምበት*›› ሁኔታ፣ ‹‹*ከምንጀምርበት*›› ሁኔታ የበለጠ ጠቃሚ ነው በሚለው እሳቤ ከእኔ ጋር እንደምንስማማ ቁጠሩ፡፡

በክርስትና ሕይወት መሠረት እንደሚገባ መጨረስ ማለት ጌታ፣ ‹‹አንተ ታማኝ አገልጋይ፣ መልካም አድርገሃል!›› ሲለን መስማት ማለት ነው፡፡ ለእኛ ሁሉም ነገራችን ከሆነው ጌታ እንዲህ ያሉትን ድንቅ ቃላት ለመስማት እኔና እናንተ የሚያስፈልገን ምን ይሆን?

ሕይወትን እንደሚገባ መጨረስ፣ ሕይወትን እንደሚገባ መኖርን ይጠይቃል፡፡ ይህ ደግሞ፣ ‹‹ተስፋ አለመቁረጥን›› ማሳደግን የሚጠይቅ መሆኑ አያጠራጥርም፡፡ በአጭሩ፣ ባለ ጽኑ መንፈስ መሆን ማለት ነው፡፡ ታዲያ ያንን የምናገኘው እንዴት ነው? ይህን ያህል አስፈላጊ የሆነውስ ለምንድነው?

እውነቱን ለመናገር ብዙ አማኞች እንደሚገባ መፈጸም አለመቻላቸው በጣም ያሳስበኛል፡፡ አንድ ጊዜ እግዚአብሔር ከዚህ መጽሐፍ ዐቢይ ሐሳብ ጋር የሚያያዝ ራእይ ሰጥቶኝ ነበር፡፡[1]

1. ይህን ራእይ ከዚህ ቀደም በጻፍኩት *A Heart Ablaze* በሚለው መጽሐፍ በአጭሩ አንስቼው ነበር፡፡ አሁን ግን ይህን ታሪክ እንደ ገና ማቅረብና የበለጠ ማብራራት እንዳለብኝ ተሰምቶኛል፡፡

# 5 ጽናት

እጅግ አደገኛ ማዕበል ባለበት ወንዝ ውስጥ አንድ ሰው ጀልባ እየቀዘፈ ነበር፡፡ ከዚያ ማዕበልና ወጀብ ለመውጣት የሚችለውን ያህል እየታገለ ነበር - ሥራው አስቸጋሪ ቢሆንም ከዐቅም በላይ ግን አልነበረም፡፡

እየተዝናኑ ያሉ ሰዎች የያዙ ሌሎች ትልልቅና ምቾት ያላቸው ጀልባዎች በየጊዜው በአጠገቡ ያልፉ ነበር፤ በውሃው ኃይል እየተነዱ ቁልቁል ይወርዱ ነበር፡፡ በእነዚህ ጀልባዎች የነበሩ ሰዎች ይስቁ ነበር፣ ይጠጡና ዘና ብለው ዐርፈው ነበር፡፡ አልፎ አልፎም ከማዕበሉ ጋር የሚታገለውን ሰው ዐየት እያደረጉ ያፌዙበት ነበር፡፡ ወደ ፊት አንድ ርምጃ ለመሄድ እርሱ እያንዳንዱን ስንዝር ይታገላል፤ እነርሱ ግን ምንም የሚያደርጉት አልነበረም፤ ቢያደርጉ እንኳ እጅግ ሲበዛ ጥቂት ነበር፡፡

ከጥቂት ጊዜ በኋላ ሰውየው ከማዕበሉ ጋር በሚያደርገው ትግል ሰለቸ፡፡ በጣም ተዳክሞና ተስፋ ቆርጦ መቅዘፊያዎቹን አስቀመጠ፡፡ በውሃው ግፊት ወዲያ ወዲህ እየተላጋ ጥቂት ወደ ፊት ሄደ፤ በኋላ ግን ቀጥ ብሎ ቆመ፡፡ ከዚያም በጣም አሳዛኝና አስጨናቂ ነገር ሆነ፣ ጀልባዋ ፊቷን ያቀናችው ወደ ፊት ቢሆንም፣ በወጀብና ማዕበሉ ተገፍታ ቁልቁል ወረደች፡፡

ሰውየው ወዲያውኑ ሰዎች የሞሉባት አንድ ጀልባ ያያል፡፡ ይህኛው እስካሁን ካያቸው ጀልባዎች የተለየ ነበር፤ ልክ እንደ የእርሱ ጀልባ ሁሉ ፊቱን ወደ ላይ ያቀና ቢሆንም፣ በማዕበሉ ተገፍቶ ቁልቁል እየወረደ ነበር፡፡ ይኸኛውም ጀልባ የሚስቁ፣ የሚንጫጩና ዘና ያሉ ሰዎች ይዞ ነበር፡፡ ሰውየው መሄድ ፈልጎ ወደ ነበረበት አቅጣጫ ወደ ላይ ያቀና ቢሆንም፣ እንጣጥ ብሎ በመዝለል ወደ እነርሱ ሄዶ ሊቀላቀላቸው ፈለገ፡፡ በዚህ ጊዜ ሁለቱ ጀልባዎች በጣም ተቀራርበውና ተጠጋግተው ነበር፡፡ ፊታቸውን ወደ ታች ካቀኑትና ወደዚያም እየሄዱ ከነበሩት ከሌሎቹ ጀልባዎች በተለየ መልኩ ይኸኛው ጀልባ ፊቱን ወደ ላይ አቅንቶ ነበር፡፡ ይሁን እንጂ፣ በማዕበሉ እየተገፋ በሚያሳዝን ሁኔታ ቁልቁል እየወረደ ነበር፡፡

የዚህ ራእይ ትርጉም ምንድነው? ወንዙ ይህን ዓለም ይወክላል፤ ጀልባው በዚህ ዓለም ለመኖርና ለመንቀሳቀስ የሚያስችለን የሰው ልጅ አካል ነው፡፡ ጀልባው ውስጥ የነበረው ሰው አማኝ ነው፤ መቅዘፊያው እንዲሁ በነጻ ከእግዚአብሔር የተቀበልነው ጸጋ ምሳሌ ነው፡፡ ሰዎች የነበሩባቸው ጀልባዎች ለአንድ ዓላማ መሰለፍን ያመለክታል፤ ወንዙ ላይ የተነሣው ማዕበል በክፉው ቁጥጥር ሥር ያለውን የዚህን ዓለም አካሄድ ይወክላል፡፡

በጸጋ መቅዘፊያ አማካይነት ሰውየው የእግዚአብሔርን መንግሥት እያስፋፋ ማዕበሉን ተቋቁሞ ወደ መጨረሻ ግቡ መድረስ ይችል ነበር፡፡

ድካምና ትግሉ የሰውየውን እምነት ይወክላል፡፡ በጣም የሚያሳዝነው ግን ዐቅሙ እየደከመና በውጊያው እየተሰላቸ እየሄደ ነበር፡፡ የሚያስፈልገው ሁሉ እንዳለው አላሰበም፤ እውነታው ግን በተሟላ ሁኔታ ሁሉም ያለው መሆኑ ነው፡፡ የኃላ ኃላ ያለው ዐቅም ሁሉ ተሟጦ ወደ ፊት መጓዙን አቋረጠ፡፡

ሰውየው መቅዘፉን ካቆመ በኃላም ቢሆን፣ ቀደም ሲል ከነበረው ግፊት የተነሣ ብቻ ለአጭር ጊዜ ጀልባዋ ወደ ፊት (ወደ ላይ) መንቀሳቀስ ቀጥላ ነበር፡፡ እንግዲህ መሳት የሚመጣው እዚህ ላይ ነው፡፡ ምንም እንኳ ፍሬዎቹን በሚያፈራው ኃይል እየተንቀሳቀስ ባይሆን እንኳ አሁንም ቢሆን፣ በሕይወቱ አንዳንድ ፍሬዎች እያየ ነው፡፡ ስለዚህም በመሳሳት ዘና ብዬ መኖር እችላለሁ ብሎ ያስባል፤ ንቃትና ትጋት ባይኖረውም፣ የተሳካ የክርስትና ሕይወት መኖር የሚችል ይመስለዋል፡፡

በመጨረሻ ጀልባዋ ቀጥ ብላ ትቆማለች፤ ከዚያም ወደ ኃላ መዋኘቅ ትጀምራለች (ወደ ታች) - መጀመሪያ በቀስታ፣ የኃላ ኃላም እየገፋት ባለው ማዕበል ፍጥነት ቁልቁል ትወርዳለች፡፡ እዚህ ላይ የራእዩን መልእክት ዘርዝር አድርገን እንይ፣ ጀልባው ፊቷን ያቀናችው ወደ ላይ ቢሆንም፣ በማዕበሉ እየዋለለች ወደ ኃላ እየተገፋች ነበር፡፡ እዚህ ደረጃ ላይ እያለም ቢሆን ሰውየው የክርስትና መልክ ነበረው - አነጋገሩን ይችላል፤ አዘማመሩን ይችላል፤ የእግዚአብሔር መንግሥት አኗኗርን ወግ ይችላል - እንደ እውነቱ ከሆነ ግን በዚህ ዓለም መንገድ እየኖረ ነው (1 ዮሐንስ 2፥15-17 ይመ)፡፡

በመጨረሻ የታሪካችን ባለቤት ሌላ ጀልባ - እንደ እርሱ፣ ‹‹አማኝ›› የሆኑ ሰዎች የያዘች ሌላ ጀልባ ያያል፡፡ የሁሉም ፊት ወደ ላይ ያቀና በመሆኑ፣ እነርሱም የቤተ ክርስቲያን አካል እንደ ሆኑ ያስባሉ፡፡ አነጋገሩን ያውቃሉ፤ አዘማመሩን ያውቃሉ፤ የአኗኗር ወጉን ያውቃሉ፡፡ ይሁን እንጂ፣ ፍሬ ቢስ፣ ‹‹የክርስትና›› ሕይወት እየኖሩና ማዕበሉን የሚቆጣጠረው ክፉ ኃይል ተገዥ በመሆናቸው ዘና ብለው ዐርፈዋል፡፡

በዚህ፣ ‹‹የክርስትና ጀልባ›› ውስጥ ያሉት ምንም ስደት የለባቸውም ወይም የማያምነው ዓለም አያፌዝባቸውም፡፡ እንዲያውም ተቀባይነት አግኝተዋል፤ አንዳንዴም ተፅዕኖ ፈጣሪ የሚባሉ ዓለማውያን እንኳ ላይቀሩ ያጨበጭቡላቸዋል፡፡ ‹‹እግዚአብሔር በክርስቶስ ኢየሱስ ወደ ላይ ስለ ጠራኝ ሽልማት ለመቀዳጀት ወደ ግቡ እፈጥናለሁ›› (ፊልጵስዩስ 3፥14) በማለት ሐዋርያው ጳውሎስ ክርስቲያኖችን ሁሉ በሚመክርበት ሁኔታ ከእንግዲህ ወደ ፊት አይገፉም፡፡ እንዲያውም እነዚህ ዋዣቂ አማኞች፣ ከዚህ ዓለም አስተሳሰብ ምንም ተቃውሞ አይገጥማቸውም፤ ቢገጥማቸውም በጣም በጥቂቱ ነው፡፡

እስቲ ሐዋርያው ዮሐንስ የጻፈውን እንመልከት -

በዓለም ያለው ሁሉ - የሥጋ ምኞት፣ የዓይን አምሮትና የኑሮ ትምክሕት ከዓለም እንጂ ከአብ የሚመጣ አይደለም፡፡ ዓለምና ምኞቱ ያልፋሉ፤ የእግዚአብሔርን ፈቃድ የሚፈጽም ግን ለዘላለም ይኖራል (1 ዮሐንስ 2፥16-17)፡፡

ያካፈልኳችሁ ራእይ ሦስት ዐይነት ሰዎች ያቀርባል - አማኝ - የማያምን - የሳተ (የተሳሳተ) ሰው፡፡

– የማያምን ሰው - መጨረሻውን ሳይገነዘብ ከማዕበሉ ጋር አብሮ ይነጉዳል፡፡

– አማኝ - የመንግሥቱ መስፋፋትን ግብ ለማሳካት ወደ ግቡ ይፈጥናል፡፡

– የሳተ (የተሳሳተ)፣ ‹‹ክርስቲያን በመምሰልና›› መጽሐፍ ቅዱስን እንደሚመቸው አድርጐ በመጥቀስ እውነተኛ ማንነቱን ይሰውራል፡፡

ይህ ራእይ በዚህ ዘመን ያለነውን አማኝ ነን የምንል ሰዎች ያለንበትን ሁኔታ እንደሚወክል ዐውቃለሁ፤ ይሁን እንጂ፣ ‹‹እኔ የትኛውን ሰው ነው የምመስለው?›› የሚለውን ጠቃሚ ጥያቄ እያንዳንዳችን እንድንጠይቅ ያደርገናል፡፡ የእግዚአብሔር ቃል የሚያዝዘንስ ይህንኑ አይደል…

> በእምነት መሆናችሁን ለማወቅ ራሳችሁን መርምሩ፣ ራሳችሁን ፈትኑ፡፡ ፈር የወጣችሁ ካልሆነ በስተቀር ኢየሱስ ክርስቶስ በውስጣችሁ እንዳለ አታውቁምን? (2 ቆሮንቶስ 13፥5)፡፡

ይህን ራእይ ካየሁና ትርጒሙንም ከተረዳሁ በኋላ በእነዚህ ለዕብራውያን ክርስቲያኖች በተጻፉ ቃሎች በጣም እየተነካሁ መጥቻለሁ፣

> የዛለውን ክንዳችሁንና የደከመውን ጉልበታችሁን አበርቱ፡፡ ዐንካሳው እንዲፈወስ እንጂ የባሰውኑ እንዳያነክስ - ለእግራችሁ ቀና መንገድ አብጁ…ከእናንተ ማንም የእግዚአብሔር ጸጋ እንዳይጐድልበት ተጠንቀቁ (ዕብራውያን 12፥12-13፣15)፡፡

እንደ የእግዚአብሔር ልጆች ለእርሱ ክብር በሚሆን ሁኔታ በሚገባ ለመፈጸም፣ አጥብቀን መፈለግ አለብን፡፡ በመሰላቸት፣ መቅዘፊያችን በመጣልና በዚህ ዓለም ሥርዐት ማዕበል ወዲያ ወዲህ በመዋዠቅ፣

ከእግዚአብሔር ጸጋ ወደ ኃላ እንዳንል እኔና እናንተ መጠንቀቅ ይኖርብናል፡፡

ሰዎች እንደሚገባ ሲጨርሱና ሳይጨርሱ ሲቀሩ ምን እንደሚሆን፣ ከቅዱሳት መጻሕፍት ውጪ ሌሎች ምሳሌዎች መፈለግ አይኖርብንም፡፡ እስቲ ጥበበኛውን፣ ባለ ጸጋውን፣ በዘመኑ ከነበሩ ሰዎች የበለጠ ብርቱ የነበረውን የዳዊት ልጅ ሰሎሞንን ተመልከቱ፡፡ ከእርሱ በፊት ከነበረው ትውልድ፣ ከእርሱም በኃላም ብዙዎች መድረስ ከሚችሉበት የበለጠ ከፍታ ላይ ደረሰ፡፡ ይሁን እንጂ፣ በበኃለኛው የንጉሥነት ዘመኑ ተሰናከለ፣ መቅዘፊያውን አስቀመጠ፤ ከዚህ ዓለም ሥርዐት ጋር ለመወዳጀት ልቡን ከእግዚአብሔር መለሰ፡፡

ሰሎሞን ብዙ ባዕዳን ሚስቶች ስለ ነበሩት ከእግዚአብሔር ጋር ለመሆንና ለእርሱም ለመታዘዝ አንድ ልብ እንዳይኖረው በቤተ ሰቡ ውስጥ ግጭት ሳይገጥመው አልቀረም፡፡ ሰላም ለመፍጠር ሲል ለእግዚአብሔር ታማኝ ሳይሆን ቀረ፤ ይልቁን ለሚስቱ አማልክት መሠዊያ ሠራ፤ ሌላው ቀርቶ ከሌሎች አስበልጦ የሚወዳቸው ሚስቶቹን ባዕዳን አማልክት አመለከ፡፡

በዚህ ጥፋቱ ሰሎሞን በጣም ተጐድቶ ነበር፤ ይሁን እንጂ፤ ልጆቹና የልጅ ልጆቹ ከእርሱ በጣም በሚብስ ሁኔታ ተጐድተዋል፡፡ ከአባቱ ከዳዊት ታማኝነት የተነሣ ብርቱ የነበረው፣ በኃላም በሰሎሞን መንግሥት ጅማሬ ላይ የበለጠ አድጐ የነበረው በኃላፊነት የተቀበለው መንግሥት በጣም ተጐዳ፣ ተከፋፈለ፣ በመጨረሻም ሰሎሞን በአግባቡ መጨረስ ባለ መቻሉ በጣም ተዳከመ፡፡ ሰሎሞን በአምላኩ የጸና ልብ ኖሮት ቢሆን ኖሮ፣ የእስራኤል ታሪክ ምናልባት አሁን ካለበት በጣም የተለየ ይሆን ነበር፡፡

እስቲ ሰሎሞንን ከመጥምቁ ዮሐንስ ጋር እናነጻጽር፡፡ ዮሐንስ በውሳኔው የጸናና እውነትን አጥብቆ የያዘ ሰው ነበር፤ በያዘው እውነት የሚኖርና ያንንም የሚናገር ሰው ነበር፡፡ እንደ ሰሎሞን እርሱንም አስቸጋሪ ሁኔታ ገጥሞት ነበር፤ የእርሱ ችግር ግን በአንድ ወይም በበርካታ ሚስቶች ዙሪያ ሳይሆን፣ ዮሐንስ የሚናገረውን እውነት መቀበል ካልፈለገው ከይሁዳ ንጉሥ ጋር የተያያዘ በመሆኑ የበለጠ ከባድ ነበር፡፡ ሰሎሞንን ያጋጠመው የተከፋፈለ ቤተ ሰብ ነበር፤ ዮሐንስን የገጠመው ግን እስራት ስቃይ፣ ከዚያም አልፎ ምናልባት ሞት እንኳ ሊሆን ይችላል፡፡ ያም ሆኖ፣ እንዲህ ካለው ከባድ መከራ ጋር ቢጋፈጥም፣ ዮሐንስ በአኗኗርም ሆነ ለሌሎች በማስተማር ረገድ ምንም ሳይናወጥ እውነትን አጥብቆ ያዘ፡፡ ዮሐንስ ትቶት ያለፈው ምሳሌነት ከሰሎሞን እጅግ የላቀ ሆነ፡፡

ችግርና ማዕበል በዮሐንስና በሰሎሞን ብቻ አያበቃም፤ እኔና እናንተም የተለያየ ችግር ይገጥመናል። ከንቱና ጠፊ ከሆነው ከዚህ ዓለም ሥርዐት ከባድ ውጊያ ሊገጥመን ይችላል። ዓለም እኛ ላይ የሚያሳድረው ተፅዕኖ በጣም ብርቱ ነው። አሳሳችም ነው። የሚያባብልም ነው። መሰላቸት፣ ጽናትን መተው፣ እጅ መስጠትና በማዕበሉ ወዲያ ወዲህ መዋዠቅ በጣም ቀላል ነው። ይሁን እንጂ፣ እኔና እናንተ በአግባቡ እንድንጨርስ ከተፈለገ በእምነታችን ከመጽናት በቀር ሌላ መንገድ የለም። እንደዚያ ስናደርግ ደግሞ፣ በዋዛ የማንታይ ጠላት፣ ለጨለማው መንግሥትም እውነተኛ ስጋት እንሆናለን።

## ጽናት ያለው መንፈስ

ለመሆኑ ጽናት ምን ማለት ነው? ቃሉ ቆራጥነትን፣ ያለ ማወላወልንና አልሸነፍም የማለት ዝንባሌን ወይም ዐቋምን ያመለክታል። በቀላል አነጋገር ተሸናፊ አይደለም። ተሸናፊነት ልልነት ወይም አሜን ብሎ ሽንፈትን መቀበል ነው። ጽናትን ለመረዳት የሚያግዙ አንዳንድ ተመሳሳይነት ያላቸው ቃሎች፣ ‹‹ግትር፣ እልከኛ፣ ቆራጥ፣ የማያወላውል፣ ማንም ሊያስቆመው የማይችል፣ ሙጭጭ ባይ፣ እንዲያውም፣ ‹‹ችኮ›› የተሰኙት ናቸው። ሌሎች ገለጻዎች፣ ‹‹አለመታከት፣ ብርታት፣ አንድ ልብ፣ ጠንካራ፣ አዘውታሪ እና ‹‹ጥብቅ›› የተሰኙት ናቸው።

ጽናት ለመልካም ብቻ ሳይሆን፣ ክፉ ነገርን ለማመልከትም ጥቅም ላይ ይውላል፣ አሁን ግን ቀና እና መንፈሳዊ ጠቀሜታውን ብቻ ነው የምንመለከተው። ስለሆነም ቃሉን - የያዘውን ሥራ ለማጠናቀቅ ደፋርና ወሳኝ ለሆነ ሰው እንጠቀምበታለን። አጭር ጊዜ በሚጠይቅ መልኩም ሆነ፣ ረጅም ጊዜ በሚጠይቅ መልኩ፣ ጽኑ ልብ ውስጥ በሚጠበቀው መንገድ የመጨረስ ፍላጎት አለ። እንዲህ ያለውን ሰው ግቡን ከማሳካት ምንም የሚያግደው አይኖርም።

ጽናት ያለው አማኝ ...
በእውነተኛ መልኩ ታሪክ
ሠሪ ነው፣

ጽናት ስላለው አማኝ ስንነጋገር መከራው የቱንም ያህል ከባድ ቢሆን እንኳ በእምነት፣ በተስፋና ለእግዚአብሔር በመታዘዝ መሸነፍን ስለማያውቅ ሰው መነጋገራችን ነው። ጽናት ያለው አማኝ በሁሉም መንገድ በሚገባ ለመጨረስ የወሰነ ነው፤ በእውነተኛ መልኩ ታሪክ ሠሪ ነው፣ በመጨረሻም፣ ‹‹መልካም አድርገሃል›› የሚለውን የጌታውን ልባዊ ቃል ይሰማል።

የጽናት መገለጫ የሆኑት እነዚህ ቃሎች፣ አንድ እኔ በጣም የማውቀውን ሰው አይመለከቱም - ያ ሰው ሌላ ሳይሆን እኔ ራሴ ነኝ! በያዝኩት ነገር ሁሉ ተሸናፊ እንጂ ጽኑ አልነበርኩም፤ ጀምሮ ባለ መጨረስና አቋርጦ በመውጣት የታወቅሁ ነበርኩ፡፡

እ.ኤ.አ. 1979 ዓ.ም ፑርዱ ዩኒቨርሲቲ እየተማርኩ እያለ የእግዚአብሔር ልጅ ሆንኩ፡፡ ያ ሴሚስተር ሲያበቃ ወደ ቤት የተመለስኩት ከፍተኛ ስሜት ውስጥ ሆኜ ነበር፤ እቤት እንደ ደረስኩ በእውነት ጌታን መቀበሌን ካቶሊኮች ለነበሩት ወላጆቼ ነገርኳቸው፡፡ እናቴ ምን ያለችን ይመስላችኋል? ‹‹ጆን፣ ምናልባት ይህም፣ ከዚህ በፊት በወረት ይዘኻቸው እንደ ነበሩ ነገሮች እንዳይሆን እፈራለሁ፣ ሌላውን ነገር እንደ ተወኸው ሁሉ ውሎ አድሮ ይኸኛውንም ትተወዋለህ›› ነበር ያለችኝ፡፡

ምንም እንኳ የእናቴ አነጋገር የሚያምምና አሉታዊ ቢመስልም በጣም ትክክል ነበር፤ ማንኛውንም ነገር ጀምሬ ዳር ሳላደርስ የማቋረጥ ታሪክ ነበረኝ፡፡

ወንደላጤ በነበርኩ ጊዜ ምናልባት ዘላቂ ትዳር ላይኖረኝ ይችል ይሆን? በማለት የነበርኩበትን ፍርሃት አስታውሳለሁ፡፡ ከአንድ ወይም ከሁለት ግፋ ካለም ከሦስት ጊዜ በላይ ከልጃገረዶች ጋር አልገናኝም ነበር፡፡ በጣም ቆንጆዎች፣ ማራኪዎችና ትልልቅ ሰብዕና የነበራቸው ቢሆኑም፣ ለእኔ ግን በቀላሉ ይሰለቹኛል፡፡ በኋላ ግን ሌሎች ጓደኞቼ ከእነዚህ ልጃገረዶች አንዳንዶቹ ጋር ተዋውቀው በጣም ደስ የሚል ትዳር መሥርተዋል፡፡ የእኔ ባሕርይ ግን ዛሬ የአንዷ፣ ነገ የሌላዋ፣ ከነገ ወዲያ ደግሞ የሌላዋ ጓደኛ መሆን ነበር፡፡

ዘላቂነት የሌለኝ ከልጃገረዶች ጋር ባለኝ ትውውቅ ብቻ አልነበረም፡፡ ፒያኖ መማር ጀምሬ ነበር፤ ከስድስት ወር በኋላ ግን እንዳቋርጥ መወትወት ያዝኩ፡፡ ወላጆቼ እንዳቋርጥ አልፈለጉም ነበር፡፡ በኋላ ግን፣ ሲበዛ ደንታ ቢስ ሆኜ በመገኘቴ የፒያኖ ትምህርቴን እንዳቋርጥ እንዲፈቀድልኝ የፒያኖ አስተማሪዋ ራሷ አባቴንና እናቴን መለመን ያዘች፡፡ ፒያኖ ባስተማረችበት ዘመን ሁሉ ትምህርቱን እንዲያቆም ያበረታታችው ተማሪ እኔ ብቻ ሳልሆን አልቀርም!

በኋላም ጊታር እንድማር ለወላጆቼ ነገርኳቸው፡፡ በጣም ውድ የሆነ ጊታር ተገዛ፤ በስሜት ማንኮራኮር ጀመርኩ፤ ሆኖም ከጥቂት ወሮች ያለፈ መዝለቅ አልቻለም፡፡

ስፖርትን በተመለከተም ይኸው ነበር፡፡ ቤዝቦል እጫወት ነበር፤ ግን ከጥቂት ዓመቶች በኋላ ተውኩት፡፡ ቀጣዩ ባስኬትቦል ነበር፤ እርሱም ከአንድ ወቅት ወረትነት አላለፈም፡፡ ቀጥሎ ጐልፍ፣ እርሱም የአንድ ሰሞን ወረት ሆኖ አበቃ፡፡ ቀጥሎ ሩጫ ሲሆን ጥቂት ውጤት አሳይቼ ነበር፡፡

ዝርዝሩ ሊቀጥል ይችላል፡፡ መጽሐፍ ማንበብ እጀምራለሁ፤ ግን አልጨርስም፡፡ ሁለተኛ ደረጃ እያለሁ ጨርሼ ያነበብኩት አንድ መጽሐፍ ብቻ ሲሆን እርሱም - *ሽማግሌውና ባሕሩ* የተሰኘው የኧርኔስት ሔሚንግዌይ መጽሐፍ ነበር፡፡ እርሱንም ቢሆን ጨርሼ ያነበብኩት የግድ መነበብ የነበረበት መጽሐፍ ስለ ነበረና በዚያ ላይ በጣም አጭር ስለ ነበር ይመስለኛል፡፡

የአንድ ክለብ አባል እሆናለሁ፤ ከአጭር ጊዜ በኋላ አቋርጣለሁ፡፡ ፊቴን ወደ ልዩ ዐይነት መስኮች እመልስና ውድ መሣሪያዎች እገዛለሁ፤ በስሜት ከጀመርኩት በኋላ ግን ብዙም ሳይቆይ ወረቱ ያልቅና በመቀመጥ ብዛት ይበላሻል፡፡

በአጭሩ፣ እኔን በተመለከተ እናቴ የተናገረችው ትክክል ነበር፡፡ ታዲያ፣ ዛሬም ያው ልማዴ ይደገም ይሆን? ክርስትናን፣ በእግዚአብሔር የጀመርኩት አዲስ እምነትና አዲስ ተነሳሽነት አቋርጥ ይሆን? መጽሐፍ ቅዱሴና የማጥኛ መጻሕፍቶቼም እንዲሁ ወረታቸው አልፎ ይጣሉ ይሆን?

በጣም ደስ የሚለው ግን ይህ ጀምሮ በማቋረጥ ይታወቅ የነበረ ሰው፣ ከልቡ እና በሙሉ ፍቅር፣ ኢየሱስ ክርስቶስን መከተል ከጀመረ አሁን ከሰላሣ ዓመት ያለፈው መሆኑ ነው፡፡ ወደ ቤት መጥቼ በጌታ ኢየሱስ ማመኔን ለወላጆቼ እንደ ተናገርኩበት ቀን ሁሉ፣ እንዲያውም ከዚያም ይበልጥ ዛሬም በጌታ ደስ ይለኛል፡፡ ሁሉን ቻዩ አባቴ እግዚአብሔር ቶሎ ተስፋ ከመቁረጥና ቶሎ ከመሰልቸት ሕይወት ጨርሶ ለውጦኛል፡፡ በመንፈስ ቅዱስ አማካይነት ጽናት ያለውን መንፈስ ውስጤ አኑሮአል፡፡

እግዚአብሔር ጽናት ያለው አማኝ አድርጎኛል፡፡

ኢየሱስ ክርስቶስን ጌታና አዳኝ አድርገህ ተቀብለህ ከሆነ፣ አንተም ብትሆን ይህን ባሕርይ ማግኘት ትችላለህ፡፡ ሆኖም፣ በየጊዜው ማደግና መዳበር ይኖርበታል፡፡ የዚህ መጽሐፍ ዓላማ ይኸው ነው - እንደሚገባ እንድትኖርና እንደሚገባ እንድትጨርስ፣ እግዚአብሔር በነጻ የሰጠህን ይህን ችሎታ እንዴት ማሳደግና ማበርታት እንደምትችል መግለጽ፡፡

## እግዚአብሔር ስለ አንተ መጽሐፍ ጽፏል

ማንነትህንና እግዚአብሔር ምን ያህል እንደሚፈልግህ ተረድተህ ይሆን? ዓላማውን በዚህ ምድር እውን የማድረግ ዕጣ ፈንታህን እንድትፈጽም ሊጠቀምብህ እንደሚፈልግ ተገንዝበህ ይሆን? ሰማያዊው አባት አንተን መፈለጉ ይገርምህ ይሆን?

እግዚአብሔር ለአንተ ራሱን የቻለ የሕይወት አቅጣጫ አለው! መላው ሕይወትህ ከመወለድህ በፊት እንኳ ተጽፎአል፡፡ ይህን በተመለከተ ዘማሪው፣

> ዐይኖችህ ገና ያልተበጀውን አካሌን አዩ፤ ለእኔ የተወሰኑልኝም ዘመናት፣ ገና አንዳቸው ወደ መኖር ሳይመጡ በመጽሐፍ ተመዘገቡ (መዝሙር 139፥16) ብሏል፡፡

ወላጆችህ አንተን እንደሚወልዱ እንኳ ሳያስቡ - ገና አንዳቸውም ወደ መኖር ሳይመጡ፣ እግዚአብሔር ስለ አንተ መጽሐፍ ጽፏል፡፡ ታሪካቸው በመጽሐፍ የሰፈረላቸው የዚህ ዓለም ታላላቆችና ታዋቂ ሰዎች ብቻ አይደሉም፡፡ የአንተም ተጽፎአል፤ በጣም አስደናቂው ደግሞ ገና አንተ ከመወለድህ በፊት በራሱ በእግዚአብሔር የተጻፈ መሆኑ ነው፡፡

ይህን ስታነብ፣ ‹‹የእኔ ወንድም ለማን እየተናገርህ እንደ ሆነ አላወቅህም! ካደረግሁዋቸው መጥፎ ምርጫዎች የተነሣ ሕይወቴ ተበለሻሽቷል፡፡ ታዲያ፣ ይህን ሁሉ እግዚአብሔር ጽፎታል ነው የምትለኝ?›› በማለት መቀበል ያቅትህ ይሆናል፡፡

እንደዚያ አይደለም፤ በፍጹም እንደዚያ ማለት አይደለም! እርግጥ ነው ሕይወታችን በእግዚአብሔር ተጽፎአል፤ እርሱ ባዘጋጀልን አስደናቂ መንገድ ለመጓዝ ትክክለኛ ምርጫ ማድረግ ግን የእኛ ፈንታ ነው፡፡ መጥፎ ምርጫዎቻችን መንገዳችንን ያበላሻሉ፤ እውነተኛ ንስሐ ግን መልሶ ወደ መንገድ ያገባናል፡፡

ምናልባትም፣ ‹‹ከእኔ መጥፎ ምርጫ የተነሣ ሳይሆን፣ በሕይወቴ ብዙ አስከፊ ነገሮች ተፈጽመዋል፡፡ ሕይወት ለእኔ ደግ አይደለችም፡፡ እግዚአብሔር ይህን ሁሉ ተስፋ መቁረጥና መከራ ጽፎት ይሆን?›› የሚል ጥያቄ ታነሣ ይሆናል፡፡

እንደ ገና መልሴ፣ አይደለም ነው! የምንኖረው በወደቀ ዓለም ውስጥ ነው፡፡ መከራ እንደሚደርስብንና መራራ ውጣ ውረድ እንደሚገጥመን ኢየሱስ ተናግሮአል፡፡ ደስ የሚለው ዜና ግን አንተን ከመንገዱ ለማውጣት ስለሚገጥምህ ክፉ ነገር እግዚአብሔር ከመወለድህ በፊት እንኳ ስላወቀ

በታላቅ ጥበቡ ማምለጫ መንገድ፣ እንዲያውም በአሸናፊነት የምትወጣበትን መንገድ ማዘጋጀቱ ነው፡፡ በመንገዳቸው የጸኑ አማኞችን የእግዚአብሔር ቃል፣ ‹‹አሸናፊዎች›› በማለት የሚጠራቸው በዚህ ምክንያት ነው፡፡

ዕብራውያን 12÷1፣ ‹‹በፊታችን ያለውን ሩጫ በጽናት እንሩጥ›› በማለት እያንዳንዳችንን ይመክራል፡፡ ለእኔም ሆነ ለእናንተ፣ ለልጆቹ ሁሉ፣ እግዚአብሔር በፊታችን ሩጫ አስቀምጧል፡፡ እንግዲህ በሚገባ ሩጫውን እንድንፈጽም ከተፈለገ በጽናትና ተስፋ ባለ መቁረጥ መሮጥ ይኖርብናል፡፡ ይህ በሌላ መንገድ እውን ሊሆን አይችልም፡፡ በዚህ ምንባብ አጽንዖት የተሰጠው ምግባር ይህ ብቻ መሆኑን ማስተዋልም ይጠቅማል፡፡ ጸሐፊው፣ ‹‹ደስ እያለን እንሩጥ›› አላለም፤ ‹‹በዓላማ እንሩጥ›› አላለም፤ ወይም፣ ‹‹ከልባችን እንሩጥ›› አላለም፡፡ እርግጥ ነው ደስታ፣ ዓላማና ከልብ መሆን እንደ ሌሎቹ ምግባሮች ሁሉ ለክርስትና ሕይወታችን አስፈላጊ ናቸው፡፡ እዚህ ላይ ቁልፍ የሆነው ምግባር ግን፣ ‹‹ጽናት›› ነው፡፡

በሚገባ መጨረስ ጽኑ መንፈስ ይጠይቃል፡፡ በሚገባ መጨረስ አጥብቆ መያዝና ትዕግሥት ይጠይቃል፡፡ ሜሴጅ የተሰኘው የመጽሐፍ ቅዱስ ውርስ ትርጉም ዕብራውያን 12÷1 ያስቀመጠበትን መንገድ እወደዋለሁ፣ ‹‹ትብታብን ፍቱ፤ መሮጥ ጀምሩ፤ በፍጹም አታቋርጡ!›› ነው የሚለው፡፡ ሩጫችንን መፈጸም ለእኛ ብቻ ሳይሆን፣ እኛ በጐ ተፅዕኖ እያሳደርንባቸው ላሉትም ሰዎች በጣም ወሳኝ ነው፡፡ ወደ ኃላ አለመመለስና እግዚአብሔር በፊታችን ከኖረው ሩጫ ዓይኖቻችን አለማንሣት ጠቃሚ ነው፡፡ በእውነት የእግዚአብሔር ከሆንህ የሚያስፈልገው ነገር ሁሉ አለህ! ያን የሚያስችል መንፈስን ማለትም መንፈስ ቅዱስን እግዚአብሔር በውስጥህ አድርጓል፡፡ ጸንተህ ጉዞህን ከቀጠልህ ከሐዋርያው ጳውሎስ ጋር፣ ‹‹ሩጫውን ጨርሻለሁ፤ ሃይማኖትን ጠብቄአለሁ›› ማለት ትችላለህ (2 ጢሞቴዎስ 4÷7)

ምናልባት በትዳርህ፣ በቤተ ሰብህ፣ በመሥሪያ ቤትህ፣ በግል ሥራህ፣ በትምህርት ቤትህ፣ በኢኮኖሚህ፣ በጤናህና በሌላውም ነገርህ ችግር ገጥሞህ ይሆናል፡፡ ያለህበት ሁኔታ ጨርሶ ተስፋ አስቆራጭና መፍትሔ የሌለው ይመስል ይሆናል፤ አስፈሪና አስደንጋጭ ማዕበል ተስፋ እንድትቆርጥ ወዲያ ወዲህ ዋዥቀህ እንድትሄድ ሊያደርጉህ እየሞከሩ ይሆናል፡፡ የምሥራቹ ግን፣ ‹‹ይህ በሰው ዘንድ አይቻልም፤ በእግዚአብሔር ዘንድ ግን እንዲህ አይደለም፤ በእግዚአብሔር ዘንድ ሁሉ ይቻላል›› (ማርቆስ 10÷27)፡፡ ያለህበት ሁኔታ የቱንም ያህል ከባድ ቢሆን፣ ለእግዚአብሔር የማይቻል አይደለም፡፡ ይሁን እንጂ፣ ኢየሱስ ከዚህ ተስፋ ቃል ጋር አንድ አስፈላጊ ነገር ተናግሮአል፣ ‹‹ለሚያምን ሰው ሁሉም ነገር ይቻላል›› (ማርቆስ 9÷23)፡፡ የማይቻለው

ሲቻል ለማየት ጽናት ያለው አማኝ መሆንን ይጠይቃል፡፡ የመልእክቱ አንኳር ነጥብ ይኸው ነው፤ ከሰብዓዊ ዐቅምህ በላይ ከሆነ ነገር ጋር መጋፈጥ፣ ከዚያም፣ በእግዚአብሔር ብርታትና ጸጋ የማይቻለው ሲቻል ማየት፡፡

የራሱ የእግዚአብሔርን ያህል የአንተን ሕይወት መሳካት የሚፈልግ የለም፡፡

ልብ አድርገህ ስማኝ! እግዚአብሔር በፊቱ፣ ‹‹ታላቅ›› እንድትሆን ይፈልጋል፡፡ (ሉቃስ 1፥15)፡፡ እግዚአብሔር የአንተ ነው፤ የራሱ የእግዚአብሔርን ያህል የአንተን ሕይወት መሳካት የሚፈልግ የለም፡፡ እርሱ ድንቅ ሕይወት አዘጋጅቶልሃል፤ ለሌሎች ጥቅም የሚሆን እምነት፣ ፋይዳ ያለው ነገርና ታላቅነትን ትተህ ማለፍ እንድትችል፣ በአንተ ውስጥ ታላቅ ፍጻሜ አስቀድሞ ዐይቷል፡፡ ይህ ሁሉ ግን የአንተን ጽናት ያለው አማኝ መሆንን ይጠይቃል፡፡

ምናልባትም፣ ‹‹የእኔ ወንድም፣ እውነቱን ለመናገር እኔ'ኮ ይህን ያህል ውሳኔ ማድረግ የምችል ሰው አይደለሁም፡፡ አስቸጋሪ ጊዜ ሲመጣ ጸንቶ የመቆም ታሪክም የለኝም›› ትለኝ ይሆናል፡፡

አንተ ራስህን የምታየው እንደዚያ ከሆነ፣ እንግዲያው ሌላ የምሥራች ልንገርህ፡፡ ያለፈ ታሪክህ ይህን ያህል አስፈላጊ አይደለም፡፡ ከኢየሱስ ክርስቶስ ጸጋ የተነሣ ያለፈውን አትደግመውም፡፡ በእርግጥ ጽኑ አማኝ መሆንና በሚገባ መጨረስ ይቻልሃል፡፡ የታሰበው ፍጻሜ እውን ሲሆን የማየት ታላቅ ደስታ ዕጩ ነህ፡፡ በአጭር ጊዜም ሆነ፣ በረጅም ጊዜ የሕይወት ምዕራፍ፣ በእግዚአብሔር ፊት ታላቅ እንድትሆን ተወስነሃል፡፡ የእርሱ ተስፋ ቃል ይኸው ነው!

የኢየሱስን መንገድ የምንከተል ከሆነ የሚጠብቀንን ችግር ማምለጫ የለም፡፡ መከራው ታላቅ የመሆኑን ያህል፣ ዘላለማዊ ሽልማቱም በዋጋ የማይገመት ነው የሚሆነው፡፡ በግልጽ ለማስቀመጥ ያህል የሕይወት ዓላማህን ማጨናገፍና እግዚአብሔር ያቀደልህን ተልዕኮ ማበላሸት የሚፈልግ አደገኛ ጠላት አለህ፡፡ ሰይጣንን በተመለከተም ከሆነ ለእርሱ ስጋት በመሆንህ ሊያስቆምህ ይፈልጋል፤ እንዲያውም፣ ‹‹ብትሞት›› ደስታው ነው፡፡ ይሁን እንጂ፣ መስቀል ላይ ከተፈጸመው የተነሣ ሰይጣን የተሸነፈ ጠላት ነው! እርሱ ጋር የምናደርገው እያንዳንዱ ውጊያ ቀድሞውኑ ያለቀና ያበቃለት ነው! ይሁን እንጂ፣ አሁንም ቢሆን እርሱን፣ ሰራዊቱንና የሚሳድሩትን ተጽዕኖ በጽናት መዋጋት አለብን፡፡ ያ፣ እንዴት እንደሚሆን አብረን እናያለን፡፡

በዚህ ዓለም አንዳች ለውጥ እንድታመጣ ተፈጥረሃል፡፡ እርሱን ወክለህ እንድትገዛ የተወሰንህ የንጉሥ ልጅ ነህ፡፡ ከእርሱ የተነሣ

የመንግሥቱ ሥልጣን በእጅህ ነው! ወደ እርሱ ስትቀርብና በእምነት ለመጽናት ራስህን ስትሰጥ፣ እርሱ አንተ ላይ የሚነሣውን ብርቱ ማዕበል ለማሸነፍ የሚስፈልግህን ብርታትና ምሪት ይሰጥሃል፡፡

ወደሚቀጥለው ምዕራፍ ከማለፋችን በፊት፣ አብረን ይህን ጉዞ ለጌታ እንስጥ፣

> *የተወደድህ እግዚአብሔር፣ ይህን መጽሐፍ እያነበብኩ እያለ መንፈስ ቅዱስህ ያስተምረኝ፣ ማስተዋልን ይስጠኝ፡፡ ከመረጃ ወይም ከተነሣሽነት ያለፈ ነገር እፈልጋለሁ፣ በሕይወቴ ላይ ያኖርኸውን ጥሪ ባለጠግነትና ትልቅነት ማወቅ እፈልጋለሁ፡፡ የታሰበልኝን ግብ ማሳካት እንድችል እኔ ውስጥ ያኖረኸውን ኃይል ማወቅ እፈልጋለሁ፡፡*
>
> *በዚህ መልእክት በእውነት ጸንቼ እንድቆም አበርታኝ፣ በእኔ አማካይነት መፈጸም የምትፈልገውን ለማደናቀፍ የሚነሣውን ጠላት ለመዋጋት ጽናት ስጠኝ፡፡ ለእንዲህ ያለው ጊዜ አድርሰኸኛል፣ ይህ የጽናት መልእክት ለአንተ ክብርን ለልብህ ደስታን ለማምጣት፣ መለኮታዊ ዕቅድህን ለማሳካት እንዲረዳኝ፣ እንዲያስታጥቀኝ እጸልያለሁ፡፡ ይህን ልመና በኢየሱስ ክርስቶስ ስም አቀርባለሁ፡፡ አሜን፡፡*

# 2

# በሕይወት መንገሥ

*የእግዚአብሔር ቃል ሕያውና የሚሠራ (ብርቱ) ነውና*

*ዕብራውያን 4፥12*

የእግዚአብሔርን ቃል ባለበት ትክክለኛ ሁኔታ አንብበን ቢሆን ኖሮ፣ ብዙዎቻችን አሁን ካለንበት በሚገርም ሁኔታ እንለወጥ ነበር፡፡

አንዳንዴ ትልቁ ችግራችን፣ አሁን ያለንበትን ሁኔታ በተመለከተ ቃሉ የሚለውን ማመን ነው፡፡ ነገሮችህ አሁን ያሉበት ሁኔታ ደስ የማይል ቢሆን እንኳ እንደሚለወጥ ታውቃለህ - አሁን ያለው የመጨረሻ አይደለም፡፡ በፍጹም የማይለወጥ የእግዚአብሔር ቃል ብቻ ነው፡፡ ከዘመናት በፊት ኢየሱስ ክርስቶስ፣ ‹‹ሰማይና ምድር ያልፋሉ፤ ቃሌ ግን አያልፍም›› ብሎአል (ሉቃስ 21፥33)፡፡ ቀና ብለህ የሰው ልጅ እዚህ መኖር ከጀመረ አንሥቶ ብርሃንና ሙቀት ስትሰጠን የኖረችው ፀሐይን ተመልከት፡፡ የእግዚአብሔር ቃል ሐሰት ከሚሆን ይልቅ የእርሷ ማለፍ ይቀላል፡፡ የእግዚአብሔር ቃል ለዘላለም ጸንቶ ይኖራል!

ሁሉን ቻዩ አባታችን፣ ‹‹ቃሌን እፈጽመው ዘንድ እተጋለሁና›› ይላል (ኤርምያስ 1፥12)፡፡ ምን ያህል ዝግጁ መሆኑን አስተውሉ፡፡ ቃሉን የሚፈጽመው መቼ ነው? ቀላሉ መልስ አንድ ሰው በእርሱ ሲያምን ነው፡፡ ኢየሱስ፣ ‹‹ለሚያምን ሰው ሁሉም ነገር ይቻላል›› በማለት አረጋግጧል (ማርቆስ 9፥23)፡፡ ስለዚህ በጽናት እንመን!

## በዚህ ሕይወት ልንገዛ ነው

በሚቀጥሉት አራት ምዕራፎች እጅግ ሲበዛ አስፈላጊ የሆነ አንድ እውነት በጥልቀትና በስፋት ለማየት እንሞክራለን - እንደ ጠንካራ አማኝ በሚገባ እንድንጨርስ ከተፈለገ፣ ይህ እውነት በዋነኛነት ደረጃ ጠቃሚ ነው፡፡

በመጠኑም ቢሆን ከርዕሰ ጉዳያችን የወጣን ሊመስላችሁ ይችል ይሆናል፤ ግን አብራችሁኝ ሁኑ፡፡ ጉዞአችንን በሚገባ እንድናጠናቅቅ እኛን ለመርዳት ሁሉም ነገር እንደሚገጣጠም አረጋግጥላችኃለሁ፡፡

ይህን በአእምሮአችን በመያዝ አዲስ ኪዳን ውስጥ በጣም ብርቱ ከሆኑ ጥቅሶች አንዱን እንመልከት፡፡

> ይልቁን የጸጋን ብዛትና የጽድቅን ስጦታ ብዛት የሚቀበሉ በአንዱ በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል በሕይወት ይነግሣሉ (ሮሜ 5፥17)

*በሕይወት ይነግሣሉ* የሚለውን ሐረግ ልብ አድርጋችሁ ተመልከቱ፡፡ እንደ የእግዚአብሔር ልጆች እኔና እናንተ እንደ ንጉሦችና ልዕልቶች ልንገዛ ነው! ይህ ቃል ተራ የሰው ቃል አይደለም፤ ምክንያቱም፣ ‹‹ቅዱሳት መጻሕፍት ሁሉ የእግዚአብሔር መንፈስ ያለባቸው›› መሆኑን እናውቃለን (2 ጢሞቴዎስ 3፥16)፡፡ ስለሆነም በልጁ ኃይል በሕይወት እንደምንነግሥ እግዚአብሔር በግልጽ እየነገረን ነው፡፡ ‹‹አንድ ቀን በመንግሥት ሰማይ ትግሣላችሁ››፣ ወይም፣ ‹‹በሚቀጥለው ሕይወት ትነግሣላችሁ›› አለማለቱን ልብ አድርጉ፡፡ በፍጹም እንደዚያ አይደለም፤ በክርስቶስ በኩል እንደ ንጉሦችና ልዕልቶች በዚህ ሕይወት እንደምንነግሥ ነው በግልጽ የበየነው፡፡

አንድ መዝገበ ቃል ንጉሥ ወይም ልዕልት የሚለውን ቃል፣ ‹‹በአንድ የተወሰነ ክልል ውስጥ ፍጹም የበላይነት ወይም ቀዳሚነት ያለው›› በማለት ይተረጉመዋል፡፡ መንገሥ ወይም መግዛት የሚለውን ቃል ደግሞ፣ ‹‹የበላይነት ወይም ገደብ የሌለው ተፅዕኖ ማሳደር›› በማለት ይፈታዋል፡፡ እንደ ንጉሥ ወይም እንደ ልዕልት መግዛት ፍጹማዊ ግዛትና በአንድ የተወሰነ ክልል፣ ገደብ የሌለው ተፅዕኖ ማሳደር መቻል ነው፡፡ ታዲያ፣ መግዛት ወይም ገደብ የሌለው ተፅዕኖ ማሳደር የምንችለው በየትኛው ክልል ነው? በሕይወት ክልል፡፡

በሌላ አነጋገር የዚህ ምድር ሕይወት ጫና ሊያደርግብን አይገባም፤ ይልቁን እኛ ልንገዛው ይገባል ማለት ነው፡፡ ይህ የእግዚአብሔር ቃል ነው፤ ለእናንተ የሰጠው ተስፋ ነው፡፡ ለዚህ ቃል ልባችሁ ውስጥ ሁነኛ ቦታ እንድትሰጡ አበረታታችኃለሁ፡፡

## የተሳሳተ አባባል

እስቲ ለዘመናት ሲነገር የሰማነውን የተሳሳተ አባባል እንመልከት፡፡ ሁኔታዎች አስቸጋሪ፣ የማይመቹ፣ ጐጂ፣ እና ከዚያም አልፎ ሕይወትን የሚያሰጉ ሆነው ሲገኙ አስተዋይ ናቸው ያልናቸው ሰዎች እግዚአብሔር

ነገሮችን እየተቆጣጠረ የመሆኑን ሐቅ የተሳሳተ መንገድ ይረዱታል፡፡ ይህ አመለካከት እርሱ ሁሉንም ነገር እየተቆጣጠረ በመሆኑ፣ በፍቅርና በመልካምነቱ እግዚአብሔር በመጨረሻ ነገርን ሁሉ ለበጐ ስለሚያደርገው የሚገጥመንን ተቃውሞ መቋቋም የለብንም ማለትን ያሳያል፡፡

እውነቱ ግን፣ እግዚአብሔር ተቆጣጣሪዎች እንድንሆን እኛን እዚህ ማስቀመጡ ነው፡፡ ይህን መጽሐፍ ከማስቀመጣችሁ በፊት እስቲ በሚገባ አድምጡኝ፡፡

ዘማሪው፣ ‹‹ሰማየ ሰማያት የእግዚአብሔር ናቸው፤ ምድርን ግን ለሰው ልጆች ሰጣት›› ይላል (መዝሙር 115፥16)፡፡ ሜሴጅ የተሰኘ ትርጉም ደግሞ፣ ‹‹ሰማየ ሰማያት የእግዚአብሔር ናቸው፤ ምድርን ግን እንድንገዛ እኛን እዚህ አኖረ›› ይላል፡፡

በምድር ላይ ኃላፊነት የተሰጠው ለማን ነው? ለእኛ ነው!

ሁሉን ቻዩ አምላክ፣ ሉዓላዊ ፈጣሪ ነው፤ በምድር ላይ መግዛትንና ነገሮችን መቆጣጠርን ለሰው ልጆች ለመስጠት ሉዓላዊ ምርጫ አድርጓል፡፡ ብዙዎች እንደሚያምኑት እግዚአብሔር በምድር የሚደረገውን ነገር ሁሉ ቢቆጣጠር ኖሮ፣ አዳም የተከለከለውን ፍሬ ለመብላት ባነሣ ጊዜ ጣልቃ በመግባት ከእጁ ያስጥለው ነበር፡፡ ‹‹አዳም ምን እያደረግህ ነው?›› ይለው ነበር፣ ‹‹እያደረግህ ያለኸው የሚያመጣብህን ውጤት አታውቅም? ስቃይ፣ መከራ፣ በሽታ፣ ደዌ፣ ችጋር፣ ራብ፣ ድኸነት፣ ግድያ ሌብነት እና ሌሎችም አንተና ዘሮችህ ላይ እንደሚመጡ አታውቅም? በአንተ አለመታዘዝ የምድር መንቀጥቀጥ፣ ዐውሎ ነፋስ፣ ቸነፈር፣ ድርቅ እና የዱር አራዊት አደጋ እንደሚመጣ አታውቅም? ተፈጥሮ ሁሉ ብልሽት እንደሚገጥመው አታውቅም? ከሁሉም የበለጠ ደግሞ የሰው ልጅን ወደ እኔ መልሼ ለማምጣት አንድና ብቸኛ ልጄ አሰቃቂ አሟሟት እንዲሞት መላክ ሊኖርብኝ ነው›› ይለው ነበር፡፡

እግዚአብሔር አንድን ነገር የሚሰጠው ለዘለቄታው ነው፡፡

ሆኖም፣ እግዚአብሔር አዳምን አልያዘውም፤ ምክንያቱም ምድርን ለሰው ልጅ ሰጥቷል፡፡ የሚወደን ፈጣሪ ሥልጣን ቢሰጡም እነርሱ በሚፈልጉት መንገድ ሥራ ላይ ካልዋለ መልሰው እንደሚወስዱ እንደ ሌሎች ብዙዎች አይደለም፡፡ እግዚአብሔር አንድን ነገር የሚሰጠው ለዘለቄታው ነው፡፡ ለዚህም የቃሉ ማረጋገጫ አለን፣ ‹‹የእግዚአብሔር ስጦታና ጥሪ ጸጸት የለበትም›› (ሮሜ 11፥29)፡፡

ምናልባት አንድ ሰው፣ ‹‹ግን'ኮ መጽሐፍ ቅዱስ - ምድርና በእርሷ ያለው ሁሉ፣ ዓለምና በውስጧ የሚኖር ሁሉ የእግዚአብሔር ነው›› ይላል (መዝሙር 24፥1) በማለት መከራከሪያ ያቀርብ ይሆናል፡፡ እስቲ ለዚህ መልስ እንዲሆነኝ ባለፉት ጥቂት ዓመቶች ውስጥ በቤተ ሰቤ የሆነ አንድ ነገር ልንገራችሁ፡፡

ከጥቂት ዓመታት በፊት በሰባዎቹ ዓመቶች ውስጥ ያለች የሚስቴ የሊዛ እናት ሺርሊ አንድ ዘመድ እንኳ አጠገቧ በሌለበት በፍሎሪዳ አፓርትመንት ውስጥ ትኖር ነበር፡፡ እኔና ሊዛ ቤተ ሰባችን አጠገብ እንድትኖር ከልባችን እንፈልግ ነበር፤ ታዲያ አንድ ቀን ሚስቴ ከቤታችን አምስት ደቂቃ እንኳ በማይርቅ ቦታ የሚሸጡ ትልልቅ ቤቶች ታያለች፡፡ ስለዚህም ወደ ሺርሊ ሄደን፣ ከቤቶች አንዱን ገዝተንላት እኛ አጠገብ እንድትኖርና ሜሴንጀር ኢንተርናሽናል የተሰኘው አገልግሎታችን ባልደረባ እንድትሆን እንደምንፈልግ ነገርናት፡፡ ሐሳቡን በደስታ ነበር የተቀበለችው፡፡ አንዱ ቤት ተገዛና የባለቤቴ እናት ትኖርበት ጀመር፣ ምናልባት ራስን ችሎ የመኖር ስሜቷን እንዳይጐዳ በማለትም በየወሩ መጠነኛ ኪራይ ልናስከፍላት ወሰንን፡፡ እዚያ ቤት መኖር ከጀመረች ጥቂት ዓመት ሆኖአል፤ በማንኛውም የሕይወት ገጽታዋም እየተባረከች ነው፡፡

ምንም እንኳ፣ የቤቱ ባለቤት እኔ ብሆንም፣ በዚያ ጊዜ ሁሉ ቤቱን እንዴት መያዝ እንዳለባት፣ የቤት ዕቃዎቿን የት የት ቦታ ማድረግ እንዳለባት፣ አንድም ቀን ነግሬአት አላውቅም፡፡ ቤቷን እንዴት ማስተዳደር እንዳለባት፣ ለቁርስ፣ ለምሳ፣ ለእራት ምን ዐይነት ምግብ መሥራት እንዳለባት ወይም ምን ዐይነት የኤሌክትሪክ ዕቃዎች መጠቀም እንዳለባት ነግሬአት አላውቅም፡፡ የዕለት ተዕለት ጉዳዮችን መምራት የሊዛ እናት ኃላፊነት ነበር፡፡ እርግጥ ነው፣ የቤቱ ባለቤት እኔ ነኝ፤ ሕጋዊ ማረጋገጫም አለኝ - ሆኖም አሁን ለእሷ አከራይቼዋለሁ፤ አሁን ቤቱን እየተጠቀመችበት ያለች እርሷ ናት፡፡ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ የእኔን ርዳታ መጠየቅ ትችላለች፤ እርሷ ካልጠየቀች በእርሷ ጉዳይ ጣልቃ አልገባም፡፡

በተመሳሳይ መንገድ፣ ምድር የእግዚአብሔር ናት፡፡ ባለቤቷ እርሱ ነው፤ ይሁን እንጂ፣ በኃላፊነት ለሰው ልጅ ሰጥቷታል፡፡ እርሱ እኛን በፈጠረ ጊዜ፣ በምድር ላይ ኃላፊነትን የሰጠን ጊዜ፣ የተናገረውን ስሙ፣

> እግዚአብሔር ሰውን በራሱ መልክ ፈጠረው፤ በእግዚአብሔር መልክ ፈጠረው፤ ወንድና ሴት አድርጐ ፈጠራቸው፡፡ እግዚአብሔርም፣ ብዙ ተባዙ ምድርን ሙላት፤ ግዟትም አላቸው (ዘፍጥረት 1፥27-28)፡፡

እግዚአብሔር በዚህ ምድር ኃላፊነት ሰጥቶናል፡፡ በዚህ ፕላኔት ነገሮችን የመቆጣጠር ሥልጣን አለን፡፡

## አዲስ ባለቤት

በኤደን ገነት ትልቅ ችግር የተነሣው፣ ሰይጣን እባብ አካል ውስጥ ገብቶ በእግዚአብሔር ቃል እንዲያምፁና የእርሱን ሐሰት እንዲቀበሉ አዳምና ሔዋንን ያሳመነ ጊዜ ነበር፡፡ የሰው ልጅ ይህን ካደረገ በኃላ ራሳችንን ለአዲሱ ባለቤት አሳልፈን ሰጠን፤ የዚያ አዲስ ባለቤት ስም ሰይጣን ይባላል፡፡ የሰጠነው ራሳችንን ብቻ አልነበረም፤ በእኛ አገዛዝ ሥር የነበረውንም ነገር ሁሉ ሰጥተነዋል፡፡ ራሷ ተፈጥሮንም ጨምሮ የሰው ልጅ ዘር ሁሉ አሁን በዚህ ክፉ ቁጥጥር ሥር ሆነ፡፡ ወደ አዲሱ ባለቤት የተደረገው ሽግግር በኃላ ላይ በሰይጣንና በኢየሱስ መካከል ውጊያ የተደረገበትን ምክንያት ግልጽ ያደርጋል፡፡ ሰይጣን ኢየሱስን ወደ አንድ ረጅም ተራራ ወስዶ፣ የዓለምን መንግሥታት ሁሉ አሳየው፡፡ ‹‹የእነዚህ መንግሥታት ሥልጣንና ክብር ሁሉ ለእኔ ተሰጥቶአል፤ እኔም ለምወደው ስለምሰጥ ለአንተ እሰጥሃለሁ›› አለው (ሉቃስ 4፥6)፡፡

የዓለም መንግሥታት ሁሉ ለሰይጣን የተሰጡት መቼ ነበር? ከብዙ ዓመታት በፊት አዳም የተሰጠውን ምድርን የመግዛት መብቱን የተወ ጊዜ ነበር ይህ የሆነው፡፡ እግዚአብሔር ለሰው ሰጥቶት የነበረው፣ አሁን በዋናው ጠላቱ በሰይጣን እጅ ሆነ፡፡ ‹‹እኛ ከእግዚአብሔር እንደ ሆንን፣ መላው ዓለምም (አካባቢያችን ሁሉ) በክፉው ሥር እንደ ሆነ እናውቃለን›› በማለት መጽሐፍ ቅዱስ የሚነግረን በዚህ ምክንያት ነው (1ዮሐንስ 5፥19)፡፡

## መልሶ የመውሰድ ዕቅድ

እግዚአብሔር አዳም ያስወሰደውን ማስመለስና እንደ ገና በሰው ልጅ እጅ ውስጥ ማስገባት ፈለገ፡፡ ይሁን እንጂ፣ በአምላክነቱ መጥቶ መልሶ መንጠቅ አይችልም፤ ምክንያቱም አዳም በግልጽ ያስረከበውን እግዚአብሔር ሊወስድለት አይችልም፡፡ ያስወሰደው ሰው ነበር፤ ማስመለስ ያለበትም ሰው ነው፡፡ ኢየሱስ፣ ‹‹የሰው ልጅ›› ሆኖ የመጣው በዚህ ምክንያት ነበር፡፡ ከድንግል ተወለደ፤ ይህም ፍጹም ሰው አደረገው፡፡ የተፀነሰው በመንፈስ ቅዱስ ስለ ነበር ፍጹም አምላክ ነበረ (ስለሆነም ከኃጢአት እርግማን ነጻ ነበር)፡፡ ይሁን እንጂ፣ ‹‹ጊዜው ሲደርስ ኢየሱስ በመጣ ጊዜ፣ የባሪያን መልክ ይዞ፣ በሰውም አምሳል ተገኝቶ ራሱን ባዶ›› እንዳደረገ በግልጽ ተነግሮናል (ፊልጵስዩስ 2፥7)፡፡ ምንም እንኳ አምላክ ቢሆንም፣ አምላክነቱን በመተው እንደ ሰው በዚህ ምድር ተመላለሰ፡፡

ኢየሱስ ሙሉ በሙሉ ለአባቱ በመታዘዝ ኖረ፡፡ በፈቃደኝነት መስቀልን በመቀበል፣ አዳም ያስወሰደውን በገዛ ደሙ መግዛት ቻለ፡፡ መጽሐፍ ቅዱስ፣ ‹‹የአለቆችንና የባለ ሥልጣናትንም ማዕረግ በመግፈፍ በመስቀሉ ድል ነሥቶ በአደባባይ እያዞራቸው እንዲታዩ አደረገ›› ይላል (ቈላስይስ 2÷15)፡፡ አሁን አዳም ያስወሰደው ሥልጣን ያለው እርሱ እጅ ውስጥ ነው፡፡ ‹‹ሥልጣን ሁሉ በሰማይና በምድር ተሰጥቶኛል›› በማለት የተናገረው በዚህ ምክንያት ነበር (ማቴዎስ 28÷18)፡፡

አንድ ቀን መጥቶ ተፈጥሮን ሁሉ አዳም በኤደን ገነት ከመውደቁ በፊት ወደ ነበረው ሁኔታ ይመልሳል፡፡ ይህን በተመለከተ ሐዋርያው ጳውሎስ እንዲህ በማለት ጻፈ፣

> ፍጥረት ሁሉ ለከንቱነት ተዳርጐአል፤ ይኸውም በራሱ ምርጫ አይደለም… ፍጥረት ራሱ ከመበስበስ ባርነት ነጻ ወጥቶ ለእግዚአብሔር ልጆች ወደ ሆነው ወደ ከበረው ነጻነት እንዲደርስ ነው (ሮሜ 8÷20-21)፡፡

አሁንም ቢሆን ፍጥረት ለድካም እንደ ተገዛ ነው፤ አካላችን ያረጃል፤ ኃላም ይሞታል፤ ቁሳዊው ዓለም ይበላሻል፣ ይበሰብሳል፤ ዛሬም የዱር አራዊት ደካማውን እንስሳ እያደኑ ይበላሉ፤ ዛሬም እባቦች የሚገድል መርዝ አላቸው፤ በሽታ በጣም ተስፋፍቶአል፤ ዐውሎ ነፋስና ማዕበል ጥፋት ያደርሳሉ፡፡ ይሁን እንጂ፣ በእነዚህ ሁሉ ላይ ሥልጣን ያለው አለ፣ እርሱ ክርስቶስ ነው፤ እርሱ ሁኔታውን መለወጥ ይችላል፡፡

## ክርስቶስ ማን ነው?

እዚህ ላይ ጥያቄው ለመሆኑ ክርስቶስ ማን ነው? የሚል ይሆናል፡፡ ያልታደሰ አእምሮ በድጋሚ ሐቁን ከእግዚአብሔር ልጆች የሚሰርቀው እዚህ ላይ ነው፡፡ ብዙዎች ስለ ክርስቶስ ሲያስቡ፣ ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ ብቻ ነው የሚያስቡት፤ ክርስቶስ የመጨረሻ ስሙ ይመስላቸዋል፡፡ እነዚህ የተወደዱ ወገኖች መስቀል ላይ ከሞተውና ከሞት ከተነሣው ታላቁ ንጉሣችን ውጪ ሌላ አያስቡም፡፡ እርግጥ ነው፣ ክርስቶስ የሚለው ስም ጌታና አዳኛችንን ነው የሚመለከተው፤ ሆኖም፣ እስቲ የእግዚአብሔር ቃል የሚለውን እንስማ፡፡

ሐዋርያው ጳውሎስ፣ ‹‹እንግዲህ እናንተም የክርስቶስ አካል ናችሁ፤ እያንዳንዳችሁም የአካሉ ብልቶች ናችሁ›› ይላል (1ቆሮንቶስ 12÷27)፡፡ እኛ አማኞች በአንድነት፣ የክርስቶስ አካል ነን፡፡ እያንዳንዳችን ሁነኛ፣ ‹‹የአካሉ ብልቶች›› ነን፡፡ ኢየሱስ ራስ ሲሆን፣ እኛ አካል ነን፤ ነገሩ ያን ያህል ቀላል ነው!

እያንዳንዳችሁ የየራሳችሁ ራስ አላችሁ፤ ሁለት እጆች፣ ሁለት እግሮች፣ ሁለት ጉልበቶች፣ ሁለት ክንዶች፣ ደረት፣ ሆድ፣ ጉበት፣ ሁለት ኩላሊቶችና ወዘተ አሉዋችሁ፡፡ እንግዲህ ስለ ራሳችሁ ስታስቡ ከአካላችሁ የተለየ አድርጋችሁ ታስባላችሁ? ራሳችሁን በአንድ የተፀውዖ ስም፣ አካላችሁን ደግሞ በተለየ የተፀውዖ ስም ትጠራላችሁ? በፍጹም እንደዚያ አታደርጉም፤ ምክንያቱም አንድ ሰው ናችሁ፤ አንድ አካል ናችሁ፡፡ የእኔን ራስ ብቻ ብታዩ፣ እንኳ፤ ጆን ብቨሬ ነው ትላላችሁ፡፡ ለጊዜው ራሴ ተከልሎ ቢሆንና አካሌን ብቻ ብታዩ አሁንም ቢሆን፣ ጆን ቢቨሬ ነው ትሉታላችሁ፡፡ ራሴና አካሌ አንድ ናቸው፡፡

በተመሳሳይ መልኩ፣ የክርስቶስ ራስ እና የክርስቶስ አካል አንድ ነው፡፡ ኢየሱስ ራስ ነው፤ እኛ ደግሞ የተለያዩ የአካሉ ብልቶች ነን፤ ስለዚህ በክርስቶስ አንድ ነን፡፡ ስለሆነም፣ አዲስ ኪዳን ውስጥ፣ ‹‹ክርስቶስ›› የሚለውን ቃል ስታዩ፣ በመስቀል ላይ የሞተውን ብቻ ሳይሆን ስለ ራሳችሁም ማሰብ ይኖርባችኋል፡፡ መጽሐፍ ቅዱስ፣ ‹‹የሚቀድሰውና የሚቀደሱት ሰዎች ከአንድ ቤተ ሰብ ናቸው›› በማለት የሚናገረው ለዚህ ነው (ዕብራውያን 2÷11)፡፡ ኢየሱስ ራሱም፣ ‹‹የእነርሱን ትምህርት ተቀብለው በእኔ ለሚያምኑ ጭምር እንጂ፣ ለእነዚህ ብቻ አልጸልይም፤ ይህም አባት ሆይ፣ አንተ በእኔ፣ እኔም በአንተ እንዳለሁ ሁሉም አንድ እንዲሆኑ፣ እንዲሁም አንተ እኔን እንደ ላክኸኝ ዓለም ያምን ዘንድ እነርሱም በእኛ እንዲሆኑ ነው›› በማለት ጸልዮአል (ዮሐንስ 17÷20-21)፡፡

እስከ አሁን በተመለከትናቸው ጥቅሶች መሠረት ከኢየሱስ ጋር አንድ ነን! ስለሆነም፣ አንዱን ወይም ሁለቱን ጥቅስ ከዐውደ ምንባቡ እያወጣሁ የተሳሳተ ትርጉም እየሰጠሁ እንዳልሆነ እርግጠኛ መሆን ትችላላችሁ፤ ይህን አስደናቂ መርሕ አስመልክቶ እምነትና ግንዛቤያችሁን ለማጠናከር ቶሎ ቶሎ ሌሎች ጥቅሶችንም አካፍላችኋለሁ፡፡ ልክ ከዚህ በፊት አንብባችሁ ወይም ሰምታችኋቸው የማታውቁ ያህል እነዚህን ጥቅሶች በጥንቃቄ እንድታነቡና በጥልቀት እንድታስቡባቸው እጠይቃችኋለሁ፡፡

- ‹‹ከመለኮት ባሕርይ ተካፋዮች›› እንድንሆን፣ ከእግዚአብሔር ቃል እንደ ገና እንደ ተወለድን ጴጥሮስ ይጽፋል (1ጴጥሮስ 1÷23፤ 2 ጴጥሮስ 1÷4)፡፡ *ባሕርይ* የሚለው ቃል፣ ‹‹የአንድ ሰው ፀባይ፣ ውስጣዊ ወይም ወሳኝ ማንነት›› ተብሎ ሊተረጎም ይችላል፡፡ አንድ ሰብዓዊ ፍጡር እንጂ፣ ሁለት ስላይደለሁ ራሴ ውስጥ ያለው ተፈጥሮ እጄም ውስጥ እንዳለ ሁሉ፣ እኔና እናንተም ወሳኝ የክርስቶስ ባሕርያት አሉን፡፡

- ሐዋርያው ዮሐንስ፣ ‹‹ከእርሱ ሙላት… ተቀብለናል›› በማለት ጽፎአል (ዮሐንስ 1፥16)፡፡ *ሙላት* የሚለውን ቃል ልብ አደረጋችሁ? እንግዲህ የዮሐንስን ቃል ከጴጥሮስ ጋር በማጣመር የክርስቶስን ወሳኝ ባሕርያት ወይም ተፈጥሮአዊ ማንነት ሙላት መቀበላችንን እንመለከታለን፡፡
- ቆየት ብሎም መጀመሪያ መልእክቱ ላይ ዮሐንስ፣ ‹‹በዚህም ዓለም እርሱን (ኢየሱስን) እንመስላለንና›› በማለት ጽፎአል (1 ዮሐንስ 4፥17)፡፡ በዚህ ምንባብ እየተናገረ ያለው፣ ቀጥሎ ስላለው ሕይወት አይደለም፡፡ ስለ አሁን ጊዜ ነው የሚናገረው፣ ኢየሱስ እንደ ሆነው እኛም እንደዚያው ነን፡፡ አሁን በዚህ ምድር እያለን ኢየሱስን መምሰል እንችላለን ማለት ነው!
- ጳውሎስ፣ ‹‹ሰውነታችሁ የክርስቶስ የአካሉ ብልቶች እንደ ሆነ አታውቁምን?›› በማለት ጽፎአል (1 ቆሮንቶስ 6፥15)፡፡ የሚናገርበት ሁኔታ ይህ ግንዛቤ መሠረታዊ መሆን እንዳበት ያመለክታል፡፡ ይህን መሠረታዊ እውነታ ዘንግተን ይሆን? እንደ ቤተ ክርስቲያን በእውነት ይህን ቃል እያመንን ይሆን?

## የክርስቶስ ሥልጣን

*ክርስቶስ* የሚለውን ቃል ስንሰማ፣ እኛንም እንደሚጨምር አሁን ተመልክተናል፤ እስቲ አሁን ደግሞ በእርሱ ያለንን ሥልጣንና ኃይል መጠን በተመለከተ ይህ መገለጥ ምን ማለት እንደ ሆነ ለመረዳት እንሞክር፡፡ በኤፌሶን መልእክቱ እያንዳንዱ የክርስቶስ ተከታይ፣ ‹‹ታላቅ የሆነውን ኃይሉን›› እንዲያውቅ ጳውሎስ ከልቡ ይጸልያል (ኤፌሶን 1፥19)፡፡

ምንኛ ድንቅ ገላጭ ቃል ነው! ጥልቀትና ከፍታው ምን ያህል ታላቅ ነው! የክብር ጌታ ክርስቶስ የማይለካና የማይወሰን ኃይል እንዳለው ትስማማላችሁ? የእርሱ ኃይል ማንኛውንም ታላቅነት፣ ማንኛውንም ሥልጣን፣ ማንኛውንም በአጽናፈ ዓለሙ ያለ ብርታት እንደሚበልጥ ታምናላችሁ? ያለ ምንም ማቅማማት ይህን እንደምታምኑ እርግጠኛ ነኝ፡፡

በክርስቶስ ያላችሁን እናንተነት በተመለከተስ ይህን ለማለት ትደፍራላችሁ? ከዚያም የበለጠ በእውነት ታምኑበታላችሁ? እንደዚያ ካልሆነ፣ ራሳችሁን ከክርስቶስ ለይቷችኋል ማለት ነው፡፡ ለመሆኑ፣ የክርስቶስ ሳይሆን የአንድ የተለየ አካል ብልቶች ናችሁ እንዴ? የክርስቶስ አካል፣ የአካሉ ብልቶች አይደላችሁም? ምናልባትም፣ የኔ ወንድም፣ አሁንስ አበዛኸው! ትሉኝ ይሆናል፡፡ ግን አብዝቼዋለሁ እንዴ? እንዳላበዛሁት

ለማረጋገጥ ከላይ ያለውን ጥቅስ ቀጣይ ሐረግ ተመልከቱ፣ ‹‹ለእኛ ለምናምነው ከሁሉ በላይ ታላቅ የሆነውን ኃይሉን እንድታውቁ እጸልያለሁ›› (ኤፌሶን 1፥19)፡፡

ጳውሎስ በአንድነት ስለ ሁላችንም እየተናገረ ነው፡፡ እንዴት? በኢየሱስ ክርስቶስ አማኝ እንደ መሆናችሁ መጠን፣ የክርስቶስ አካል ክፍል ናችሁ፡፡ ስለሆነም ክርስቶስ ያለው ኃይል እናንተም አላችሁ! ‹‹በዚህም ዓለም እርሱን (ኢየሱስን) እንመስላለንና፡፡›› ይህ እውነት ወደ ልባችሁ ዘልቆ እንዲገባ ትፈቅዳላችሁ? እስቲ የኤፌሶን ሰዎችን አስመልክቶ ጳውሎስ ያቀረበውን ጸሎት ጥቂት ሰፋ አድርገን እንይ፣

> ይህም ኃይል እንደ እርሱ ታላቅ ብርታት አሠራር፣ ክርስቶስን ከሙታን ሲያስነሣውና በሰማያዊ ስፍራ በቀኙ ሲያስቀምጠው የታየው… (ኤፌሶን 1፥19-20)፡፡

ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ መሰቀሉን፣ መሞቱን፣ መቀበሩን፣ ከሞት መነሣቱንና አሁን ከፍ ባለ ሥልጣን ቦታ መቀመጡን ታምናላችሁ? እውነተኛ ክርስቲያን ከሆናችሁ ሙሉ በሙሉ ታምናላችሁ፡፡ እናንተን በተመለከተስ ይህ ሁሉ እውነት መሆኑንስ ታምናላችሁ? አብዛኞቹ አማኞች በዚህ ብርሃን ራሳቸውን አያዩም፡፡ ይሁን እንጂ ጳውሎስ፣

> ከክርስቶስ ኢየሱስ ጋር አንድ እንድንሆን የተጠመቅን፣ ከሞቱ ጋር አንድ እንሆን ዘንድ እንደ ተጠመቅን አታውቁምን? ስለዚህ ክርስቶስ በአብ ክብር ከሞት እንደ ተነሣ እኛም እንዲሁ በአዲስ ሕይወት እንድንኖር በጥምቀት ሞተን ከእርሱ ጋር ተቀብረናል (ሮሜ 6፥3-4) በማለት ነበር የጻፈው፡፡

ይህ ምንባብ እየተናገረ ያለው ዳግም በተወለድን ጊዜ በእግዚአብሔር መንፈስ በክርስቶስ አካል መዋጣችን እንጂ፣ ስለ የውሃ ጥምቀትን ሥርዓት እንዳልሆነ ልብ አድርጉ (1 ቆሮንቶስ 12፥13 ይመ)፡፡ የክርስቶስ አካል ነን፣ ስለዚህም በእርሱ በተዋጥንበት ቅጽበት ታሪካችን ተለውጧል፡፡ ከእርሱ ጋር ሞተናል፤ ከእርሱ ጋር ተቀብረናል፤ ከእርሱ ጋር ተነሥተናል፤ እንደ አዲስ ፍጥረት እርሱ እንደ ኖረ እንኖራለን! ‹‹በዚህም ዓለም እርሱን እንመስላለንና›› የሚለውን በድጋሚ አስተውሉ፡፡ በክርስቶስ ነን! የክርስቶስ ነን! የእርሱ አካል ነን! ከእርሱ ጋር አንድ ሆነናል!

የክርስቶስ አካል በመሆናችን በኤፌሶን 1፥20 መሠረት ከክርስቶስ ጋር አገዛዝ ቦታ ላይ ተቀምጠናል፡፡ እንዲያውም ይህ ቦታ ከእግዚአብሔር አብ ውጪ አጽናፈ ዓለሙ ውስጥ እጅግ ከፍ ያለ የሥልጣን ቦታ ነው፡፡

ኢየሱስ፣ ‹‹ሥልጣን ሁሉ በሰማይና በምድር ተሰጥቶኛል›› አለ (ማቴዎስ 28፥18)። በመቀጠል ጳውሎስ፣

> ከግዛትና ከሥልጣን፣ ከኃይልና ከጌትነት እንዲሁም በአሁኑ ዘመን ብቻ ሳይሆን በሚመጣውም ዘመን ቢሆን፣ ሊሰየም ከሚቻለው ስም ሁሉ በላይ ነው (ኤፌሶን 1፥21) አለ።

ኢየሱስ ክርስቶስ በዚህ ዓለም እና በመላው አጽናፈ ዓለም ከግዛት፣ ከሥልጣንና ከኃይል ሁሉ በላይ በሆነ ቦታ መቀመጡን ታምናላችሁ? አዎን፣ ክርስቲያኖች እንደ መሆናችሁ መጠን ታምናላችሁ። ግን በድጋሚ ልጠይቃችሁ፣ እናንተን በተመለከተ፣ ይህ እውነት መሆኑን ታምናላችሁ? ምናልባት ራሳችሁን በዚህ ብርሃን እያያችሁ ላይሆን ይችላል። በግልጽ ለማስቀመጥ፣ ይህን እውነት በሚገባ አታምኑም። እንደዚያ ከሆነ፣ በአስተሳሰባችሁ ወይም በእምነታችሁ ራሳችሁን ከክርስቶስ ለይታችኋል ማለት ነው። የአንድ ሌላ አካል ብልቶች ናችሁ እንዴ? አይደለም፣ የክርስቶስ አካል ብልቶች ናችሁ! በክርስቶስ ሁላችንም እንደዚያው ነን። የእርሱ አካል ነን! ጳውሎስ ይህን ሲያረጋግጥ ልብ አድርጋችሁ አድምጡ፣

የክርስቶስ አካል በመሆናችን አሁን አገዛዝ ቦታ ላይ ተቀምጠናል።

> እግዚአብሔርም ሁሉን ከእግሩ በታች አስገዛለት፤ በቤተ ክርስቲያንም በማንኛውም ነገር ላይ ራስ አድርጎ ሾመው። እርሱም ሁሉን ነገር በሁሉም ረገድ የሚሞላው የእርሱ ሙላት የሆነች አካሉ ናት (ኤፌሶን 1፥22-23)።

አካሉ ነን፤ የኢየሱስ ክርስቶስ ሙላት ነን፤ ፍጹም ከእርሱ ጋር አንድ ነን። ጳውሎስ ሁሉም ነገር ከእግሩ በታች እንደ ተገዛለት ይናገራል። እንግዲህ በክርስቶስ አካል ውስጥ የእግር ዐውራ ጣት እንኳ ከሆናችሁ በዚህ ምድር ሆነ ከምድር በታች፣ ከግዛት፣ ከኃይልና ከሥልጣን ሁሉ በላይ ናችሁ ማለት ነው። በክርስቶስ ሥልጣናችሁ ተመልሷል፤ ሌላው ቀርቶ አዳም ካስወሰደው የበለጠ ሥልጣን እንኳ አላችሁ።

የዚህን እውነታ ትልቅነት መቀበል እንደሚከብደን እግዚአብሔር አስቀድሞ ማየት መቻሉ መልካም ነው፤ ስለዚህም በኤፌሶን መልእክት ሁለተኛው ምዕራፍ ይበልጥ ግልጽ እንዲያደርገው ጳውሎስን አነሣሥቶታል። ለጥርጥር ምንም ቦታ አልተወም። የመጽሐፍ ቅዱስ ምዕራፎችና ቁጥሮች በኋላ የተጨመሩ መሆናቸውን ልብ አድርጉ ይህ - አንድ መልእክት፣ አንድ ቀጣይ ሐሳብ ነው፣

> እግዚአብሔር ከክርስቶስ ጋር አስነሣን፤ በክርስቶስ ኢየሱስ በሰማያዊ ስፍራ ከእርሱ ጋር አስቀመጠን (ኤፌሶን 2፥6)፡፡

ራስ ከአካል የተለያየ አይደለም፡፡ ሁላችንም በአንድነት በሰማያዊው ክልል በግዛት፣ በሥልጣንና በኃይል ቦታ ተቀምጠናል፡፡ በሌላ አነጋገር፣ በዚህ ምድር ካለ ማንኛውም ኃይል በላይ የሆነ ቦታ ላይ ነን ማለት ነው - እንዲያውም ከሁሉ በላይ!

ማንኛውም ጋኔን፣ የወደቀ መልአክ ወይም ራሱ ሰይጣን እንኳ ቢሆን፣ እኛ ላይ ኃይል ያለው አንድም የለም፡፡ በክርስቶስ ካለን ቦታና ሥልጣን የተነሣ እጅግ ከፍ ብለን እንገዛለን!

ሃሌ ሉያ!

## በሕይወት መንገሥ

እንግዲህ እስካሁን አጽንዖት ስንሰጥ በነበረው ብርሃን አማካይነት ቀደም ሲል በዚህ ምዕራፍ አንሥተን የነበረውን ጥቅስ እንደ ገና እንይ፣

> የጸጋን ብዛትና የጽድቅን ስጦታ ብዛት የሚቀበሉ፣ በአንዱ በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል በሕይወት ይነግሣሉ (ሮሜ 5፥17)፡፡

እስቲ ለአንድ አፍታ ትኩረታችሁን፣ ‹‹በክርስቶስ በኩል በሕይወት ይነግሣሉ›› የሚለው ሐረግ ላይ አድርጉ፡፡ እንደ የክርስቶስ አካል ብልቶች፣ በሕይወትና እግዚአብሔርን በመምሰል ላይ በሚነሣብን ማንኛውም ተቃውሞ ላይ እንገዛለን፡፡ በዚህ ምድር መግዛት ያለብን እኛ እንደ መሆናችን መጠን ነገሮች መበላሸታቸውና በዚያ ሁኔታ መቀጠላቸው ምክንያቱ ሥልጣናችንን አሳልፈን መስጠታችን ወይም በሥልጣናችን እንደሚገባ አለመጠቀማችን ይሆን?

ከብዙ ዓመት በፊት የቤተ ክርስቲያናችን ፓስተር ወደ ስብከት አገልግሎት እንደምገባ በትልቅ ጉባኤ ፊት ተናግሮ ነበር፡፡ ከጥቂት ቀን በኋላ አንድ ሽማግሌ አገልጋይ ወደ ሚስቴ መጥቶ፣ ‹‹ሊዛ፣ ባልሽን በተመለከተ ከጌታ ቃል አለኝ›› አላት፡፡

በዚያ ጊዜ በጣም ወጣቶችና በጌታ ማደግና መማር የምንፈልግ ነበርን (ዛሬም እንደዚያው ነን)፡፡ ሊዛም፣ ‹‹ቃሉን ንረገኝ፣ እኔ ደግሞ ለጆን እነግረዋለሁ›› አለችው፡፡

ሽማግሌው አገልጋይ፣ ‹‹እግዚአብሔር በሰጠው ሥልጣን የማይመላለስ ከሆነ፣ ሥልጣኑን ሌላው እንደሚወስደውና በእርሱ ላይ እንደሚጠቀምበት ለጆን ንገሪው›› አላት፡፡

ሊዛ ያንን ቃል ስትነግረኝ ልክ እንደ አንድ የተሳለ ቢላ ልቤን ሰንጥቆ ውስጤ ገባ፡፡ ለእኔ ብቻ ሳይሆን በክርስቶስ ላሉት ሰዎች ሁሉ፣ ያ ቃል እውነት መሆኑን በዘመናት ውስጥ ማረጋገጥ ችዬአለሁ፡፡ በእውነት እግዚአብሔርን የሚወዱ ብዙዎች የተቃውሞ ኃይላትና ሁኔታዎች እስረኞች ሆነው ሳይ ብዙ ጊዜ በጣም አዝናለሁ፡፡ ጌታ ኢየሱስ ያን ያህል ከባድ ዋጋ የከፈለው እነርሱን ነጻ ለማድረግ ነበር፤ እነርሱ ግን አሁንም በባርነት ውስጥ ናቸው፡፡ አስቸጋሪ የአየር ሁኔታ፣ የተፈጥሮ አደጋ፣ ሕመም፣ ደዌ፣ አጋንንታዊ ተፅዕኖ፣ ተቃውሞ የበዛበት ሁኔታ ዝርዝሩ ተቆጥሮ አያልቅም፡፡ እነዚህ ኃይሎች በሕይወት ንጉሦችና ልዕልቶች እንዲሆኑ የተወሰኑትን፣ ሆኖም በክርስቶስ ያላቸውን ማንነት ያላወቁትን መልካም ሰዎች ይገዟቸዋል፤ ይቆጣጠሯቸዋል፡፡

አንተም ብትሆን መግዛት ሲገባህ፣ እየተገዛህ ከሆነ የምሥራች አምጥቼልሃለሁ፡፡ በዚህ ምዕራፍ የተመለከትነው የእግዚአብሔር ቃል ልብህ ውስጥ ቦታ ሊኖረው ከቻለ፣ ሕይወትህ መለወጥ ይጀምራል፡፡ ዐላዋቂዎችና ደካሞች የሆኑትን ለመርዳት ያለህን ኃይልና ሥልጣን አሁን ታውቃለህ፤ ችግር ውስጥ ላሉት የመንግሥቱን መልካም ሕይወት አሁን ማምጣት ትችላለህ፡፡

ሐዋርያው ዮሐንስ የክርስቶስ አካል ለሆንነው ሁሉ ጠንከር ያለ ቃል ይናገራል፣ ‹‹ማንም በእርሱ እኖራለሁ የሚል፣ ኢየሱስ እንደ ተመላለሰ መመላለስ ይገባዋል›› (1ዮሐንስ 2፥6)፡፡

‹‹አብ እኔን እንደ ላከኝ እኔም እናንተን እልካችኋለሁ›› በማለት የተናገረ ጊዜ ኢየሱስ ቀደም ሲል ይህንኑ አመልክቶ ነበር (ዮሐንስ 20፥21)፡፡ እርሱ እንደ ገዛ ሁሉ እኛም እንድንገዛ ይፈልጋል፡፡ ኢየሱስና አብረውት የነበሩትን ለማጥፋት ማዕበል በተነሣ ጊዜ፣ ለነፋሱና ለባሕሩ ተናገረ፤ እነርሱም ታዘዙለት፡፡ በምድረ በዳ ለነበሩት ብዙዎች ምግብ በፈለገ ጊዜ፣ የነበራቸውን ጥቂቱን ነገር በተአምር አበረከተና በሺዎች የሚቆጠሩትን መገበ፣ እንዲያውም፤ መጀመሪያ ከነበራቸው ይልቅ የተራረፈው ምግብ በለጠ፡፡ ጀልባ ባልነበረው ጊዜ፣ ባሕሩን መሻገር ፈልጐ ነበር፤ ስለዚህ ውሃው ላይ ተራመደ፡፡ በሰርግ ቤት ወይን ጠጅ ባለቀባቸው ጊዜ፣ ውሃውን ወደ ወይን ጠጅ ለወጠ፡፡ ከአፉ በወጣ ቃል ብቻ የበለስ ዛፏ እንድትጠወልግና እንድትደርቅ አደረገ፡፡ እርሱን ሊያጠቃ የመጣው ሰው ጆሮ በሰይፍ

በተቆረጠ ጊዜ ጆሮውን ቀጠለለት፡፡ ደዌ ያለባቸውን አነጻ፤ ዕውሮች እንዲያዩ፣ ደንቆሮዎች እንዲሰሙ፣ ሽባዎች እንዲራመዱ አደረገ፡፡ በሕይወት ለነገሠው ኢየሱስ ከእነዚህ ምድራዊ ተግዳሮቶች አንዱ እንኳ አልተቋቋመውም፡፡

አጋንንት ያነሣሡዋቸው ሰዎች አላሸነፉትም፤ በማንኛውም ተቃውሞ የተነሡበትን ፀጥ የሚያደርግ መልስ ነበረው፡፡ ክፉ ባለ ሥልጣኖች ሊይዙት አልቻሉም፤ በቁጣ የገነፈሉ ሰዎች ከገደል አፋፍ ገፍትረው ሊጥሉት አልቻሉም፤ ይልቁን በመካከላቸው አልፎ ሄደ፡፡ አጋንንት የነበሩባቸው ሰዎች አላስፈራቱትም፤ እንዲያውም ነጻ አወጣቸው፡፡ የኢየሱስን ሕይወት ባቀረበበት ታሪክ ዮሐንስ፣ ‹‹ኢየሱስ በዚህ መጽሐፍ ያልተጻፉ ሌሎች አያሌ ታምራዊ ምልክቶችን በደቀ መዛሙርቱ ፊት አድርጓል. . . ኢየሱስ ያደረጋቸው ሌሎችም ብዙ ነገሮች አሉ፤ ሁሉም ነገር ቢጻፍ፣ ለተጻፉት መጻሕፍት ሁሉ ዓለም በቂ ቦታ የሚኖረው አይመስለኝም›› እንዳለው ሁሉ ዝርዝሮቹ ማለቂያ አይኖራቸውም (ዮሐንስ 20፥30፤ 21፥25)፡፡

ኢየሱስ ክርስቶስ ሕይወት ላይ ገዛ (ነገሠ)፡፡ ተቃውሞና አዳጋች ሁኔታ ላይ ገዛ፡፡ መንግሥተ ሰማይን ወደ ምድር አመጣ፡፡ እንድንከተለው ፈለጉን ተወልን፡፡ እንዲያውም ከእርሱ የበለጠ እንድናደርግ እንኳ ይፈልጋል፡፡ ‹‹እውነት እላችኋለሁ፤ በእኔ የሚያምን እኔ የማደርገውን ሥራ ይሠራል፤ እንዲያውም ከእነዚህም የሚበልጥ ያደርጋል›› አለ (ዮሐንስ 14፥12)፡፡

ይህ ደግሞ ወደሚቀጥለው ምክንያታዊ ጥያቄ ያመጣናል፡፡ በሕይወት የምንነግሠው እንዴት ነው? ያ ኃይል የሚመጣው ከየት ነው?

# 3

# የኃይሉ ምንጭ

*የጸጋን ብዛትና የጽድቅን ስጦታ ብዛት የሚቀበሉ*

*በአንዱ በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል በሕይወት ይነግሣሉ።*

*ሮሜ 5፥17*

ቀደም ሲል በተመለከትነው መሠረት፣ እንደ ንጉሦችና ልዕልቶች በሕይወት ላይ መግዛት እንዳለብን እናውቃለን፡፡ የዚህ ምድር ሕይወት ሊገዛን አይገባም፤ እኛ መግዛት አለብን፡፡ እንግዲህ ሁለተኛው ምክንያታዊ ጥያቄ፣ ያንን ማድረግ የሚያስችለኝ ኃይል ወይም ችሎታ አለኝ? የሚል ይሆናል፡፡

እስቲ፣ ስለ አንዲት ትንሽ የውሻ ቡችላና ግዙፍ አጥቂ ድብ ማሰብ ሞክሩ፡፡ ቡችላው ኃይለኛና አስፈሪ ይመስላል፡፡ እንዲህ ያለ የውሻ ቡችላ አይታችሁ ታውቁ የለ? የእኔ ነው ከሚለው አካባቢ እስኪሄዱለት ድረስ ያለ ማቋረጥ ይጮኻል፡፡ ምናልባት የሱሪያችን ታችኛ ክፍል ይቦጭቀው ይሆናል፡፡ ቀስ ብላችሁ ገፋ ካደረጋችሁት፣ እንደ ገና እናንተ ላይ የበላይነት ለማሳየት ሙከራውን ይቀጥላል፡፡ ይሁን እንጂ፣ በጣም ስትናደዱ አንድ ጥሩ ካልቾ ታቀምሱታላችሁ፣ የምትችሉትን ያህል ትጮኹበታላች፤ ያኔ ውሻው ደንግጦ ከአጠገባችሁ ይጠፋል፤ አሳፋሪ ሽንፈቱን መቀበል ግድ ይሆንበታል፡፡ ለምን? ምክንያቱም፣ ያ ትንሽ ውሻ አካለ መጠን የደረሰ ሰው ላይ ኃይል ስለሌለው፡፡

በሌላ በኩል ደግሞ አንድ ተለቅ ያለ ድብ ሊያጠቃችሁ ከተነሣና እናንተ ግን ኃይለኛ መሣሪያ ከሌላችሁ ከባድ ችግር ይገጥማችኋል፡፡ ያ ድብ በቀላሉ ያሸንፋችኋል፤ በኋላም ይገድላችኋል፡፡

አሳምረን እንደምናውቀው በሚገባ እንድንጨርስ የማይፈልጉ ኃይሎች አሉ፡፡ ከእነርሱ ጋር በምንገጥመው ትግል የምናሸንፍበት ኃይል ያለን

መሆኑን የምናውቀው እንዴት ነው? እነዚህ ልዕለ ተፈጥሮአዊ ጠላቶችን ስንዋጋ እንደ ቡችላው ነው የምንሆነው ወይስ እንደ አደገኛው ድብ? መግዛት የሚያስችለን ኃይል ከየት ይመጣል?

መልሱ ሮሜ 5፥17 ውስጥ አለ፤ መግዛት የምንችለው ከእግዚአብሔር፣ ‹‹ከእግዚአብሔር የጸጋ ብዛት›› የተነሣ ነው (Extraordinary የተሰኘው መጽሐፌ ጸጋን በተመለከተ የተሟላና ሰፋ ያለ ገለጻ ያቀርባል፤ እዚህ ላይ የማቀርበው ግን ለአሁኑ ርዕሳችን በጣም አስፈላጊ የሆኑ ነጥቦችን ብቻ ነው)፡፡

## ትልቁ አለመግባበት

ብዙውን ጊዜ በክርስቲያኖች መካከል አለመግባባት የሚፈጠረው የእግዚአብሔርን፣ ‹‹ጸጋ ብዛት›› በሚመለከት ርዕሰ ጉዳይ ነው፡፡

2009 ዓ.ም ላይ አገልግሎታችን በመላው አሜሪካ ላሉ በሺዎች ለሚቆጠሩ ዳግም ለተወለዱ፣ መጽሐፍ ቅዱስን ለሚያምኑ፣ አዘውትረው ወደ ቤተ ክርስቲያን ለሚሄዱ፣ የተለያዩ ቤተ እምነት አባል በሆኑ ሰዎች ላይ ዳሰሳ ጥናት አድርጎ ነበር፡፡ ዳሰሳ ጥናቱ፣ ‹‹የእግዚአብሔርን ጸጋን በተመለከተ፣ ሦስት ወይም ከዚያ በላይ ገለጻ ወይም ትርጉም ስጥ›› የሚል ነበር፡፡ አብዛኞቹ መልስ ሰጪዎች የእግዚአብሔርን ጸጋ የገለጡት 1) ድነት የምናገኝበት 2) ያለ ልፋት የምናገኘው ስጦታ እና 3) የኃጢአት ይቅርታ የምንቀበልበት በማለት ነበር፡፡

የዳንነው በጸጋና በጸጋ ብቻ መሆኑን ክርስቲያኖች በማወቃቸው በጣም ደስ ይለኛል፡፡ በውሃ በመረጨት፣ የቤተ ክርስቲያን አባል በመሆን፣ ሃይማኖታዊ ሕግ በመጠበቅ፣ ወይም የመጥፎ ሥራችን ሚዛን እንዲያጋድል የሚያደርግ መልካም ነገር በማድረግ ድነት አይመጣም፡፡ ኤፌሶን 2፥8-9፣ ‹‹በእምነት፣ በጸጋ ድናችኃልና ይህም የእግዚአብሔር ስጦታ ነው እንጂ፣ ከእናንተ አይደለም፤ ማንም እንዳይመካ በሥራ አይደለም›› በማለት በግልጽ ያመለክታል፡፡ የእግዚአብሔር ጸጋ በኢየሱስ ክርስቶስና በቤዛነት ሥራው በማመን እንጂ፣ በልፋት የምናገኘው ወይም ለመልካም ሥራ የምንቀበለው ክፍያ አለመሆኑን ወንጌላውያን ክርስቲያኖች በሚገባ መረዳታቸውን ማወቅ በጣም ደስ ይላል፡፡

በጣም ያስተውላሉ፣ ብዙ ነገር ያውቃሉ፤ የምንላቸው ሰዎች በራሳቸው ጥረት በእግዚአብሔር ዘንድ ተቀባይነት ለማግኘት መሞከራቸው ያሳዝናል፡፡

በጣም ያስተውላሉ፣ ብዙ ነገር ያውቃሉ፤ የምንላቸው ሰዎች በራሳቸው ጥረት በእግዚአብሔር ዘንድ ተቀባይነት ለማግኘት

መሞከራቸው ያሳዝናል፡፡ ከእግዚአብሔር ጋር ያላቸውን ግንኙነት ለማስተካከል በራሳቸው ሥራ ወይም ጥሩ ፀባይ የሚተማመኑ ብዙ ሰዎች አውቃለሁ፡፡ ማኀበረ ሰቡ ስለ እናንተ የቱንም ያህል መልካም ቢናገር፣ ኤፌሶን 2፥8-9 በሰው ልጅ ላይ ሊመጣ ካለው ፍርድ በራሳችሁ ጥረት ማምለጥ እንደማትችሉ ነው ግልጽ የሚያደርገው፡፡ ድነት የሚገኘው በእምነት ብቻ ነው፤ ምክንያቱም በልጁ ሞትና ትንሣኤ በኩል የምናገኘውና የምንቀበለው የእግዚአብሔር ስጦታ በመሆኑ ነው፡፡

በሌላ በኩል ደግሞ የእግዚአብሔርን የዘላለም ድነት ስጦታ በእምነት የተቀበሉ፣ ቀጣይ ጸጋውን በራሳቸው ሥራ የሚያገኙ ይመስል ሲደክሙና ሲጥሩ መመልከትም እንዲሁ አሳዛኝ ነው፡፡ እነዚህ አማኞች የእግዚአብሔርን መልካም ነገር ለማግኘት ረዘም ያለ ሰዓት መጸለይ፣ አዘውትረው መጾም፣ ለሌሎች መልካም ማድረግና ተያያዥ ክርስቲያናዊ ተግባሮችን መፈጸም ያለባቸው ይመስላቸዋል፡፡ ሐዋርያው ጳውሎስ በዚህ ዐይነቱ የተሳሳተ አስተሳሰባቸው የገላትያን ክርስቲያኖች ገሥጸዋቸዋል፣ ‹‹በሕግ ለመጽደቅ የምትጥሩ፣ ከክርስቶስ ተለይታችኋል፤ ከጸጋ ርቃችኋል›› ይላቸዋል (ገላትያ 5፥4)፡፡ በዚህ ዘመን ብዙ ቀና ልብ ያላቸው ሰዎች፣ በእንዲህ ዐይነቱ ወጥመድ ውስጥ መውደቃቸው ያሳዝናል፡፡

የዳሰሳ ጥናቱ ክርስቲያኖች በአጠቃላይ ኃጢአታችን የሚሰረየው በእግዚአብሔር ጸጋ መሆኑን እንደሚያውቁ ያመለክታል፡፡ ኤፌሶን 1፥7 ይህን ድንቅ እውነት ያረጋግጣል፣ ‹‹በእርሱም እንደ እግዚአብሔር ጸጋ ባለ ጠግነት መጠን፣ በደሙ በተደረገ ቤዛነት የኃጢአትን ይቅርታ አገኘን፡፡›› ኃጢአታችንን ለዘላለም የሚያስተሰርይ ነጻ የእግዚአብሔር ስጦታ ነው፡፡ እግዚአብሔር ይመስገን! ስለሆነም አብዛኞቹ ክርስቲያኖች የእግዚአብሔር ጸጋ ድነትንም የሚጨምር መሆኑን፣ ነጻ ስጦታ መሆኑን፣ የኃጢአት ይቅርታ የሚገኝበት መሆኑን በተመለከተ የተደላደለ መሠረታዊ እውነቶች ላይ የተመሠረቱ ይመስላል፡፡ በዚህ አስፈላጊ እውነት ዙሪያ አጽንዖት በመስጠት የወንጌል አገልጋዮች መመስገን የሚገባው ሥራ የሠሩም ይመስላል፤ ይህን በተመለከተ እግዚአብሔርም ደስ የሚለው ይመስለኛል፡፡

የዳሰሳ ጥናቱ ግልጽ ያደረገው አሳዛኙ ነገር የመጣው ከዚህ በኋላ ነው፡፡ ‹‹ጸጋ፣ የእግዚአብሔር ማስቻል/ማብቃት ዐቅም መሆኑን የሚያምኑ ጥናቱ ከተደረገባቸው በሺዎች የሚቆጠሩ አማኞች መካከል ሁለት እጅ ብቻ ሆነው ተገኙ፡፡ ያም ሆኖ ግን ጸጋውን አስመልክቶ እግዚአብሔር የሚናገረው በዚህ መልኩ ነው፤ የሚከተለውን ጥቅስ ልብ አድርጋችሁ አንብቡ፤

> እርሱ ግን (ጌታ) ጸጋዬ ይበቃሃል፤ ኃይሌ ፍጹም የሚሆነው በድካም ጊዜ ነውና አለኝ (2 ቆሮንቶስ 12÷9)፡፡

ኢየሱስ የተናገራቸውን ሁሉ በቀይ ቀለም፣ ሌሎች የተናገሩት ሁሉ በጥቁር ቀለም በሚያቀርብ መጽሐፍ ቅዱስ ይህን ጥቅስ ብትመለከቱ በጥቁር አለመጻፉን ትመለከታላችሁ፤ የተጻፈው በቀይ ነው፡፡ ስለሆነም፣ ምንም እንኳ ይህን ቃል የተናገረ ሐዋርያው ጳውሎስ ቢሆንም፣ ቃሉ የእርሱ አልነበረም - በቀጥታ ከራሱ ከጌታ የመጣ ነበር፡፡ እግዚአብሔር ጸጋውን የሚገልጸው የሚያስችልና ብቃት የሚሰጥ አድርጐ ነው፡፡ ያም ሆኖ፣ በጥናቱ መሠረት ይህን የሚያውቁና የሚረዱ ሁለት እጅ ብቻ ነበሩ፡፡ (ትክክለኛው ቁጥር 1.9 ሲሆን፣ ይህ ማለት ከ100 አማኞች መካከል ከሁለት እጅ ያነሱ ነበሩ ማለት ነው! ሁሉን ቻዩ አባት የእርሱን ጸጋ፣ የሚያስችልና ብቃት የሚሰጥ በማለት ቢገልጸውም፣ ያንን የሚያውቁ ከ100 ሁለት ብቻ ናቸው፡፡ ምን ያህል አስደንጋጭ ነው!)፡፡

## ጸጋ የማስቻል፣ ብቁ የማድረግ ኃይል

2 ቆሮንቶስ 12÷9 ላይ ጥቅም ላይ በዋለበት መልኩ፣ ድካም የሚለው ቃል፣ ‹‹አለመቻል›› ማለት ነው፡፡ እግዚአብሔር፣ ‹‹ከችሎታህ በላይ ከሆነ ነገር ጋር ስትጋፈጥ የእኔ ጸጋ (ኃይል) የማስቻል ዐቅም አለው›› እያለ ነው፡፡ ይህም የመቄዶንያ አማኞችን በተመለከተ ጳውሎስ ከሰጠው አስተያየት ግልጽ ሆኗል፣ ‹‹እግዚአብሔር በመቄዶንያ ላሉት አብያተ ክርስቲያናት የሰጠውን ጸጋ እንድታውቁ እንፈልጋለን. . . እንደ ዐቅማቸው ብቻ ሳይሆን፣ ከዐቅማቸው በላይ በፈቃዳቸው እንደ ሰጡ እንመሰክርላቸዋለን›› (2 ቆሮንቶስ 8÷1፡3)፡፡ እግዚአብሔር የመቄዶንያ ክርስቲያኖችን ከዐቅማቸው ያለፈ ነገር ለማድረግ አስቻላቸው፡፡ ያ ጸጋ ነው - የእግዚአብሔር ማስቻል/ብቁ የማድረግ ኃይል ነው፡፡

ቀደም ሲል፣ ‹‹ከእናንተ ጋር ባለን ግንኙነት ከእግዚአብሔር በሆነ ቅድስናና ቅንነት እንደ ኖርን. . . ይህም በሰው ጥበብ ሳይሆን በእግዚአብሔር ጸጋ ነው›› በማለት ጳውሎስ ለእነዚሁ ወገኖች ጽፎላቸው ነበር፡፡ እዚህም ላይ ጸጋ፣ የእግዚአብሔር ማስቻል ወይም ዐቅም እንደ ሆነ ነው የተመለከተው፡፡

ጴጥሮስም የእግዚአብሔርን ጸጋ በተመሳሳይ መንገድ ገልጾታል፡፡ ‹‹ጸጋና ሰላም ይብዛላችሁ. . . በገዛ ክብሩና በበጐነቱ የጠራንን እርሱን በማወቅ ለሕይወትና ለእውነተኛ መንፈሳዊነት የሚያስፈልገንን ሁሉ የመለኮቱ ኃይል (ጸጋው) ሰጥቶናል›› (2 ጴጥሮስ 1÷2-3)፡፡ እንደ ገና ጸጋ፣

‹‹የመለኮት ኃይል›› ተብሏል፡፡ እግዚአብሔር እንደሚፈልገው ለመኖር የሚያስችለንን ሁሉ በእምነት በተቀበልነው ጸጋ ብርታት እናገኛለን እያለ ነው ጴጥሮስ፡፡

እስቲ አሁን ደግሞ ግሪኩ ምን እንደሚል በመጠኑ ሰፋ አድርገን እንይ፡፡ ጸጋ ለሚለው አዲስ ኪዳን ውስጥ ተደጋግሞ ጥቅም ላይ የዋለው ቃል ካሪስ *(Charis)* የሚለው ሲሆን፣ ስትሮንግ የሚሉት ሰው ያዘጋጀው ኤክዞስቲቭ ኮንኮርዳንስ ኦፍ ዘ ባይብል የተሰኘው ተወዳጅ ቃላት ማብራሪያ፣ ‹‹ስጦታ››፣ ‹‹ጥቅም››፣ ‹‹ሞገስ››፣ ‹‹ደግነት›› እና ‹‹ለጋስነት›› በማለት ይተረጉመዋል፡፡ እነዚህን ፍቺዎች ከሮሜ፣ ከገላትያ እና ከኤፌሶን መልእክት ከተመረጡ ጥቅሶች ጋር ብታያይዙዋቸው አብዛኞቹ ክርስቲያኖች በጣም የለመዱትን የጸጋ ገጽታዎች ታገኛላችሁ፡፡ ከላይ የተመለከትነው ሰው ግን፣ ጸጋን በተመለከተ የሚሰጠውን ገለጻ በመቀጠል፣ ‹‹ልብ ውስጥ የሚፈጸም፣ እንዲሁም በሕይወት የሚንጸባረቅ መለኮታዊ ተፅዕኖ›› ይላል፡፡

ከዚህ ገለጻ ልብ ውስጥ የተደረገው ውጫዊ መገለጫ መኖሩንና ይህም የጸጋ የማስቻል ዐቅም መሆኑን በጉልህ ማየት ይቻላል፡፡ በርናባስ ወደ አንጾኪያ ቤተ ክርስቲያን በሄደ ጊዜ፣ ‹‹እግዚአብሔር በጸጋው የሠራውን ባዬ ጊዜ ደስ›› እንዳለው መጽሐፍ ቅዱስ ይነግረናል (ሐዋርያት ሥራ 11፥23)፡፡ ስለ ጸጋ አልሰማም፤ ይልቁንም የጸጋ ሥራ ማስረጃ የሆነ ነገር አዬ፡፡ ልባቸው ውስጥ የነበረው ጸጋ ተገልጦ፣ በሕዝቡ አኗኗር ላይ ሲንጸባረቅ አዬ፡፡

ያዕቆብ ‹‹እምነትህን (ጸጋህን) ከሥራ ለይተህ አሳየኝ፤ እኔም እምነቴን (ጸጋዬን) በሥራዬ አሳይሃለሁ›› በማለት የጻፈው በዚህ ምክንያት ነው (ያዕቆብ 2፥18)፡፡ እምነት በሚለው ቃል ጐን በቅንፍ ጸጋ የሚለውን የጨመርኩት ወደ እግዚአብሔር ጸጋ የሚያደርሰን እምነት ስለ ሆነ ነው (ሮሜ 5፥2 ይመ)፡፡ ‹‹በእምነት አማካይነት በእርግጥ ጸጋ ተቀብላችሁ ከሆነ፣ ያንን በእውነት የሚያሳይ ኃይል ወይም የእግዚአብሔር የማስቻል ዐቅም›› አሳየኝ እያለ ነው ያዕቆብ፡፡

በዞንዴርቫን የተዘጋጀው የመጽሐፍ ቅዱስ ቃላት መድበል፣ ጸጋ (ካሪስ) የሚለውን ቃል፣ ‹‹ይህ ጸጋ የሚሠራና የሚንቀሳቀስ ነው፤ እኛን በማጽደቅና ከእግዚአብሔር ጋር ያለንን ግንኙነት በማስተካከል ብቻ አይወሰንም፡፡ ጸጋ፣ የሕይወት ልምምዳችንም ላይ ተፅዕኖ ይኖረዋል፡፡ ምንጊዜም ቢሆን ጸጋ ድካማችንን ለማሸነፍ የሚያስችል የእግዚአብሔር ሥራ ነው›› በማለት ይገልጸዋል፡፡

ስለ ጸጋ የሚናገር ማንኛውንም የአዲስ ኪዳን ጥቅስ በጥንቃቄ ካነበብሁ በኃላ፣ ማግኘት የቻልኩትን የግሪክ መዝገበ ቃላት ለሰዓቶች ያህል ካጠናሁ በኃላ፣ የጠለቀ ግሪክኛ ዕውቀት ካላቸው ግለ ሰቦች ጋር ከተነጋገርኩ በኃላ፣ ጸጋን በተመለከተ የደረስኩበት የግሌ አጭር ገለጻ፣

> ጸጋ ከተፈጥሮአዊ ችሎታችን በላይ ርቀን መሄድ የሚያስችለን ነጻ የእግዚአብሔር ማስቻል/ብቁ የማድረግ ዐቅም ነው - የሚል ሆኗል፡፡

## ለምን አሳዛኝ ሆነ?

ከአብዛኞቹ ክርስቲያኖች መካከል የእግዚአብሔርን ጸጋ፣ የማስቻል/ብቁ የማድረግ ዐቅም የተረዱ ከመቶ ሁለት ብቻ መሆናቸው አሳዛኝ የሆነው ለምንድነው? እስቲ አንድ ምሳሌ በማቅረብ ማስረዳት ልሞክር፡፡

በአንድ ወቅት ባደረግነው ጥናት፣ በአፍሪካ ምድር ወገብ አካባቢ ከዘመኑ ሥልጣኔ በጣም ርቀው ጫካ ውስጥ የሚኖሩ ጐሳዎች አግኝተን ነበር፡፡ እነዚህ ሰዎች ለመጠጥ የሚሆን ውሃ ለማግኘት በየቀኑ ሁለት ኪሎ ሜትር ያህል በእግራቸው መሄድ ነበረባቸው፡፡ ከዚያም ያንን ንጹሕ የመጠጥ ውሃ በሸክም ለቤተ ሰባቸው ያደርሱ ነበር፡፡

ምግባቸውን በተመለከተም የዱር እንስሳ ማደንና አንዳንዴ ያንን ያደኑትን እንስሳ ወደ ቤታቸው ለመውሰድ ከስምንት እስከ ዐሥር ኪሎ ሜትር ያህል ተሸክመው ይሄዱ ነበር፡፡

የሚያስፈልጋቸውን ነገር በአካባቢያቸው ካላገኙ ሰላሣ አምስት ኪሎ ሜትር ያህል ተጉዘው ይገዙና ያንኑ ያህል ርቀት ተጉዘው ቤታቸው ይደርሱ ነበር፡፡

ይህን ችግራቸውን ከተረዳን በኃላ አንድ ነገር ልንሰጣቸው ፈለግን፡፡ አዎን፣ ችሮታና ልግስና ልናደርግላቸው፣ ጥቅም ያለው ነገር (እነዚህ ነገሮች ስትሮንግ የተሰኘው ጸሐፊ ጸጋ ለሚለው ቃል የሰጠው ትርጒም ናቸው) ልንሰጣቸው ፈልገናል፡፡ አዲስ ላንድ ሮቨር መኪና ገዝተን ልንሰጣቸው ነበር የወሰንነው፡፡

መኪናውን ገዝተን በመርከብ ወደ አፍሪካ ጠረፍ አደረስን፣ ከዚያም ራሳችን እየነዳን ሰዎቹ ወዳሉበት አካባቢ ወሰድነው፡፡ በአቅራቢያው ባለው ሜዳ ላይ ካቆምነው በኃላ ወደ መንደሩ ሄደን የጐሳ መሪውን አገኘነው፣

ከዚያም መኪናውን ወዳቆምንበት ቦታ ወሰድነው፡፡ በደስታ እየተፍለቀለቅን፣ ‹‹ይኼ ለእናንተ ያመጣነው ስጦታ ነው!›› በማለት ነገርነው፡፡

የጎሳው መሪ ወደ መኪናው ገብቶ ጋቢና ውስጥ እንዲቀመጥ አደረግን፡፡ አንድ ሰው ሞተሩን አስነሥቶ እየነዳ፣ ‹‹ክቡር ሆይ፣ ይህ ላንድ ሮቨር በጣም ድንቅ ነገር ነው! መኪናው አየር መቆጣጠሪያ አለው! ለምሳሌ ውጪ 108 ዲግሪ ፋረንሃይት ከሆነ፣ ማድረግ ያለብህ ይህን ቁልፍ እያዞርክ 72 ላይ ማድረግ ነው፤ ያኔ ውጪ ያለው አየር የቱንም ያህል ቢሆን፣ መኪናው ውስጥ 72 ዲግሪ ይሆናል›› አልነው፡፡

በመቀጠልም፣ ‹‹አየህ፣ ይህ መኪና ማሞቂያም አለው፡፡ ስለዚህ ውጪ ያለው አየር በጣም ቀዝቃዛ ከሆነ፣ አንተ ማድረግ ያለብህ ይህን ቁልፍ እያዞርክ 75 ላይ ማድረግ ነው፤ ውጪ ያለው አየር ከ40 ዲግሪ በታች ቢሆን እንኳ፣ የመኪናው ውስጥ አየር ግን 75 ዲግሪ ይሆናል፡፡

‹‹ይህ መኪና ሳተላይት ሬድዮም አለው፡፡ እዚህ መኪና ውስጥ ሆነህ በዓለም ያሉ ሬዲዮ ጣቢያዎችን በሙሉ በቀጥታ ማድመጥ ትችላለህ›› አልነው – የጎሳ መሪው በጣም ተገረመ፡፡

‹‹ግን'ኮ ይኸ ብቻ አይደለም›› በማለት ቀጠልን፡፡ ይህ መኪና ዲቪዲ ማጫወቻም አለው›› እንዱን ዲቪዲ እያጫወትን አሳየነው፡፡ የጎሳ መሪው መገረም መግለጽ ከሚችለው በላይ ነበር፡፡

‹‹መች በዚህ ብቻ ያበቃና፣ ይህ መኪና ሲዲ ማጫወቻም አለው›› አንዱን ሲዲ ከፍተን በጣም ደስ የሚል የአምልኮ መዝሙር አሰማነው፡፡

በመጨረሻ ከመኪናው ስንወጣ፣ የጎሳ መሪው፣ ‹‹ታዲያ፣ ለዚህ ድንቅ ስጦታ ምንድነው የምንከፍላችሁ››? በማለት ጠየቀ፡፡

‹‹ምንም እንዲከፈለን አንፈልግም፡፡ ለአንተና ለሕዝብህ በነጻ የምንሰጠው ነው፡፡ ሁላችሁንም በጣም እንወዳችኃለን!›› በማለት እርግጡን ነገርነው፡፡

መሪውና ሕዝቡ በጣም አመሰገኑን፡፡ እኛም ወደ መጣንበት ተመለስን፡፡ ከጥቂት ወሮች በኃላ ግን እነዚያ ሰዎች ውሃ ለማምጣት አሁንም በቀን አራት ኪሎ ሜትር በእግራቸው እየተጓዙ መሆኑን ሰማን፡፡ አሁንም ቢሆን ያደኑትን እንስሳ ተሸክመው ወደ ሰፈራቸው ለማድረስ እንደ ቀድሞው ሰላሣ አምስት ኪሎ ሜትር በእግራቸው እየተጓዙ ነበር፡፡ ለምን? ምክንያቱም፣ የመኪና ዋናው አገልግሎት መጓጓዣ መሆኑን ሳንነግራቸው በመቅረታችን ነው፡፡ ስለ መኪናው ብዙ ዝርዝር ነገሮች ለመሪው ነግረነዋል፤

መኪናው ወደ ፈለጉት ቦታ እንደሚወስዳቸውና ሸክማቸውን እንደሚሸከምላቸው ግን አልነገርናቸውም፤ በመሠረቱ የመኪና ዋናው አገልግሎትም ይኸው ነበር፡፡

በተመሳሳይ መልኩ፣ ብዙ ክርስቲያን አገልጋዮች የእግዚአብሔር ጸጋ ዋና ሥራ ማስቻል/ብቁ ማድረግ መሆኑን ለክርስቲያኑ ማኅበረ ሰብ መናገርን ዘንግተዋል፡፡

## ዋነኛ ተግባርን በተመለከተ

‹‹የእግዚአብሔር ጸጋ ዋነኛ ተግባር ማስቻል/ብቁ ማድረግ ነው›› ብለሃል ለመሆኑ፣ እንዴት እንዲህ ለማለት ደፈርክ?›› በማለት ትጠይቁኝ ይሆናል፡፡

በቅርቡ ጸሎት ላይ እያለሁ፣ ‹‹ልጄ፣ አዲስ ኪዳን ውስጥ ጸጋን በእንዴት ዐይነት ሁኔታ ነበር ያስተዋወቅሁት?›› በማለት ጌታ በጥልቅ ማሰብ የሚያስፈልገው ጥያቄ አቀረበልኝ፡፡ ከዐሥራ ሁለት በላይ መጻሕፍት የጻፍኩ ሰው እንደ መሆኔ መጠን ጥያቄው ለእኔ የተለየ ትርጉም ነበረው፡፡ አንድ አዲስ ቃል የምጠቀም ከሆነና፣ ያንን ቃል ብዙዎች በሚገባ ላይረዱት እንደሚችሉ ከጠረጠርኩ ምን ማለት እንደ ሆነ ዋነኛውን ትርጉም የመግለጽ ልማድ አለኝ፡፡ በኋላም መጽሐፉ ውስጥ፣ ሁለተኛና ሦስተኛ ትርጉሙን እሰጣለሁ፤ ይሁን እንጂ፣ መጀመሪያ ላይ ዋናውን ትርጉም መስጠት በጣም ወሳኝ ነው፡፡

ለምሳሌ ያህል ላንድ ሮቨሩን (መኪናውን) አስመልክቶ ለመሪው ለመግለጽ ደብዳቤ መጻፍ ካለብኝ፣ መጀመሪያው አንቀጽ ላይ የሚከተለውን ዐይነት ማብራሪያ መጻፍ አለብኝ፣

> *የተከበሩ የጐሳ መሪ፣ አንድ አዲስ መኪና ልንሰጣችሁ ነው፡፡ የመኪናው ዋና ተግባር በመጓጓዣነት ማገልገል ነው፡፡ ከእንግዲህ ውሃ ተሸክማችሁ በየቀኑ ረጅም ኪሎ ሜትር መጓዝ የለባችሁም፤ ከእናንተ አንዱ መኪናውን እየነዳ ሄዶ ውሃውን ይዞ መመለስ ይችላል፡፡ በአደን የገደላችሁትን እንስሳ ወደ ሰፈራችሁ ለማድረስ ያን ያህል ርቀት በሸክም መድከም የለባችሁም፤ ከእናንተ አንዱ መኪናውን እየነዳ ሄዶ ማምጣት ይችላል፡፡ አስፈላጊ ነገሮችን ለመግዛትም ቢሆን ሰላሣ አምስት ኪሎ ሜትር አቅራቢያችሁ ወዳለው መንደር በእግራችሁ መሄድና መመለስ የለባችሁም፤ የሰጠናችሁ መኪና ከዚህ ሁሉ ውጣ ውረድ ያሳርፋችኋል፡፡*

በመጀመሪያ የመኪናውን ዋነኛ ዓላማ ማስረዳት ያስፈልጋል፤ ምክንያቱም፣ መሪውም ሆነ ሕዝቡ ከዚያ በፊት መኪና አይተው አያውቁም፡፡

በደብዳቤው ሁለተኛ አንቀጽ፣ ምናልባት ስለ አየር ማሞቂያውና ማቀዝቀዣው መግለጽ ያስፈልግ ይሆናል፡፡ ሦስተኛው አንቀጽ ላይ ስለ ሳተላይት ሬዲዮው፣ አራተኛው አንቀጽ ላይ ስለ ዲቪዲና ሲዲ ማጫወቻው እነግራቸዋለሁ፡፡ ከዚያም ይህ ሁሉ ነጻ ስጦታ መሆኑን በመግለጽ ደብዳቤውን እደመድማለሁ፡፡ የመኪናው ዋነኛ ተግባር መጓጓዣ መሆኑን ግን፣ የደብዳቤው መጀመሪያ አንቀጽ ላይ በሚገባ ማስረዳት ይኖርብኛል፡፡

እንግዲህ ይህን በአእምሮአችን በመያዝ፣ - አዲስ ኪዳን ውስጥ ጸጋን በእንዴት ዐይነት ሁኔታ ነበር ያስተዋወቁት? በማለት ጌታ አቅርቦልኝ ወደ ነበረው ጥያቄ እንመለስ፡፡

በወቅቱ የሰጠሁት መልስ፣ ‹‹አላውቅም›› የሚል ነበር፡፡ በኃላ ግን ኮምፒዩተሬ ውስጥ ያለውን የመጽሐፍ ቅዱስ መዝገበ ቃላት በመክፈት፣ አዲስ ኪዳን እግዚአብሔር ጸጋን ያስተዋወቀው በእንዴት ዐይነት ሁኔታ እንደ ነበር ማጥናት ጀመርኩ፡፡ ለምሳሌ ዮሐንስ 1፥16 ላይ፣ ‹‹ከእርሱ (ኢየሱስ) ሙላት ሁላችንም በጸጋ ላይ ጸጋ ተቀብለናል›› ይላል፡፡

ዮሐንስ፣ ‹‹በጸጋ ላይ ጸጋ›› ማለቱን እናስተውል፡፡ በአቴንስ የሚኖር ግሪካዊ ጓደኛ አለኝ፡፡ ግሪክኛን እንደ መጀመሪያ ቋንቋው የሚናገር አገልጋይ ብቻ ሳይሆን፣ ጥንታዊ ግሪክኛንም ጭምር ያጠና ሰው ነበር፡፡ ግሪክኛ ቋንቋን በተመለከተ መረዳት የምፈልገው ነገር ካለ፣ ብዙ ጊዜ ይህን ሰው ነበር የምጠይቀው፡፡ እዚህ ላይ ዮሐንስ እየተናገረ ያለው እግዚአብሔር፣ ‹‹የጸጋን ብዛት፣ ባለ ጠግነት›› እንደ ሰጠን መሆኑን አስረዳኝ፡፡ በሌላ አነጋገር ሐዋርያው የሚያመለክተው ያ ጸጋ ያደረገው ሙላት - ያ ጸጋ ያደረገው ብዛት፣ ለእኛ የኢየሱስ ክርስቶስን ሙላት መስጠት መሆኑን ነው! በደንብ ሰማችሁ? የራሱ የኢየሱስ ክርስቶስን ሙላት! ያ ደግሞ የሚያመለክተው ማስቻልና ዐቅም የመሆን ኃይልን ነው፡፡

ይህን በሚገባ መረዳታችሁን ማረጋገጥ እፈልጋለሁ፡፡ ለምሳሌ ያህል ወደ አንድ በሰፈሩ ባለ ቡድን ውስጥ ሲ ደረጃ ላይ ወዳለ ቴኒስ ተጫዋች ሄጄ፣ ‹‹በአሁኑ ዘመን'ኮ የሮጀር ፌደርን ሙላት – ማለትም ሙሉ ችሎታ የሚሰጥህ ሳይንሳዊ ዘዴ ተግባር ላይ ውሏል›› አልኩት እንበል (ፌደር በዚህ ስፖርት ታዋቂ የዓለማችን ሰዎች መካከል አንዱ ነው)፡፡ ያ ሰው ምን የሚል ይመስላችኃል? ‹‹እባክህን ያንን ዘዴ አሁኑኑ ስጠኝ!›› ነው የሚለው፡፡ የሮጀር ፌደርን ሙላት ከሰጠነውስ ምን ይሆናል? የቡድኑ ሻምፒዮን ይሆናል፣ ከዚያ

ወደ ብሔራዊ ደረጃ ይሻገራል፤ ከዚያ በዓለም አቀፍ ደረጃ ታዋቂ ቴኒስ ኳስ ተጫዋች ይሆናል፡፡

አንድ የመጀመሪያ ዓመት ሥነ ሕንፃ ተማሪን፣ ‹‹በአሁኑ ዘመን'ኮ የፍራንክ ሎይድን ሙሉነት – ማለትም ሙሉ ችሎታ የሚያጐናጽፍህ ሳይንሳዊ ዘዴ ተገኝቷል›› ብለው ያ ተማሪ ምን የሚል ይመስላችኋል? ‹‹አሁኑኑ ስጠኝ›› ይለኛል፡፡ እንዴ ያንን ካገኘ ተማሪው ትምህርቱን ይተውና ከፍ ያለ ሽልማት ወደሚያሰጠው ሙያ ይገባል፡፡

ይህን በሚገባ ውስጣችሁ ለማኖር አንድ ሌላ ተጨማሪ ምሳሌ ላቅርብ፡፡ ወደ አንድ ተራ የቢዝነስ ሰው ሂጄ፣ ‹‹በአሁኑ ዘመን'ኮ የቢል ጌትስን ሙሉነት – ማለትም ሙሉ ችሎታ የሚያሰጥህ ሳይንሳዊ ዘዴ ተገኝቷል›› ብለው ያ የቢዝነስ ሰው ምን የሚል ይመስላችኋል? ‹‹እባክህን አሁኑኑ ስጠኝ!›› ይላል፡፡ የቢል ጌትስን ሙሉ ችሎታ ካገኘ በኋላስ? አዳዲስ ውጤቶች ሊያስገኝለት በሚችል መንገድ ማሰብ ይጀምራል፤ ከዚያ በፊት አስቦ ወደማያውቀው ፈጠራ ይገባል፡፡

ጸጋ የሰጠን ከላይ የተመለከትናቸውን ሰዎች ሙላት የአንዱንም እንኳ አይደለም፡፡ ያ ለጸጋ በጣም ትንሽ ይሆንበታል፡፡ የእግዚአብሔር ጸጋ የሰጠን የራሱ የኢየሱስ ክርስቶስን ሙላት ነው፡፡ የእርሱን ችሎታ ነው! የእርሱን ኃይል ነው! ይህን መረዳት ትችላላችሁ?

ስለሆነም፣ ምንም እንኳ ነጻ የእርሱ ስጦታ በመሆኑ እግዚአብሔርን እጅግ ማመስገን ቢኖርብንም፣ በአዲስ ኪዳን እግዚአብሔር በመጀመሪያ ጸጋን ያስተዋወቀው በነጻ ስጦታነቱ አይደለም፡፡ ምንም እንኳ የእርሱ ጸጋ ኃጢአታችንን በመውሰዱ እጅግ ማመስገን ቢኖርብንም፣ እግዚአብሔር መጀመሪያ ላይ ጸጋን ያስተዋወቀው የኃጢአታችን ስርየት መሆኑን አልነበረም፡፡ ጸጋን ያስተዋወቀው የኢየሱስ ክርስቶስን ሙላት እንደሚሰጠን ብቁ የማድረግ የማስቻል ዐቅም ነበር፡፡

የእግዚአብሔር ጸጋ የራሱ የኢየሱስ ክርስቶስን ሙላት ሰጥቶናል!

ካለፈው ምዕራፍ እንደምታስታውሱት እግዚአብሔር፣ ‹‹ከመለኮታዊ ባሕርይ ተካፋዮች›› እንዳደረገን ጴጥሮስ ጽፎአል (2 ጴጥሮስ 1፥2-4)፡፡ ባሕርይ የአንድን ሰው ወሳኝ ማንነት ወይም ፀባይ ይገልጻል፡፡ ስለሆነም የእግዚአብሔር ጸጋ የራሱ የኢየሱስ ክርስቶስን ወሳኝ ማንነትና ፀባይ በሙላት ይሰጠናል ማለት ነው! ‹‹በዚህም ዓለም እርሱን እንመስላለንና››

በማለት ዮሐንስ የጻፈው በዚህ ምክንያት ነበር (1 ዮሐንስ 4፥17)፡፡ የዚህን ቃል ስፋትና ጥልቀት ማሰብ ትችላላችሁ?

እንግዲህ በሕይወት ላይ ለመንገሥ የሚረዳን ይህ የእግዚአብሔር የማስቻል/ብቁ የማድረግ ዐቅምና ኃይል ነው ማለት ነው! የእግዚአብሔር ጸጋ ኢየሱስን እንድንመስል እንደ ገና ፈጥሮናል፤ እርሱ እንደ ኖረ እንድንኖር ያስችለናል፡፡ በክርስቶስ ውስጥ ነን፡፡ የክርስቶስ አካል ነን፡፡ በዚህ ምድር እንደ እርሱ ነን፡፡ ክርስቲያኖች ነን፡፡ ‹‹ማንም በእርሱ እኖራለሁ የሚል፣ ኢየሱስ እንደ ተመላለሰ ሊመላለስ ይገባዋል›› በማለት ዮሐንስ በድፍረት የጻፈው ከዚህ የተነሣ ነበር (1 ዮሐንስ 2፥6)፡፡

ይህ ቃል ወደ ልባችሁ ጠልቆ ይግባ፤ ኢየሱስ በዚህ ምድር እንደ ኖረው መኖር አለብን፡፡ ይህ የመጽሐፍ ቅዱስ አስተያየት ሳይሆን፣ የመጽሐፍ ቅዱስ ትእዛዝ ነው!

# 4

# ኢየሱስ የተመላለሰው እንዴት እንደ ነበር

*ማንም በእርሱ እኖራሁ የሚል፣ ኢየሱስ እንደ ተመላለሰ ሊመላለስ ይገባዋል፡፡*

*1 ዮሐንስ 2፥6*

ኢየሱስ እንደ ተመላለሰ መመላለስ ከፈለግን፣ ‹‹ለመሆኑ፣ እርሱ እንዴት ነበር የተመላለሰው?›› ብለን መጠየቅ ይኖርብናል፡፡ በመጀመሪያ፣ በሚያስደንቅ መንፈሳዊነትና ንጽሕና ነበር የተመላለሰው፡፡ የዚህ ዓለም ፍቅር አልገዛውም፤ እርሱ ያልተለመዱና መንፈሳዊ ያልሆኑ ምኞቶችን ገዛ፡፡ በተመሳሳይ ሁኔታ ሐዋርያው ጳውሎስ በእግዚአብሔር ዘንድ ተቀባይነት ስላለው አገልግሎት ይነግረናል፣

*ሥጋንና መንፈስን ከሚያረክስ ነገር ሁሉ ራሳችንን እናንጻ፣...* ቅድስናችንንም ፍጹም እናድርገው (2 ቆሮንቶስ 7፥1)

‹‹ራሳችንን እናንጻ›› የሚለውን ቃል ልብ አደረጋችሁ? ‹‹እግዚአብሔር ያነጻችኋል›› አለማለቱ በጣም የሚገርም ነው፡፡ እስቲ ግልጽ ላድርገው፡፡ የኢየሱስ ደም ከኃጢአት ሁሉ ያነጻናል – ይህ በእርሱ መዋጀታችን ያስገኘልን ጥቅም ነው፡፡ ይሁን እንጂ፣ እዚህ ላይ ሐዋርያው እየተናገረ ያለው እኛ ራሳችንን እንድናነጻ ነው፣ በሌላ አነጋገር ቀድሞውኑ በነጻ በተደረገልን እንድንኖር ነው፡፡ እንደ አማኞች ከእኛ የሚጠበቀውን አኗኗር ነው የሚያመለክተው፡፡ የመዋጀታችን ውጤት ስለ ሆነው ውጫዊ ለውጥ ነው የሚናገረው፡፡

በዚያ ጥቅስ ውስጥ *ነገር ሁሉ* የሚለውንስ ቃል ልብ አደረጋችሁ? ሥጋንና መንፈስን ከሚያረክሱ አንዳንድ ነገሮች፣ ወይም ብዙ ነገሮች እንድንቀደስ ሳይሆን ከነገር ሁሉ ነው መቀደስ ያለብን፡፡ ቅድስናችንን ፍጹም ለማድረግ ራሳችን እንድናነጻ ይጠበቅብናል፡፡ ‹‹የጠራችሁ እርሱ ቅዱስ እንደ ሆነ እናንተም በኑሮአችሁ ሁሉ ቅዱሳን ሁሉ›› በማለት ጴጥሮስ

ይህን እውነት ያጸናል (1 ጴጥሮስ 1፥15)፡፡ እንግዲህ ምንም ሳንበራርዝ (አንዳንዶች እንደሚያስተምሩት) ይህን ቃል ከምራችን ከወሰድነው በእግዚአብሔር ዘንድ ተቀባይነት ያለው አገልግሎት ኢየሱስ በተመላለሰበት ዐይነት መንፈሳዊነት መመላለስ ይሆናል ማለት ነው፡፡ ለመሆኑ፣ ያንን የምናደርገው እንዴት ነው? በእግዚአብሔር ጸጋ አማካይነት፡፡

እስቲ ማብራሪያ ልስጥ፡፡ የሁለተኛ ደረጃ ተማሪ እያለሁ የባሰብኝ ኃጢአተኛ ነበርኩ፡፡ እንዲህ ስል ምን ማለቴ ነው? የነበረኝ ኃጢአት የማድረግ ባሕርይ ነበር ያንን የማደርገው ደግሞ ከልቤ ነበር፡፡

በዐሥራዎቹ ዓመቶቼ መጀመሪያዎቹ ላይ አባቴ በቻርለስተን ሔስተን መሪ ተዋንያነት የተሠራውን ዘ ቴን ኮማንድመንት የተሰኘ ፊልም እንድናይ እኔና ታናሽ እኅቴን ይዞን ይሄዳል፡፡

ፊልሙን በማየት ላይ እያለን ምድር ተከፍታ ዳታንንና በሙሴ ላይ ያመፁ ክፉ ጓደኞቹን ሁሉ ስትውጣቸው የሚታይበት ክፍል ይመጣል፡፡ በሕይወት እያሉ ምድር ተከፍታ ስትውጣቸው ሳይ ኃጢአተኝነቴ ተሰምቶኝ እንደ አንድ አእምሮውን እንደ ሳተ ሰው ንስሐ ማድረግ ጀመርኩ፡፡ ኃጢአቶቼን ሁሉ በመዘርዘር እግዚአብሔር ይቅር እንዲለኝ ለመንኩ፤ ከእንግዲህ ወዲያ ኃጢአት በዞረበት ላለመዞር ቃል ገባሁ፡፡ ከዚያ የፊልም አዳራሽ ፍጹም የተለወጠ ወጣት ሆኜ የወጣሁ መሰለኝ፡፡ ያ የቆየው ግን ለአንድ ሳምንት ብቻ ነበር፣ ከዚያ ወደ ቀድሞው ኃጢአት የማድረግ ሕይወቴ ተመለስኩ፡፡ ያ የሆነው ለምን ነበር? ምክንያቱም ንስሐ ቢኖረኝም፣ ጸጋ ግን ስላልነበረኝ ነበር፡፡

ከዓመታት በኃላ የኮሌጅ ተማሪ እያለሁ አንድ ሰው ግሬት ኮሚሽን የሚያዘጋጀውን አራቱ መንፈሳዊ ሕጎች ሰጠኝ፡፡ አራተኛውን ሕግ ካነበብኩ በኃላ ኢየሱስ ክርስቶስን ጌታዬና አዳኜ አድርጌ ተቀበልኩ፡፡ በዚያው ቅጽበት የእግዚአብሔር ልጅ ሆንኩ፡፡ ይሁን እንጂ፣ ክርስቶስን ከመቀበሌ በፊት አድርጋቸው የነበሩ አንዳንድ ኃጢአቶች እያደረግሁ ነበር፡፡ ይህ ሊሆን የቻለው ተገቢ ትምህርት ስላልተሰጠኝና የመጽሐፍ ቅዱስ ዕውቀት ስለ ጐደለኝ እንደ ነበር እረዳለሁ፤ ምክንያቱም ለእኔ ስለ ተዘጋጀው ኃጢአትን የማሸነፍ ኃይል ምንም የማውቀው አልነበረም፡፡

በዚህ ሁኔታ ጥቂት ዓመቶች አለፉ፡፡ አንድ ቀን ግን ከዚያ በፊት ብዙ ጊዜ ያነበብኩት አንድ ጥቅስ ከመጽሐፉ ገጽ ላይ ዘሎ የመጣ ይመስል ወደ ልቤ መጣ፡፡ ያ ጥቅስ፣ ‹‹. . . ለመቀደስም ፈልጉ፤ ያለ ቅድስና ማንም ጌታን ማየት አይችልም›› የሚለው ነበር (ዕብራውያን 12፥14)፡፡ ቃሉ በጣም

ነበር የነካኝ፡፡ እግዚአብሔርን ማየት እፈልጋለሁ፤ ይህ ጥቅስ ደግሞ ያንን ማድረግ ከፈለግሁ መቀደስ እንዳለብኝ ይናገራል! በጣም የሚያሳዝነው ግን ይህንንም ቢሆን በሚገባ አልተረዳሁም ነበር፤ እንዲያውም አጉል ሕግ አክራሪነት የሚያጠቃኝ ሰው ሆንኩ፡፡ ሕግና ወግን መሠረት ያደረገ ምክንያት እየደረደርኩ በዙሪያዬ ያሉትን ሰዎች መንደፍ ጀመርኩ፡፡ ‹‹የተቀደሰ ሕይወት›› እንዲኖሩ እነግራቸዋለሁ፣ ያን ለማድረግ የሚያስችላቸውን ኃይል ግን ላመለክታቸው አልቻልኩም፡፡ ቅድስና የሰው ጥረትና ሙከራ ውጤት ይመስለኝ ነበር፤ ያንን የሚያደርግ የእግዚአብሔር ማስቻል/ማብቃት ዐቅም መሆኑ ገና አልተረዳሁም ነበር፡፡ በቃላት እየተናደፍኩ ሚስቴን፣ ጓደኞቼንና የሚቀርቡኝን ሰዎች ሁሉ ዕረፍት አሳጣሁዋቸው፡፡

አንድ ቀን እየጸለየኩ እያለ፣ ‹‹ቅድስና የአንተ ሥጋ ሥራ ሳይሆን፣ የእኔ ጸጋ ውጤት ነው›› በማለት ጌታ ተናገረኝ፡፡ ይኸው ነው! ያጣሁት ይህንኑ ነበር፡፡ ጸጋ በራሴ ጥረት ማድረግ የማልችለውን ማለትም ሥጋና መንፈስን ከሚያረክስ ነገር ሁሉ ራሴን ማንጻትና ሙሉ በሙሉ እንድቀደስ የሚረዳኝ የማስቻል/ብቃት የሚሰጥ ዐቅም መሆኑን ወደ መገንዘብ መጣሁ፡፡ ይህ ተቀባይነት ያለው እግዚአብሔርን የማገልገል መንገድ ነው፡፡ የዕብራውያን መልእክት ጸሐፊም፣

> እግዚአብሔርን ደስ እያሰኘን የምናመልክበትን ጸጋ እንያዝ (12፥28) የሚለው በዚህ ምክንያት ነው፡፡

ጸጋ እግዚአብሔርን ደስ በሚያሰኝ ሁኔታ እርሱን እንድናመልከው (እንድናገለግለው) ያስችለናል፤ በራሳችን ጥረት ማድረግ የማንችለውን ራሳችንን ለማንጻት ያበቃናል፡፡

ቀደም ሲል ከተመለከትነው ብሔራዊ የዳሰሳ ጥናት ከመቶ 98 እጅ ክርስቲያኖች በራሳቸው ችሎታ እግዚአብሔር ደስ የሚሰኝበትን ሕይወት መኖር እንደሚሞክሩ አይተናል፡፡ ጸጋ የእግዚአብሔር ማስቻል/ማብቃት ዐቅም መሆኑን የተረዱ 2 እጁ ብቻ ነበሩ፤ ይህ ማለት ደግሞ 98 እጁ ይህን የማስቻል/የማብቃት ዐቅም መለማለድ አይችሉም ማለት ነው፤ ምክንያቱም፣ በመጀመሪያ ደረጃ እንዲህ ያለ ነገር መኖሩን እንኳ አያውቁም፡፡ በእምነት ከእግዚአብሔር እንቀበላለን፤ በማናውቀው ነገር ደግሞ እምነት ሊኖረን አይችልም፡፡ ይህን አስመልክቶ ጳውሎስ፣ ‹‹ስለ እርሱስ ሳይሰሙ እንዴት ያምኑበታል?›› ይላል (ሮሜ 10፥14)፡፡ መጠቀም የምንችለው እንዳለን በምናውቀው ነገር ብቻ ነው፡፡

አንድ የአፍሪካ ጐሳን በተመለከተ አንሥተው ወደ ነበረው ምሳሌ ስንመለስ፣ የመኪና ዋነኛ ተግባር መጓጓዣነት መሆኑን ስላላወቁ ሊጠቀሙበት አልቻሉም ነበር፡፡ ውስጡ ገብተው መጨፈር ይችሉ ይሆናል፤ ዲቪዲውን ይመለከቱ፣ ሲዲውን ይሰሙ ይሆናል፤ ሬዲዮኑን ያዳምጡ ይሆናል፤ ይሁን እንጂ፣ መንዳቱን ጨርሶ አያስቡትም፡፡ ካልነዱትና ለመጓጓዣነት ካልተጠቀሙበት ደግሞ ዋነኛ ተግባሩን ዘንግተዋል ማለት ነው፡፡

በአንድ ወቅት አንድ ግሩም ካሜራ ገዝቼ ነበር፡፡ ፓኬቱን ከፈትኩ፣ ካሜራውን አወጣሁ፤ ወዲያውኑ በሌሎች ካሜራዎች አደርግ የነበረውን ሁሉ ማድረግ ጀመርኩ፤ ይህንንም ያንንም ፎቶ ማንሣት ጀመርኩ፤ አብዛኞቹ ሰዎች ካሜራ ሲገዙ የሚያደርጉትም ከዚህ ያለፈ እንዳይደለ አስባለሁ፡፡

አንድ ቀን ግን፣ ጓደኛዬ እንደሚያደርገው እኔም በካሜራዬ አስደናቂ ፎቶዎችን ማንሣት የማልችለው ለምንድነው? በማለት ራሴን ጠየቅሁ፡፡ የእኔ ካሜራ የጓደኛዬ ካሜራ ያለው ነገር ሁሉ ያለው መሆኑን ተረዳሁ፡፡ ካሜራውን ስገዛ አብሮት የነበረውን ጽሑፍ አውጥቼ በማንበብ በካሜራው ማድረግ የሚቻለውን ነገር ሁሉ አወቅሁ፡፡ ከዚያ በኃላም እኔም አስገራሚ ፎቶዎችን ማንሣት ቻልኩ፡፡ በእጄ ያለውን ባለማወቄ በሚገባ ሳልጠቀምበት መቅረቴ ገባኝ፡፡

ያልታደሉት 98 እጁ አማኞችን በተመለከተም ይህ እውነት ነው፡፡ ለእነርሱም ቢሆን የእግዚአብሔር ጸጋ ያዘጋጀላቸውን ከሕይወት መመሪያ ከመጽሐፍ ቅዱስ አንብበው አልተረዱም፡፡ ያላቸውን ባለማወቃቸው የውሱንነት ሕይወት ሲኖሩ ዘመናት አሳልፈዋል፡፡

በራሳችን ችሎታ የቅድስና ሕይወት ለመኖር ስንሞክር የሚሆነው ምንድን ነው? ከሁለት አንዱ ነገር ይሆናል - ግብዝ ሕግ አጥባቂዎች እንሆናለን (አንድን ነገር አስመልክቶ ጠንከር ያለ ዐቋም እንዳለን ብንናገርም፣ በግል ሕይወታችን ግን ከዚያ በሚቃረን ሁኔታ እንኖራለን) ወይም ደግሞ፣ ‹‹ጸጋ ማንኛውንም የማደርገውን ኃጢአት ይሸፍናል›› የሚል መጽሐፍ ቅዱሳዊ ያልሆነ እምነት እንኖራለን፡፡ ስለሆነም፣ እንደ ኢየሱስ መኖር ዐይነተኛ የሕይወት ግብ ቢሆንም፣ ከእውነታ የራቀና የማይቻል እንደ ሆነ እናስባለን፡፡

እንዲህ ያለውን አስተሳሰብ መሠረት በማድረግ አንዳንድ አማኞችና አስተማሪዎች፣ ‹‹የኢየሱስ ክርስቶስ ቤዛነት ሞት የእግዚአብሔር ልጆች አድርጎናል፤ ይሁን እንጂ፣ ሁላችንም ሰዎች በመሆናችን አሁንም ከኃጢአት

አልተላቀቅንም›› የሚል ጤናማ ያልሆነ አስተምህሮ አምጥተዋል፡፡ ገና በኃጢአት ውስጥ ካለው አብዛኛው የሰው ልጅ በተለየ ሁኔታ መኖር እንደማንችል እናስባለን፤ ስለሆነም ኃጥእ ለሆነ አኗኗራችን ሰበብና ሽፋን እንፈልግለታለን፡፡ ይህ ደግሞ ወደ ሰላማዊና የተረጋጋ ወደሚመስል ሐሰተኛ ሕይወት ይመራናል፡፡

ይህ በመሠረቱ የአዲስ ኪዳን ትምህርት አይደለም፡፡ የምሥራቹ ቃል ወይም ወንጌል ኢየሱስ ዋጋ የከፈለው ከኃጢአት ቅጣት ነጻ ሊያደርገን ብቻ ሳይሆን፣ ከኃጢአት ኃይል ነጻ ሊያደርገንም ጭምር እንደ ሆነ ነው የሚናገረው! ‹‹ከጸጋ በታች እንጂ፣ ከሕግ በታች ስላልሆናችሁ ኃጢአት አይገዛችሁምና›› በማለት ጳውሎስ ይህን ግልጽ ያደርገዋል (ሮሜ 6÷14)፡፡ ሕግ ሰዎች ኃጢአት እንዳይሠሩ ይከለክላል፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ ጸጋ በራሳችን ችሎታ መላቀቅ ካቃተን ኃይል ማለት ከኃጢአት ነጻ እንድንሆን ያስችለናል፡፡ ‹‹የተቀበላችሁትን የእግዚአብሔርን ጸጋ ከንቱ እንዳታደርጉ›› በማለት ጳውሎስ የቆሮንቶስ ክርስቲያኖችን የሚመክረው ከዚህ የተነሣ ነው (2 ቆሮንቶስ 6÷1)፡፡

ጳውሎስ እየተናገረ ያለው አብዛኞቹ የምዕራቡ ዓለም ቤተ ክርስቲያኖች የሚያስተምሩትን ጸጋ ከንቱ ስለ ማድረግ አይደለም፡፡ ያ ዐይነቱ ጸጋ፣ ‹‹መኖር እንደሚገባኝ እየኖርኩ እንዳልሆነ አውቃለሁ፤ ይሁን እንጂ፣ በእግዚአብሔር ጸጋ በመዳኔና በዚሁ ጸጋ በመሸፈኔ ምንም ችግር የለም፡፡›› የሚል ነው፡፡ እንዲያውም አንዳንዶች በጣም ርቀው በመሄድ፣ ‹‹ድነቴ የተመሠረተው ኢየሱስ ያደረገልኝ ላይ እንጂ፣ እኔ የማደርገው ላይ ባለ መሆኑ የፈለግሁትን ማድረግ እችላለሁ፡፡ በእግዚአብሔር ጸጋ ተሸፍኛለሁ›› በማለት ያስባሉ ወይም ይናገራሉ፡፡ እንዲህ ከሆነ ደግሞ፣ መንፈሳዊ ሕይወት እንዲኖሩ የሚወቅሳቸው ነገር አይኖርም ማለት ነው፡፡ ታዲያ፣ ከንቱ እንዳታደርጉ የሚለው ይህን ዐይነቱን ጸጋ ሊሆን ይችላል ብላችሁ ታስባላችሁ? ይህ አስተሳሰብ የእግዚአብሔርን ጸጋ ዓላማና ኃይል በተሳሳተ መንገድ የመረዳት ውጤት ነው፡፡

ይሁን እንጂ፣ ጸጋ በራሳችን ችሎታ ማድረግ የማንችለውን ማለትም ሥጋንና መንፈስን ከርኩሰት ማንጻትና ፍጹም መቀደስ የሚያስችለን የእግዚአብሔር ማስቻል/ማብቃት ዐቅም መሆኑን ከተረዳን ያንን ጸጋ እንዴት ከንቱ ማድረግ እንደሚቻል ይገባናል፡፡

እስቲ ከዐሥር ዓመት በኋላ ወደነዚያ ላንድ ሮቨሩን ሰጥተናቸው ወደ ነበሩ በአፍሪካ የሚኖሩ ሰዎች ተመልሰን ሄድን ብለን እናስብ፤ አሁንም መኪናው እዚያው እነበረበት ቦታ መሆኑን እናስብ፡፡ አቧራና ቆሻሻ

ሸፍኖታል፣ በመኪናው ዙሪያና መኪናው ላይ ሣር በቅሎአል፡፡ በብዙ ትግል በሩን ከፍተን ስንገባ፣ ርቀት ቆጣሪው የዛሬ ዐሥር ዓመት እነበረበት ላይ ነው፡፡ ታዲያ ይህን ስንመለከት፣ ‹‹ከዐሥር ዓመት በፊት በነጻ የሰጠናቸውን ነገር ከንቱ አድርገውታል›› ማለት ይበዛብናል?

እነዚህ ሰዎች ላንድ ሮቨሩን በነጻ ማግኘታቸውን አስመልክቶ ዘምረው ይሆናል፤ ወይም ስጦታውን በተመለከተ እርስ በርስ ሲነጋገሩ ከርመው ይሆናል፡፡ ይህ ሁሉ ግን ምንም አይረባቸውም፡፡ መኪናው ለታቀደለት ተቀዳሚ ዓላማ ተግባር ላይ ባለ መዋሉ ስጦታውን ከንቱ አድርገውታል!

በተመሳሳይ መንገድ ጳውሎስ አስደናቂው የእግዚአብሔርን ጸጋ ያስገኘልንን በረከትና ጥቅም እኔና እናንተን እንዲያመልጠን አይፈልግም፣

> የተቀበላችሁትን የእግዚአብሔርን ጸጋ ከንቱ እንዳታደርጉት. . . ሥጋንና መንፈስን ከሚያረክስ ነገር ሁሉ ራሳችንን እናንጻ፤ ቅድስናችንን ፍጹም እናድርገው – ይለናል (2 ቆሮንቶስ 6፥1፣7፥1)

ከዚህ በላይ እንዴት ግልጽ ሊሆን ይችላል? የእኔ ጥያቄ፣ ይህን በተመለከተ በየአብያተ ክርስቲያኖቻችን ለምን ትምህርት ሳይሰጥ ኖረ፣ ለምንስ ተገቢ አጽንዖት አልተሰጠውም? የሚል ነው፡፡

## ኢየሱስ የሰውን ልጅ መሻት አሟልቷል

ቀደም ሲል፣ ‹‹ማንም በእርሱ እኖራለሁ የሚል ኢየሱስ እንደ ተመላለሰ ሊመላለስ ይገባዋል›› የሚለውን መጽሐፍ ቅዱሳዊ ትእዛዝ ተመልክተን ነበር (1ዮሐንስ 2፥6)፡፡ እዚህ ላይ ይገባዋል የሚለውን ቃል ልብ አድርጉ፡፡ ይህ ቃል ትእዛዝ እንጂ፣ እንዲሁ አስተያየት ብቻ አይደለም፡፡ ኢየሱስ እንደ ተመላለሰ እንድንመላለስ እግዚአብሔር ይጠብቅብናል፡፡ ስለዚህም፣ ኢየሱስ የተመላለሰው እንዴት ነበር? ብለን እንጠይቅ፡፡

ኢየሱስ ለሰው ልጅ ችግር መፍትሔ መስጠቱ በወንጌሎቹ ግልጽ ሆኖአል፡፡ የታመሙትን ፈወሰ፣ የቆዳ ሕመም የነበረባቸውን አነጻ፣ ሰዎችን ከባርነት ቀንበር አዳነ፣ ማየት ያቃታቸውን ዐይኖች፣ መስማት የተሳናቸውን ጆሮዎች ከፈተ፣ ዲዳው እንዲናገር፣ ሽባው እንዲራመድ አደረገ፤ የተራቡትን ለመመገብ ምግቡ እንዲበረክት አደረገ፡፡ ሌላው ቀርቶ የሞተውን እንኳ አስነሣ፡፡ ከዚያም፣ ‹‹አብ እኔን እንደ ላከኝ እኔም እናንተን እልካችኃለሁ›› በማለት ተናገረን (ዮሐንስ 20፥21)፡፡

እንዲህ ያሉ ነገሮችን ማድረግ የምንችለው እንዴት ነው? በእግዚአብሔር ጸጋ ነጻ ስጦታ! መጽሐፍ ቅዱስ ስለ መጀመሪያዋ ቤተ ክርስቲያን ሲናገር፣ ‹‹ሐዋርያትም ስለ ጌታ ኢየሱስ ትንሣኤ በታላቅ ኃይል መመስከራቸውን ቀጠሉ፤ በሁላቸውም ላይ ታላቅ ጸጋ ነበር›› ይላል (ሐዋርያት ሥራ 4፥33)፡፡

ከጥቅሱ እንደ ተመለከትነው እግዚአብሔር ታላቅ ኃይልንና ታላቅ ጸጋን ያያያዘው ለምንድነው? ምክንያቱም ጸጋ የእግዚአብሔር ኃይል በመሆኑ ነው!

ምናልባትም፣ ይሀ'ኮ የሚናገረው ስለ ሐዋርያት ነው፤ እኔ ግን ሐዋርያ ወይም ፓስተር አይደለሁም ትሉኝ ይሆናል፡፡ እንደዚያ ከሆነ ስለ አንድ፣ ‹‹ተራ›› ሰው ልንገራችሁ፡፡ በኢየሩሳሌም ከተማ ምግብ የማደል ሥራ ይሠራ የነበረ እስጢፋኖስ የሚሉት ሰው ነበር፡፡ ሐዋርያ፣ ነቢይ፣ ወንጌላዊ፣ ፓስተር ወይም መምህር አልነበረም፡፡ ሥራው ላረጁ ሴቶች ምግብ ማደል ነበር፡፡ ይሁን እንጂ፣ መጽሐፍ ቅዱስ ስለ እርሱ ሲናገር፣ ‹‹እስጢፋኖስ ጸጋንና ኃይልን ተሞልቶ በሕዝቡ መካከል ድንቅ ነገሮችንና ታምራዊ ምልክቶችን ያደርግ ነበር›› ይላል (ሐዋርያት ሥራ 6፥8)፡፡

ሐዋርያ ወይም ፓስተር ካልሆነ እንዴት እነዚያን አስገራሚ ተአምራት ማድረግ ቻለ? በእግዚአብሔር ጸጋ ኃይል ነጻ በሆነው የጸጋ ስጦታ ኃይል፣ የሰው ልጅን ችግር ለመፍታት ኢየሱስ ያደረገውን እርሱም አደረገ፡፡

ይኸንኑ ነጻ ስጦታ ማንኛውም አማኝ መቀበል ይችላል፡፡ የእናንተ ነው፤ የእኔም ነው፡፡ ኢየሱስ፣ ‹‹ወደ ዓለም ሁሉ ሂዱ፤ ወንጌልንም ለፍጥረት ሁሉ ስበኩ፡፡ የሚያምኑትን እነዚህ ምልክቶች ይከተሏቸዋል፤ እጃቸውንም በሕመምተኞች ላይ ይጭናሉ፤ እነርሱም ይፈወሳሉ›› በማለት ያዘዘን በዚህ ምክንያት ነው (ማርቆስ 16፥15፣17-18)፡፡ ኢየሱስ፣ ‹‹ተአምራት የማድረግ ኃይል የሚሰጠው ለሐዋርያት ብቻ ነው›› አላለም፡፡ ‹‹ጸጋ (የእግዚአብሔር ልጆች የመሆን ሥልጣን) የሚሰጠው ለሐዋርያት ብቻ ነው›› አላለም፡፡ ይልቁንም፣ ‹‹ለተቀበሉትና በስሙ ላመኑት ሁሉ ግን፣ የእግዚአብሔር ልጆች የመሆንን መብት (ሥልጣን) ሰጣቸው›› ነው የሚለው (ዮሐንስ 1፥12)፡፡ ይህ መብት ያለን መሆኑን ማመን አይከብደንም አይደል? እንደዚያ ከሆነ፣ ኢየሱስ እንደ ተመላለሰ መመላለስ እንድንችል፣ ‹‹የሚያምኑትን (ሐዋርያት ብቻ ሳይሆኑ) እነዚህ ምልክቶች (ነጻ የጸጋ ስጦታ) ይከተሏቸዋል›› በማለት የነገረን ይኸው መጽሐፍ ቅዱስ ነው! በእግዚአብሔር ኃይል በሽታ ላይ፣ ደዌ

ላይ፣ እና እኛ ላይ፣ እንዲሁም የምንወዳቸው ሰዎች ላይ፣ ሕይወት በሚያመጣው ችግር ላይ መግዛት (መንገሥ) እንችላለን፡፡

## ጥበብ፣ ማስተዋል፣ ራእይ፣ ችግር ፈቺ፣ አዲስ ሐሳብ አፍላቂ

ኢየሱስ የተመላሰበት ሌላው ነገር ምን ነበር? በአስደናቂ ጥበብ፣ ማስተዋል፣ ራእይ፣ ችግር ፈቺ እና አዲስ ሐሳብ አፍላቂ በመሆን ነበር የተመላለሰው፡፡ ጥበቡ በጣም የተማሩትን ሰዎች እንኳ አስገርሟል፡፡ የኢየሱስ ጥበብ የመጣው ከየት ነበር?

> ‹‹ሕፃኑም (ኢየሱስ) እያደገና እየጠነከረ ሄደ፤ በጥበብ ተሞላ፤ የእግዚአብሔርም ጸጋ በእርሱ ላይ ነበረ›› (ሉቃስ 2፥40)፡፡

ኢየሱስ ልዩ ጥበብ ሊኖረው የቻለው በእግዚአብሔር ጸጋ ነበር፡፡

ይህ ደግሞ አንድ ጥሩ ጥያቄ እንድናነሣ ያደርገናል፡፡ እንግዲህ፣ የእግዚአብሔር ጸጋ የሚሰጠው ለኃጢአት ይቅር መባልና መንግሥተ ሰማይ ለመግባት ብቻ ከሆነ (ብዙ ክርስቲያኖች እንደ ተማሩት) ኢየሱስ ጸጋ ለምን ያስፈልገው ነበር? ምክንያቱም፣ እርሱ ኃጢአት አላደረገም፣ ይቅር መባልም አያስፈልገውም፡፡ ይሁን እንጂ፣ ምንም እንኳ ኢየሱስ የእግዚአብሔር ልጅ ቢሆንም፣ እንደ ሰው በዚህ ምድር መወለዱንና መኖሩን እናውቃለን፡፡ ከመለኮታዊና አምላክ ከመሆን መብቱ ራሱን ባዶ አደረገ (ፊልጵስዩስ 2፥7 ይመ.)፡፡ ስለሆነም በጥበብ፣ በማስተዋል፣ በራእይ፣ በችግር ፈቺነትና በአዲስ ሐሳብ አፍላቂነት መመላለስ የሚያስችለው የእግዚአብሔር ጸጋ አስፈለገው፤ እነዚህ ነገሮች በሕይወቱ ይታዩ ነበር፡፡

የጥበቡን ሐሳብ አፍላቂነት፣ ችግር ፈቺነትና ራእይ እወደዋለሁ፡፡ አንዲት ሴትን ሊገጥማት ከነበረ ሞት አድኖአል፡፡ ዮሐንስ 8 ለሃይማኖታችን ቅንዓት አለን የሚሉ ሰዎች አንዲት ሴት ስታመነዝር ይዘው እንደ ነበር ይነግረናል፡፡ እየጐተቱ ወደ ቤተ መቅደስ አደባባይ አምጥተው ኢየሱስ ፊት ጣሏት፡፡ (አብሯት ያመነዘረውን ወንድ ግን ለምን እንዳላመጡት ግልጽ አይደለም)፡፡ ‹‹ሙሴም እንደዚች ያሉ ሴቶች በድንጋይ እንዲወገሩ በሕግ አዞናል፤ አንተስ ምን ትላለህ?›› በማለት ጠየቁት፡፡

እንዲህ ያለ ሁኔታ ሲያጋጥም፣ ትልቅ ጥበብ ይጠይቃል፡፡ ኢየሱስ ጐንበስ ብሎ በጣቱ በምድር ላይ ይጽፍ ጀመር፡፡ (ምናልባት የሰዎቹን ድብቅ የሴት ወዳጆች ስም እየጻፈ ሳይሆን እንዳልቀረ አምናለሁ)፡፡ መወትወታቸውን በቀጠሉ ጊዜ፣ ጌታ ከሚጽፍበት ቀና ብሎ፣ ‹‹ከእናንተ

ኃጢአት የሌለበት እርሱ አስቀድሞ ድንጋይ ይወርውርባት›› አላቸው፡፡ ከዚያም እንደ ገናም ጐንበስ ብሎ በምድር ላይ መጻፉን ቀጠለ፡፡

እነዚያ ተመፃዳቂዎች በስሞቹ ዝርዝር ውስጥ ከእነርሱ ጋር ሲያመነዝሩ የነበሩ ሴቶችን ስም ተመልክተው ይሆናል፡፡ በዚህ ምክንያት ይሁን ወይም ደግሞ ኢየሱስ በተናገረው ቃል አፍረው፣ ሁሉም ይዘዋቸው የነበሩን ድንጋዮች እየጣሉ ወዲያውኑ ከአካባቢ ጠፉ፡፡ መጽሐፍ ቅዱስ፣ ‹‹ይህን እንደ ሰሙ፣ ከሽማግሌዎች ጀምሮ አንድ በአንድ ወጡ›› ይለናል (ዮሐንስ 8፥9)፡፡ ኢየሱስ ብቻ ከሴቲቱ ጋር ቀረ፡፡

ከዚያም ኢየሱስ ቀና ብሎ ሴትየዋን፣ ‹‹አንቺ ሴት፣ ሰዎቹ የት ሄዱ? የፈረዱብሽ የሉምን?›› በማለት ጠየቃት፡፡ ከሳሾቿ ሁሉ መሄዳቸውን ነገረችው፡፡ ኢየሱስም፣ ‹‹እኔም አልፈርድብሽም፤ በይ ሂጂ፤ ከእንግዲህ ግን ኃጢአት አትሥሪ አላት›› (ቁጥር 10-11)፡፡

የኢየሱስ ጥበብና አዲስ ሐሳብ አፍላቂነት ሕይወቷን አዳነ፡፡ ኢየሱስ ሴቲቱ ላይ አለመፍረዱን ልብ አድርጉ፡፡ ኃጢአት የሌለበት እርሱ ብቻ ነበር፤ ስለሆነም በዚያ ቅጽበት የምሕረት ቃል ተናገረ፡፡ በሕጉ መሠረት ይገባት የነበረውን ፍርድ አልተናገረም፡፡ ይሁን እንጂ፣ ‹‹ከእንግዲህ ኃጢአት አትሥሪ›› ብሏታል፡፡ አሁን ጸጋ ተናገረ፤ ጸጋ የማይገባንን ሲሰጠን፣ ምሕረት ግን የሚገባንን (ቅጣት) እንዳናገኝ ያደርጋል፡፡ ምሕረት ሴቲቱ ላይ አልፈረደም፤ የእግዚአብሔር ጸጋ ግን ከእንግዲህ ሂጂ፣ ለሞት የሚያበቃ አመንዝራነት ወጥመድ ውስጥ እንዳትወድቅ አስቻላት/አበቃት፡፡

ኢየሱስ ላይ የነበረው የእግዚአብሔር ጸጋ፣ ከሃይማኖት አክራሪዎች ፍርድ ሴትየዋን ነጻ የሚያደርግ ጥበብ ሰጠው፡፡ ጸጋ ምንኛ ብርቱ ነው!

አንድ ሌላ ቀን ደግሞ ኢየሱስ፣ ከዓሣ አጥማጆች ጋር በገሊላ ባሕር አጠገብ ነበር፤ እነዚያ ዓሣ አጥማጆች አንድ ዓሣ እንኳ ሳያጠምዱ የዋሉበት ቀን ነበር፡፡ አንድ ሱቅ ቢኖራችሁና ቀኑን ሙሉ ምንም ነገር ሳትሸጡ ብትውሉ ምን ይሰማችኃል? ያ ቀን ለእናንተ መጥፎ ቀን እንደ ነበር ይታሰባል፡፡ ሆኖም፣ ከኢየሱስ የወጣ አንድ የጥበብ ቃል ሁኔታውን በዕድሜ ዘመናቸው ሁሉ ዐይተው ወደማያውቁት ፍሬያማ ቀን ለወጠው! ኢየሱስ ዓሣ አጥማጅ አልነበረም፤ ግን ጸጋ ነበረው! ምንኛ ድንቅ ጥበብ፣ ምንኛ ድንቅ ኃይል! ሌላ ጊዜ ደግሞ ከጥበቡ የተነሣ አንዲት አህያ የት እንዳለች እንኳ አውቆ ነበር፡፡ አንድ ሌላ ጊዜ ደግሞ ቀረጥ የሚከፍለው አልነበረውም – ሄደ ዓሣ እንዲያጠምድ ለጴጥሮስ ነገረው፣ የዓሣውንም አፍ

ጸጋ ምንኛ ብርቱ ነው!

ሲከፍት የሚፈለገውን ያህል ሳንቲም እዚያ ውስጥ ተገኘ፡፡ ያ የጸጋ ሥራ ነበር፡፡

ኢየሱስ የነበረው ነገሮችን የማየት ዐቅም አስደናቂ ነበር፡፡ ሰይጣን ዐመፁን በይሁዳ በኩል ከመግለጹ በፊት ደቀ መዛሙርቱ መካከል ሤራ እየሸረበ እንደ ነበር አውቆ ነበር፡፡ ገና ዓይን ለዓይን ከመተያየታቸው በፊት እንኳ፣ ናትናኤል ተንኰል የሌለበት ሰው መሆኑን አውቆ ነበር፡፡

## ማኅበረ ሰብ መለወጥ

በአንድ በኩል በኢየሱስ ሕይወት የነበረ የእግዚአብሔር ጸጋ፣ የነበረበትን ማኅበረ ሰብ መለወጥ የሚችልበት ችሎታ ሰጥቶት ነበር ማለት ይቻላል፡፡ አንድ ቀን ቃና የሚባል አካባቢ ወደ ነበረ ሰርግ ቤት ሄዶ ነበር፡፡ ሰርግ ቀላል ነገር አይደለም፣ የሰፈሩ ሰው ሁሉ ይሳተፍበታል፡፡ ይኸኛው ሰርግ ግን አስደንጋጭ ሁኔታ የታየበት ነበር፤ ገና ሕዝቡ ተስተናግዶ ሳያበቃ ወይን ጠጅ አለቀባቸው፡፡ እነዚያ ቤተ ሰቦች ምን ያህል እንደሚያፍሩና እንደሚሳቀቁ ይታያችኃል? በኢየሱስ ሕይወት የነበረው የእግዚአብሔር ጸጋ ግን፣ ያንን ሰርግ የተዋጣለት ሰርግ አደረገው፡፡

ናይን በሚባል ከተማ አንዲት መበለት ነበረች፤ የነበራት አንድ ልጅ ሞቶባት ነበር፡፡ ከእንግዲህ የሚጠብቃት ቀሪ ዘመንዋን በሰዎች እየተረዳች መኖር ነበር፡፡ በኢየሱስ ሕይወት ከነበረው የእግዚአብሔር ጸጋ የተነሣ ግን ታሪክ ተለወጠ፤ ልጇ ከሞት ተነሣ (ሉቃስ 7፥11-15 ይመ)፡፡

ሌላ ሰፈር ውስጥ የታወቀ የወረበሎች ቡድን መሪ ነበር፡፡ ምናልባትም በዚህ ዘመን የማፊያዎች መሪ ልንለው እንችላለን፡፡ በኢየሱስ ሕይወት ከነበረው የእግዚአብሔር ጸጋ የተነሣ ዘኬዎስ ከእንግዲህ ከማንም ያለ አግባብ ገንዘብ እንደማይወስድ ቃል ገባ፤ ከእንግዲህ ማኅበረ ሰቡ ሀብታምና ለኑሮ የሚመች ይሆናል፡፡ ከእንግዲህ ሰዎች በዚያ ግብር ሰብሳቢ አይጭበረበሩም፡፡ ያም ብቻ አይደለም፣ ዘኬዎስ፣ ‹‹ያለኝን ግማሽ ለድኾች እሰጣለሁ›› አለ፡፡ በዚህም ምክንያት የማኅበረ ሰቡ ድኾች ይጠቀማሉ፡፡›› ግን እዚያም ላይ አላበቃም፤ ዘኬዎስ ያለ አግባብ የወሰደውን አራት ዕጥፍ እንደሚመልስ ተናገረ፤ የዚያ ማኅበረ ሰብ ኢኮኖሚ ይነቃቃል (ሉቃስ 19፥1-8 ይመ)፡፡ ይህ ሁሉ የተከናወነው ከእግዚአብሔር ጸጋ ጋር፣ አንዴ በመገናኘት ብቻ ነበር!

ሌላ ጊዜ ደግሞ አንድ የሚያስብለት ያልነበረው የአእምሮ ሕመምተኛ ነበር፡፡ በዚያ ዘመን የአእምሮ ሕሙማን የሚታከመበት ሆስፒታል አልነበረም፡፡ በኢየሱስ ሕይወት ከነበረው የእግዚአብሔር ጸጋ የተነሣ ግን፣ ያ

ሰው ፍጹም ተፈወሰ፡፡ በእርሱ መፈወስ ማኅበረ ሰቡም ሰላም አገኘ፡፡ በዚህ የእግዚአብሔር ጸጋ በነካው ሰው ምክንያት ዴካፓሊስ ይባሉ የነበሩ ዐሥሩ ከተማ ሰዎች፣ ስለ የእግዚአብሔር መንግሥት ሰሙ (ማርቆስ 5 ይመ)!

በኢየሱስ ካለው የእግዚአብሔር ጸጋ የተነሣ መስማት የተሣናቸው፣ ማየት የተሣናቸው፣ ሽባዎች፣ የተለያየ ደዌ ያደረባቸውና ማንኛውም አካላዊ ችግር ያለባቸው ሁሉ ሲፈወሱና የማንም ተረጂ ከመሆን ነጻ ሲወጡ ምን እንደሚሆን አስቡ፡፡ ያም ብቻ ሳይሆን፣ እነዚሁ ሰዎች የማኅበረ ሰቡ አምራች ዜጎች ሲሆኑ አስቡ፡፡ እንዲህና እንዲያ እያልን ወንጌሎቹ ውስጥ ከተጻፈው በላይ አልፈን መሄድ እንችላለን፤ ምክንያቱም በሦስት ዓመት ተኩል ይፋ አገልግሎቱ ኢየሱስ ያደረጋቸው የጸጋ ተአምራት ሁሉ ቢጻፉ ኖሮ ለመጻሕፍቱ ዓለም ራሱ እንኳ ሊበቃቸው እንደማይችል ዮሐንስ መጻፉን ቀደም ብለን ተመልክተናል፡፡

‹‹በእኔ የሚያምን እኔ የማደርገውን ሥራ ይሠራል - እንዲያውም ከእነዚህም የሚበልጥ ያደርጋል›› በማለት ኢየሱስ ተስፋ ቃል መስጠቱን አስታውሱ (ዮሐንስ 14፥12)፡፡ እንዴት? በነጻ ከሚሰጥ፣ የእኛ ጥረት ውጤት ካልሆነ ነጻ የእግዚአብሔር ጸጋ ስጦታ የተነሣ፡፡ በእግዚአብሔር ነጻ የጸጋ ስጦታ - ኢየሱስ የራሱን ማኅበረ ሰብ እንደ ለወጠ ሁሉ እኛም የራሳችንን መለወጥ አለብን!

## ፍሊጋው

እንዲህ ያለውን ዕውቀት ከእኛ መሰወር፣ የጨለማው ዓለም ኃይሎችና አገዛዞች ዋና ግባቸው ማድረጋቸውን አጥብቄ አምናለሁ፡፡ ጸጋ ነጻ፣ ዋጋ የማይከፈልበት ስጦታ፣ የኃጢአት ይቅርታ መሆኑን 98 እጁ ክርስቲያን ማኅበረ ሰብ ቢያምንም፣ እጅግ ታላቅ ኃይሉን በተመለከተ ግን ቸልተኞች መሆናቸው እነዚህን ክፉ ኃይላት እፎይ ሳያሰኛቸው እንደማይቀር አስባለሁ፡፡ ይህም ማለት ለምሽጋቸው እውነተኛ ስጋት የሚሆኑት የተቀሩት 2 እጅ ብቻ ይሆናሉ ማለት ነው፡፡

ለእኛ የተዘጋጀውን እጅግ አስደናቂ ኃይል እስካላወቅን ድረስ፣ የሚያማምሩ የቤተ ክርስቲያን ሕንፃዎቻችን፣ በብዛት የሚታተሙ መጻሕፍቶቻችን፣ ትልልቅ ስብሰባዎቻችን፣ የቴሌቪዥን ፕሮግራሞቻችን ወይም የሳተላይት ስርጭታችን ጠላትን አያስፈራውም፡፡ የጨለማ ኃይሎችን የሚያስፈራቸው እግዚአብሔር እኛ ውስጥ በነጻ ያስቀመጠውን ታላቅ ኃይል ማወቃችንና ከዚህም የተነሣ ኢየሱስ የነበረበትን ማኅበረ ሰብ እንደ ለወጠ ሁሉ እኛም በድፍረትና አዲስ ሐሳብ በማፍለቅ ማኅበረ ሰባችንን መለወጥ

የምንችል መሆኑን መገንዘባችን ነው፡፡ ሕይወት ላይ የመንገሥ ቦታችንን መያዛችንን ይፈሩታል፡፡

ጥቅምት 31, 1517 ዓ.ም ማርቲን ሉተር በዊተንበርግ ባለው ኦል ሴንትስ ቤተ ክርስቲያን በር ላይ ክርስቲያናዊ አስተምህሮን የሚመለከቱ ዘጠና አምስት ነጥቦች የለጠፈ ጊዜ አንድ ፍለጋ ላይ ነበር ማለት ይቻላል፡፡ ከዚያ ጊዜ ወዲህ ቤተ ክርስቲያን በፍጹም የዱሮዋ አልሆነችም፡፡ የእግዚአብሔር መንፈስ በዚያ ሰው አማካይነት እየሠራ ነበር፡፡ የዚያ ፍለጋ መደምደሚያው፣ *ጻድቅ በእምነት ይኖራል* የሚለው ሆነ፡፡ ሰዎችን ከቀንበር በታች ያደረገውን በዚያ ዘመን የነበረችው ቤተ ክርስቲያንን ከንቱ አስተሳሰብና የአምልኮ ወግ ፊት ለፊት ተጋፈጠ፡፡

እኔም ፍለጋ ላይ ነኝ፡፡ እንደ እኔ ያሉ ሌሎች ብዙዎች መኖራቸውንም አውቃለሁ፡፡ እናንተም ከእኛ ጋር እንድትሆኑ እንፈልጋለን፡፡ አማኝ ወገኖቻችን ልብ ውስጥ እንጂ፣ ያረጀ በር ላይ ዘጠና አምስት የእምነት ጥያቄዎች አንለጥፍም፡፡ የእኛ መልእክት – ጸጋ እግዚአብሔር ኃጢአታችንን ይቅር ማለቱ ብቻ አይደለም፡፡ ጸጋ እንደ ኢየሱስ እንድንኖር፣ የሰማይን ሥልጣንና ኃይል በመግለጥ በዙሪያችን ያለውን ዓለም በመለወጥ በሕይወት እንድንነግሥ የሚያስችለንም ጭምር ነው የሚል ነው፡፡

2 እጁን የክርስቲያን ማኅበረ ሰብ ቁጥር ወደ 100 እጅ ከፍ ለማድረግ እንነሣ፡፡ አማኞች ጸጋ የሚለውን ቃል ሲሰሙ ወዲያውኑ፣ ‹‹ከእኛ ሰብዓዊ ችሎታ በላይ የሆነ፣ የእግዚአብሔር የማስቻል/ ብቁ የማድረግ ዐቅም›› የሚለውን እንድናስብ እግዚአብሔር ይርዳን፡፡

# 5

# ራስን መለየት፣ ልቆ መገኘት

*የጸጋን ብዛትና የጽድቅን ስጦታ ብዛት የሚቀበሉ በአንዱ በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል በሕይወት ይነግሣሉ*

*ሮሜ 5፥17*

ሮሜ 5፥17 የያዘው ሐሳብ ስፋትና ጥልቀት እውነታ መቀበል ከምንችለው በላይ ነው፡፡ መልእክቱ እጅግ ግሩም ነው፡፡ ምናልባትም ብዙዎች ችላ ብለው የሚያልፉት በዚህ ምክንያት ሊሆን ይችላል፡፡

ኢየሱስን የሕይወታችን ጌታ አድርገን የተቀበልን እያንዳንዳችን ሕይወት ላይ እንነግሣለን ወይም እንገዛለን፡፡ የእግዚአብሔርን ጸጋ የተቀበልን ሁሉ ይህ ዓለም እኛ ላይ ከሚያመጣው ማንኛውም ችግር በላይ የምንሆንበት ኃይል ወይም የማስቻል/የማብቃት ዐቅም አለን፡፡ የዚህ ምድር ሕይወት ሊገዛን አይገባም፤ ይልቁን፣ እኛ ነን ልንገዛው ልንነግሥበት የሚገባን፡፡ ኢየሱስ የራሱን ማኅበረ ሰብ እንደ ለወጠ፣ እኛም የራሳችንን መለወጥ አለብን፡፡ ይህ የእኛ ኃላፊነት ነው፡፡

## በተግባር የሚገለጥ ንግግር

አሁን ደግሞ፣ በእግዚአብሔር ጸጋ በሕይወት መንገሥ ወይም መግዛት ሲባል ምን ማለት እንደ ሆነ እንይ፡፡ ከተለመደው አስተሳሰብ ርቀን መሄድ፣ ማኅበረ ሰቡ አይደፈርም የሚለውን መስበር አለብን፡፡ ከእንግዲህ ሕይወትን በብዙ ውጣ ውረድ ካሳለፍን በኋላ በሞት እንደሚጠናቀቅ፣ የመጨረሻም ግቡም መንግሥተ ሰማይ መግባት የሆነ አድርገን ብቻ አናየውም፡፡ እግዚአብሔር እንድንኖር ያቀደው በዚህ መልኩ አይደለም፡፡ ከዚያ እጅግ ለበለጠ ጉዳይ ነው የተፈጠርነው!

ጅራት ሳይሆን ራስ፣ ከታች ሳይሆን ከላይ፣ (ዘዳግም 28፥13) እንድንሆን እግዚአብሔር የጠራን መሆኑን በማወቅ፣ በጐ ተፅዕኖ አሳዳሪዎች እንሆናለን፡፡ በሕይወት በሚገጥሙን አዳጋች ሁኔታዎች ላይ የበላይ መሆን

ብቻ ሳይሆን፣ ከእግዚአብሔር ጋር ኪዳን ከሌላቸው የበለጠ መድመቅና የተለየን ሆነን መገኘት አለብን፡፡ አብርሆት በሌላው ዓለም መካከል መሪዎች መሆን አለብን፡፡ አቅጣጫን፣ መንገድንና ዝንባሌን የሚወስን ራስ ነው፤ ጅራት ግን ከኋላ ሆኖ ይከተላል፡፡ በማኅበረ ሰባችን ማንኛውም ጉዳይ መሪዎች መሆን አለብን እንጂ፣ ግትልትል ተከታዮች መሆን የለብንም፡፡

አስተማሪ ከሆንህ በጸጋ ስጦታ አማካይነት፣ ሌሎች መምህራን ማሰብ እንኳ ከሚችሉት በላይ ለተማሪዎችህ ጥበብና ዕውቀት ለማድረስ ዘወትር ትኩስና አዳዲስ ሐሳብ የምታፈልቅ መሆን አለብህ፡፡ መድረሻ ግቡን ከፍ በማድረግ፣ ሌሎችን በሚያስደንቅ ሁኔታ ተማሪዎችህን ታነሣሣለህ፡፡ በዚህም ምክንያት የሥራ ባልደረቦችህ፣ ‹‹ለመሆኑ፣ እንዲህ ያለውን አስደናቂ ሐሳብ የሚያፈልቀው እንዴት ነው?›› በማለት እርስ በርስ ይነጋገራሉ፡፡

ያለኸው በሕክምና ሙያ ውስጥ ከሆነ፣ በእግዚአብሔር ጸጋ ስጦታ በሽታና ደዌን የምታክምበት አዳዲስና ውጤታማ መንገድ ይዘህ ትመጣለህ፡፡ የሥራ ባልደረቦችህም በመገረም፣ ‹‹እንዲህ ያለውን ድንቅ ሐሳብ ያገኘው ከየት ነው?›› በማለት ይጠያየቃሉ፡፡

ዲዛይነር ከሆንህ፣ በእግዚአብሔር ጸጋ ስጦታ ሌሎች የሚወዱትና የሚደነቁበት አዳዲስ ፈጠራዎች ታፈልቃለህ፡፡ ማኅበረ ሰቡ በስፋት የሚቀበለው ልቆ የሚወጣ ስልትና አሠራር ታኖራለህ፡፡ በሥራህ ትፈለጋለህ፤ አዳዲስ ዐይነት አካሄድ በመጀመርም ትታወቃለህ፡፡ ከሙያ ባልደረቦቻችሁ ሁሉ ይልቅ ቀድማችሁ ስለምትሄዱ፣ ‹‹በመገረምና በመደነቅ እንዲህ ያለውን ሐሳብ የሚያገኘው ወይም የምታገኘው ከየት ነው?›› በማለት እርስ በርስ ይጠያየቃሉ፡፡

በፖለቲካው መስክ ያላችሁ ሰዎች ከሆናችሁም በእግዚአብሔር ጸጋ አማካይነት ሌሎች አይቻልም ያሉትን የማኅበረ ሰቡን ችግር በመፍታት ረገድ፣ የላቀ ጥበብ ታሳያላችሁ፡፡ መፍትሔ በማስገኘት ግንባር ቀደም ትሆናላችሁ፤ ከሥራ ጓደኞቻችሁ ቀድማችሁ ለበለጠ ኃላፊነት ትመረጣላችሁ ወይም በፍጥነት ዕድገት ታገኛላችሁ፡፡ አዳዲስ ሐሳብ ማቅረባችሁና መፍትሔ ማፍለቃችሁ በዙሪያችሁ ያሉ ሰዎችን፣ ‹‹እንዲህ ያለ የሚገርም ሐሳብ የሚያገኘው ወይም የምታገኘው ከየት ነው?›› በማለት እንዲጠይቁ ታደርጓቸዋላችሁ፡፡

ሕግ አስከባሪዎች ከሆናችሁ፣ በሕይወታችሁ ካለው የእግዚአብሔር ጸጋ የተነሣ ሌሎች ከዐቅማችን በላይ ነው ባሉት ሁኔታ ውስጥ ሰላም ታመጣላችሁ፡፡ ኢየሱስ አህያዋ የት እንዳለች በተአምር እንዳወቀ ሁሉ፣

እናንተም ወንጀለኞች ያሉበትን ቦታ ታውቃላችሁ፡፡ በማኅበረ ሰባችሁ ካለ ማንኛውም ባለ ሙያ ቀድማችሁ ችግሩን መፍታት የሚችል ሐሳብ ትገጣጥማላችሁ፡፡ ጥበባችሁ፣ ችሎታችሁና አዳዲስ ሐሳብ አፍላቂነታችሁ በጣም ስለሚደንቃቸው ሰዎች፣ ‹‹እንዲህ ያለ መፍትሔ የሚሆን ሐሳብ የሚያወጣው ወይም የምታወጣው ከየት ነው?›› በማለት ይጠያየቃሉ፡፡

በንግዱ ዓለም ያላችሁ ወንዶች ወይም ሴቶች ከሆናችሁ፣ በእግዚአብሔር ጸጋ ከሌሎች ሁሉ ቀድማችሁ አዳዲስ ነገሮችን፣ የአሻሻጥ ዘዴዎችንና የገበያ ስልቶችን ትጠቀማላችሁ፡፡ የትኛው አትራፊ እንደ ሆነና የትኛው አትራፊ እንዳልሆነ በውስጥ ልባችሁ ትረዳላችሁ፡፡ መቼ መግዛትና መቼ መሸጥ፣ መቼ መሰብሰብና መቼ ማከፋፈል እንዳለባችሁ ታውቃላችሁ፡፡ ይህን የሚመለከቱ ሌሎች የሥራ ጓደኞቻችሁ የስኬታማነት ምስጢራችሁ ምን እንደ ሆነ ለመረዳት ይጓጓሉ፡፡

ከላይ የተዘረዘሩት በጣም ርቀው ያሉና በተግባር መተርጐም የማይችሉ ምሳሌዎች አይደሉም፡፡ ማድረግ ወይም መሆን የምንችለውን ነገር የሚጠቁሙ ምሳሌዎች ናቸው፡፡ እያንዳንዳችን ማኅበረ ሰቡ ውስጥ የተለያየ ቦታ እንዲኖረን ተጠርተናል፤ ሆኖም፣ በየትኛውም የሕይወት ገጽታ ብንሆን ራስ የመሆንን፣ መሪ የመሆንን፣ ማንኛውንም ነገር ጠንቅቀን ማወቅን ማሳየት አለብን፡፡ የጀመርነው ሥራ ማበብና ማደግ አለበት፡፡ የምንኖርበት ማኅበረ ሰብ ምቹ፣ ደስ የሚልና የተሟላ መሆን አለበት፡፡ ከእኛ የተነሣ ተቀጥረን የምንሠራበት ቦታ እንኳ መባረክ አለበት፡፡ ሙዚቀኞች ከሆንን፣ ሙዚቃችን ትኩስና ተደጋጋሚ ያልሆነ መሆን አለበት፤ እንደ እውነቱ ከሆነ ዓለማዊ ሙዚቀኞች በክርስቲያኖች መቅናት እንጂ፣ ክርስቲያኖች የዓለማውያንን ሙዚቃ አጨዋወት ስልት መኮረጅ አልነበረባቸውም፡፡

የግራፊክ፣ የቪዲዮ፣ የአርኪቴክትና ዲዛይን ሥራዎቻችንን በተመለከተም ይኸው መሆን አለበት፡፡ የእግዚአብሔር ቤተ ሰብ አዳዲስ ነገሮች የመፍጠር ችሎታ የሚያነሣሣና የሚፈለግ መሆን አለበት፡፡ -በአትሌቲክሱም ሆነ በመዝናኛው፣ በኪነ ጥበቡም ሆነ በመገናኛ ብዙኀን፣ ወይም በሌሎች መስኮች ያሉ የመድረክ ሰዎቻችን ለሌሎች ምሳሌ መሆን አለባቸው፡፡ ጽድቅ ሲገዛና ሲሰለጥን ከተሞቻችን፣ ክልሎቻችን ማበብና መበልጸግ አለባቸው፡፡

አማኞች በሚሳተፉበት ነገር ሁሉ ፈጠራ፣ ውጤታማነት፣ ሰላም፣ ማስተዋልና አዳዲስ ነገሮችን ማፍለቅ ሞልቶ መትረፍረፍ አለበት፡፡ በጨለማው ብርሃን መሆን ይኖርብናል፡፡ በሕይወታችን ካለው ከአእምሮ

በላይ ከሆነ የእግዚአብሔር ጸጋ የተነካ፣ በጨለማው ማኅበረ ሰብ ውስጥ የተለየን መሆን አለብን፡፡

## ራሳችንን መለየት፣ ልቀን መገኘት

በእግዚአብሔር ጸጋ የማስቻልና ብቁ የማድረግ ኃይል በማንኛውም የሕይወት ገጽታዎች ደምቀንና ልቀን መታየት ይኖርብናል፡፡ እስቲ፣ ስለ ዳንኤል የተሰጠውን ምስክርነት ረጋ ብላችሁ አንብቡ፣

> ከመሳፍንቱና ከበላይ አስተዳዳሪዎቹ ሁሉ ይልቅ ዳንኤል ልዩ የጥበብ መንፈስ የሞላበት ሆኖ በመገኘቱ፣ ንጉሡ በመላው ግዛቱ ላይ ሊሾመው አሰበ፡፡ (ዳንኤል 6፥3)፡፡

በጣም ትኩረት የሚያሻው ጉዳይ ነው፡፡ ዳንኤል ራሱን ለየ፡፡ መጽሐፉ፣ ‹‹እግዚአብሔር ዳንኤልን የተለየ አደረገው›› አለማለቱን ልብ አድርጉ፡፡ ዋና ዋናዎቹ የመጽሐፍ ቅዱስ ትርጉሞች ይህ ድንቅ ወጣት ራሱን እንደ ለየ ነው የሚያመለክቱት፡፡ አንድ በዘመናዊ ቋንቋ የቀረበ ትርጉም፣ ‹‹ዳንኤል ከሌሎች ባለ ሥልጣኖች ሁሉ ይልቅ ራሱን የተለየ አደረገ›› ይላል፡፡

ያንን ማድረግ የቻለው እንዴት ነበር? ከእግዚአብሔር ጋር ተቀራርቦ ይኖር የነበረ በመሆኑ፣ በሌሎች ያልነበረ ባሕርይ ሊኖረው ቻለ፡፡ ከፈጣሪ ጋር ያልተቋረጠ ግንኙነት ስለ ነበረው፣ ዳንኤል ራስን የመግዛትና በሥርዐት የመኖር ችሎታ ነበረው፡፡ ከእግዚአብሔር ጋር ኪዳናዊ ኅብረት ያለውን ሰው በተመለከተም ዛሬም ቢሆን ከዚህ የተለየ መሆን የለበትም፡፡

አዲሱ የአሜሪካ መደበኛ ትርጉም፣ (The New American Standard Version) ‹‹ዳንኤል ራሱን ለየ. . . ምክንያቱም እርሱ የተለየ ዓይነት መንፈስ ነበረው›› በማለት ይነበባል፡፡ የተለየ ዓይነት የሚለው፣ ‹‹ከተለመደው ወጣ ያለ፣ ማኅበረ ሰቡ ልማድ አድርጎ የያዘውን ጥሶ የወጣ፣ ከተለመደው መስፈርት አልፎ የሄደ›› ተብሎ ሊተረጎም ይችላል፡፡ አንዳንዴ የአንድን ቃል ትርጉም በሚገባ ለመረዳት ተቃራኒውን ማየቱ ጠቃሚ ሊሆን ይችላል፤ የዚህ ቃል ተቃራኒ፣ ‹‹የተለመደ፣ ተራ ወይም መደበኛ ተብሎ የተያዘ›› የሚል ነው፡፡ ስለሆነም የተለመደና ተራ የሆነ የአኗኗር መንገድ፣ የተለየ ዐይነት መንፈስ ያለው ሰው አኗኗር ተቃራኒ ነው ማለት ነው፡፡

ጽሑፉ የሚነግረን የዳንኤል መንፈስ የተለየ እንደ ነበር እንጂ፣ የተለየ አእምሮ ወይም ቁመና እንደ ነበረው አይደለም፡፡ መንፈሳችን የተለየ ከሆነ አእምሮአችን፣ አካላችን፣ የፈጠራ ዐቅማችን፣ አዳዲስ ነገሮች የማፍለቅ

ችሎታችን፣ ጥበባችን፣ ዕውቀታችንና ሌሎች የሕይወት ገጽታዎቻችን በሙሉ በዚያው መሠረት ይቃኛሉ፡፡ ሕይወታችንን የሚቀርጸው መንፈሳችን ነው፡፡ የተሰጠንን ጸጋ በሚገባ ብናውቅ ኖሮ፣ ከዚያ ጸጋ የተነሣ ወሰን ወይም ገደብ እንደሌለን እናውቅ ነበር፤ ምክንያቱም፣ ‹‹ለሚያምን ሰው ሁሉም ነገር ይቻላል›› (ማርቆስ 9፥23)፡፡ ዳንኤል ከእግዚአብሔር ጋር ካለው ቀረቤታ የተነሣ ባገኘው ጸጋ ተጠቀመ፡፡ ሁሉን ከሚችል አምላክ ጋር ባለው ኪዳን ዳንኤል፣ ሁኔታዎችን መግዛት እንጂ፣ በሁኔታዎች መገዛት እንደሌለበት ተረዳ፤ ራስ እንጂ ጅራት መሆን እንደሌለበት አወቀ፡፡

እስቲ፣ ሰፋ አድርገን ስለዚህ ጉዳይ እናስብ፡፡ ዳንኤልና ጓደኞቹ እስራኤል ከምትባለዋ ታናሽ አገር፣ በዓለም ውስጥ እጅግ ኃያል ወደ ነበረ አገር ተወስደው ነበር፡፡ ምናልባት አንዳንዶቻችሁ ካለፉት አያሌ ዓመታት ጀምሮ አሜሪካ ታላቅ አገር ነች ብላችሁ የምታስቡ ከሆነ፣ ከባቢሎን ኃያልነትና ብርታት ጋር ስትነጻጸር አሜሪካ ምንም ማለት እንዳይደለች እነግራችኋለሁ፡፡ ባቢሎን በዘመኑ ይታወቅ የነበረውን ዓለም በሙሉ ትገዛ ነበር! በኢኮኖሚ፣ በፖለቲካ፣ በወታደራዊ ኃይል፣ በማኅበረ ሰባዊ አኗኗር በሳይንሳዊ ግኝት፣ በዕውቀትና በሌሎች አቅጣጫዎች በሙሉ የበላይ ነበረች፡፡ ይሁን እንጂ፣ ‹‹ንጉሡ በጠየቃቸው በማንኛውም የጥበብና የማስተዋል ጉዳይ በመላው ግዛቱ ካሉት. . . (ዳንኤል፣ አናንያ፣ ሚሳኤልና አዛርያስ) ዐሥር እጅ በልጠው›› እንዳገኛቸው እንመለከታለን (ዳንኤል 1፥20)፡፡ አንዳንድ ትርጉሞች እነዚህ አራት ሰዎች ዐሥር እጅ የተሻሉ፣ ዐሥር እጅ ጥበበኞችና ማስተዋል ያላቸው ሆነው እንደ ተገኙ ያመለክታሉ፡፡ የባቢሎን ሰዎች አስበው እንኳ የማያውቁትን ጥበብ የሞላባቸው ሐሳቦች ያቀርቡ እንደ ነበርና ያቀረቧቸው ሐሳቦች በሙሉ በተግባር ሊተረጐሙ የሚችሉ እንደ ነበሩ ያመለክታሉ፡፡

## ከዳንኤል የበለጠ፣ ከዮሐንስ የበለጠ

እንግዲህ ይህን በአእምሮአችሁ በመያዝ፣ ‹‹ከሴት ከተወለዱት መካከል ከዮሐንስ የሚበልጥ የለም›› በማለት ኢየሱስ የተናገረውን አንብቡ (ሉቃስ 7፥28)፡፡ ይህም ማለት መጥምቁ ዮሐንስ ከዳንኤልም ይበልጣል ማለት ነው፡፡ ሁለቱን ሰዎች ባከናወኑዋቸው ነገሮች ለማወዳደር አትሞክሩ፤ ምክንያቱም ዮሐንስ የተሰማራው በመንፈሳዊ አገልግሎት ሲሆን፣ ዳንኤል የነበረው በመንግሥት ሥራ ውስጥ ነበር፡፡ ያም ሆኖ ግን፣ ኢየሱስ ዮሐንስን የበለጠ፣ ‹‹ታላቅ›› አድርጎ አቅርቦታል፡፡ ይሁን እንጂ፣ ይህን ካለ በኋላ በመቀጠል፣ ‹‹በእግዚአብሔር መንግሥት ግን ከሁሉ የሚያንሰው ይበልጠዋል›› ብሏል (ሉቃስ 7፥28)፡፡

በመንግሥተ ሰማይ ከሁሉ የሚያንሰው ከዳንኤል ወይም ከዮሐንስ የሚበልጠው ለምንድነው? ኢየሱስ ይህን በሚናገርበት ጊዜ የሰው ልጅን ነጻ ለማድረግ ገና መስቀል ላይ አልሞተም ነበር፤ ስለዚህም ዮሐንስ ዳግም የተወለደ መንፈስ አልነበረውም፡፡ ገና የክርስቶስ አካል ብልት አልሆነም ነበር፡፡ ‹‹መጥምቁ ዮሐንስ እንደ ኢየሱስ ነበር›› ተብሎ ሊነገርለትም አይችልም፡፡ ዮሐንስ ከክርስቶስ ጋር ከሞት አልተነሣም፤ ከክርስቶስ ጋር በሰማያዊው ስፍራ አልተቀመጠም፡፡ እኛን በተመለከተ ግን እነዚህ ነገሮች ሁሉ እውን ሆነዋል፡፡ እንግዲህ፣ በመንግሥተ ሰማይ ከሁሉም የሚያንሰው ከዮሐንስ የሚበልጠው በዚህ ምክንያት ነው፡፡

ከኢየሱስ ትንሣኤ ወዲህ በምድር ላይ በግምት ሁለት ቢሊዮን ክርስቲያኖች መኖራቸው ይታመናል፡፡ እንግዲህ አንተ ወይም አንቺ ከእነዚህ ሁለት ቢሊዮን ሰዎች ‹‹ከሁሉም የምታንሱ›› ብትሆኑ እንኳ፣ ያ ራሱ ከመጥምቁ ዮሐንስ የበለጣችሁ ያደርጋችኋል ማለት ነው! እንዲህ ከሆነ ደግሞ ከዳንኤልም ትበልጣላችሁ ማለት ነው! እንግዲህ ጥያቄው የሚነሣው ይኼኔ ነው፤ ለመሆኑ፣ እናንተ ራሳችሁን ለይታችኋል?

አብረዋችሁ ከሚሠሩና በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል ከእግዚአብሔር ጋር ኪዳናዊ ግንኙነት ከሌላቸው ሰዎች ይልቅ ዐሥር እጅ አስተዋች፣ ዐሥር እጅ የፈጠራ ችሎታ ያላችሁና አዳዲስ ሐሳብ አፍላቂዎች ናችሁ? ዐሥር እጅ የግንዛቤና ንቁነት ዐቅም አላችሁ? (እንግዲህ ይህ አብሩዋችሁ ከሚሠሩ ሰዎች ሁሉ ይልቅ ዐሥር እጅ የበለጠ ታጋሽ፣ አፍቃሪዎች፣ ራሳችሁን የምትቆጣጠሩ፣ ደጐች፣ ሰዎችን የምትቀበሉ፣ ርኅሩኆችና ቸሮች ሆናችኋል ወይ? የሚለውን ሳንጨምር ነው)፡፡ ካልሆነ ለምን? ዳግም ተወልደናል ከሚሉ አማኞች እጅግ ብዙዎቹ በጌታ ኢየሱስ ከማያምኑ ሰዎች የሚበልጡ አስተዋዮች ያልሆኑት ለምንድነው? በሕይወት እንድንገዛና ዳንኤል እንዳደረገው ራሳችንን እንድንለይ፣ ከተፈጥሮአዊ ችሎታችን በላይ አልፈን እንድንሄድ የሚያስችለን ጸጋ የእግዚአብሔር የማብቃት ወይም የማስቻል ዐቅም መሆኑን የተረዳን ከመቶ 2 እጅ ብቻ ስለሆንን ይሆን? (ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ያሉ ደካሞችን ሸክም እንድንሸከም እንደ ተነገረን አስታውሱ፡፡ ይሁን እንጂ፣ ዕድሜ ልካቸውን ደካሞች ሆነው መቅረት እንዳለባቸው መጽሐፍ ቅዱስ አይናገርም፡፡ እነርሱም ቢሆኑ ባሉበት ሁኔታ ራሳቸውን መለየት እንዲችሉ ራእይ ሊሰጣቸው ይገባል)፡፡

ኢየሱስ ‹‹የዓለም ብርሃን›› እንደ ሆንን ይናገራል (ማቴዎስ 5፥14 ይመ.)፡፡ በአዲስ ኪዳን ውስጥ ልጆቹ በጨለማ መካከል ብርሃን እንዲሆኑ የተናገረው አንድ ጊዜ ብቻ አይደለም፤ ምክንያቱም የሚከተሉት ጥቅሶች

የክርስቶስን ምሳሌያዊ አነጋገር ይደግፋሉ - ማቴዎስ 5፥14-16፤ ሉቃስ 12፥3፤ ዮሐንስ 8፥12፤ ሐዋርያት ሥራ 13፥47፤ ሮሜ 13፥12፤ ኤፌሶን 5፥8፣ 14፤ ቈላስይስ 1፥12፤ ፊልጵስዩስ 2፥15፤ 1ተሰሎንቄ 5፥5፤ 1ዮሐንስ 1፥7፤ 2፥9-10። ስለዚህም ለጨለማው ዓለም ብርሃን መሆን፣ በክርስቶስ ያለን ሕይወት ዐቢይ ሐሳብ መሆኑን ማየት እንደምትችሉ አስባለሁ።

የዓለም ብርሃን መሆን ምን ማለት እንደ ሆነ ቆም ብላችሁ አስባችሁ ታውቃላችሁ? በጣም የሚያሳዝነው ግን ብዙዎች ‹‹ብርሃን›› መሆንን የሚስቡት በምሄዱበት ሁሉ መጽሐፍ ቅዱስ ይዘው የሚታዩ፣ ባገኙት አጋጣሚ ሁሉ ዮሐንስ 3፥16ን የሚጠቅሱ፣ ዐመለ ሸጋዎችና ተግባቢዎች ከመሆን የተለየ አድርገው አይደለም። ግን ብርሃን መሆንን በተመለከተ ዳንኤል የነበረው አስተሳሰብ የዚህ ዐይነት ቢሆን ኖሮ ምን የሚሆን ይመስላችኋል? የሕይወት ግብ አድርጎ የያዘው በባቢሎን ተግባብቶ የሚኖር ሰው መሆንንና ለሚያገኛቸው ሰዎች ሁሉ መዝሙር 23፣ ‹‹እግዚአብሔር እረኛዬ ነው የሚያሳጣኝም የለም. . .›› ይላል እያለ መጥቀስ ቢሆን ኖሮ ምን የሚሆን ይመስላችኋል?

በምሳ ሰዓት የሚያደርገውን ጸሎት ለማድረስ ዳንኤል ከቢሮ ሲወጣ ሠራተኞቹና አለቆቹ ምን ማለት የሚችሉ ይመስላችኋል? ምናልባትም፣ ‹‹ያ ለፍላፊ ቢሮውን ለቆ በመሄዱ ደስ ብሎኛል። ይኼኔ ሄዶ ከሰዓት በኋላውን በሙሉ ሲጸልይ ይውላል። አንጎሉ ጤነኛ መሆኑን እጠራጠራለሁ›› የሚለውን የመሳሰሉ ቃሎች የሚናገሩ ይመስለኛል።

ዳንኤል እንዳይጸልይ ሕግ እንዲወጣ የፈለጉት ለምን ይመስላችኋል (ዳንኤል 6፥6-8 ይመ)? የሚኖረን ብቸኛ አሳማኝ ምክንያት፣ ከእነርሱ ይልቅ ዳንኤል ዐሥር እጅ ጥበበኛ፣ ዐሥር እጅ ዐዋቂ፣ የፈጠራና አዳዲስ ሐሳቦች የማፍለቅ ችሎታ ስላለው ነው የሚለው ይሆናል። በሁሉም ላይ አለቃ እስኪሆን ድረስ፣ በየጊዜው እያደገና ከፍ እያለ ነበር። በዚህ በጣም ግራ ተጋብተው ነበር፡ ‹‹በጥበብ፣ በዕውቀትና በችሎታ በመላው ዓለም ታዋቂነት ባላቸው መምህራን፣ ሳይንቲስቶችና ሊቃውንት ተምረን ነበር። ያም ሆኖ የሚገባንን ደረጃ አላገኘንም። እርሱ ግን ምንም ከማትታወቅ ትንሽ አገር የመጣ ነው። ታዲያ፣ በየጊዜው የሚያፈልቃቸውን አዳዲስ ሐሳቦች ያገኘው ከየት ነው? ከእኛ በልጦ የተገኘበት ምስጢር ምንድነው? ምናልባት ይህን ሁሉ ያገኘው ከጸሎቱ ሊሆን ይችላል። በቀን ሦስት ጊዜ ወደ እግዚአብሔር ይጸልያል! ስለዚህ በእኛ ላይ ከፍ ከፍ ማለቱ እንዳይቀጥል፣ አንድ ሕግ ማውጣት አለብን!›› በማለት እርስ በርሳቸው ተነጋግረው ይሆናል።

እጅግ ሲበዛ ልዩ ሰው በመሆኑ፣ በዚያ ጨለማ በዋጠው ባሕል ውስጥ ዳንኤል ቦግ ብሎ የሚታይ መብራት ሆኖ ነበር፡፡ አብረውት ይሠሩ የነበሩት ግን ይህን አልወደዱለትም፤ ምቀኝነት ያዛቸው፡፡ ይሁን እንጂ፣ ንጉሡን ጨምሮ ሌሎች ብዙዎች በዳንኤል ችሎታ ውስጥ የሕያው አምላክን መገኘት ማየት ሳይችሉ እንዳልቀረ አስባለሁ፡፡ የዳንኤል ልቆና በልጦ መገኘት መሪዎቹን ወደ ዳንኤል አምላክ ሳይስባቸውና እርሱን እንዲያከብሩ ሳያደርጋቸው አልቀረም፡ ትኩረታቸውን ዳንኤል ላይ እንዲያደርጉ ያደረጋቸው የዳንኤል መጽሐፍ ቅዱስ ዕውቀት፣ ጥሩ ሰው መሆኑ ወይም በቀን ሦስት ጊዜ መጸለዩ አልነበረም ይልቁን - ዳንኤል በተሰማራበት የሥራ መስክ በልጦና ልቆ መገኘቱ ነበር፡፡

እንግዲህ ከዚህ አንጻር፣ ብርሃን መሆንን አስመልክቶ ኢየሱስ የተናገረውን ስሙ፣ ‹‹ሰዎች ሥራችሁን አይተው በሰማይ ያለውን አባታችሁን እንዲያከብሩ ብርሃናችሁ በሰዎች ሁሉ ፊት ይብራ›› (ማቴዎስ 5፥16)፡፡ ሥራችን በማያምኑ ሰዎች ዘንድ ጐልቶ መታየት እንደሚገባው ኢየሱስ ይናገራል፡፡ ታዲያ እኛ ሰዎችን በጨዋነት ወደ ማስተናገድና ከዚህና ከዚያ ቅዱሳት መጻሕፍትን ወደ መጥቀስ ደረጃ ዝቅ ያደረግነው ለምንድነው?

## የዘመኑ ምሳሌዎች

በዓለም ታላላቅ ከሆኑ አውቶሞቲቭ ካምፓኒዎች አንዱ ምክትል ፕሬዚዴንት የሆነ ቤን የሚሉት ወዳጅ አለኝ፡፡ አንድ ምሽት ራት እየበላን ስንጨዋወት ምክትል ፕሬዚዴንት ከመሆኑ በፊት ተፎካካሪ በሆኑ ዋነኛ መሐንዲሶች ስብስብ የተቋቋመ ድርጅት ውስጥ ይሠራ እንደ ነበር ነገረኝ፡፡ ‹‹ዳንኤልና ጓደኞቹ አብረዋቸው ይሠሩ ከነበሩ ሁሉ ይልቅ ዐሥር እጅ በልጠው መገኘታቸውን ከትንቢተ ዳንኤል አነበብኩ›› አለ ያ ወዳጄ፡፡ ‹‹ስለዚህም፣ ጌታ ሆይ ዳንኤልና ጓደኞቹ በአሮጌው ኪዳን ዘመን ከሥራ ጓደኞቻቸው ሁሉ ዐሥር እጅ በልጠው ከተገኙ፣ በአዲሱ የጸጋ ኪዳን ውስጥ ያለሁት እኔ ደግሞ አብረውኝ ከሚሠሩ ሰዎች በትንሹ ዐሥር እጅ መብለጥ አለብኝ በማለት ጸለይኩ፡፡››

ጓደኛዬ በመቀጠል፣ ‹‹ይህ ዋና ኮርፖሬሽን በከፍተኛ ዲዛይን ደረጃ በእያንዳንዱ ሠራተኛ ላይ በየዓመቱ የወጪ ቅነሣና ምርታማነት ጥናት ያደርጋል››፡፡ በሌላ አነጋገር ይህ የእያንዳንዱን ቡድን ሐሳብ አፍላቂነትና ውጤታማነት ይመረምራል ማለት ነው፡፡ በዚያ ዓመት፣ ‹‹በጠቅላላው ቡድን ውስጥ ካሉት ሁለተኛ ምርጥ ሠራተኞች የሰላሣ አምስት ሚሊዮን ዶላር

ወጪ ቅነሣና ምርታማነት አስገኙ፡፡ እኔ ምን እንዳደረግሁ ታውቃለህ?›› አለ፡፡

ያሰብኩትን እንደሚናገር በመጠበቅ፣ ‹‹ምን አደረግህ?›› አልኩት፡፡

‹‹በወጪ ቅነሣና በምርታማነት ሦስት መቶ ሃምሳ ሚሊዮን ዶላር አስገኘሁ፡፡ ያ ከሁለተኛው ሰው ዐሥር ዕጥፍ የበለጠ ነበር፡፡›› እንግዲህ ቤን በአሜሪካ ካሉ ታላላቅ ኮርፖሬሽኖች አንዱ በሆነው ውስጥ ከዋነኞቹ ሥራ አስኪያጆች አንዱ ወደ መሆን ደረጃ ያደገው በዚህ መንገድ ነበር፡፡

ሜሴንጀር ኢንተርናሽናል ውስጥ ሠራተኞች የነበሩ ባልና ሚስት አስታውሳለሁ፡፡ አንድ ቀን እነዚህን መርሖዎች አስመልክቶ ወደማስተምርበት ስብሰባ ሁለት ወንዶች ልጆቻቸውን ይዘው መጥተው ነበር፡፡ ከስብሰባው በኋላ ዐሥራ አንድ ዓመት እየሞላው የነበረው ታናሽየው ልጅ ትይለር አባቱን፣ ‹‹የእግዚአብሔር ጸጋ ስላለኝ በከተማችን ባለው ቡድን ከሌሎች የበለጥሁ እግር ኳስ ተጫዋች እሆናለሁ›› አለው፡፡ ከብዙ ልምምድ በኃላ በቀጣዩ የእግር ኳስ ግጥሚያ ወቅት የሆነውም እጅግ አስደናቂ ውጤት ማስመዘዝገቡንና እውነትም ከሌሎች ይልቅ ዐሥር እጅ በልጦ መገኘቱን የሚያመለክት ነበር፡፡

ብዙ ወጣቶች በቀላሉ የእግዚአብሔርን ቃል ማመናቸውና በዚያም መሠረት መንቀሳቀሳቸው በጣም ይገርመኛል፡፡ ወጣቱ ትይለር ለሁላችንም የሚሆን ምሳሌ አኑሮልናል!

## እኛ ውስጥ ያለ ጸጋ

እግዚአብሔር በቃሉ ውስጥ የገለጸውን እኛ በቀላሉ የማናምነው ለምንድነው? ከእርሱ ጋር ያለን ኪዳን፣ ‹‹እንግዲህ በእኛ ውስጥ እንደሚሠራው እንደ ኃይሉ (ጸጋው) መጠን፣ ከምንለምነው ወይም ከምናስበው ሁሉ በላይ እጅግ አብልጦ ማድረግ ለሚቻለው…›› ይላል (ኤፌሶን 3፥20)፡፡ አልፎ አልፎ ከሰማይ በሚመጣ ኃይል መጠን አይደለም የሚለው፤ የተለየ ዐይነት የአገልግሎት ስጦታ ያላቸው ወንዶችና ሴቶችን ፈልገን ስናገኝ የሚመጣ ነው አይልም፤ ይልቁንም በእኛ ውስጥ እንደሚሠራው እንደ ኃይሉ መጠን ነው የሚለው

ጥቅሱ ውስጥ ቁልፍ የሆነውን ቃል ልብ አድርጉ - እግዚአብሔር ይችላል፡፡ እስቲ በአንድ አገር ውስጥ ከባድ ራብ ገባ ብለን እናስብ፡፡ ይሁን እንጂ፣ አንድ በልግስናው የሚታወቅ የሌላ አገር መንግሥት የተለያየ ዐይነት ምግቦችና የመጠጥ ውሃ የጫኑ ብዙ አውሮፕላኖች ሥራውን ከሚያከናውኑ

ወታደሮች ጋር ወደዚያ ችግር ወዳጠቃው አካባቢ ላከ እንበል፡፡ የወታደሮቹ ጄኔራል፣ ‹‹እናንተ መውሰድ የምትችሉትን ያህል ምግብና መጠጥ ልንሰጣችሁ እንችላለን›› የሚል መግለጫ ሰጠ ብለን እናስብ፡፡ የመጀመሪያው ሰው አንድ መለስተኛ መያዣ ዕቃ ይዞ መጣና፣ ለሁለት ሰዎች ለጥቂት ቀኖች የሚበቃ ምግብ ወሰደ፡፡ ሁለተኛው ሰው ደግሞ አንድ ትልቅ መያዣ ይዞ መጣና ለቤተ ሰቡ ለአምስት ቀን የሚበቃ ምግብ ይዞ ሄደ፡፡ ሦስተኛው ሰው ግን አንድ አነስተኛ መኪና ይዞ መጥቶ ለራሱ ቤተ ሰብና ለጐረቤቶቹ ለአንድ ወር ያህል የሚበቃ ምግብ ይዞ ሄደ፡፡

መለስተኛ መያዣ ይዞ መጥቶ የነበረውና በዚያው ዕቃ ምግብ የወሰደው ሰው፣ ባለ መኪናው ሰው በጣም ብዛት ያለው ምግብ ጭኖ በእርሱ ቤት በር በኩል ሲያልፍ ያያል፡፡ በጣም ተናደደ፤ እንዲያውም በጣም በሸቀ የሚሉት ቃሎች የተሰማውን ቁጣ ለመግለጽ የሚበቁ አይመስልም! አድልዎ እንደ ተፈጸመበት ለጐረቤቶቹና ላገኘው ሰው ሁሉ ተናገረ፤ በመጨረሻ ሰውየው እያወራ የነበረው ጄኔራሉ ጆሮ ይደርሳል፡፡ ጄኔራሉ ሰውየውን ያስጠራና፣ ‹‹የእኔ ወንድም፣ እናንተ መውሰድ የምትችሉን ያህል ምግብ ልንሰጣችሁ እንደምንችል ግልጽ አድርገን ነበር፡፡ ታዲያ፣ ለምንድነው ትንሽ መያዣ ይዘህ የመጣኸው? ለምን አንድ መለስተኛ የጭነት መኪና ይዘህ መጥተህ አልወሰድህም?›› አለው፡፡

አንድ ክርስቲያን ወደ እግዚአብሔር ጸጋ ሲመጣ መቀበያ ዕቃው ምንድነው? በኤፌሶን 3፥20 መሠረት፣ የምንለምነውና የምናስበው ነው፡፡ እግዚአብሔር፣ ‹‹የእኔ ጸጋ እናንተ ይዛችሁ ከምትመጡት ማንኛውም መያዣ እጅግ አብዝቶ ይበልጣል!›› እያለን ነው፡፡ በሌላ አነጋገር ወሰንና ገደብ ከሌለው የእግዚአብሔር ልግስና የምንወስደውን የሚወስነው እፊቱ ያቀረብነው መያዣ መጠን ነው ማለት ነው፡፡ በጣም ደፈር ብለን ለመናገር ያህል፣ እግዚአብሔርን የሚወስነው ይዘነው የመጣነው መያዣ ነው፡፡ ‹‹እንዴት ሊገኝ እንደሚችል ብቻ የምታስቡት ለምንድነው? ስለ ራሳችሁና ስለ ቤተ ሰባችሁ ብቻ የምታስቡት ለምንድነው? በውስጣችሁ ባኖርኩት ሙሉ ኃይል የማትጠቀሙትና ዳንኤል እንዳደረገው ሌሎች ሰዎች ላይ በጐ ተፅዕኖ የምታሳድሩት ለምንድነው?›› በማለት እግዚአብሔር እኔና እናንተን እየጠየቀ እንደ ሆነ አምናለሁ፡፡

እግዚአብሔርን የሚወስነው ይዘነው የመጣነው መያዣ ነው፡፡

‹‹ለእኛ ለምናምነው ከሁሉ በላይ ታላቅ የሆነውን ኃይሉን›› እንድናውቅና እንድንረዳ ጳውሎስ አጥብቆ የሚጸልየው በዚህ ምክንያት ነው (ኤፌሶን 1፥19)፡፡

እስቲ ጳውሎስ የተጠቀመባቸውን ቃሎች ልብ አድርጉ፤ *ከሁሉ በላይ፣ ገደብ ወይም መጠን የሌለው፣ ከአእምሮ በላይ የሆነ ታላቅ*፡፡ እግዚአብሔር ለእኛ ያለውን ኃይል በተመለከተ እነዚህ ቃሎች ምን ትርጒም ይሰጡዋችኃል? ጳውሎስ እየተናገረ ያለው፣ ‹‹እኛ ውስጥ›› ስላለ እንጂ፣ ከአንድ የተመረጠ አገልጋይ አልፎ አልፎ ስለምንቀበለው ኃይል አለመሆኑን አስተውሉ፡፡ ‹‹የእኛ የሆነ ኃይል›› ማለትም፣ በዚህ ሕይወት ላይ መንገሥ እንድንችል የሚረዳን ዐቅም፣ ብቃት የሚሆነንም ኃይል ነው፡፡ ሰዎች የኢየሱስ ክርስቶስ ትንሣኤ ማስረጃ የሚሆን ነገር ከሕይወታችን ማየት እንዲችሉ፣ ወደ ላይ ከፍ የሚያደርገንና ራሳችንን መለየት የሚያስችለንም ኃይል ነው፡፡ በድንግዝግዙ ዓለም ውስጥ ደምቀን ማብራት የሚስችለን ኃይል ነው፡፡

እንግዲህ፣ ኢየሱስ ከፍ ያለ ዋጋ ከከፈለበት ደረጃ በጣም ዝቅ ያለ ሕይወት እየኖርን ይሆን? በማለት ራሳችንን መጠየቅ አለብን፡፡ ግልጽና እውነተኞች ከሆንን መልሳችን አዎን ነው መሆን ያለበት፡፡ ራሳችን በራሳችን ላይ ያመጣነው እንደ ነገሩ የሆነ አኗኗራችን ያለንበትን አካባቢ ለክርስቶስ እንዳንማርክ ተፅዕኖ አድርጎብናል፡፡

ብዙ ጊዜ እምነት በሌለበት ዓለማዊ አኗኗር መንገድ የምንኖረው ለምንድነው? ለምሳሌ ያህል የዕቃዎች ዋጋ ሲያሻቅብና ነገሮች ከጠበቅነው ውጪ ሲሆኑ፣ እንደ ሌሎች የምንፈራውና የምንናወጠው ለምንድነው? አንዳንዴ ሳስበው ፊልጵስዩስ 4፥19ን ‹‹የብር የመግዛት ዋጋ ሲስተካከል አምላኬ የሚያስፈልጋችሁን ሁሉ ይሞላባችኃል›› በሚል መልኩ የተረዳነው ይመስላል፡፡ ይሁን እንጂ፣ ከእግዚአብሔር ቃል ስናጠና ከነበረው እውነት አንጻር፣ የጨለማ ጊዜ የበለጠ ደምቀን የምናበራበት ጊዜ ነው! ዕጦት ወይም ችግር አለ ማለት ነገሮች ሁሉ ከዓለም ጠፍተዋል ማለት አይደለም፡፡ ሐሳብ አይታገድም፤ የፈጠራ ችሎታ ምንጭ አይደርቅም፤ አዳዲስ ነገሮችን ማፍለቅም ሆነ በርትቶ መሥራት ከምድር ድራሹ አይጠፋም፡፡ እንዲህ ያለው የጨለማ ጊዜ ሰዎችን መርዳት የሚችል የእግዚአብሔር ኃይል ሲያበራልን፣ የእርሱ ሕዝብ ወደ መድረኩ ብቅ ብለው መፍትሔ የሚሰጡበት ጊዜ ነው፡፡ የኢኮኖሚ ችግር መጣ ማለት የተለመደው የገንዘብ መተላለፊያ መንገድ ታውኮአል ወይም ተቋርጦአል፣ አሁን የሚያስፈልገው አዳዲስ መንገዶችና አዳዲስ ሐሳቦች ናቸው ማለት ነው፡፡ እነዚያን አዳዲስ

መንገዶችና አዳዲስ ሐሳቦች ይዘን መምጣት ያለብን እኔና እናንተ መሆን ነበረብኝ፤ ምክንያቱም የፈጠራና አዳዲስ ሐሳብ የማፍለቅ ችሎታችን ጨርሶ የማይደርቅ በመሆኑ!

በ1920ዎቹ ዓመታት እሚ ሴምፕል ምክፐርሰን መሐል ሎስ አንጀለስ ከተማ ላይ አምስት ሺህ ሕዝብ መያዝ የሚችል አዳራሽ ለመሥራት ስትነሣ፣ ምናልባት በዚያ ዘመን ሴት ልጅ ያንን ማድረግ እንደማትችል ሳይነገራት አልቀረም፡፡ ጊዜው ታላቁ የኢኮኖሚ ድቀት ዓለምን የመታበት ጊዜ ስለ ነበር፣ ለሥራው የሚያስፈልጉ ነገሮችን ማሟላት ከባድ እንደ ሆነ ሳይነገራትም አልቀረም፡፡ እርሷ ግን አድርጋው ተገኘች፡፡ እዚያ አዳራሽ ውስጥ ሰብኬ አውቃለሁ፤ አሁንም ቢሆን እዚያ ክርስቲያኖች ይሰበሰባሉ፡፡ እርሷ በምትሰብክበት ጊዜ የምትጠቀምባቸውን አስደናቂ ምሳሌዎች ሰምተው ሐሳብ ለማግኘት የሆሊውድ ፊልም ሠሪዎች ሹልክ ብለው ወደ እሚ የእሑድ ምሽት አገልግሎት ይመጡ እንደ ነበር ይነገራል፡፡ ከእርሷ የሚሰሟቸውን ምሳሌዎች ለሆሊውድ የሚስማማ አድርገው ይጠቀሙባቸው ነበር፡፡ እሚ እንደ ብርሃን እያበራች፣ በዙሪያ ያለው ዓለም ላይ ተፅዕኖ አሳድራ ነበር፡፡

የእሚን አገልግሎት ቀደም ሲል ካየሁት የቲቪ ፕሮግራም ጋር አነጻጽራለሁ፡፡ አንድ ሰው ብዙ ሕዝብ ፊት ቆሞ፣ ‹‹አስደናቂ ጸጋ›› የተሰኘውን መዝሙር እየዘመረ ነበር፡፡ ፊት ለፊቱ ሦስት ዳኞች ተቀምጠዋል፡፡ ሰውየው ዘምሮ ሲያበቃ፣ ዳኞቹ ድምፅና አዘማመሩን በተመለከተ አስተያየት መስጠት ጀመሩ፡፡ ‹‹ድምፅህ ለክፉ አይሰጥም፤ ትንሽ ቢሞረድ ጥሩ ይሆን ነበር፤ እጅህን ባታወዛውዝ ይሻል ነበር. . .›› በማለት ሲናገሩ እኔ ከፍቶኝ ነበር፡፡

በጣም አዝኜ፣ ‹‹እግዚአብሔር ሆይ አንተ አጽናፈ ዓለሙን ፈጥረሃል፡፡ የሚታየውንና የማይታየውን ዓለም የፈጠርህ አንተ ነህ፤ አስደናቂ የባሕር ውስጥ ፍጥረቶችን የፈጠርህ አንተ ነህ፡፡ አንተ በመንፈስህ አማካይነት እኛ ውስጥ ትኖራለህ፡፡ ይሁን እንጂ፣ እነርሱ ወደ እኛ መምጣት ሲገባቸው ተነሳሽነት ለማግኘት እኛ ወደ አሜሪካን አይዶል እየሄድን ነው!›› በማለት ጸለይኩ፡፡ እስቲ አስቡ፤ እሚ በፈጠራ ችሎታዋ ሆሊውድ ላይ ተፅዕኖ አሳድራ ነበር፤ እኛ ውስጥ ያለው ጸጋ ግን እምቅ ብቻ ሆኖ በመቀመጡ፣ ተነሣሽነትና ራእይ ከሆሊውድ እንቀላውጣለን፡፡

ይህን አስመልክቶ ረዘም ያለ ጊዜ ወስጄ ነበር ያሰብኩበት፡፡ በመጨረሻም፣ ‹‹አዎን፣ ጸጋ ኃጢአታችን ይቅር የሚባልበትና ወደ መንግሥተ ሰማይ የምንገባበት ነው በማለት ብቻ የምናስተምር ከሆነ፣ በዚህ

ዓለም ብርሃን መሆን አይቻለንም›› የሚል መደምደሚያ ላይ ደረስኩ፡፡ በዓለም ዓይን መሳቂያና መሳለቂያ እንድንሆን እግዚአብሔር አሳልፎ የሰጠንም ይመስላል፡፡ የምንፈልገው ጣፋጭና ለሁሉም የሚመች መልእክት ማቅረብ በመሆኑ፣ በእምነት መጽናት ወይም በእምነት መዋጋት አይጠይቀንም፡፡ ይህን ሁሉ እየታዘበ ያለው እግዚአብሔር፣ ‹‹የገዛ ራሳችሁ ጥበብ የሚያመጣባችሁ እፍረት እንዲደርስባችሁ አደርጋለሁ›› በማለት የፈረደብንም ይመስላል፡፡

እግዚአብሔር ቃሉ ውስጥ የሰጠው ተስፋ ተፈጻሚ እንዲሆን እኛ ማሟላት ያለብንን አስመልክቶ የተናገረውን ያላመንነው ለምንድነው? ሕይወታችንን በእርሱ እውነት መሠረት ከመኖር ይልቅ፣ የእርሱ ሐሳብ ከእኛ አኗኗር ጋር እንዲስማማ ለማድረግ የምንሞክረው ለምንድነው?

## ጸጋን በተመለከተ የእኔ ተመክሮ

የሁለተኛ ደረጃ ተማሪ በነበርኩበት ዘመን በጣም የሚከብደኝ ትምህርት እንግሊዝኛ በተለይም ደግሞ የፈጠራ ጹሑፌነት ነበር፡፡ ጽሑፌትን የሚጨምር አንድ የቤት ሥራ (አሳይንመንት) ከተሰጠኝ በጣም ነበር ግራ የምጋባው፡፡ አንድ ወይም ሁለት ገጽ ለመጻፍ በጥቂቱ ሦስት ወይም አራት ሰዓት ያስፈልገኝ ነበር፡፡ እንዴት እንደምጀምር እያወጣሁና እያወረድሁ ባዶው ወረቀት ላይ ረዘም ላለ ጊዜ አፈጥበት ነበር፡፡ (በዚያ ዘመን እንዳሁኑ የግል ኮምፒዩተርና አይፓድ አልነበረም!) በመጨረሻ አንድ ዐረፍተ ነገር ይመጣልኝና እጽፈዋለሁ፤ ትንሽ ቆየት ብዬ የጻፍኩ ያስጠላኝና ወረቀቱን እቀዳድደዋለሁ፡፡ በሚቀጥለው ሙከራዬ ምናልባት፣ ሁለት ዐረፍተ ነገሮች ይመጡልኝና እጽፋለሁ፤ ሆኖም፣ ብዙም ሳይቆይ አስቀያሚ ይሆኑብኝና ወረቀቱን ጨባብጬ እጥለዋለሁ፡፡ በዚህ ሂደት ብዙ ወረቀቶችና ረጅም ጊዜ ይባክን ነበር፡፡ ከአንድ ሰዓት ወይም ከዚያ በኋላ ምናልባት አንድ ወይም ሁለት ጥሩ የሚመስሉ አንቀጾች እጽፋለሁ፡፡ የኋላ ኋላ ግን እነዚያ በእኔ ዐይን ጥሩ የመሰሉ ጽሑፎች፣ አስተማሪው ፊት ሲቀርቡ እጅግ የወረደ ውጤት ነበር የሚያገኙት፡፡

አንዳንዴም፣ በሚቀጥለው ዓመት እዚሁ ክፍል እንዳያገኘን ሲል ብቻ የእንግሊዝኛ አስተማሪዬ ጥሩ ውጤት ሰጥቶ ቢያሳልፈን ምን ነበረበት በማለት አስባለሁ፡፡ እንዲህ ስል ምናልባት እያጋነንኩ ይመስላችሁ ይሆን? እውነቱ ግን የSat ፈተናን በተመለከተ በእንግሊዝኛ ከ800-370 ብቻ ማግኘቴ ነው፡፡ ያ ማለት ከሚጠበቀው ወይም ከሚፈለገው 46 እጅ ማለት ነው፡፡ እንደ መታደል ሆኖ ግን በሒሳብና በሳይንስ ጥሩ ችሎታ ነበረኝ፤ ያ

ፑርዱ ዩኒቨርስቲ በዋነኛነት መሐንዲስነት ለመማር ተቀባይነት እንዳገኝ አድርጎአል፡፡

ስለዚህም በ1991 ዓ.ም ጸሎት ላይ እያለሁ፣ ‹‹ልጄ ሆይ፣ እንድትጽፍ እፈልጋለሁ›› በማለት እግዚአብሔር ሲናገረኝ በጣም ነበር የደነገጥኩት፡፡ መቼም እግዚአብሔር በዚህ ፕላኔት በጣም ብዙ ልጆች አሉት፤ ስለሆነም መልእክቱ ለእኔ ሳይሆን፣ ለሌላ ሰው ሊሆን እንደሚችል ሳላስብም አልቀረሁም፡፡

ዛሬ ላይ ሆኜ ይህን ስነግራችሁ እፍረት ይሰማኛል፤ እግዚአብሔር የነገረኝ የሚታመን መስሎ ስላልታየኝ ምንም ሳላደርግ ቀረሁ፡፡ በዚያ ዘመን የእግዚአብሔር ጸጋ የማስቻልና የማብቃት ዐቅምን በተመለከተ አሁን እያካፈልኳችሁ ያለሁት ዕውቀት አልነበረኝም፡፡

ከዐሥር ወር በኋላ በሁለት ሳምንት ጊዜ ውስጥ በተለያዩ የአሜሪካ ከተሞች ይኖሩ የነበሩ ሁለት ሴቶች ወደ እኔ መጡ፡፡ አንደኛዋ ከቴክሳስ፣ ሁለተኛዋ ከፍሎሪዳ ነበሩ፡፡ ምንም እንኳ እርስ በርስ የማይተዋወቁ ቢሆኑም፣ ሁለቱም የተናገሩት አንድ ዐይነት ነበር - ‹‹ጆን ቢቨሬ፣ እግዚአብሔር የሰጠህን መልእክት የማትጽፍ ከሆነ፣ ለሌላ ሰው ይሰጠዋል፤ አንተም ባለ መታዘዝህ ትቀጣበታለህ›› የሚል ነበር፡፡

ከሁለት ሳምንት በፊት ሰምቼው የነበረውን ማስጠንቀቂያ ሁለተኛዋ ሴት ስትናገር ስሰማ የእግዚአብሔር ፍርሃት ወደቀብኝ፡፡ መታዘዝ አለብኝ፣ መጻፍ አለብኝ አልኩ! ይሁን እንጂ፣ አሁንም ቢሆን ልቤ ውስጥ ጥርጥር ነበር፡፡ መጽሐፍ መጻፍ ቀርቶ አሥር ገጽ የሚወጣው ጽሑፍ ማርቀቅ እንኳ አልችልም ነበር፡፡ የማደርገው ግራ ቢገባኝ፣ ‹‹እግዚአብሔር ሆይ፣ የአንተ ጸጋ ያስፈልገኛል፤ አንተ ካላስቻልከኝ እኔ ይህን ማድረግ አልችልም›› በማለት አንድ ወረቀት ላይ ጻፍኩ፡፡ ይህ እንግዲህ፣ ከእግዚአብሔር ጋር ውል ማድረግ መሆኑ ነው! ከሥሩ ፊርማዬንና ቀኑን አሰፈርኩ፡፡

ከተወሰነ ጊዜ በኃላ ለመጻፍ ተቀመጥኩ፡፡ የጀመርኩት ዋና ዋና ነጥቡን በመጻፍ አልነበረም፤ ምክንያቱም እንዴት እንደምጀምርና የጀመርኩት የት እንደሚደርሰኝ ጨርሶ ሐሳቡ አልነበረኝም፡፡ ስለ አንድ ጉዳይ እንዲሁ ድፍን ያለ ሐሳብ ብቻ ነበር ያለኝ፡፡ በድንገት ከዚያ በፊት አስቤ፣ አስተምሬ፣ ወይም ሌላ ሰው ሲያስተምር ሰምቼ የማላውቃቸው ሐሳቦች ወደ አእምሮዬ መጡ፡፡ ሥራዬ መጻፍ… መጻፍ አሁንም… መጻፍ ሆነ፡፡ የኃላ ኃላ አንድ መጽሐፍ የሚወጣው ጽሑፍ ሆነ፡፡ ቀይቶ ሁለተኛውን ቀጥሎ ደግሞ ሦስተኛውን መጽሐፍ ጻፍኩ፡፡ እስከ ዛሬ የጻፍኩቸው

መጻሕፍት ዐሥራ አምስት ሆነዋል፤ ሁሉም በአንድነት ተጠቃለው በሚሊዮን የሚቆጠሩ ቅጂዎች ተሸጠዋል፤ አማርኛን ጨምሮ በዓለም ዙሪያ ባሉ ከስድሳ በላይ ቋንቋዎች ተተርጉመዋል፡፡ Drawing Near የተሰኘው አንድ መጽሐፌ የ2004 ዓ.ም ዓመታዊ ተመራጭ መጻሕፍት አንዱ ሆኖአል፤ በርካቶቹም በብሔራዊና በዓለም አቀፋዊ ደረጃ በከፍተኛ ብዛት ተሸጠዋል፡፡

የራሴን፣ ‹‹ተፈጥሮአዊ›› ችሎታ መሠረት አድርጌ ተነሥቼ ቢሆን ኖሮ፣ እዚህ ደረጃ ላይ መድረስ እንደማልችል ይታያችኃል? ያን ሁሉ ያደረገው የእግዚአብሔር ጸጋ ነው!

አንድ ጊዜ በአውሮፓ ከስምንት ሺህ በላይ ሰዎች በተሰበሰቡበት ቦታ ተገኝቼ ነበር፤ አብዛኞቹ ክርስቲያን መሪዎች ስለ ነበሩ ከመጽሐፎቼ አንዱን ያነበቡ ምን ያህሉ እንደ ነበሩ ጠየቅሁ፡፡ ሁሉም ሊባል በሚቻል መልኩ አብዛኞቹ እጃቸውን ማውጣታቸውን ስመለከት በጣም ተደነቅሁ፡፡ በምሥራቅ አውሮፓ ተደርጐ በነበረ ዓለም አቀፍ ኮንፈረንስ ተገኝተው ለነበሩ ከስድሳ ከሚበልጡ አገሮች ለመጡ ስድስት ሺህ መሪዎች በገዛ ቋንቋቸው ከታተመው ከመጽሐፎቼ ቢያንስ አንዱን አንብበው እንደ ሆነ የስብሰባው አዘጋጅ ጠይቆአቸው ነበር፡፡ 90 እጅ ያህል እጃቸውን ሲያወጡ ማየት በእርግጥም እጅግ የሚገርም ነበር፡፡ በኢራን የነበሩ መጻሕፍት አሳታሚች በአንድ ወቅት፣ ‹‹መጻሕፍቶቻቸው በመላው ኢራን ከሚነበብላቸው ክርስቲያን ደራሲዎች አንዱ አንተ ነህ›› በማለት ነግረውኝ ነበር፡፡ (በዚያ ጊዜ ሰባት መጻሕፍቶቼ በኢራን ብሔራዊ ቋንቋ በፋርሲ ታትመው ነበር)፡፡ ከተለያዩ አገሮች እንዲህ ያሉ ሪፖርቶች መምጣት ቀጥለዋል፡፡ እኔ ግን እንዴት ድንቅ ጸጋ ነው! እያልኩ ነው፡፡

ልቤ ውስጥ ካሉ ምኞቶች አንዱን ላካፍላችሁ - እነዚያን የሁለተኛ ደረጃ የእንግሊዝኛ አስተማሪዎቼን አግኝቼ በእግዚአብሔር ጸጋ የጻፍኩዋቸውን ዐሥራ አምስቱን መጽሐፎች ላሳያቸው እፈልጋለሁ፤ ከዚያም ወደ ክርስቶስ ልመራቸው እፈልጋለሁ፡፡ የሥራው ፍሬ በእነርሱ ዐይን የተለየሁ ያደርገኛል፤ የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ አስደናቂ ጸጋ ግልጽ ማሳያም ይሆናል!

‹‹በእግዚአብሔር ጸጋ አሁን የሆንሁትን ሆኛለሁ›› በማለት ጳውሎስ በልበ ሙሉነት የተናገረው ከዚህ የተነሣ ነበር (1ቆሮንቶስ 15፥10)፡፡ የተወደዳችሁ አንባቢዎች ስሙኝ፣ አሁን የሆናችሁትን የሆናችት ከእነማን በመወለዳችሁ አይደለም፤ በየትኛው አካባቢ በማደጋችሁ፤ ከየትኛው ዘር በመሆናችሁ፣ የት ወይም እንዴት በመማራችሁ አይደለም፤ የትኛው ዐይነት

ጸጋ ስላላችሁ አይደለም፡ አሁን የሆናችሁትን የሆናችሁት በእግዚአብሔር ጸጋ ነው!

ቀደም ባለው ሕይወቴ ሕዝብ ፊት ንግግር በማድረግ በጣም ደካማ ነበርኩ፡፡ እኔና ሊዛ ከተጋባን በኋላ ወንጌል ስሰብክ በሰማችበት በመጀመሪያው ቀን ገና ዐሥር ደቂቃ እንኳ ሳልሰብክ ድብን ያለ እንቅልፍ ይዟት ነበር፡፡ በጣም የምትቀርባት ጓደኛዋ አሚም ብትሆን እያንቀላፋች ስለ ነበር ማንኮራፋቷ ሌሎችን ሳይረብሽ አልቀረም! መልእክቴን አቅርቤ ስጨርስ ሁለቱም እንደ ተኙ ነበር፡፡

ከጥቂት ዓመት በፊት ሊዛ በ1984 ዓ.ም ስሰብክ የተቀዳ ቪዲዮ አግኝታ ነበር፡፡ ያንን ቪዲዮ ማጫወት በጀመረች ጥቂት ሰኮንዶች ውስጥ፣ ‹‹ሊዛ እባክሽን ጣዩው!›› እላት ነበር፡፡ እርሷ ግን በጣም እየሳቀች፣ ‹‹ይኸንማ አልጥለውም፣ አንተን ማስፈራሪያ ነው!›› ትለኝ ነበር፡፡ ዛሬ ግን በእግዚአብሔር ጸጋ በዓለም ዙሪያ ባሉ አምስት ሺህ፣ ዐሥር ሺህ፣ ሃያ ሺህ ከዚያም በላይ ሰዎች ፊት ሰብኬአለሁ፡፡ አንዳንዴ ሰዎች፣ ‹‹ከመናገርህ በፊት በጣም ትፈራለህ? ‹‹በማለት ይጠይቁኛል፡፡ ‹‹አልፈራም፤ በፍጹም አልፈራም›› እላቸዋለሁ፡፡

ብዙውን ጊዜ በምሰጣቸው መልስ ግራ በመጋባት፣ ‹‹ይህን ያህል ሕዝብ ፊት ስትቆም የማትፈራው ለምንድነው?›› ይሉኛል፡፡

እኔም፣ ‹‹ምን ያህል ደካማ መሆኔን አውቃለሁ፤ የእግዚአብሔር ጸጋ ባይገለጥ ኖሮ፣ ሁላችንም ለምንም የማንበቃ እንሆን ነበር›› በማለት እነግራቸዋለሁ፡፡ አሁን የእግዚአብሔርን ጸጋ አውቃለሁ፤ የእርሱ ጸጋ በፍጹም አያሳፍርም፤ ሁሌም በቦታው ነው!

ጳውሎስ፣ በተጠራችሁ ጊዜ፣ ‹‹በሰው መስፈርት ከእናንተ ብዙዎቻችሁ ዐዋቂዎች አልነበራችሁም፤ ብዙዎቻችሁም ከትልቅ ቤተ ሰብ አልተወለዳችሁም›› የሚለው በዚህ ምክንያት ነው (1ቆሮንቶስ 1፥26)፡፡ ለምን? ምክንያቱም ዐዋቂዎች፣ ኃያላንና ታላላቆች በእግዚአብሔር ጸጋ ከመታመን ይልቅ በራሳቸው ችሎታ ነው የሚተማመኑት፡፡

ቀደም ባለው ሕይወቱ ጳውሎስ ከጠቢባን አንዱ ነበረ፤ ከትልቅ ቤተ ሰብ ከተወለዱት አንዱ ነበር፡፡ ይህን አስመልክቶ ፊልጵስዩስ 3፥4 ላይ ሲናገር፣ ‹‹ማንም በሥጋ የሚመካበት ነገር ያለው ቢመስለው እኔ እበልጠዋለሁ›› ብሎ ነበር፡፡ ነገር ግን ጳውሎስ በጸጋ መታመንን መረጠ፤ ‹‹ይጠቅመኝ የነበረውን ሁሉ (ጥበብ፣ ብርታት፣ የትልቅ ሰው ዘር መሆን) አሁን ለክርስቶስ ስል እንደ ጉድለት ቈጥሬዋለሁ›› አለ (ፊልጵስዩስ 3፥7)፡፡

እነዚህ ሰብዓዊ ባሕርያት እንደ ከንቱ የተቆጠሩት ለምንድነው? ምክንያቱም ከራሱ ተፈጥሮአዊ ችሎታና ማንነት ይልቅ ጳውሎስ ያለ ክፍያ ባገኘው የክርስቶስ ትንሣኤ ጸጋ መመላለስ ፈለገ፤ ከዚህም የተነሣ፣ ‹‹ክርስቶንና የትንሣኤውን ኃይል እንዳውቅ…እፈልጋለሁ›› አለ (ቁጥር 10)፡፡ እንዲህ ሲባል፣ ጳውሎስ የራሱን ጥረት አላደረገም ማለት አይደለም፡፡ በሁሉም ረገድ ልቆ ለመገኘት በትጋት አጥንቷል፤ በጥበብና በመንፈሳዊ ማስተዋል ሁሉ፣ የእግዚአብሔርን ፈቃድ በማወቅ የተሞላ ሆኖ ይገኝ ዘንድ አጥብቆ ጸልዮአል፡፡ ማንኛችንም ማድረግ እንደሚገባን ሁሉ ጳውሎስም የራሱን ተሳትፎ አድርጎ ነበር፤ ይሁን እንጂ፣ መለኮታዊ የማብቃትና የማስቻል ዐቅም ማለትም የእግዚአብሔር ጸጋ ተፈጥሮአዊ ጥረቱን እንደሚያነሣሣለትም አምኗል፡፡

አንተ ወይም አንቺ ተማሪ ከሆናችሁ፣ በርትታችሁ አጥኑ፤ ይሁን እንጂ፣ በዚህ ሁሉ ውስጥ የራሳችሁ መረዳት ችሎታ ሊያደርሳችሁ ወደማይቻለው ሐሳብና ስኬት ደረጃ የእግዚአብሔር ጸጋ እንደሚያደርሳችሁ ማመን ይኖርባችኋል፡፡ ዶክተሮች ወይም የሕክምና ሰዎች ከሆናችሁ፣ ከዘመናዊው ሕክምና ሳይንስ ግኝት ጋር አብራችሁ መጓዝ አለባችሁ፤ ሆኖም ትምክህታችሁ ችሎታችሁ ወይም ትምህርታችሁ ላይ አይሁን፡፡ ትምክህታችሁ፣ ከሚታወቀው በላይ አልፋችሁ መሄድ እንድትችሉ በሚረዳችሁ ልዕለ ተፈጥሮአዊ ጥበብና የእግዚአብሔር ጸጋ መፍጠር ችሎታ ላይ መሆን አለበት፡፡ አትሌትክስን እንደ ሙያ የያዛችሁ ሰዎች ከሆናችሁ፣ በትጋት መሥራትና ልምምድ ማድረግ ይኖርባችኋል፤ ሆኖም ትምክህታችሁ አብረዋችሁ ካሉ የማያምኑ ሰዎች ሊያስበልጣችሁና ሊያልቃችሁ በሚችል የእግዚአብሔር ጸጋ ላይ ይሁን፡፡

የሚወደን ፈጣሪያችን እኛ ከመወለዳችን በፊት የእያንዳንዳችንን ሕይወት ታሪክ መጻፉን በዚህ መጽሐፍ መጀመሪያ ምዕራፍ ተመልክተን እንደ ነበር አስታወሳችሁ? ትዝ ይላችሁ ከሆነ ዳዊት፣ ‹‹ዐይኖችህ ገና ያልተበጀውን አካሌን አዩ፤ ለእኔ የተወሰኑልኝም ዘመናት ገና አንዳቸው ወደ መኖር ሳይመጡ በመጽሐፍ ተመዘገቡ›› በማለት መናገሩንም ተመልክተን ነበር (መዝሙር 139፥16)፡፡

እስቲ የሕይወት ታሪካችሁን በተመለከተ ልንገራችሁ፡፡ እግዚአብሔር የጻፈው ታሪካችሁን በራሳችሁ ችሎታ አሟልታችሁ መገኘት በፍጹም አትችሉም፡፡ እንዲያውም ያን ማድረግ ጨርሶ የማይታሰብ ነው፡፡ እግዚአብሔር የጻፈው የሕይወት ታሪካችሁን እናንተ በምታደርጉት ጥረት መፈጸም የምትችሉ ከሆነ ክብሩን ለእናንተ ማካፈል ሊኖርበት ነው፡፡

እግዚአብሔር ግን ያ እንዲሆን አይፈቅድም፡፡ ምክንያቱም ‹‹ክብሬን ለሌላ አልሰጥም›› በማለት በግልጽ ተናግሮአል (ኢሳይያስ 42፥8)፡፡ ስለዚህም፣ ከእናንተ ተፈጥሮ ችሎታ በላይ እግዚአብሔር የሕይወት ታሪካችሁን የጻፈው፣ ያንን መፈጸም በሚችል ጸጋው እንድትተማመኑ ሆን ብሎ በዓላማ ነበር ማለት ነው፡፡ ክብሩን ሁሉ የሚያገኘው በዚያ መንገድ ነው!

የጻፍኩዋቸው መጻሕፍትን በተመለከተ ለሰዎች የምነግረውም ይህንኑ ነው፡፡ የእነዚህ መጻሕፍት እውነተኛ ደራሲ ማን መሆኑን፣ ከእኔ ከራሴ በቀር የሚያውቅ የለም፡፡ በእኔ ችሎታ የተፈጠሩ አይደሉም፡፡ የእኔ ስም መጻሕፍቶቹ ላይ የተጻፈው ለመቀበል የመጀመሪያው ሰው በመሆኔ እንጂ የእኔ የራሴ ዕውቀት ውጤት ስለሆኑ አይደለም፡፡ በእርሱ ችሎታ፣ በእርሱ ጸጋ የሆንሁትን ሁሉ ሆንሁ እንጂ፣ ከእኔ የሆነ አይደለም፡፡ ነጻ የእግዚአብሔር ስጦታ ነው፡፡

አስደንጋጩ እውነት ግን፣ ቀድሞውኑ የተወሰነ የሕይወት ታሪካቸውን በሚገባ መፈጸም እንዲችሉ የማብቃትና የማስቻል ዐቅም ያለውን የእግዚአብሔር ጸጋ የተረዱ አማኞች ሁለት እጁ ብቻ መሆናቸው ነው፡፡ ታዲያ፣ 98 እጁ ጥሪያቸውን በገዛ ራሳቸው ችሎታ እንዴት መፈጸም ይችላሉ? በፍጹም፣ አይችሉም፡፡ በማኅበረ ሰባችን ላይ ሁነኛ ለውጥ ሲመጣ የማናየው በዚህ ምክንያት ይሆን?

## መግቢያው

በነጻ የሚሰጥ!

ይህ የምጽፍለት ኃይል፣ ይህ የእግዚአብሔር ጸጋ፣ በልፋት፣ በሽልማት ወይም የሚገባችሁ ስለሆናችሁ ወይም ብዙ ጥረት ስላደረጋችሁ የምትቀበሉት አይደለም፡፡ ጳውሎስ እንደሚያረጋግጠው ይህን ጸጋ መቀበል የሚቻለው በእምነት ብቻ ነው፤ ‹‹በእምነት፣ በጸጋ ድናችኃልና፤ ይህም የእግዚአብሔር ስጦታ ነው እንጂ ከእናንተ አይደለም፤ ማንም እንዳይመካ ከሥራ አይደለም›› (ኤፌሶን 2፥8-9)፡፡ በሮም ለነበሩ አማኞች ደግሞ፣ ‹‹በእርሱም በኩል አሁን ወደ ቆምንበት ጸጋ በእምነት መግባት ችለናል›› በማለት ጽፎላቸዋል (ሮሜ 5፥2)፡፡ ወደ እግዚአብሔር ጸጋ መግባትን የሰጠን ምንድነው? ጠንክረን መሥራታችን አይደለም፣ ጥሩ ሕይወት መኖራችን፣ በቀን የተወሰኑ ሰዓቶች መጸለያችን፣ በወር የተወሰኑ ቀኖች መጾማችን አይደለም - በምናደርገው ብርቱ ጥረትም አይደለም፡፡ ወደዚህ ጸጋ መግባት ያገኘነው በእምነት ብቻ ነው!

ታዲያ፣ በቀላሉ ማመን ያቃተን ለምንድነው? እስቲ በዚህ መልኩ እንየው፡፡ ንጹሕ ውሃ የምታገኙበት ምንጭ ከደረቀ ችግር ላይ ናችሁ ማለት ነው፡፡ ንጹሕ ውሃ ካጣችሁ እናንተም ሆናችሁ ቤተ ሰባችሁ በጥቂት ቀኖች ውስጥ ትሞታላችሁ፡፡ ግን ከመንገዱ ማዶ ከተማው ውስጥ ሚሊዮን ጋሎኖች ንጹሕ ውሃ የሞላበት ግዙፍ ግድብ አለ፤ ከዚያ ግድብ ዋና ዋና ቧንቧዎች አንዱ በቤታችሁ በር በኩል ያልፋል እንበል፡፡ ታዲያ፣ ምንድነው የምታደርጉት? ወደ ውሃና ፍሳሽ አገልግሎት ቢሮ ሄዳችሁ ችግራችሁን ትናገራላችሁ፤ እነርሱም የቧንቧ መስመር ይዘረጉላችኃል፡፡ ያኔ እናንተም ሆናችሁ ቤተ ሰባችሁ ሚሊዮን ጋሎኖች ንጹሕ ውሃ ከያዘው ግድብ የመጠቀም (የመግባት) መብት ይኖራችኃል፡፡ ቀለል ባለ አነጋገር እምነት ጸጋ በሚተላለፍበት የውሃ ቧንቧ ይመስላል፡፡ ስለዚህም ሮሜ 5፥2ን በዚህ ብርሃን ስናነብ፣ ‹‹በእምነት ቧንቧ በኩል የሚስፈልገን የጸጋ ውሃ ከሚተላለፍበት ግድብ የመጠቀም (የመግባት) መብት አለን›› በማለት ማንበብ እንችላለን ማለት ነው፡፡ ያን ያህል ቀላል ነው - የሚያስችል፣ ብቃት የሚሰጥ፣ ጸጋ የሚገኘው በእምነት በኩል ብቻ ነው፡፡ የዕብራውያን መልእክት ጸሐፊ፣ ‹‹ለእነዚያ እንደ ተሰበከ ለእኛም ደግሞ የምሥራቹ ቃል ተሰብኮልናልና፡፡ ነገር ግን ሰሚዎቹ ቃሉን ከእምነት ጋር ስላላዋሐዱት አልጠቀማቸውም›› በማለት የሚናገረው በዚህ ምክንያት ነው (4፥2)፡፡

እየተናገረ ያለው ስለ አብርሃም ዘሮች - ስለ የእግዚአብሔር ተስፋ ቃል ወራሾች ነው፡፡ በምሳሌያዊ አነጋገር፣ የሰማይ ኃይልና ልግስና ሁሉ በቤታቸው ወይም በድንኳናቸው ደጅ እያለፈ ነበር፡፡ ይሁን እንጂ፣ ቃሉ የገባውን ተስፋ ለመቀበል፣ ‹‹የእምነት ቧንቧቸውን›› ስላላስገጠሙ እግዚአብሔር በነጻ የሰጠው በረከት ተጠቃሚ መሆን አልቻሉም፡፡

እንግዲህ ከዚሁ አንጻር የእግዚአብሔር ጸጋ ከተፈጥሮአዊ ችሎታችን በላይ እንድናደርግ፣ ታላላቅ ነገሮችንም በማድረግ በዚህ ዓለም ጨለማ ደምቀን እንድናበራ የሚያስችለን ወይም የሚያበቃን ኃይል መሆኑን የተገነዘቡ ሁለት እጅ የሆኑት አማኞች ብቻ ከሆኑ ታዲያ፣ እኛ እንደ ቤተ ክርስቲያን ማመን የምንችለው እንዴት ነው? እንዴት ነው መሳተፍ የምንችለው? ጳውሎስ በዚህ መልኩ ነው ያስቀመጠው፣ ‹‹ስለ እርሱስ ሳይሰሙ እንዴት ያምኑበታል? ሰባኪ ሳይኖር እንዴት መስማት ይችላሉ›› (ሮሜ 10፥14)፡፡

መቼም ቢሆን፣ ያላወቅነውን ማመን አንችልም፡፡

እንግዲህ እኛ ክርስቲያኖች ችሎታ/ብቃት ስለሚሰጥ

የእግዚአብሔር ጸጋ፣ ቃሉ የሚናገረውን ካላወቅን እንዴት ማመን እንችላለን? መቼም ቢሆን፣ ያላወቅነውን ማመን አንችልም፡፡ ከጸጋው ጋር የሚያያይዘን ብንቢ ከሌለ ቃሉ ውስጥ የተገባው ተስፋ ተጠቃሚ አንሆንም፡፡

ይህ እግዚአብሔርን ያሳዝነዋል፡፡ ዳንኤልና መጥምቁ ዮሐንስ ማድረግ ከቻሉት በላይ አልፈን እንድንሄድ – የበዛና የተትረፈረፈ ሕይወቱ፣ ሕያው ምሳሌ እንድንሆን ኢየሱስ እጅግ ታላቅ ዋጋ ከፍሎአል፡፡ ያም ሆኖ ግን፣ የኃጢአት ይቅርታ የሚሰጠንና ከችግር የሚያወጣን ብቻ እንደ ሆነ በማመን ትክክለኛ መልእክቱን አፍነነዋል፡፡ እነዚህ ድንቅ ስጦታዎች ቢሆኑም፣ እዚህና አሁን የእግዚአብሔርን ጸጋ በሙላት ለመለማመድ፣ የእግዚአብሔርን ቃል ተግባራዊ ማድረግን ዘንግተናል፡፡ ስለዚህም በዚህ ጨለማ ዓለም የእግዚአብሔርን ሥራ መሥራት አልቻልንም፤ ለእርሱ ክብር ጽናት ያለው ሕይወት መኖር አልቻልንም፡፡

በኋላ ላይ የኢየሱስ ተከታዮች፣ ‹‹የእግዚአብሔርን ሥራ ለመሥራት ምን ማድረግ አለብን?›› በማለት ጠይቀው ነበር (ዮሐንስ 6፥28)፡፡ ግራ ተጋብተዋል፡፡ እነርሱም እንደ ኢየሱስ በእግዚአብሔር ኃይል የተሞዳውን የሰው ልጅ መርዳት ፈልገው ነበር፡፡ ኢየሱስም ቢሆን የእርሱን ምሳሌ እንዲከተሉ ነገሮአቸው ነበር፡፡ በጣም ግራ በመጋባት፣ ‹‹አንተ የምታደርገውን ማድረግ የምንችለው እንዴት ነው?›› በማለት ላቀረቡት ጥያቄ ኢየሱስ የሰጠው አጭር መልስ፣ ‹‹እመኑ!›› የሚል ነበር (ዮሐንስ 6፥29)፡፡

ይኸው ነው፡፡ እምነት! ለመቀበል የሚያስፈልገው የእግዚአብሔርን፣ ‹‹ጸጋ ቃል›› ማመን ብቻ ነው፡፡ ጳውሎስ የኤፌሶን አማኞችን የተሰናበተው፣ ‹‹አሁንም ለእግዚአብሔር፣ እንዲሁም ሊያንጻችሁና በቅዱሳን ሁሉ መካከል ርስት ሊያወርሳችሁ ለሚችለው ለጸጋው ቃል ዐደራ እሰጣችኋለሁ›› በማለት ነበር (ሐዋርያት ሥራ 20፥32)፡፡

ጳውሎስ እነዚያ ወዳጆቹን ትቶ ሊሄድ ነው፤ ከእንግዲህ በዚህ ዓለም በድጋሚ እንደማይገናኙ አውቋል፡፡ የምትናገሩ የመጨረሻውን ቃል መሆኑን ካወቃችሁ ለምትወዷቸው ሰዎች ትታችሁ የምታልፉትን ቃል በተመለከተ በጣም ጥንቃቄ ታደርጋላችሁ፡፡ ለእግዚአብሔር ብቻ ሳይሆን፣ ‹‹ለጸጋውም ቃል›› ጭምር ጳውሎስ ዐደራ ሰጣቸው፡፡

በዚህ ዘመን ብዙ ቀና አመለካከት ያላቸው ክርስቲያኖች፣ ‹‹በእግዚአብሔር እመኑ›› ወይም፣ ‹‹የሚያስፈልጋችሁ የእግዚአብሔር በሕይወታችሁ መኖር ብቻ ነው›› ወይም፣ ‹‹ወደ እግዚአብሔር መጠጋት

ይኖርባችኋል›› የሚሉትን የመሳሰሉ ጥሩ ጥሩ ነገሮች ሲናገሩ እሰማለሁ፡፡ እንዲህ ያለው አባባል ሰዎችን ወደ ትክክለኛ አቅጣጫ የሚጠቁም ቢሆንም፣ የተሟላ አይደለም፡፡ ጳውሎስ አማኝ ወዳጆቹን በዐደራ የሰጠው ለእግዚአብሔር ብቻ ሳይሆን ‹‹ለጸጋውም ቃል›› ጭምር ነበር፡፡ የእግዚአብሔር ጸጋ ያንጸናል፤ ርስት ያሰጠናል፡፡ የእናንተ ርስት ምንድነው? ገና ከመወለዳችሁ በፊት እግዚአብሔር የጻፈው የሕይወት ታሪካችሁ ነው!

ጸጋን በተመለከተ የተሟላ ትምህርት ባለ መሰጠቱ ብዙ ክርስቲያኖች (በትክክል ለማስቀመጥ 98 እጁ) አስደናቂ የእግዚአብሔርን ማስቻልና ብቁ የማድረግ ኃይል መለማመድ የምንችለው፣ የሚገባንን ያህል ከጾምን፣ ወይም በክርስቲያናዊ አገልግሎት ብዙ ትጋት ካሳየን፣ ወይም የተቀደሰ አኗኗር ከኖርን ብቻ እንደ ሆነ ያስባሉ፡፡ የዚህ ያልተሟላ አመለካከት አንዱ ችግር በቂ የሚባለው የት ላይ ሲደርስ መሆኑን አለማወቃችን ነው፡፡ ከዚህም የተነሣ ጳውሎስ የገላትያ ክርስቲያኖችን እንዲህ በማለት በጥያቄ አፋጥጦአቸው ነበር፣

> እግዚአብሔር መንፈሱን የሚሰጣችሁ፣ በእናንተም ዘንድ ታምራትን የሚሠራው፣ ሕግን ስለ ጠበቃችሁ ነው ወይስ የሰማችሁትን ስላመናችሁ? (ገላትያ 3÷5)፡፡

እግዚአብሔርን በተመለከተ ሕግን መጠበቃችን ብቻ የትም አያደርሰንም፣ ምክንያቱም ይህ ማሳየት የሚችለው የእኛን ብርታትና ጥረት ብቻ ነው፡፡ የዚህ ምዕራፍ ትምህርት ነጻ ወደ ሆነው፣ የማብቃት/የማስቻል ዐቅም ወዳለው ጸጋ ለመግባት ወሳኙ ነጥብ፣ በእምነት ጸጋውን መቀበልና ጸጋውን በእምነት ተግባራዊ ማድረግ ነው፡፡

መጀመሪያ ከዳናችሁበት መንገድ የተለየ አይደለም፡፡ እስቲ የጳውሎስን አቀራረብ እዩ፣ ‹‹ከእናንተ ዘንድ አንድ ነገር ብቻ ማወቅ እፈልጋለሁ፤ መንፈሱን የተቀበላችሁት ሕግን በመጠበቅ ነው ወይስ የተሰበከላችሁን በማመን?›› (ገላትያ 3÷2)፡፡

በማመንና ምላሽ በመስጠት፣ መጀመሪያውኑ በጸጋ በዳንንበት ሁኔታ አሁንም ጉዞአችንን ለመቀጠል በጸጋ መኖር አለብን፡፡

## ትንሽ የውሻ ቡችላ ወይስ ግዙፍ አጥቂ ድብ?

ይህ ምዕራፍ 3 ላይ አንሥተነው ወደ ነበረ ጥያቄ ይመልሰናል፡፡ በእምነታችንና በጉዞአችን ጽናት እንዲኖረን የሚረዳ ኃይልና ችሎታ አለን? በሕይወታችን የቱን ነው የምንመስለው፣ ትንሽ የውሻ ቡችላ ወይስ ግዙፍ

አጥቂ ድብ? እስካሁን ስናጠና ከነበረው መጽሐፍ ቅዱሳዊ እውነት አንጻር እኔና እናንተ አጥቂውን ድብ መምሰል እንዳለብን እንደምትስማሙ ተስፋ አደርጋለሁ፡፡ በአእምሮአችንና በልባችን ይህን መታመን በመያዝ ጽናት ያለው ሕይወት ምን ማለት እንደ ሆነ የጀመርነውን ጥናት እንቀጥል!

# 6

# ማየት ወይስ መግባት

*የጸጋን ብዛትና የጽድቅን ስጦታ ብዛት የሚቀበሉ በአንዱ በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል በሕይወት ይነግሣሉ፡፡*

*ሮሜ 5፥17*

ሮሜ 5፥17ን ደጋግሜ ፊት ለፊታችሁ ባኖርላችሁ ልክ እንደ ዮሐንስ 3፥16 ሁሉ አእምሮአችሁ ውስጥ እንደሚታተም ተስፋ አደርጋለሁ፡፡ ምናልባትም ሕይወት ላይ እንድትነግሡ የእግዚአብሔር ፈቃድ መሆኑን በጥልቅ ልቦናችሁ በማወቅ የኃላ ኃላ በእንቅልፍ ውስጥ እያላች እንኳ ጥቅሱን ደጋግማችሁ ትጠቅሱት ይሆናል፡፡ በሚገባ ለመጨረስ፣ ‹‹አሸናፊ›› እና ጽኑ አማኝ ለመሆን፣ ይህ ጽኑ እምነት እጅግ አስፈላጊ ነው፡፡

ወደ ፊት ከመግፋታችን በፊት፣ እስከ አሁን የተመለከትናቸውን መሠረታዊ እውነቶች ጥቂቶቹን እንደ ገና ላቅርብላችሁ – የእግዚአብሔርን ጸጋ ነጻ ስጦታ የተቀበሉ ሁሉ፣ በዚህ ሕይወት ልቀው የሚወጡበትን ዐቅም ይቀበላሉ፡፡ በሕይወት በሚገጥሙን ሁኔታዎች ራስ እንጂ ጅራት መሆን የለብንም፤ ከላይ እንጂ ከታች መሆን የለብንም፡፡ እግዚአብሔር የሚፈልገውን አኗኗር መንገድ ለዚህ ምድር በማስተዋወቅ፣ ተፅዕኖ ፈጣሪዎችና የመንግሥቱ ምሳሌዎች መሆን አለብን፡፡

## አብዛኞቹ ክርስቲያኖች በሕይወት የማይነግሡት ለምንድነው?

ክርስቲያኖች ሁሉ በዚህ ሁኔታ የማይኖሩት ለምንድነው? አብዛኞቹ ክርስቲያኖች ሕይወት ላይ ከመንገሥ ይልቅ ሕይወት የሚነግሥባቸው ለምንድነው?

የመጀመሪያውንና በጣም ግልጽ የሆነውን መልስ ተመልክተን ነበር፡፡ በ2009 በተደረገ ጥናታዊ ዳሰሳ 98% ክርስቲያኖች የእግዚአብሔር ጸጋ፣ የእርሱ የማስቻልና ዐቅም የመሆን ኃይል እንደ ሆነ አልተረዱም፡፡ ይህ አሐዝ በመላው ዓለም ያሉ አብያተ ክርስቲያናትንም ሊወክል እንደሚችል

አስባለሁ፡፡ በጸጋ አማካይነት እግዚአብሔር ያዘጋጀውን ልዕለ ተፈጥሮአዊ ኃይል ባለ ማወቃቸው አብዛኞቹ አማኞች እግዚአብሔር እንዲኖሩ ባቀደው ሁኔታ እየኖሩ አይደለም፡፡ ያ ብርቱ ላንድ ሮቨር መኪና ቢኖራቸውም፣ ለመጓጓዣነት ስላለው ጠቀሜታ ምንም ዕውቀት እንዳልነበራቸው እንደ እነዚያ አፍሪካውያን ሆነዋል፡፡ ላንድ ሮቨርን የመሰለ ድንቅ መጓጓዣ ቢኖራቸውም፣ አሁንም በትከሻቸው ከባድ ሸክም ተሸክመው በእግራቸው ረጅም ርቀት ይጓዛሉ፡፡

ክርስቲያኖች በሕይወት የማይነግሡበት ሁለተኛው ምክንያት፣ የተቀረው የዚህ መጽሐፍ ትኩረት ይሆናል፡፡ ከጌታ ለመጠየቅ በድብቅ መጥቶ ለነበረው ኒቆዲሞስ ለሚባለው የአይሁድ አለቃ ኢየሱስ በነገረው ቃል እንጀምራለን፡፡ ኢየሱስ በመጀመሪያ የነገረው፣ ‹‹እውነት እልሃለሁ፤ ማንም ዳግመኛ ካልተወለደ በቀር የእግዚአብሔርን መንግሥት ሊያይ አይችልም›› የሚል ነበር (ዮሐንስ 3፥3)፡፡

ኢየሱስ መንግሥቱን ስለ ማየት ተናገረ፡፡ በመቀጠል ለኒቆዲሞስ የነገረው ግን፣ ፍጹም ልዩ ስለ ሆነ ነገር ያመለክታል፡፡ ‹‹እውነት እልሃለሁ ማንም ከውሃና ከመንፈስ ካልተወለደ በቀር ወደ እግዚአብሔር መንግሥት ሊገባ አይችልም›› (ዮሐንስ 3፥5)፡፡ ኢየሱስ አጽንዖቱን የእግዚአብሔርን መንግሥት ከማየት (ቁጥር 3) ወደ እግዚአብሔር መንግሥት ወደ መግባት (ቁጥር 5) ያዛወረው ለምንድነው? የመጽሐፍ ቅዱስ ትርጉምን ለመረዳት የአማርኛ ወይም የሌላ ቋንቋ ዕውቀታችንን ብቻ መሠረት የምናደርግ ከሆነ አንዳንዴ የጽሑፉን እውነተኛ ትርጉምና ፋይዳ በቀላሉ መሳት እንችላለን፡፡ የመጀመሪያው ቋንቋ የሚለውን መስማት፣ እግዚአብሔር እንድንረዳ የሚፈልገውን ነገር በተሻለ ሁኔታ እንድንጨብጥ ይረዳናል፡፡

በመሠረቱ ኢየሱስ ስለ የእግዚአብሔር መንግሥት ሲናገር ስለ ‹‹የእግዚአብሔር አገዛዝ›› መናገሩ ነው፡፡ ወንጌሎች ውስጥ የእግዚአብሔር መንግሥት ለማለት በብዛት ጥቅም ላይ የዋሉ ግሪክኛ ቃሎች ባሲሊያ ቱ ቴዎስ (Basileia tou Theos) የሚሉት ናቸው፡፡ ቴዎስ፣ እግዚአብሔር ማለት ሲሆን፣ ባሲሊያ ደግሞ፣ ‹‹ንጉሣዊ፣ አገዛዝ፣ አስተዳደር›› ተብሎ ይገለጻል፡፡ ባሲሊያ ‹‹መሠረት›› (base) ወይም፣ ‹‹ሥር›› (Foundation) ከሚለው ግሪክና ቃል የተወሰደ ነው፡፡ አንዳንድ ምሑራን ባሲሊያ ቱ ቴዎስ ለሚለው ጥሩ ትርጉም፣ ‹‹ወሳኝ ንጉሣዊ የእግዚአብሔር አገዛዝ›› ወይም ‹‹የእግዚአብሔር አስተዳደር›› የሚለው እንደ ሆነ ያምናሉ፡፡ ወሳኝ ንጉሣዊ አገዛዝ የሚለውን እወደዋለሁ፡፡ ከትርጉሞቹ አንዱ ‹‹ፍጻማዊ የበላይ ኃይል›› የሚለው ነው፡፡

ለምሳሌ፣ በተለምዶ የጌታ ጸሎት በሚባለው ውስጥ ኢየሱስ፣ ‹‹በሰማያት የምትኖር አባታችን ሆይ፣ ስምህ ይቀደስ፤ መንግሥትህ ትምጣ፤ ፈቃድህ በሰማይ እንደ ሆነች እንዲሁ በምድር ትሁን›› በማለት እንድንጸልይ ነግሮናል (ሉቃስ 11፥2)፡፡ ቃል በቃል፣ ‹‹በሰማያት የምትኖር አባታችን ሆይ፤ አንተ ሁሉን ቻይ እግዚአብሔር ነህ፡፡ ፍጹማዊ ኃያል አገዛዝህ ትምጣ፡፡ በሰማይ እንደ ሆነ ሁሉ፣ ፈቃድህ በዚህ ምድርም ይፈጸም›› ማለቱ ነበር፡፡ ሆኖም፣ ምንም እንኳ የእግዚአብሔር መንግሥት ቢመጣም፣ ብዙ ሰዎች ግን ገና ወደ ፊት የሚፈጸም እንደ ሆነ አድርገው ስለሚያስቡ እዚህ ላይ ችግር ይነሣል! እርግጥ ነው፣ ኢሳይያስ በትንቢት እንዳመለከተው የእግዚአብሔር መንግሥት በአካል ገና አልመጣም፤ ያ የሚሆነው ኢየሱስ እንደ ገና መጥቶ ለዘላለም ሲገዛና የሰይጣን ተፅዕኖ ላንዴና ለሁልጊዜ ሲወገድ ነው፡፡ ይሁን እንጂ፣ በመንፈሳዊ መልኩ የእግዚአብሔር መንግሥት መጥቷል፡፡ በእግዚአብሔር ኪዳን ሕዝብ ውስጥ ነው፤ ምክንያቱም ኢየሱስ፣ ‹‹የእግዚአብሔር መንግሥት በሚታዩ ምልክቶች አትመጣም፤ ሰዎችም 'እዚህ ነው' ወይም 'እዚያ ነው' ማለት አይችሉም፤ እነሆ የእግዚአብሔር መንግሥት በመካከላችሁ (በውስጣችሁ) ናትና›› ብሎአል (ሉቃስ 17፥20-21)፡፡

ኢየሱስ መስቀል ላይ ካደረገው የተነሣ፣ አሁን የእግዚአብሔር መንግሥት በእያንዳንዱ የክርስቶስ ተከታይ ውስጥ ናት፡፡ ባለንበትና በምንሄድበት ሁሉ ይህንኑ ግዛትና አስተዳደሩን ማስፋፋት አለብን፡፡ በኢየሱስ ክርስቶስ አማካይነት በተሰጠን ብርቱ የእግዚአብሔር ጸጋ ነጻ ስጦታ በሕይወት መንገሥ አለብን፡፡ አሁን ደግሞ ኢየሱስ፣ ‹‹የእግዚአብሔር መንግሥት›› የሚለውን ቃል የተጠቀመበትና፣ ‹‹ብርቱና ፍጹማዊ የእግዚአብሔር አገዛዝ›› በሚለው የተካበትን ሌላውን የመጽሐፍ ቅዱስ ቃል እንመልከት፡፡ እንዲህ ያለ ለውጥ በመደረጉ እነዚህ ቃሎች ለዘመኑ አማኝ የሚሰጡትን ፋይዳ ያለው ትርጒም ማየት በጣም የሚገርም ነው፡፡

ለምሳሌ ማቴዎስ 12፥28 ላይ ኢየሱስ ያቀረበው ትምህርት፣ ‹‹እኔ አጋንንትን የማስወጣው በእግዚአብሔር መንፈስ ከሆነ፣ *ፍጹማዊ የእግዚአብሔር ኃያል መንግሥት* ወደ እናንተ መጥታለች›› ተብሎ ሊነበብ ይችላል፡፡ ኢየሱስ የእግዚአብሔር መንፈስ የሚለው የተሰጠንን የእግዚአብሔር ጸጋ (ኃይል) እንዲሠራ የሚያደርገው ሁለተኛው የሥላሴ አካል መንፈስ ቅዱስን ነው፡፡ አዲስ ኪዳን ውስጥ፣ ‹‹የጸጋ መንፈስ›› ተብሎ ተጠርቷል (ዕብራውያን 10፥29 ይመ)፡፡

እንደ ገና ኢየሱስ፣ ‹‹ሀብታም ፍጹማዊና ብርቱ ወደ ሆነው የእግዚአብሔር አገዛዝ ከሚገባ፣ ግመል በመርፌ ቀዳዳ ቢሾልክ ይቀላል›› በማለት ተናግሮአል (ማቴዎስ 19፥24)፡፡

ሀብታም ሰው፣ ‹‹ለስኬት የሚያበቃኝ ብቁና ብርቱ ዐቅም አለኝ›› የሚል ነው፡፡ ባለው ዕውቀት፣ ገንዘብ፣ ጉልበት፣ ንግግር ዐዋቂነት፣ ከሁነኛ ሰዎች ጋር ባለው ቀረቤታና አለኝ በሚላቸው ነገሮች ሙሉ በሙሉ ለራሱ ብቁ እንደ ሆነ ያምናል፡፡ ኢየሱስ ግን፣ ‹‹እናንተ ድኾች ብፁዓን ናችሁ›› ምክንያቱም፣ ‹‹ፍጹማዊ የእግዚአብሔር አገዛዝ የእናንተ ናትና›› ይላል (ሉቃስ 6፥20)፡፡

እየተናገረ ያለው ገንዘብ ስለሌላቸው ሰዎች አይደለም፤ በእግዚአብሔር ጸጋ የሚተማመኑትን እየባረከ ነው፡፡ ለድኾች ወንጌልን ለመስበክ የእግዚአብሔር መንፈስ በእርሱ ላይ እንደ ሆነ ኢየሱስ ተናግሮአል፤ ያም ሆኖ ግን፣ በሂደባቸው ማኅበረ ሰቦች ውስጥ ከአንዳንድ ሀብታሞች ጋር ሆን ብሎ ተገናኝቶአል፤ አንዳንዶቹንም አገልግሎአቸዋል፡፡ ስለ ግመል በመርፌ ቀዳዳ መሹለክ የተናገረው ከእግዚአብሔር ይልቅ በሀብቱ ከተማመነው ባለጸጋ ወጣት ገዢ ጋር ከተነጋገረ በኋላ ስለ ነበር አባባሉ ትክክል ነበር፡፡

የእግዚአብሔርን መንግሥት አስመልክቶ ኢየሱስ የተናገረውን ሌላ ቃል ተመልከቱ፣ ‹‹ለእናንተ የእግዚአብሔር ብርቱና ፍጻማዊ አገዛዝ ምስጢር ተሰጥቶአችኋል፤ በውጭ ላሉ ግን ነገር ሁሉ በምሳሌ ይነገራቸዋል›› (ማርቆስ 4፥11)፡፡ በእግዚአብሔር ጸጋ የተሰጠን ሥልጣንና ኃይል፣ በእርግጥም ምስጢር ነው፣ ማለትም መንፈስ ቅዱስ ብቻ መግለጽ የሚችለው ስውር እውነት ነው፡፡ ‹‹ዐይን ያላየውን፣ ጆሮ ያልሰማውን፣ የሰውም ልብ ያላሰበውን፣ እግዚአብሔር ለሚወዱት አዘጋጅቶአል፤ እግዚአብሔር ግን ይህን በመንፈሱ አማካይነት ለእኛ ገልጦልናል›› (1ቆሮንቶስ 2፥9-10)፡፡ እኔና እናንተ በእግዚአብሔር ጸጋ በሕይወት የመንገሣችን እውነት፣ አዲስ ኪዳንን በጻፉ ሐዋርያት በኩል፣ መንፈስ ቅዱስ ለእኛ እስኪ ገለጠው ጊዜ ድረስ ምስጢር ነበር፡፡ አሁን ግን ምስጢሩ ስለ ተገለጠ፤ ማድረግ ያለብን በእምነት መቀበል ብቻ ነው፡፡

የእግዚአብሔርን መንግሥት አስመልክቶ ኢየሱስ የተናገረው ሌላ አባባል፣ ‹‹እውነት እላችኋለሁ፣ እዚህ ከቆሙት መካከል ብርቱና ፍጹማዊ የእግዚአብሔር አገዛዝ በኃይል ስትመጣ እስከሚያዩ ድረስ ሞትን የማይቀምሱ አንዳንዶች አሉ›› የሚለው ነው (ማርቆስ 9፥1)፡፡ መሲሑ ራሱ የተናገረው ይህ ቃል የእግዚአብሔር መንግሥት አመጣጥ የወደ ፊት

የመሆኑን ያህል፣ እዚህና አሁን መሆኑንም አስመልክቶ ያለንን እምነት ሊያጠናክርልን ይገባል፡፡ በበዓለ ሃምሳ ቀን የጸጋ መንፈስ ከመጣ ወዲህ፣ ብርቱና ፍጹማዊ የእግዚአብሔር አገዛዝ በኢየሱስ ተከታዮች ውስጥ ይኖራል፡፡ አንድ ጊዜ ኢየሱስ ላቀረበው ጥያቄ በማስተዋል መልስ ለሰጠው ጸሐፊ፣ ‹‹አንተ ከእግዚአብሔር ብርቱና ፍጹማዊ አገዛዝ የራቅህ አይደለህም›› ያለው በዚሁ መንፈስ ነበር (ማርቆስ 12፥34)፡፡

የእግዚአብሔርን መንግሥት አስመልክቶ እስከ አሁን ካካፈልኳችሁ ጥቂት ምሳሌዎች ማየት እንደቻላችሁት በግሪኩ መሠረት ስናነባቸው የበለጠ ገላጭና ጠቃሚ ትርጉም ይኖረዋል፡፡ አዲስ ኪዳን ውስጥ የእግዚአብሔር መንግሥት የሚል ቃል ሲገጥማችሁ፣ የእግዚአብሔር ፍጹማዊና ብርቱ አገዛዝ በሚለው መተካታችሁን ብትቀጥሉ ላቅ ያለ ትርጉሙን መረዳት ያስችላችኃል፤ ደግሞም ያበራላችኃል፡፡

ሆኖም፣ የእግዚአብሔር ፍጹማዊና ብርቱ አገዛዝን በተመለከተ አንድ በጣም አስፈላጊ ገጽታ ማስታወስ አለብን፡፡ መግዛትን ለእኛ ሰጥቷል! ‹‹ሰማየ ሰማያት የእግዚአብሔር ናቸው፤ ምድርን ግን ለሰው ልጆች ሰጣት›› (መዝሙር 115፥16)፡፡ የሰው ልጅ ሆኖ በመምጣት ኢየሱስ አዳም ያስነጠቀውን እንደ ገና አስመለሰ፡፡ ከዚያ በኋላም ኢየሱስ፣ ‹‹ሥልጣን ሁሉ (የመግዛት ኃይል) በሰማይና በምድር ተሰጥቶኛል›› አለ (ማቴዎስ 28፥18)፡፡ ይሁን እንጂ፣ ጌታችንና ንጉሣችን የሆነው ክርስቶስ አሁን በአካል በምድር ላይ አይደለም፤ የእርሱ አካል የሆንነው እኔና እናንተ ፍጹማዊና ብርቱ የእግዚአብሔርን አገዛዝ ማከናወን አለብን፡፡ ያንን ካላደረግን በዚህ ዓለም ኃይላት እጅ ይቆያል፤ በሕይወት ከመንገሥ ይልቅ ሕይወት ይነግሥብናል፡፡ እንደዚያ እንዲሆን የእግዚአብሔር ዕቅድ አይደለም! በክርስቶስ በኩል በሕይወት እንድንነግሥ በእግዚአብሔር ጸጋ ብቁ ሆነናል!

## ማየትና መግባት

አሁን ኢየሱስ ለኒቆዲሞስ የነገረውን ሰፋ አድርገን እንመልከት፡፡ በመጀመሪያ ጌታ፣ ‹‹እውነት እልሃለሁ፤ ማንም ዳግመኛ ካልተወለደ በቀር የእግዚአብሔርን መንግሥት ሊያይ አይችልም›› ማለቱን ታስታውሳላችሁ (ዮሐንስ 3፥3)፡፡ ጥቂት ቆየት ብሎ ደግሞ፣ ‹‹እውነት እልሃለሁ፤ ማንም ከውሃና ከመንፈስ ካልተወለደ በቀር ወደ እግዚአብሔር መንግሥት ሊገባ አይችልም›› በሚል መልኩ ገለጠው (ዮሐንስ 3፥5)፡፡

የእግዚአብሔርን መንግሥት አስመልክቶ ከግሪኩ ቃል ያገኘነውን ዕይታ ግምት ውስጥ በማስገባት፣ መንግሥቱን በማየትና ወደ መንግሥቱ

በመግባት መካከል ኢየሱስ ልዩነት ያደረገበትን ምክንያት መረዳት እንችላለን፡፡ የእግዚአብሔርን መንግሥት፣ ሰማይ ላይ እንዳለ ቁሳዊ ነገር የምናየው ከሆነ፣ ቁጥር 3 መንግሥተ ሰማይ ለመግባት ማየት ብቻ እንጂ፣ ዳግም መወለድ አስፈላጊ እንዳይደለ ያመለክታል ማለት ነው፡፡ ይህ ግን እውነት አይደለም፡፡ ኢየሱስ እየተናገረ ያለው ስለ ፍጹማዊ፣ ብርቱ፣ የእግዚአብር አገዛዝ ወይም የመንግሥት አገዛዝ መሆኑን ስንረዳ እነዚህ ጥቅሶች ለመረዳት የማያዳግት ፍጹም የተለየ ትርጉም ይኖራቸዋል፡፡

ቁጥር 3 ላይ *ማየት* ለሚለው ጥቅም ላይ የዋለው የግሪኩ ቃል አይዶ (eido) የሚለው ነው፡፡ ዋነኛ ትርጕሙ፣ ‹‹ማየት፣ መገንዘብ፣ መረዳት ወይም መያያዝ›› ነው፡፡ ዳግም የተወለዱ ሁሉ ፍጹማዊና ብርቱ የሆነ አገዛዝን ማለትም፣ የእግዚአብሔርን መንግሥት እንደሚያዩ፣ እንደሚገነዘቡ፣ እንደሚረዱና ከመንግሥቱ ጋር እንደሚያያዙ ኢየሱስ እየነገረን ነው፡፡

በሚቀጥለው ንግግሩ ግን ማየት (eido) በሚለው ቃል አይጠቀምም፤ የእግዚአብሔርን አገዛዝ በተመለከተ *መግባት* በሚለው ቃል ነው የሚጠቀመው፡፡ መግባት ለሚለው የተጠቀመበት የግሪኩ ቃል ኢሰርቾማይ (eirerchomai) የሚል ነው፡፡ ዋነኛ ትርጉሙ፣ ‹‹ተነሥቶ ወደ ውስጥ መምጣት›› ወይም ‹‹ተነሥቶ መግባት›› የሚል ነው፡ ስለሆነም ኢየሱስ በእነዚህ ሁለት ዐረፍተ ነገሮች ፍጹማዊና ብርቱ የሆነው የእግዚአብሔር አገዛዝን ከመገንዘብ ተነሥቶ ወደ መግባት እየተሻገረ ነው፡፡ ልዩነቱን አያችሁ?

ምሳሌ ለማቅረብ ያህል፣ ወደ አንድ ቦታ ለመብረር በአውሮፕላን ስሳፈር አውሮፕላኑ ከስበት ኃይል ውጪ የመሆን ችሎታ እንዳለው፣ እኔንም ከምድር በጣም ከፍ እንደሚያደርገኝና ወደ አንድ የተወሰነ ቦታ እንደሚያመጣኝ በሚገባ እረዳለሁ፡፡ እንደ አንድ ተጓዥ በዚያ አውሮፕላን የመብረርን ጥቅም አያለሁ፤ እንዲሁም እለማመዳለሁ፡፡

ታዲያ፣ አንድ ቀን አንድ ወዳጄ የበረራ ትምህርት እንድማር ይከፍልልኛል እንበል፡፡ ጥቂት የመጀመሪያ ሥልጠና ካደረግሁ በኋላ፣ ባለ አንድ ሞተር ወደ ሆነው አውሮፕላን ውስጥ እገባለሁ፤ አስተማሪውም ምን ማድረግ እንዳለብኝ ይነግረኛል፡፡ ብዙም ሳይቆይ አውሮፕላኑን ማብረር እጀምራለሁ፡፡ በሕልም የማደርገው ነገር ሊመስለኝ ይችላል፡፡ በመጀመሪያው በረራዬ አእምሮዬ ውስጥ በጣም ጎልቶ የሚመጣ ሐሳብ፣ በፈለግሁ ጊዜና ወደ ፈለግሁበት ቦታ ያንን አውሮፕላን ማብረር የመቻሌ እውነት ነው፡፡ ስለዚህም አውሮፕላን ማድረግ የሚችለውን ከመረዳት አልፌ፣ እንደ ተሳፋሪ

ብቻ ሳይሆን፣ አሁን አውሮፕላኑን ወደ ፈለግሁበት ቦታ ማብረር የምችል ፓይለት ሆኜአለሁ፡፡ ስለዚህም ወደ ማብረር ነጻነት ገባሁ ማለት ይቻላል፡፡

የኢየሱስ አነጋገር ሁለት ዐይነት አማኞች መኖራቸውን ያመለክታል፡፡ በመጀመሪያው ምድብ ውስጥ ያሉትን፣ እንደ ተሳፋሪዎች አውሮፕላኑን የሚያዩ፣ የሚረዱና የበረራን ጥቅም በተለማመዱ ሰዎች ልንመስላቸው እንችላለን፡፡ ሁለተኞቹ ደግሞ፣ ተነሥተው እንደ ፓይለት ወደ ማብረሪያው ክፍል በሚገቡና የት መሄድና በምን ያህል ፍጥነት ማብረር እንዳለባቸው በሚወስኑ ፓይለቶች ልንመስላቸው እንችላለን፡ ምንም እንኳ ተሳፋሪዎቹ በአውሮፕላን የመብረር ጥቅም ቢኖራቸውም፣ ምንጊዜም ቢሆን፣ እንዴት እንደሚያበርሩ ችሎታው ባላቸው ሰዎች እጅ ናቸው፡፡

የእግዚአብሔርን መንግሥት በማየትና ወደ እግዚአብሔር መንግሥት በመግባት መካከል ስላለው ሁነኛ ልዩነት ተጨማሪ ምሳሌ ለማግኘት፣ አንድ ደሴት ውስጥ ሆነው ከዚያ መውጫ ያጡ ሰዎችን አስቡ፡፡ ደሴቱ ሰዎችን የሚበሉ አስፈሪ የዱር አራዊት፣ መርዛማ እባቦች፣ ሸረሪቶችና ጊንጦች የሞሉበት አደገኛ ደሴት ነበር፡፡ እንዲህ መሆኑ ይህን ያህል ከባድ መስሎ ካልታያችሁ፣ ደሴቱ ላይ ሰዎችን የሚበሉ፣ ከሥልጣኔ በጣም የራቁ ሰዎችም ነበሩበት፡፡ እነዚያ ሰዎች ከባድ ችግር ውስጥ ነበሩ፡፡ ሆኖም፣ አንድ የምሥራች አለ፤ ደሴቱ ላይ አንድ የአውሮፕላን ማኮብኮቢያና ነዳጅ በሚገባ የተሞላ ጀት ነዳጅ እንደ ተሞላ ማኮብኮቢያው ላይ አርፏል፡፡ ሰዎችን በቀላሉ ወደ ደኅና ቦታ ሊወስዳቸው ይችላል፡፡ ሆኖም፣ አንድ በጣም ከባድ ችግር ነበር፤ ከእነዚያ ሰዎች አንዱ እንኳ አውሮፕላን ማብረር አይችልም! ብዙዎቻችን ልምድ ያለን ተሳፋሪዎች ነን፤ ሆኖም አንዳችንም አውሮፕላን የማብረር ችሎታ ወዳለው ፓይለት ደረጃ ከፍ ብለን አናውቅም፡፡ ምንም እንኳ፣ አውሮፕላኑ ወደ ደኅንነትና ወደ ነጻነት መብረር የምንችልበትን ኃይል ቢሰጠንም፣ አውሮፕላኑን ከማኮብኮቢያው ማብረር ቀርቶ፣ ሞተር ማስነሣት እንኳ ባለ መቻላችን ተጠቃሚዎች መሆን አልቻልንም፡፡

ይህ ምሳሌ ፍጹማዊ የእግዚአብሔርን ብርቱ አገዛዝ ማየትና መለማመድ በሚችል አማኝና፣ ፍጹማዊ የእግዚአብሔር ብርቱ አገዛዝ ውስጥ ተነሥቶ በሚገባ አማኝ መካከል ያለውን ልዩነት ሊያሳየን ይችላል፡፡

ሁለቱ በጣም ይለያያሉ፤ አይደለም እንዴ? ታዲያ፣ እናንተ መሆን የምትፈልጉት የትኛውን ዐይነት አማኝ ነው?

## ወደ አገዛዙ መግባት

እዚህ ላይ የሚነሣ ምክንያታዊ ጥያቄ፣ አንድ የእግዚአብሔር ልጅ የእግዚአብሔርን አገዛዝ ከማየት ወደ መግባት የሚሸጋገረው እንዴት ነው? የሚል ይሆናል፡፡ በሌላ አነጋገር መንፈሳዊ ተሳፋሪዎች ከመሆን፣ መንፈሳዊ ፓይለቶች ወደ መሆን የምንሸጋገረው እንዴት ነው? ሐዋርያው ጳውሎስ ለዚህ ጥያቄ መልስ ሰጥቶልናል፡፡

ከመንፈስ ቅዱስ ግልጽ ምሪት በመቀበል፣ ጳውሎስና በርናባስ ከአጥቢያ ቤተ ክርስቲያናቸው ተነሥተው የመጀመሪያውን ሐዋርያዊ ጉዞ አድርገው ነበር (ሐዋርያት ሥራ 13፥1-4)፡፡ ከረጅም ጉዞ በኋላ በእስያ የነበሩ ብዙ ከተሞችን ጐብኝተው ወደ አገራቸው ለመመለስ ረጅሙን መንገድ ተያይዘው እያሉ ከዚያ በፊት የመሠረቱዋቸውን አዳዲስ ቤተ ክርስቲያኖች የነበሩበትን ጥቂት ከተሞች በድጋሚ እየጐበኙ ነበር፡፡ በዚያ ዘመን ጉዞ ማድረግ እንደ አሁኑ ዘመን ቀላል አልነበረም፡፡ በዚህ ዘመን አውሮፕላን ተሳፍሬ ወደ ማንኛውም ከተማ ብዙውን ጊዜ በሃያ አራት ሰዓት ውስጥ መድረስ እችላለሁ፡፡ ከአንድ ቦታ ተነሥቼ ወደ ሌላው ስሄድ፣ ከጉዞው ውስብስብነት የተነሣ የተለየሁዋቸውን ሰዎች እንደ ገና አያቸው ይሆን? የሚል ስጋት አይኖረኝም፡፡ በጳውሎስ ዘመን ግን ከአንድ ቦታ ተነሥቶ ወደ ሌላው መሄድ በጣም የሚያሳስብ ጉዳይ ነበር፡፡ እነዚያን አብያተ ክርስቲያናት ትቶ ሲሄድ በመንፈስ የወለዳቸውና የእግዚአብሔር መንግሥት አባሎች ያደረጋቸውን እነዚያን የተወደዱ ሰዎች በሰማይ እንደ ገና ከማግኘቱ በፊት በዚህ ምድር ማየት የማይችልበት ብዙ ምክንያቶች ነበሩ፡፡ ከዚህም የተነሣ ለእነዚያ አዳዲስ  አማኞች የተናገረውን ቃል ምን ያህል በጥንቃቄ እንደ መረጠ ማሰብ እንችላለን፡፡ ለእነርሱ የሰጠው ምክር፣ የእግዚአብሔርን አገዛዝ ከማየት፣ ወደ መግባት እንዴት መሸጋገር እንደምንችል ለእኛም ይጠቅመናል፡፡

> ወደ ልስጥራን፣ ወደ ኢቆንዮንና ወደ አንጾኪያ ተመለሱ፡፡ የደቀ መዛሙርትንም ልብ በማበረታታትና በእምነታቸው ጸንተው እንዲኖሩ በመምከር፣ ወደ እግዚአብሔር መንግሥት ለመግባት በብዙ መከራ ማለፍ አለብን አሏቸው (የሐዋርያት ሥራ 14፥21-22)፡፡

ጳውሎስ እነዚያን ሦስት ከተሞች ትቶ የሄደው፣ ምንም እንኳ እነዚህ ነገሮች የራሳቸው ጥቅም ቢኖራቸውም – ገንዘብ የሚያገኙበትን ሰሚናር፣ ቤተ ክርስቲያን የምታድግበትን ኮንፈረንስ፣ የመሪዎች ሥልጠና ሲምፖዚየም በማዘጋጀት፣ ሌላው ቀርቶ ልብን የሚያነቃቃ የተስፋ መልእክት በመስጠት

እንኳ አልነበረም፡፡ ይልቁንም አማኞች በጽናት ለመኖርና በሚገባ ለመጨረስ የሚያበቃቸውን ምክር በመስጠት ነበር እነዚያን ጀማሪ አማኞች የተለያቸው፡፡ የእርሱ ዋና ዓላማ ወደ አገዛዙ እንዲገቡ እነርሱን ማዘጋጀት ነበር፡፡

የጳውሎስ ቃል ዛሬም ለእኛ እውነት መሆኑ እንደ ተጠበቀ ነው፡፡ ይህ እውነት ልባችንና ነፍሳችን ውስጥ መቀረጽ አለበት – ወደ ፍጹማዊና ብርቱ ወደ ሆነው የእግዚአብሔር አገዛዝ ለመግባት በብዙ መከራ ውስጥ ማለፍ አለብን፡፡ ልብ አድርጉ – ይህ የተስፋና የእምነት እንጂ፣ የሽብር መልእክት አይደለም፡፡ እስቲ በዚህ መልኩ እናስብ፣ መከራ ይመጣል፤ በፍጹም የማይቀር ነገር ነው፡፡ መከራ ለተከታዮቹ የሕይወት ሐቅ መሆኑን ኢየሱስ በግልጽ ተናግሮአል፡፡ ‹‹በዓለም ሳላችሁ መከራ አለባችሁ፤ ነገር ግን አይዞአችሁ እኔ ዓለምን አሸንፌዋለሁ›› ብሏቸዋል (ዮሐንስ 16፥33)፡፡ እርሱ አሸንፎአል፤ ይህም ማለት፣ ይህ ዓለም እኛ ላይ ማድረስ የሚችለውን ማንኛውንም ነገር ማሸነፍ እንድንችል ለእኔና ለእናንተም ኃይልና ሥልጣን ተሰጥቶናል ማለት ነው፡፡ የእርሱ አካል ነን፤ በዚህ ምድር የክርስቶስ ተወካዮች ነን፡፡ በክርስቶስ ዓለምን አሸንፈናል!

መከራ የሚለው ቃል፣ ‹‹ችግር ወይም ታላቅ ስቃይ ያለበት ሁኔታ›› በሚል ተገልጿል፡፡ ግሪክኛው ቃል ትሊፕሲስ (thlipsis) ነው፡፡ አንድ የመጽሐፍ ቅዱስ ቃላት መድበል ትሊፕሲስን በዚህ መንገድ ይገልጸዋል፣ ‹‹ከውጫዊ ወይም ከውስጣዊ ጉዳት የተነሣ የሚመጣ ታላቅ ስሜታዊና መንፈሳዊ ጫና ውስጥ መሆን፡፡ አዲስ ኪዳን ውስጥ ይህ ቃል ሃምሳ አምስት ጊዜ ጥቅም ላይ ሲውል፣ ሃምሳ ሦስቱ ምሳሌያዊ ነው፡፡›› ጫናው ከጠላቶች፣ ከባድ ከሆኑ አካባቢዎች፣ ከተሳሳቱ ውሳኔዎች ወይም ከዓላማ መበላሸት ሊመጣ ይችላል፡፡

ጀምስ ስትሮንግ ትሊፕሲስን፣ ‹‹ጫና (በእውን ያለ ወይም ምሳሌያዊ)፣ መከራ፣ መራራነት፣ ሸክም፣ ስደት፣ ስቃይ፣ ችግር›› በማለት ይተረጉመዋል፡፡ ደብልዩ ኢ. ቫይን ደግሞ በአጭሩ፣ ‹‹ነፍስ ወይም መንፈስ ላይ ሸክም የሚሆን ማንኛውም ነገር›› በማለት ይተረጉመዋል፡፡

እኔ ደግሞ መከራ ወይም ትሊፕሲስ ለሚለው የምሰጠው ቀላል ቃል፣ ‹‹ምድረ በዳ›› በረሃ የሚል ነው፡፡

አንድ የመጽሐፍ ቅዱስ ትርጒም ሐዋርያት ሥራ 14፥22ን፣ ‹‹ወደ እግዚአብሔር መንግሥት ለመግባት በብዙ ችግር ማለፍ አለብን›› በማለት ተርጉሞታል፡፡ ለምሳሌ ያህል አንድን ከተማ አሸንፎ የያዘ፣ አንድ ታላቅ

ንጉሥ እያገለገላችሁ ነው እንበል፡፡ ወደ ዋና ከተማው ገብቶ ከብረት በጠነከረ ክንድ ሲገዛ የነበረውን ጨቋኝ መሪ ከሥልጣን ገልብጦታል፡፡ የተገለበጠው መሪ ለሕዝቡ ጨካኝ ነበር፤ በሐሰት ፕሮፓጋንዳ አእምሮአቸውን መርዞአል፣ መልካምና እውነት ከሆነ ነገር ጋር እንዳይጣጣሙ አድርጓል፤ የምታገለግሉት መሪ ትክክለኛና ፍትሐዊ መንገድ ላይ ጥላቻና ንቀት አነሳሥቷል፡፡

ወደ ምድሪቱ ገብተው ጠላት የያዛቸው ክልሎችና አሁንም እንዳሉ ያሉ ምሽጎችን በመያዝ የእርሱን አሸናፊነት እውን እንዲያደርጉ መልካሙ መሪ አገልጋዮቹን ላከ፡፡ በየቦታው አሁንም ምሽጎችና ታላላቅ ግንቦችን የያዙ የጨቋኙ ገዢ ባላባቶች ነበሩ፡፡ የድሮውን ክፉ ንጉሥ መንገዶች ማስፋፋታቸውን ቀጥለዋል፡፡ ከዚህም የተነሣ አሁንም ቢሆን፣ የክፉው ንጉሥ ሥርዐት ምርኮኞች የሆኑ ብዙዎች ነበሩ፡፡ ምንም እንኳ ዋናው ውጊያ በድል ቢጠናቀቅም፣ ያንን ድል ለማስፈጸም አሁንም መሠራት ያለበት ብዙ ሥራ ነበር፡፡

በጠላት ክልል ውስጥ ያለ አንድ ምሽግ ለመያዝ ወደዚያው እየመራችሁ ነው፡፡ መንገድ ላይ ብዙ አደጋዎች ይገጥሟችኋል፤ አንዳንዴ ፊት ለፊት ትጋጫላችሁ፤ መፍረስ ያለበትን ታፈርሳላችሁ፣ ጠላት በያዛቸው መሬቶች ታልፋላችሁ፡፡ እነዚህን መሬቶች እንዳትይዙ ለመከላከል ጠላታችሁ ብዙ ወጥመዶች አድርጓል፡፡ ያም ሆኖ ግን የተገኘው ድል እንዲረጋገጥ አንድ በአንድ በእነዚህ ችግሮች ማለፍ ይኖርባችኋል፡፡ አንዴ ወደ ክልሉ ከገባችሁ እስካሁን ድረስ ከገጠማችሁ ሁሉ የበለጠ ፈተና ይገጥማችኋል፤ ይኸውም የጠላትን ምሽግ ጨርሶ መደምሰስ ነው፡፡ በጣም ደስ የሚለው ግን የጠላትን ወጥመድ፣ ውጊያና መንገድ ላይ የሚገጥማችሁን ከበባ ጥሳችሁ ባለፋችሁ መጠን፣ በጦር ሜዳ ውሎ የሚኖራችሁ ተመክሮና ልምዳችሁም እየዳበረ መምጣቱ ነው፡፡ መከላከያ ግንቡን በቁጥጥር ሥር ካዋላችሁ ምሽጉንም ትቆጣጠራላችሁ፡፡ ያም ብቻ ሳይሆን፣ ችሎታችሁንና ታማኝ ጠረኝነታችሁን በማስመስከር ለንጉሣችሁ ይዛችሁ በነበረው ክልል ሁሉ ላይ ለመግዛት ተገቢ ሰው ትሆናላችሁ፡፡

በጠላት ክልል ውስጥ ያለ አንድ ምሽግ ለመያዝ ወደዚያው እየመራችሁ ነው፡፡

በዚህ ታሪክ የተመለከትነው መልካም ንጉሥ ጌታ ኢየሱስን ይወክላል፡፡ ወደ ፊት እንድንገሠግሥና አሁንም ይህን ዓለም እየገዙ ባሉ የጨለማ ኃይላት ላይ፣ የእሱን ድል እንድናረጋግጥ ታማኝ ወታደሮቹ እኛን አዝዞናል፡፡ ወደ ፊት በገፋን መጠን፣ እዚህም እዚያም ችግር ይገጥመናል፤

ሆኖም የኃላ ኃላ በጠላት ዘዴ፣ አሠራርና ፕሮፓጋንዳ ደንቁረው አሁንም ምርኮኛ የሆኑ ብዙዎችን ነጻ እናወጣለን፡፡

ወደ አገዛዙ ለመግባት እኔና እናንተ በብዙ መከራ ማለፍ ይኖርብናል፡፡ ይሁን እንጂ፣ ኢየሱስ እንዳለው እርሱ ዓለምን በማሸነፉ ደስ ሊለን ይገባል፡፡ እኛን ለመገዳደር ዓለም መንገዳችን ላይ የሚያኖረውን ተግዳሮት ሁሉ ማሸነፍ እንድንችል የእርሱ ጸጋ ኃይልና ሥልጣን ሰጥቶናል፡፡

የተሰጠን የእግዚአብሔር ጸጋ ብቁ የማድረግ ወይም የማስቻል ዐቅም ብቻ አይደለም፡፡ ክርስቶስ አዳኛችንና ጌታችን መሆኑን የምናምን እኛ በእግዚአብሔር ጸጋ ልዩ ስፍራ አለን፡፡ ጳውሎስ ለሮም ክርስቲያኖች የተናገረውን ደስ እያላችሁ አንብቡ፣

> የእግዚአብሔር ልጆች መሆናችን ያ መንፈስ ራሱ ከመንፈሳችን ጋር ሆኖ ይመሰክርልናል፡፡ ልጆች ከሆንን ወራሾች ደግሞ ነን፤ የክብሩ ተካፋዮች እንሆን ዘንድ በእርግጥ የመከራው ተካፋዮች ብንሆን፣ የእግዚአብሔር ወራሾች ነን፡፡ የአሁኑ ዘመን ሥቃያችን ወደ ፊት ሊገለጥ ካለው ለእኛ ከተጠበቀልን ክብር ጋር ሲነጻጸር ምንም እንዳይደለ እቈጥራለሁ፡፡ (ሮሜ 8፥16-18)

እንደ አማኞች እኔና እናንተ የእግዚአብሔር ወራሾች ነን! የእግዚአብሔር ወራሾችና ከክርስቶስ ጋር አብረን ወራሾች ነን፡፡ ወራሽ ተብሎ የተተረጐመው ግሪክ ቃል፣ ክሌሮኖሞስ (Kleronomos) ሲሆን፣ ‹‹ንብረት፣ ቅርስ የሚወስድ ወይም የሚወርስ ማለት ነው፡፡ አጽንዖቱ የወራሹ ንብረት የመውሰድ መብት ላይ ነው፡፡›› እጄ ላይ ያለ ሌላ መዝገበ ቃላት ወራሽን፣ ‹‹የሚወርስና ከእርሱ በፊት የነበረውን ቅርስ (ሌጋሲ) የሚያስቀጥል ሰው›› ይለዋል፡፡ ‹‹የሌላውን ሥልጣን ለመያዝ ሕጋዊ መብት ያለው ሰው›› የሚል ሁለተኛ ትርጒምም አለ፡፡ ሐሳቡን በሚገባ ያዛችሁ? እግዚአብሔር የፈጸመውና የእርሱ የሆነው ማንኛውንም ነገር ወራሾች አድርጐናል! የእርሱ የሆነው የእኛ ነው፡፡ እርሱ እንደሚገዛ እኛም እንገዛለን፡፡

ሁሉም የእግዚአብሔር ነው፤ ስለዚህም ሁሉም እኛ ነው፡፡ ‹‹እንግዲህ ማንም የሰው ልጅ ማድረግ በሚችለው አይመካ›› በማለት ጳውሎስ ለአማኞች ይጽፋል፡፡ ‹‹ምክንያቱም ሁሉ ነገር የእናንተ ነውና›› (1ቆሮንቶስ 3፥21)፡፡ ሁሉም ነገር! እኔና እናንተ ነው፤ በእውነት የእግዚአብሔር ወራሾ ነን! አንድ ዘመናዊ የእንግሊዝኛ ትርጒም፣ ‹‹ዓለምን፣ ሕይወትን፣ ሞትን፣ አሁን ያለውን፣ ወደ ፊት የሚመጣውን ጨምሮ፣ ሁሉም የእናንተ ነው፡፡ ሁሉ ነገር

የእናንተ ሆኗል›› ይላል፡፡ እስቲ፣ ቆም በሉና ለአንድ ወይም ለሁለት ቀን ያህል ይህን አሰላስሉ፡፡ እኔና እናንተ በክርስቶስ በዓለም ካለው ሀብታሙ ሰው የበለጥን ሀብታሞች ነን!

ግን፣ አንድ መሠረታዊ ገደብ አለ፡፡ ሮሜ 8 ላይ ያለው ምንባብ እንዲህ ቢሆን የሚል አለው፡፡ ውርሳችን ቅድመ ሁኔታ አለበት፤ በሌላ አነጋገር ለማንኛውም ክርስቲያን ወዲያውኑ የሚሆን አይደለም፡፡ ለመሆኑ ቅድመ ሁኔታው ምንድነው? ከእርሱ ጋር መከራ መቀበል አለብን፡፡ ምንባቡን እንደ ገና አንብቡ፡፡ ከክርስቶስ ጋር አብሮ ወራሽ ወደ መሆን እውነታ ለመግባት፣ እርሱ እንዳደረገው ሁሉ የእርሱ በሆነው ነገር መንገድ ላይ የቆመ ተቃውሞን ለማሸነፍ መዋጋትና መጋፈጥ አለብን፡፡ *የመከራው ተካፋዮች ብንሆን* የሚለውን ቃል ልብ አድርጉ፡፡ ተቃውሞን ማሸነፍ ፀጥ ባለ አትክልት ቦታ መንሸራሸር አይደለም፡፡ ውጊያ ነው፤ ከውጊያ ጋር ደግሞ መከራ ይኖራል፡፡

እኛን በተመለከተ ግን ለሽንፈት የምንዳረግበት መከራ አይደለም፡፡ ሮሜ 8፥18 ላይ በመከራ ማለፍ አዎንታዊና ተስፋ የሞላበት ሊሆን እንደሚችል ጳውሎስ ያመለክታል፡፡ ‹‹የአሁኑ ዘመን ሥቃያችን ወደ ፊት ሊገለጥ ካለው ለእኛ ከተጠበቀልን ክብር ጋር ሲነጻጸር ምንም እንዳይደለ እቆጥራለሁ፡፡›› እዚህ ላይ እንድታመዛዝኑና አጥብቃችሁ እንድትይዙ የምፈልገው መርሖ አለ፣

> የሥቃዩ (ትሊፕሲስ) ጫና የቱንም ያህል የበረታ ቢሆን፣ በመከራው ውስጥ ካለፋችሁ በኃላ ከምትለማመዱት የገዢነት ደረጃ ጋር ሲነጻጸር ምንም ማለት አይደለም፡፡

በክርስትናችን በትክክል የምንኖር ከሆነ፤ መከራ መምጣቱ አይቀርም፡፡ ከእያንዳንዱ የድል ውጊያ ጋር ግን፣ ከእኛ ውስጥ የበለጠ ክብር፣ ብርታትና ጥበብ ጐልቶ ይወጣል፡፡ ጳውሎስ እየተናገረ ያለው በሰማይ ፍርድ ወንበር ፊት ስለሚሰጠን ክብር ብቻ ሳይሆን፣ ለዚህ ለአሁኑ ዘመን ስለምንቀበለው ጥቅም ጭምር ነው፡፡ በመከራ ውስጥ አልፈን ስንወጣ፣ ላቅ ወዳለ አገዘዝ እንሻገራለን (እንገባለን)፡፡

## ከእርሱ ጋር መከራ መቀበል

*የመከራው ተካፋዮች ብንሆን...* የሚለውን ስናነብ፣ ኢየሱስ መከራ የተቀበለው እንዴት ነበር? በማለት መጠየቅ አለብን፡፡ ሁለት የመከራ ዐይነቶች አሉ፤ ብዙዎች ግራ የሚጋቡት እዚህ ላይ ነው፡፡ አንዱ ለጽድቅ

ሲባል የሚመጣ መከራ ሲሆን፣ ሌላው ግን ለዓለም ሲባል የሚመጣ ነው፡፡ እስቲ ጥቂት ላብራራው፡፡

አንደኛው የመከራ ዐይነት የሚመጣው መላው የዓለም ሥርዐት በክፉው ቁጥጥር ሥር በመሆኑ ነው (1ዮሐንስ 5÷19 ይመ.)፡፡ ስለሆነም በየቀኑ ሰዎች ላይ ጨካኝና ክፉ ነገር ይደርሳል፡ ሕፃናት ይጨነግፋሉ ወይም ለአጉል ነገር ይውላሉ፤ ልጃገረዶች ለወሲብ ባርነት ተላልፈው ይሰጣሉ፤ በሽታ የታዳጊዎችን ሕይወት ይቀጥፋል፤ ድኽነትና ራብ ይበዛል፤ ፀብና ጭቅጭቅ ቤተ ሰቦችን ይበታትናል፤ ሰካራም ሾፌሮች ጥፋት ያደርሳሉ – ይህ እንግዲህ ከብዙ በጥቂቱ ነው፡፡ በዚህ ዐይነቱ መከራ ውስጥ ምንም መልካም ወይም ጠቃሚ ነገር የለም፡፡ አሳዛኝና አሰቃቂ ቢሆንም፣ ይህ አዳም ሥልጣኑን ለጨካኝ ጌታ አሳልፎ የመስጠቱ ኃጢአት ውጤት ነው፡፡

ሁለተኛው መከራ ለጽድቅ ሲባል የሚመጣ ሲሆን፣ አሁን እኛ የምናተኩረው ይኸኛው ላይ ይሆናል፤ ኢየሱስና ጳውሎስ እየተናገሩ የነበረው ስለ እንዲህ ዐይነት መከራ ነበር፡፡ በእግዚአብሔር ብርታት ከተቀበልነው፣ ለጽድቅ ሲባል የሚመጣ መከራ ሁሉ ጠቃሚ ነው፡፡ ምንጊዜም ቢሆን ውጤቱ ክብር ያለበት ነው የሚሆነው፡፡ ወደ አገዛዝ እንድንገባ የቀረበልን ጥሪ፣ ይህን በጽናት እንድንቀበል ያበረታናል፡፡

ኢየሱስ በአገልግሎቱ ይህን አሳይቶናል፡፡ ከእርሱ ጋር እንድንነግሥ ከተፈለገ፣ ከእርሱ ጋር መከራ መቀበል ያለብን መሆኑን አስታውሱ፡፡ ለመሆኑ፣ እርሱ መከራ የተቀበለው እንዴት ነበር? ኢየሱስ ሰላሣ ዓመት ለአገልግሎት እየተዘጋጀ ነበር፤ በኋላም ዮሐንስ በሚባል ታዋቂ ነቢይ በዮርዳኖስ ወንዝ ተጠመቀ፡፡

ኢየሱስ በተጠመቀ ጊዜ ሰማያት ተከፍተው መንፈስ ቅዱስ በርግብ አምሳል ወርዶ እርሱ ላይ ዐረፈ፡፡ እግዚአብሔር አብ፣ ‹‹የምወድህ ልጄ አንተ ነህ፤ በአንተ ደስ ይለኛል›› በማለት ሁሉም እንዲሰሙት አድርጎ ከሰማይ ተናገረ (ሉቃስ 3÷22)፡፡ በዚያ ሕዝብ መካከል ሆናችሁ ኢየሱስን በተመለከተ እንዲህ ያለ ሰማያዊ ማረጋገጫ ሲሰጥ ብትሰሙ ምን ሊሆን እንደሚችል አስቡ፡፡ የፖለቲካና የሃይማኖት መሪዎችን ጨምሮ ብዙ ታላላቅ ሰዎችም ይህን ሰምተው ነበር፡፡

*እኛ ኢየሱስን ብንሆን ኖሮ፣ ብዙዎቻችን፣ አገልግሎቱን ለመጀመር ይህ ትክክለኛ ጊዜ ነው፤ ይህ ሁሉ ሕዝብ በተሰበሰበበት የመጀመሪያ መልእክቴን ማሰማት አለብኝ፡፡ ለዚህ፣ ጊዜ ሰላሣ ዓመት ሙሉ ስዘጋጅ ነበር፡፡ ምናልባትም ገንዘብ የሚያሰባስብና ማስታወቂያ የሚሠራ ድርጅት*

ያስፈልገኝ ይሆናል፡፡ እዚህ ያሉ ሰዎች ሁሉ ለወቅቱ የተነሣሁ የእግዚአብሔር ሰው መሆኔን ማወቅ አለባቸው በማለት እናስብ ነበር፡፡

መቼም፣ ይህ ምክንያታዊና በስፋት መነገር የሚያሻው ጉዳይ ይመስላል፤ ኢየሱስ ያደረገው ግን ያንን አልነበረም፤ ‹‹ኢየሱስ በመንፈስ ቅዱስ ተሞልቶ ከዮርዳኖስ እንደ ተመለሰ መንፈስ ወደ በረሓ ወሰደው፤ በዚያም አርባ ቀን በዲያብሎስ ተፈተነ›› (ሉቃስ 4፥1-2)፡፡ አንዳንድ አማኞች ኢየሱስ የተፈተነው አርባ ቀን በበረሐ ከቆየ በኃላ እንደ ሆነ እንደሚያስቡ ተረድቻለሁ፡፡ ነገሩ ግን እንደዚያ አልነበረም፡፡ ኢየሱስ ሦስት በውል የሚታወቁ ፈተናዎች እንደ ደረሱበት ወንጌሎቹ ቢያመለክቱም፣ አርባ ቀኑን ሙሉ እንደ ተፈተነ (መከራ እንደ ተቀበለ) ግልጽ ነው፡፡

ኢየሱስን ወደ በረሓ የወሰደው ማን እንደ ሆነ ልብ አድርጉ፡፡ ወደዚያ የወሰደው ዲያብሎስ አልነበረም፡፡ በመንፈስ ቅዱስ አማካይነት አባቱ ነበር የወሰደው፡፡ አንዳንድ ሰዎች፣ ኢየሱስ መከራና ተቃውሞ እንደሚደርስበት እያወቀ፣ እግዚአብሔር ልጁን ወደ በረሓ የወሰደው ለምንድነው? በማለት ይጠይቁ ይሆናል፡፡ አንድ መታወቅ ያለበት እውነት፣ የምናሸንፍበትን ኃይል ሳይሰጠን፣ እግዚአብሔር ወደ ማዕበሉ የማይወስደን መሆኑ ነው (ለዚህ መርሖ ድጋፍ የሚሆነውን ሐሳብ በሚቀጥለው ምዕራፍ አብራራለሁ፡፡) እዚህ ላይ የምንመለከተው እግዚአብሔር የመከራ ወይም የትሊፕሲስ ምንጭ አለመሆኑን ነው፡፡ የምንኖረው ብልሹ በሆነ ዓለም ውስጥ እንደ ሆንና ዓለምን እንድናሸንፍና እንድንገዛ ከተፈለገ፣ ከክፉ ኃይሎቹ ተቃውሞ እንደሚገጥመን ያውቃል፡፡ ስለሆነም ለበለጠ ድል ሊያበረታንና ሊያዘጋጀን እግዚአብሔር ያሠለጥነናል፡፡

ለበለጠ ድል ሊያበረታንና ሊያዘጋጀን እግዚአብሔር ያሠለጥነናል፡፡

ከጥምቀቱ በኋላ ኢየሱስ በመንፈስ ቅዱስ ተሞልቶ ወዲያውኑ ለሚቀጥለው አርባ ቀን መከራ (ትሊፕሲስ) ወደሚቀበልበት በረሓ ተወሰደ፡፡ ጸጋን የተሞላ ሰው ሆኖ በመካከላችን ለመመላለስ ኢየሱስ መለኮታዊ መብቱን ሁሉ ትቶ እንደ መጣ አስታውሱ (ፊልጵስዩስ 2፥7 እና ሉቃስ 2፥40 ይመ)፡፡ መከራን ተጋፈጠ፤ መከራን አሸነፈ፤ አንድ ጊዜ እንኳ ለዲያብሎስ ፈተና እጅ አልሰጠም፡፡ ከዚያም ከአርባ ቀን በኃላ፣ ‹‹ኢየሱስም በመንፈስ ኃይል ወደ ገሊላ ተመለሰ፤ ዝናውም በአካባቢው ባለው አገር ሁሉ ወጣ›› (ሉቃስ 4፥14)፡፡ ወደ በረሐ የሄደው በእግዚአብሔር መንፈስ ተሞልቶ ነበር፤ ያንን ከባድ መከራ ካሸነፈ በኋላ ግን በጸጋ መንፈስ ኃይል ተሞልቶ ተመለሰ፡፡ ሮሜ 8፥18 ላይ ጳውሎስ የተናገረውን አስታውሱ፣ ‹‹የአሁኑ ዘመን

ሥቃያችን ወደ ፊት ሊገለጥ ካለው ለእኛ ከተጠበቀልን ክብር ጋር ሲነጻጸር ምንም እንዳይደለ እቈጥራለሁ፡፡›› ይህን ምንባብ ቀለል ባለ ሁኔታ፣ ‹‹ይህ የአሁኑ ዘመን ሥቃይ፣ ለእኛ ከሚገለጠው ሥልጣንና ኃይል ጋር ለመነጻጸር እንደማይበቃ አስባለሁ›› በማለት ማንበብ ይቻላል፡፡ ኢየሱስ ላቅ ወዳለ አገዛዝ ደረጃ የገባው በአሸናፊነት በመከራ (ትሊፕሲስ) ውስጥ ካለፈ በኋላ ነበር፡፡

ሐዋርያው ያዕቆብ ይህን፣ ‹‹በፈተና የሚጸና ሰው የተባረከ ነው፤ ምክንያቱም ፈተናን ሲቋቋም እግዚአብሔር ለሚወዱት የሰጠውን ተስፋ የሕይወትን አክሊል ያገኛል›› በማለት ግልጽ አድርጐታል (ያዕቆብ 1፥12)፡፡

አርባ ቀን በበረሓ በቆየ ጊዜ ኢየሱስ እንዳደረገው ፈተናን ስናሸንፍ፣ ‹‹የሕይወትን አክሊል›› እንደምናገኝ አስታውሱ፡፡ ይህ አክሊል የሚሰጠው በሰማይ የፍርድ ወንበር ፊት ነው በማለት እንደምታስቡ እገምታለሁ፡፡ ይህ እውነት ነው፡፡ ይሁን እንጂ፣ ያዕቆብ እየተናገረ ያለው በሰማይ ስለምናገኘው አክሊል ብቻ ሳይሆን፣ እዚህ እያለን ስለምንገባበት የላቀ ሕይወት የአገዛዝ ደረጃም እንደ ሆነ አምናለሁ፡፡ አክሊል ሥልጣንን ያመለክታል፡፡ ከሥልጣን ጋር የሚመጣው ምንድነው? ኃይል ነው፡፡ ኢየሱስ በመንፈስ ተሞልቶ ወደ በረሐ ሄደ፤ በኃላም፣ በኃይል ተመለሰ፡፡ ወደ አገዛዝ የምንገባው፣ የእርሱ መከራ ተካፋይ ስንሆን እንደ ሆነ አስታውሱ፡፡ ስለዚህም መከራ (ትሊፕሲስ) ስንቀበልና፣ የቱንም ያህል ተቃውሞ ቢኖር እንኳ ለእግዚአብሔር ቃል በመታዘዝ የምንጸና ከሆነ፣ ወዲያውኑ የሚገኝ ጥቅም ማለትም፣ ጸንተን በቆምንበት የሕይወት ክልል ውስጥ ታላቅ ሥልጣን ይኖራል፡፡

## የሚስቴ እናት ምስክርነት

የሚስቴ የሊዛ እናት ለዚህ ተስፋ ዓይነተኛ ምሳሌ ልትሆነን እንደምትችል አስባለሁ፡፡ በ1979 ዓ.ም በኢንዲያና የነበሩ ሐኪሞች ምርመራ አድርገው ሺርሊ የጡት ካንሰር እንዳለባት ዐወቁ፡፡ ሕመሙ ቶሎ ስላልተደረሰበት ወደ ደም ሥሮቿ (lymphnodes) ሁሉ ተሰራጭቶ ነበር፡፡ ከ30 እጁ ሊምፍኖድ ጋር ጡትዋ ተቆረጠ፤ ዶክተሩ መዳን እንደማትችል ነግሯት ነበር፡፡

ሺርሊ ተጨማሪ ማረጋገጫ ማግኘት ስለ ፈለገች ካንሰርን በማከም ረገድ በአሜሪካ በጣም ከፍተኛ ሆስፒታሎች አንዱ ወደ ሆነው ሒዩስተን ቴክሳስ ወዳለው ኤም ዲ አንዴርሰን ሆስፒታል ትሄዳለች፡፡ እዚያ የነበረው የእርሷ ዶክተር የአንኮሎጂ ክፍል ኃላፊ ነበር፡፡ የሕክምናው ሪፖረት ተስፋ ሰጪ አልነበረም፡፡ ከመጀመሪያው ዶክተር ጋር ተመሳሳይ የሆነ ምርመራ

ካደረገላት በኋላ እርሱና የሕክምና ቡድኑ የሚነግሯትን በትክክል ካደረገች ሁለት ዓመት ምናልባትም ቢበዛ ሦስት ዓመት በሕይወት መኖር እንደምትችል ገለጹላት፡፡ ከሕክምና ሳይንስ አንጻር ምንም መፍትሔ የሚሆን ነገር አልነበረም፡፡ የሕክምናው ሂደት ከባድ ጨረር መደረግ፣ ከዚያም አንዲያና ወደ ነበረው ቤቷ ተመልሳ ሁለት ወይም ሦስት ሳምንት ማረፍ፣ ከዚያም ኬሞቴራፒ ለመውሰድ እንደ ገና ወደ ሒዩስተን መመለስን ይጠይቅ ነበር፡፡

ሒዩስተን እያለች በጸሎት አገልግሎቱ በሀገሩ ሁሉ ለሚታወቅ አንድ ቴሌቪዥን ጣቢያ ትደውላለች፡፡ ጥሪውን የተቀበለው ሰው ኤም ዲ አንደርሰን ውስጥ ያሉትን ተመላላሽ ሕመምተኞችን የሚንከባከቡ ባልና ሚስት ያውቅ ነበር፡፡ ወደ እነርሱ በመደወል ለእርሷ የተለየ እንክብካቤ ማድረጋቸውን እንዲቀጥሉ ነገራቸው፡፡ ባልና ሚስቱ ሺርሊ ጋር ግንኙነት ፈጠሩ፡፡ ወደ ቤተ ክርስቲያናቸው፣ ኳስ ጨዋታ ወዳለበት ቦታ ይወስዷት ነበር፤ አንዳንዴም ይዘዋት በመሄድ ውጪ ራት ይጋብዟት ነበር፤ በዚህ ጊዜ ውስጥ ሁሉ ግን ከእግዚአብሔር ቃል እምነት የሚገነቡ የተስፋ ቃሎች ያካፍሉዋት ነበር፡፡

ሺርሊ አዲስ ክርስቲያን ነበረች፡፡ ካንሰር እንዳለባት ከማወቋ ጥቂት ቀደም ሲል አገልግሎት ውስጥ የነበሩ ባልና ሚስት ጋር ወዳጅነት ነበራት፤ በተለይ ሚስትዮዋ መሠረታዊ የእምነት መርሖዎችን አስተምራት ነበር፡፡ ወደ ኢንዲያና በተመለሰች ጊዜ ከዚህችው ክትትል ከምታደርግላት ሴት ጋር ራት እየበላች እያለ፣ እግዚአብሔር ሁሉንም ሰው እንደማይፈውስ ትነግራታለች፡፡ ከእንዲህ ዐይነቱ ከባድ ሕመም ያልተፈወሱ ሌሎች ብዙ ክርስቲያኖች መኖራቸውን እንደ ምሳሌ ታቀርብላታለች፡፡ ሺርሊ ቀደም ሲል ያገኘቻቸው ባልና ሚስቱ የነገሩዋትን ተስፋ ሰጪ የቅዱሳት መጻሕፍት ክፍሎችን ስታካፍላት ምክርዋን ባለ መቀበልዋ ሴትየዋ በጣም ትቆጣለች፡፡

በዚህ ጊዜ ሺርሊ በጣም ግራ ተጋብታ ነበር፡፡ ኬሞቴራፒ ለማድረግ ወደ ሒዩስተን ስትመለስ፣ እነዚያ ባልና ሚስት በየቀኑ እያገኙ ከእግዚአብሔር ቃል መጽናኛና መበረታቻ ይሰጧት ነበር፡፡ በመጨረሻ ሺርሊ ፈውስን በተመለከተ የእግዚአብሔር ቃል የሚናገረው እውነት መሆኑን በጥልቅ ልብናዋ ወደ ማመን መጣች፡፡ ከእንግዲህ እግዚአብሔር በቃሉ የተናገረውን አትጠራጠርም፡ ከእንግዲህ እርሷ ልትፈወስ ነው!

ኬሞቴራፒ መውሰድን ለማቋረጥ የወሰነች ጊዜ ዶክተሩ አእምሮዋን እንደ ሳተች ነበር ያሰበው፡፡ ከሆስፒታሉ በመውጣት ላይ እያለች ኤሊቨተሩ ድረስ ተከትሎ ሕይወቷን አደጋ ላይ የሚጥል ስሕተት እየፈጸመች እንደ ሆነ

አስጠነቀቃት፡፡ ሺ.ርሊ ግን አንዴ ቆርጣ ነበር፡፡ ኤም.ዲ. አንዴርሰንን ለቃ ወጣች፤ ከዚያ በኃላም ወደዚያ አልተመለሰችም፡፡ ወደ ቤቷ ተመልሳ በመጻሕፍት፣ በካሴት መልእክቶችና በመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት አማካይነት በየቀኑ ሕይወቷን በእግዚአብሔር ቃል መሙላት ጀመረች፡፡

ይህ ከሆነ አሁን፣ ሰላሣ አንድ ዓመት ቢያልፈውም ዛሬም ጤነኛ ነች፣ እኛ ካለንበት ቦታ መንገዱን ተሻግሮ ያለ ቤት ውስጥ ነው የምትኖረው፡፡ እንዲያውም በሰባ አምስት ዓመቷ በመጻሕፍቶቻችን አማካይነት በመላው አሜሪካ ያሉ ሃያ አምስት ሺህ አብያተ ክርስቲያናትን እያገለገለ ካለው ሰባት ሰዎች ባሉበት ከቤተ ክርስቲያን ጋር ተያያዥነት ባለው አገልግሎት ዘርፍ ውስጥ እያገለገለች ነው፡፡ በሥራ ድርሻዋ የሚያስፈልጋቸውን ማግኘት እንዲችሉ ብዛት ያላቸው ፓስተሮችንና የቤተ ክርስቲያን ሠራተኞችን ረድታለች፡፡

በአገልግሎት ባሳለፍኩዋቸው ዓመታት ሁሉ ለፈውስ ለመጸለይ የሺ.ርሊን ያህል የሚቀለኝ ያገኘሁት በጣም ጥቂት ሰዎችን ነው፡፡ እኔና ሊዛ ከተጋባን በኋላ በጣም ብዙ ሳይቆይ፣ አንድ ቀን ከሥራ ወደ ቤት ስመጣ ልትጠይቀኝ ወደ እኛ መጥታ የነበረችው ሺ.ርሊ ከባድ ፍሉ አሞአት ነበር፡፡ ወደ ቤት ስገባ ሺ.ርሊ ራሷን እየጐተተች ፎቅ ላይ ወዳለው አልጋ እየሄደች ነበር፡፡ እንደ ልቧ ለመራመድ እንኳ ዐቅም አልነበራትም፡፡ መምጣቴን እንዳየች ወዲያውኑ፣ ‹‹ጆን እንድትጸልይልኝና ከዚህ ፍሉ እንድገላገል እፈልጋለሁ›› አለች፡፡

እየጸለይኩላት እያለ የእግዚአብሔር ኃይል ስለ ነካት መቆም አልቻለችም፡፡ ወለሉ ላይ ተዘረረች፡፡ ብዙም ሳትቆይ ተስፈንጥራ በመነሣት ክፍሉ ውስጥ እየተንጐራደደች፣ ‹‹ፍጹም ተፈውሻለሁ፤ ራት ልሠራላችሁ እችላለሁ!›› አለች፡፡ በጣም የሚጣፍጥ ምግብ ሠርታልን በላን፡፡ እኔም እየሳቅሁ፣ እንዴት ይገርማል ጴጥሮስም፣ የዚህ ዐይነት ሁኔታ ገጥሞት ነበር አልኩ፡፡ የሚስቱ እናት ታምማ ነበር፤ ኢየሱስ ፈወሳት፤ እርሷም የሚበላ ነገር ሠራችላቸው (ማቴዎስ 8፥14-15 ይመ)፡፡

ሺ.ርሊ በቀላሉ ጸሎት የምትቀበል ብቻ ሳትሆን ሌሎች እንዲፈወሱ መጸለይን በተመለከተም ኃይል የሞላባት ሴት ነበረች፡፡ አንድ የታመመ ወይም ጉዳት የደረሰበት ሰው አጠገቧ ካለ የእግዚአብሔርን ቃል ማካፈልና ለሕመምተኛው መጸለይ ለእርሷ ቀላል ነገር ነበር!

ሺ.ርሊ ከካንሰር ነጻ ሆና ሰላሣ አንድ ዓመት በጤንነት ኖረች፤ አሁንም እየኖረች ነው! የገጠማትን መከራ በጽናት በእግዚአብሔር ቃል

በመዋጋት ፈውስን በተመለከተ የሕይወት አክሊል አገኘች፡፡ ያን መከራ ታግሣ አሸነፈች፤ አሁን ጸንታ ባለችበት ሕይወት እየነገሠች ነው፡፡

## ድል ነሺዎች

ሌሎችም ተመሳሳይ ዐይነት ምስክርነት አላቸው፡፡ በአሁኑ ጊዜ ያለው በሰማይ ቢሆንም፣ ቅርስና ምሳሌነቱ ዛሬም ሕያው የሆነው ኦራል ሮበርትስን ውሰዱ፡፡ የአሥራ ሰባት ዓመት ወጣት እያለ ኦራል በሳምባ በሽታ ሊሞት ነበር፡፡ የእግዚአብሔርን ቃልና ጸሎትን ተገን በማድረግ ሕመሙን በጽናት ተዋጋ፤ በኃላም ፍጹም እንደ ተፈወሰ ዶክተሩ መሰከረለት፡፡ እንደ ሺርሊ ሁሉ ኦራልም ከፈውስ አንጻር የሕይወትን አክሊል አገኘ፤ በኃላም በሕይወቱና በአገልግሎቱ ሚሊዮኖች ተነክተዋል፤ ሚሊዮኖች ተፈውሰዋል፡፡

ለዓመታት ፓስተር የነበረና በአገልግሎቱ ብዙዎች ላይ ተፅዕኖ ማሳደር የቻለ ጂሚ የሚባል ጓደኛ አለኝ፡፡ ገና በወጣትነቱ ይሞታል ብለው ዶክተሮች ተስፋ ስለ ቆረጡ ኦራል ሮበርትስ ያደርግ ወደ ነበረው ስብሰባ ተወስዶ ነበር፡፡ ኦራል ከጸለየለት በኋላ፣ ጂሚ በተአምር ተፈወሰ፡፡

ወጣት በነበረ ጊዜ ኦራል በእምነት ባይጸና ኖሮስ? በኦራል ሮበርትስ አገልግሎት ፈውስ ካገኙ ሌሎች ሚሊዮኖች ጋር፣ ያ ፓስተር ጓደኛዬ የት ነበር የሚገኘው? ፓስተር ጂሚ የዘላለምን ሕይወት ወደ መቀበል የመራቸው ሰዎችስ ዛሬ የት ይሆኑ ነበር? ኦራል አገዛዝ ውስጥ ገብቷል፡፡ በእምነት የመጽናት ውጤት በሙላት የሚታወቀው በፍርድ ወንበር ፊት ብቻ ነው፡፡

ወይም ደግሞ ኬኔዝ ኢ.ሔጊንን ውሰዱ፡፡ ጤናማ ካልነበረ ልብ ጋር በምክኒ ቴክሳስ በ1917 ዓ.ም ተወለደ፤ በኃላም በተደረገለት ምርመራ አልፎ አልፎ ብቻ የሚገኝ የማይድን የደም ችግር እንዳለበት ታወቀ፡፡ በአሥራ ስድስት ዓመቱ የአልጋ ቁራኛ ሆነ፤ አሥራዎቹን ዓመታት ያልፋል ተብሎም አልተጠበቀም ነበር፡፡ በ1933 ዓ.ም ኬኔዝ ሦስት ጊዜ ሞቶ ገሃነምን አይቷል፡፡ ሦስቱንም ጊዜ በተአምር ተመልሷል፡፡ ኬኔዝ ኢየሱስን የሕይወቱ ጌታ አደረገ፡፡ የእግዚአብሔርን ቃል በጽናት በማመን በሽታውን ተዋጋ፡፡ እርሱን ለመጠየቅና ለማጽናናት መጥቶ የነበረ ፓስተር፣ ‹‹ልጄ፣ አይዞህ በርታ፤ በጥቂት ቀኖች ውስጥ ሁሉም ያበቃል›› አለው፡፡ ከአንድ ዓመት በኃላ ኬኔዝ፣ ‹‹ለሞት ከተኛበት አልጋ›› ተነሣ፤ ከዚያም ብዙም ሳይቆይ መስበክ ጀመረ፡፡

የኬኔዝ ሔጊን አገልግሎት በመላው ዓለም ታዋቂ ሆነ፤ መጻሕፍቶቹ ከስልሣ አምስት ሚሊዮን በላይ ቅጂዎች ታትመዋል፤ ከሰላሣ ሺህ በላይ ወንዶችና ሴቶች የተመረቁበት የመጽሐፍ ቅዱስ ማሠልጠኛ ማዕከል

መሥርቶአል፤ ከእነዚህ ብዙዎቹ አሁንም የሙሉ ጊዜ አገልግሎት ውስጥ ናቸው፡፡ ስልሳ አምስት ዓመት በአገልግሎት ካሳለፈ በኃላ አሁን ኬኒዝ ከጌታ ጋር ነው፤ ቅርስና ምሳሌነቱ ግን አሁንም አብሮን አለ፡፡ ከፈውስ አንጻር የሕይወትን አክሊል አገኘ፤ ከዚያም የተነሣ ስፍር ቁጥር የሌላቸው ብዙዎች ተፈውሰዋል፤ በታማኝ አገልግሎቱ የብዙዎች ሕይወት ተለውጦአል፡፡

ኬኔዝ በእምነት ባይጸና ኖሮስ? እርሱ ያገለገላቸው ሚሊዮኖች ምን ዓይነት ተፅዕኖ ሊያድርባቸው ይችል ነበር?

እነዚህ ታሪካቸውን ያካፈልኳችሁ ሦስት ሰዎች ማለትም፣ የሚስቴ እናት፣ ሺርሊ ኦራል ሮበርትስና ኬኔዝ ሔጊን አንድ የጋራ ነገር አላቸው፡፡ ሁሉም ጥቃት ደርሶባቸዋል፤ ሐሰት ተወርቶባቸዋል፤ ክፉዎች ናቸው ተብለዋል፡፡ የእግዚአብሔርን ፈዋሽነት ለማመን ከወሰነች በኋላ የሺርሊ ጐረቤት ባል ከእርሷ ጋር መነጋገር አቁሞአል፡፡ በሕይወት በነበሩ ጊዜ ኦራል ሮበትስና ኬኔዝ ሔጊን ተሳስተዋል፤ ጽንፈኞች ሆነዋል፤ መናፍቃን ሆነዋል ተብለዋል፤ ሌላው ቀርቶ የሚሠሩት በአጋንንታዊ ኃይሎች እንደ ሆነ እንኳ ተወርቶባቸው ነበር፡፡ ግን እነዚህን የመሳሰሉ ሁኔታዎች በተመለከተ ኢየሱስ ምን ብሎ ነበር? ‹‹ሰዎች ሁሉ ስለ እናንተ መልካሙን ሲናገሩላችሁ ወዮላችሁ፤ የቀድሞ አባቶቻችሁ ለሐሰተኞች ነቢያት ያደረጉላቸው ይህንኑ ነበርና›› (ሉቃስ 6፥26)፡፡

ሰዎችን ላለማስቀየም በማሰብ የመንግሥቱን መልእክት ያላሰለሱና የሸቃቀጡ ብዙ አገልጋዮችና አማኞች አሉ፡፡ ‹‹ጽንፈኞች›› – ወይም፣ ‹‹ጥበብ የጐደላቸው›› እንዳይባሉ በመፍራት መልካሙን የእምነት ገድል ከመጋደል ወደ ኃላ አፈግፍገዋል፡፡ በእነርሱ አስተሳሰብ የሚሆነው ነገር ሁሉ የእግዚአብሔር ፈቃድ ነው፤ ስለሆነ ማንኛውንም ነገር አሜን ብሎ መቀበል ይገባል፡፡ ሰዎችን ያሰናክላል ብለው የሚያስቡትን ክፍል ከወንጌሎቹ አውጥተዋል፤ ይሁን እንጂ፣ ኢየሱስ ራሱ፣ ‹‹የመሰናከያ ዐለት›› ተብሎ እንደ ነበር ዘንግተዋል፡፡ መጽሐፍ ቅዱስ ኢየሱስን ‹‹የመሰናከያ ዐለት›› በማለት ቢጠራውም፣ እነርሱ ለማንም መሰናክል ወደማይሆን ትንሽ ጠጠር ደረጃ አውርደውታል፡፡

እነዚህ ፓስተሮች፣ አገልጋዮችና አማኞች ሰዎች ሁሉ መልካሙን እንዲናገሩላቸው የሚፈልጉ ይመስላሉ፣ ጽንፈኛ፣ መናፍቅ፣ ወይም የሚሠሩት በአጋንንት ኃይል ነው ተብለው አይከሰሱም፡፡ ኢየሱስ ግን እነዚህ ነገሮች ሁሉ እንደሚኖሩ ያውቃል፡፡ እውነትን በተመለከተ ግን አላወላወለም፡፡ ሰዎች ሁሉ መልካሙን እንዲናገሩላቸው የሚፈልጉ ሰዎችን ስሕተት

አጋልጦአል፡፡ ‹‹ሰዎች… ሲጠሏችሁ፤ ከመካከላቸው ሲለዩዋችሁና ሲነቅፏችሁ ክፉ ስምም ሲሰጧችሁ ብፁዓን ናችሁ›› ብሏል (ሉቃስ 6፥22)፡፡ ይህ ደግሞ መልካም ብቻ የሚወራላቸው ከመሆን በጣም ይቃረናል፡፡

እውነታው ይህ ነው፤ በሕይወት የሚነግሥ ጽናት ያለው አማኝ መሆን ከመረጣችሁ፣ ኢየሱስ ክርስቶስን እንከተላለን በሚሉ ይሁን እንጂ በሕይወት ምቾት በተዋጡ ሰዎች፣ የምትነቀፉበት፣ በሐሰት የምትከሰሱበት፣ የሚረዳችሁ ሰው የምታጡበትና እንዲያውም የምትገለሉበት ሁኔታ ሊኖር ይችላል፡፡ የእነርሱን የተሳሳተ መንገድ ትክክል ለማስመሰል እናንተን ዋጋ ሊያሳጧችሁ ይሞክራሉ፡፡ እውነተኞቹ የብሉይ ኪዳን ነቢያት፣ መጥምቁ ዮሐንስ፣ ኢየሱስና የአዲስ ኪዳን መሪዎችም ላይ ይህንኑ አድርገው ነበር፡፡ ዛሬም ያንኑ እያደረጉ ነው፡፡ ብዙ ጊዜ ትልቅ ተቃውሞ ሊገጥማችሁ የሚችለው እግዚአብሔርን እናውቃን ከሚሉ ሰዎች ነው፡፡ ውሸት ከማስወራት ጀምሮ እስከ ፊት ለፊት ነቀፋ፣ ከዚያም እስከ ማግለል ሊደርስ ይችላል፡፡ እንዲያውም ከዚያ በጣም አልፎ፣ ‹‹የሚገድላችሁ ሁሉ እግዚአብሔርን እንዳገለገለ የሚቈጥርበት ጊዜ ይመጣል›› በማለት ኢየሱስ ትንቢት እስከ ተናገረለት ደረጃ ሊደርስ ይችላል (ዮሐንስ 16፥2)፡፡

ለእግዚአብሔር ክብር ሕይወት ላይ መንገሥ ትፈልጋላችሁ? ለእግዚአብሔር መንግሥት ሰዎች ላይ ለዘላለም ተፅዕኖ ማሳደር ትፈልጋለችሁ? በዚያ ታላቅ ቀን ጌታ፣ ‹‹አንተ ታማኝ አገልጋዬ መልካም አድርገሃል›› ሲላችሁ መስማት ትፈልጋላችሁ? እንደዚያ ከሆነ አሁኑኑ እርግጠኛ ሁኑ፤ አንዳንዴ በጣም ከባድ መከራ (ትሊፕሲስ) ሊገጥማችሁ ይችላል፡፡ በእግዚአብሔር ጸጋ መቻልና በመጨረሻም ማሸነፍ ይኖርባችኋል፡፡

አሁንም አገዛዝ ውስጥ ለመግባትና መከራን ለመቀበል በእውነት ፈቃደኛ ከሆናችሁ፣ ማንበባችሁን ቀጥሉ፡፡ የበለጠው ጥሩ ነገር ፊታችሁ ነው ያለው፡፡

# 7

# ከመከራው በስተ ጀርባ ያለው ማነው?

*በክርስቶስ እንድታምኑ ብቻ ሳይሆን ስለ እርሱ መከራ እንድትቀበሉም ይህ ጸጋ ተሰጥቷችኋል፡፡*

*ፊልጵስዩስ 1፥29*

ፊልጵስዩስ 1÷29ን መጀመሪያ ሲያነቡት የሚስብ ነገር አለው፡፡ ‹‹… ይህ ጸጋ ተሰጥቷችኋል››፡፡ የተቀረውን የጥቅሱን ክፍል ሳናውቅ ይህን ቃል ብቻ ሰምተን ቢሆን ኖሮ፣ ‹‹የተሰጠን ምንድነው? የተገባልን ቃል ምንድነው?›› በማለት በመጓጓት እንጠይቅ ነበር፡፡

መልሱ፣ ‹‹መከራ እንድትቀበሉ›› ነው፡፡

ምን? መከራ የመቀበል መብት መቼም ቢሆን ለሰው አእምሮ የሚመች አይደለም፡፡ ይሁን እንጂ፣ እግዚአብሔር ማንንም አያታልልም፤ ምክንያቱም እርሱ መዋሸት አይችልም፡፡ እንዲሁ ላይ ላዩን ለሚያስብ ሰው፣ ይህ ጥቅስ አንድ ዓይነት ማታለል ያለበት ሊመስለው ይችላል፤ ለሚያስተውል ሰው ግን በጣም የሚያጓጓ ተስፋ አለበት፡፡ በክርስቶስ እየተመላለሱና እያደጉ ያሉ ሰዎች፣ በጥልቅ ልቦናቸው ውስጥ ይህን እውነት ያውቃሉ፣ ውጊያው ታላቅ የመሆኑን ያህል ድሉም የዚያኑ ያህል ታላቅ ይሆናል፡፡

ዘወትር ለውጊያ እየሠለጠነ ስላለ አንድ ታማኝ ወታደር አስቡ፡፡ የውጊያውን ወሳኝነት በሚገባ ይረዳል፤ ውጊያ መኖሩ ራሱ የሚገኘውን ድል አመላካች ነው፡፡ በጥልቅ ልቦናው ሽንፈት አያውቅም፤ የንጉሡን ዓላማ ማገልገልም ይፈልጋል፡፡ ገና ጦርነቱ ሲታወጅ እርሱና ጓደኞቹ ባገኙት ዕድል ደስ ይሰኛሉ፤ ምክንያቱም በሚገኘው ድል ለንጉሣቸው ክብርና ታላቅነትን፣ ለሕዝባቸውም ጥቅምን እንደሚያመጣ ያውቃሉ፡፡ አሸናፊ ሆኖ ይገኝ ዘንድ ለንጉሡና ለመንግሥቱ ውጊያ በሚያስከትለው ውጣ ውረድ

የመካፈል መብት ለእርሱ ተሰጥቶታል፡፡ ፊልጵስዩስ 1፥29 ከዚህ ምሳሌ ጋር ሊኖረው የሚችለውን ተዛማጅነት አያችሁ?

ምናልባትም፣ ‹‹እኔ'ኮ ወታደር አይደለሁም፤ አሸንፋለሁ የሚል ተስፋም የለኝም›› ትሉኝ ይሆናል፡፡ በክርስቶስ ከሆናችሁ በእርግጥ ወታደሮች ናችሁ፤ ምክንያቱም ዘሩ መንፈሳችሁ ውስጥ ይኖራል፡፡ ኢየሱስ እስከ ዛሬ ከኖሩት ሁሉ የበለጠ ታላቅ ወታደር ነበር፡፡ እርሱን በተመለከተ መጽሐፍ ቅዱስ የሚናገረውን ስሙ፣ ‹‹...በጽድቅ ይፈርዳል፤ ይዋጋልም፡፡ ዐይኖቹ እንደ እሳት ነበልባል ናቸው... ስለታም ሰይፍ ከአፉ ወጣ›› (ራእይ 19፥11-12፣15)፡፡ በእርሱ መልክና አምሳል እንደ ገና ተፈጥራችኋል፤ የእርሱ ባሕርይ አላችሁ፡፡ ክርስቶስ ተዋጊ ስለ ሆነ እናንተም ተዋጊዎች ናችሁ፡፡ አዲስ ኪዳን ደጋግሞ ስለ ውጊያ የሚናገረው በዚህ ምክንያት ነው፡፡ ጳውሎስ እንዲህ ይላል፣

> ተጋድሎአችን ከሥጋና ከደም ጋር ሳይሆን፣ ከዚህ ከጨለማ ዓለም ገዦች፣ ከሥልጣናትና ከኃይላት እንዲሁም በሰማያዊ ስፍራ ካሉ ከርኩሳን መናፍስት ሰራዊት ጋር ነው (ኤፌሶን 6፥12)፡፡

ለሕይወት ወይም ለሞት ውጊያ ላይ ነን፤ ይህን ውጊያ እስከ መጨረሻው መዋጋት አለብን እንጂ ልናስወግደው አንችልም፡፡ ጳውሎስ ለቆሮንቶስ ቤተ ክርስቲያንም ተመሳሳይ መልእክት ጽፎአል፤ ‹‹የምንኖረው በዚህ ዓለም ቢሆንም፣ የምንዋጋው በዚህ ዓለም ስልት አይደለም፡፡ ደግሞም የምንዋጋበት የጦር መሣሪያ የዚህ ዓለም መሣሪያ አይደለም፤ . . . መሣሪያችን መለኮታዊ ኃይል ያለው ነው›› (2 ቆሮንቶስ 10፥3-4)፡፡ ውጊያ ላይ ያለን መንፈሳዊ ወታደሮች መሆናችን ግልጽ ነው! የተጠራችሁት ለዚህ ውጊያ ነው፡፡ ከልባችሁ ተዋጊዎች ናችሁ፡፡ ጳውሎስ፣ ‹‹እንደ ክርስቶስ ኢየሱስ በጎ ወታደር፣ ከእኛ ጋር መከራን ተቀበል፡፡ በውትድርና የሚያገለግል ሰው አዛዡን ለማስደሰት ይጥራል እንጂ በሌላ ነገር ራሱን አያጠላልፍም›› በማለት ይመክረናል (2 ጢሞቴዎስ 2፥3-4)፡፡ ቁርጣችሁን እወቁ፤ በክርስቶስ ወታደሮች ናችሁ፡፡

እንደ አንድ ወታደር ከውጊያ በመራቅ ወይም በመሸሽ የፈሪን መንገድ መምረጥ ትችላላችሁ፤ ወይም ደግሞ ውጊያውን በድል ለመወጣት እንደ ጀግና በወኔ የመዋጋትን መንገድ መምረጥ ትችላላችሁ፡፡ የመጀመሪያውን ከመረጣችሁ፣ ግን በሚያሳዝን ሁኔታ እንደ ከሃዲ ትታሰባላችሁ፡፡ የጀግንነትን መንገድ ከመረጣችሁ፣ በንጉሡ ፊት ለጀግና የሚገባውን ምስጋና ትቀበላላችሁ፡፡

በክርስቶስ የተወደዳችሁ ወገኖቼ፣ በልባችሁ ንጉሣችንን ደስ ለማሰኘት፣ እርሱን ለማክበርና ለእርሱ ለመኖር እንደምትፈልጉ አውቃለሁ፡፡ እንዲገዛችሁ ከፈቀዳችሁለት የክርስቶስ መከራ ተካፋይ የመሆንን ዕድል የሚያሳጣችሁና ተፅዕኖ የሚያደርግባችሁ ሥጋችሁ ብቻ ነው፡፡

የእርሱ መከራ ተካፋዮች ከሆንን፣ ከኢየሱስ ክርስቶስ ጋር እንደምንነግሥ ከሮሜ መልእክት ተመልክተናል፡፡ ውጊያን መጋፈጥና ተቃውሞንና መከራንም ማሸነፍ እንደሚገባን ግልጽ ነው፡፡ ይሁን እንጂ፣ ዝንባሌያችን በደስታ የመጠባበቅ መሆን አለበት፤ መከራን እንደ አንድ ስጦታ እንጂ፣ እንደ አንድ አስፈሪ ነገር መቁጠር የለብንም፡፡ ውጊያው ታላቅ የመሆኑን ያህል ድሉም ታላቅ ይሆናል - የኃላ ኃላ የሚገኘውም ክብር ታላቅ ይሆናል፡፡ አንድ የምሥራች ልንገራችሁ፤ በውጊያው በፍጹም አትሸነፉም! ምክንያቱም፣ ‹‹በክርስቶስ ሁልጊዜ በድል አድራጊነት እያዞረ ለሚመራን አምላክ ምስጋና ይሁን›› የሚል ተስፋ ቃል ተሰጥቶናል (2 ቆሮንቶስ 2፥14)፡፡

## እግዚአብሔር ልጅ ልቅ እንዲሆን አይፈቅድም

ባለፈው ምዕራፍ የኢየሱስን ጥምቀት ተከትሎ፣ ወዲያውኑ ስለ ተፈጸሙ ጉልህ ነገሮች ተመልክተናል፡፡ መንፈስ ቅዱስ ለአርባ ቀንና ሌሊት ወደሚፈተንበት በረሓ ኢየሱስን መራው፡፡ ኢየሱስን ወደ በረሓ የወሰደው እግዚአብሔር እንጂ፣ ዲያብሎስ አልነበረም፡፡ ልጁ ላይ ከባድ ፈተና እንደሚደርስ እግዚአብሔር ያውቅ ነበር፤ ሆኖም፣ በዓላማ ወደዚያ ወሰደው፡፡ የተማርነው መርሕ፣ የምናሸንፍበትን ኃይል ሳይሰጠን እግዚአብሔር በፍጹም ወደ ማዕበሉ አይወስደንም የሚል ነበር፡፡ ይህ እውነት፣ ለዘለቄታው ልባችሁ ውስጥ ይታተም፤ ምክንያቱም አንድ ቀን ከመከራ ጋር ስትጋፈጡ ብርታት ይሰጣችኃል፡፡

በመጀመሪያ የአባቱ ፈቃድ መሆኑን እርግጠኛ ካልሆነ በቀር ምንም እንደማያደርግ ወይም ምንም እንደማይናገር ኢየሱስ ግልጽ አድርጓል፡፡ ሙሉ በሙሉ የሚመራው በእግዚአብሔር መንፈስ ነበር፤ ‹‹አብ ያስተማረኝን እናገራለሁ፤ በራሴም ፈቃድ ምንም አላደርግም›› ብሏል (ዮሐንስ 8፥28)፡፡

አንድ ቀን ኢየሱስ ቀኑን ሙሉ ሕዝቡን ሲያስተምር ውሎ ስለ ነበር በጣም ደክሞት ነበር፡፡ በበኩሌ ምን ሊሰማው እንደሚችል በመጠኑም ቢሆን አውቃለሁ፡፡ አንዳንዴ በቀን አራት ወይም አምስት ጊዜ ስለምሰብክ ወዳረፍኩበት ሆቴል ስመለስ በጣም ስለሚደክመኝ ቶሎ መተኛት እንጂ፣ ከማንም ጋር መጨዋወት አልፈልግም፡፡

ኢየሱስ ላይ የሆነውም ይኸው ሊሆን ይችላል፡፡ ምሽት በመድረሱ ሌሊቱን በጥሩ እንቅልፍ ለማሳለፍ ተዘጋጅቶ ነበር፤ ሆኖም፣ ከባሕሩ ማዶ ወዳለው ቦታ የሚሄዱበት ጀልባ እንዲያዘጋጁ ለደቀ መዛሙቱ እንዲናገር መንፈስ ቅዱስ ኢየሱስን አሳሰበው፡፡ ከባሕሩ ወዲያ ማዶ ነጻ መሆን የነበረበት አንድ አጋንንት ያደሩበት ሰው ነበር፡፡ ሁሉም በጀልባ ተሳፈሩ፤ ኢየሱስን ግን ጀልባው ውስጥ ጭልጥ ያለ እንቅልፍ ወስዶት ነበር፡፡

ባሕሩ ላይ ከባድ ማዕበል ተነሣ፡፡ አብረውት ከነበሩት ሰዎች አራቱ ዕድሜ ልካቸውን በባሕር ሲመላለሱ የኖሩ ልምድ ያላቸው ባሕረኞች ነበሩ፡፡ ባሕር ላይ ሊኖር የሚችለውን አደጋና እንዴት መወጣት እንዳለባቸው ያውቁ ነበር፤ ይኸኛው ግን ተራ ማዕበል አልነበረም፡፡ እያከታተለ ማዕበል ይመታቸው ነበር፤ በመጨረሻም እነዚህ ከፍተኛ ልምድ የነበራቸው ባሕረኞች እየጮኹ ኢየሱስን ቀሰቀሱት፤ ‹‹ለመሆኑ ሁላችንም ተያይዘን ስናልቅ ምንም ግድ አይልህም?›› አሉት፡፡ ከዚያ አደጋ (ትሊፐሲስ) በሕይወት የመትረፉ ዕድል አልታያቸውም፡፡

በዚያ ማዕበል ምክንያት እግዚአብሔር አብና መንፈስ ቅዱስ የተሸበሩ ይመስላችኋል? እርስ በርስ እየተያዩ፣ ‹‹በፍጹም አናምንም! እንዲህ ያለ አደገኛ ማዕበል ይመጣል ብለን አላሰብንም ነበር! ታዲያ፣ ምን ማድረግ አለብን? ወደ ባሕሩ ማዶ እንዲሄድ ለኢየሱስ ለምን ነገርነው? ትልቅ ስሕተት ፈጽመናል!›› የተባባሉ ይመስላችኋል?

እንዲህ ያለውን ማሰቡ ራሱ እንኳ ያስቃል፡፡ ማዕበል እንደሚነሣ መንፈስ ቅዱስ ያውቅ ነበር፤ እርሱ ከመጀመሪያ እስከ መጨረሻ ያለውን ያውቃል፡፡ ‹‹የመጨረሻውን ከመጀመሪያው፣ ገና የሚመጣውንም ከጥንቱ ተናግሬአለሁ፤ ዐላማዬ የጸና ነው›› (ኢሳይያስ 46፥10)፡፡ ከባድ ማዕበል እንደሚጠብቀው በሚገባ እያወቀ ነበር በጀልባው እንዲሳፈር ኢየሱስን የመራው፡፡ ያም ሆኖ ግን፣ የምናሸንፍበትን ኃይል ሳይሰጠን፣ እግዚአብሔር በፍጹም ወደ ማዕበሉ አይመራንም፡፡ ከእንቅልፉ ከነቃ በኋላ ኢየሱስ ወደ ጀልባው የፊት ክፍል ሄዶ ፀጥ እንዲል ማዕበሉን አዘዘው፤ ከዚያም ወደ ደቀ መዛሙርቱ ዘወር ብሎ፣ ‹‹ስለ ምን እንዲህ ፈራችሁ? እስከዚህ እምነት የላችሁም? በማለት ጠየቃቸው (ማርቆስ 4፥40)፡፡

> መንፈስ ቅዱስ ... ከመጀመሪያ እስከ መጨረሻ ያለውን ያውቃል፡፡

ሕይወታቸውን ለማዳን ያን ሁሉ ትግል ላደረጉ ደቀ መዛሙርት፣ ኢየሱስ እንዲህ ያለ ጠንከር ያለ የተግሣፅ ቃል የተናገረው ለምንድነው? ገና ከመነሣታቸው በፊት፣ ‹‹ወደ ማዶ እንሻገር›› ብሎአቸው ነበር (ቁጥር 35)፡፡

‹‹ወደ ባሕሩ መካከል ሄደን እንስጠም›› አልነበረም ያላቸው፡፡ በኢየሱስ ቃል ውስጥ ወደ ማዶ የሚያደርሳቸው ጸጋ (ኃይል) መኖሩን ሊያውቁ ይገባ ነበር፡፡ ጀልባው ዳር ቆመው፣ ‹‹አንተ ማዕበል፣ በፍጹም ልታጠፋን ወይም ልታስቆመን አትችልም! ጌታ፣ ወደ ማዶ እንሻገር ስላለ ወደ ባሕሩ ዳርቻ እንደርሳለን፤ ይልቁን መንገዳችንን ልቀቅ!›› በማለት ሊገሥጹት ይገባቸው ነበር፡፡

ማዕበል እንደሚነሣ እግዚአብሔር ያውቅ ነበር፡፡ ወደዚያ የመራቸው እርሱ ነበር፤ ሆኖም፣ ማዕበሉን የሚገዙበትን ኃይልና ሥልጣን ለኢየሱስ ደቀ መዛሙርት ሰጥቷቸውም ነበር፡፡ ቁልፉ ያለው እዚያ ላይ ነበር፡፡ በሕይወት የሚገዙትን፣ በሕይወት ከሚሸነፉት የሚለያቸው፣ ውጊያና ግጭት የማይቀር መሆኑን ማወቃቸውና ከተፈጥሮአዊው ሰው በተለየ ሁኔታ በመንገዳችን በሚገጥመን ነገር ሁሉ ላይ ሥልጣን ያለን መሆኑን ማወቃቸው ነው፡፡ ስለዚህም ውጊያው በድል እስኪጠናቀቅ ድረስ በጽናት መዋጋት እንችላለን፤ ደግሞም ይኖርብናል፡፡ 2 ቆሮንቶስ 2፥14 ላይ ያለው ቃል ወደ እያንዳንዱ የሰውነታችን ክፍል ዘልቆ ይግባ፣ ‹‹በክርስቶስ ሁልጊዜ በድል አድራጊነት እያዞረ ለሚመራን አምላክ ምስጋና ይሁን››፡፡

ሁኔታው ለደቀ መዛሙርቱና ውሱን ለሆነ ዕይታቸው ተለቆ ቢሆን ኖሮ፣ ሁሉም ሰጥመው ይሞቱ ነበር፡፡ ይሁን እንጂ፣ ማዕበሉን ለመዋጋት ኢየሱስ በመወሰኑ፣ እነርሱ በሕይወት ከመትረፋቸው በተጨማሪ፣ ከባሕሩ ማዶ ለነበረው ለዚያ አጋንንት ለነበሩበት ሰው ነጻ መውጣትም ምክንያት ሆነ፡፡

ጥቅሙ እዚያም ላይ አላበቃም፤ የተፈወሰው ሰውዬ በዴካፖሊስ በነበሩ ዐሥር ከተሞች የእግዚአብሔርን መንግሥት ዐወጀ፡፡ የኃላ ኃላም ብዙዎች ለእግዚአብሔር መንግሥት ሳይማረኩ አልቀረም፡፡ ኢየሱስና አብረውት የነበሩትን ሰዎች መንፈስ ቅዱስ ወደ ማዕበሉ መራቸው፤ በዚያም ምክንያት ችግር ገጠማቸው፤ ሆኖም፣ እንዲሸነፉ የእግዚአብሔር ፈቃድ አልነበረም፡፡ ይልቁንም፣ የእግዚአብሔር ትኩረት ከማዕበሉ ባሻገር ያለው ክብር ላይ ነበር፡፡

ሐዋርያቱን አግኝተን፣ ‹‹ያንን ሰው ነጻ ለማውጣት በዚያ ሁሉ ማዕበል ውስጥ ማለፍ ተገቢ ነበር ወይ?›› ብለን ብንጠይቃቸው፣ ያለ ምንም ጥርጥር፣ ‹‹በጣም እንጂ!›› በማለት ይመልሱ ነበር፡፡

እስቲ ሌላም ነገር እንመልከት፡፡ ሐዋርያው ጳውሎስ በመንፈስ ቅዱስ ተመርቶ ለአገልግሎት ወደ ኢየሩሳሌም እየሄደ ነበር፡፡ ግን እዚያ የሚጠብቀውን ከራሱ አንደበት እንስማ፣

> እዚያ ስደርስ የሚደርስብኝን ባላውቅም፣ መንፈስ ቅዱስ ወደ ኢየሩሳሌም እንድሄድ ግድ እያለኝ ነው፡፡ ነገር ግን በምሄድባቸው ከተሞች ሁሉ እስራትና መከራ እንደሚጠብቀኝ መንፈስ ቅዱስ ይመሰክርልኛል፡፡ (ሐዋርያት ሥራ 20፥22-23)

ከላይ ባለው ጥቅስ መከራ የሚለው ግሪክ ቃል ትሊፕሲስ ነው፡፡ (ከዚህ በፊት አይተነው እንደ ነበር፤ ትዝ አላችሁ?) መንፈስ ቅዱስ ጳውሎስን ከባድ መከራ ወደሚያገኘው ቦታ እየመራው ነበር፡፡ አሁንም በድጋሚ ለመናገር፣ እርሱ ወደሚመራን ቦታ ስንሄድ መንገድ ላይ የሚገጥመንን ሁሉ ማሸነፍ የምንችልበትን ጸጋ እግዚአብሔር ሁሌም ይሰጠናል፡፡

በዚያ መከራ ውስጥ ጳውሎስ በጽናት በመቆሙ ውጤቱ ምን ሆነ? በኢየሩሳሌም የነበሩ አይሁድም ሆኑ አሕዛብ ወንጌልን ከመስማታቸው ሌላ፣ ወታደሮች፣ ዳኞች፣ የአካባቢ ንጉሦችና ሌላው ቀርቶ ቄሳር ራሱ እንኳ ሳይቀር፣ በሮም ግዛት የነበሩ ብዙዎች ወንጌልን መስማት ቻሉ! እንግዲህ ይህ ሁሉ፣ የዚያ ወደ ማዕበሉ የተመራ ሰው ውጤት ነበር፡፡ እግዚአብሔር የማዕበሉ ወይም የመከራው ፈጣሪ አልነበረም፤ ይሁን እንጂ፣ የእግዚአብሔር መንገድ ጠላት በሆነው የወደቀው ዓለም ምክንያት ያ ጳውሎስ ላይ እንደሚደርስ ያውቅ ነበር፡፡ ያም ሆኖ የመንፈስን ምሪት እንዲከተል የክርስቶስ ፍቅር ጳውሎስን ግድ አለው፤ እግዚአብሔር መከራውን የሚያሸንፍበት ጸጋ ሰጠው፡፡ ጳውሎስ ጉዞውን እጥር ምጥን ባለ ቃል ሲገልጸው፣ ‹‹ጌታ ግን ከእነዚያ (ከመከራዎቹ) ሁሉ አዳነኝ›› ብሏል (2 ጢሞቴዎስ 3፥11)፡፡ አነጋገሩ፣ ‹‹ከመከራ ሁሉ ታድጐኛልና›› ከሚለው የዘማሪው ቃል ጋር ይመሳሰላል (መዝሙር 54፥7)፡፡ ከአንዳንድ መከራዎች ወይም ከአብዛኞቹ መከራዎች ሳይሆን ከሁሉም መከራዎች፡፡ ያም 100% ማለት ነው!

ይኸው የተስፋ ቃል እኔና እናንተንም ይጨምራል!

## የወላጅ ምክር

የመጀመሪያ ልጃችን ኤዲሰን የመጀመሪያ ደረጃ ተማሪ እያለ እርሱ ክፍል ውስጥ የነበሩ አንዳንድ ጉልበተኞች ያስቸግሩት ነበር፡፡ ብዙ ጊዜ ወደ ቤት ሲመጣ እነዚህ ጉልበተኞች መጫወቻ ቦታ ላይ ባደረጉበት ነገር መንገድ ላይ ያለቅስ ነበር፡፡ እንደ አንድ አባት ምን ማድረግ እንደ ፈለግሁ

ሳትገምቱ አትቀሩም፡፡ ወደዚያ መጫወቻ ሜዳ ሄጄ፣ ልባቸው እስኪጠፋ ድረስ ብቆነጥጣቸውና፣ ‹‹ከእንግዲህ የኔን ልጅ ትነኩና ወይም ታስፈራሩና ወዮላችሁ!›› ብዬ ባስጠነቅቃቸው እፈልግ ነበር፡፡ ያ ግን ሦስት ችግሮች ይኖሩት ነበር፡፡ በመጀመሪያ፣ የሚደረገው ነገር መንፈሳዊነት ያለው አይሆንም፡፡ ሁለተኛ፣ እንደዚያ ማድረግ የኤዲሰንን ባሕርይ በማዳበር ረገድ ያልተፈለገ ውጤት ማስከተል ይችል ነበር፡፡ በሦስተኛ ደረጃ በዚያ ማጫወቻ ሜዳ የሚሆነውን ነገር የመቆጣጠር ሥልጣን የለኝም፡፡ የመጫወቻ ሜዳው የእኔ ቦታ ሳይሆን ልጄ ሊገዛው፣ በሥልጣን ሊጠቀምበት የሚገባ ቦታ ነው፡፡

ስለዚህም አይዞህ ብለን ካበረታታነው በኃላ እኔና ሊዛ ለኤዲሰን ማድረግ ያለብን የተሻለው ነገር እየደረሰበት ያለውን ችግር (ትሊፐሲስ) እንዴት ማስተናገድ እንዳለበት ማስተማር እንደ ሆነ ወሰንን፡፡ ሁሉጊዜ ማታ ማታ እኔና እናቱ በእነዚያ ጉልበተኞች ምክንያት እየደረሰበት ባለው ችግር ውስጥ ባሸናፊነት መውጣት የሚችልበትን ሐሳብና ምክር እንሰጠው ጀመር፡፡ በሚቀጥለው ቀን ወደ ትምህርት ቤት የምንሰደው የሚገጥሙትን አስቸጋሪ ሁኔታዎች ማስተናገድ በሚችልባቸው ዘዴዎች በማዘጋጀት ነበር (እርግጥ ነው፣ ኤዲሰን ላይ አደጋ የሚያደርስ ነገር ቢኖር ኖሮ አስተማሪውንና ዳይሬክተሩን እናናግር ነበር፡፡)

ስለዚህም በዚህና በልጅነት ጊዜው በገጠሙት ሌሎች ችግሮች ውስጥ በስኬት ካለፈ በኋላ፣ ከሰዎች ጋር አብሮ መኖርን በተመለከተ ኤዲሰን የተዋጣለት ሆነ፡፡ በ2004 ዓ.ም በጀማሪ ደረጃ አገልግሎታችንን ተቀላቅሎ ነበር፡፡ በዚያ ዘመን የዕድሜ ገደባቸው ከዐሥራዎቹ ጀምሮ በስልሳዎቹ ዓመታት ውስጥ የነበሩ አርባ ሠራተኞች ነበሩን፡፡ ልጄ በመሆኑ ብቻ ለኤዲሰን ምንም የተለየ ነገር እንዳይደረግለት ለአስተዳደር ቡድኑ ተናግሬ ነበር፡፡ በስድስት ወር ውስጥ መሪዎቻችን፣ ‹‹በቤተ ክርስቲያን ጉዳዮች ክፍል መሪ እንዲሆን ልናሳድገው እንፈልጋለን›› አሉኝ፡፡ ቤተ ክርስቲያን ነክ የሆኑ ጉዳዮች፣ የአገልግሎት በጣም አስቸጋሪ ገጽታ መሆኑ ይታወቃል፤ ስለዚህም ያንን ክፍል እንዲመራ ኤዲሰንን በደረጃ ማሳደግ ያስፈለገው ለምን እንደ ሆነ ጠየቅሁ፡፡ የቡድኑ መልስ፣ ‹‹የመሪነት ባሕርይ ስላለው›› የሚል ነበር፡፡

ኤዲሰን ያንን ኃላፊነት ያዘ፤ ሥራውም እየሰፋ ይሄድ ጀመር፡፡ ችግሮችን በመፍታትና አለመግባባትን በማስወገድ ረገድ ያለውን ብልህነትና ጥበብ ያስተዋሉ ሠራተኞችንና የመላው የአገልግሎቱ ኃላፊዎችን አመኔታ አገኘ፡፡ ዛሬ በሃያ አምስት ዓመቱ የሜሴንጀር ኢንተርናሽናል ስምሪት ክፍል ዋና ኃላፊ ሆኗል፤ ጥሩ ሥራም እየሠራ ነው፡፡ የዕድሜ ደረጃቸው ምንም

ይሁን ምን፣ የሠራተኞቹን ልብ መማረክ ችሏል፡፡ ስለዚህ ኃላፊነት ሰጡት፤ በአመራር ችሎታውም ይተማመናሉ፡፡

አሁን አንድ ጥያቄ ላንሣ፣ የመጀመሪያ ደረጃ ተማሪ እያለ በጉልበተኞቹ በገጠመው ችግር ምክንያት ኤዲሰንን ከዚያ ትምህርት ቤት አስወጥተን፣ ሌላ ትምህርት ቤት ብናስገባው ይሻል እንደ ነበር ታስባላችሁ? ከእነዚያ ጉልበተኞች በየቀኑ እንደሚገናኝ እያወቅሁ፣ መልኼ እርሱን ወደዚያው ትምህርት ቤት በመስደዴ፣ እኔን ክፉና ለልጁ ደንታ እንደሌለው አባት ትቆጥሩ ይሆን? ብዙዎች እንደዚያ እንደሚያስቡ አውቃለሁ፡፡ በተመሳሳይ መንገድ እግዚአብሔር እኛን በአስቸጋሪ ቦታዎች ማለትም፣ ለእግዚአብሔር መንግሥት መወረስ ባለባቸው አዳጋች ቦታዎች የሚመራንን ጨካኝና ለልጆቹ ደንታ የሌለው አባት ስለሆነ አይደለም፡፡ ያ ለዘለቄታ ጥቅማችን እንደሚሆን ያውቃል፣ ለእርሱ ክብርን እንደሚያመጣና ተግዳሮቶችን በእርሱ ጸጋ ካስተናገድን በመጨረሻ ለሕዝቡ ዘለቄታ ያለው ጥቅም እንደሚሆን ያውቃል፡፡

## የመከራ ምንጭ

ወደ ፊት ከመግፋታችን በፊት የመከራን ምንጭና በዚያ መሐል እግዚአብሔር ለእኛ የሚኖረውን ፈቃድ በተመለከተ ነገሩ ግልጽ ሊሆን ይገባል፡፡ ለብዙ ግለ ሰቦች በተለይም በሦስት ዋና ዋና የሕይወት ገጽታዎች መሰናከል ሊሆን ስለሚችል ይህን ርዕሰ ጉዳይ በሚገባ ማጥናት ወሳኝ ነው፡፡ በጣም አስፈላጊ ከመሆኑ የተነሣ ወደ አገዛዙ መግባትን በተመለከተ ጥናታችንን ከመቀጠላችን በፊት የተቀረውን የዚህ ምዕራፍ ክፍል ለዚሁ ርዕሰ ጉዳይ ላውለው እፈልጋለሁ፡፡

እስካሁን ድረስ የተመለከትናቸው ምሳሌች እግዚአብሔር የመከራ (የትሊፕስሲ) ምንጭ አለመሆኑን ያመለክታሉ፡፡ ይልቁንም ትሊፕሲስ ወይም ከባድ ግጭት፣ ተቃውሞና መከራ የሚመጣው ከወደቀው ዓለም ኃይላት ነው፡፡ ይህ ሁሌም እውነት ይሆን? እየገጠማችሁ ያለው ችግር ፈጣሪ፣ ምንጭ ወይም ምክንያት እግዚአብሔር ሊሆን ይችላል በማለት የምታስቡ ከሆነ የሚገባችሁን ያህል ለማሸነፍ ላትዋጉ ትችላላችሁ፤ ስለዚህም ለጥያቄው ተገቢ መልስ መስጠት ይኖርብናል፡፡

አንድ ወደ ጦር ሜዳ የሚሄድ ወታደር ማንን ወይም ለማን እንደሚዋጋ በሚገባ ያውቃል፡፡ በጣም አስተዋይ ከሆነም ጠላት የሚጠቀምበትን ዘዴ እንኳ ያውቃል፡፡ የጠላቱን ማንነትና ምንነት በተመለከተ በወታደሩ አእምሮ ቅንጣት ጥርጥር አይኖርም፡፡ ይሁን እንጂ፣

ከሰላሣ ዓመት በላይ ባሳለፍኩት የአገልግሎት ዘመን፣ በሚገጥማቸው መከራ በስተጀርባ ያለው ማን እንደ ሆነ እርግጠኛ ያልሆኑ ብዙ አማኞች አግኝቻለሁ፡፡ ምንም እንኳ፣ ‹‹ይህንንም የምናደርገው ሰይጣን መግቢያ ቀዳዳ እንዳያገኝ ነው፤ የእርሱን ዕቅድ አንስተውምና›› ተብሎ ቢነገረንም፣ እነዚህ ወገኖች የጠላታቸውን ስልት በሚያሳዝን ሁኔታ አልተገነዘቡም (2 ቆሮንቶስ 2፥11)፡፡

የሰይጣንን ዘዴ የምናውቀው እንዴት ነው? ኢየሱስ እንዲህ በማለት እየነገረን ነው! የሌባው ዓላማ መስረቅ፣ መግደልና ማጥፋት ብቻ ነው፤ የእኔ ዓላማ ግን ሕይወት እንዲኖራቸውና እንዲትረፈረፍላቸው ነው›› (ዮሐንስ 10፥10)፡፡

ቀደም ሲል ዮሐንስ 10 ላይ ኢየሱስ፣ ‹‹ሌባው›› ሰይጣንና ሰራዊቱ እንደ ሆኑ አስረግጧል፡፡ በመቀጠል ደግሞ፣ ‹‹የዚህ ዓለም ገዥ›› በማለት ጠርቶታል (ዮሐንስ 16፥11)፡፡ ጳውሎስም፣ ‹‹የዚህ ዓለም አምላክ›› (2ቆሮንቶስ 4፥4)፣ እና፣ ‹‹በአየር ላይ ላሉት መንፈሳውያን ኃይላት ገዥ›› ብሎታል (ኤፌሶን 2፥2)፡፡ የዚህን ዓለም ሥርዐት የሚመራው እርሱ ነው፡፡ ያለ ጥርጥር የችግርና የመከራችን ምንጭ ሰይጣን ነው፡፡ ጳውሎስ እንዲህ ይላል፣

> ተጋድሎአችን ከሥጋና ከደም ጋር ሳይሆን፣ ከዚህ ከጨለማ ዓለም ገዦች፣ ከሥልጣናትና ከኃይላት እንዲሁም በሰማያዊ ስፍራ ካሉ ክርኩሳን መናፍስት ሰራዊት ጋር ነው፡፡ (ኤፌሶን 6፥12)፡፡

ዮሐንስ 10፥10 ላይ ጌታ የተናገረው፣ በኤፌሶን መልእክቱ ጳውሎስ የተናገረው፣ መሥረቅ፣ መግደልና፣ ማጥፋት ምድብ ውስጥ የሚካተት ማንኛውም ዓይነት መከራ ኤፌሶን 6፥12 የተገለጹ የተለያዩ የጨለማ ኃይላት ተፅዕኖ ውጤት መሆኑን መጠራጠር በማይቻል ሁኔታ ግልጽ ያደርጋሉ፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ የኢየሱስ ዓላማ ግልጽ ሲሆን፣ ይህም የእግዚአብሔር ፈቃድ ነው፡፡ ስለሆነም እግዚአብሔር ለእኛ ያለው ፈቃድ ሕይወት ነው፤ የበዛና የተትረፈረፈ ሕይወት ነው፡፡ ስለዚህ ጫና፣ ችግር ወይም ማንኛውም ዓይነት መከራ ሲገጥመን፣ ከጀርባ ያለው እግዚአብሔር ይሁን ወይም ደግሞ ጠላት መሆኑን ለመለየት ዮሐንስ 10፥10ን እንደ ማጣሪያ ልንጠቀምበት እንችላለን፡፡ ይህ እንዴት እንደሚሠራ ለማሳየት እስቲ አንዳንድ የተለመዱ ምሳሌዎች እንመልከት፡፡

## እፍረት፣ በደለኝነት፣ ፍርድ

እፍረት፣ በደለኝነትና ፍርድ የሚያመጡትን ስሜት በዮሐንስ 10፥10 ማጣሪያ ውስጥ ብናሳልፈው ያለ ጥርጥር በእግዚአብሔር ሳይሆን በሌላው ምድብ ውስጥ ነው የሚወድቁት፡፡

ያም ሆኖ፣ በጣም እርግጠኞች ለመሆን ጠለቅ ብለን እንመርምር፡፡ ዘማሪው፣ ‹‹ነፍሴ ሆይ፣ እግዚአብሔርን ባርኪ (በፍቅርና በጋለ ስሜት አመስግኚው) ውለታውንም ሁሉ አትርሺ - ኃጢአትሽን ሁሉ ይቅር የሚል (አንድ እንኳ ሳይቀር)፣ ደዌሽንም ሁሉ (እያንዳንዳቸው) የሚፈውስ›› በማለት ጽፎአል (መዝሙር 103፥2-3)፡፡

እስቲ ከምታውቋቸው ሁሉ የበለጠ ታማኝ ስለ ሆነ አንድ ሰው አስቡ፡፡ የትዳር ጓደኛችሁ ሊሆን ይችላል፤ ከእናት አባታችሁ አንዱ ሊሆን ይችላል፤ ወይም ከአያቶቻችሁ አንዱ ሊሆን ይችላል፡፡ ያ ሰው ዋሽቶአችሁ ወይም አታልሎአችሁ አያውቅም፡፡ ባለፈው ሕይወታችሁ እንደዚያ ያለ ሰው ሳይገጥማችሁ እንዳልቀረ ተስፋ አደርጋለሁ፡፡ ይህ ሰው እነዚህ አሁን ያነበብናቸውን ተስፋዎች እንደ ሰጣችሁ አስቡ፡፡ ያም ብቻ ሳይሆን፣ የገባውን ቃል የመፈጸም ብቃት አለው ብላችሁም አስቡ፡፡

አሁን ደግሞ ይህን አስቡ፤ እግዚአብሔር እናንተ ከምታውቁት ከማንኛውም ሰው የበለጠ ታማኝ ነው፡፡ ካደረገልን ውለታዎች አንዱንም እንኳ እንዳንረሳ ነግሮናል፡፡ የመጀመሪያ ውለታው ኃጢአታችንን ሁሉ ይቅር ማለቱ ነው፡፡ እጅግ ድንቅ ነው! ምን ዓይነት ደግነት፣ ምን ዓይነት ምሕረት፣ ምን ዐይነት ፍቅር ነው! እንደዚያ ካላደረጋችሁ አሁኑኑ እርግጠኛ ሁኑ፤ በክርስቶስ ኢየሱስ ኃጢአታችሁ ይቅር ተብሏል፡፡ በፈሰሰው ክቡር ደሙ መደምሰስ የማይችል ኃጢአት አላደረጋችሁም፡፡ ባለፈ ሕይወታችሁ አንድ ቦታ ላይ ያሰባችሁት፣ የተናገራችሁት፣ ወይም ያደረጋችሁ እፍረት፣ በደል ወይም ፍርድ የሚያስከትል ነገር ቢኖርና ያንን በተመለከተ የእግዚአብሔርን ይቅርታ ጠይቃችሁ ከሆነ፣ ከእንግዲህ ከእነዚህ አስጨናቂ ስሜቶች በስተ ጀርባ ያለው እግዚአብሔር አይደለም፡፡ ይህን አስመልክቶ የጳውሎስን የድል ቃል ስሙ፣

> እግዚአብሔር የመረጣቸውን የሚከስ ማን ነው? የሚያጸድቅ እግዚአብሔር ነው፤ ታዲያ የሚፈርድ ማን ነው? የሞተው፣ እንዲሁም ከሞት የተነሣው፣ በእግዚአብሔር ቀኝ የተቀመጠው ክርስቶስ ኢየሱስ ስለ እኛ ይማልዳል፡፡ (ሮሜ 8፥33-34)፡፡

በጣም ግልጽ በሆነ ቃል ነው የተቀመጠው፡፡ የሚከስሰን ማነው… እግዚአብሔር ነው? በፍጹም አይደለም!… የሚፈርድብን ማነው? ክርስቶስ ኢየሱስ ነው? በፍጹም አይደለም! ገና ጠላቶች እያለን ነበር ስለ እኛ እንዲሞት እግዚአብሔር ኢየሱስ ክርስቶስን የላከው፡፡ ኢየሱስም ያንን ለማድረግ ተስማማ፤ መንፈስ ቅዱስ እውን አደረገው፡፡ ታዲያ፣ ከእግዚአብሔር ልጆች አንዱ እንጂ፣ ከእንግዲህ ጠላት ካይደላችሁ እግዚአብሔር አብ፣ ወልድና መንፈስ ቅዱስ እንዴት ይፈርዱባችኋል? እንዴትስ ያሳፍሩዋችኋል? ፍርዱን የመሥዋዕቱ በግ ላይ አድርጎት እያለ፣ እግዚአብሔር እናንተ ላይ እንዴት ይፈርዳል? የኢየሱስ መሥዋዕት መሆን በቂ አይደለም ማለት ነው? ዘላለማዊ አይደለም ማለት ነው? የዕብራውያን መልእክት ጸሐፊ እንዲህ በማለት እውነቱን ያረጋግጥልናል፣

በዘላለም መንፈስ አማካይነት ራሱን ነውር አልባ መሥዋዕት አድርጎ ለእግዚአብሔር ያቀረበው የክርስቶስ ደም ሕያው እግዚአብሔርን እንድናመልክ ኅሊናችንን ከምውት ሥራ እንዴት ይበልጥ ያነጻ ይሆን! (ዕብራውያን 9፥14)

የክርስቶስ መሥዋዕት በእግዚአብሔር ፊት ኃጢአታችንን መደምሰስ ብቻ ሳይሆን፣ ኅሊናችንን ከፍርድ፣ ከበደለኝነትና ኃጢአት ከሚያመጣው እፍረት አንጽቶአል፡፡ እንግዲህ ለእርሱ ለመኖርና ለፈቃዱ ለመታዘዝ የምትፈልጉ ከሆነ፣ ያም ሆኖ፣ አሁንም በእነዚህ ሐሳቦችና ስሜቶች እየተሰቃያችሁ ከሆነ መነሻቸው ከጠላት ነው፤ እናንተን ቁልቁል ለመጎተት እየሞከረ ነው፡፡ አጥብቃችሁ ይህን ክፉ ምንጭ መቃወም አለባችሁ፡፡ እንዴት? በበረሓ በተፈተነ ጊዜ ኢየሱስ ይኸንኑ ጠላት በተዋጋበት መንገድ – ማለትም በእግዚአብሔር ቃል! (በኃላ በምንመለከታቸው ምዕራፎች ይህን በዝርዝር አነሣዋለሁ፡፡)

ግን፣ ለእግዚአብሔር ባለ መታዘዝ የምትኖሩ ከሆነ እየፈረደባችሁ ያለው የገዛ ራሳችሁ ልብ ነው ማለት ነው፡፡ ዮሐንስ፣ ‹‹ልባችን በእኛ ላይ በሚፈርድብን ነገር ሁሉ እግዚአብሔር ከልባችን ይልቅ ታላቅ ነውና ሁሉን ነገር ያውቃል፡፡ ወዳጆች ሆይ፣ ልባችን የማይፈርድብን ከሆነ በእግዚአብሔር ፊት ድፍረት አለን›› በማለት ይጽፋል (1 ዮሐንስ 3፥20-21)፡፡ ብዙ ጊዜ እንደዚያ ያለ ትርጉም ቢኖረውም፣ እዚህ ላይ ፍርድ የሚለው ቃል፣ ‹‹ለአንድ በደል የሚሰጥ ፍርድ›› ማለት አይደለም፡፡ ይልቁንም ካታጂኖስኮ (Kataginosko) የሚለው ግሪክ ቃል ትርጉም፣ ‹‹አንድ ሰው ላይ ነገር መያዝ›› ማለትም፣ ‹‹አንድ ሰው ላይ ጥፋት ማግኘት›› ወይም፣ ‹‹ክስ›› ማግኘት›› የሚል ትርጉም ነው ያለው፡፡

ኀሊናችን ከእግዚአብሔር ጋር ካለን ኅብረት እንዳንወጣ ወይም እንዳናፈነግጥ ይጠብቀናል፤ ይከላከልልናል፡፡ እያደግን ወይም ወደ ፊት እየተጓዝን ካልሆነ ልክ እንደ አንድ ልጁን የሚወድ አባት መንፈስ ቅዱስ ይገሥጸናል፤ ‹‹ልጄ ሆይ፣ የጌታን ቅጣት አታቃል፤ በሚገሥጽህም ጊዜ ተስፋ አትቁረጥ›› (ዕብራውያን 12፥5)፡፡ ከእርሱ ጋር ያለንን ኅብረት ለማደስና፣ ይበልጥ እርሱን ወደ መምሰል ደረጃ ሊያደርሰን ይቀጣናል፤ የእርሱ ዓላማ መግደል፣ መስረቅና ማጥፋት አይደለም፡፡

ፍርድና ተግሣጽ ደስ የማይል ስሜት እንዳላቸው – እንደሚያምሙ፣ ምንጊዜም ቢሆን አስታውሱ! ‹‹ቅጣት ሁሉ በወቅቱ የሚያሳዝን እንጂ፣ ደስ የሚያሰኝ አይመስልም›› (ዕብራውያን 12፥11)፡፡ ይሁን እንጂ፣ በሁለቱ መካከል አንድ ትልቅ ልዩነት አለ፡፡ ፍርድ መውጫ መንገዱን አይሰጣችሁም፤ ይልቁንም ለዘለቄታው እንዲያሰቃያችሁ ከእፍረትና በደለኝነት ስሜት ጋር ይተዋችኋል፡፡ እርምት ወይም ተግሣጽ ግን፣ መውጫ መንገዱን ይሰጣችኋል፤ ንስሐ የሚባለው ይኸው ነው፡፡

ለእግዚአብሔር ባለ መታዘዝ እየኖራችሁ እንደ ሆነ ኀሊናችሁ የሚያውቅ ከሆነ፣ እግዚአብሔር ያንንም ያውቃል፤ ምክንያቱም እርሱ ከኀሊናችሁ የበለጠ ታላቅ ነው፡፡ እርሱ አንድ በደል ሲያሳያችሁ ወዲያውኑ በንስሐ ተመለሱ፤ መጸጸታችሁን ንገሩት፡፡ ይቅር ይላችኋል፡፡ ያን ያህል ቀላል ነው፡፡

> ዮሐንስ እንዲህ በማለት ይጽፋል፤ ‹‹ይህን የምጽፍላችሁ ኃጢአት እንዳትሠሩ ነው፤ ነገር ግን ማንም ኃጢአት ቢሠራ፣ በአብ ዘንድ ጠበቃ አለን፤ እርሱም ጻድቁ ኢየሱስ ክርስቶስ ነው›› (1ዮሐንስ 2፥1)፡፡

ዮሐንስ፣ ‹‹ኃጢአት ማድረግ ስትፈልጉ›› አለማለቱን ልብ አድርጉ፤ በፍጹም እንደዚያ አይደለም የሚለው፤ ግቡ ኃጢአት እንዳታደርጉ ነው፡፡ ኃጢአት የማድረግ ስሜት ካላችሁ፤ ኃጢአት ወደ ማድረግ ይመልሳችኋል፣ ከእግዚአብሔር ጋር የተስተካከለ ኅብረት እንዳላችሁ ማሰብ ግን ከኃጢአት ይጠብቃችኋል፡፡ ይህ ግንዛቤ፣ የኃጢአት ኃይል ከሕይወታችሁ እንደ ተሰበረና በውስጥም ሆነ በውጭ ከኃጢአት ነጻ ሆናችሁ የምትኖሩበት ጸጋ እንደ ተሰጣችሁ ማስታወስ እንድትችሉ ይረዳችኋል፡፡ ‹‹ከጸጋ በታች እንጂ፣ ከሕግ በታች ስላልሆናችሁ፤ ኃጢአት አይገዛችሁምና›› (ሮሜ 6፥14)፡፡

ስለሆነም ግቡ ኃጢአት ማድረግ አይደለም፡፡ የእግዚአብሔር ጸጋ እዚህ ግብ ላይ ለመድረስ ያበቃናል፡፡ ግን፣ ምናልባት ኃጢአት ብናደርግ

እንኳ፣ ወዲያውኑ መፍትሔ ልንፈልግለትና፣ ‹‹ኃጢአታችንን ብንናዘዝ ኃጢአታችንን ይቅር ሊለን፣ ከዐመፃ ሁሉ ሊያነጻን እርሱ ታማኝና ጻድቅ ነው›› በሚለው የተስፋ ቃል አምነን ንስሐ ማድረግ እንችላለን (1 ዮሐንስ 1፥9)፡፡ ታማኝ ማለት ዘወትር ይቅር የሚል ማለት ነው፡፡ ጻድቅ ማለት ማንም ሁኑ ምን፣ የተናገረውን የሚያደርግ ማለት ነው፡፡ ከማንኛውም በደል ማለትም፣ ከሁሉም ዐይነት በደል ያነጻናል፤ ያኔ በፊቱ ንጹሕ ሆነን እንገኛለን፤ ምንም በደል አድርጐ እንደማያውቅ ሰው እንሆናለን፡፡ የኢየሱስ ደም ያንን ኃጢአት ምሥራቅ ከምዕራብ እንደሚርቅ ከእኛ ያርቀዋል!

አንድ አማኝ በሕይወት እንዳይነግሥ እንቅፋት ከሚሆኑ ነገሮች አንዱ በኃጢአት ሐሳብ መሞላት ነው፡፡ ንስሐ የገባንበትንና በእግዚአብሔር ፊት የተናዘዝነውን ኃጢአት አስመልክቶ ሁሌም እፍረት፣ በደለኝነት ወይም ፍርድ የሚሰማን ከሆነ በመንፈሳዊ ሕይወታችን ያደክመናል፡፡ ከእግዚአብሔር ሳይሆን ከጠላት በሚመጣ የበደለኝነት ስሜት ወይም እፍረት ምክንያት እምነታቸውን ትተው የሄዱ ብዙ ሰዎች አይቻለሁ፡፡ ከገደብ ያለፈ አንድን ኃጢአት እንዳደረጉ ወይም ይቅር የማይባል ኃጢአት እንደ ፈጸሙ ይሰማቸዋል፡፡ ምንም እንኳ እግዚአብሔር እየፈረደባቸው ባይሆንም፣ ያልታደሰ አእምሮአቸውን በመጠቀም ሰይጣን የበለጠ በደለኝነት እንዲሰማቸው፣ የበለጠ እፍረት እንዲሰማቸውና የበለጠ ተስፋ እንዲቆርጡ ያደርጋቸዋል፡፡ ስለዚህም ወይ ሁሉን ጥለው ይሄዳሉ፤ ወይም ፍሬ ቢስና የበደለኝነት ስሜት በሞላበት እምነት ማዝገም ይቀጥላሉ፡፡ በሕይወት ከመንገሥ ይልቅ፣ ሕይወት ይነግሥባቸዋል፡፡

ስለዚህ አሁኑኑ እርግጠኛ ሁኑ፤ ኃጢአት አድርጋችሁ ከነበረና ያንን ኃጢአት በእውነት ለጌታ ከተናዘዛችሁት፣ በእግዚአብሔር ፊት ምንም በደል አድርጐ እንደማያውቅ ሰው ትሆናላችሁ፡፡ ከአስደናቂ ጸጋው የተነሣ ይህን እውን አድርጐታል፡፡ ያንን በእርግጠኝነት ማመን ትችላላችሁ!

እዚህ ላይ ይህን አጭር ማሳሰቢ ማካተት ጠቃሚ ነው፡፡ በእውነት የእግዚአብሔር ልጆች ከሆናችሁ፣ ከምንም ከማንም ይልቅ እርሱን ደስ ማሰኘት ትፈልጋላችሁ፤ ምክንያቱም የእርሱ ዘር በውስጣችሁ ይኖራል፡፡ ሆኖም፣ ሆን ብሎ ባለ መታዘዝ ሕይወት የሚቀጥል ሰው፣ በእውነት ከእግዚአብሔር አልተወለደም፡፡ ኃጢአታችሁን እንደ ትክክለኛ ነገር ለማቅረብ የምትሞክሩ ከሆነ አደገኛ መሳት ውስጥ ናችሁ፡፡ ግልጹን ለመናገር በእውነት አልዳናችሁም፡፡ መጽሐፍ ቅዱስ ይህን በጣም ግልጽ አድርጐታል፤ ‹‹ኃጢአት የሚያደርግ ግን እርሱን አላየውም ወይም አላውቀውም… እርሱ ከዲያብሎስ ነው›› (1 ዮሐንስ 3፥6-8)፡፡

## ሕመም፣ ደዌና አካላዊ ድካም

ሕመም፣ ደዌ ወይም ማንኛውንም ዐይነት አካላዊ ድካም ላይ እንድንነግሥ የእግዚአብሔር ጸጋ ምን ዐይነት ኃይል ነው የሰጠን? እስቲ ዘማሪው የጻፈውን በድጋሚ እንመልከት፣

ነፍሴ ሆይ፣ እግዚአብሔርን ባርኪ፣ (ከልብሽ በጣም አመስግኚው) ውለታውንም አትርሺ፣ (አንድ እንኳ ሳታስቀሪ)

ኃጢአትሽን ሁሉ ይቅር የሚል (አንድ እንኳ ሳይቀር) ደዌሽንም (እያንዳንዱን) ሁሉ የሚፈውስ፡፡ (መዝሙር 103፥2-3)

እንደ ገና በሕይወታችሁ በጣም ስለምታምኑት ሰው አስቡ፤ ከዚያም እግዚአብሔር ደግሞ ከሁሉም የበለጠ ታማኝ መሆኑንና የገባውን ቃል የማያጥፍ መሆኑን ተቀበሉ፡፡ በመጀመሪያ የተመለከትነው የእግዚአብሔር ውለታ እያንዳንዱ ኃጢአታችንን ይቅር የሚል መሆኑን ነበር፡፡ ያም ብቻ አይደለም፤ በዚያው ቃል ሌላው በረከቱንም እንዳንረሳ ታዝዘናል፤ በፍጹም የማይዋሽ እግዚአብሔር፣ ‹‹ደዌያችሁንም ሁሉ እፈውሳለሁ›› ብሎናል፡፡ አብዛኞቹ ደዌዎቻችሁን ወይም 98% ደዌዎቻችሁን እፈውሳለሁ ሳይሆን 100% ደዌዎቻችሁን እፈውሳለሁ ነው ያለን፡፡ የእርሱ ፈውስ የኢየሱስ የቤዛነት ሥራ አካል ነው፤ ኃጢአታችንን ይቅር ከማለቱ ጋር ዕኩል ነው፡፡ ስለ መንፈሳዊና አካላዊ ነጻነታችን ኢየሱስ የሚቀበለውን መከራ ኢሳይያስ በትንቢት አመልክቶ ነበር፤

በእርግጥ እርሱ ደዌያችንን ወሰደ፤

ሕመማችንንም ተሸከመ፤

እኛ ግን በእግዚአብሔር እንደ ተመታ፤

እንደ ተቀሠፈ፤ እንደ ተሠቃየም ቈጠርነው፡፡

ነገር ግን እርሱ ስለ መተላለፋችን ተወጋ፤

ስለ በደላችንም ደቀቀ፤

በእርሱ ላይ የወደቀው ቅጣት ለእኛ ሰላም አመጣልን፤

በእርሱም ቁስል እኛ ተፈወስን፡፡ (ኢሳይያስ 53፥4-5)፡፡

በዚህ በኢሳይያስ ምንባብ ላይ ደዌ የሚለው የዕብራይስጡ ቃል ቾሊ (Choli) ነው፡፡ የስትሮንግ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅስ ማውጫ፣ ‹‹ሀዘን፣ ደዌ፣

ሕመም›› በሚል ገልጾታል፡፡ ታዋቂው የመጽሐፍ ቅዱስ ምሑርና ደራሲ ሔንሪ ታየር ደግሞ፣ ‹‹መከራ፣ ደዌ፣ ሀዘን፣ በሽታና ሕመም›› በማለት ተርጉሞታል፡፡ ይህ ቃል ብሉይ ኪዳን ውስጥ ሃያ አራት ጊዜ የሚገኝ ሲሆን፣ ከእነዚህ ውስጥ ሃያ አንዱ በተለይ ሕመምና ደዌን በሚመለከት ሁኔታ ነው የተጠቀሰው፡፡ ከላይ ባለው ጥቅስ ቾሊ ፣ ‹‹ሕመም›› ወይም ‹‹ደዌ›› ተብሎ መተርጎሙ ተገቢ እንደ ሆነ አስባለሁ፡፡

አምፕሊፋይድ የተሰኘው የመጽሐፍ ቅዱስ ትርጒም ይህን ድምዳሜ ይደግፋል፣

በእርግጥ እርሱ ሀዘናችንን (ሕመማችንን፣ ድካማችንን ሥቃያችንን ወሰደ)... በመገረፉ (ማለት በቁስሉ) እኛ ተፈወስን፤ ሙሉ ሆንን›› (ኢሳይያስ 53፥4-5)፡፡ ዘ ዎርልድ ኢንግሊሽ ባይብልም፣ ‹‹በእርግጥ እርሱ ሕመማችንን ወሰደ... በእርሱ ቁስል እኛ ተፈወስን›› ይላል፡፡ ዘ ኒው ኢንግሊሽ ትራንስሌሽንም፣ ‹‹ሕመሞቻችንን አነሣ... ምክንያቱም በመገረፉ ቁስል እኛ ተፈውሰናል›› ይላል፡፡

እግዚብሔር ቃሉን አያጥፍም

ዘማሪውም ሆነ ነቢዩ ኢሳይያስ፣ የኃጢአትን ሁሉ ይቅር፤ መባልና የሕመምን ሁሉ መፈወስ በአንድ ዐረፍተ ነገር ማቅረባቸው አጋጣሚ ነው ማለት አይቻልም፡፡ ሁለቱም መስቀል ላይ ኢየሱስ በነጻ ያዘጋጀልን የቤዛነት ሥራው ክፍል ናቸው፡፡

ፈውስ ፍለጋ ወደ ኢየሱስ መጥቶ አንድም ሰው የፈለገውን ሳያገኝ እንዳልተመለሰ ከወንጌሎቹ እንመለከታለን፡፡ ኢየሱስ አንድ ጊዜ እንኳ፣ ‹‹ይህን ሕመም መቀበል አለብህ፤ ምክንያቱም በዚያ ውስጥ አባቴ የሚያስተምርህ ነገር ይኖራል›› አላለም፡፡ ያም ሆኖ ግን፣ ብዙ አማኞች እንዲያውም ብዙ መምህራን እንደዚያ ሲሉ ሰምቻለሁ፡፡ ወገኖቼ ምክንያታዊ እንሁን፤ ኢየሱስ ያኔ ከፈወሰ ዛሬ ለምን ይለወጣል? በዚህ ላይ ደግሞ እርሱ፣ ትናንትና፣ ዛሬና ለዘላለም እርሱ ያው እንደ ሆነ ተነግሮናል (ዕብራውያን 13፥8 ይመ)፡፡ በምድራዊ አገልግሎቱ ዘመን ማንንም እንዳልመለሰ ሁሉ፣ ዛሬም እንዲሁ እንድንመለስ አያደርግም፡፡ ከዚህም ሌላ፣ በሕመማችሁ እግዚአብሔር አንድ ነገር እያስተማራችሁ እንደ ሆነ የምታምኑ ከሆነ፣ ከዚያ ሕመም ለመፈወስ ለምን ወደ ሐኪም ትሄዳላችሁ? እግዚአብሔር ሊያስተምራችሁ የፈለገውን የምትቋቋሙት ለምንድነው? ይህ አስተሳሰብ ምን ያህል ምክንያታዊ አለመሆኑን አያችሁ?

የሐዋርያት ሥራም ቢሆን እግዚአብሔር እንደሚፈውሰው አምኖ ወደ እነርሱ የመጣ ሰው፣ ሳይፈወስ እንደ ተመለሰ አይናገርም፡፡ ሐዋርያቱ አንድም ጊዜ፣ ‹‹አንተን መፈውስ የእግዚአብሔር ፈቃድ እንደ ሆነ አናውቅም፤ ለማንኛውም እንደሚፈውስህ ተስፋ አድርግ›› አላሉም፡፡ ይልቁንም ምንጊዜም ቢሆን፣ ፈውስ የተረጋገጠ ጉዳይ ነበር፤ በኢሳይያስ 53 እና መዝሙር 103 መሠረት ፈውስ፣ እንደ የኃጢአት ይቅርታ ሁሉ የኢየሱስ ቤዛነት ሥራ ክፍል በመሆኑ፣ ፈውስ ፈልጎ የመጣ አንድ ሰው እንኳ አፍሮ አልተመለሰም፡፡ አንዱን አንቀበልም የምትሉ ከሆነ፣ ሌላውንም መቀበል የለባችሁም!

ዛሬም ከዚያ የተለየ አይደለም፡፡ ሕመም፣ ደዌ፣ ወይም ማንኛውም አካላዊ ድካም፣ መስረቅ፣ መግደልና ማጥፋት ምድብ ውስጥ ነው የሚካተቱት፡፡ በኢየሱስ መስቀል ላይ መሥዋዕት መሆን ከእነርሱ ነጻ መሆናችንን በመገንዘብ በልበ ሙሉነት የምንቋቋማቸው ችግሮች አሉ፡፡ እነዚህ ነገሮች ለሕይወታችን የእግዚአብሔር ፈቃድ አይደሉም፡፡ የኢየሱስ ቤዛነት ያስገኘው ውጤት ዛሬም ጽኑ ነው፤ ዛሬም እንደ ተጠበቀ ነው፤ ‹‹የሰላም አምላክ ራሱ ሁለንተናችሁን ይቀድስ፤ መንፈሳችሁ ነፍሳችሁና ሥጋችሁ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በሚመጣበት ጊዜ ያለ ነቀፋ ይጠበቁ›› በማለት ጳውሎስ የጻፈው በዚህ ምክንያት ነበር (1ተሰሎንቄ 5፥23)፡፡ መንፈሳችሁና ነፍሳችሁ ጤናማ እንዲሆኑ እንደሚፈልግ ሁሉ፣ ሥጋችሁም ጤነኛ እንዲሆንና እርሱ በፈጠረው ሁኔታ እንዲሠራ እንደሚፈልግ ለማመልከት ከመንፈስና ከነፍሳችሁ ጋር አብሮ ስለ ሥጋችሁም ተናግሮአል፡፡

ምናልባትም፣ ‹‹እግዚአብሔር እንደሚፈውሰው ቢያምንም፣ ሳይፈወስ የሞተ ሰው አውቃለሁ›› የሚል ይኖራል፡፡ እስቲ ይህን ልጠይቃችሁ፣ በእግዚአብሔር ያላችሁ እምነት የተመሠረተው በሌለው ሰው ልምምድ ላይ ነው ወይስ በዘላለማዊ ቃሉ እግዚአብሔር በተናገረው ላይ? ይህን በተመለከተ በልባችሁና በአእምሮአችሁ ቁርጥ ያለ ውሳኔ ማድረግ ይኖርባችኃል፡ ጳውሎስ፣ ‹‹አንዳንዶች እምነት ባይኖራቸውስ? የእነርሱ አለማመን የእግዚአብሔርን ታማኝነት ዋጋ ያሳጣዋልን? ፈጽሞ አይሆንም!... እግዚአብሔር እውነተኛ ይሁን›› በማለት ጽፎአል (ሮሜ 3፥3-4)፡፡

በግልጽ እንነጋገር ከተባለ፣ ያ ሳይፈወስ የሞተው ሰው በእውነት በልቡ ያምን የነበረውን በእርግጠኝነት ማወቅ አትችሉም፡፡ በእግዚአብሔር ፈዋሽነት እንደሚምን በተደጋጋሚ ቢናገርም፣ ‹‹ላልፈወስ እችላለሁ›› የሚል ፍርሃቱን ለመደበቅ እንደ ሽፋን የሚጠቀምበት ሊሆን ይችላል፡፡ እውነተኛ

እምነት ልባችን ውስጥ ጥርጥር እንዲኖር አያደርግም፡፡ አንድ ሰው ትክክል መሆኑን በማወቅ አንድ ነገር ይናገር ይሆናል፤ ልቡ ውስጥ ያለው እምነት ግን ከዚያ የተለየ ሊሆን ይችላል፡፡

ታዲያ፣ ፈራጅ ሳንሆን፣ መጽሐፍ ቅዱስ ከሚናገረው የሚቃረን የሌሎችን ልምምድ እንዴት ማስተናገድ አለብን? ለምሳሌ ያህል አንድ የቤተ ሰብ አባል ወይም አንድ የቅርብ ወዳጅ ታምሞ ያለ ዕድሜው ቢሞት? እንዲህ ያለ ሁኔታ ሲገጥመኝ እኔ መያዝ የጀመርኩት ውጤታማ አመለካከት የሚከተለው ነው - መጽሐፍ ቅዱስ ሩጫ ሜዳ ላይ መሆናችንን ያስተምራል፡፡ ሩጫ ሜዳ ላይ ለእያንዳንዱ ሰው የሚሮጥበት መስመር አለው፡፡ የአንድ ሰው ልምምድ ከመጽሐፍ ቅዱስ መሠረታዊ እውነቶች ጋር የማይጣጣም ከሆነ፤ እዚያው እርሱ መሮጫ መስመር ላይ ተውት እንጂ ወደ ራሳችሁ አታምጡት፡፡ ጉዳዩ በሰውየውና መሐሪና ጻድቅ ፈራጅ በሆነው እግዚአብሔር መካከል መሆን ያለበት ነው፡፡ በዚህ መንገድ ካሰባችሁ የእናንተ እምነት አይደክምም፡፡ ይሁን እንጂ፣ የአንድ ሰው ምስክርነት ከዘላለማዊው የእግዚአብሔር ቃል ጋር የሚጣጣም ከሆነ፣ ለጀመራችሁት ሩጫ ጉልበት እንዲሆናችሁ ወደ ራሳችሁ መሮጫ መስመር አምጡት፡፡

የተስፋ ቃሉን ፍጻሜ ከመቀበላችሁ በፊት፣ የእግዚአብሔር ቃል የሚናገረውን በጥልቅ ልቦናችሁ ውስጥ ማኖር አለባችሁ፡፡ እንደዚያ ካደረጋችሁ በእምነታችሁ ጽኑ ትሆናላችሁ – ልክ በርጤሜዎስ እንደሚሉት ሰው፡፡

ኢየሱስ ከደቀ መዛሙርቱ ጋር ከኢያሪኮ እየወጣ ነበር፤ ብዙ ሰዎችም ተከትለውት ነበር፡፡ በርጤሜዎስ የሚሉት አንድ ዐይነ ስውር መንገድ ዳር ተቀምጦ ነበር፤ ኢየሱስ በዚያ በኩል እያለፈ መሆኑን ሲሰማ ወደ እርሱ አጥብቆ ጮኸ፡፡ በዙሪያው የነበሩ ሰዎች እየጮኸ መምህሩን እንዳያስቸግር ተቆጥተው ነገሩት፡፡ እርሱ ግን እንዲያውም የበለጠ ይጮኽ ጀመር! የዚህ ሰውየ እምነት ጭንቅላቱ ውስጥ ሳይሆን ልቡ ውስጥ ነበር፡፡ እግዚአብሔር ሊፈውሰው እንደሚፈልግ በርጤሜዎስ ከልቡ ባያምን ኖሮ፣ በተለይ በአካባቢው የነበሩ ሰዎች ከገሠጹት በኋላ በእምነቱ አይጸናም ነበር፡፡ ምናልባትም ተስፋ ሊቆርጥና፣ ኢየሱስ ወደዚህ መጥቶ የማይፈውሰኝ ከሆነ፣ ምናልባት እግዚአብሔር ዐይነ ስውር እንደ ሆንኩ እንድኖር ፈልጎ ይሆናል የሚል የተሳሳተ አስተሳሰብ መያዝ ይችል ነበር፡፡ በርጤሜዎስ ግን ይህን ውሸት አልተቀበለም፤ በእምነቱ ጸና፤ ድምፁንም አሰማ፡፡ ቀጥሎ የሆነውን ስሙ፣

ኢየሱስም ቆም ብሎ... (ማርቆስ 10፥49)፡፡

እንዴት ይገርማል! ኢየሱስ የመጣበትን ተልዕኮ ለመፈጸም ወደ ኢየሩሳሌም ለመሄድ ፊቱን ወደዚያ አቅንቶ ነበር፤ ትኩረቱ ሥራው ላይ ነበር፡፡ ብዙ ሰዎች ከብበውት ነበር፤ ብዙዎቹም የየግላቸው ችግር ሳይኖራቸው አይቀርም፤ ግን የእነርሱ ችግር አላስቆመውም፤ ለጊዜውም ቢሆን ከመጣበት ተልዕኮ አልገታውም፡፡ ይሁን እንጂ፣ አንድ ተራ ዐይነ ስውር ወደ ኢየሱስ ጮኸ፤ ማንም ዝም ሊያሰኘውም አልቻለም፡፡ ምንም ዓይነት ችግር፣ ምንም ዐይነት ቁጣና ተቃውሞ ዝም ሊያሰኘው አልቻለም፡፡ ኢየሱስን ቆም እንዲል ያደረገው የእርሱ ጩኸት እንጂ፣ የሌሎቹ ዝምታ አልነበረም፡፡ ኢየሱስ ‹‹ጥሩት›› አላቸው፡፡ ስለዚህም ደቀ መዛሙርቱ ዐይነ ስውሩን ጠሩት፡፡ ‹‹አይዞህ ተነሥ፤ ይጠራሃል!›› አሉት፡፡ (ማርቆስ 10፥49)፡፡

በበርጤሜዎስ ዙሪያ የነበሩ ሰዎች የሚያበረታቱ አልነበሩም፡፡ እንዲያውም፣ ከእርሱ ፍላጎት ተቃራኒ ነበሩ፡፡ ሆኖም፣ እንዲያወላውል አላደረጉትም፡፡ በርጤሜዎስ ከእምነቱ አላፈገፈገም፡፡ የለማኝ ቡትቶውን ጥሎ ብድግ ብሎ ቆመ፤ በኋላም ደቀ መዛሙርቱ ወደ ኢየሱስ አመጡት፡፡

ከዚያም ጌታ፣ ‹‹ምን እንዳደርግልህ ትፈልጋለህ? በማለት ጠየቀው፡፡

እንዴ? ምን ዐይነት ጥያቄ ነው? በሰዎች መሪነት ወደ እርሱ የመጣውን ዐይነ ስውር እንዲህ ብሎ መጠየቅ ምን ማለት ነው? የሚፈልገው ግልጽ ነበር፤ ታዲያ፣ ኢየሱስ ለምን እንደዚያ ጠየቀው? የዚያ ለማኝ ችግር ሳይገባው ቀርቶ ነው? ኢየሱስ ንቀቱን እያሳየው ይሆን? በፍጹም እንደዚያ አይደለም!

ጌታ የበርጤሜዎስን፣ እምነት ማስረጃ ማየት ፈለገ፡፡

ምናልባት በርጤሜዎስ፣ ‹‹መቼም ዐይኔን አብራልኝ ማለት በጣም ይከብዳል፤ ግን፣ ካለፉ ጥቂት ቀኖች ወዲህ የጀመረኝን ራስ ምታት ልትፈውሰን ፈቃደኛ ነህ?›› ቢል ኖሮስ፤ የሚያገኘው በትክክል ያንኑ ይሆን ነበር፡፡ ይህ እውነት መሆኑን፣ ዐይነ ስውሩን ከፈወሰው በኋላ ኢየሱስ ከተናገረው መመልከት ይቻላል፤ ‹‹ሂድ፣ እምነትህ አድኖሃል›› አለው፡፡

ማርቆስ የተፈወሰው ሰውየ ላይ እንጂ፣ በቦታው የነበሩ ያልተፈወሱ ብዙዎች ላይ አላተኮረም፡፡ ያልተፈወሱ ሰዎች ታሪክ ከጽኑ እምነታችሁ እንዲያናውጣችሁ አትፍቀዱ፡፡ ይህን በተመለከተ በድጋሚ በጥንቃቄ ስሙኝ፤ ከእግዚአብሔር ያልተቀበሉ ሰዎችን አትንቀፉ አትፍረዱባቸው፤ ይሁን እንጂ፣ ታሪካቸው ወደ ልባችሁ ገብቶ እንደ ማስረጃ እንዲሆንላችሁ አትፍቀዱ፡፡ ጳውሎስ፣ ‹‹አንዳንዶች እምነት ባይኖራቸውስ? የእነርሱ አለማመን የእግዚአብሔርን ታማኝነት ዋጋ ያሳጣዋልን? ፈጽሞ አይሆንም!››

ይላል (ሮሜ 3፥3-4)፡ ወደ ልባችን እንዲገቡ መፍቀድ ያለብን፣ ከእግዚአብሔር ቃል ጋር የሚስማሙ ምስክርነቶችን ብቻ ነው፡፡

## ዕጦትና ድኽነት

### ጸጋ በዕጦትና ድኽነትስ ላይ ሥልጣን ይሰጠን ይሆን?

በአንዳንድ ምክንያት ብዙ ሰዎች፣ መንፈሳዊነት በቂ ነገር ባለ ማግኘት እንደሚገለጥ ያምናሉ፡፡ አንዳንዴም ጽንፍ በለቀቀ መልኩ አንዳንዶች፣ እግዚአብሔርን ለማገልገል በድኽነት ለመኖር ስእለት ያደርጋሉ፡፡ ይህ ዓይነቱ የአእምሮ ዝንባሌ፣ ‹‹አምላኬም እንደ ባለጠግነቱ መጠን የሚያስፈልጋችሁን ሁሉ በክርስቶስ ኢየሱስ በክብር ይሞላባችኋል›› በማለት በሚናገረው ፊልጵስዩስ 4፥14 ፊት መቆም አይችልም፡፡

ያንን ጥቅስ በዐውዱ መሠረት ብታነቡት ጳውሎስ ለእነዚያ አማኞች እየተናገረ የነበረው በተለይ ገንዘብን በተመለከተ እንደ ነበር ትረዳላችሁ፡፡ በአገራችን ወይም በዓለም ዙሪያ እንዳለው የዋጋ ግሽበት ወይም የኑሮ ውድነት መጠን ሳይሆን፣ እንደ እግዚአብሔር ባለ ጠግነት መጠን የሚያስፈልገንን ሁሉ እግዚአብሔር በክብር ይሰጠናል፡፡ እጅግ ይደንቃል! እርሱ እጅግ ባለጠጋ ነው - በጣም እርግጠኛ ለመሆን፣ ባለጠግነቱ ወሰን የለሽ ነው! እንግዲህ ይህን የተስፋ ቃል መሠረት በማድረግ፣ የሚያስፈልገንን መልካም ነገር ማጣታችን የእግዚአብሔር ፈቃድ አለመሆኑን በልበ ሙሉነት መናገር እንችላለን፡፡ ዘማሪው፣ ‹‹አንበሶች ሊያጡ ሊራቡም ይችላሉ፤ እግዚአብሔርን የሚሹ ግን መልካም ነገር አይጐድልባቸውም›› ይላል (መዝሙር 34፥10)፡፡ ዕጦትና ድኽነት ሙሉ ሕይወት አይደሉም፤ ስለሆነም ለሕይወታችሁ የእግዚአብሔር ፈቃድ ሊሆኑ አይችሉም፡፡

መልካም ስም ከብዙ ሀብት ወይም ሌላው ቀርቶ ክቡር ከሆነው የእግዚአብሔር ቅባት እንኳ እንደሚበልጥ መጽሐፍ ቅዱስ ይናገራል (ምሳሌ 22፥1፤ መክብብ 7፥1 ይመ)፡፡ በጊዜው የሚፈለግብንን ክፍያ ካላጠናቀቅን፣ ስማችን በመልካም አይነሣም፡፡ የተከመረባችሁን የቤት ኪራይ መክፈል አቅቷችሁ እያለ፣ ቤት ላከራያችሁ ሰው በነጻነት ስለ ኢየሱስ መናገር ትችላላችሁ? ሕይወታችሁ የሚያሳየው ቃላችሁን መጠበቅና መክፈል የነበረባችሁን በጊዜው መክፈል አለመቻላችሁን ሲሆን፣ ለምን ብሎ የምትነግሩትን ይሰማችኋል? ይሁን እንጂ፣ ቤት ያከራያችሁ ሰው እግዚአብሔር ሲረዳችሁና የኃላ ኃላም ቤት መግዛት አስችሎአችሁ ተሰናብታችሁት ስትሄዱ ያ ለማያምኑ ሰዎች ምን ያህል ምስክር ሊሆን እንደሚችል አይታያችሁም? የእግዚአብሔር ቃል፣ ‹‹አንተ ታበድራለህ

እንጂ፣ ከአንዳቸውም አትበደርም›› ይላል (ዘዳግም 28፥12)፡፡ ከማንኛውም ዕዳ ነጻ መሆን - ያለ ምንም ብድር መሆን - ይልቁንም፣ ያለንን ከሌሎች ጋር መካፈልና ለወንጌል ሥራ በመስጠት፣ ‹‹ለአሕዛብ ማበደር›› መቻል እንዴት ያለ ምስክርነት ይሆን ነበር!

ከእነዚህ የቅዱሳት መጻሕፍት ጥቅሶች አንጻር የእግዚአብሔር ፈቃድ የሚያስፈልገንን ማሟላት ብቻ ሳይሆን፣ ከዚያም የሚያልፍ ይመስላል፡፡ እንድንበለጽግ፣ እንድንከናወን የሚፈልግ ይመስላል፡፡ የእርሱ ፈቃድ ምን እንደ ሆነ ከሐዋርያው ዮሐንስ ጸሎት ስሙ፣ ‹‹ወዳጅ ሆይ፣ ነፍስህ በመልካም ሁኔታ ላይ እንዳለች ሁሉ፣ መልካም ጤንነት እንዲኖርህና በነገር ሁሉ እንዲሳካልህ እጸልያለሁ›› (3 ዮሐንስ 2)፡፡

*በነገር ሁሉ* የሚለውን ቃል አስተዋላችሁ? እናንተ ልጆቹ በነገር ሁሉ እንዲሳካላችሁ፣ እንድትበለጽጉና በመልካም ጤንነት እንድትሆኑ እግዚአብሔር ይፈልጋል፡፡ እንደ ገና ልበለው – በነገር ሁሉ፡፡ ከሌላው ነገር ሁሉ የበለጠ! የሐዋርያው ጸሎት የእግዚአብሔር ፈቃድ ባይሆን ኖሮ፣ መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ አይገባም ነበር፡፡ እግዚአብሔር አያጋንንም ወይም ከሚገባው በላይ ደጋግሞ አይናገርም፡፡ እንደዚያ ቢያደርግ መዋሸት ይሆን ነበር፤ እግዚአብሔር ደግሞ መዋሸት አይችልም፡፡ ስለዚህ ወዳጆቼ፣ በዚህ በጣም እርግጠኛ መሆን ትችላላችሁ፤ እግዚአብሔር በነገር ሁሉ እንዲከናወንላችሁና እንድትበለጽጉ፣ በመልካም ጤንነትም እንድትሆኑ ይፈልጋል፡፡ በጣም ይገርማል!

ለመሆኑ፣ መበልጸግ ምን ማለት ነው? ለእናንተ ብቻ ሳይሆን በእናንተ ዙሪያ ያሉ ሰዎችን ፍላጎት ማሟላት ከሚችል ያለፈ ሲኖር ማለት ነው፡፡ በሌላ አነጋገር፣ በስሙ እንድትነኩዋቸው እግዚአብሔር የሚፈልጋቸውን ሰዎች ለመድረስ ገንዘብ ይህን ያህል ወሳኝ ነገር መሆን የለበትም፡፡ የእግዚአብሔር ቃል፣ ‹‹ሀብት እንድታፈራ ችሎታ የሰጠህ፣ ለአባቶችህም በመሐላ የገባውን ኪዳን ያጸናልህ እርሱ ስለ ሆነ አምላክህን እግዚአብሔርን አስበው›› የሚለው በዚህ ምክንያት ይሆን? (ዘዳግም 8፥18)፡፡

እግዚአብሔር የእኛን ሀብታም መሆን አይቃወምም፡፡ እርሱ የሚቃወመው ሀብታችን እኛን ሲገዛን ነው፡፡ የገንዘብ ፍቅር እንጂ፣ ገንዘብ ራሱ የክፋት ሁሉ ምንጭ አይደለም፡፡ በማንኛውም የሕይወት ገጽታችሁ፣ ሌላው ቀርቶ በገንዘብ ዐቅማችሁ እንኳ እንዲከናወንላችሁ የእግዚአብሔር ፈቃድ ነው፡፡

ብዙ ወጣት ወይም በሳል ያልሆኑ አማኞች የተነጋገርንባቸውን ዋና ዋና የሕይወት ገጽታዎች በተመለከተ ትግል ይገጥማሉ፡፡ ይሁን እንጂ፣ እግዚአብሔር የእፍረት፣ የበደለኝነት፣ የፍርድ፣ የሕመም፣ የደዌ፣ የአካላዊ ድካም፣ የዕጦት ወይም የድኽነት ምንጭ ባለ መሆኑ እውነት ላይ አንዴ ከተመሠረትን፣ ከጠላት የሚመጡ ሌሎች ጥቃቶችንም መለየት ይህን ያህል ከባድ አይሆንብንም፡፡ አሁን ወደ ሕይወት እውነተኛ ውጊያ - ለእግዚአብሔር መንግሥት ቦታ ወደ መያዝ ውጊያ ገብተናል፡፡

ወደ ውጊያው ስትገቡ በልባችሁ ይህን ያዙ፤ የሚገጥማችሁ ተቃውሞ በመስረቅ፣ በሞትና በጥፋት ምድብ ውስጥ የሚካተት ከሆነ፣ ከእግዚአብሔር ጋር ምንም ግንኙነት የለውም፡፡ እናንተን ተስፋ ማስቆረጥ፣ ማሸነፍና መዋጥ ከሚፈልጉ የሰይጣን ኃይሎች የመጣ ነው፡፡ በሰማይ እንደ ሆነ ሁሉ፣ የእግዚአብሔር መንግሥት በዚህም ምድር እንዲገለጥ እኔና እናንተ ጸንተን ልንዋጋቸው ይገባል፡፡

# 8

# ታጥቃችሁ ተነሡ

*እንግዲህ ክርስቶስ በሥጋው መከራን ስለ ተቀበለ እናንተም ለዚሁ ዓላማ ታጥቃችሁ ተነሡ፤ ምክንያቱም በሥጋው መከራን የሚቀበል ሰው ኃጢአትን ትቶአል።*

*1ጴጥሮስ 4፥1*

እስቲ ያለ ጥይት፣ ጠመንጃ፣ መትረየስ፣ ቦንቦች፣ ታንኮች፣ አውሮፕላኖች ወይም ሌላው ቀርቶ ያለ ሳንጃ ወታደሮቹን ወደ ጦርነት የሚልክ አንድ መንግሥት አስቡ፡፡ የእነዚያ ወታደሮች ዕጣ ፈንታ ምን ይሆናል? ያሸንፉሉ? ይፋለማሉ? ሌላው ቀርቶ በሕይወትስ ይተርፋሉ? በእኔ ግምት ብዙዎቹ ቶሎ ይገደላሉ፤ የተቀሩትም የጦር እስረኞች ይሆናሉ፡፡

ይህ ግምት ነው፤ እኔ እስከማውቀው ድረስ እንዲህ ያለ አስቂኝ ነገር ሆኖ አያውቅም፡፡ ሆኖም፣ የቱንም ያህል አስቂኝ ቢሆንም፣ ‹‹መከራ ለመቀበል ታጥቆ ካልተነሣ›› አማኝ ሁኔታ ይህን ያህል የተለየ አይደለም፡፡ በጣም የሚሳዝነው፣ ብዙዎቻችን የታጠቅን አይደለንም፡፡ ያልጠበቅነው ችግር (ትሊፕሲስ) ሲመጣ፣ ሳንታጠቅ ያገኘናል፤ ድንጋጤ፣ ፍርሃትና መገረም ውስጥ እንገባለን፡፡ ውጤቱ ደግሞ ከማጥቃት ይልቅ ማፈግፈግ ይሆናል፡፡

በመንፈስ ቅዱስ መሪነት በተጻፈው በመጀመሪያው መልእክቱ ጴጥሮስ፣ ክርስቶስ መከራ እንደ ተቀበለ፣ እኛም መከራ ለመቀበል ታጥቀን እንድንነሣ ይመክረናል፡፡ ክርስቶስ መከራ የተቀበለው እንዴት ነበር? በኃጢአት ምክንያት ነበር? በፍጹም፤ ያም ሆኖ ግን፣ ኃጢአትን መቃወም ነበረበት፡፡ ሕመም ወይም ደዌ አጥቅቶት ነበር? አይደለም፤ ግን ምናልባት፣ ያንንም መዋጋት ሳይኖርበት አይቀረም፡፡ ለሚያስፈልገው የሚከፍለው ወይም ተልዕኮውን ለመፈጸም በቂ ገንዘብ አጥቶ ይሆን? አይደለም፤ ያም ሆኖ ግን፣ ለሚያስፈልገው ሁሉ በእግዚአብሔር መተማመን ነበረበት፡፡ ኢየሱስ በሁሉም አቅጣጫ ተፈትኖ ነበር፤ ያም ሆኖ ግን፣ ጠላት በሚያቀርበው መሰናክል አልተሸነፈም፡፡ እርሱ እንደ ተመላለሰ እኛም

እንድንመላለስ ተነግሮናል፤ በማንኛውም የዲያብሎስ ተንኰል መታለል የለብንም፡፡

ወደ ውስጥ ጠለቅ ብለን የጴጥሮስን መልእክት ስናነብ ኢየሱስ ላይ የደረሰበት ትክክለኛ መከራ ከሰዎች፣ በተለይም በዘመኑ ከነበሩ ብልሹ የፖለቲካና የሃይማኖት መሪዎች የደረሰበት በደል እንደ ነበር እንረዳለን፡፡ አንድ ሰው ወደ አገዛዝ መግባት ከፈለገ፣ ይህ መቀበል ከሚገባው መከራዎች አንዱ እንደ ሆነ በግሌ አምናለሁ፡፡

በእርግጥም፣ የፍትሕ መጓደል የሐዋርያው ጳውሎስም ከባዱ ትግል ነበር፡፡ በድንጋይ ተደብድቧል፤ አምስት ጊዜ ተገርፏል፤ ሦስት ጊዜ በበትር ተቀጥቅጧል፤ ከአገሩ ሰዎች፣ ከባዕድ አገር ሰዎችና ከሐሰተኛ አማኞች የማያቋርጥ ጥቃት ይደርስበት ነበር፡፡ ጳውሎስ ተመቷል፤ ሐሰት ተወርቶበታል፤ ተቀልዶበታል፤ ተገፍቶአል፤ ተሰድቦአል፤ በሐሰት ተከስሶአል፡፡ ለእኛም ቢሆን፣ ‹‹በእርግጥም በክርስቶስ ኢየሱስ በእውነተኛ መንፈሳዊ ሕይወት መኖር የሚወዱ ሁሉ ይሰደዳሉ›› የሚል ማስጠንቀቂያ ሰጥቶናል (2 ጢሞቴዎስ 3፥12)፡፡

ዓለም እንደሚኖረው የምትኖሩ ከሆነ፣ ስደት አይደርስባችሁም፤ ምክንያቱም የጦር እስረኛ ሆናችሁ ነው ያላችሁት፡፡ ጠላት ለጦር እስረኞች ባዘጋጀው ካምፕ ውስጥ ናችሁ፡፡ ለእግዚአብሔር መንግሥት መሬት በመያዝ ረገድ ውጤታማ አይደላችሁም፤ ለእግዚአብሔር ክብር አታስገኙም፡፡ ነጻ የሆኑት፣ ምርኮኛ ያልሆኑት የጠላትን ግዛት ለመያዝ ውጊያ ላይ ያሉት ናቸው፡፡

> ዓለም እንደሚኖረው የምትኖሩ ከሆነ… የጦር እስረኞች ሆናችሁ ነው ያላችሁት

ያለነው ሙሉ በሙሉ የእግዚአብሔርን ፈቃድ በሚጻረር፣ እንዲያውም ጠላት በሆነ ዓለም ውስጥ ነው፡፡ የዚህ ሥርዐት አካሄድ ከእግዚአብሔር መንፈስ አካሄድ ጋር በቀጥታ ይጋጫል፡፡ ስለሆነም በእውነት ለጌታ የምትኖሩ ከሆነ – መከራ፣ ችግርና ስደት ይደርስባችኋል፡፡ ይህ ደግሞ የሚጠበቅ እንጂ እንግዳ ነገር አይደለም፡፡

የተከበራችሁ ወገኖቼ፣ ባለፈው ምዕራፍ በገለጽነው ዝርዝር እንደ ተካተተውም ይሁን፣ ወይም ተቃራኒ ከሆኑ የተፈጥሮ ኃይላት፣ ወይም ከሰዎች፣ ከድርጅቶች ወይም ከዚህ ዓለም ገዢዎች ከሚሰነዘር ጥላቻ፣ ለክርስቶስ በምትኖሩት ሕይወት ተቃውሞ ይደርስባችኋል፡፡ ስለዚህ ጴጥሮስ ተዘጋጁ ይላል፡፡ እርሱ እንደሚለው፣ ‹‹ታጥቀን መነሣት›› አለብን፡፡

## የታጠቀና ያልታጠቀ

አንደኛው የታጠቀ፣ ሌላው ግን ያልታጠቀ ወገን ላይ፣ ሳይታሰብ ሊደርስ ስለሚችል ጥቃት ሁለት ምሳሌዎች ብንመለከት ሊረዳን ይችላል፡፡ ከስድስት እስከ ዐሥራ ሁለት ባሉ ወሮች ውስጥ አንድ የንግድ አውሮፕላን ፓይለት ተደጋግሞ ወደሚሰጥ ሥልጠና ይላካል፡፡ የሥልጠናው ትልቁ ክፍል በከፍተኛ ቴክኒዎሎጂ የሚታገዝ ምስለ በረራ (ሲሙሌተር)፣ ውስብስብ የኮምፒዩተር አሠራር ያላቸው ማሠልጠኛ መሣሪያዎች፣ አውሮፕላኑን ለመቆጣጠር የሚያስችሉ መሣሪያዎች የተገጠሙለት ጋቢና፣ ከአውሮፕላኑ ውጪ ያለውን አስመስሎ የሚያሳይ የረቀቁ መሣሪያዎች አሉት፡፡ በፓይለቱ ቁጥጥር ወይም በውጭ ባለው ከባቢ መሠረት የሚንቀሳቀስ ማኰብኰቢያ አለው፡፡ በአጭር አገላለጽ አንዴ ውስጡ ከገባችሁ እውነተኛ አውሮፕላን ውስጥ ትሆኑ ወይም ደግሞ ምስለ በረራ (ሲሙሌተር) ውስጥ ለይታችሁ መናገር አትችሉም፡፡

ምስለ በረራው በእውነተኛ በረራ ጊዜ ሊኖር የሚችለው ማንኛውም አሠራር ወይም የአሠራር ጉድለት ማስመሰል ስለሚችል ምስለ በረራውን የሚያንቀሳቅሰው አስተማሪ ተለማማጅ ፓይለቶቹ ላይ ማንኛውንም ዐይነት ችግር (ትሊፕሲስ) ያደርስባቸዋል፡፡ ፓይለቶቹ ከባድ መናወጥ፣ ከባድ ነፋስ፣ ከመጠን ያለፈ የአየር ሁኔታ፣ የሞተር መጥፋት፣ የማሳረፊያው ፍሬን አለ መሥራትን ወዘተ የመሳሰሉ ብዙ ችግሮች እንዲደርሱባቸው ያደርጋል፡፡ ይህ ሁሉ የሚሆነው፣ በልምምድ ጊዜ ያልተጠበቁ ችግሮችን በተደጋጋሚና በአሸናፊነት የሚወጡ ፓይለቶች በእውነተኛው ዓለም የሚገጥሟቸው ችግሮችንም መፍታት ይችላሉ ተብሎ ስለሚታሰብ ነው፡፡ ከእንዲህ ዐይነቱ ተደጋጋሚ ልምምድ የተነሣ ፓይለቶቹ ድንገተኛ ነገሮችን ለይተው ማወቅና መቆጣጠርን በመማራቸው፣ ሊደርሱ ይችሉ የነበሩ ብዙ አደጋዎች ሳይደርሱ ቀርተዋል፡፡

ከ9/11/2001 ቀደም ሲል የተፈጸመ የአውሮፕላን አደጋ አስታውሳለሁ፡፡ አውሮፕላኑ እንደ ዛሬዎቹ ጋቢናውን ከተሳፋሪዎቹ የሚለዩ ደረጃቸውን የጠበቁ በሮች ያልነበሩት ትንሽ የሕዝብ ማመላለሻ አውሮፕላን ነበር፡፡ አደጋው ከተፈጸመ ጥቂት ጊዜ በኋላ ጥቁር ሳጥኑ ተገኝቶ መጠናት ጀመረ፡፡ ጋቢናው በር ስላልነበረው ባለ ሙያዎቹ የፓይለቶቹንና የተሳፋሪዎቹን ንግግር መስማት ችለው ነበር፡፡ አውሮፕላኑ ከሰማይ ቁልቁል በመውረድ ላይ እያለ ተሳፋሪዎቹ የሚይዙ የሚጨብጡትን አጥተው በሲቃ እየጮኹ ነበር፡፡ ይሁን እንጂ፣ ፓይለቶቹ ግን ረጋ ብለው እየተቆጣጠሩና፣ የችግሩን ምክንያት በመረዳት መፍትሔ ለማስገኘት እየሠሩ ነበር፡፡ የሰጡት

ምላሽ ከፍርሃት የተነሣ ሳይሆን በምስለ በረራው ባገኙት ሥልጠና መሠረት ነበር፡፡ ዋናው ፓይለት መመሪያዎች እየሰጠ ነበር፤ ረዳት ፓይለቶቹ የሚሰጣቸውን እያንዳንዱን መመሪያ ተግባር ላይ እያዋሉ ነበር፡፡ ይህ ሁኔታ እስከ መጨረሻው ድረስ ቀጥሎ ነበር፡፡ ፓይለቶቹ ለእንዲህ ዐይነት ድንገተኛ አደጋ ዝግጁ (የታጠቁ) ሲሆኑ፣ ተሳፋሪዎቹ ግን በፍጹም አልተዘጋጁም (አልታጠቁም) ነበር፤ ስለሆነም ምላሻቸውም እንዲሁ በፍጹም የተለየ ሆነ፡፡ ፓይለቶቹ በዓላማ ሲንቀሳቀሱ፣ ተሳፋሪዎቹ ግን ፍርሃት ባሳደረባቸው ስሜት ነበር የተንቀሳቀሱት፡፡

አንድ ጊዜ በግል አውሮፕላን ተሳፍሬ እየሄድኩ እያለ 39,000 ጫማ ከፍታ ላይ የበሩ እሽግ በድንገት ተበረገደ፡፡ ከጋቢናው የወጣው ፈጣን ዕምቅ አየር በጣም ከባድ ስለ ነበር ድምፁ እጅግ አስደንጋጭ ነበር፡፡ በቅጽበት ትንሿ ክፍል ውስጥ የነበረው ለሰው አተነፋፈስ ምቹ የሆነው ዕምቅ አየር እያሽቆለቆለ ሄደ፡፡ የምይዘው የምጨብጠው ስለ ጠፋኝ ምን ማድረግ እንደ ነበረብኝ አላወቅሁም ነበር፡፡ እውነቱን ለመናገር፣ ሙከራዬ ሁሉ፣ ደረቴን ቀስፎ የያዘኝን ፍርሃት መቋቋም ላይ ብቻ ያተኮረ ነበር፡፡ የምሬን መጸለይ ጀመርኩ፡፡ እንደ አጋጣሚ ሆኖ አዛዥ ፓይለቱ በዐሥር ሺዎች የሚቆጠሩ የበረራ ልምድና በተለያዩ ዐይነት ድንገተኛ ነገሮች ሥልጠና የነበረው የቀድሞ ባሕር ኃይል ሙከራ ፓይለት ነበር፡፡ እሽጉ እንደ ተሰበረ ወዲያውኑ እርሱና ረዳት ፓይለቱ ነገሩን ለማስተካከል ርምጃ መውሰድ ጀመሩ፡፡ ብዙም ሳይቆዩ ችግሩን አገኙ፤ የኦክስጂን ማስካቸውን አጠለቁ፤ የእኔንም አስተካከሉ፡፡ ያለ ኦክስጂን የተቀረውን ተግባራቸውን መፈጸም አይችሉም ነበር፡፡

ከዚያም ፓይለቱ ለረዳት ፓይለቱ ፈጣን ትእዛዝ በመስጠት ዝቅ ወዳለ አልቲትዩድ በፍጥነት መውረድ ጀመረ፡፡ በዚያ ሁሉ ቀውስ ውስጥ በእርግጠኝነትና ልበ ሙሉነት ነበር የሚንቀሳቀሰው፡፡ ሥልጠናው ምን ማድረግ እንደ ነበረበት ትክክለኛውን አሠራር አስተምሮታል፡፡ ትልቅ ችግር ውስጥ እንሆን እንደ ነበር አውቃለሁ፤ እናንተ ግን ፓይለቱ ሁኔታውን ለመቆጣጠር እያደረገ የነበረውን ብትመለከቱ ችግር መኖሩን እንኳ ላታውቁ ትችላላችሁ፡፡ ምንም ዐይነት ፍርሃት አላየሁበትም፡፡ የሚወስዳቸው ርምጃዎች ሁሉ በዓላማ፣ በፍጥነትና ወዲያውኑ ነበር፡፡ የተረጋጋና ራሱንም ሆነ ሁኔታውን መቆጣጠር የቻለበት ሁኔታ ውስጥ ነበር፡፡

አምስት ደቂቃ ባልሞላ ጊዜ ውስጥ ፓይለቱ አውሮፕላኑን ወደ 12,000 ጫማዎች ዝቅታ አወረደው፤ ያም ማለት፣ በደቂቃ ከስድስት ሺህ እስከ ስምንት ሺህ ጫማዎች መውረድ ችለን ነበር ማለት ነው፡፡ ብዙም

ሳንቆይ በሰላም ማረፍ ቻልን፡፡ አስደንጋጩ ሁኔታ ካለፈ በኋላ ፓይለቱ ‹‹የታጠቀ›› እንደ ነበርና እኔ ግን የታጠቅሁ እንዳልነበርኩ ግልጽ ሆነልኝ! ሥልጠናውና ልምምዱ በእንዲህ ዓይነቱ ሁኔታ ምን ማድረግ እንዳለበት አስተምሮታል፤ በዚያ ቀውስ ውስጥ መግዛት ያስቻለውም ይኸው ነበር፡፡

የ1ጴጥሮስ 4፥1 መልእክትም ይኸው ነው፤ ያ የአውሮፕላኑ ፓይለት ድንገተኛ ሁኔታዎችን ለመቆጣጠር ታጥቆ እንደ ነበር ሁሉ፣ እኛም ለሚገጥመን መንፈሳዊ ችግር መታጠቅ አለብን፡፡ በክርስቶስ የተዘጋጀላችሁ ፍጻሜ ላይ ለመድረስና በሕይወት ለመንገሥ በምታደርጉ ጉዞ ለሚገጥማችሁ ችግር ሁሉ ይህ ጽናት የተሰኘው መጽሐፍ እንደዚያ በረራ መለማመጃ ሲሙሌተር እንዲሆንላችሁ ጸሎቴ ነው፡፡

## መከራ መምጣቱ አይቀርም

ከመታጠቃችን በፊት መጀመሪያ ማወቅ ያለብን መከራ መምጣቱ የማይቀር መሆኑን ነው፡፡ ዮሐንስ 16፥33 ላይ ኢየሱስ፣ ‹‹በዓለም ሳላችሁ መከራ አለባችሁ›› በማለት አስረግጦ ተናግሮአል፡፡ ‹‹ምናልባት መከራ ቢደርስባችሁ››–አለማለቱን ልብ እንድታደርጉ እፈልጋለሁ፡፡ ጳውሎስም፣ ‹‹ወደ እግዚአብሔር መንግሥት ለመግባት በብዙ መከራ ማለፍ አለብን›› በማለት ይመክራል (ሐዋርያት ሥራ 14፥22)፡፡ እንደ ገና፣ ‹‹በዚህ ፈተና ማንም እንዳይናወጥ. . . ለዚህ ነገር እንደ ተመደብን እናንተ ራሳችሁ ታውቃላችሁ›› በማለት ይጽፋል (1ተሰሎንቄ 3፥3)፡፡

ወታደሮች ወደ ጦር ሜዳ እንደሚሄዱ ሁሉ፣ እኛም መከራ፣ ‹‹ለመቀበል ተመድበናል፡፡›› ማንኛውም እውነተኛ ወታደር ወደ ጦር ሜዳ የሚሄደው ለመሸነፍ አይደለም፤ አንድ ጥሩ ወታደር ትኩረቱን ሁሉ ማሸነፍ ላይ ያደርጋል፡፡ ማሸነፍ እንዲችል በችግር ውስጥ ሁሉ ለመዋጋት ይወስናል፡፡ ለጦርነቱ በሚገባ ይታጠቃል፡፡ እኔና እናንተም ጦርነት ውስጥ ነን፡፡ ድነት ከማግኘታችሁ በፊት የነበረው ሕይወታችሁ የበለጠ ፀጥተኛና ሰላማዊ እንደ ነበር ታስባላችሁን?

ገና ዳግም ለተወለዱ ክርስቲያኖች ከችግር ነጻ ወደ ሆነ፣ የተረጋጋና ሰላማዊ ሕይወት እንደሚገቡ ሲነገራቸው በጣም ነው የማዝነው፡፡ እንዲህ ያለውን ባዶ ተስፋ ለአዳዲስ ክርስቲያኖች የሚሰጡ አገልጋዮች ወይም አማኞች መጀመሪያውኑ እነርሱ ራሳቸው በእውነት አልዳኑም ወይም ደግሞ ትኩረታቸውን አዲስ ዳግም የተወለደች ነፍስን የሚገጥማት ውጊያ ላይ ሳይሆን፤ ድነት የሚስገኘው ዕረፍት ላይ ብቻ አድርገዋል፡፡ እነዚህ፣ ‹‹መምህራን›› ስለ ዘሪው ባቀረበው ምሳሌ ኢየሱስ የተናገረውን በሚገባ

መረዳታቸውን እጠራጠራለሁ፤ በዚያ ክፍል ቃሉ በሰው ልብ ውስጥ ከተዘራ በኋላ፣ በቃሉ ምክንያት፣ ‹‹መከራ ወይም ስደት›› እንደሚመጣ ነበር ያስተማረው (ማርቆስ 4፥17)፡፡ ዘ ኒው ሊቪንግ ትራንስሌሽን፣ ‹‹ቃሉን በማመናቸው፣ ችግር ወይም ስደት ይመጣባቸዋል›› በማለት ተርጉሞታል፡፡ ሁሌም እንደሚያደርገው ክርስቶስ ቀጥተኛና ግልጽ በሆነ ቃል እንደ ነገረን የእግዚአብሔርን ቃል ስናምን፣ ችግር፣ አዳጋች ሁኔታና ስደት እንደሚኖሩ እርግጠኛ መሆን አለብን፡

አዳዲስ አማኞች ከሆናችሁና ይህን ገና በልምምድ ካላወቃችሁ፣ የተጠራችሁት ከዚህ በፊት ገጥሟችሁ ለማያውቅ ውጊያ መሆኑን ለመናገር የመጀመሪያው ሰው እንድንሆን ፍቀዱልኝ፡፡ ይሁን እንጂ፣ ትልቁ የምሥራች በአንዱም ውጊያ እንኳ መሸነፍ የሌለባችሁ መሆኑ ነው! በአንዱም መሸነፍ የለባችሁም፡፡ ከመዳናችሁ በፊት በብዙ የተለያየ መንገድ ተሸንፋችሁ ነበር፤ አሁን ግን በውስጣችሁ ካለው ከመንፈስ ቅዱስና ወደር ከሌለው የእግዚአብሔር ጸጋ ጉልበት የተነሣ፣ ወደ መንገዳችሁ በሚመጣ ማንኛውም ችግር ላይ ሥልጣንና ኃይል ይኖራችኋል፡፡

## አዲስ ነገር እየደረሰባችሁ አይደለም

ለጦርነት፣ ‹‹መታጠቅን›› በተመለከተ ማወቅ ያለባችሁ ሁለተኛ ነገር ከሰማይ በታች ምንም አዲስ ነገር የሌለ መሆኑን ነው፡፡ ሌላው ሰው ላይ ያልደረሰ ችግር በፍጹም አይደርስባችሁም፤ በተለይ ደግሞ ኢየሱስ፣ በነገር ሁሉ ተፈትኖ ነበር፡፡ ጳውሎስ እንዲህ ይጽፋል፣

> በሰዎች ሁሉ ላይ ከደረሰው የተለየ ፈተና አልደረሰባችሁም፤ እግዚአብሔር ታማኝ ነው፤ ስለዚህ ከምትችሉት በላይ እንድትፈተኑ አይተዋችሁም፤ ነገር ግን በምትፈተኑበት ጊዜ ፈተናውን መታገሥ እንድትችሉ መውጫ መንገዱን ያዘጋጅላችኋል፡፡ (1ቆሮንቶስ 10፥13)

የሚደርስባችሁ ማንኛውም ችግር፣ ሌላ ሰው ላይ የደረሰና በሌላ ሰው የተሸነፈ ነው፡፡ በዚህ እርግጠኛ መሆን ትችላላችሁ! ከዐቅማችን ወይም ከችሎታችን በላይ የሆነ ችግር ወይም ስደት እንደማይደርስብን ይህ ጥቅስ ተስፋ ቃል ይሰጣል፡፡ እንደዚያ እንዲሆን እግዚአብሔር አይፈቅድለትም፡፡ መቋቋም ወይም ማሸነፍ ከምትችሉት በላይ የሆነ ተቃውሞ ወይም ችግር ሊገጥማችሁ እንደሚችል ያላችሁን ፍርሃት አሁኑኑ አውጥታችሁ መጣል ትችላላችሁ፡፡

> የሚደርስባችሁ ማንኛውም ችግር፣ ሌላ ሰው ላይ የደረሰና በሌላ ሰው የተሸነፈ ነው፡፡

እንደዚያ ያለ ነገር ወደ መንገዳችሁ እንዲመጣ የሰማዩ አባታችሁ አይፈቅድለትም፤ እርሱ መንገዱን ይዘጋል፡፡

አንድ ሌላ የመጽሐፍ ቅዱስ ትርጒም፣ ከላይ የተመለከትነውን ጥቅስ፣ ‹‹እግዚአብሔር ቃሉን ይጠብቃል፤ ጸንታችሁ መቋቋም ከምትችሉት በላይ የሆነ ፈተና እንዲደርስባችሁ አይፈቅድም›› በማለት አስቀምጦታል፡፡ የተረጋገጠው ድንቅ እውነት፣ ሰይጣን እንደ ፈለገ እናንተን ማግኘት አለመቻሉ ነው፡፡ እርሱ የሚያቅደው እያንዳንዱ ጥቃት ሁሉን በሚችል አምላክ ፈቃድ ውስጥ ማለፍ አለበት፡፡ እነዚያን ፈተናዎች የሚፈጥረውና የሚያደርሰው የሰማዩ አባታችሁ አይደለም፤ ይሁን እንጂ፣ ጠላትን ማሸነፍና ለእግዚአብሔር መንግሥት መሬት በመያዝ ለእርሱ ክብር ማስገኘት እንድትችሉ፣ አንዳንዴ እናንተ ላይ እንዲደርሱ ይፈቅዳል፡፡ አንድ ቴርቱሊያን የተባለ ከ160-230 ዓ.ም የኖረ በጣም የተከበረ የቤተ ክርስቲያን መሪ ይህን በእርግጠኝነት ይናገራል፣

> ሐሳቡን መፈጸም እንዲችል ፈቃድ (ለሰይጣን) ሲሰጠው ምንጊዜም ቢሆን እግዚአብሔር ከራሱ መልካም ዓላማ ጋር በማይጋጭ ሁኔታ ይሠራል፡፡ ሰውን ወደ ራሱ የመመለሱን ምክንያት እንዳዘገየ ሁሉ፣ የዲያብሎስንም መጥፋት አዘገየ፡፡ ራሱን ለሰይጣን ባስገዛበት በዚያው ፈቃድ ነጻነት ሰው ጠላቱን እንዲያሸንፍና፣ በድል አድራጊነት መዳንን ለማግኘት የተገባው ሆኖ እንዲገኝ፣ ችግርና መከራ እንዲኖር ፈቀደ፡፡ በዚህም መንገድ ቢሆን ዲያብሎስ መጀመሪያውኑ ጉዳት አድርሶበት በነበረው ጨርሶ ድል በመነሣት፣ የበለጠውን መራራ ቅጣት ያገኛል፡፡ እግዚአብሔርም በእንዲህ ያለ አሠራር ይበልጥ መልካምነቱን ያረጋግጣል፡፡[1]

በአንድ በኩል ከመዳናችን በፊት ላሳለፍነው ወድቀት፣ ምክንያት በመሆኑ እግዚአብሔር ጠላትን ለማጥቃት የመምረጥን መብት ሰጥቶናል፡፡ በዚህም ምክንያት ክብሩ ሁሉ ለእግዚአብሔር ይሆናል፡፡ ከእንግዲህ ጠላት፣ የእግዚአብሔር እጅ ሥራ በሆነው የሰው ልጅ ላይ ማላገጥ አይችልም፡፡ በኤደን ገነት በነበረ ጊዜ አዳም በኃጢአት ሲወድቅ አላግጦ ነበር፤ በኃላ ግን ኢየሱስ መጥቶ ትጥቅ አስፈታው፤ ከግዛቱ አባረረው፡፡ አሁን ደግሞ ያንን የዲያብሎስን ሽንፈት የበለጠ የተሟላ የማድረግን መብት እግዚአብሔር ሰጠን፡፡

1. David W.Bercot, editor, *A Dictionary of Early Christian Belief* (Peabody, M.A: Hendrickson, 1998).

ጳውሎስ፣ ‹‹ስለ እናንተ በተቀበልሁት መከራ አሁንም ደስ ይለኛል፤ ክርስቶስ ስለ አካሉ ስለ ቤተ ክርስቲያን ከተቀበለው መከራ የጐደለውን በሥጋዬ አሟላለሁ›› በማለት ይጽፋል (ቈላስይስ 1፥24)፡፡ አንድ ሰው በሚገባ ሳይረዳ ይህን ቃል ካነበበ፣ የክርስቶስ መከራ ድንነታችንን ሙሉ ለማድረግ ብቁ አለመሆኑን ጳውሎስ ይናገራል በማለት ሊሳሳት ይችላል፡፡ በመጠኑም ቢሆን አባባሉ ጥቂት ግር የሚል ስለሆነ አንዳንድ ክርስቲያኖች ይህን ቃል ዐይተው እንዳላየ ያልፉታል፤ ትኩረት ሊሰጡትም አይፈልጉም፡፡ (እንዲያውም፣ ይህ ጥቅስ መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ መኖሩን እንኳ የማያውቁ ብዙ የተማሩ አገልጋዮችና አማኞች መኖራቸውን ብታውቁ በጣም ትገረማላችሁ፡፡)

ጳውሎስ የሚለው ግን እንደዚያ አይደለም፡ ይልቁንም እስከ ምድር ዳርቻ ድረስ መንግሥቱን የማስፋፋትን ሥራ የመፈጸም መብት እንዳለን ነው የሚያመለክተው፡፡ የእርሱን ያለቀና ያበቃለት ሥራ እስከ ምድር ዳርቻ የማድረስን መብት ኢየሱስ ሰጥቶናል፡፡ ጠላት በታላቅ ቁጣና ዓመፅ ይህን ስለሚቃወም መከራ ይኖራል፤ ሆኖም፣ ያ መከራ ወደ ድል የሚያደርስ መከራ ነው የሚሆነው፡፡ ኢየሱስ እንዳለው፣ ‹‹የገሃነም ደጆችም አያሸንፉትም›› (ማቴዎስ 16፥18 ይመ)፡፡ ይህ ጦርነትን ነው የሚያሳየው፡፡ ጉዞ ላይ ነን፤ በእግዚአብሔር ጸጋ የማስቻልና ብቁ የማድረግ ዐቅም ድል ለማድረግ እየወጣን ነው፤ ገሃነም ራሱ እንኳ አያስቆመንም ወይም አያሸንፈንም፡፡ ለዚህ ደግሞ የእግዚአብሔር ቃል ማረጋገጫ አለን!

በክርስትና ጉዞአችሁ ሊገጥማችል የሚችል ማንኛውም ችግር፣ ሌላው ሰው ላይ፣ እንዲያውም፣ ራሱ ክርስቶስ ላይ የደረሰ መሆኑንና በድል የተወጣ መሆኑን አስታውሱ፡፡ ይህን በተመለከተ፣ ‹‹በዓለም ዙሪያ ያሉት ወንድሞቻችሁ ተመሳሳይ መከራ እንደሚቀበሉ አውቃችሁ በእምነት ጸንታችሁ ተቃወሙት›› እያለ ጴጥሮስ ያበረታታናል (1ጴጥሮስ 5፥9)፡፡ እየተናገረለት ያለው መከራ እግዚአብሔር እንደሚፈልገው ሆነን ከመኖር ጋር እጅ ለእጅ ተያይዞ የሚሄድ ነው፤ በእርሱ ጸጋ ኃይል ጸንተን ስንቆም ግን፣ በአሸናፊነት እንወጣለን፡፡

## መሸነፍ የለብንም

አሁን፣ ‹‹ትጥቅን›› በተመለከተ ወደ ሦስተኛው አስፈላጊ ነጥብ መጥተናል፤ ይኸውም መሸነፍ እንደሌለብን ማወቅ ነው፡፡ ቀጥሎ የምታነቡትን የኢየሱስ ቃል እንዲሁ ላይ ላዩን አትመልከቱት፡፡ እንደ ውሃ ጠጡት፤ በጥልቀት አሰላስሉት፡፡

ስሙ! እንግዲህ... በጠላትም ኃይል ሁሉ ላይ ሥልጣን ሰጥቻችኋለሁ፤ የሚጐዳችሁም አንዳች ነገር አይኖርም፡፡ (ሉቃስ 10፥19)፡፡

ይህ ቃል በውስጡ ብዙ ነገር ይዞአል! በመጀመሪያ ደረጃ፣ ስሙ ከሚለው ቃል በማያያዝ ምን ያህል ትኩረት እንደ ሰጠው አስተውሉ፡፡ የቃለ አጋኖ ምልክቱን ልብ አድርጉ፡፡ ተርጓሚዎቹ በኢየሱስ ንግግር ውስጥ የቃለ አጋኖ ምልክት ከጨመሩ፣ ከፍ ያለ ትኩረት መስጠት አለብን ማለት ነው፡፡ ክብደት ያለው ቃል ነው ማለት ነው፡፡

በመቀጠል፣ አንዳንድ ኃይሎች ላይ ወይም አብዛኞቹ ኃይሎች ላይ ሳይሆን፣ በጠላት ኃይል ሁሉ ላይ ሥልጣን እንደ ተሰጠን ይናገራል፡፡ በጠላት ኃይል ሁሉ ላይ መቶ በመቶ ሥልጣን ያላችሁ መሆኑ ብቻ ሳይሆን ሰይጣን እናንተ ላይ ከሚያሰማራቸው ክፉ ኃይሎችም ላይ በጣም የበለጠ ኃይል ሰጥቷችኋል፡፡ ‹‹በጠላትም ኃይል ሁሉ ላይ ሥልጣን ሰጥቻችኋለሁ›› የሚለው፣ ‹‹ለእኛ ለምናምነው ከሁሉ በላይ ታላቅ የሆነውን ኃይሉን›› እንድናውቅ ጳውሎስ ለእኛ ከጸለየው ጋር ይያያዛል፤ ያ ኃይል፣ ‹‹ከግዛትና ከሥልጣን፣ ከኃይልና ከጌትነት. . . ሊሰየም ከሚቻለው ስም ሁሉ በላይ ነው›› (ኤፌሶን 1፥19-21)፡፡ በላይ ብቻ ሳይሆን ከሁሉም የበለጠ የበላይ! በጠላት ኃይል ሁሉ ላይ የበለጠ ሥልጣንና ኃይል ያለን ብቻ ሳይሆን፤ ተጨማሪ ድጋፍ የሚሆነን፣ ተጨማሪ አስደናቂ ሐቅ አለ፡፡ ‹‹ልጆች ሆይ፣ እናንተ ከእግዚአብሔር ናችሁ፤ እነርሱንም አሸንፋችኋቸዋል (የክርስቶስ ተቃዋሚ መንፈሶችን) ምክንያቱም በእናንተ ውስጥ ያለው በዓለም ካለው ይበልጣል›› (1ዮሐንስ 4፥4)፡፡ ክፉ መናፍስት ሁሉ የክርስቶስ ተቃዋሚ መንፈሶች ናቸው፤ የመከራ ሁሉ ምንጭም እነርሱ ናቸው፡፡ እኛ ውስጥ ያለውና ብቁ የሚያደርገን እርሱ፣ ስላሸነፋቸው እኛም አሸንፈናቸዋል፡፡

ሉቃስ 10፥19፣ ‹‹የሚጐዳችሁም አንዳች ነገር አይኖርም›› የሚለውን የኢየሱስ ተስፋ ቃል ይጠቅሳል፡፡ እናንተን የሚጐዳ ምንም ክፉ ኃይል፣ የለም! በሽንፈት የምታበቁበት ምንም ጦርነት አይገጥማችሁም፡፡ ስትዋጉ፣ እግዚአብሔር በሰጣችሁ መሣሪያ በጽናት ተዋጉ፤ እንደዚያ ከሆነ ሁሌም የበላይ ትሆናላችሁ፡፡ ለዚህም ቢሆን የቃሉ ማረጋገጫ አለን፤ ‹‹በክርስቶስ ሁልጊዜ በድል አድራጊነት እያዞረ ለሚመራን. . . አምላክ ምስጋና ይሁን›› (2ቆሮንቶስ 2፥14)፡፡

እርሱን የምንሰማ ከሆነ በማንኛውም ሁኔታ፣ በማንኛውም ውጊያ ውስጥ፣ እግዚአብሔር በአሸናፊነት ይመራናል፡፡ ዮሐንስ ይህን ያረጋግጣል፤

ከእግዚአብሔር የተወለደ ሁሉ ዓለምን ያሸንፋል፡፡ ዓለምን የሚያሸንፈውም እምነታችን ነው፡፡ (1ዮሐንስ 5÷4)

ዓለም እኛ ላይ የሚወረውረውን ማንኛውንም ነገር የሚያሸንፍ እምነታችን ነው፡፡ ሰይጣን፣ ‹‹የዚህ ዓለም አምላክ›› ተብሎ መጠራቱን አትርሱ፡፡ በድል የምንወጣበትን መንገድ ቀድሞውኑ እግዚአብሔር ስላዘጋጀልን እኛ ላይ መወርወር የሚሞክረውን ማንኛውንም ነገር እናሸንፋለን፡፡

ዮሐንስ እንደሚነግረን ዓለምን የሚያሸንፈውና የሚያንበረክከው እምነታችን ነው፡፡ ለመሆኑ፣ እምነት ለምን አስፈለገ? ምክንያቱም ለማሸነፍ ወደሚያስችለን ኃይል የመግባትን ጸጋ (ዐቅም) የሚሰጠን እምነት በመሆኑ ነው፡፡ በእግዚአብሔር ጸጋ በሕይወት መንገሥ እንዳለብን ተመልክተን ነበር፡፡ ይሁን እንጂ፣ ምንም እንኳ ለሁሉም በነጻ የሚሰጥ ቢሆንም፣ እምነት ከሌለን (ካላመንን) ያንን ጸጋ አናገኝም፤ እምነት ወደሚገጥመንና ልናሸንፈው ወደሚገባን ሁኔታ የእግዚአብሔር ጸጋ (ኃይል) ወደ እኛ የሚመጣበት መስመር ነው፡፡ ጳውሎስ፣ ‹‹አሁን ወደ ቆምንበት ጸጋ በእምነት መግባት ችለናል›› ይላል (ሮሜ 5÷2)፡፡

የእግዚአብሔር ጸጋ ነጻ ስጦታ ነው፤ ለልጆቹ ሁሉ የተሰጠ ነው፤ ሆኖም፣ ‹‹በጸጋው ቃል›› ካላመንን፣ (እምነት ከሌለን) ምንም ጸጋ የሚኖረን እንኳ አይመስልም፤ ‹‹ሊያንጻችሁና በቅዱሳኑ ሁሉ መካከል ርስት ሊያወርሳችሁ ለሚችለው ለጸጋው ቃል ዐደራ እሰጣችኋለሁ›› ይላል ጳውሎስ (ሐዋርያት ሥራ 20÷32)፡፡ ለእግዚአብሔር ክብር በሕይወት ሊነግሡበት የሚገባውን ርስት ሊሰጣቸው ወደሚችለው ማለትም - ወደ ጸጋው ቃል ያመለክታቸዋል፡፡

## ጸጋ፣ ማንኛውንም ውጊያ ለማሸነፍ በቂ ነው

‹‹መታጠቅን›› በተመለከተ፣ ይህ ወደ አራተኛው አስፈላጊ እውነት ያመጣናል፤ ይኸውም በሚገጥመን ማንኛውም ችግር ላይ ለመግዛት የእግዚአብሔር ጸጋ በቂ ኃይል ያለው መሆኑ ነው፡፡

ይህን ጳውሎስ በግል ሕይወቱ ከገጠመው ትግል ማየት እንችላለን፡፡ የነበረው ማስተዋል፣ በየጊዜው ይቀበል የነበረው መገለጥ፣ ለጨለማው መንግሥት እጅግ ጉጂ ሆነው ነበር፡፡ ከመንፈስ ቅዱስ የተቀበላቸው እውነቶች በዘመኑ የነበሩ አማኞችን በጣም አጠንክረው ነበር፡፡ ወደ ፊት የሚመጣውን ትውልድ በተመለከተም ይህ እንደ ተጠበቀ ይሆናል፡፡ ስለዚህም ጳውሎስ እንዲህ ሲል ጻፈ፣

> ከዚህ ታላቅ መገለጥ የተነሣ እንዳልታበይ የሥጋዬ መውጊያ እርሱም የሚያሠቃየኝ የሰይጣን መልእክተኛ ተሰጠኝ፡፡
>
> (2ቆሮንቶስ 12፥7)፡፡

ጳውሎስን ያጋጠመው ይህ ‹‹መውጊያ›› በመጽሐፍ ቅዱስ መምህራን መካከል አለመግባባት ፈጥሮአል፡፡ እንደ እውነቱ ከሆነ ግን እንደዚያ መሆን አልነበረበትም፤ እስቲ ይህን አለመግባባት ማስተካከል እንሞክር፡፡

በመጀመሪያ ደረጃ፣ ‹‹የሥጋዬ መውጊያ›› የሚለውን ነገር ለጳውሎስ የሰጠው ማን ነበር? መቼም፣ እግዚአብሔር ሊሆን እንደማይችል ግልጽ ነው፤ ምክንያቱም፣ ‹‹የተወደዳችሁ ወንድሞቼ ሆይ፣ አትታለሉ፡፡ በጎ ስጦታና ፍጹም በረከት ሁሉ ከላይ ከሰማይ ብርሃናት አባት ይወርዳሉ፤ በእርሱ ዘንድ መለዋወጥ፣ ከመዞር የተነሣ የሚያርፍ ጥላ የለም›› ተብሎ ተነግሮናል (ያዕቆብ 1፥16-17)፡፡ መልካም ወይም ፍጹም ያልሆነ ነገር ከእግዚአብሔር ይመጣል በማለት የምናስብ ከሆነ ተታልለናል ወይም ተሳስተናል ማለት ነው፡፡ የሰይጣን መልእክተኛ በምንም ዐይነት መልካም፣ ከዚያም አልፎ ፍጹም ሊሆን አይችልም፡፡ ምናልባትም፣ ‹‹ጳውሎስ እንዳይታበይ ስላደረገ በዘወርዋራ መንገድ ቢሆን እንኳ መልካም ነው›› የሚሉ ሰዎች ሊኖሩ ይችላሉ፡፡ ሐዋርያው ያዕቆብ፣ ‹‹እግዚአብሔር በክፉ አይፈተንም፤ እርሱም ማንንም አይፈትንም›› በማለት ይህን የተሳሳተ ሐሳብ ያፈርሳል (ያዕቆብ 1፥13)፡፡

እስቲ የያዕቆብን ቃል ተመልከቱ፣ ‹‹እግዚአብሔር. . . ማንንም በክፉ አይፈትንም፡፡›› ያንን የሰይጣን መልእክተኛ የላከ እግዚአብሔር ሊሆን አይችልም፤ እንደዚያ ከሆነ ጳውሎስን በክፉ እየፈተነው ነው፤ ስለዚህም በያዕቆብ በኩል የተነገረው ሐሰት ነው ማለት ነው፡፡ እግዚአብሔር ደግሞ አይዋሽም፡፡ ስለዚህም ያለ ምንም ማመንታት ያ ‹‹መውጊያ›› ከእግዚአብሔር አይደለም ብለን መደምደም እንችላለን፡፡

በሁለተኛ ደረጃ፣ የጳውሎስ ሥጋ መውጊያ ምን ነበር? አንዳንድ ሰዎች በሽታ፤ የዐይን ሕመም ወይም ሥጋው ላይ የነበረ አንድ ዐይነት ድካም ነበር ይላሉ፡፡ ለዚህ አባባላቸው መሠረት የሚያደርጉት ጳውሎስ ቀጥሎ የጻፈውን ነው፤

> ይህ ነገር ከእኔ እንዲወገድልኝ ጌታን ሦስት ጊዜ ለመንሁት፤ እርሱ ግን፣ ‹‹ጸጋዬ ይበቃሃል፤ ኃይሌ ፍጹም የሚሆነው በድካም ጊዜ ነውና›› አለኝ፡፡ ስለዚህ የክርስቶስ ኃይል በእኔ ያድር ዘንድ ይበልጥ ደስ እያለኝ በድካሜ እመካለሁ፡፡ (2ቆሮንቶስ 12፥8-9)

ከላይ ባለው ጥቅስ ውስጥ ያሉትን ድካምና ሕመም የተሰኙት ቃሎች ለየት ብለው እንዲጻፉ አድርጌአለሁ፡፡ በመጀመሪያ ሁለተኛው ላይ ላተኩር፡፡ ‹‹በድካሜ›› ከሚል አባባሉ በመነሣት አንዳንድ ግራ የገባቸው መምህራን የጳውሎስ የሥጋ መውጊያ አካላዊ ሕመም ነው ብለዋል፡፡ ድካም ለሚለው የግሪኩ ቃል አስቴንያ (astheneia) ሲሆን አዲስ ኪዳን ውስጥ ዐሥራ ሁለት ጊዜ ጥቅም ላይ ውሏል፡፡ ወንጌሎቹ ውስጥ ይህ ቃል ብዙ ጊዜ የሚገልጸው አካላዊ ሕማምን ነው፡፡ መልእክቶቹ ውስጥ ግን ሰብዓዊ ድካምን ማለትም በራሳችን ችሎታ አንድን ነገር ለመፈጸም ወይም ለማሸነፍ ዐቅም የሌለን መሆኑን ለማመልከት ነው ጥቅም ላይ የዋለው፡፡ በእንዲህ ባለ መልኩ ከተቀመጠ የሚያመለክተው አካላዊ ሕመምን አይደለም ማለት ነው፡፡

ለዚህ ምሳሌ የሚሆነን፣ ‹‹እንዲሁም ደግሞ መንፈስ በድካማችን ያግዘናል፤ እንዴት መጸለይ እንደሚገባን አናውቅም፤ መንፈስ ግን በቃላት ሊገለጥ በማይችል መቃተት ለእኛ ይማልድልናል›› የሚለው ሮሜ 8፥26 ነው፡፡ እዚህም ላይ ድካም ለሚለው ግሪክኛው ቃል አስቴንያ ነው ጥቅም ላይ የዋለው፡፡ መቼም፣ ክርስቲያኖች ሁሉ በሽተኞች፣ ሕመምተኞች ናቸው ማለት አይቻልም፡፡ ታዲያ፣ ከምልጃ ጸሎት አንጻር ማንኛውም አማኝ ያለበት ድካም ምንድነው? መልሱ፣ ከሰብዓዊ ውሱንነታችን የተነሣ እንዴት መጸለይ እንዳለብን የማናውቅበት ጊዜ አለ የሚለው ነው፡፡

ለምሳሌ፣ እናቴ በአንድ አገር ብትሆንና እኔ ደግሞ በሌላ አገር ብሆን፣ በጣም ጸሎት የሚያስፈልገው አንድ አጣዳፊ ነገር ቢፈጠር፣ እርሷ ግን ከእኔ ጋር መገናኘት ባትችል፣ ከሰብዓዊ ውሱንነቴ የተነሣ ያለችበትን ሁኔታ ማወቅ አልችልም፡፡ መንፈስ ቅዱስ ግን ለእርሷ እንድጸልይ በመምራት በዚህ ውሱንነት (ድካም) ውስጥ ይረዳኛል፡፡ በድጋሚ ይህ አስቴንያ የተሰኘው ግሪክ ቃል ከተፈጥሮአዊ ሰብዓዊ ድካም ጋር እንጂ፣ ከአካላዊ ድካም (ሕመም) ጋር ምንም ግንኙነት የለውም፡፡

ሌላው ምሳሌ ሊሆነን የሚችል ዕብራውያን 4፥15 ላይ ያለው፣ ‹‹በድካማችን የማይራራልን ሊቀ ካህናት የለንምና፤ ነገር ግን እንደ እኛ በማንኛውም ነገር የተፈተነ ሊቀ ካህናት አለን፤ ይሁን እንጂ፣ ምንም ኃጢአት አልሠራም›› የሚለው ነው፡፡ ድካም ለሚለው ግሪክኛ ቃል ያው አስቴንያ ነው፡፡ በድጋሚ ይህ ግሪክኛ ቃል አካላዊ ሕመምን ሳይሆን ከእግዚአብሔር ችሎታ ጋር ሲነጻጸር የእኛን ሰብዓዊ ደካማነት ነው የሚያመለክተው፡፡ እኛ የሚገጥመንን ውጣ ውረድ ለመለማመድና ውጤት ባለው መንገድ እንዲረዳን ኢየሱስ በፈቃደኝነት ሰብዓዊ ድካማችን ወሰደ፡፡ ‹‹ከኃጢአት በቀር በሁሉም ነገር ተፈትኖአል›› የሚለው ሕመምን ሳይሆን፣

በዚህ ምድር ሕይወቱ ዘመን በፈቃደኝነት የተቀበለውን ሰብዓዊ ድካምን ነው የሚያመለክተው፡፡

እንግዲህ ይህን በአእምሮአችን በመያዝ ቀደም ሲል የተመለከትነውን የጳውሎስ ቃል ብናነብ የበለጠ ግልጽ ይሆንልናል፡፡ ቀጥሎ ያለውን እናንብብ፤

> ይህ ነገር ከእኔ እንዲወገድልኝ፣ ጌታን ሦስት ጊዜ ለመንሁት፤ እርሱ ግን፣ ‹‹ጸጋዬ ይበቃሃል፤ ኃይሉ ፍጹም የሚሆነው በድካም ጊዜ ነውና አለኝ፡፡ ስለዚህ የክርስቶስ ኃይል በእኔ ያድር ዘንድ ይበልጥ ደስ እያለኝ በድካሜ እመካለሁ፡፡ (2 ቆሮንቶስ 12፥8-9)

እዚህም ላይ ድካምና ሕመም የተሰኙት ቃሎች ለየት ብለው እንዲጻፉ አድርጌአለሁ፡፡ ምክንያቱም ሁለቱም አስቴኒያ ከሚል ግሪከኛ ቃል ነው የመጡት፡፡ ስለሆነም የጳውሎስን ቃል በዚህ መንገድ በቀላሉ መተርጎም ይቻላል፤

> ‹‹ጸጋዬ ይበቃሃል፤ ምክንያቱም ኃይሌ ፍጹም የሚሆነው ሰው ዐቅም ሲያጣ ነውና›› አለኝ - ስለዚህ የክርስቶስ ኃይል በእኔ ያድር ዘንድ ይበልጥ ደስ እያለኝ ዐቅም በማጣቴ አመካለሁ፡፡

እንዲያውም ይህ ምንባብ በሌሎች ትርጉሞች በዚሁ መንገድ ተተርጉመዋል፡፡ ከእነዚህ አንዱ፣ ‹‹ለአንተ የሚያስፈልግህ የእኔ ችሎታ ነው፡፡ አንተ ስትደክም የእኔ ኃይል የበለጠ ብርቱ ይሆናል፤ ስለዚህ ክርስቶስ ኃይሉን የሚሰጠኝ በዚህ መንገድ ከሆነ ደስ እያለኝ በደካማነቴ እመካለሁ›› የሚለው በዘመናዊ እንግሊዝኛ የቀረበ መጽሐፍ ቅዱስ ሊሆን ይችላል፡፡

መንፈስ ቅዱስ እያመለከተ ያለው በሽታን ብቻ ነው ብለን የምናስብ ከሆነ፣ ራሳችንን እያታለልን ነው ማለት ነው፡፡ ነገሩ እንደዚያ ቢሆን ኖሮ ምንባቡ፣ ‹‹ኃይሌ የሚበረታው አንተ ስትታመም ነው፡፡ ስለዚህ ክርስቶስ ኃይሉን የሚሰጠኝ እኔ ስታመም ከሆነ ደስ እያለኝ ሕማሙን እችለዋለሁ›› ይል ነበር ያ ደግሞ በጣም ግራ የሚያጋባ አይሆንም ነበር ትላላችሁ? በሚገባ ከፈተሽነው ይህ አስተሳሰብ ምንኛ የተሳሳተ መሆኑን ማየት እንችላለን፡፡

በተጨማሪም መልእክቱን በሙሉ በዐውዱ መሠረት ካነበብነው ጳውሎስ እየተናገረ ያለው ስለ ሕመም ወይም በሽታ እንዳይደለ ግልጽ ይሆንልናል፡፡ ‹‹የሰይጣን መልእክተኛ›› የተባለው እንዴት እያጠቃው ስለ ነበረበት ሁኔታ ጳውሎስ ሲናገር፣

አይሁድ ለአርባ ጅራፍ አንድ የቀረው አምስት ጊዜ ገርፈውኛል፡፡ ሦስት ጊዜ በዱላ ተደብድቤአለሁ፤ አንድ ጊዜ በድንጋይ ተወግሬአለሁ፤ ሦስት ጊዜ የመርከብ አደጋ ደርሶብኛል፤ አንድ ጊዜ ሌሊትና ቀን በባሕር ላይ አድሬአለሁ፤ ብዙ ጊዜ በጉዞ ተንከራትቻለሁ፤ ደግሞም ለወንዝ ሙላት አደጋ፣ ለወንበዴዎች አደጋ፣ ለገዛ ወገኖቼ አደጋ፣ ለአሕዛብ አደጋ፣ ለከተማ አደጋ፣ ለገጠር አደጋ፣ ለባሕር አደጋ፣ እንዲሁም ለሐሰተኞች ወንድሞች አደጋ ተጋልጬ ነበር፡፡ ብዙ ደክሜአለሁ፤ ብዙ እንቅልፍ አጥቻለሁ፤ ተርቤአለሁ፤ ተጠምቻለሁ፤ ብዙ ጊዜ ምግብ ሳልቀምስ ኖሬአለሁ፤ በብርድና በራቁትነት ተቆራምጃለሁ.... መመካት ካለብኝ ደካማነቴን በሚያሳዩ ነገሮች እመካለሁ – ብሏል፡፡ (2ቆሮንቶስ 11÷24-27፣30)

ጳውሎስ በተደጋጋሚ እርሱን ለማጥፋት የሞከረ የሰይጣን መልእክተኛ ያደረሳቸውን መከራዎች ይዘረዝራል፡፡ በራሱ ችሎታ እንዲህ ያሉ ያልተጠበቁ ችግሮችን ጳውሎስ መከላከል ወይም ማስቆም አይችልም፡፡ በዚህም ምክንያት፣ ‹‹ደካማነቴን በሚያሳዩ ነገሮች እመካለሁ›› አለ፡፡ በዚህ መልእክት የተጠቀሰው፣ ‹‹ድካም›› ወይም፣ ‹‹የሥጋ መውጊያ›› ከክፉ የዓይን ሕመም፣ ከበሽታ፣ ከደዌ ወይም ከማንኛውም አካላዊ ሕመም ጋር የሚያገናኘው ነገር እንደሌለ በጣም ግልጽ ነው፡፡

የጳውሎስ፣ ‹‹የሥጋዬ መውጊያ›› ከበሽታ ጋር ምንም ግንኙነት እንደሌለው በማመልከት ረገድ በጣም ራቅ ብለን መሄድ ካስፈለገ፣ በሌሎች የቅዱሳት መጻሕፍት ክፍሎችም ጥቅም ላይ የዋለበትን ሁኔታ እንመልከት፡፡ ከአሁን ውጪ ይህ ሐረግ ሦስት ጊዜ ጥቅም ላይ ውሏል፤ ሦስቱም የሚገኙት ብሉይ ኪዳን ውስጥ ነው፡፡ ሦስቱም በተደጋጋሚ እስራኤላውያንን ያጠቁ የነበሩ ከነዓናውያንን ይመለከታሉ፡፡ ‹‹የምድሪቱን ነዋሪዎች አሳዳችሁ ሳታስወጧቸው ብትቀሩ ግን፣ እንዲኖሩ የተዋችኋቸው ሰዎች ለዐይናችሁ ስንጥር፣ ለጐናችሁም እሾክ ይሆኑባችኋል፡፡ በምትኖሩበትም ምድር ችግር ይፈጥሩባችኋል›› በማለት እግዚአብሔር ለሕዝቡ ተናግሮ ነበር (ዘኍልቁ 33÷55)፡፡ በእያንዳንዱም ጊዜ፣ ‹‹የጐን እሾክ›› በሚል ተለዋጭ ዘይቤ የተገለጹት ፍሬያማ ሕይወትን የሚያጨናግፉ ተቃዋሚ ሰዎች ናቸው፡፡ይህ ሐረግ አንድም ጊዜ በሽታን ወይም ደዌን ለማመልከት ብሉይ ኪዳን ውስጥ ጥቅም ላይ በፍጹም አልዋለም፡፡ የቅዱሳት መጻሕፍት ምሑር የነበረው ጳውሎስ በየሄደበት ሁሉ ይገጥመው የነበረውን ችግር ለማመልከት በተመሳሳይ መልኩ በዚህ ሐረግ ተጠቅሟል፡፡

## ታላቅ የአስተሳሰብ ለውጥ

በተደጋጋሚ እየገጠመው በነበረው መሰናክል፣ ችግሮች፣ ፈተናዎችና ስደቶች ጳውሎስ በጣም ሳያዝን አልቀረም፤ አንዴ ሳይሆን ሦስት ጊዜ፣ ከእነዚህ ነገሮች በስተጀርባ የነበረ ሰይጣናዊ ተፅዕኖን እንዲያስወግድለት ወደ እግዚአብሔር ጮኸ፡፡ መጀመሪያ ላይ እግዚአብሔር ለጳውሎስ መልስ ያልሰጠው ጥያቄው የተሳሳተ ስለ ነበር መሆኑን አምናለሁ፤ ጳውሎስ ካለ ቦታው መልስ እየጠበቀ ነበር፡፡ ከሦስተኛው የጳውሎስ ጥያቄ በኋላ፣ እግዚአብሔር አበራለት፤ በእርሱ ውስጥ ያለውንም መፍትሔ ሰጠው፡፡

> አሁንም ገና አላስተዋልክም? በጠላት ኃይል ሁሉ ላይ ጸጋዬን (የማይከፈልበት የማስቻል ዐቅም) ሰጥቼሃለሁ፡፡ ስለሆነም፣ ለአንተ የሚያስፈልግህ የእኔ ጸጋ (የማስቻል ዐቅም) ብቻ ነው፤ ምክንያቱም በሰብዓዊ ችሎታህ ማድረግ በማትችለው ማንኛውም ነገር ላይ ኃይሉን ይገልጣል፡፡ በሌላ አነጋገር፣ ተቃውሞው ታላቅ የመሆኑን ያህል፣ አንተ ካመንህ የእኔ ጸጋም ታላቅ በሆነ ሁኔታ በሕይወትህ ሲገለጥ ታያለህ (2ቆሮንቶስ 12፥9 ደራሲው እንዳፍታታው)

ይህ ነገር ለጳውሎስ ግልጽ ከሆነለት በኋላ አስደናቂ ነገር መሆን ጀመረ፡፡ ከአንድ አስተሳሰብ መንገድ ወደ ሌላው የሚያሻግር፣ ታላቅ ወይም ሥር ነቀል ለውጥ አገኘ፡፡ በየጊዜው ይገጥመው ስለ ነበረው ሰይጣናዊ ተቃውሞ የነበረው ዝንባሌ ሁሉ ተለወጠ፡፡ ከዚያ በኋላ ከእርሱ እንዲወገድለት እግዚአብሔርን አልለመነም፤ ይልቁንም በጋለ ስሜት ተነሣሥቶ፣

> ስለ ክርስቶስ በድካም፣ በስድብ፣ በመከራ፣ በስደትና በጭንቀት ደስ የምሰኘው ለዚህ ነው፤ ስደክም ያን ጊዜ ብርቱ ነኝ (2ቆሮንቶስ 12፥10) በማለት ጻፈ፡፡

አሁን የእርሱ ትምክህት፣ ‹‹ከዚህ ቅጽበት አንሥቶ በሚገጥመኝ ማንኛውም ችግር (ትሊፕሲስ) ላይ ምንም ዐቅም ስለሌለኝ ደስ ይለኛል!›› የሚል ሆነ፡፡

በምንድነው ደስ ይለኛል የሚለው? ይህ እንዴት ሊሆን ቻለ? ጳውሎስ አእምሮውን ሳተ እንዴ? ወይስ እያጋነነ ነው? ወይስ እየዋሸ? በፍጹም፤ በእስትንፋሰ መንፈስ ቅዱስ የተነሣሣ ሰው እንዲህ ያሉ ነገሮችን አያደርግም፤ ምክንያቱም እግዚአብሔር አይዋሽም፡፡ ታዲያ፣ አንድ ሰው በስድብ፣ በመከራ፣ በስደት፣ በጭንቀትና በሌሎች ችግሮች ደስ የሚሰኘው እንዴት ነው? መልሱ ቀላል ነው፤

ታላቅ ተቃውሞን ለማሸነፍ ታላቅ ኃይል ይጠይቃል፤ ያ ደግሞ ታላቅ ድል ያስገኛል፡፡

ከበድ ያለ ችግር ሲደርስባቸው ብዙ ክርስቲያኖች ደስ አይላቸውም፡፡ በእንዲህ ዐይነት ሁኔታ ውስጥ ከጠላት ጋር ውጊያ መግጠም ያስከፋቸዋል፡፡ ቀለል ያለ፣ ምቾት ያለው፣ ለስላሳና ተቃውሞ የሌለው ሕይወት ቢኖራቸው ይመርጣሉ፡፡ ጳውሎስ የተረዳው እውነት እነርሱ ልብ ውስጥ የለም፡፡ ተቃውሞዎች ሁሉ ወደሚቀጥለው በክርስቶስ የማደግና የመብሰል ደረጃ የሚያደርሷቸው ታላቅ ኃይል (ጸጋ) በውስጣቸው እንዲገለጥ መልካም አጋጣሚ መሆናቸውን አይገነዘቡም፡፡ እግዚአብሔር አስተሳሰቡን ከመለወጡ በፊት ጳውሎስም የሚገጥመውን ችግር በተመለከተ የዚህ ዓይነት ዝንባሌ ነበረው፤ ከእግዚአብሔር ያገኘው አንድ ቃል ግን አስተሳሰቡን ሁሉ ለወጠው፡፡ 2ኛ ቆሮንቶስን የጻፈው በ56 ዓ.ም. አካባቢ ነበር፡፡ ከጥቂት ዓመት በኋላ የሮሜ መልእክትን ጻፈ፡፡ በኋላ በጻፈው መልእክቱ ችግርን (ትሊፕሲስን) አስመልክቶ ያዳበረውን ፍጹም የተለየ ዝንባሌ ተመልከቱ፤

> ከክርስቶስ ፍቅር የሚለየን ማን ነው? ችግር ነው ወይስ ሥቃይ ወይስ ስደት፣ ወይስ ረሃብ፣ ወይስ ዕራቁትነት፣ ወይስ አደጋ፣ ወይስ ሰይፍ?... በዚህ ሁሉ በወደደን በእርሱ ከአሸናፊዎች እንበልጣን፡፡ (ሮሜ 8፥35፣37)፡፡

በተለይ፣ ‹‹በዚህ ሁሉ በወደደን በእርሱ ከአሸናፊዎች እንበልጣለን›› የሚለው ቃል ምንጊዜም በውስጣችሁ ይሁን፡፡ ታላቅ የአስተሳሰብ ለውጥ ከማድረጉ በፊት ጳውሎስ፣ ከችግር ጋር መጋፈጡ እንዲያበቃ እግዚአብሔርን ሲለምን ነበር፡፡ አሁን ግን መልእክቱ ፍጹም የተለየ መልክ ይዟል፡፡ የእግዚአብሔር ጸጋ መከራን በትዕግሥት ለመቀበል ብቻ ሳይሆን፣ አስደናቂ ድል ለማግኘትም ከበቂ በላይ ነው፡፡ አሁን የጳውሎስ ዐቋም፤ ‹‹በክርስቶስ የበለጠውን ድል እንዳገኝባቸው ተቃውሞዎችን ደጋግማችሁ አምጡ›› የሚል ሆኗል፡፡ ጳውሎስ መከራ ለመቀበል ‹‹ታጥቋል›› ከውጊያው በፊት ከነበረው ይልቅ፣ የበለጠ ብርቱ ሆኖ ለመውጣት፣ ድል ለማድረግ ለመዋጋት ታጥቋል፡፡

## ፈተናን እንደ አንድ ዐይነት ዕድል ማየት

በመጨረሻም፣ ‹‹ታጥቀን የምንገኘው›› ከውጊው በፊት፣ በውጊያው ውስጥና ከውጊያው በኋላ መከራን በተመለከተ በልባችንም ሆነ በአእምሮአችን ጽናት ያለው ተስፋ ሲኖረን ነው፡፡ ከእንግዲህ እንደ አንድ ዐይነት ዕድል

እንጂ፣ ፈተናዎችና ችግሮችን እንደ መሰናክል ስለማናያቸው እነርሱን በተመለከተ አዎንታዊ ዝንባሌን መያዝ እንችላለን!

ሐዋርያው ያዕቆብ፣ ‹‹ወንድሞች ሆይ፣ ልዩ ልዩ መከራ ሲደርስባችሁ እንደ ሙሉ ደስታ (ዕድል) ቁጠሩት›› በማለት ይጽፋል (ያዕቆብ 1፥2)፡፡ ጦርነቱ ቀድሞውኑ በክርስቶስ በድል መጠናቀቁንና ድጋፍ የሚሆነን ሥልጣንና የሰማይ ኃይል እንዳለን እናውቃለን፡፡ እጅ ካልሰጠን፣ በጽናት ቆመን ከተዋጋን፣ ሁሌም አሸናፊዎች ሆነን እንወጣለን፡፡ እግዚአብሔር ለሕይወታችን ያለው ፈቃድና የመጨረሻ ፍጻሜም ይኸው ነው፡፡

ሮሜ 8፥31 ላይ ጳውሎስ፣ በድፍረት እንደሚለው፣ ‹‹እግዚአብሔር ከእኛ ጋር ከሆነ፣ ማን ሊቃወመን ይችላል?››

# 9

# በጸጋው በርቱ

*ተጋድሎአችን ከሥጋና ከደም ጋር ሳይሆን ከዚህ ከጨለማ ዓለም ገዦች፣ ከሥልጣናትና ከኃይላት እንዲሁም በሰማያዊ ስፍራ ካሉ ከርኩሳን መናፍስት ሰራዊት ጋር ነው፡፡*

*ኤፌሶን 6፥12*

እያንዳንዱ የእግዚአብሔር ልጅ ውጊያ ላይ ነው፡፡ እንደዚያ ካልሆነ ከዚህ ዓለም ነን ማለት ነው፤ የእግዚአብሔር ነን እያልን በማሰብ ራሳችንን አታልለነዋል ማለት ነው፡፡

አባባሉ ከባድ መሆኑን እገነዘባለሁ፤ ግን እስቲ እውነታውን በምሳሌ እንዳቀርብ ፍቀዱልኝ፡፡ በአዶልፍ ሒትለር ዘመን በጀርመን እየኖራችሁ እንደ ነበር አስቡ፡፡ ይህ ጨቋኝ መሪ፣ ናዚ ጀርመን የኃላ ኃላ መላው የአውሮፓ አህጉርን ጨርሶ የምትቆጣጠርበት አዲስ ሥርዐት ማቋቋም ፈልጎ ነበር፡፡ እንደ እውነቱ ከሆነ ለሌሎች ሁሉ ጭፍን ጥላቻ ነበረው፣ በጣም የሚጠላው ግን የአይሁድ ዝርያ ያላቸውን ነበር፡፡ የጀርመን ዘር ከሆናችሁና፣ የአዶልፍ ሒትለርን አስተሳሰብ የማትቃወሙ ከሆነ፣ በምንም ዐይነት ሁኔታ ጥቃት ይደርስብናል ብላችሁ አትሰጉም፡፡

ይሁን እንጂ፣ በትውልድ አይሁድ ከሆናችሁ ሕይወታችሁ ፍጹም የተለየ ሁኔታ ውስጥ ይሆናል፡፡ ጥቃትን በመፍራት በማያቋርጥ ስጋት ውስጥ ትኖራላችሁ፡፡ በየትኛውም ጊዜ ያልሆነ ስም ሊሰጣችሁ፣ ሊተፉባችሁ፣ ልትዘረፉ፣ ልትሰረቁ ትችላላችሁ፤ እንዳትያዙ፣ ባርያ እንዳትደረጉ፣ ስቃይ እንዳይደርስባችሁና እንዳትገደሉ ነቅታችሁ ራሳችሁን መጠበቅ አለባችሁ፡፡ ብትወዱትም ብትጠሉትም እናንተም ውጊያ ላይ ናችሁ፡፡ አስተዋይና ንቁ የሆኑ አይሁድ ራሳቸውን አስታጥቀው ነበር፤ ከሒትለር ጭቆና አገዛዝ ለማምለጥም የሚያስፈልገውን ሁሉ ያደርጉ ነበር፡ እንደዚያ ያላደረጉ ማጎሪያ ካምፕ ውስጥ ታስረው የኃላ ኃላ ተገድለዋል፡፡

ሰይጣንና ሰራዊቱ ከሒትለርም ሆነ ከናዚ አገዛዝ እጅግ በጣም የከፉ ናቸው፡፡ የዲያብሎስ ዘሮች ከሆናችሁ፣ የጥቃት ዒላማ አትሁኑም፡፡ ጠርነት

ውስጥ እንዳለ ሰው መዘጋጀትም አይኖርባችሁም፡፡ በዘመኑ የነበሩ ግብዝ መንፈሳዊ መሪዎችን ኢየሱስ፣ ‹‹እናንተ ከዚህ ዓለም ናችሁ›› ብሏቸው ነበር (ዮሐንስ 8፥23)፡፡ በኃላም በደንብ እንዲገባቸው በማሰብ በቀጥታ፣ ‹‹እናንተ የአባታችሁ የዲያብሎስ ናችሁ›› አላቸው (ዮሐንስ 8፥44)፡፡ ምንም እንኳ እነዚህ ሰዎች ሁሉን ቻይ እግዚአብሔርን እያገለገሉ እንደ ነበር ቢያምኑም፣ በእውነቱ ግን የዚህ ዓለምን ጨቋኝ መሪ እያገለገሉ ነበር፡፡

በእውነት ከእግዚአብሔር ከሆናችሁ፣ የምትኖሩበት ዓለም የእግዚአብሔር መንግሥት ለሆነ ማንኛውም ነገር ጠላት ስለሆነ፣ ዘወትር በተጠንቀቅ መሆን አለባችሁ፡፡ በሚከተለው ቃሉ ኢየሱስ ይህን አመልክቷል፤

ከዓለም ብትሆኑ ኖሮ ዓለም የራሱ እንደ ሆኑት አድርጎ በወደዳችሁ ነበር፤ ከዓለም ለይቼ ስለ መረጥኃችሁ የዓለም አይደላችሁም፤ ዓለም የሚጠላችሁም ለዚህ ነው፡፡ (ዮሐንስ 15፥19)

ዓለም የሚጠላችሁም… የሚለውን ልብ አድርጉ፡፡ ይህን ማድበስበስ አይቻልም፡፡ የዓለም ከሆናችሁ ዓለም የራሱ የሆኑትን ያቅፋል፤ የእግዚአብሔር ከሆናችሁ የዚህ ዓለም ሥርዐት ይቃወማችኃል፤ ይጠላችኃል፡፡

## የጸጋ መሣሪያዎች

ስለዚህ በሚገባ መታጠቅን በተመለከተ አሁን ወደ ሌላው ጠቃሚ ገጽታ መጥተናል፤ ይኸውም፣ በክርስቶስ ኢየሱስ አማካይነት በተሰጠን መሣሪያ እንደሚገባ መጠቀምን ማወቅ ነው፡፡ መሣሪያዎቹ ብርቱ ናቸው፤ መንፈሳዊ ናቸው፤ ምክንያቱም ጳውሎስ፣ ‹‹የምንዋጋበት የጦር መሣሪያ የዚህ ዓለም መሣሪያ አይደለም፤ ይሁን እንጂ፣ ምሽግን ለመደምሰስ የሚችል መለኮታዊ ኃይል ያለው ነው›› ብሏል (2ቆሮንቶስ 10፥4)፡፡

ምሽግ የሚያፈርስ፣ ‹‹መለኮታዊ ኃይል›› ምንድነው? መቼም ይህ፣ እጅግ ድንቅ ከሆነው፣ በዋጋ ከማይገዛውና ለአማኞች ሁሉ በነጻ ከተሰጠው ከእግዚአብሔር ጸጋ በቀር ሌላ ሊሆን አይችልም፡፡ ይህን በመገንዘብ በመጀመሪያው መልእክቱ ጴጥሮስ ይህን ታላቅ እውነት እንዴት እንዳስፋፋው ለመመልከት ወደ ፊት እንግፋ፡፡ እንደዚያ እያደረግን እያለ ጸጋ በሚለው ቃል ምትክ ኃይል ወይም የማብቃት፣ የማስቻል ዐቅም፣ በሚሉ ቃላት መተካት እንችላለን፡፡ እነዚህ ቃሎች በልውውጥ ጥቅም ላይ መዋል የሚችሉ ናቸው፡፡

. . . ሁላችሁም እርስ በርስ በመከባበር ትሕትናን ልበሱ፤ ምክንያቱም፣ ‹‹እግዚአብሔር ትዕቢተኞችን ይቃወማል፤ ለትሑታን ግን ጸጋን (ኃይል) ይሰጣል፡፡›› ስለዚህ እርሱ በወሰነው ጊዜ ከፍ እንዲያደርጋችሁ ከእግዚአብሔር ብርቱ እጅ በታች ራሳችሁን ዝቅ አድርጉ፤ እርሱ ስለ እናንተ ስለሚያስብ የሚያስጨንቃችሁን ሁሉ በእርሱ ላይ ጣሉት፡፡ ራሳችሁን የምትገዙ ሁኑ፤ ንቁም፤ ጠላታችሁ ዲያብሎስ የሚውጠውን በመፈለግ እንደሚያገሣ አንበሳ ወዲያ ወዲህ ይዞራል፡፡ በዓለም ዙሪያ ያሉት ወንድሞቻችሁ ተመሳሳይ መከራ እንደሚቀበሉ ዐውቃችሁ በእምነት ጸንታችሁ ተቃወሙት፡፡ በክርስቶስ ወደ ዘላለም ክብሩ የጠራችሁ የጸጋ ሁሉ (የማብቃት የማስቻል) አምላክ ለጥቂት ጊዜ መከራ ከተቀበላችሁ በኋላ እርሱ ራሱ መልሶ ያበረታችኋል፤ አጽንቶም ያቆማችኋል . . . ይህንን አጭር መልእክት የጻፍሁላችሁ ልመክራችሁና ይህ እውነተኛ የእግዚአብሔር ጸጋ (ኃይል) መሆኑን ልመሰክርላችሁ ብዬ ነው፡፡ በዚህ ጸጋ ጸንታችሁ ቁሙ፡፡ (1ጴጥሮስ 5፥5-12)፡፡

እነዚህን ጥልቅ የጴጥሮስ ቃሎች እጥርጥር አድርጌ ቶሎ ቶሎ እንዳቀርብ ፍቀዱልኝ፤ ከዚያ በጥቂት በጥቂቱ መልእክቱን እያዳበርሁ እሄዳለሁ፡፡ የዚህ መልእክት ዐቢይ ሐሳብ የእግዚአብሔር ጸጋ ነው፡፡ ጴጥሮስ እርስ በርሳችን እንድንከባበር በመምከር ይጀምራል፡ በሌላ አባባል ይህ፣ ‹‹በአንድ ዐይነት ተልዕኮ ሥር ሁኑ›› የማለት ያህል ነው፡፡ ከዚያም እግዚአብሔር ለትሑታን ጸጋውን ይሰጣል ይላል፤ በራሳችን ብርታት ሳይሆን በእርሱ ጸጋ (ኃይል) የሚያስፈልገን እንደሚሟላ ተስፋ ስናደርግ ትሕትናችንን እያሳየን ነው፡፡

ጴጥሮስ እየተናገረ ያለው ስለ ምን ዐይነት ጭንቀት ነው? የሚያስፈልጉንን ነገሮች፣ ኃላፊነቶቻችንን፣ ችግሮቻችንን ወይም የተለያዩ ፍላጐታችንን የሚመለከቱ የሕይወት ጉዳዮች ናቸው፡፡ አንዳንድ የሚያሳስቡን ነገሮች ጊዜያዊ ሊሆኑ ይችላሉ፤ ከሁሉም በላይ ደግሞ ዘላለማዊ ሊሆኑ ይችላሉ፤ የመንግሥቱን ሙላት መለማመድና በእኛ ተፅዕኖ ሥር ላሉ ሌሎችም መትረፍ መቻልን የሚመለከቱ ሊሆኑ ይችላሉ፡፡ ይህን የጸጋ ተልዕኮ ለመፈጸም በምናደርገው ጥረት፣ ከዋናው ጠላታችን፣ ከዲያብሎስና ከሰራዊቱ ተቃውሞ ሊገጥመን ይችላል፡፡ እንዲያውም ሊውጠን ይችላል፤ ያ ግን የእግዚአብሔር ዕቅድ አይደለም፡፡ ስለዚህ በማንኛውም ሁኔታ ረጋ ያለ አእምሮ ሊኖረን ይገባል፤ የእግዚአብሔርን ኪዳን ተስፋ በሚገባ መረዳትና በጸሎትም መትጋት አለብን፡፡ እንዲህ ከሆነ የመንግሥቱን ዓላማ ለማራመድ

ሁሌም ዝግጁ መሆንና ወጤት ባለው ሁኔታ ዋናው ጠላታችንን መቃወም እንችላለን፡፡

በዚህ ውጊያ ብቻችንን አይደለንም፤ ተመሳሳይ ዐይነት የጸጋ ተልዕኮ ያላቸው ወንድሞቻችንና እኅቶቻችን በመላው ዓለም የውጊያው ተሳታፊዎች ናቸው፡፡ የዚህ ውጊያ መልካም ነገሩ፣ ብስለትና ብርታት የሚሰጥ መሆኑ ነው፡፡ ከእያንዳንዱ ድል በኃላ፣ በክርስቶስ ከፍ ያለ ሥልጣን ወዳለበት ደረጃ እናድጋለን፡፡

ጴጥሮስ ምንባቡን የሚያበቃው፣ ይህ፣ (ዓላማው) እውነተኛ የእግዚአብሔር ጸጋ ነው በሚል ሐሳብን በሚያነቃቃ ቃል ነው፡፡ ከሁለት ሺህ ዓመት በፊት እውነተኛ ጸጋ ብሎ እንዲጽፍ የእግዚአብሔር መንፈስ ጴጥሮስን ማነሣሣቱ አይገርምም? ይህ በአጋጣሚ አይደለም፤ በኃለኛው ዘመን የእግዚአብሔር ጸጋ፣ ኃጢአትን ወደ ማስተሰረያና የመንግሥት ሰማይ መግቢያ ቲኬት ወደ መሆን ደረጃ (ሌላው ቢቀር በምዕራባውን አስተሳሰብ) ዝቅ እንደሚል መንፈስ ቅዱስ አስቀድሞ አውቆ ነበር፡፡ እውነተኛ የእግዚአብሔር ጸጋ እነዚህንም ይጨምራል፤ ይሁን እንጂ ከዚያም በላይ፣ ፊት ለፊታችን ላለው ተልዕኮ፣ ተፈጥሮአዊ ችሎታችንን አልፈን መሄድ የምንችልበትን ዐቅም ይሰጠናል፡፡ የዚህ ተልዕኮ ዋነኛ ገጽታ እግዚአብሔርን ለማክበርና መንግሥቱን ለማስፋት ሲባል ራሳችንን እንድንለይ ነው፡፡

እንግዲህ ይህን ግንዛቤ በመያዝ፣ ብዙ አማኞች ደምቀው ማብራት ያልቻሉበትን ምክንያት መረዳት እንችላለን፡፡ ራስን መለየት የሚመጣው በተፋፋመ ውጊያ ውስጥ ነው፤ ብዙዎቻችን ግን በውጊያው ውስጥ መሳተፍ አንፈልግም፡፡ እንደ እውነቱ ከሆነ፣ ዓለምን ወደ ኢየሱስ ክርስቶስ ለማምጣት የምናደርገውን ጥረት ጠላት ተኝቶ አያይም፡፡ ተልዕኮአችንን አጥብቆ ይቃወማል፤ እኛም ጸንተን በመቆም እርሱን መቃወምና እግዚአብሔር የሰጠንን ግብ መፈጸም አለብን፡፡ ቀደም ሲል ያየነው ጥቅስ፣ ‹‹ይህ እውነተኛ የእግዚአብሔር ጸጋ ነው. . . በዚህ ጸጋ ጸንታችሁ ቁሙ›› ይላል፡፡ ይህን ካነበብን በኋላ ጳውሎስ ለጢሞቴዎስ ይበልጥ ጠንከር ያለ ቃል እንደ ጻፈለት እናያለን፡፡

እንግዲህ ልጄ ሆይ፣ አንተ በክርስቶስ ኢየሱስ ጸጋ በርታ . . . እንደ ክርስቶስ ኢየሱስ በጐ ወታደር ከእኛ ጋር መከራን ተቀበል፡፡ (2 ጢሞቴዎስ 2፥1፣ 3)

የታዘብኩት ብዙዎቻችን በጸጋ መሣሪያ እየተጠቀምን አለመሆኑን ነው፡፡

ጢሞቴዎስ አካላዊ፣ ማኅበረ ሰባዊ፣ ስሜታዊ ወይም አእምሮአዊ ብርታት እንዲኖረው አልተነገረውም፡፡ በጸጋ እንዲበረታ ነው የተነገረው፡፡ ጸጋ የጀመርነውን በሚገባ ለመፈጸም የሚያስችለን መሣሪያ ነው፡፡ ከሃያ አምስት ዓመት በላይ በአገልግሎት ካሳለፍኩ በኋላ የታዘብኩት ብዙዎቻችን በጸጋ መሣሪያ እየተጠቀምን አለመሆኑን ነው፡፡ ቀደም ሲል እንደ ተመለከትነው 98% ክርስቲያኖች ይህን በነጻ የሚገኝ ብርቱ መሣሪያ በሚገባ አልተረዱም፡፡ ብዙዎቻችንም በእጃችን ያለውን ነገር ገና አላወቅንም፡፡

ወደ ሁለተኛው ጢሞቴዎስ ምዕራፍ 2 ከመምጣቱ ቀደም ሲል ጳውሎስ ወጣቱ የእግዚአብሔር ሰው ከተቃውሞና ከገጠመው ስደት ለመሸሽ መፈለጉን በተመለከተ እርምት አድርጎ ነበር፡፡ መረዳት እንደሚቻለው ወጣቱ ጢሞቴዎስ በጠላቶቹ ተደናግጦ ነበር፤ ጳውሎስ እንደ ነገረው በጽናት እየተቃወመና እየተዋጋ አልነበረም፡፡ እግዚአብሔር የፍርሃትን መንፈስ እንዳልሰጠው፤ ይልቁንም እርሱ የሰጠው የኃይልን፣ የፍቅርንና ራስን የመግዛትን መንፈስ እንደ ሆነ ጳውሎስ ለጢሞቴዎስ ያሳስበዋል፡፡ አማኞች ሁሉ እንዳላቸው፣ ጢሞቴዎስም ማንኛውንም ተቃውሞ ለማሸነፍ የሚያስፈልገው ነገር ነበረው፤ ስለዚህም ያንን እንዲያነቃቃ፣ በክርስቶስ ባለው ጸጋም እንዲበረታ፣ ጳውሎስ ይመክረዋል (2 ጢሞቴዎስ 1፥6-7፤2፥1 ይመ)፡፡

ወደ ተጠራንበት ከፍ ያለ ደረጃ መድረስ፣ መናፈሻ ውስጥ ወዲያ ወዲህ መንሸራሸር አይደለም፡፡ በእግራችን አውራ ጣቶች ቆመን ትልቅነት ላይ መድረስ፣ ወይም ልዩ በሚያደርገን ሕይወት መሳተፍ አንችልም፡፡ ጳውሎስ፣ ‹‹እግዚአብሔር በክርስቶስ ኢየሱስ ወደ ላይ ስለ ጠራኝ፣ ሽልማት ለመቀዳጀት ወደ ግቡ እፈጥናለሁ›› በማለት አጽንዖት ሰጥቶ ይናገራል (ፊልጵስዩስ 3፥14)፡፡ እንግዲህ ወደ ላይ ከፍ ማለት ጳውሎስን እንኳ ይህን ያህል ትጋት ከጠየቀው ተቃውሞ ይኖራል ማለት ነው፡፡

ምዕራፍ አንድ ላይ ያነበብነውን ራእይ አስታውሱ፡፡ ባለ ታሪኩ ማለት ጀልባ ይቀዝፍ የነበረው ሰውየ ከወንዙ ብርቱ ማዕበል በተቃራኒ ወደ ፊት ይገፋ፣ ይገፋ፣ ደጋግሞ ይገፋ ነበር፡፡ በኋላ ግን ዐቅሙ ሁሉ ተሟጠጠ፡፡ ለምን? ብዙ ዓለማቸውን ይቀጩ የነበሩ፣ ይስቁና ይዝናኑ የነበሩ፣ የተሳካለት የሚመስል ሕይወት ይኖሩ የነበሩ፣ ምንም ተቃውሞ የሌለባቸው ሰዎችን የያዙ ጀልባዎች በአጠገቡ ሲንሸራሸሩና አልፎ አልፎ እርሱን እያዩ ሲስቁበት አሁንም በምናቤ ይታየኛል፡፡ የኋላ ኋላ ይህ እውነት ያልሆነ፣ ግን እውነት

መስሎ ወደሚታይ ነገር አደረሰው፡፡ እንደ ማንኛውም፣ ‹‹ክርስቲያን›› የተመቻቸ ሕይወት ለመኖር ወሰነ፡፡ በጣም የሚገርመው ደግሞ እዚህ ውሳኔ ላይ ሲደረስ የነበረበት ተቃውሞ እየቀነሰ መምጣቱ ነው፡፡ እንዴት ያለ መሳት ነው፡፡

እስቲ አንድ ምሳሌ እንመልከት፡፡ አንድ ከጦር ሜዳ ያፈገፈገ ወታደር፣ ውጊያ መስመር ላይ ያሉ ጓዶቹ ካሉበት ይልቅ፣ በጣም ፀጥተኛና ዘና ያለ ሕይወት ይኖራል፡፡ በመሠረቱ ውጊያው ገና አላበቃም ነበር፤ ይህ ወታደር ግን ወደ ኃላ ስላፈገፈገ ግጭት ውስጥ አልነበረም፡፡ ጀልባው ውስጥ እንደ ነበረው ሰውዬ ይህ ወታደርም ለጦርነት የተዘጋጀ ይመስላል፤ የደንብ ልብስ ለብሷል፤ ትጥቁን አሳምሯል፤ መትረየስ ይዟል፡፡ ያም ሆኖ ግን ምንም ተቃውሞ አይገጥመውም፡፡

የተጠራነው ክርስቶስን የምንመስል ሆነን ለመታየት ብቻ ሳይሆን፣ መንግሥቱን በማስፋፋትና የዲያብሎስን ሥራ በማፍረስ በእውነት ክርስቶስን እንድንመስል ነው (1 ዮሐንስ 3፥8 ይመ)፡፡ እንደዚያ ማድረግ ደግሞ ተቃቃሞና ዐመፅ ይደርስብናል ማለት ነው፡፡

ችግርና መከራን ለማሸነፍ የሚያስፈልገን የእግዚአብሔር ጸጋ (ኃይል) መሆኑን ማስታወስ ይኖርብናል፡፡ ይሁን እንጂ፣ በእምነት በመጽናት ከጸጋው ጋር መተባበር አለብን፤ የዚያ እምነታችን መገለጫ ደግሞ የምንወስደው ርምጃ ነው፡፡ ጴጥሮስ በባሕሩ ላይ የተራመደ ጊዜ እንግዳና የማይቻል ነገር አድርጎ ነበር፡፡ ኢየሱስ፣ ‹‹ና›› አለው፤ በዚያ ቃል ውስጥ ደግሞ ጴጥሮስ በባሕር ላይ እንዲራመድ የሚያስችል ጸጋ ነበር፡፡ ማመኑን ሲያቋርጥ ግን ጸጋው (ኃይሉ) ደከመ፤ እርሱም መስጠም ጀመረ፡፡ ‹‹ና›› በሚለው የኢየሱስ ቃል ውስጥ ጴጥሮስን ወደ ኢየሱስ ሊያደርሰው የሚችል፣ እንዲያውም እርሱ ቢፈልግ ኖሮ የገሊላ ባሕርን በሙሉ አቋርጦ መሄድ የሚያስችለው በቂ ጸጋ ነበር፡፡ ሆኖም እምነቱ ሲደክም፣ ጸጋው ዐቅም አጣ፡፡ በክርስቶስ ገደብ የሌለው ጸጋ አለን፤ ወደዚያ መግባት የምናገኘው በእምነት ብቻ ነው፤ ‹‹አሁን ወደቆምንበት ጸጋ በእምነት መግባት ችለናል›› (ሮሜ 5፥2)፡፡

ችግሩ ጸጋ መድከሙ ሳይሆን፣ የእኛ እምነት መዛሉ ነው፡፡ ከዚህ የተነሣ ጸጋ ይቋረጣል፡፡ ከዚያም በገዛ ራሳችን ብርታት የምንዋጋበት ሁኔታ ላይ እንሆናለን፡፡ ወደ ቤታችሁ ውሃ ስለሚመጣበት ቧንቧ አስቡ፡፡ ቧንቧው ከተቋረጠ ውሃ ወደ ቤታችሁ መምጣት አይችልም፡፡ እምነት ቧንቧ ሲሆን፣ ጸጋ ደግሞ በቧንቧው የሚመጣው ውሃ ነው፡፡

እንዲህ ያለ ችግር እንዳይኖር ከተፈለገ፣ በእምነት ራሳችንን መገንባት አለብን፡፡ እንዴት? የእግዚአብሔርን ቃል በማጥናት፣ በምስጋና፣ በአምልኮ፣ ስለ ማንነቱና ስለ ጸጋ ስጦታው እግዚአብሔርን በማመስገን፣ በመንፈስ በመጸለይ፡፡ እምነታችንን ለመገንባት እነዚህን ነገሮች የማናደርግ ከሆነ፣ የኃላ ኃላ ማመናችንን ትተን ከእግዚአብሔር ይልቅ በገዛ ራሳችን ብርታት መኖር እንጀምራለን፡፡ ያኔ ዓለምን መግዛት የነበረብንን ሰዎች፣ ዓለም እኛን መግዛት ይጀምራል፡፡

‹‹በጌታችንና በአዳኛችን በኢየሱስ ክርስቶስ ጸጋ. . . እደጉ›› በማለት ጴጥሮስ የሚያበረታታን በዚህ ምክንያት ነው፡ (2 ጴጥሮስ 3፥18)፡፡ በእግዚአብሔር ኃይል የማደግ ኃላፊነት ተሰጥቶናል፡፡ ያን የምናደርገው ደግሞ እምነታችንን በመገንባት ነው፤ ያኔ በእምነት እንጨምራለን፡፡ ጳውሎስ፣ ‹‹ጻድቅ በእምነት ይኖራል ተብሎ እንደ ተጻፈ የእግዚአብሔር ጽድቅ ከእምነት ወደ እምነት በእርሱ ይገለጣል›› ይላል (ሮሜ 1፥17)፡፡ እስቲ በዚህ መልኩ አስቡት፤ እምነታችሁ ባደገ መጠን፣ ‹‹ቧንቧው›› ይሰፋል፤ በዚህም ምክንያት ብዙ ውሃ (ጸጋ) ይኖራችኃል፡፡ ስለዚህም የበለጠ ኃላፊነት ሊሰጣችሁ ይችላል፡፡

እንደ የዕብራውያኑ መልእክት ጸሐፊ እኔም ከልቤ፣

የዛለውን ክንዳችሁንና የደከመውን ጉልበታችሁን አበርቱ!... ለእግራችሁ ቀና መንገድ አብጁ... ከእናንተ ማንም የእግዚአብሔር ጸጋ እንዳይጎድልበት (ዕብራውያን 12፥12-13፣15) በማለት አበረታታችኃለሁ፡፡

ከእግዚአብሔር ጸጋ ወደ ኃላ ማለት፣ ከጠላት ተቃውሞ ማፈግፈግ፣ ገለልተኛ መሆንና ደንታ ቢስ መሆን ማለት ነው፡፡ እጅግ ታላቅ ከሆነ የእግዚአብሔር ጸጋ፣ ከልዕለ ተፈጥሮአዊው ኃይል ወደ ኃላ የሚባለው ለምንድነው? የሚያስችልና ብቁ የሚያደርግ አስደናቂውን ጸጋ ተግባራዊ የማናደርገው ለምንድነው?

ውጊያ ውስጥ ነን፤ ብርቱዎች ሆነን መጨረስ የምንችለው በእምነት ስንጸና ብቻ ነው፡፡ መጽናት ጌታን ደስ ማሰኘትና ለጨለማው መንግሥት እውነተኛ ስጋት መሆን ማለት ነው፡፡ የተጠራነው ለዚህ ነው፤ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስን በማገልገል ፍጻሜያችንም ሆነ አለን የምንለው መብታችን ይኸው ነው፡፡

# 10

# የትሕትና መሣሪያ

*ሁላችሁም እርስ በርስ በመከባበር ትሕትናን ልበሱ፤ ምክንያቱም፣ «እግዚአብሔር ትዕቢተኞችን ይቃወማል፤ ለትሑታን ግን ጸጋን ይሰጣል፡፡» ስለዚህ እርሱ በወሰነው ጊዜ ከፍ እንዲያደርጋችሁ ከእግዚአብሔር ብርቱ እጅ በታች ራሳችሁን ዝቅ አድርጉ፤ እርሱ ስለ እናንተ ስለሚያስብ የሚያስጨንቃችሁን ሁሉ በእርሱ ላይ ጣሉት፡፡*

*1ጴጥሮስ 5፥5-7*

እርስ በርስ ተከባበሩ... ትሕትናን ልበሱ... ራሳችሁን ዝቅ አድርጉ፡፡››

ጴጥሮስ ከላይ የተናገራቸው ቃሎች ውጤታማ ሕይወት ለመኖርና በማንኛውም የሕይወት ገጽታ የተጀመረውን እንደሚገባ ለመጨረስ ወሳኝ ናቸው፡፡ ሐዋርያው የሚጀምረው፣ ‹‹እርስ በርስ ተከባበሩ›› በሚል ትእዛዝ ነው፡፡ በዚህ ዐውድ መሠረት መከባበር ወይም አንዳችን ለሌላው መገዛት፣ ‹‹በአንድ ዐይነት ተልዕኮ ሥር መተባበር›› ማለት ነው፡፡ በስፋት የሚለያይ ሰብዕና፣ ብርታትና ፍላጎት ያለን እንደ መሆናችን መጠን ይህን ማድረግ እንዴት ይቻላል? ትሕትናን በመልበስ፡፡ እግዚአብሔር ትዕቢተኛን ይቃወማል፤ እኛ ደግሞ እግዚአብሔር እንዲቃወመን አንፈልግም! በሌላ በኩል ደግሞ ለትሑታን ጸጋን (ኃይል) ይሰጣል፡፡

ስለዚህ ጥያቄው ትዕቢተኛ ማን ነው? ትሑቱስ ማነው? የሚል ነው፡፡

## ትሑታን የእግዚአብሔርን ጸጋ ይቀበላሉ

በእውነት ትሑታን የሆኑ ክርስቲያኖች በሚያስቡት፣ ምክንያት ብለው በያዙት፣ በሚሰማቸው ስሜትና ባላቸው ፍላጎት ላይ የእግዚአብሔርን ቃል ያምናሉ፤ ለቃሉ ይታዘዛሉ፡፡ ከዚህም የተነሣ ከራሳቸው ይልቅ በፍጹም ልባቸው በእግዚአብሔር ችሎታ ይተማመናሉ፡፡ የራሳቸውን ወይም የሌላውን ሳይሆን፣ የእርሱን ፈቃድ ይፈልጋሉ፡፡ እነዚህ ወገኖች የእርሱን ሥራ በማከናወን ላይ ናቸው፡፡ መጽሐፍ ቅዱስ፣ ‹‹እነሆ እርሱ ታብዮአል፤ ምኞቱ ቀና አይደለም፤ ጻድቅ ግን በእምነቱ ይኖራል›› ይለናል (ዕንባቆም 2፥4)፡፡

ዕንባቆም 2፥4 ትዕቢትና እምነት በጣም የሚቃረኑ መሆናቸውን ያመለክታል፡፡ ይህን ጥቅስ፣ ‹‹እነሆ ትሑት ያልሆነ ሰው፤ ምኞቱ ቀና አይደለም፤ ጻድቅ ግን በእምነት ይኖራል›› ብሎ ማንበብ ይቻላል፡፡ ከዚህ እንደምንመለከተው ትሕትናና እምነት አብረው ይሄዳሉ፡፡ በተመሳሳይ መንገድ ትዕቢትና አለማመንም አብረው ይሄዳሉ፡፡ እግዚአብሔርን አለማመን ከእርሱ የተሻለ እናውቃለን ማለትና ከእርሱ ይልቅ በራሳችን አመለካከት መተማመን ነው፡፡ አለማመን ሌላ ነገር ሳይሆን፣ ራሱን የሸፋፈነ ትዕቢት ነው፡፡

እስራኤል ከግብፅ ከወጡ በኋላ የነበረውን አንድ ዓመት እንደ ምሳሌ እንድጠቀም ፍቀዱልኝ፤ እግዚአብሔር ሙሴን፣ ‹‹ለእስራኤላውያን የምሰጠውን የከነዓንን ምድር እንዲሰልሉ ጥቂት ሰዎች ላክ›› በማለት አዝዞት ነበር (ዘኍልቁ 13፥2)፡፡ እንደ ሁልጊዜው ሁሉ፤ እዚህም ላይ የእግዚአብሔር ትእዛዝ ግልጽና ቀጥ ያለ ነበር፡፡

ስለዚህም ሙሴ ከእያንዳንዱ ነገድ አንድ አንድ ሰው፣ ዐሥራ ሁለት መሪዎች ሰደደ፡፡ ይሁን እንጂ፣ ዐሥሩ በጣም፣ ‹‹ትሑታን›› ነበሩ፤ ሁለቱ ግን በጣም ‹‹ትዕቢተኞች›› ነበሩ፡፡ (መቼም ታሪኩን የምታውቁ ከሆነ፣ በተቃራኒው እየተናገርኩ እንደ ሆነ ይገባችኃል፤ ያን የማደርገው ትኩረት ለመሳብ ነው፡፡)

ዐርባ ቀን በተስፋው ምድር ከቆዩ በኋላ ሰላዮቹ ተመለሱ፡፡ በመጀመሪያ ዐሥሩ፣ ‹‹ትሑታን›› – ‹‹ምድሪቱን ሁሉ ሰለልን፤ ወተትና ማር የምታፈስስ በጣም ለም ምድር ናት፡፡ እስቲ ይህን ያመጣነውን ፍሬ ተመልከቱ፡፡ ይሁን እንጂ፣ እዚያ ግዙፍና ኃይለኞች ሰዎች አሉ፡፡ ከፍ ያለ ችሎታ ያላቸው ጦረኞች ናቸው፤ እኛ ካለን የበላለጡ መሣሪያዎችም አላቸው፤ እኛ'ኮ ትናንትና ነጻ የወጣን ደካማ ባሪያዎች ነን፡፡ ለሚስቶቻችንና ለልጆቻችን ማሰብ አለብን! ራሳችንንም ሆነ የእኛ የሆኑትን ከወንዙ ወዲያ ማዶ ላሉ ሰዎች ጭካኔ፣ ስቃይ፣ አስገድዶ መድፈር፣ ሌላው ቀርቶ ግድያ እንኳ አሳልፈን የምንሰጠው ለምንድነው? ማመዛዘን የምንችል አባቶችና ባሎች መሆን አለብን፤ ሪፖርታችንም እውነታን ያገናዘበ መሆን አለበት፡፡ ያቺን ምድር በፍጹም መያዝ አንችልም›› በማለት ተናገሩ፡፡

ምንም እንኳ ሕዝቡ ምድሪቱን የራሳቸው ማድረግ ቢፈልጉም፣ መጀመሪያ በሕይወት መኖርና ደኅና መሆን ያስፈልጋል፡፡ ስለዚህም የእነዚህን ሰዎች አስተዋይነትና ትሕትና በማድነቅ አጨበጨቡላቸው፡፡ የዐሥሩን ሰላዮች ሪፖርት የሰሙ አብዛኞቹ አባቶችና እናቶች ያን ያህል ትሑት በመሆናቸው ሳያመሰግኗቸው እንዳልቀሩ አስባለሁ፡፡ እርሰ በርሳቸው፣

‹‹እነዚህ ሰዎች ከእኛ ቀድመው ወደ ቦታው በመሄዳቸው ደስ ይለናል፡፡ እንዴት ያሉ ታላላቅ መሪዎች ናቸው? የሐሰት ሪፖርት በማቅረብ እኛን ለአደጋ ማጋለጥ አልፈለጉም፡፡ እነርሱ አስተዋይ ባይሆኑ ኖሮ ምን ይደርስብን ነበር?›› በመባባል ራሳቸውን አጽናኑ፡፡

ከዚያም ሁለቱ፣ ‹‹ትዕቢተኞች›› – መሪዎች ካሌብና ኢያሱ፣ ‹‹እስቲ፣ አንድ አፍታ ታገሡ! ለመሆኑ እዚህ ምንድነው የምናደርገው? አሁኑኑ ሄደን ምድሪቱን መውረስ አለብን! ደግሞ ያን ማድረግ እንችላለን! እግዚአብሔር አምላክ ቃል ገብቶልናል፡፡ ቃሉ ዋስትናችን ነው! እነዚያን ሰዎች ማጥፋት እንችላለን፡፡ ብቻ ቶሎ ብለን ርምጃ እንውሰድ!›› በማለት ጣልቃ በመግባት ተናገሩ፡፡

ሰው ሁሉ በሰማው ነገር ግራ ተጋባ፡፡ በጥርጣሬ እርስ በርስ ተያየ፡፡ ለካሌብና ለኢያሱ ችኮላና ሥርዐት ያልተከተለ ምክር ሌሎቹ ዐሥር ሰላዮች የሰጡትን ምላሽ መገመት ትችላላችሁ? በበኩሌ፣ ‹‹እናንተ ሁለት ሰዎች ምንድነው የምትሉት? አእምሮአችሁን ሳታችሁ እንዴ? መቼም ሁላችንም አብረን ነው ያየነው – ጥንካሬአቸውን፣ መሣሪያቸውንና የተመሸጉ ከተሞቻቸውን አይተናል፡፡ ግዙፍ ናቸው፤ ልምድ ያላቸው ጦረኞች ናቸው፤ እኛ ግን እፍኝ የማንሞላ ባሪያዎች ነን፡፡ ከእነርሱ ጋር መወዳደር አንችልም! እናንተ ግን ለሚስቶቻችንና ለልጆቻችን ከዚያም በላይ ለመላው ሕዝባችን ደኅንነት አታስቡም፡፡ ሞኞች፣ እብሪተኞችና እውነታን የማታገናዝቡ ናችሁ፡፡ አጉል ጀብደኝነታችሁን አቁሙ!›› የሚል መልስ ሳይሰጧቸው እንዳልቀረ አስባለሁ፡፡

ግራና ቀኙን የሰሙ ሕዝብም፣ ‹‹እነዚያ አስተዋይ ሰዎች፣ በእነዚህ አጉል ሰዎች ክርክር ባለ መሸነፋቸው እግዚአብሔር ይመስገን፡፡ ብዙኀኑ ሰላዮች አስተዋይ በመሆናቸው ዕድለኞች ነን፡፡ ሁሉም እንደ ካሌብና እንደ ኢያሱ ትዕቢተኛና እብሪተኛ ቢሆኑ ኖሮ ምን ላይ እንወድቅ እንደ ነበር ማሰብ አትችሉም?›› ሳይሉ አልቀሩም፡፡

ሆኖም፣ እንደ ሁሌው ሁሉ፣ የመጨረሻው ቃል የእግዚአብሔር ነው፡፡ ‹‹ይህ ሕዝብ እስከ መቼ ይንቀኛል?›› በማለት ለሙሴ ተናገረ፡፡ ‹‹የማያምንብኝስ እስከ መቼ ነው?›› (ዘኁልቁ 14፥11)፡፡ ብዙኀኑ በነበራቸው ዝንባሌ እግዚአብሔር ደስ አልተሰኘም፡፡ እነርሱ ትሕትና ያሉት በፍጹም ትሕትና አልነበረም፡፡ እውነቱን ለመናገር እምነት አልነበራቸውም፡፡ አለማመናቸው ደግሞ ትዕቢት ነበር፡፡ ስሌቶቻቸውን ሁሉ የመሠረቱት በራሳቸው ጥበብ፣ ችሎታና ብርታት ላይ ነበር፡፡

ከብዙ ጊዜ በኃላ ከብሉይ ኪዳን እንደምንመለከተው እግዚአብሔር፣ ‹‹በሰው የሚታመን፣ በሥጋ ለባሽ የሚመካ የተረገመ ይሁን. . . ነገር ግን በእግዚአብሔር የሚታመን፣ መታመኛውም እግዚአብሔር የሆነ ሰው ቡሩክ ነው›› ብሏል (ኤርምያስ 17፥5፣7)፡፡ ዐሥሩ ሰላዮች ያዩት እዚያ የነበሩ ሰዎች ምን ያህል ትልቅ እንደ ነበሩ ነው፤ የፈሪ ዕቅዳቸው መሠረት ያደረጉት የራሳቸውን ብርታት ነበር፡፡ ካሌብና ኢያሱ ግን፣ ከጠላት ጋር ሲወዳደር እግዚአብሔር ምን ያህል ትልቅ መሆኑን አይተዋል፤ ተስፋቸውን ሁሉ የመሠረቱት የእግዚአብሔር ጸጋ ላይ ነበር፡፡ እነዚህ ሁለቱ ማለት፣ ካሌብና ኢያሱ ተባረኩ፤ ዐሥሩ ሰላዮችና ሌሎች ያላመኑ ሰዎች ግን ተረገሙ፡፡

እንግዲህ ከዚህ አንጻር በእውነት ትሑታን የነበሩት የትኞቹ ናቸው? በእውነት ትዕቢተኛ የነበሩትስ የትኞቹ ናቸው? በእግዚአብሔር ዐይን ዐሥሩ ትዕቢተኞች ነበሩ፤ ሁለቱ ግን ትሑታን ነበሩ፡፡

ማመን እውነተኛ ትሕትና ይጠይቃል፤ ምክንያቱም ትሑት ስንሆን በራሳችን ችሎታ ሳይሆን፣ በማንኛውም ሁኔታ ውስጥ ሊያሳልፈን በሚችል በእግዚአብሔር ችሎታ (ጸጋ) እንተማመናለን፡፡ ዐሥሩ ሰላዮች በትሕትና በእግዚአብሔር ተማምነው ቢሆን ኖሮ፣ ሄደው ምድሪቱን ይይዙ ነበር፡፡ ውሱን ከሆነ ብርታታቸውና ሰብዓዊ ምክንያታቸው ይልቅ ለእግዚአብሔር ቃል ይገዙ ነበር፤ በዚህም ምክንያት እርስ በርስ አንዳቸው ለሌላው ይገዙ ነበር – በአንድ ዓላማ በታች ይሆኑ ነበር፡፡

ካሌብና ኢያሱ እየተዋጉ በነበሩ ጊዜ ዳር ሆነው የሚመለከቱ ሰዎች – የአብርሃም ዘሮች በገዛ ራሳቸው ብርታት እየተዋጉ ነው ይሉ ይሆናል፤ እንደ እውነቱ ከሆነ ግን፣ በእነርሱ ውስጥ ይሠራ የነበረው የእግዚአብሔር ጸጋ – ልዕለ ተፈጥሮአዊ ኃይል ነበር፡፡ የእግዚአብሔር የማስቻልና ብቁ የማድረግ ዐቅም በእኛ ውስጥ ነገሮችን ሲያከናውን በገዛ ራሳችን ኃይል ያደረግነው የሚመስለን ጊዜ አለ፡፡ ሌላ ጊዜ ግን ያንን ያደረገ በትክክል የእግዚአብሔር ችሎታ መሆኑ ግልጽ ይሆንልናል፡፡ ይሁን እንጂ፣ ዳር ለቆሙ ሰዎች ምንም መስሎ ቢታያቸውም፣ እኛ በፍጹም ልባችን በእርሱ ኃይል እንደገፋለን፤ እምነታችንን በቃሉ ላይ በማድረግም ወደ ፊት እንገሠግሣለን፡፡

የተወደዳችሁ አንባቢዎች፣ ያ ጽናት ያለው እምነት ነው፡፡ ሆኖም፣ በእግዚአብሔርም ፊት ሆነ እርስ በርሳችን ትሑታን በመሆን ነው የሚጀምረው፡፡

ትሕትናን መልበስ ከራሳችን ይልቅ የእግዚአብሔርን መሣሪያ መታጠቅ ማለት ነው፡፡ 1ጴጥሮስ 5÷5-6፣ ‹‹ትሕትናን ልበሱ... ከእግዚአብሔር ብርቱ እጅ በታች ራሳችሁን ዝቅ አድርጉ›› በማለት ያዝዛል፡፡ በቅዱሳት መጻሕፍት መሠረት የእግዚአብሔር እጅ ችሎታውን፣ ኃይሉን፣ ብርታቱን ዐቅሙን፣ ወይም መሣሪያውን፣ ይወክላል፡፡

ይህ በተግባር የሚገለጠው እንዴት ነው? ከእግዚአብሔር ብርቱ እጅ በታች ራሳችንን ዝቅ ማድረግ አለብን፡፡ የሰው ሐሳብና ልምምድ፣ ከእግዚአብሔር ቃል በላይ ከፍ እንዳይል ማድረግ አለብን፡፡ ይልቁንም ከተፈጥሮአዊ ምክንያታዊነታችን በተለየ ሁኔታ እንኳ ቢሆን፣ በእግዚአብሔር ማመንና የእርሱ ቃል ርምጃዎቻችን እንዲመራ መፍቀድ አለብን፡፡

አራት መቶ ዓመት በግብፅ መገዛታቸው፣ የእስራኤል ልጆችን ከእነርሱ የበለጠ መሣሪያ ከታጠቁት ኃይሎች ራሳቸውን መከላከል እንደማይችሉ አስተምሯቸው ነበር፡፡ ግብፅ በጭቆና ገዝታቸው ነበር፡፡ ራሳቸውን ነጻ ለማውጣት ምንም ማድረግ የሚችሉት አልነበረም፤ ያ የእግዚአብሔር ድርሻ ነበር፡፡ እርሱም ብርቱ በሆነ እጁ በክብር አዳናቸው፡፡ ሙሴ ያንን ሲያስታውስ፣ ‹‹እግዚአብሔር በኃያል ክንዱ ከግብፅ አውጥቶአችኋል›› ይላል (ዘፀአት 13÷9)፡፡ ይሁን እንጂ፣ ‹‹ያደረገውን ወዲያውኑ ረሱ›› ተብሎም ተነግሮአል (መዝሙር 106÷13)፡፡ ካዳናቸው ከእግዚአብሔር እጅ ይልቅ፣ ከረጅም ዘመን የባርነት ልምምዳቸው ጋር ተጣበቁ፡፡ ግብፃውያንን የመታ ኃያል እጅ፣ ከግብፃውያን ሰራዊት በጣም ያነሱ ከነዓናውያንንም መምታት ይችል ነበር፡፡

ሆኖም፣ በእምነተ ቢስነታቸው እስራኤላውያን ላይ ከመፍረዳችን በፊት እኔ እናንተ ራሳችንን ማየት አለብን፡፡ እኛስ እነርሱ ያደረጉትን ስንቴ ነበር ያደረግነው? ወደ እግዚአብሔር ቤተ ሰብ ከመምጣታችን በፊት ከጨቋኙ የሰይጣን አገዛዝ ሥር ነበርን፡፡ የእርሱ ባሕርይ ነበረን፤ ከእርሱ የምናመልጥበት ተስፋም አልነበረም፡፡ ሆኖም፣ የእግዚአብሔር ኃያል ክንድ፣ ‹‹ከጨለማ ግዛት ታደገን፤ ወደሚወደው ልጁ መንግሥትም አሻገረን›› (ቈላስይስ 1÷13)፡፡ እንግዲህ ይህን ታላቅ ነገር ካደረገ፣ በሕይወታችን የሚገጥሙንን ከዚያ ያነሱ ውስብስብና አስቸጋሪ ነገሮችን እንዴት ማስወገድ አይችልም? ከበሽታ ወይም ከሕመም መፈወስ፣ ማንኛውንም ጉድለታችንን መሙላት፣ ከሌሎች የምንለይበትንና፣ ‹‹የማይቻሉ›› ከሚመስሉ ሁኔታዎች በአሸናፊነት የምንወጣበትን ጥበብና ኃይል ይሰጠናል፡፡ ‹‹ያደረገውን ወዲያውኑ ረሱ›› እንደ ተባለው የእስራኤልን ውድቀት አንድገም፡፡ ካሌብና ኢያሱ እንዳደረጉት እኔና እናንተ ትሕትናን እንልበስ፡፡

## ትሕትናን ማሳሳት

ብዙ ጊዜ ትሕትና ደካማነት፣ ቅልስልስነትና ወኔ ቢስነት ተደርጐ ይወሰዳል፡፡ እንደ እውነቱ ከሆነ ግን ከዚህ በጣም የተለየ ነው፡፡ ብዙ ጊዜ መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ፣ በእውነት ትሑት የሆኑ ሰዎች እንደ ትዕቢተኛና እብሪተኛ ተቆጥረው ነበር፡፡ ለምሳሌ ዳዊትን ውሰዱ፡፡ አባቱ ባዘዘው መሠረት፣ ከፍልስጥኤማውያን ጋር ለመዋጋት ጦር ሜዳ የነበሩ ታላላቅ ወንድሞቹን ለመጠየቅ ሄዶ ነበር፡፡ ጦርነቱ ቦታ ሲደርስ ወንድሞቹን ጨምሮ ወታደሮቹ ሁሉ በፍርሃት ሲርበደበዱ አገኛቸው፡፡ ግዙፉ ፍልስጥኤማዊ የጐልያድን ቁመት፣ ጥንካሬ፣ መሣሪያ አይተው፣ ስለ እርሱ የተወራውን ሰምተው፣ ተደናግጠው ነበር፡፡ የፍልስጥኤማዊው ጀግና የጐልያድ ዛቻና ማስፈራራት አርባ ቀን ሙሉ ቀጥሎ እንደ ነበር ሲሰማ፣ ‹‹የሕያው እግዚአብሔርን ሰራዊት ይገዳደር ዘንድ ይህ ያልተገረዘ ፍልስጥኤማዊ እርሱ ማን ነው?›› በማለት ጠየቀ (1ሳሙኤል 17፥26)፡፡

የዳዊት አነጋገር ታላቅ ወንድሙ ኤልያብን በጣም አስቆጣው፡፡ ኤልያብ ምን ሊያስብ እንደሚችል ትገምታላችሁ? ‹‹የእኔ ታናሽ ወንድም እኮ ልጅነት ብቻ ሳይሆን አጉል ጀብደኝነትም አለበት›› በማለት አስቦ ይሆናል፡፡ ከዚያም አልፎ፣ ‹‹ትዕቢትህንና የልብህን ክፋት ዐውቃለሁ›› በማለት ነበር ለዳዊት የነገረው (ቁጥር 28)፡፡ ወንድሞቹ እንደ ዐይን አውጣ፣ እብሪተኛና ትዕቢተኛ ነበር ዳዊትን የቆጠሩት፡፡

ግን እውነት እንነጋገር ከተባለ፣ ትዕቢተኛው ማን ነበር? ከዚህ ቀደም ሲል ከነበረው ምዕራፍ እንደምንመለከተው የሚቀጥለውን ንጉሥ ለመቀባት ሳሙኤል ወደ እሴይ ቤት መጥቶ ነበር፡፡ ከእሴይ ልጆች ሁሉ ታላቅ ስለ ነበረ፣ ረጅምና ጠንካራ መስሎ ይታይ ስለ ነበር፣ ሳሙኤልም ሆነ እሴይ ኤልያብ እንደሚመረጥ ጠብቀው ነበር፡፡ እግዚአብሔር ግን በግልጽ፣ ‹‹እኔ ንቄዋለሁ›› ነበር ያለው (1ሳሙኤል 16፥7)፡፡

ለመሆኑ፣ እግዚአብሔር ኤልያብን የናቀው ለምን ነበር? ዳዊትን የከሰሰበት ትዕቢት ኤልያብም ውስጥ ስለ ነበር ይሆን? በኃላ ግን እንደ ልቡ የሆነ ሰው መሆኑን በመናገር፣ እግዚአብሔር የዳዊትን ትሕትና መሰከረለት (ሐዋርያት ሥራ 13፥22 ይመ)፡፡ የዳዊት ሕይወት ትሕትና የተሞላ ነበር፤ ይህ ታላቅ መሪ ደካማ፣ ቅልስልስና ወኔ ቢስ እንዳልነበር ሁላችንም እናውቃለን፡፡ ‹‹እግዚአብሔር ከእኔ ጋር ነው አልፈራም፤ ሰው ምን ሊያደርገኝ ይችላል?›› ብሎ የጻፈ እርሱ ነበር (መዝሙር 118፥6)፡፡

ወደ ጦር ሜዳው ስንመለስ ዳዊት፣ የኤልያብን ንቀት ችላ በማለት፣ የግዙፉ ሰው ራስ እንደሚቆረጥ በልበ ሙሉነት ተናገረ፡፡ ከዚያም ወደ ጠላት ሰፈር ሮጦ በመሄድ ከወንጭፉ በተወረወረ አንድ ድንጋይ ብቻ ጐልያድን ገደለ፤ እንደ ተናገረውም ራሱን ቆረጠ፡፡

የዳዊት ታላላቅ ወንድሞች ነገሩን ያሰሉት፣ ዐሥሩ ሰላዮች እንዳደረጉት በራሳቸው ዐቅም ላይ በመመሥረት ነበር፡፡ በሌላ በኩል ዳዊት የጦር ሜዳውን ያየው ከእግዚአብሔር ብርታትና ኃያል እጅ አንጻር ነበር፡፡ ዳዊት ትሕትናን ለበሰ፡፡ ንጉሥ ሳኦል ለዳዊት የራሱን መሣሪያ ሰጥቶት ነበር፤ ትንሹ ልጅ ግን አልተቀበለውም፤ ይልቁን እርሱ በእግዚአብሔር መሣሪያ ተማመነ፡፡ ያኔም ቢሆን እንደ ካሌብና እንደ ኢያሱ ሁሉ በራሳቸው ብርታት በተማመኑ ሰዎች እንደ እብሪተኛና ትዕቢተኛ ነበር የተቆጠረው፡፡

እኛ ለትሕትና ያለንን ትክክለኛ አመለካከት ለማጣመም ጠላት ጠንክሮ እንደሚሠራ አምናለሁ፡፡ ትሕትናን እንደ ደካማነትና ቅልስልስነት በመመልከት፣ ብዙ አስተዋይ የሚባሉ ክርስቲያኖች ከማያምን ዓለም ጋር ይተባበራሉ፡፡ ይህ ግን ከቃሉ እውነተኛ ትርጉም በጣም ይርቃል፡፡ እስቲ ሌሎች ሁለት የመጽሐፍ ቅዱስ ምሳሌዎች – ሙሴና ኢየሱስን ተመልከቱ፡፡

ሙሴን በተመለከተ ከኦሪት ዘኁልቁ፣ ‹‹ሙሴ በምድር ካሉት ሰዎች ሁሉ ይልቅ ትሑት ሰው ነበር›› የሚል እናነባለን (ዘኁልቁ 12፥3)፡፡

በጣም የሚገርም ቃል ነው! እኛን በተመለከተ በዚህ መልኩ ቢነገር እኔና እናንተ በጣም ደስ አይለንም? በመሠረቱ፣ እኔና እናንተ ስለ ራሳችን እንደዚያ መናገር አንደፍርም፤ ምክንያቱም ምን ያህል ትሑት እንደሆነ ለሰዎች የሚናገር እብሪተኛና ስለ ራሱ የተጋነነ አመለካከት ያለው ሰው ብቻ ነው የሚል አስተሳሰብ አለ፡፡ ግን ዘኁልቁን የጻፈው ማን ነበር? - ሙሴ ራሱ ነው! ይህ አስደናቂ የእግዚአብሔር ሰው ራሱን በምድር ካሉት ሰዎች ሁሉ ይልቅ ትሑት እንደ ነበር ገለጸ፡፡

እንዴት ሊሆን ይችላል? አንድ አገልጋይ፣ የክርስቲያኖች ኮንፈረንስ ፊት ቆሞ፣ ‹‹ሁላችሁም በደንብ ስሙኝ፤ እኔ በጣም ትሑት ሰው ነኝ፤ እስቲ ስለዚያ ልንገራችሁ›› በማለት ቢናገር ምን እንደሚሆን አስቡ፡፡ በጣም ይሳቅበታል፤ ያም ብቻ ሳይሆን ከመድረክ እንዲወርድም ይደረግ ነበር፡፡

ግን እስቲ ኢየሱስ ስለ ራሱ የተናገረውን ስሙ፤ ‹‹እናንተ ሸክም የከበዳችሁና የደከማችሁ ሁሉ ወደ እኔ ኑ፤ …እኔ በልቤ የዋህና ትሑት ነኝ›› (ማቴዎስ 11፥28-29)፡፡

በሌላ አነጋገር ኢየሱስ፣ ‹‹ስሙ! እኔ ትሑት ነኝ፤ ስለ ትሕትና ላስተምራችሁ እፈልጋለሁ›› እያለ ነበር፡፡ እንደ ሙሴ ሁሉ ኢየሱስም ስለ ራሱ ትሕትና መናገሩ በዛሬው ዓለም በመልካም አይታይም፡፡ ይሁን እንጂ ችግሩ፣ ሙሴም ሆነ ኢየሱስ የተናገሩት ላይ ሳይሆን፣ ትሕትናን በተመለከተ ባለን አስተሳሰብና መረዳት እኛ ከመስመር መውጣታችን ነው፡፡ ትሕትና ማለት ለምንም እንደማይጠቅም አንድ ትል መኖር ነው ብለን ስለምናስብና ስለ አለመቻላችንና ጉስቁልናችን ብቻ መናገር ስለሚመስለን፣ እውነተኛ ትርጉሙን ስተናል፡፡ ያም ሆኖ ግን እግዚአብሔር ባቀደው መልኩ ትሕትና፣ በጣም ቀና እና ብርቱ ኃይል ያለው ምግባር ነው፡፡ እውነተኛ ትሕትና በፍጹም ልብ ለእግዚአብሔር መታዘዝና በእርሱ መደገፍ ነው፡፡ እውነተኛ ትሕትና በማንኛውም ነገር እግዚአብሔርን የመጀመሪያ፣ ሌሎችን ሁለተኛ፣ ራስን ግን በሦስተኛ ደረጃ ያስቀምጣል፡፡ ትሕትና ከእግዚአብሔር ነጻ ጸጋ ስጦታ የተነሣ፣ በልበ ሙሉነትና በጽናት መኖር እንጂ ከመቅለስለስና ራስን ከማጣጣል ጋር ምንም ግንኙነት የለውም፡፡

## ትሕትና በጽናት እንድንኖር ያደርጋል

ጸንተው የሚኖሩና የክርስትና ሕይወታቸውን በሚገባ የሚፈጽሙ ሰዎች ስለሚቀበሉት ሽልማት የተነጋገርነውን አስታወሳችሁ? ጳውሎስ - ጥበብ ከሚመስል፣ ከዚህ ሽልማት ሊያዘናጋን ከሚሞክር ዐጉል ትሕትና እንድንጠነቀቅ ይመክረናል፣ ‹‹ዐጉል ትሕትናንና የመላእክትን አምልኮ የሚወድ ማንም ሰው እንዳያደናቅፋችሁ ተጠንቀቁ›› (2 ቈላስይስ 2፥18)፡፡ የዐሥሩ የእስራኤል ሰላዮች ታሪክ፣ ዐጉል ትሕትና ምን ያህል እግዚአብሔር ካቀደልን ሽልማት ሊያወጣን እንደሚችል ምሳሌ ሊሆነን ይችላል፡፡

ዐሥሩ ሰላዮች ወደ ተስፋው ምድር ላለ መግባት መከሩ፡፡ ያቀረቡት ምክንያት አሳማኝና ማስተዋል ያለበት ይመስላል፤ ሆኖም መሠረት ያደረገው መልካሙንና ክፉውን የምታሳውቀውን ዛፍ እንጂ፣ የእግዚአብሔርን ተስፋ ቃልና ጥበብ አልነበረም፡፡ ያታለሉት ራሳቸውን ብቻ ሳይሆን ቤተ ሰባቸውንና ሌሎች ሚሊዮኖችንም ጭምር ነበር፤ ስለዚህም ወደ ተስፋው ምድር ሳይገቡ ቀሩ፡፡ ከዐጉል ትሕትና የተነሣ፣ እግዚአብሔር ያዘጋጀላቸውን ፍጻሜ የሚያጡ ሰዎች ዕጣ ፈንታ ይኸው ነው፡፡ በዚያ ትውልድ መካከል ከነበሩ ትልልቅ ሰዎች ወደ አዲሱ ምድር እንዲገቡ እግዚአብሔር የፈቀደላቸው በትሕትና መንፈስ መልካም ሪፖርት ያቀረቡት ካሌብና ኢያሱ ብቻ ነበሩ፡፡ በኢያሱ መሪነት አዲሱ የእስራኤል ትውልድ ከእግዚአብሔር ብርቱ እጅ በታች ትሑት በመሆን በድፍረት ገባ፡፡ በዚህም ምክንያት ማሸነፍ ቻለ፡፡

አንድ ጊዜ አንድ ሰው፣ ‹‹ጆን በጣት ለሚቆጠሩ መሪዎች መስበክ ነው የምትፈልገው ወይስ የተለያየ ታሪክ ላላቸው ሚሊዮኖች? በማለት ጠየቀኝ፡፡

እኔም፣ ‹‹በሚሊዮኖች ለሚቆጠሩት ነው›› አልኩት፡፡

ሰውየውም፣ ‹‹እንግዲያውስ ትክክለኛ ምርጫ አላደረግህም፤ ምክንያቱም ሚሊዮኖች እግዚአብሔር ያዘጋጀላቸውን ፍጻሜ እንዲያጡ ያደረጉ ምድራቱን የሰለሉ ዐሥሩ መሪዎች ናቸው›› አለኝ፡፡

ሁላችንም መሪዎችና ተፅዕኖ ፈጣሪዎች እንድንሆን ተጠርተናል፡፡ ታዲያ፣ እንዴት ነው የምንመራው? ብርቱ ከሆነው የእግዚአብሔር እጅ በታች በመሆን በትሕትና ነው ወይስ በዐጉል ትሕትና በራሳችን ብርታት በመንቀሳቀስ?

በተጨማሪም ጳውሎስ፣ ‹‹ከአሸናፊዎች እንበልጣለን›› ብሏል (ሮሜ 8፥37) ሆኖም፣ ከእግዚአብሔር ቃል ውጪ የሆነው የእኛ የራሳችን ሐሳብ፣ ዕቅድ ወይም መመሪያ፣ ‹‹ከዐጉል ትሕትናና ሰውነትን ከመጨቆን አንጻር በእርግጥ ጥበብ ያለባቸው ይመስላሉ፤ ነገር ግን የሥጋን ልቅነት ለመቆጣጠር አንዳች ፋይዳ የላቸውም›› (ቈላስይስ 2፥23)፡፡

በካሌብና በኢያሱ ትውልድ ውስጥ የነበረ ማንኛውም ሰው አሸናፊ እንዲሆን ተመድቦ ነበር፡፡ ኤልያብና ወንድሞቹ ታናሹ ዳዊት ወደ ቦታው ከመምጣቱ ረጅም ጊዜ በፊት ማሸነፍ ነበረባቸው፡፡ ይሁን እንጂ፣ ዐጉል ትሕትና ብርታታቸውን፣ ተስፋቸውን፣ ፍሬያቸውን በሕይወት የመንገሥ ችሎታቸውን፣ የኃላ ኃላም ዘላለማዊ ሽልማታቸውን ነጠቃቸው፡፡ በዚህም ምክንያት ጳውሎስ ጠንከር አድርጎ፣

> እርስ በርሳችሁ በመስማማት ኑሩ፡፡ ዝቅተኛ ኑሮ ውስጥ ካሉ ጋር አብራችሁ ለመሆን ፍቀዱ እንጂ አትኩራሩ፣ በራሳችሁም አትመኩ - በማለት ይመክረናል (ሮሜ 12፥16)፡፡

ትሑት አእምሮ በራሱ አስተሳሰብ አስተዋይ ላይመስል ይችላል፡፡ አንድ ታዋቂ ዓለም አቀፍ መጽሔት፣ አንድ አወዛጋቢ ጉዳይ ላይ መጣጥፍ እያቀረበ የነበረበትን ጊዜ አስታውሳለሁ፡፡ የመጽሔቱ አዘጋጆች ወደ ቢሮዋችን በመደወል ሐሳቤን እንድሰጥ ጥያቄ አቅርበው ስለ ነበር ረዳቴ ጥያቄውን ለእኔ አቅርባ ነበር፡፡ ‹‹እስቲ ላስብበት›› አልኳት፡፡

በሚቀጥለው ቀን መንፈሴ ውስጥ ሁከት ነበር፤ ምክንያቱ ምን ሊሆን እንደሚችል ማወቅ አልቻልኩም፡፡ ‹‹ችግሩ ምን ይሆን?›› በማለት ራሴን

መጠየቅ ጀመርኩ፡፡ እያወከኝ ያለው ምን እንደ ሆነ ግን መረዳት አልቻልኩም ነበር፡፡ በመጨረሻም ነገሩን በጸሎት ጌታ ፊት አቀረብኩ፤ ከአንድ ወይም ሁለት ቀን በኃላ በድንገት አንድ ነገር ግልጽ ሆነልኝ፡፡ ከሊዛ ጋር እየተነጋገርን እያለ፣ ‹‹መጽሔቱ ያቀረበውን ጥያቄ በተመለከተ ለምን እየታወከሁ እንደ ነበር አሁን ግልጽ ሆኖልኛል፡፡ በጣም ቀላል ነው - ለመሆኑ፣ የራሴን ሐሳብ ለመስጠት እኔ ማን ነኝ? እንደራሴዎች (አምባሳደሮች) የሚሰጡት የራሳቸውን ሐሳብ ነውን?›› አልኩ፡፡

መጽሐፍ ቅዱስ፣ ‹‹እኛ የክርስቶስ እንደራሴዎች (አምባሳደሮች) ነን፤ እግዚአብሔርም በእኛ አማካይነት ጥሪውን ያቀርባል›› ይላል (2ቆሮንቶስ 5፥20)፡፡ የኢትዮጵያ መንግሥት ለሌላ አገር መልእክቱን እንዲያደርስላት አንድ አምባሳደር ቢልክ፣ ያ አምባሳደር የመንግሥትን ሳይሆን የራሱን ሐሳብ ቢሰጥ፣ ትልቅ ችግር ላይ ይወድቃል፡፡ ስለ እግዚአብሔር አብና ስለ ጌታዬ ክርስቶስ ኢየሱስ የምናገር ከሆነ መናገር ያለብኝ ቃሉን ነው፡፡ የራሴን አመለካከት ለመስጠት እኔ ማን ነኝ? የዐሥሩ ሰላዮች ትልቁ ውድቀት ይኸው ነበር፡፡ የራሴን ሐሳብ እንድሰጥ ያ መጽሔት የወንጌል አገልጋይ ወደ ሆንኩት ወደ እኔ መጣ፤ እንደዚያ ማድረግ በዐደራ የተሰጠኝን የእግዚአብሔር ጸጋ መናቅ ነው የሚሆነው፡፡

ይህ አጋጣሚ ከዓመታት በፊት ጸሎት ላይ እያለሁ እግዚአብሔር የተናገረኝን እንዳስታውስ አደረገኝ፡፡ የአገልግሎታችን የመጀመሪያዎቹ አራት ዓመታት በጣም አስቸጋሪ ነበሩ፤ ምድረ በዳ ወይም በረሐ ነበር ማለት እችላለሁ፡፡ እኔና ሊዛ ትንሿ ሆንዳ ሲቪክ መኪናችንን እየነዳን በዩናይትድ ስቴት ምሥራቃዊ አጋማሽ ላይና ታች እንመላለስ ነበር፤ ኃላ ወንበር ላይ ልጆቻችንን አስቀምጠን፣ ባለው ባዶ ቦታ ሻንጣዎቻችንን አጭቀን ነበር የምንመላለሰው፡፡ የአገልግሎት በሮች እንዲከፈቱልን አጥብቀን እንጸልይ ነበር፡፡ አብዛኛውን ስብሰባ የምናደርገው አንድ መቶ ወይም ከዚያ ብዙ ያልበለጡ አባሎች በነበሩባቸው ቤተ ክርስቲያኖች ነበር፤ ቁጥራቸው ሲያድግ ወይም በነበሩበት ማኅበረ ሰብ ይህን ያህል ተፅዕኖ ሲያደርጉ አይታይም ነበር፡፡

ከዚህ አድካሚ አገልግሎት አራት ዓመት በኃላ አንድ ቀን ጠዋት እግዚአብሔር፣ *ጆን ባለፉት አራት ዓመታት ጥቂት ተፅዕኖ ማሳደር ወደ ቻሉ ቤተ ክርስቲያኖችና ኮንፈረንሶች ልኬህ ነበር፣ አንተም በታማኝነት ታዝዘኸኛል፡፡ እስከአሁን ድረስ ላገለገልካቸው ሰዎች እኔ ማሳቤን እቀጥላለሁ፤ አሁን ግን ሁነኛ ለውጥ ላደርግ ነው፡፡ አሁን አንተ አስበህ እንኳ ከማታውቀው በላይ ዕድገት ላመጣ ነው፡፡ በከተሞቻቸውና በአገሮቻቸው*

*ፋይዳ ያለው ተፅዕኖ ከሚያደርጉ ቤተ ክርስቲያኖችና ኮንፈረንሶች ጥሪ ስለሚቀርብልህ፣ በአገልግሎት የምትደርሳቸው ሰዎችም ብዛት ብዙ ዕጥፍ ይሆናል፡፡ እጅግ ከፍ ባለ ሁኔታ በኢኮኖሚ፣ በማኅበራዊና በመንፈሳዊ ሕይወት ትባረካለህ፡፡ ዋጋህ ያለው በእኔ ዘንድ ነው፣ መልእክትህ ወደ ብዙዎች የሚደርስበት ጊዜ መጥቷል በማለት ተናገረኝ፡፡*

(የቁጥሮች ብዛትን አስመልክቶ ይህን ጠቃሚ ነጥብ እንዳቀርብ ፍቀዱልኝ፡፡ ማኅበረ ሰባቸው ላይ ተፅዕኖ የማያሳድሩ ብዙ አባሎች ያሉዋቸው ቤተ ክርስቲኖች አሉ፤ በአንጻሩ በጣም ተፅዕኖ አድራጊ የሆኑ ትንንሽ ቤተ ክርስቲያኖች አሉ፡፡ የአንድ ውጤታማ ቤተ ክርስቲያን ጠቃሚ ገጽታ ጥራቱ፣ ወንጌል ማዳረሱና ተፅዕኖ ማሳደር መቻሉ እንጂ የአባሎቹ ቁጥር ብዛት አይደለም፡፡)

እግዚአብሔር በግልጽ ለልቤ በተናገረው ነገር በጣም ደነገጥኩ፤ በጣም ተገረምኩ፡፡ በኋላም ለሊዛ ስነግራት እርሷም ደስ አላት፡፡ ግን ከጥቂት ጊዜ በኋላ እግዚአብሔር ዝግ ባለ ሁኔታ፣ *መፈተኛው ይህ ነው፡፡ ተፅዕኖ ማሳደር ወዳልቻሉት ትንንሽ ቤተ ክርስቲያኖች ስትሄድ ለሚያስፈልግህ እያንዳንዱ ሳንቲም አምነህብኝ ነበር፤ ለእያንዳንዱ ቃል ተማምነህብኝ ነበር፡፡ በአገልግሎትህ ከእኔ ፈቃድ ከወጣህ በጣም እንደምትጐዳ በማወቅህ ዘወትር የእኔን ምክር ፈልገሃል፡፡*

*በኢኮኖሚ ስባርክህ ገንዘብህን ለአልባሌ ነገር ታባክናለህ? ወይስ በድርቅ ጊዜዎች እንዳደረግኸው ያኔም የእኔን ምክር ትጠይቃለህ? ወይስ ያኔ የእኔን ምሪት ከመጠየቅ ይልቅ አንተ ወደ ፈለግኸው ቦታ ተነሥተህ ትሄዳለህ? እኔን ወክሎ እንደሚናገር ሰው ለእያንዳንዱ ቃል በእኔ ከማመን ይልቅ በየመድረኩ የራስህን ሐሳብ ትሰጣለህ? ልጆቼ በሁለት ዋና ዋና መንገዶች ይፈተናሉ - በበረሓ እና ሁሉም በሞላበት ቦታ፡፡ ብዙዎች የወደቁት በበረሓ ሳይሆን ሁሉም ሞልቶ በተረፈበት ጊዜ እና ቦታ ነው፡፡*

በመገረም እየተንቀጠቀጥኩ ነበር፡፡ ከጸሎት ከተነሣሁ በኋላ ወዲያውኑ እግዚአብሔር የነገረኝን ለሊዛ አካፈልኳት፡፡ እርሷም፣ ‹‹ጆን፣ እግዚአብሔር የነገረህን ቃል የመጀመሪያ ክፍል ስሰማ ወጥ ቤቱ ውስጥ ማሽብሸብ ቃጥቶን ነበር፡፡ አሁን ሙሉውን መልእክት ስሰማ ግን በፍርሃት ተንቀጥቅጫለሁ!›› አለችኝ፡፡

እኔም፣ ‹‹ትክክል ነሽ›› – ‹‹ምክንያቱም እግዚአብሔርን ለመፍራት የሚሰጠው ትክክለኛ ምላሽ ይኸው ነው›› አልኳት፡፡

እግዚአብሔርን መፍራት፣ መሸቆጥቆጥ ወይም መርበትበት እንዳይደለ ብዙዎች ገና አልገባቸውም፡፡ ይልቁንም መሸቆጥቆጥና መርበትበት የሚመጣው ከእርሱ ሲርቁ ነው! እግዚአብሔርን መፍራት የጤነኛ፣ የጥበብ፣ የኃይልና ዋስትና ያለው ሕይወት ሥርና መሠረት ነው፡፡ ለምሳሌ ያህል ሀብታም ወደ መሆን ስንመጣ፣ በተገቢው መንገድ ከያዝነውና እርሱን በተመለከተ ትክክለኛ አመለካከት ካለን ጥሩ ነገር ነው፡፡ ይሁን እንጂ፣ ከሀብት ጋር በቀላሉ መታለልም ተያይዞ ይመጣል፡፡ ማቴዎስ 13፥22 ላይ፣ ‹‹በብልጽግና ሐሳብ መታለልን›› በተመለከተ ኢየሱስ አስጠንቅቋል፤ ሆኖም በእግዚአብሔር ምክር፣ ቃልና ጥበብ ማለትም በእግዚአብሔር ፍርሃት ውስጥ ከሆንን፣ እንዲህ ያለው መታለል አያሳስተንም ወይም ጉዳት አያደርስብንም፡፡

እንደ የክርስቶስ አምባሳደር የእኔ የራሴን ሐሳብ መስጠት፣ እግዚአብሔርን አለመፍራት ከመሆኑ ሌላ ትዕቢት እንጂ ሌላ ሊሆን አይችልም፡፡ ጳውሎስ፣ ‹‹ከትሑታን ጋር አብራችሁ ለመሆን ፍቀዱ እንጂ፤ በራሳችሁ ሐሳብ አትኩራሩ ወይም አትመኩ›› የሚለው በዚህ ምክንያት ነው (ሮሜ 12፥16)፡፡ ግልጽ በሆነ ሁኔታ እግዚአብሔር ፈቃዱን አሳውቆ ስለ ነበር፣ ካሌብና ኢያሱ የጓደኞቻቸውን ሐሳብ አልተከተሉም፡፡ እግዚአብሔር ፈሩ፤ ከዚህም የተነሣ በመልካም ፈጸሙ፡፡ መጽሐፈ ምሳሌ እንደሚለው፣ ‹‹እርሱ (እግዚአብሔር) በዕቡያን ፌዘኞች ላይ ያፌዛል፤ ለትሑታን ግን ሞገስ ይሰጣል›› (3፥34)፡፡

መቼም፣ ጤነኛ አእምሮ ያለው ሰው፣ እግዚአብሔር እንዲያፌዝበት አይፈልግም፡፡ ራሴ ለራሴ እበቃለሁ የሚል አስተሳሰብ በትክክል የሚያደርገው ይህን ነው፡፡ የክብር አምላክ ትዕቢትን በቸልታ አያልፍም፡፡ በጣም ይጠላዋል፤ ይጸየፈዋል፡፡ ሉሲፈር ለእርሱ በጣም የቀረበ ነበር፤ ከመላእክቱ ሁሉ በላይ ለእርሱ የቀረበ ነበር፤ ግን እግዚአብሔርን ባለ መፍራቱ በመልካም ሁኔታ አልዘለቀም፡፡ ‹‹እግዚአብሔርን መፍራት ንጹሕ ነው፤ ለዘላለም ጸንቶ ይኖራል›› ተብሎ ተነግሮናል (መዝሙር 19፥9)፡፡ እግዚአብሔርን መፍራት በሚገባ ለመጨረስ የሚያስፈልገንን ችሎታ የሚሰጠን፣ ጸንቶ መቆም የሚያስችለን ኃይል ነው፡፡ አዳምና ሔዋን በክብሩ ሐልዎት ውስጥ ይኖሩ ነበር፣ ሆኖም ከእርሱ እንዳይለዩ እግዚአብሔርን አልፈሩም፡፡ ከዚህም የተነሣ ለዘላለም በኤደን አልኖሩም፡፡

መንፈሳዊ ፍርሃት፣ እምነትና ትሕትና በቀላሉ የማይቆረጥ በሦስት የተገመደ እውነተኛ ገመድ ነው (መክብብ 4፥12 ይመ)፡፡ እግዚአብሔርን የምትፈሩ ከሆነ ትሑት ትሆናችሁ እንጂ፣ በራሳችሁ ሐሳብ ጥበበኛ

አትሆኑም፡፡ በተመሳሳይ መንገድ ትዕቢት፣ ዐመፅና አለማመን በሦስት የተገመደ ለመበጠስ የሚያስቸግር የጨለማ ገመድ ነው፡፡ እግዚአብሔር በቃሉ የተናገረውን ችላ በማለት የራሱን ሐሳብ አጥብቆ የያዘ ሰው አሳዩኝ፤ እኔም ለዘለቄታው የማይጸና ሰው አሳያችኃለሁ፡፡ የእንዲህ ያለው ሰው ተስፋ፣ እውነተኛ ንስሐና ትሕትና ብቻ ነው፡፡

## ጆርባን የሚከልል መሣሪያ

ትዕቢት አሳሳች ነው፡፡ እንደሚገባ እንዳንጨርስ ለመከላከል ጠላት የሚጠቀምበት በጣም ዋናው መሣሪያ እንደ ሆነ አምናለሁ፡፡ የሚያጠቃው ከጆርባ በመሆኑ ትዕቢተኛው ጠላት እየመጣ መሆኑን ማየት አይችልም፡፡ እኔና እናንተ ሁሉንም የሚያሳጣ ጥፋት የደረሰባቸው ሰዎች፣ ‹‹መምጣቱን አላየሁም ነበር›› ሲሉ ስንቴ ነበር የሰማነው?

ለዚህ ምክንያት አለ፡፡ የእግዚአብሔርን መሣሪያዎች ከመጽሐፍ ቅዱስ ብንመለከት ከፊት ለፊት የሚከልሉ ብቻ መሆናቸውን እናያለን፡፡ የእውነት ዝናር፤ የጽድቅ ጥሩር፤ የሰላም ወንጌል፤ የእምነት ጋሻ፤ የመዳን ራስ ቁር፤ እንደ ሰይፍ የሚያገለግለው የእግዚአብሔር ቃል... ፊት ለፊት የሚከልሉ ናቸው፡፡ ጆርባችንን የሚከልል ምንድነው? ነቢዩ ኢሳይያስ መልሱን ይሰጣል፤ ‹‹የእግዚአብሔር ክብር ደጀን ይሆንሃል›› (58፥8)፡፡

አንድ ሌላ የመጽሐፍ ቅዱስ ትርጉም፣ ‹‹የእግዚአብሔር ክብር ከጆርባ ይከልልሃል›› ይላል፡፡ የእርሱ ክብር ጆርባችንን ይጠብቃል፡፡ ያም ሆኖ ክብሩን ከሌላ ጋር እንደማይካፈል እግዚአብሔር አጽንዖት ሰጥቶ የተናገረውን መዘንጋት የለብንም (ኢሳይያስ 42፥8) ፡፡ የራሳችንን አመለካከት ከፍ አድርገን የምናይ ከሆነ በትዕቢት ተሞልተናል፤ ደጀን የሚሆንልን ክብሩን አጥተናል ማለት ነው - ያኔ ጆርባችን ያለ ምንም ከለላ ይሆናል!

እውነተኛ ትሕትናንና ትዕቢትን በተመለከተ ያለን አመለካከት በጣም የተሳሳተ መሆኑን ሳስብ በጣም አዝናለሁ፡፡ እግዚአብሔር፣ ‹‹ሕዝቤ ዕውቀት ከማጣቱ የተነሣ ጠፍቶአል›› ይላል (ሆሴዕ 4፥6)፡፡ ባላዋቂነታችን የጠፉን ወይም የምንጠፋ ስንቶቻችን እንሆን? ዐሥሩ ሰላዮችና እስራኤል ሁሉ የካሌብና የኢያሱን ትሕትና እንደ ትዕቢት ከቆጠሩት፣ የዳዊትን ትሕትና ኤልያብ እንደ ትዕቢትና እብሪት ከቆጠረው፣ ዛሬስ እንዴት ይሆን?

ይህ ሁኔታ በአካባቢው ላይ አደገኛ አራዊት መኖራቸውን ሳያውቁ፣ ረጅም ጉዞ ከመጀመር ጋር ሊነጻጸር ይችላል፡፡ ዐጉል ቦታ ላይ ከመኪናችሁ ወርዳችሁ ወዲያ ወዲህ ካላችሁ ከባድ ጉዳት ሊደርስባችሁ ይችላል፡፡

አንድ ጊዜ እኔና ሊዛ አደን ነክ ጉዞ እንድናደርግ ተጋብዘን ነበር፡፡ ቦታው በጣም ምቹና ባለ አምስት ኮከብ መስተናገጃ ሲሆን፣ ለእያንዳንዱ ጥንድ የየራሳቸው ትንንሽ ቤቶች ነበሩዋቸው፡፡ ራት ከምንበላበት ገላጣ ቦታ ወደየቤታችን ስንሄድ የሠለጠነ አዳኝ ያጅበን ነበር፡፡ ከመመገቢያው ቦታ እስከ ማረፊያ ቤታችን የነበረው ርቀት አጭር የሚባል አልነበረም፡፡ በመጀመሪያው ምሽት አጃቢያችን እኔና ሊዛን፣ ‹‹በቀላሉ ለጥቃት ልትጋለጡ ስለምትችሉ በምንም ዐይነት ሁኔታ ሌሊት ከቤታችሁ እንዳትወጡ፡፡ ሌሊት ሌሊት ለአደን የሚወጡ የተራቡ የዱር አራዊት አሉ፤ እነርሱን የሚከልል ምንም አጥር የለም›› በማለት አጥብቆ ነግሮን ነበር፡፡

ይህን ባለ ማወቅ ወይም ችላ በማለት ዕኩለ ሌሊት ላይ የሚበላ ነገር ፍለጋ ወደ ምግብ ቤት ብወጣ ምን የሚሆን ይመስላችኃል? እኔ ራሴ ምግብ ልሆን እችላለሁ፡፡ ዕውቀት በማጣት ልጠፋ እችላለሁ፡፡ እንግዲህ በዚህ ምዕራፍ የተመለከትነውን መሠረት በማድረግ የሆሴዕን ቃል፣ ‹‹በእውነተኛ ትሕትናና በትዕቢት መካከል ያለውን ልዩነት አስመልክቶ ሕዝቤ ዕውቀት በማጣቱ ጠፍቷል›› በሚል መልኩ ልንወስደው እንችላለን፡፡

በትሕትና መታጠቅ ምን ማለት እንደ ሆነ ለመማር ጊዜያችሁን ስለ ሰጣችሁ በጣም ደስ ይለኛል፡፡ ግን እዚህ ላይ እንዳታቆሙ፡፡ ቅዱሳት መጻሕፍትን በሚገባ አጥኑ፤ መንፈስ ቅዱስ እንዲያበራላችሁ ጠይቁ፡፡ ዕውቀት ከማጣት የተነሣ፣ በአንድ አቅጣጫ ብቻ በማየት በሕይወታችሁ ቁልቁል አትውረዱ፡፡ የእግዚአብሔር ዓላማ በሚገባ እንድትጨርሱ ነው፡፡ የእግዚአብሔርን ተስፋ ቃል ስሙ፣

> ትሑታን በእግዚአብሔር፣ ምስኪኖች በእስራኤል ቅዱስ፣ እንደ ገና ሐሤት ያደርጋሉ፡፡ (ኢሳይያስ 29፥19)፡፡

እንዴት ትልቅ ተስፋ ነው! ሁላችንም ሐሤት ማድረግ እንወዳለን፡፡ ግን፣ በጣም አስፈላጊ ተስፋ የሆነው ለምንድነው? ምክንያቱም፣ ‹‹የእግዚአብሔር ደስታ ኃይላችን›› በመሆኑ ነው (ነህምያ 8፥10)፡፡ በሚገባ ለመጨረስ የሚያስችለን ኃይል ነው፡፡ ያለ እርሱ በጽናት ሩጫውን መጨረስ አንችልም፡፡ ትሕትናን ከለበስን፣ በደስታ ወይም በብርታት ይበልጥ እየጨመርን እንደምንሄድ እግዚአብሔር ለእኔና ለእናንተ ቃል ገብቶልናል፡፡ በተጨማሪም እንዲህ የሚል ተስፋ ሰጥቶናል፡፡

> ከፍ ከፍ ያለውና ልዕልና ያለው እርሱ፣
>
> ስሙም ቅዱስ የሆነው፣ ለዘላም የሚኖረው

እንዲህ ይላል፤

‹‹የተዋረዱትን መንፈሳቸውን ለማነሣሣት፣

የተሰበረ ልብ ያላቸውን ለማነቃቃት፣

ከፍ ባለውና በቅዱሱ ስፍራ እኖራለሁ፤

የተሰበረ ልብ ካለውና በመንፈሱ ከተዋረደው

ጋር እሆናለሁ (ኢሳይያስ 57፥15)

እግዚአብሔር በውስጣችን ከኖረ፣ ያለ ጥርጥር ሩጫችንን በጽናት እንፈጽማለን፡፡ መፈለግ ያለብን በእግዚአብሔር መጐብኘትን አይደለም፡፡ ይልቁንም እርሱ በውስጣችን እንዲኖር መፈለግ አለብን፡፡ ይህ የሚያጸና ኃይል ይሆነናል፡፡

ስለዚህ ውድ አንባቢዎች፣ ‹‹ትሕትናን ልበሱ፤ ምክንያቱም እግዚአብሔር ትዕቢተኞችን ይቃወማል፤ ለትሑታን ግን ጸጋን ይሰጣል፡፡ …እርሱ በወሰነው ጊዜ ከፍ እንዲያደርጋችሁ ከእግዚአብሔር ብርቱ እጅ በታች ራሳችሁን ዝቅ አድርጉ፡፡››

# 11

# ሽክምን እንጣል

*ሁላችሁም እርስ በርስ በመከባበር ትሕትናን ልበሱ፤ ምክንያቱም፣ «እግዚአብሔር ትዕቢተኞችን ይቃወማል፤ ለትሑታን ግን ጸጋን ይሰጣል፡፡» ...ስለዚህ እርሱ በወሰነው ጊዜ ከፍ እንዲያደርጋችሁ ከእግዚአብሔር ብርቱ እጅ በታች ራሳችሁን ዝቅ አድርጉ፤ እርሱ ስለ እናንተ ስለሚያስብ የሚያስጨንቃችሁን ሁሉ በእርሱ ላይ ጣሉት፡፡*

*1ጴጥሮስ 5፥5-7*

ትሕትናን የመልበስ ዋናው ገጽታ፣ ካሌብና ኢያሱ እንዳደረጉት ራሳችንን ከእግዚአብሔር ተልዕኮ በታች ማኖር ነው፡፡ እንደዚያ ካደረግን አሁን ባለንበት ሁኔታና በመለኮታዊው ተልዕኮ መፈጸም መካከል የሚቆም ማንኛውም ፈተና የሚሸነፍ ይሆናል፡፡ በትሕትና የእኛን ስሌት ሁሉ፣ ከእግዚአብሔር ብርቱ እጅ በታች እናኖራለን፡፡ በትሕትና ማንኛውም ምርጥ ሰብዓዊ አመክንዮ እኛ ላይ የሚያሳድረውን ጫና በመተው የእርሱን ሪፖርት እናምናለን፡፡ በትሕትና በስሜቶቻችን ወይም በተፈጥሮአዊ ዕውቀታችን ሳይሆን በእምነት እንመላለሳለን፡፡

በእውነት በዚህ መልኩ እንድንኖር፣ የሚያስጨንቀንን ሁሉ እርሱ ላይ መጣል አለብን፡፡ አንዳንዶቹን ብቻ ሳይሆን ሁሉን፡፡ ሚስቶቻቸውንና ልጆቻቸውን በተመለከተ ካሌብና ኢያሱ ያደረጉት ይህንኑ ነበር፡፡ እንደ አባቶችና እንደ ባሎች እነርሱም በጣም የሚያስቡላቸው ቤተ ሰቦች ነበሩዋቸው፡፡ ይሁን እንጂ፣ በእነርሱ ዘንድ ከሰብዓዊ አመክንዮና ፍርሃት ይልቅ የእግዚአብሔር ቃል ቀዳሚውን ቦታ ያዘ፡፡ የእግዚአብሔርን ፈቃድ በማስቀደም ቤተ ሰቦቻቸው እንደሚጠበቁና የሚያስፈልጋቸው ሁሉ እንደሚሰጣቸው ተረድተዋል፡፡ ካሌብና ኢያሱ በእግዚአብሔር ፊት በእውነት ትሑታን ነበሩ፤ ከዚህም የተነሣ ለቤተ ሰባቸው የነበራቸው ሐሳብና ጭንቀት በመላው አጽናፈ ዓለም ዐቅም ባላቸው እጆች ውስጥ ሆነ፡፡

## የሚያሳስበንን ሁሉ እርሱ ላይ መጣል

የሚሳስበንን ሁሉ እግዚአብሔር ላይ መጣል በተልዕኮአችን የመጽናት ችሎታ ይሰጠናል፡፡ ወደ ፊት እንድንሄድ ከተፈለገ፣ ምቾት የሚነሣ ሸክም መሸከም የለብንም፡፡ መጽሐፍ ቅዱስ፣ ‹‹ሸከም የሚሆንብንን ሁሉ፣ በቀላሉም ተብትቦ የሚይዘንን ኃጢአት አስወግደን በፊታችን ያለውን ሩጫ በጽናት እንሩጥ›› በማለት ይነግረናል (ዕብራውያን12፥1)፡፡

ሸክም ያዘገየናል፤ በሚገባ እንዳንጨርስ ያደርገናል፡፡ ሃምሳ ኪሎ የሚመዝን ነገር ተሸክማችሁ ማራቶን መሮጥ ምን ይመስላችኃል? ሩጫውን መጨረስ ቀርቶ መጀመርን እንኳ አዳጋች ያደርገዋል!

ወደ ፊት እንዳንጓዝ የሚያግድ አንዱ ከባድ ሸክም ለሕይወት ያለን ስጋትና ሐሳብ ነው፡፡ በሚገባ ያልጨረሱትን ዐሥር ሰላዮች የከበዳቸውም ሸክም ይኸው ነበር፡፡ ሚስቶቻቸውና ልጆቻቸው ላይ ሊደርስ ይችላል ብለው ያሰቡት አደጋ ወደ እግዚአብሔር ተስፋ ቃል ምድር እንዳይሄዱና ፈቃዱን እንዳያደርጉ ከባድ ሸክም ሆነባቸው፡፡

ቤተ ሰቦቻችን ሸክም እንዳይደሉና ይልቁንም ሸክም የሚሆንብን ለቤተ ሰባችን ያለን ሐሳብ መሆኑን ግልጽ ማድረግ አስፈላጊ ነው፡፡ በወቅቱ የሚያስፈልገውን ሁሉ ለመስጠትና ጥበቃ ለማድረግ እግዚአብሔር ያለውን ችሎታ ወይም ፍላጐት ጥያቄ ውስጥ የምናስገባ ከሆነ፣ ታማኝነትና ብርታቱን እየተጠራጠርን ነው፡፡ ከእነዚያው ከነዓናውያን ጋር ውጊያ ባደረጉ ጊዜ ቤተ ሰቦቻቸው በምንም ሁኔታ አለመጐዳታቸውን፣ ካሌብና ኢያሱ የኃላ ኃላ የጓደኞቻቸውን ስሕተት ማሳየታቸውን ማስታወስ ጠቃሚ ነው፡፡ እንዲያውም ለሚስቶቻቸውና ለልጆቻቸው ፍሬያማ ምድር ማውረስ በመቻላቸው፣ በጦርነቱ በመካፈላቸው ባርከዋቸዋል ማለት ይቻላል፡፡

የተለያዩ ውጤቶችን በተመለከተ በጥንቃቄ እናስብ፡፡ በእግዚአብሔር ምሪት ከመታመን ይልቅ ለቤተ ሰቦቻቸው መከላከል የፈለጉ ዐሥሩ ሰላዮች፣ ለቤተ ሰቦቻቸው ያወረሱት በረሐውን ነበር፡፡ ከዐርባ ዓመት ችግርና ጉድለት በኃላ ያ መሆኑ፣ ማንኛውም ሰው የማይፈልገው ፍጻሜ ነበር፡፡ ሆኖም፣ የእግዚአብሔርን ቃል ያመኑና ለእርሱም የታዘዙ ሁለቱ መሪዎች ለቤተ ሰቦቻቸው ያላቸውን ሐሳብ ለእርሱ ታማኝነት አደራ በመስጠታቸው ቤተ ሰቦቻቸው የተስፋውን ምድር - ‹‹ወተትና ማር›› የሚያፈስሰውን ምድር እንዲወርሱ አደረጉ፡፡ ፍጻሜያቸው ያ ሆነ፡፡

በሕይወታችን የተለያየ ወቅት እያንዳንዳችን በጊዜያዊ ምቾትና ዘላቂ ፍጻሜ መካከል ምርጫ የምናደርግበት ጊዜ ይኖራል፡፡ ፋይዳ ወዳለው ነገር

የሚመራውን መንገድ እንመርጣለን ወይስ ጊዜያዊ ምቾትና ደኅንነታችንን ማረጋገጥ እንሞክራለን? ራሳችሁን ማኖር ብቻ የምትፈልጉ ከሆነ፣ ያ የተዘጋጀላችሁ መለኮታዊ ፍጻሜ ላይሆን ይችላል፡፡ ዋስትናና ደኅንነታችሁን በማስጠበቅ ረገድ ሊሳካላችሁ ይችል ይሆናል፤ ይሁን እንጂ፣ የኃላ ኃላ በክርስቶስ ፍርድ ወንበር ፊት፣ ጊዜያዊ ምቾታችሁን ለማስጠበቅ ያጣችሁትን የበዛና የተትረፈረፈ ሕይወት ትረዳላችሁ፡፡

እግዚአብሔር ያቀደላችሁን ጉዞ እንድትፈጽሙ ከተፈለገ ሸክማችሁንና የሚያሳስባችሁን ነገር ሁሉ ለእርሱ መተው እንዳለባችሁ በእግዚአብሔር ቃል ውስጥ ደግሞ ደጋግሞ ተነግሮአል፡፡ የእርሱ መንገድ የጀብድና የእምነት መንገድ ነው፤ ሽልማቱም ከእኛ ዋስትናና የደኅንነት ስሜት ሁሌም በጣም የበለጠ ታላቅ ነው፡፡ የሚያሳስባችሁን ሁሉ እርሱ ላይ በመጣል ወደ ታች የሚጐትታችሁን ሸክም አራግፉ፡፡

## ግላዊ ተግዳሮቶቻችን

በግል ሩጫዬ መጣል ስለ ነበሩብኝ አንዳንድ ሸክሞች እንዳካፍላችሁ ፍቀዱልኝ፡፡ በዕድሜ እያደግሁ በሄድሁ መጠን፣ ለቤተ ሰቦቼ የሚያስፈልጋቸውን የሚያቀርብ አባትና ባል የመሆንን አስፈላጊነት እያመንሁ መጣሁ፡፡ የተቆጠበ ገንዘብ በእርግጥ የተቀመጠ ገንዘብ መሆኑን በማስተማር ለዚህ ጥሩ አርዓያ የሆነኝ ወላጅ አባቴ ነበር፡፡ ዋስትና ያለውና የተረጋጋ ቤተ ሰብ ያለው አባትና ባል የመሆን ፍላጐት ያደረብኝ ገና ልጅ እያለሁ ነበር፡፡ መጀመሪያ ፓይለት መሆን እፈልግ ነበር፤ ግን በዚያ ዘመን ፓይለት መሆን አስተማማኝ ሥራ ተደርጐ ስለማይታሰብ አባቴ ከለከለኝ፡፡ አባቴ የበለጠ አስተማማኝ ነው ብሎ ወደሚያስበው የሙያ መስክ መራኝ፡፡ መሐንዲስነት ተማርኩና በ1981 ዓ.ም ሮክዌል ኢንተርናሽናል ውስጥ የኃላፊነት ቦታ ያዝኩ፡፡

እንደ ጁኒየር መሐንዲስ ጥሩ ደመወዝ ነበረኝ፡፡ ለሚስቴ የሚያስፈልጋትን ሁሉ ማቅረብ መቻል ደስ የሚል ስሜት ይሰጣል፡፡ እንደ አንድ ወጣት አርዓያ የሆነኝን እከተል ነበር፡፡ ግን ከአንድ ውስጣዊ ግጭት ጋር ትግል ነበረብኝ፤ ወደ አገልግሎት የመግባት በጣም የጋለ ጥሪ ነበረኝ፡፡ ይህ ጥሪ ከደረሰኝ ጥቂት ዓመት ቢሆነውም፣ በአገልጋይ ገቢ ለሚስቴና በኃላም ለልጆቼ የሚያስፈልጋቸውን ማቅረብ የምችልበት መንገድ አልታየኝም፡፡ ስለዚህ እኔና ሊዛ አንድ ነገር አሰብን፡፡

ወደ ሌላ አገር በተለይም፣ ወደ መካከለኛው ምሥራቅ ሄደው በኃላፊነት ለሚሠሩ ሰዎች ካምፓኒው በጣም ከፍ ያለ ደመወዝ እንደሚከፍል

ከአንድ ሌላ ሠራተኛ ተረድቼ ነበር፡፡ ስለዚህም ወደ ፐርሰኔል ዳይሬክተሩ ሄጄ ወደ ሳውዲ አረቢያ እንዲያዛውረኝ ጠየቅሁ፡፡ እኔና ሊዛ ያሰብነው እንደ ምንም ታግሠን እዚያ ጥቂት ዓመት ለመኖር፣ ገንዘብ ለማጠራቀም፣ ወደ አሜሪካ ተመልሰን በካሽ መጠነኛ ቤት መግዛትና ከዚያም በአገልግሎት መሰማራት ነበር፡፡

አንዱ ችግር፤ ዕቅዳችን ሁሉ የእኛ ችሎታ ላይ የተመሠረተ መሆኑ ነበር፡፡ አንድ ምሽት ከጥቂት ዓመት ወዲህ እኔና ሊዛን የሚያውቅ አገልጋይ፣ እኔን ቁጭ አድርጎ ለሁለት ሰዓት ያህል ገሠጸኝ፡፡ የመልእክቱ አንኳር ሐሳብ፣ ‹‹ጆን በሕይወትህ የእግዚአብሔር ጥሪ ይታያል፤ አንተ ግን ያንን በተመለከተ ምንም እያደረግህ አይደለም፡፡ አሁን ባለህበት ቦታ ከቆየህ እግዚአብሔር ካቀደልህ ፍጻሜ ትወጣና በመሐንዲስት ታረጃለህ›› የሚል ነበር፡፡

ቃሉ በጣም አስፈራኝ፤ ግን እውነት መሆኑን አውቅ ነበር፡፡ በዚያ ምሽት ወደ ቤት ስመለስ ለሊዛ፣ ‹‹በማንኛውም ቦታ ለመሥራት ራሴን ለቤተ ክርስቲያን እሰጣለሁ፡፡ በመጀመሪያ በሚከፈተው በር እገባበታለሁ፡፡ በዚህ ትስማሚያለሽ?›› አልኳት፡፡ ‹‹አዎን፣ እስማማለሁ›› አለች፡፡

አገልግሎት ውስጥ እንድገባ እግዚአብሔር በር እንዲከፍትልኝ በቀጣዮቹ ጥቂት ወሮች አጥብቄ መጸለይ ጀመርኩ፡፡ በዚያው ጊዜ በፈቃደኛነት ደረጃ ቤተ ክርስቲያናችን ውስጥ እንዳገለግል ማድረግ የምችለውን ሁሉ እያደረግሁ ነበር፡፡ አስተናጋጅ ሆንሁ፣ ከቤተ ክርስቲያኑ የእስር ቤት አገልግሎት ጋር አብሬ መሥራት ጀመርኩ፤ ሌላው ቀርቶ የፓስተራችንን ልጆች እንዴት ቴኒስ መጫወት እንደሚችሉ አስተምር ነበር (የኮሌጅ ተማሪ እያለሁ አንድ ክለብ ውስጥ ቴኒስ አስተምር ነበር፡፡)

ከጥቂት ወሮች በኋላ በ1983 የሙሉ ጊዜ አገልግሎት በር ተከፈተ፡፡ ሮክዌልን ትቼ ለአጥቢያ ቤተ ክርስቲያኔ መሥራት ጀመርኩ፡፡ አዲሱ ቦታዬን ስይዝ የወር ገቢዬ እጅግ በጣም ዝቅ አለ፤ አባቴ አእምሮዬን የሳትኩ መሰለው (የሮክዌል አለቃዬም እንደዚያ ነበር ያሰበው)፡፡ ሌሎች ጓደኞቼም የውሳኔዬን ትክክለኛነት መጠየቅ ጀመሩ፤ እኔም ብሆን ለቤተ ሰቤ የሚያስፈልገውን እንዴት ማሟላት እንዳለብኝ ከሐሳቤ ጋር ትግል እየገጠምኩ ነበር፡፡ የወር ገቢዬ ከማወጣው ውጪ በጣም ያነሰ ነበር፡፡

ሆኖም፣ እዚህ ቦታ ላይ መሆኔ እግዚአብሔር ለእኔ ያለው ዕቅድ እንደ ሆነ አውቅ ነበር፡፡ ስለዚህ እኔና ሊዛ ለሚያስፈልገን ነገር ማሰብን ለእግዚአብሔር ተውንለት፡፡ አንድ ምግብ እንኳ አልጎደለብንም፤ ሁሌም

ለሚያስፈልገን ሁሉ የሚበቃ ያህል ነበረን፡፡ አንድ ቃል እንኳ ለማንም ሳንናገር በየጊዜው የሚያስፈልገንን ሁሉ እግዚአብሔር በተአምር ሲያዘጋጅልን እናይ ነበር፡፡ እኔና ሊዛ በየግላችን የሚያስፈልገንን ለእግዚአብሔር እናቀርብ ነበር፤ በእግዚአብሔር ቃል ጠላትን እንዋጋ ነበር፤ ከአንድ ተአምር ቀጥሎ ሌላ ተአምር በኑሮአችን ሲደረግ እንመለከት ነበር፡፡

አንድ ጊዜ ዐሥራት ከመክፈል ወይም ገንዘቡን የሚያስፈልጉንን ነገሮች ለመግዛት ከማዋል አንዱን የመምረጥ ምርጫ ገጥሞን እንደ ነበር አስታውሳለሁ፡፡ በማንኛውም ነገራችን ለእግዚአብሔር ቅድሚያ ለመስጠት መጀመሪያውኑ ወስነን ስለ ነበር ይህን ያህል ትግል አልሆነብንም፡፡ ስለሆነም ከደመወዛችን 10% ዐሥራት እንሰጥ ነበር፤ ያ ማለት ደግሞ የተቀረው ዕዳ ለመክፈልና ለአንዳንድ ያልተጠበቁ ወጪዎች መዋል አለበት ማለት ነው፤ አንደኛው ወጪ ፈላጊ መኪናችን ነበር፡፡

በዚያ ዘመን ያለን አንድ መኪና ብቻ ነበር፤ ኦልተርኔተሩ ተበላሽቶ ነበር፡፡ በቤተ ክርስቲያኔ ሥራ በጣም በመወጠሬ ያንን ለመጠገን ጊዜ አልነበረኝም፡፡ በዚህ ላይ ከሥራ ወደ ቤት፣ ከቤት ወደ ሥራ ለትራንስፖርት የምጠቀመው በቤተ ክርስቲያኑ መኪና ነበር፡፡ ስለሆነም መኪናችን መቀመጥ ነበረባት፡፡ ኦልተርኔተሩ ከተበላሸ ጥቂት ቀን በኋላ፤ የኃላ ጐማው ፈነዳ፡፡ ነገሩን የከፋ ያደረገው ያለን ትርፍ ጐማ የማይጠቅም መሆኑ ነበር፡፡ የምንኖረው በዳላስ ቴክሳስ ሲሆን በዚያ በጋ ወቅት ሙቀቱ በጣም ከፍ ብሎ ነበር፡፡ አንድ ምሽት ከሥራ ወደ ቤት ስመጣ ከመኪናዋ መስኮቶች አንዱ ብትንትኑ ወጥቶ አገኘሁት፡፡ የመኪናዋ ውስጥ ሙቀት በጣም ግሎ ስለ ነበር መውጫ ያጣው አየር ነበር ከመስኮቶቹ አንዱን ያፈነዳው፡፡

የሚረብሽ ነገር ተባብሶ ነበር፡፡ ኦልተርኔተሩን ብጠግነው እንኳ ጐማ ስላልነበረኝ መኪናዋን መንዳት አልችልም፡፡ መስኮቱን በቆሻሻ ማጠራቀሚያ ላስቲክና ፕላስተር ሸፈንነው፤ ያም ሆኖ፣ ከባድ ዝናብ ከመጣ የመስኮቱ ሽፋን በቀላሉ እንደሚለቅና መኪናው ውስጥ ውሃ ሊገባ እንደሚችል እናውቅ ነበር፡፡ በጊዜ ብዛት ቅዝቃዜው የመኪናዋን ውስጥ ሊያዝገው ይችላል፡፡ ነገሩ ለነገ የሚባል ችግር እንዳይደለ ይገባኛል፡፡ ስለዚህ ለአንዳንድ ጋራዦች ደውዬ ችግሬን ነገርኳቸው፤ ሆኖም የሚጠይቁት ገንዘብ እኛ መክፈል ከምንችለው በላይ ነበር፡፡ ለመኪናችን መጠነኛ ጥገና ለማስደረግ እንኳ ገንዘብ አልነበረንም፡፡ ዱሮ በማገኘው የመሐንዲስ ደመወዝ ቢሆን በጣም ቀላል ጉዳይ ነበር፡፡ ለራስ የማዘን ስሜትን መዋጋት ነበረብኝ፤ መኪናዬ በቆመችበት ቦታ ዝጋ ስትበስብስ ይታየኝ ነበር፤ ይህንንም ቢሆን መዋጋት ነበረብኝ፡፡

በመጨረሻ በጣም ተሰላቸሁ፡፡ ከእግዚአብሔር ጋር የምገናኝበት ወደ አንድ ገለልተኛ ቦታ ሄድኩና፣ ‹‹ጌታ ሆይ፣ የሚያስጨንቀኝን ሁሉ አንተ ላይ እንድጥል ተናግረሃል፡፡ ስለዚህ ለዚህች አውቶሞቢል ያለኝን ሐሳብና ስጋት ሙሉ በሙሉ በዚህ ሰዓት አንተ እጅ ላይ አኖራለሁ፡፡ ከዚህ በኋላ የአንተ እንጂ፣ የእኔ ሐሳብ አይደለም፡፡ እንግዲህ መኪናዋ በቆመችበት ቦታ ዝጋ ብትበላሽ የእኔ ጥፋት አይሆንም፤ ምክንያቱም ከእንግዲህ ለዚያ ማሰብ የእኔ ጉዳይ አይደለም! ትኩረቴ ሁሉ አንተ እንዳደርግ የነገርከኝ ላይ ይሆናል፡፡ መፍትሔውን ስለ ሰጠኸኝ አሁን አመሰግንሃለሁ›› በማለት ወደ እግዚአብሔር ጮኽኩ፡፡

ጸሎቴ የምርና ልባዊ ነበር፡፡ ኦልተርኔተሩ ከተበላሸ ወዲህ ለመጀመሪያ ጊዜ ነፍሴ ውስጥ ሰላም ይሰማኝ ጀመር፡፡ ልክ የእግዚአብሔር ቃል ተስፋ የገባለት ዓይነት ሰላም ነበር፡፡

በነገር ሁሉ በጸሎትና በምልጃ፣ ከምስጋናም ጋር ልመናችሁን በእግዚአብሔር ፊት አቅርቡ እንጂ ስለ ማንኛውም ነገር አትጨነቁ፡፡ ከማስተዋል በላይ የሆነው የእግዚአብሔር ሰላም ልባችሁንና አሳባችሁን በክርስቶስ ኢየሱስ ይጠብቃል፡፡

(ፊልጵስዩስ 4፥6-7)

ከዚያ ጠላትን መቃወም ጀመርኩ፡፡ አምርሬና ኮስተር ብዬ፤ ‹‹ሰይጣን ልብ አድርገህ ስማኝ፡፡ አምላኬ፣ እንደ ባለጠግነቱ መጠን የሚያስፈልገኝን ሁሉ በክብር ይሞላብኛል፡፡ ምንም የሚጎድልብኝ አይኖርም፤ የእግዚአብሔርን መንግሥት ስለ ማስቀድም፤ የሚያስፈልገኝ ሁሉ ይጨመርልኛል ፡፡ ስለዚህ በኢየሱስ ስም እቃወምሃለሁ፤ የቆሸሸ እጅህን ከገንዘባችንና ከመኪናችን ላይ እንድታነሣ አዝዝሃለሁ›› በማለት ጸለይኩ፡፡

አንድ ነገር እንደ ተበጠሰ ተሰማኝ፡፡ ወዲያውኑ ራሴን ሲስቅ አገኘሁት፡፡ ለመሆኑ ምን ማለቴ ነው? አልኩ በልቤ፡፡ ጥልቅ እኔነቴ ውስጥ ካለ ምንጭ ደስታ እየፈሰሰ ነበር፡፡ ያ የሚያስፈልገኝን ጉልበት የሚሰጠኝ የእግዚአብሔር ደስታ እንደ ሆነ አወቅሁ፡፡ በዚያ ብርታት ሩጫዬን በጽናት መቀጠል እንደምችል አውቃለሁ፡፡ ከእንግዲህ የሚያሳስበኝና የሚያስጨንቀኝ ነገር ሁሉ በእግዚአብሔር ብርቱ እጅ ውስጥ ነው፤ ጠላትም ታስሮአል፡፡ እግዚአብሔር የሚሠራውን በናፍቆት የምጠባባቅበት ሁኔታ ውስጥ ሆንኩኝ፡፡

በሚቀጥለው ቀን አንድ የሊዛ ጓደኛ መጥታ በምንኖርበት አፓርታማ መኪና ማቆሚያ ቦታ የነበረችውን በጣም የተጎዳች መኪናችንን አየች፡፡ መኪናዋ ለማየት እንኳ የምታስጠላ ነበረች፡፡ ‹‹ሊዛ፣ እኔ አንድ ሜካኒክ ጓደኛ

አለኝ፡፡ ለአንቺና ለጆን ማድረግ የሚችለው ነገር ካለ እንዲያደርግ ለምን ደውየ እንድጠይቀው አትፈቅዱልኝም›› አለች፡፡ ጓደኛዋ ሌሎች ጋራዦች ሊያስከፍሉን ፈልገው ከነበረው በጣም ባነሰ ጊዜና ገንዘብ ማንኛውንም ነገር አስተካከለልን፡፡ እግዚአብሔር በአስደናቂ መንገድ የሚፈለገውን ሲያዘጋጅ አየን፤ ያም እኛን አበረታን፡፡

ዐሥራታችን በመክፈላችን አሁንም ለግሮሰሪ ወጪዎቻችን የሚተርፍ ገንዘብ አልነበረንም፤ እስከሚቀጥለው ዐሥራ ሁለት ቀን ድረስ ምንም አይከፈለኝም፡፡ አንድ ምሽት መኪና ውስጥ ሆነን አለቀስን፡፡ እንባችን በዕቅድ መጨናገፍ ምክንያት እንጂ ያለ ማመን አልነበረም፡፡ ሌሎች ተንደላቀው ሲኖሩ እኛ ለእያንዳንዱ ነገር ለምን ይህን ያህል ትግል እንደምናደርግ ሊገባን አልቻለም፡፡ አንድ ወቅት ላይ ሐዋርያው ጳውሎስ እንደ ነበረው ሁሉ፣ በችግራችን መሐል እየተከናወነ የነበረውን የመረዳት ችግር ነበረብን፡፡ ችግሮቻችንን አታካች፣ አሰልቺ፣ አዋኪና ጊዜያችንን የሚያባክኑ አድርገን ነበር የምንመለከታቸው፡፡ በኃላ ላይ ለእግዚአብሔር የበለጠ ክብር የሚሆን ነገር ለማምጣት ከአሁኑ ችግር በእግዚአብሔር ጸጋ የበለጠውን ተግዳሮት ለማሸነፍ የሚያስችለንን ብርታት እያገኘን መሆኑን አልተገነዘብንም ነበር፡፡ ከጥቂት እንባዎች በኃላ ሊዛና እኔ፣ በእግዚአብሔር ቃል ያለንን እምነት አጸናን፤ መለኮታዊ አገልግሎታችንን ቀጠልን፡፡

ከሁለት ቀን በኋላ በዚያው ሳምንት አግኝንተናቸው የነበሩ ከሳን አንቶኒዮ የመጡ ጥንዶች ወደ እኔ መጡ፡፡ ‹‹ጆን፣ ለምን እንደ ሆነ አናውቅም፤ እግዚአብሔር ግን ይህን እንድንሰጥህ እየተናገረን ነው›› አሉኝ፡፡ የ200 ዶላር ቼክ ያለበት ፖስታ ሰጡኝ፡፡ ሊዛና እኔ በጣም ተገረምን፡፡ የነበርንበትን ሁኔታ ከእግዚአብሔር በቀር ሌላ ማንም አያውቅም ነበር፤ በዚህ መልኩ እንደ ገና የሚያስፈልገንን ሰጠን፡፡

## ከሚያሳስበን ነገር አዲስ የመፈታት ደረጃ

በሚቀጥሉት ጥቂት ዓመታት በእምነታችንም ሆነ በአገልግሎታችን እያደግን ስንሄድ፣ በፍሎሪዳ ያለ አንድ በጣም ትልቅ ቤተ ክርስቲያን የወጣቶች ፓስተር የመሆን ኃላፊነት ተቀበልኩ፡፡ ያኔም ቢሆን የቀድሞው ዓይነት የገንዘብ ችግር ነበረብን፤ እንዲያውም ወደዚያ ቦታ የመጣሁት በፊት ከማገኘው ደመወዝ ቅናሽ ተደርጎ ነበር፡፡ በዚህ ጊዜ የዐሥራ ስምንት ወር ወንድ ልጅ ስለ ነበረን ኑሮ የበለጠ ከበድ ብሎን ነበር፡፡ ያም ሆኖ ለሚያስፈልገን ሁሉ ኃላፊነቱን ለእግዚአብሔር ሰጠን፣ ጠላትን ተቃውምን፣

ተአምራዊ ረድኤትም ይደረግ ነበር፡፡ ትኩረቴን አገልግሎቱ ላይ አደረግሁ፤ የሚያስፈልገን ሁሉ በአስደናቂ መንገድ ደግሞ ደጋግሞ ይሟላልን ነበር፡፡

መስከረም 1988 ወደ ቀጣዩ አገልግሎት ማለትም ከአገር አገር፣ ከቦታ ቦታ እየተዘዋወርኩ ሙሉ ጊዜ ማገልገል እንዳለብኝ እግዚአብሔር አሳየኝ፡፡ ያም ሆኖ ለፓስተሬ ራሴን እያስገዛሁ ነበር፤ ስለዚህም በመቀጠል ለእኔ ያለውን ዓላማ እግዚአብሔር ለእርሱም እንዲያሳየው ለማንም ምንም ሳልናገር ለመጠበቅ ወሰንኩ፡፡ እየጸለይኩ እያለ እግዚአብሔር ያሳየኝን፣ ከእኔ፣ ከሊዛና ሌላ ክፍለ ሀገር (ስቴት) ትኖር ከነበረች ጓደኞችን በቀር ማንም አያውቅም ነበር፡፡

በ1989 የካቲት ወር የአስተዳደር ስብሰባ ላይ እያለን ፓስተሬ ባለፈው ሌሊት ስላየው በጣም ግልጽ ራእይ ተናገረ፡፡ በሙሉ ጊዜ አገልግሎት ለመሰማራት ወደ ተለያየ ቦታ ለመሄድ እኔና ሊዛ ያንን ቤተ ክርስቲያን ለቀን ስንሄድ ማየቱን አካፈለን፡፡ ያንን ስሰማ በመገረም አለቀስኩ፡፡ በሐዋርያት ሥራ 13፥1-5 ላይ የበርናባስና የጳውሎስን ጥሪ እንዳጸና ሁሉ መንፈስ ቅዱስ የእኛንም ጥሪ አረጋገጠልን፡፡

ከስድስት ወር በኃላ ማለት ነሐሴ 1989 በሦስት ሳምንት ውስጥ በሰባት ቤተ ክርስቲያኖች እንዳገለግል ተጋበዝኩ፡፡ ይህን ለፓስተሬ ነገርኩት፤ እርሱም ሳቅ እያለ፣ ‹‹እግዚአብሔር ያሳየን ይህንኑ ነበር፤ ወደዚያ ለመግባት ጉዞ የጀመርክ ይመስላል›› አለ፡፡ አያይዞም፣ ‹‹ይህን የበልግ ወራት እንደ ፈለግህ ወዲያ ወዲህ ማለት ትችላለህ፤ ቤተ ክርስቲያናችን እስከ ዓመቱ ማብቂያ ድረስ ደመወዝህን ትከፍልሃለች፡፡ ከጥር ወር በኋላ ግን ክፍያን በተመለከተ ራስህ ኃላፊነቱን ትወስዳለህ›› አለኝ፡፡

በቀጣዮቹ ጥቂት ወሮች ወደ እነዚያ ሰባት ቦታዎች እየሄድኩ አገለገልኩ፤ በጣም ደስ የሚል የአገልግሎት ጊዜ ነበረኝ፤ ግን ሌላ ግብዣ አልመጣም ነበር፤ የምሄድበትም ቦታ አልነበረም፡፡ ይህን ያስተዋለው ፓስተሬ ደመወዜ ከመቋረጡ ሁለት ወሮች ቀደም ሲል፣ በጣም ጥሩ የድጋፍ ደብዳቤ ጻፈልኝ፣ እርሱ ራሱ ያገለገለባቸው በአሜሪካ ያሉ ስድስት መቶ ቤተ ክርስቲያኖች አድራሻም ሰጠኝ፡፡ (ፓስተሬ በአገር ውስጥም ሆነ በዓለም አቀፍ ደረጃ በጣም የታወቀ አገልጋይ ነበር፡፡)

ወዲያውኑ የእርሱን የድጋፍ ደብዳቤና የእኔንም ደብዳቤ የያዙ ፖስታዎች ለስድስት መቶዎቹ ቤተ ክርስቲያኖች ለመላክ ተዘጋጀሁ፡፡ ገና ዐርባ ፖስታ እንዳዘጋጀሁ መንፈስ ቅዱስ፣ *ልጄ፣ ምን እያደረግህ ነው?* ሲለኝ ሰማሁ፡፡

‹‹ጥሪ ካደረጉልኝ፣ ወደ ቤተ ክርስቲያናቸው መጥቼ ላገለግላቸው ዝግጁ እንደ ሆንኩ ለፓስተሮቻቸው ደብዳቤ እየጻፍኩ ነው›› አልኩ፡፡

*እንደዚያ ካደረግህ ከእኔ ፈቃድ ትወጣለህ፡፡*

‹‹ግን'ኮ ጌታ ሆይ፣ ራሴን ካላስተዋወቅሁ ማንም አያውቀኝም›› አልኩ ጥቂት በብስጭት ዓይነት ስሜት፡፡

*እኔ አውቅሃለሁ፡፡ ተማመንብኝ፡፡*

እዚያ ነጥብ ላይ ምርጫ ማድረግ ነበረብኝ፡፡ ልቤ ውስጥ ለተናገረኝ የእግዚአብሔር ምሪት በትሕትና መታዘዝ ወይም ደግሞ በራሴ ጥረት የሚያስፈልገኝን ማግኘት፡፡ በሌላ አነጋገር የሚያሳስበኝንና የሚያስጨንቀኝን ሁሉ ለእርሱ እጆች እሰጣለሁ ወይስ፣ ለሚያሳስበኝና ለሚያስጨንቀኝ ነገር የራሴን መፍትሔ እፈልጋለሁ? ወዲያውኑ ትክክለኛውን ውሳኔ አደረግሁ፡፡ የራሴ አእምሮ ወይም ስሜት ጣልቃ ከመግባቱ በፊት ዐርባዎቹንም ፖስታዎች ቀዳድጄ ጣልኩ፡፡ እግዚአብሔር እየተናገረኝ ነው ወይም ያ ካልሆነ አእምሮዬ ተቃውሶአል ማለት ነው በማለት አሰብኩ፡፡

ጊዜ እየሮጠ ነበር፡፡ አሁን የታህሣሥ ወር አጋማሽ ሆኖአል፤ የደረሱኝ ሁለት ግብዣዎች ብቻ ነበሩ፡፡ አንደኛው ጥር ወር መጀመሪያ ሳምንት ላይ ደቡብ ካሮላይና ባለች ትንሽ ከተማ፣ አንዲት በጣም ትንሽ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ሲሆን፣ ሰዎቹ የሚሰበሰቡት የቀብር ሥርዐት በሚፈጸምበት ቤት ውስጥ ነበር፡፡ ሁለተኛው፣ ቴኔሲ በሚባል ከተማ ኮረብቶች ላይ ባለች ትንሽ ቤተ ክርስቲያን ሲሆን የተያዘልኝ ቀጠሮ የካቲት ወር መጨረሻ ላይ ነበር፡፡

በዚህ ጊዜ ፓስተራችን ለእኛ በጣም እያሰበ ነበር፡፡ በቅርቡ በየዕለቱ የሚሰራጭ የቴሌቪዥን ፕሮግራም ለመጀመር እየተዘጋጀ ነበር፤ ውሎ አድሮ ፕሮግራሙን በመላው ዓለም ለማሰራጨት ታስቦአል፡፡ ሊዛ የቴሌቪዥን ዝግጅት ልምድ ነበራት፤ ስለዚህም ፓስተራችን በሰዓት $45 እየተከፈላት አዲሱን ፕሮግራም የማዘጋጀት ሥራ እንደሚሰጣት ቃል ገባላት፡፡ እሮይ አልኩ፤ በጣም ደስ አለኝ፡፡ እንዲዚያ ከሆነ የሚስፈልገውን ገንዘብ እናገኛለን፤ እኔም በየቦታው እየዞርኩ አገልግሎቱን እቀጥላለሁ፡፡

ከጥቂት ቀኖች በኋላ ግን እየጸለይኩ እያለሁ መንፈስ ቅዱስ እንደ ገና ለልቤ ተናገረ፡፡ *ሊዛ የቴሌቪዥን ፕሮግራም የማዘጋጀት ሥራውን የምትቀበል ከሆነ የምታገኘውን ገንዘብ ከጉዞህ ከምታገኘው ላይ እቀንሳለሁ፡፡*

*ሊዛ ለፓስተራችሁ እንድትሠራ አልፈልግም፡፡ እጐንህ እንድትሆን ነው የምፈልገው፡፡*

በጣም ነበር የደነገጥኩት፡፡ ይህንኑ መልእክት ለሊዛ ነገርኳት፤ በጣም የገረመኝ እርሷም መስማማቷ ነበር፡፡ እርሷም በጸሎት ጊዜዋ ይህንኑ መልእክት ተቀብላ ነበር! ስለሆነም በጨዋነት ፓስተራችን ያቀረበልንን ግብዣ ሳንቀበል ቀረን፤ ያም ሆኖ ግን አሁንም ለእኛ ያስብ ነበር፡፡

*አሁን ታህሣሥ* ማብቂያ ላይ ነን፡፡ ከቤተ ክርስቲያኑ የምናገኘው ገንዘብ ሊቋረጥ ነው፤ አሁንም በቀጠሮ የያዝኩት ሁለት አገልግሎት ብቻ ነበር፡፡ ፓስተራችን እንደ ገና ወደ እኔ መጣ፡፡ ‹‹ጆን፣ እሑድ ጠዋት በሚኖረን የቴሌቪዥን ስርጭት አንተ ከቦታ ቦታ እየተዘዋወርክ እያገለገልህ እንደ ሆነና ወደ ቤተ ክርስቲያናቸው መጥተህ ልታገለግላቸው ዝግጁ መሆንህን በአገር አቀፍ ደረጃ የሚሰራጨውን የቴሌቪዥን ፕሮግራም ለሚከታተሉ ፓስተሮች ሁሉ መድረክ ላይ አስተዋወቅሃለሁ፡፡ በተጨማሪም ቤተ ክርስቲናችን በየወሩ ትረዳሃለች›› አለኝ፡፡

እንደ ገና በጣም ደስ አለኝ፡፡ ይህ የእግዚአብሔር ሰው ሚሊዮኖች ፕሮግራሙን የሚከታተሉለት በአሜሪካ ካሉ በጣም ታዋቂ ፓስተሮች አንዱ ነበር፡፡ ይህ የእግዚአብሔር መንገድ መሆኑን እርግጠኛ ነበርኩ፤ እንደዚያ ከሆነ፣ ከእርሱ የተቀበልኩትን ጥሪ ለመፈጸም እንደ ልቤ መንቀሳቀስ እንደምችል አሰብኩ፡፡

ከጥቂት ቀኖች በኃላ እየጸለይኩ እያለ ግን መንፈስ ቅዱስ፣ *ልጄ፣ ፓስተራችሁ በቴሌቪዥን ፕሮግራሙ አያስተዋውቅህም፤ ቤተ ክርስቲያንህም በየወሩ አትረዳህም* በማለት እንደ ገና ተናገረኝ፡፡

አሁን ተስፋ መቁረጥ ጀመርኩ፡፡ ‹‹ለምን? አልኩ ቆጣ ብዬ፡፡›› ፓስተራችን'ኮ እንደዚያ እንደሚያደርግ ነግሮኛል!››

*ወዲያውኑ ልቤ ውስጥ ምክንያቱም፣ እንደዚያ እንዲያደርግ እኔ አልፈቅድለትም፤ እርሱ ከእኔ የሚሰማ ሰው ነው* ሲለኝ ሰማሁ፡፡

‹‹ቃል የገባልኝን እንዲያደርግ የማትፈቅድለት ለምንድነው?››

በዚህ ጊዜ እግዚአብሔር በፍጹም የማልረሳውን ነገር ነገረኝ – *ምክንያም፣ እንደዚያ ካደረገ ችግር በገጠመህ ጊዜ ሁሉ ወደ እኔ ሳይሆን፣ ወደ እርሱ ትሮጣለህ፡፡*

እውነትም ፓስተራችን የቴሌቪዥኑን ፕሮግራም በሚከታተሉ ሰዎች ፊት እኔን ሳያስተዋውቅ ቀረ፡፡ እንዲያውም፣ ሌላው ቀርቶ ስለ አዲሱ አገልግሎቴ እንኳ አላነሣም፤ ቤተ ክርስቲያኑ በየወሩ እንድትረዳኝም አላደረገም፡፡ ዛሬ ላይ ሆኜ ሳስበው ሁለቱንም ባለ ማድረጉ ደስ ይለኛል፡፡ ለሚያስፈልገኝ ሁሉ የበለጠ በእግዚአብሔር እንድተማመን አድርጎኛል፤ ገንዘብ ላላቸውና ተፅዕኖ ማድረግ ለሚችሉ ሰዎች ስለ ችግሬ ፍንጭ ከመስጠት ይልቅ፣ እንድጸልይና እንድዋጋ አድርጎኛል፡፡

ጥር መጣ፤ ቤተ ክርስቲያንዋ ለእኔ ደመወዝ መስጠት አቋረጠች፡፡ በዚያ ጊዜ ሊዛና እኔ በእጃችን ያለው $ 300 ብቻ ነበር፡፡ በዚያ ጊዜ ሁለት ትንንሽ ልጆች ነበሩን - ኤዲሰን ሦስት ዓመት ተኩል ሲሆነው፣ አውስቲን ደግሞ ገና ዘጠኝ ወሩ ነበር፡፡ ለቤት ዕዳ $1,000፣ ለመኪና ዕዳ ደግሞ $200 በየወሩ መክፈል ነበረብን፡፡ የሚቀጥለው ገንዘብ ከየት መምጣት እንደሚችል አላውቅም ነበር፡፡ ካልጸለይኩ በሕይወት እንደማልኖር ያህል አጥብቄ መጸለይ ጀመርኩ፤ በእርግጥም ይህ የበለጠ ወደ መንፈስ ቅዱስ እንድቀርብ አደረገኝ፡፡

በሚገርም መንገድ የአገልግሎት በሮች ሲከፈቱ ማየት ጀመርን፡፡ የቀብር ሥርዐት በሚፈጸምበት ቤት ውስጥ ለሚሰበሰቡ ሰዎች ያደረግሁት የመጀመሪያ ስብከት በጣም የተዋጣ ነበር፡፡ አንድ ተጨማሪ ሳምንት እንዲራዘም ተደረገ፡፡ ወሬው እየተስፋፋ ሄደ፤ ከደቡብ ካሮላይና ኮሎምቢያ ከሚባል አገር የመጣ ፓስተር ስብሰባው ላይ ተገኝቶ ነበር፡፡ ስብሰባው ካበቃ በኋላ ወደ እርሱ ቤተ ክርስቲያን ለመሄድ ፈቃደኛ መሆን አለመሆኔን ጠየቀኝ፡፡ እኔና ሊዛ ወደዚያ ፓስተር ቤተ ክርስቲያን ሄድን፣ በእርሱ ቤተ ክርስቲያን በኩል ሌላም የአገልግሎት በር ተከፈተልን፡፡ እንዲህ እንዲህ እያለ መቀጠል ጀመረ፡፡

ጥቂት ወሮች አለፉ፤ እንደ ገና የአገልግሎት በር እየጠበበ ሄደ፡፡ ከፍተኛ የገንዘብ እጦት ነበረብን፤ ግን ዕዳችንን ከመክፈል ዘግይተን አናውቅም ነበር፡፡ አንድ ጠዋት ማለዳ ላይ ለመጸለይ ወደ ውጭ ወጣሁ፡፡ ‹‹እግዚአብሔር አባቴ ሆይ፣ አንተ አድርግ ያልከኝን እያደረግሁ ነው፡፡ የአገልግሎት በሮችን ካልከፈትህልኝና ለቤተ ሰቤ የሚያስፈልገኝን ገንዘብ ካልሰጠኸኝ ከሥራ ለወጡ ሰዎች የሚደረገውን ድጎማ ለመቀበል መገደዴ ነው፤ አንተ በአገልግሎቴ እንዳልረዳኸኝም ለሰዎች መናገር ሊኖርብኝ ነው፡፡ አባት ሆይ፣ ራሴን እዚያ ደረጃ ላይ ላገኘው አልፈልግም፡፡ በእውነት አንተ ከጠራኸኝ በሮች ይከፈቱ፡፡ ሙሉ በሙሉ ይህን ኃላፊነት ለአንተ እሰጣለሁ›› በማለት ድምፄን ከፍ አድርጌ ጸለይኩ፡፡

ከዚያም ወደ ሰሜን ዘወር ብዬ በሮች እንዲከፈቱ አዘዝኩ፡፡ ወደ ደቡብ፣ ወደ ምሥራቅና በመጨረሻም ወደ ምዕራብ ፊቴን እያዞርኩ በእያንዳንዱ ጊዜ በሮች እንዲከፈቱ አዘዝሁ፡፡ ከዚያም እግዚአብሔር ያዘዘኝን ከማድረግ ሊያግደኝ እንደማይችል ለሰይጣን በመናገር ዘወር እንዲል ጠላትን አዘዝሁ፡፡

ከዚያ ጸሎት ጥቂት ቀኖች በኋላ፣ በሚቺጋን ያለ ቤተ ክርስቲያን የአራት ቀን አገልግሎት ጥሪ አደረገልኝ፡፡ ታላቅ መንፈሳዊ እንቅስቃሴ ተቀጣጠለ፡፡ የአራት ቀኑ ስብሰባ ወደ ሳምንቶች ተራዘመ፡፡ ሰዎች ዘጠና ማይሎች ርቀት ላይ ካሉ ቦታዎች ሳይቀር እየነዱ ይመጡ ጀመር፡፡ በየምሽቱ በሚኖረው ስብሰባ ቤተ ክርስቲያኑ በጣም ይሞላ ነበር፡፡ ልጆቿን ይዛ ወላጆቼ ቤት አጠገብ ፍሎሪዳ አንድ መዋኛ ቦታ የነበረችውን ሊዛ እንድትመጣ ጠራኋት፡፡ ስለ ስብሰባው ነገርኳት፤ ልጆቹን ይዛ ወደ ሚችጋን እንድትመጣ የአውሮፕላን ቲኬት ላክሁላት፡፡

ዕረፍት ላይ የነበረ አንድ ፓስተር ሊዛ አጠገብ ተቀምጦ፣ እርሷ በስልክ እየተናገረች የነበረውን እየሰማ ነበር፡፡ ‹‹ይቅርታ አድርጊልኝ የእኔ እኅት፣ ከባልሽ ጋር በስልክ እየተነጋገርሽ የነበረውን ሰምቻለሁ፡፡ እኔ በላይኛው ኒውዮርክ አንድ ሺህ አምስት መቶ አባሎች ያሉት ቤተ ክርስቲያን ፓስተር ነኝ፡፡ አሁን እየተነጋገርሽ ያለው ዐይነት መንፈሳዊ እንቅስቃሴ በቤተ ክርስቲያናችንም እንዲኖር እፈልጋለሁ፡፡ ባልሽን እንድጋብዘው የእግዚአብሔር ፈቃድ ይመስለኛል›› ይላታል፡፡

ስለዚህ በሚቺጋን የነበረው አገልግሎት ካበቃ በኋላ ወደ ኒው ዮርክ ሄድን፡፡ ይኸኛውም ቢሆን እጅግ ደስ የሚል አገልግሎት ነበር፡፡ በተደጋጋሚ ወደዚያ ቤተ ክርስቲያን ተመላልሰናል፡፡ እንዲህ ያለው ሁኔታ ከሳምንት ወደ ሳምንት ቀጠለ፡፡ በመጀመሪያዎቹ አራት ከቦታ ወደ ቦታ የመንቀሳቀስ አገልግሎታችን፣ ግብዣ እንዲያደርጉልን ለአንድ ቤተ ክርስቲያን እንኳ ደብዳቤ ጽፈን ወይም ስልክ ደውለን አናውቅም ነበር፡፡ እኔ በገለጽኩላችሁ ወይም በሌላ አስገራሚ መንገድ የአገልግሎት በሮች ይከፈቱ ጀመር፡፡

## የቀጠለው ልግስና

አንድ ወንድ ለቤተ ሰቡ የሚያስፈልጋቸውን ሁሉ ማሟላቱ የግድ አስፈላጊ ነው የሚል ሐሳብ ይገፔ ያደግሁ መሆኔን በድጋሚ እናገራለሁ፡፡ እንደዚያ ካላደረግሁ፣ ከማያምን ሰው እንኳ የባስኩ እንደምሆን የሚናገረው 1ጢሞቴዎስ 5÷8 ይህን ያረጋግጣል፡፡ ለቤተ ሰቤ የሚያስፈልገውን ማቅረብ ተገቢ እና መንፈሳዊ ጉዳይ ነው፡፡ ይሁን እንጂ፣ ይህን ሐሳብ ከሁሉም ነገር

ባስበልጠው ኑሮ፣ ለእግዚአብሔር በመታዘዝ ወደ ፊት አልራመድም ነበር፡፡ ያ ሐሳብ ሩጫዬን የሚያሰናክል ከባድ ሸክም ይሆንብኝ ነበር፡፡

ከቦታ ቦታ፣ ከአገር አገር፣ እየተዘዋወርኩ ጥቂት ዓመቶች ካገለገልኩ በኋላ፣ የሚያስፈልጋቸውን በተለየ መንገድ ለማሟላት የመረጡ አገልጋዮችን የማየት ዕድል አገኘሁ፡፡ እንደ ዐሥሩ ሰላዮች ሁሉ እነዚህም ሰዎች፣ የሚያስፈልጋቸውን ለማግኘት የራሳቸውን ስሌት የሚከተሉ ይመስላል፡፡ ራሳቸውን ሲያስተዋውቁ፣ ገንዘብ እንደሚያስፈልጋቸው ፍንጭ ሲሰጡ፣ ፖለቲካዊ ዘዴ ሲጠቀሙ አይቻቸዋለሁ፡፡ እውነተኛ ጥሪ እንዳላቸውና ይሁን እንጂ፣ ራሳቸውን እያስተዋወቁና ለእግዚአብሔር ጊዜ እንደሌላቸው ስላወቅሁ በጣም አዝንላቸዋለሁ፡፡ ዛሬም እንኳ ቢሆን፣ ከእነዚህ አገልጋዮች ብዙዎቹ ወደ መንግሥቱ አገዛዝ ገና አልገቡም፡፡ አንድ ፓስተር ተነሥቶ፣ ‹‹የሚያስፈልግህን በተመለከተ ፍንጭ ካልሰጠህ እምነት ብቻውን የሞተ ነገር እንደ ሆነ አታውቅም?›› ብሎ ሲናገር የሰማሁ ጊዜ በጣም ነበር ያዘንኩት፡፡

በተዘዋዋሪ አገልግሎት ባሳፍነው የመጀመሪያው ዓመት እግዚአብሔር በአስደናቂ ሁኔታ የሚያስፈልገንን ሲሰጠን አይቻለሁ፡፡ አንድ ጊዜ የቤት ዕዳችንን ለመክፈል $700 ያስፈልገን ነበር፣ ያ ገንዘብ በሚቀጥለው ቀን ነበር መከፈል የነበረበት፡፡ ወደ ፖስታ ቤት ስሄድ አላባማ ይኖሩ ከነበሩ ባልና ሚስት የተላከ ደብዳቤ አገኘሁ፡፡ *ደብዳቤው፣ ጆን እና ሊዛ፣ ለምን እንደ ሆነ አናውቅም፤ ይህን የ$ 300 ቼክ እንድንልክላችሁ እግዚአብሔር ልባችን ውስጥ አኑሮአል* የሚል ነበረበት፡፡

በዚያው ምሽት ዐርባ ሰዎች ብቻ በነበሩበት ቤተ ክርስቲያን እየተናገርኩ ነበር፡፡ ፓስተሩ በኪስ ወረቀት ሞልቶ የነበረ መባ ሰጠኝ፡፡ ወደ ቤት መጥቼ ከተኛሁ በኃላ ገንዘቡን እንዳልቆጠርኩ ትዝ አለኝ፡፡ እኔና ሊዛ የሚያሳስበንን ሁሉ ለእግዚአብሔር ሰጥተን ስለ ነበር በሚቀጥለው ቀን የሚከፈለው የቤት ዕዳ እንኳ አላሳሰበንም ነበር፡፡ ተነሥቼ የመባውን ገንዘብ ቆጠርኩት፡፡ $397.26 ነበር፡፡ ይህ ከባልና ሚስቱ ስጦታ ጋር አብሮ ለቤታችን ለሚያስፈልገን ክፍያ በቂ ሆነ፡፡ እንደ ገና እግዚአብሔር የሚያስፈልገንን አዘጋጀልን፡፡

በጊዜ ውስጥ እኛን ለማስተማር እግዚአብሔር እየተጠቀመበት የነበረውን ሂደት መረዳት ቻልን፡፡ በመጀመሪያ ደረጃ፣ የመኪና አልተርኔተርን ለመሳሰሉ ጥቃቅን ነገሮች ሐሳባችንን እግዚአብሔር ላይ መጣን ተማርን፡፡ ደመወዛችን በጣም ዝቅ ባለ ጊዜ እንዴት ማመንና መዋጋት እንዳለብን መማራችን አስፈላጊ ነበር፡፡ ለምን? ምክንያቱም ከአገር አገር እየተዘዋወርን ሙሉ ጊዜ ወደ ማገልገል ስንገባ ዝቅ ካለ ደመወዝ፣

ምንም ደመወዝ ወደማናገኝበት ደረጃ ስለምንወርድ ነው፡፡ በዚያ ውስጥ በእምነት እያደግን ሄድን፣ የበለጠ ከባድ ለሆነ አገልግሎት ዝግጁ ሆንን፡፡ በመጀመሪያው ዓመት የገጠመን ተግዳሮት፣ የበለጠ እንድናድግ ረዳን፤ ለሚያስፈልገን ቀጣይ የእምነት ደረጃም ዝግጁ አደረገን፡፡

ይህን እየጻፍኩ ባለሁበት ጊዜ የሜሴንጀር ኢንተርናሽናል የአንድ ሳምንት በጀት $100,000 ሆኗል፡፡ የሚያሳስበኝን ሁሉ ለእግዚአብሔር መስጠትንና ደረጃ በደረጃ በእርሱ መታመንን ባልማር ኖሮ አሁን ያለሁበት ደረጃ ላይ አልደርስም ነበር፡፡ *ትልቁ የምሥራች ደግሞ፣ ስለሚያስፈልገን ነገር በመጨነቅ የአንዲት ደቂቃ እንቅልፍ እንኳ አለማጣቴ ነው፡፡* ከማስተዋል በላይ የሆነ የእግዚአብሔር ሰላም እንደ ተስፋ ቃሉ በክርስቶስ ኢየሱስ ልባችንና አእምሮአችንን ጠብቋል፡፡

## ከእምነት ወደ እምነት

እምነታችንን ለማሳደግ እግዚአብሔር የተጠቀመበት መንገድ የአካል ግንባታን ያስታውሰኛል፡፡ በሰላሣ አምስት ዓመቴ ለአገልግሎት በጣም እዘዋወር ስለ ነበር የአካል እንቅስቃሴ ወደሚደረግበት ቦታ (ጂም) መሄድ ጊዜ ማባከን ይመስለኝ ነበር፡፡ ከዚህም የተነሣ በአትላንታ ጆርጂያ እየሰበክሁ እያለ ራሴን ስቼ ከመድረክ ልወድቅ ነበር፡፡

ጐረቤታችን ያለው ሰውየ በዚያ ዘመን የዓለም የነጻ ትግል ፌዴሬሽን ለሚባለው ፕሮፌሽናል ታጋይ ነበር፡፡ እርሱ፣ ሚስቱና ልጆቹ ጥሩ ወዳጆቻችን ሆነው ነበር፡፡ ከዚያ ቀደም ሲል ወደ ጂም ሊወስደኝ ፈልጐ ነበር፤ እኔ ግን እንቢ አልኩ፡፡ በአትላንታ ከደረሰብኝ ሁኔታ በኋላ ግን፣ ዝንባሌዬ በፍጹም ተለወጠ፡፡ የሰውነቴን ቅርጽ ለማስተካከል ይረዳኝ እንደ ሆነ ጠየቅሁት፡፡

ጓደኛዬ 260 ፓውንድ የሚመዝን ግዙፍ ሰው ቢሆንም፣ ሰውነቱ ውስጥ ያለ የስብ ክምችት 4 ፐርሰንት ብቻ ነበር፡፡ የክንዱ ታችኛና ላይኛ ጡንቻ ከእኔ ጭን የበለጠ ነበር፡፡ አዘውትረን ወደ ጂም መሄድ ጀመርን፡፡ ቀደም ሲል አካላቸውን ከገነቡ ጥቂት ግዙፍ የሆኑ ጓደኞቹ ጋር ተዋውቄ ነበር፤ የሚያሠለጥኑበትንም ዘዴ ለመመልከት ችዬ ነበር፡፡ ዝቅ ያለ ክብደት ያለውን ነገር ብዙ ጊዜ ደጋግሞ በማንሣት ጡንቻ ሊገነባ እንደማይችል ተረድቼ ነበር፡፡ ከዚያ ይልቅ እነዚያ ሰዎች በትንሹ ሦስቴ ወይም አራቴ መነሣት እንዲችል ዘንጉ ላይ ያለውን ክብደት ከፍ ያደርጉታል፡፡ ክብደቱን ሦስት ጊዜ ያህል ደጋግመው ሲያነሡ አይቻለሁ፤ እውነተኛው ትግል ያለው አራተኛው ላይ ነበር፡፡ አግዳሚው ላይ በጀርባው የተንጋለለው ሰውየ

ለአራተኛ ጊዜ ሸክሙን ወደ ላይ ብድግ የሚያደርግበት ዐቅም አልነበረውም፤ ፊቱ ተኮሳተረ፤ ሥሮቹ ተወጣጠሩ፣ ሰውነቱ ተንቀጠቀጠ፤ ግራና ቀኙን የነበሩ ጓደኞቹ፣ ‹‹አይዞህ በርታ፤ አይዞህ ግፋ፤ ትንሽ፣ አዎን ትንሽ ግፋ›› እያሉ ይጮኹ ነበር፡፡ እርሱም ሸክሙን ለአራተኛ ጊዜ ወደ ላይ ለማንሣት ባለው ዐቅም ሁሉ ይገፋ ነበር፡፡ ሰውነቱ ውስጥ ያለ ጡንቻ ምላሽ የሚሰጠውና የሚያድገው ያኔ ነው፡፡

በመጀመሪያ ወደ ጂም ስሄድ አንድ ወር ሙሉ የማነሣው 95 ፓውንድ ብቻ ነበር፡፡ ከዚያ 135 ፓውንድ ጨመርኩ፤ ከስድስት ወር በኋላ 185 ፓውንድ ሆነ፤ በመጨረሻም 205 ፓውንድ ደረሰ፡፡ ለጥቂት ዓመታት ያህል በ205 ተወስኜ ቀረሁ፡፡

ከዚያ በኋላ ቀድሞ አካል ገንቢ (ቦዲቢዩልደር) የነበረ ሰው በአገልግሎታችን ውስጥ ለመሥራት መጣ፡፡ እየተነጋገርን እያለ ብርታትና ጡንቻ ስለ መገንባት የነበረኝን ትውስታ ቀሰቀሰብን፡፡ ጡንቻን ለመገንባት፣ ከዝቅተና መጀመር እንደሚገባ ረስቼ ነበር፡፡ ስለዚህም የመገንባቱን ሂደት እንደ ገና ጀመርን፤ ለአገልግሎት ወደ ፍሬንሶ ካሊፎርንያ አብሮኝ እስኪሄድ ድረስ ቀጥለን ነበር፡፡ ኮንፈረንሱ መሐል ክፍት ጊዜ ስናገኝ፣ ጥቂቶቻችን ተያይዘን ወደ ጂም ሄድን፡፡ ‹‹ጆን፣ ዛሬ 225 ታነሣለህ›› አለ ያ የሥራ ባልደረባዬ፡፡

‹‹እንደዚያማ አልችልም›› አልኩ፡፡

‹‹አዎን፣ ትችላለህ፤ ይልቁን አግዳሚው ላይ በጀርባህ ተንጋለልና ሸክሙን እናቀብልህ›› እውነትም 225 ፓውንድ አነሣሁ፡፡ በጣም ገረመኝ፡፡ ልምምዱን በመቀጠል እስከ 245 ፓውንድ ካነሣሁ በኋላ ግን፣ ከዚያ ከፍ ማለት አቃተኝ፡፡ ምንም እንኳ ይሳካልኛል የሚል እምነት ባይኖረኝም አንድ ቀን እስከ 315 ፓውንድ ድረስ የማንሣት ግብ ነበረኝ፡፡

ከጥቂት ጊዜ በኋላ ዲትሮይት ሚቺጋን ወዳለ አንድ ቤተ ክርስቲያን ሄጄ ነበር፤ ከቤተ ክርስቲያኑ አባሎች አንዱ በአገር አቀፍ ደረጃ በጣም የታወቀ የሰውነት ግንባታ አሠልጣኝ እንደ ሆነ ፓስተሩ ነገረኝ፡፡ ፓስተሩ ራሱ በቅርቡ በጀርባው ተንጋሎ 545 ፓውንድ አንሥቶ ነበር፡፡ ከእሑድ አገልግሎታችን በኋላ ባለው ቀን ፓስተሩ ከአሠልጣኙ ጋር አገናኘኝና 265 ፓውንድ አነሣሁ፡፡ በጣም ደስ አለኝ! በጣም ከባድ የሆነ ፕሮግራም ውስጥ አስገብቶኝ ነበር፤ ይህንንም እኔና አንዳንድ የሥራ ጓደኞቼ በሚቀጥሉት ጥቂት ወሮች ያንን በትጋት ስንፈጽም ነበር፡፡

በሚቀጥለው ጊዜ ዲትሮይት ወዳለው ቤተ ክርስቲያን ስመለስ እሑድ ጠዋትም ሆነ እሑድ ምሽት የሰበክሁት ስለ መንፈስ ቅዱስ ነበር፡፡ ሰኞ ጠዋት ወደ ጂም ሄደን እያለ፣ ባለፈው ጊዜ አግኝቼው የነበረ አሠልጣኝ፣ ‹‹ጆን፣ አግዳሚው ላይ ተንጋልለህ 300 ፓውንድ ስታነሣ ባለፈው ሌሊት በሕልሜ አይቻለሁ›› አለኝ፡፡

‹‹እንዴ፣ እንደዚያማ አይሆንም›› አልኩ፡፡

ትኩር ብሎ እያየኝ፣ ‹‹እሺ ሰውዬ፣ ትናንትና መንፈስ ቅዱስ እንዴት እንደሚናገረን ጧትና ማታ ስታስተምር ነበር፡፡ ባለፈው ሌሊት ለእኔም ተናግሮኛል፡፡ ስለዚህ ፀጥ ብለህ አግዳሚው ላይ በጀርባህ ሁን፡፡ ዛሬ 300 ፓውንድ ታነሣለህ›› አለኝ፡፡

እኔም እንደ ተነገረኝ ፀጥ ብዬ አግዳሚው ላይ ተንጋለልኩ፡፡ ሰውነታችንን ከሚሚቅን በኋላ ጓደኛዬ ዘንጉ ላይ 300 ፓውንድ አደረገ፡፡ ከዚያም ኮስተር ብሎ፣ ‹‹ዘንጉ ወደ ታች ሲወርድ፣ በኃይል ወደ ላይ ግፋው፡፡ እንዲያውም አታስበው፡፡ ዝም ብለህ ብቻ ግፋ!›› አለኝ፡፡

ዘንጉ በጣም ዝቅ እያለ ሲመጣ እርሱና በዙሪያችን የነበሩ ሌሎች ‹‹ግፋ! ግፋ! አዎን ግፋ!›› እያሉ ይጮኹ ነበር፤ እኔም ባለኝ ዐቅም ሁሉ እገፋ ነበር፡፡ ከፍ፣ አሁንም ከፍ እያለ ወደ ላይ ወጣ! ከዚያ ዘንጉን አነሡልኝ፤ እኔም በደስታ እየጮኽኩ ዘልዬ ተነሣሁ፡፡ በጣም ነበር የገረመኝ፡፡

አሠልጣኙ ወዳጄ፣ የአምስት ደቂቃ ደስታ ብቻ ነበር የሰጠኝ፤ ከዚያም ትኩር ብሎ አየኝ፡፡ አስተያየቱ የቅድሙ ዓይነት ነበር፡፡ ‹‹አሁን ደግሞ 315 ፓውንድ ታነሣለህ››

‹‹በፍጹም - በፍጹም ያንን አልችልም፤ ይህንንም በሕልሜ አየሁ ልትለኝ ነው?›› አልኩ፡፡

እርሱም ፈገግ ብሎ በጨዋነት፣ ‹‹ፀጥ ብለህ አግዳሚው ላይ ተንጋለል›› አለ፡፡

በእውነትም በዐርባ አራት ዓመቴ 315 ፓውንድ ማንሣት ቻልኩ፡፡ በደስታ ወደ ላይ ወደ ታች እዘል ጀመር፡፡ ከዲትሮይት አውሮፕላን ማረፊያ በመደወል ወሬውን ለሊዛ መንገሬን በፍጹም አልረሳውም፡፡

በኋላም እነዚህ አሠልጣኞች – የሥራ ባልደረቦቼ፣ በካሊፎርንያ የነበሩት ፓስተሮች፣ በዲትሮይት የነበረው አሠልጣኝ ሁሉም በአንድነት እንደ መንፈስ ቅዱስ እንደ ነበሩ ተማርኩ፡፡

በሰዎች ሁሉ ላይ ከደረሰው የተለየ ፈተና አልደረሰባችሁም፤ እግዚአብሔር ታማኝ ነው፤ ስለዚህ ከምትችሉ በላይ እንድትፈተኑ አይተዋችሁም፤ ነገር ግን በምትፈተኑበት ጊዜ ፈተናውን መታገሥ እንድትችሉ መውጫ መንገዱን ያዘጋጅላችኃል - የሚለውን የጳውሎስን ቃል አስታውሱ (1ቆሮንቶስ 10፥13)

እነዚያ አሠልጣኞች እኔ ማድረግ የምችለውንና ማድረግ የማልችለውን ያውቁ ነበር፡፡ እኔ መግፋት የምችለው 315 ብቻ ሆኖ እያለ 405 ፓውንድ አይጭኑብኝም፡፡ ዕውቀቱ ስላላቸው የሰውን ዕምቅ ዐቅም ለይተው ያውቃሉ፡፡ እኔ ማየት ከምችለው በላይ ማየት በመቻላቸው በጣም ተገርሜአለሁ፡፡ በእያንዳንዱ ጊዜ እኔ የእነርሱን ያህል ማንሣት የምችለውን መገመት አልቻልኩም ነበር፡፡ እነርሱ ግን እኔ ውስጥ የነበረውን ብርታትና ዕምቅ ኃይል አይተዋል፡፡

መንፈስ ቅዱስም እንዲሁ ነው፡፡ እኛ የምንችለውንና የማንችለውን ያውቃል፡፡ ወደ ጂም በሄድኩ በመጀመሪያ ቀን ያ የአካል ግንባታ አሠልጣን 315 ፓውንድ እንዳነሣ አድርጐ ቢሆን ኖሮ ምን ነበር የሚሆነው? በግራቪቲ ፍጥነት ዘንጉ ወርዶ የደረትና የጐን አጥንቶቼን ያደቃቸው ነበር፤ ልሞት የምችልበት ሁኔታ እንኳ ይኖር ነበር፡፡ ከ95 ፓውንድ ጀምሬ እያደር ከፍ እያልኩ መሄድ ነበረብኝ፡፡

በተመሳሳይ መንፈስ ቅዱስ ለእኔና ለሊዛ የተዘጋጀውን ያውቃል፡፡ ‹‹ለእናንተ ያለኝን ዕቅድ እኔ ዐውቃለሁ ይላል እግዚአብሔር›› (ኤርምያስ 29፥11)፡፡ እርሱ እምነታችንን መገንባት አለበት፤ እኛ ደግሞ በመገንባቱ ሂደት፣ የሚያሳስበንንና የሚያስጨንቀንን እርሱ ላይ መጣልን መማር አለብን፡፡ ነገሩ ቀላል አልነበረም፤ ግን ምንጊዜም ጠቃሚ ነው፡፡ ተስፋ የመቁረጥ ወይም የማቋረጥን ስሜት ብዙ ጊዜ ተዋግቻለሁ፤ ሆኖም፣ ኢየሱስ እኔ ላይ ተስፋ ስላልቆረጠ፣ እኔም በራሴ ተስፋ መቁረጥ አልቻልኩም፡፡ ከዚህ የተነሣ በመለኮታዊ ጥሪያችን እንጸናለን፣ መንገዱ ላይ የሚገጥመንን ተቃውሞ ማሸነፋችንን እንቀጥላለን፡፡

ዛሬ ላይ ሆኜ ዞር ብዬ ሳስብ ዝቅተኛው ደመወዝ፣ የኦልተርኔተሩ ችግር፣ የገንዘብ ፍሰት መቋረጥና ያለፍንባቸው ሌሎቹም ፈተናዎች ለሚመጣው ድል የሚያበረቱን ማሠልጠኛዎች እንደ ነበሩ ተረድቻለሁ፡፡

የእያንዳንዱ ሳምንት በጀታችን $100,000 እንደሚሆን እግዚአብሔርን በማመን ጀምረን ቢሆን ኖሮ፣ ወደ ጂም በሄድኩ በመጀመሪያው ቀን እኔ ላይ 315 ፓውንድ የመጫን ያህል ይሆን ነበር፡፡ መንፈስ ቅዱስ እንደዚያ አያደርግም፤ ይልቁንም ለትልልቅ ነገሮች በእግዚአብሔር የምንተማመንበት ደረጃ ላይ ሊያደርሰን፣ ቀስ በቀስ፣ በቀጣይነት ያሳድገናል፡፡

## ሥልጠናውን አታደናቅፉ

በሥልጠናችን ሂደት መጀመሪያዎቹ ዓመታት ላይ የገጠመን ተቃውሞ፣ የግል ችግሮቻችንን ማለትም፣ መኪናዋን ማስተካከልን፣ የግሮሰሪዎች ክፍያን፣ ሌሎች ወጪዎችን መሸፈንንና የቤታችንን ዕዳ መክፈልን የመሳሰሉትን የሚመለከቱ ነበሩ፡፡ ዛሬ የሚገጥመን ፈተና ግን የግል ችግሮቻችንን የሚመለከት ሳይሆን፣ እግዚአብሔር በአገልግሎት የሰጠን ሚሊዮኖችን ደኅንነት የሚመለከት ነው፡፡ ገና መጀመሪያው ላይ የእግዚአብሔርን ሥልጠና ሂደት አደናቅፈን ቢሆን ኖሮ፣ በዚህ ጊዜ እግዚአብሔር ወደ እኛ ለላካቸው ሰዎች የሚሆን ብርታት አይኖረንም ነበር፡፡ ያንን ሌላ ሰው እንዲሠራው ያደርግ ነበር፡፡

የሥልጠናውን ሂደት ሳይፈጽሙ በመቅረታቸው፣ እግዚአብሔር የሚፈልጋቸው ዓይነት ሰዎች መሆን ደረጃ ላይ ሳይደርሱ የቀሩ አገልጋዮች ምን ያህል ይሆኑ? ያኔ የ145 ፓውንድ ተግዳሮት መሸከም ካልቻሉ፣ ዛሬ የ405 ፓውንድ ተግዳሮት መሸከም አይችሉም፡፡ በጣም የሚያሳዝነው እግዚአብሔር የእነርሱን ሥራ የሚያጠናቅቅ ሌላ ሰው መፈለግ ያለበት መሆኑ ነው፡፡

በገጠማቸው ፈተና አማካይነት አገዛዝ ውስጥ ባለ መግባታቸው እግዚአብሔር ከጠራቸው በታች ያሉ ስንት ወንዶችና ሴቶች የቢዝነስ ሰዎች ይኖሩ ይሆን? በእግዚአብሔር ከማመን ይልቅ ወደ ሰዎች ተቋሞች ሄደዋል፤ የገጠማቸውን ችግር ለማሸነፍ ሌሎች ላይ ጫና የማድረግና የመቆጣጠር ዘዴዎች ተምረዋል፡፡ ከዚህም የተነሣ እግዚአብሔር የሰጣቸው ዕምቅ ዐቅም ላይ ሳይደርሱ ቀርተዋል፡፡

ዐሥሩ የእስራኤል ሰላዮች ካሌብና ኢያሱ እንዳደረጉት በሥልጠና ሂደት ውስጥ አለማለፋቸውን እርግጠኛ ነኝ፡፡ በእግዚአብሔር ከማመን በተለየ መልኩ በችግሮቹና በፈተናዎቹ ዙሪያ የሚሽከረከሩበት መንገድ አገኙ፡፡ እምነታቸውን አላሳደጉም፡፡ ስለዚህም በሕይወታቸው ወሳኝ ጊዜ ሲመጣ፣ ለመተማመን የሚያበቃቸው እምነትም ሆነ ብርታት ሊኖራቸው አልቻለም፡፡

አባታችን ለእያንዳንዳችን የሚያስፈልገውን የተሻለ ሥልጠና ያውቃል፡፡ ምንም እንኳ እርሱ የችግርና የመከራዎች ፈጣሪ ባይሆንም፣ እርሱ ላዘጋጀልን ዕጣ ፈንታ እኛን ለማበርታት እንዲደርሱብን ይፈቅድላቸዋል፡፡

በምንም ዐይነት የሥልጠናችሁን ሂደት አታደናቅፉ፡፡ ዛሬ የሚገጥሟችሁ ፈተናዎች፣ ነገ ለምትፈጽሙት ታላላቅ ጀብድ የሚያዘጋጁ ናቸው፡፡ ስለዚህ ወዳጆቼ፣ መጀመሪያውኑ በድል የምትወጡበትን ሥልጠና ሳያዘጋጅ፣ በፍጹም ወደ ተግዳሮት ቦታ እግዚአብሔር እንደማያመጣችሁ ምንጊዜም አስታውሱ፡፡

ከክብር ወደ ክብር፣ ከእምነት ወደ እምነት፣ ከብርታት ወደ ብርታት መሄድ እንድትችሉ የሚያሳስባችሁንና የሚያስጨንቃችሁን ነገር በእውነተኛ ትሕትና እርሱ ላይ መጣል ተማሩ፡፡

# 12

# ራሳችሁን ግዙ፤ ንቁ

*ትሕትናን ልበሱ፤ ምክንያቱም እግዚአብሔር፣ ‹‹ትዕቢተኞችን ይቃወማል ለትሑታን ግን ጸጋን ይሰጣል።›› ስለዚህ እርሱ በወሰነው ጊዜ ከፍ እንዲያደርጋችሁ ከእግዚአብሔር ብርቱ እጅ በታች ራሳችሁን ዝቅ አድርጉ፤ እርሱ ስለ እናንተ ስለሚያስብ የሚያስጨንቃችሁን ሁሉ በእርሱ ላይ ጣሉት። ራሳችሁን የምትገዙ ሁኑ፤ ንቁም፤ ጠላታችሁ ዲያብሎስ የሚውጠውን በመፈለግ እንደሚያገሣ አንበሳ ወዲያ ወዲህ ይዞራል። . . . በእምነት ጸንታችሁ ተቃወሙት።*

*1 ጴጥሮስ 5፥5-9*

ጥልቅ የሆነውን የጴጥሮስን ምክር መመርመር ከመቀጠላችን በፊት፣ እስካሁን የተማርነውን እጥርጥር ባለ ሁኔታ ለማየት እንሞክር - ጸጋ ለድነታችን፣ ለኃጢአት ስርየታችን ብቻ አይደለም፤ ይልቁንም በጨለማውና በጠፋው ዓለም ውስጥ ማብራት የምንችልበትን ዐቅም ይሰጠናል። ሆኖም፣ እንደ ብርሃን ራሳችንን መለየት የሚመጣው ምንም ተቃውሞ ሳይገጥመን አይደለም፤ ወደድንም ጠላንም፤ ውጊያ ይኖራል። ስለዚህም በጸጋ መሣሪያዎች መታጠቅ ይኖርብናል።

ራሳችንን ማስታጠቅ ከትሕትና ይጀምራል፤ ምክንያቱም ጸጋ የሚሰጠው ለትሑታን ነው። ጴጥሮስ ትሕትናን ‹‹ልበሱ›› ይለናል፤ የእውነተኛ ትሕትና እጅግ አስፈላጊ ገጽታ የሕይወት ተግዳሮቶችን በገዛ ራሳችን ችሎታ መቋቋም ከመሞከር ይልቅ የሚያሳስበንንና የሚያስጨንቀንን ሁሉ ለእርሱ መስጠትን ይጠይቃል። በግል የሚያሳስቡን ነገሮች ከተጫኑን ሩጫውን መሮጥ፣ ውጤታማ በሆነ መልኩ መዋጋት፣ አንችልም። ጭንቀት፣ ስጋትና ፍርሃት ወደ ፍጻሜያችን እንዳንደርስ የሚያሰናክሉ ጠላቶች ናቸው። እነዚህን ሸክሞች ለእግዚአብሔር መስጠት በፍጥነት እንድንሮጥና በታላቅ ኃይል በመንፈሳዊ ሰይፋችን እንድንጠቀም ያስችለናል።

ማስተዋል ያለብን ትልቅ ነገር፣ እውነተኛ ትሕትና በዚህ ዓለም ሥርዐት ማዕበል ውስጥ ነጻ ሆነን ወደ ፊት መግፋት እንድንችል ለእኛ ለራሳችን ነጻነት የሚሰጠን መሆኑን ነው። ያ ካልሆነ ግን ያለው አማራጭ

በጭንቀት ረግረግ ውሃና ጭቃ ውስጥ መልሕቃችንን መጐተት ይሆንብናል፤ በዚህ ላይ ደግሞ የወንዙ ማዕበል ይኖራል፡፡ ጴጥሮስ ንቁ፤ ትጉ ይለናል፡፡

## ንቁ፤ ትጉ

*ንቁ* የሚለው ቃል፣ ‹‹ኮስተር በሉ፣ አስተውሉ፤ ረጋ በሉ›› እንደ ማለት ይሆናል፡፡ የግሪኩ ቃል ኔፎ *(nepho)* ሲሆን፣ በወይን ጠጅ የመስከር ተቃራኒ ነው፡፡ ‹‹ረጋ ያለ፣ ንቁ የሆነ አእምሮ ይኑራችሁ›› እንደ ማለት ነው፡፡

ጀማሪ የሁለተኛ ደረጃ ተማሪ እያለሁ አልኮል እወስድ ነበር፤ ይኸው ጉዳይ እስከ ከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የየሳምንቱ ማብቂያ ድረስ ቀጥሎ ነበር፡፡ ይሁን እንጂ፣ የዩኒቨርስቲ የመጀመሪያ ዓመት ላይ መጠጣቴ ተባብሶ ነበር፤ ምክንያቱም ከወላጆቼ ቀጥታ ቁጥጥር ነጻ ነበርኩ፡፡ የዩኒቨርስቲ ሕይወትን በየመካከሉ አልፎ አልፎ ከማጥናት ውጪ፣ እንደ ፈንጠዝያ ጊዜ እንቆጥረው ስለ ነበር፣ የኮሌጅ ወጣት ወንዶች ማኅበር አባል መሆኔ ይህን ያህል አልረዳኝም ነበር፡፡ ዩኒቨርስቲው ውስጥ ብዙም ሳልቆይ ዘወትር አብዝቼ መጠጣት ጀመርኩ፡፡ በዩኒቨርስቲ በቆየሁባቸው የኃለኞቹ ዓመታት ኢየሱስ ከዚያ ሕይወት ነጻ ስላወጣኝ በጣም ደስ ይለኛል፤ በዚያ ዘልቄ ቢሆን ኖሮ ዛሬ ምን ላይ እወድቅ እንደ ነበር የሚያውቅ እግዚአብሔር ብቻ ነው፡፡

ብዙ ጊዜ ሰክሬ በነበረ ጊዜ ምን ዓይነት መጥፎ ነገር እንዳደረግሁና እንደ ተናገርኩ በኋላ ላይ ጓደኞቼ ይነግሩኝ ነበር፡፡ በቀላል አነጋገር የሰከረ ሰው የማመዛዘን ችሎታውን ያጣል፤ ንቁ ወይም አስተዋይ አይደለም ማለቴ ነው፡፡ የኮሌጅ ወጣት ወንዶች ማኅበር ውስጥ ብዙ አላጋጮች ነበሩ፤ የሰከረ ሰው ላይ የፈለጉትን ያህል አስቂኝ ነገር ማድረግ ለእነርሱ በጣም ቀላል ነበር፡፡ ንቁ ቢሆን ኖሮ፣ የማይደረግበት ነገር ይደረግበት ነበር፡፡

አንዱ ከሰከረው ጓደኛው ይሰርቃል፡፡ የሰከረው ሰው ምን ዓይነት ጠቃሚ ነገር እንደ ተወሰደበት እንኳ አያውቅም፡፡ በማግሥቱ ከስካሩ ሲነቃ የጠፋበትን ነገር ፍለጋ ክፍሉን ያመሰቃቅለዋል፡፡ እንዴትና መቼ እንደ ተሰረቀበት እንኳ ጥቂት ትውስታ የለውም፡፡ የተሰረቀበት ከላቦራቶሪ የተዋሰው ዕቃ፣ የኪስ ቦርሳው፣ የጓደኛው ፎቶግራፍ ወይም ሌላ ዋጋ ያለው ነገር ሊሆን ይችላል፤ እየፈለገ እያለ በንዴት ጠፎ ይጮኻል፡፡ አንዳንዴም ይሳደባል፡፡ ዳር ሆነው የሚያደርገውን የሚመለከቱ ጓደኞቹ ደግሞ እየተጠቃቀሱ ይስቁበታል፡፡ የሚበቃውን ያህል ከደከመ በኃላ፣ ከበፊቱ የበለጠ በሳቅ እየተንከተከቱ የወሰዱበትን ሊመልሱለት ይችላሉ፡፡

ንቁ አእምሮ ከሌላቸው ሰዎች ጠላት በቀላሉ ይሰርቃል፣ ወይም እነርሱ ራሳቸውን ይገድላል።

ብዙውን ጊዜ እንደዚያ ያለ ነገር የምናደርገው እንዲሁ ለቀልድ ነበር፣ ግን የምር ጠቃሚ ነገር ተወስዶበት ቢሆንስ? አእምሮው ንቁና ሚዛናዊ ካልሆነ በጣም የሚፈልገው ውድ ነገር ለዘለቄታው ሊጠፋበት ይችላል።

በፀብ ጊዜ ሰክሮ መገኘት ተጠቂ ያደርጋል። አንድ ጊዜ ሁለት ጓደኞቼ በቦክስ ሲደባደቡ የሆነውን አስታውሳለሁ - አንደኛው ሰክሮ ነበር፣ ሌላው ግን ጤነኛ ነበር። ሌላ ጊዜ ቢሆን ኖሮ የሰከረው ጓደኞችን ፀበኛውን በቀላሉ ያሸንፈው ነበር፣ ሰክሮ ስለ ነበረ ግን በጣም ተደበደበ። ሌላ ሰው ባይገላግለው ኖሮ የበለጠ ጥቃት ይደርስበት ነበር።

በዚህ መጽሐፍ መግቢያ ላይ ያነበባችሁትን፣ ዘ ጐስት ኤንድ ዘ ዳርክነስ በተሰኘው ፊልም የሆነውን እውነተኛ ታሪክ እንደምታስታውሱ እርግጠኛ ነኝ። ስለ ሁለት ጐበዝ ሰዎች፣ ፓተርሰን ስለ ተባለው መሐንዲስና ከ130 ሰዎች በላይ የበሉትን ሁለት አንበሶች ስለ ገደለው ሬሚንግተን ስለ ተባለው የታወቀ አሜሪካዊ አዳኝ ነግሬአችሁ ነበር። መግቢያው ላይ ያልነገርኳችሁ መጨረሻው ላይ ሬሚንግተን ከአንበሶቹ በአንዱ ሕይወቱን ማጣቱን ነበር። ከብዙ ቀኖች ውጣ ውረድ በኋላ ሁለቱ ሰዎች የመጀመሪያውን አንበሳ ገደሉት። በዚያ ምሽት የደስ ደስ፣ ሬሚንግተን እስኪሰክር ድረስ ጠጥቶ ነበረ፣ ከዚያም የተነሣ ሁለተኛው አንበሳ ገደለው። ብዙም ሳይቆይ ፓተርሰን ጓደኛው እስኪሞት ድረስ ጉዳት ያደረሰበትን ሁለተኛውን አንበሳ ተኩሶ ገደለው።

ሬሚንግተን ከፍተኛ ችሎታ ያለው አዳኝ ነበር፣ ሆኖም ሰክሮ ስለ ነበር ችሎታው በጠላቱ ከመገደል አላስጣለውም። ከአንበሳው ዐቅም በጣም የሚበልጥ መሣሪያ ነበረው፣ ይሁን እንጂ፣ ንቁ አልነበረም፣ ስለዚህም ለሞት ካበቃው የአውሬው ጥቃት ራሱን መከላከል አልቻለም።

## መንፈሳዊ ስካር

በመንፈሳዊ ሕይወትም ተመሳሳይ ነገር ሊሆን ይችላል። ንቁ አእምሮ ከሌላቸው ሰዎች ጠላት በቀላሉ ይሰርቃል፣ ወይም እነርሱ ራሳቸውን ይገድላል። በጸጋ መሣሪያዎቻችን በደንብ ልንመታው ይገባል፣ ስካር ላይ ከሆንን ግን ማስተዋላችን ስለሚወሰድ በቀላሉ ያሸንፈናል።

ሰይጣን የሚውጠውን በመፈለግ ወዲያ ወዲህ እየዞረ እንደ ሆነ ጴጥሮስ ያስጠነቅቃል (1ጴጥሮስ 5፥8)። ትዕቢተኞችንና ሽክም የከበዳቸውን ሊውጣቸው ይችላል፣ ከሁሉም ይልቅ ለእርሱ በጣም ቀላል የሚሆንለት

የሰከረ አማኝን መዋጥ ነው፡፡ ጴጥሮስ ስለ አልኮል መጠጥ እየተናገረ ይሆን? ምናልባት ሊሆን ይችላል፣ ከዚያ የበለጠ ግን፣ በዚህ ዓለም ወይን ጠጅ ስለ ሰከረ አማኝ ነው የሚያመለክተው፡፡

የዮሐንስ ራእይ መጨረሻ አካባቢ ታላቂቱ አመንዝራ ባቢሎን ላይ ስለሚመጣው ፍርድ ዮሐንስ ይናገራል፡፡ መልአኩ እንዲህ ይለዋል፣

ና፣ በብዙ ውሆች ላይ የተቀመጠችውን የታላቂቱን አመንዝራ ፍርድ አሳይሃለሁ፡፡ የምድር ነገሥታት ከእርሷ ጋር አመነዘሩ፤ የምድር ነዋሪዎችም በዝሙቷ የወይን ጠጅ ሰከሩ፡፡ (ራእይ 17፥1-2)

ይህች አመንዝራ የምትወክለው ማንን እንደ ሆነ የተለያየ አመለካከት አለ፡፡ አንዳንዶች የካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን ናት ይላሉ፡፡ ሌሎች የሚያመለክተው የጥንቷ ባቢሎንን እንደ ሆነ ያምናሉ፤ አንዳንዶች ደግሞ የሮም ከተማን ወይም የሮም መንግሥትን እንደ ሆነ ያምናሉ፡፡

በበኩሌ፣ ‹‹ታላቂቱ አመንዝራ›› የዓለም ገንዘብ ሥርዐት እንደ ሆነ ነው የማምነው፡፡ ለዚህ እምነቴ አንዱ ምክንያት፣ ‹‹ታላቂቱ ባቢሎን፣ የአመንዝሮችና የምድር ርኩሰቶች እናት›› የሚለው ግንባሯ ላይ የተጻፈው የምስጢር ስም ነው (ራእይ 17፥5)፡፡ አንዳንድ ትርጉሞች የጸያፍ ነገሮች እናት ይላሉ፤ ሆኖም የጥንቷ ባቢሎን፣ ሮም፣ የሮም መንግሥት ወይም የካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን የምድር ርኩሰቶች ወይም ጸያፍ ነገሮች ሁሉ እናት ነበሩ ብዬ አላምንም፡፡ መጽሐፍ ቅዱስ፣ ‹‹የገንዘብ ፍቅር የክፋት ሁሉ ሥር ነው›› ይላል፤ ይህን የርኩሰቶችና ጸያፍ ነገሮች ሥር በማለት ብንተካው ከቃሉ ትርጉም አንወጣም፡፡ ይህ በሚገባ መረዳት ያለብን እንጂ፣ ረዘም ያለ ክርክር የሚያሻው አይደለም፡፡

የእኔ ዋናው ነጥብ የዚህ ዓለም ሥርዐት መንገዶች፣ ስሜቶችን የሚያሳስቱና የሚያሰክሩ መሆናቸው ነው፡፡ ከላይ ባለው የዮሐንስ ራእይ ክፍል ዮሐንስ፣ ‹‹የምድር ነዋሪዎችም በዝሙቷ ወይን ጠጅ ሰከሩ›› ማለቱን ልብ አድርጉ፡፡ አንድ ሰው በዓለም ሐሳብና ጭንቀት፣ ሀብትና ደስታ ከተወሰደ ከመንፈስ ቅዱስ ጋር ካለው ጥብቅ ኅብረት በቀላሉ ሊወጣ ይችላል፡፡ በጣም አሳሳች ሁኔታ ነው፤ ምክንያቱም አማኙ በዚህ ዓለም ምኞት ሰክሮ ቢሆን እንኳ፣ ከውጭ መንፈሳዊ ሊመስል ይችላል፡፡ አንድ ሰው መንፈሳዊ ማስተዋልን ካጣ፣ ለጠላት ስርቆት፣ ማታለል፣ ጥፋት ወይም ሞት በቀላሉ ዒላማ ሊሆን ይችላል፡፡

ሰሎሞን ላይ የደረሰው ነገር ለእንዲህ ዓይነቱ ስካር ጥሩ ምሳሌ ሊሆነን ይችላል፡፡ መንፈሳዊ ጥበብን በመፈለግ ጀምሮ ነበር፡፡ የፈለገውን

አገኘ፤ ሁሌም እንደሚሆነው ያ ጥበብ ታላቅ ስኬትና ሀብት እንዲያገኝ አስቻለው (ምሳሌ 8፥11-21 ይመ)፡፡ ይሁን እንጂ፣ በጊዜ ሂደት ሰሎሞን ከጥበብ ባገኘው ጥቅም ሰከረ፤ ያንን ጥበብ ከሰጠው ከእግዚአብሔር ላይ ዐይኑን አነሣ፡፡ በዚህ ዓለም ደስታ፣ ፍትወትና ብልጽግና ሰከረ፡፡ ስካር ውስጥ ሆኖ ባለበት ጊዜ ጤናማ አእምሮ በነበረው ጊዜ የማያደርገውን ሌላው ቀርቶ፣ የማያስበውን ነገር አደረገ – ሌሎችን አማልክት ማምለክ ጀመረ፡፡

ሰሎሞን ይህን ማድረጉ፣ በተለይም ሁለት ጊዜ እግዚአብሔር ከተገለጠለት በኋላ ይህን ማድረጉ በጣም ይገርመኛል፡፡ ይሁን እንጂ፣ ከላይ በገለጽኩት ብርሃን ነገሩን ካየነው በቀላሉ ልንረዳ እንችላለን፡፡ እኔና ሌሎች የኮሌጅ ጓደኞቼ በጣም ሰክረን በነበረ ጊዜ፣ ጤናማ አእምሮ ባለን ጊዜ የማናደርጋቸው ነገሮችን እናደርግ ነበር፡፡ ሰሎሞንም ከዚህ የተለየ አልነበረም፡፡

ከእንዲህ ያለ ውድቀት የምንጠበቀውና አእምሮአችን ንቁ እንደ ሆነ መቆየት የሚችለው እንዴት ነው? መልሱ፣ እውነተኛ እርካታ የሚሰጠውን ጌታን ዘወትር በመመገብና በመጠጣት የሚል ነው፡፡ ጳውሎስ፣ ‹‹በመንፈስ ተሞሉ እንጂ በወይን ጠጅ አትስከሩ›› ይላል (ኤፌሶን 5፥18)፡፡ እኛን ማስከርና የእግዚአብሔር መንገድ ላይ ከማተኮር ሊያዘናጉን ስለሚችሉ ነገሮችም ጭምር እንጂ፣ ጳውሎስ ስለ ወይን ጠጅ ብቻ እየተናገረ ነው ብዬ አላምንም፡፡ ከመጠን ባለፈ መልኩ በሥራ መጠመድ ሊሆን ይችላል፣ ተቃራኒ ጾታ፣ ስፖርት ወይም ሆቢ፣ ኢንተርኔት ሊሆን ይችላል፤ ዝርዝሩ ማለቂያ የለውም፡፡

በመሠረቱ እነዚህ ነገሮች በራሳቸው ምንም ጉዳት የለባቸውም፣ ምክንያቱም፣ ‹‹ደስ እንዲለን ሁሉን ነገር አትረፍርፎ የሚሰጠን›› እግዚአብሔር መሆኑን እናውቃለን (1ጢሞቴዎስ 6፥17)፡፡ መዝናናት፣ የአትሌቲክስ ውድድር፣ ምግብ፣ የተፈጥሮ ውበት ሌላው ቀርቶ የቴክኖሎጂ ውጤቶች እንኳ ጤናማና ተገቢ ናቸው፡፡ ይሁን እንጂ፣ ከራሱ ከእግዚአብሔር ይልቅ እርካታ የምናገኘው ከእነዚህ ነገሮች እስኪሆን ድረስ የምንጠመድባቸው ከሆነ፣ ስካር የሚያስከትሉ ሱሶች ይሆኑብናል፡፡

የመጀመሪያ ፍቅርና ናፍቆታችን ኢየሱስ መሆን አለበት፤ በመንፈስ ቅዱስ መሞላት አለብን፡፡

## በየጊዜው ምርመራ ማድረግ

ንቁነትን እንደ ጠበቁ ለመቀጠል፣ ከሚያሰክሩና ከሚያዘናጉ ከዚህ ዓለም ነገሮች ራሳችንን ለመከላከል ከተፈለገ - እያንዳንዱ ከእግዚአብሔር

የተወለደ ሰው፣ በየጊዜው ምርመራ ማድረግ አለበት፡፡ ‹‹ነፍሴ የምትራበውና የምትጠማው ማንን ነው?›› በማለት በቅንነት መጠየቅ አለብን፡፡ ይህን በተመለከተ የሚቻላችሁን ያህል ግልጽ ሁኑ እንጂ፣ መሸፋፈን አትሞክሩ፡፡ ነጻ ጊዜያችንን ሁሉ የሚይዘው ምንድነው? በሐሳብም ሆነ በድርጊት ዘወትር የምንሳበው ወዴት ነው? የእግር ኳስ ጨዋታ ከሆነ፣ እንደ መጠጥ ሁሉ የምትደግፋቸው ቡድኖችን አብዝታችሁ ትጠጣላችሁ፤ መዝናኛ ከመሆን አልፎ የሚያሰክር መጠጥ ይሆንባችኋል፡፡ በጣም የምትወዱት፣ ‹‹መጠጥ›› ተቃራኒ ጾታ ይሆን? አስተሳሰባችሁን የያዘው ብዙ ገንዘብ ማግኘት ይሆን? ያኔ ያሰከራችሁ ምን እንደ ሆነ ታውቃላችሁ፡፡ በዚህ ምክንያት የእግዚአብሔርን ቃል እንድናነብ፣ ትኩረታችንን እንድንሰጠውና እንድናሰላስለው ተነግሮናል፡፡ የምትጠሙት ብዙ ጊዜ የምትጠጡትን ነው፡፡ የምትራቡት ብዙ ጊዜ የምትመገቡትን ነው፡፡

ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት በነበርኩ ጊዜ የኮካ ኮላ ሱሰኛ የነበረ አንድ ቴኒስ አሠልጣኝ አውቅ ነበር፡፡ በቀን አንድ በመጠጣት ነበር የጀመረው፤ ከዚያ ወደ ሁለትና ሦስት ከፍ እያለ ሄደ፡፡ ከዚያ በየቀኑ አንድ አንድ ካዝና የሚጨርስበት ደረጃ ላይ ደረሰ፡፡ ሬፍሪጂሬተሩ በተከፈተ ጊዜ ሁሉ ውስጡ ሁለት ወይም ሦስት ካዝና ኮካ ኮላዎች ይታዩ ነበር፤ በሬፍሪጂሬተሩ ታችኛ ቦታ የተጠጡትን የሚተኩ ጥቂት ካዝናዎች ይቀመጡ ነበር፡፡

ከመጠን በላይ የወፈሩና አብዝተው ለስላሳ መጠጦችን በማዘውተራቸው የጤንነት ችግር የገጠማቸው ሰዎችን አይቻለሁ፡፡ ወጣት አማኝ ከነበርኩ ጊዜ ጀምሮ፣ ሰውነቴ የእግዚአብሔር ቤተ መቅደስ እንደ ሆነና በሚገባ የመያዝ ኃላፊነት እንዳለብኝ አውቅ ነበር፡፡ አንዳንድ ለስላሳ መጠጦች ውስጥ ያሉ ነገሮች ውስጤ እንዲገቡ ስላልፈለገሁ እነርሱን መጠጣት ማቆም እንዳለብኝ ወሰኜ ነበር፡፡ ግን፣ ቀላል አልነበረም! እኔ ራሴ እነዚህ ለስላሳ መጠጦችን መጠጣት እፈልግ ነበር፡፡ ለተወሰነ ጊዜ ራሴን መካድ ነበረብኝ፡፡

ኢየሱስ፣ ‹‹ሊከተለኝ የሚወድ ራሱን ይካድ›› ብሎ ነገሮናል (ማቴዎስ 16፥24)፡፡ ከስካር ነጻ ለመሆን፣ በጣም ከምንፈልገው ነገር ራሳችንን መካድ ይኖርብናል፡፡ ለለስላሳ መጠጥ የነበረኝን ከባድ ፍላጐት፣ ከዚያ በጣም በተሻለ ነገር - ሎሚ ባለበት አንድ ብርጭቆ ውሃ መተካት ነበረብኝ፡፡ ውሃ የመጠጣት ፍላጐት አልነበረኝም፤ ውሃም አይጠማኝም፤ ግን ለስላሳ መጠጥ አምጣ አምጣ ባለኝ ጊዜ በየቀኑ ብዙ ውሃ እንድጠጣ ተገድጄ ነበር፡፡ ዛሬ የትኞቹም ለስላሳ መጠጦች ትዝ አይሉኝም፡፡ ዛሬ የማዘወትረው ውሃን ነው!

የእግዚአብሔርን ቃል በተመለከተም የተለየ አይደለም፡፡ የኢየሱስ ቃሎች መንፈስና ሕይወት፣ እንዲሁም እውነት ናቸው፡፡ የእግዚአብሔር ቃል ፍላጐታችንን ለማቀጣጠል፣ አንዳንዴ ልብና ጥማታችን አቅጣጫውን እንዲስት ያደረጉ ነገሮችን በተመለከተ ራሳችንን መካድ ይኖርብናል፡፡ ለምሳሌ አብዛኛውን ሐሳቤንና ጊዜዬን የሚወስደው ሚዲያ መሆኑን ካወቅሁ፣ ሚዲያን እጾማለሁ፡፡ ለተወሰነ ጊዜ እዘጋውና ከእግዚአብሔርና ከቃሉ ጋር በማሳልፈው ምርጥ ጊዜ እተካዋለሁ፡፡ ከተለማመድኳቸው ትርጉም ያላቸውና ውጤታማ ጾሞች ጥቂቶቹ ከምግብ መጾም ሳይሆኑ፣ ከሚዲያ መጾም ነበሩ፡፡

በቃሉ ስንሞላና ስንታዘዘው፣ ምርጥ ጊዜያችንን ለጸሎት ስናውለውና እርሱ ለሚሰጠን ምሪት ስንታዘዝ፣ በመንፈስ ቅዱስ እንሞላለን፡፡ የባቢሎን ስካርና ሱስ ማነቆ ከእኛ ላይ ይነሣል፡፡ አንዳንድ ሰዎች በጣም የተለየን እንደ ሆንን ሊያስቡ ይችላሉ፤ እውነቱ ግን የአጠጣጥ ልማዳችንን መለወጣችን ብቻ ነው፡፡ ከእንግዲህ የምንፈልገው በእውነት የሚያረካውን፣ ብቃት ወይም ዐቅም የሚሰጠውንና ከእኛ ጋር የሚዘልቀውን መንፈሳዊ ወይን ጠጅ ብቻ ይሆናል፡፡

እንደዚያ ከሆነ ደግሞ ጥርት ባለ ሁኔታ እናስባለን፣ ትክክለኛ ውሳኔ እናደርጋለን፣ እኛን ለመዋጥ ጠላት ሲመጣ በቀላሉ እንለየዋለን፡፡ የእግዚአብሔርን ኪዳን ተስፋ ስለምናውቅና ስለምናውጅ ሰይጣን ንቁ አእምሮ ያለውን አማኝ በቀላሉ ማሸነፍ አይችልም፡፡ እኛ ንቁዎችና ጠንቃቆች ሆነናል፡፡ ታጥቀናል፤ ለውጊያ ዝግጁ ሆነናል፡፡

## ራስን መግዛት

1 ጴጥሮስ 5፥5-9 ላይ ጴጥሮስ፣ ‹‹ራሳችሁን የምትገዙ ሁኑ፤ ንቁም›› በማለት ይመክረናል፡፡ መጀመሪያውኑ ራሳችሁን ካልገዛችሁ መንቃት አትችሉም፤ ግን መንቃት የግድ ራስን መግዛትን አያመለክትም፡፡ ራስን መግዛት ንቁ አእምሮ ያለው አማኝ ሆን ብሎና ፈቅዶ የሚያደርገው ነው፡፡

ለአሁኑ ትምህርታችን በሚሆን መልኩ ራስን መግዛትን፣ ‹‹ሊመጣ የሚችልን አደጋ ወይም ችግር በጥንቃቄ መጠበቅ›› በማለት እንተረጕመዋን፤ ሌላ ትርጕም ደግሞ፣ ‹‹የነቃና ቁልጭ ያለ፣ ያለ እንቅልፍ የሚጠብቅ›› ይላል፡፡ ይህ አተረጓጐም እያንዳንዱ የክርስቶስ ተከታይ ያለበትን ሁኔታ ማመልከት አለበት፡፡ ራስን መግዛት፣ ታጥቆ ለመገኘት ሌላው በጣም አንገብጋቢና አማራጭ የሌለው ነገር ነው፡፡

ከጥቂት ምዕራፎች በፊት በሒትለር ዘመን ናዚ ጀርመን ውስጥ ስለ ነበረው ሕይወት የጨረፍታ ያህል አይተን ነበር፡፡ በእነዚያ አስፈሪ ጊዜዎች አስተዋይ አይሁድ ነቅተው እንደ ኖሩ ሁሉ፣ አማኝም እያንዳንዱን ቀን ራሱን በመግዛት መኖር አለበት፡፡ የሚውጠውን በመፈለግ ዲያብሎስ ወዲያ ወዲህ እያለ ስለሆነ፣ በዙሪያችን አደጋ አለ፡፡ ሆኖም፣ በናዚ አገዛዝና አሁን እኛ ባለንበት ዓለም መካከል ትልቅ ልዩነት አለ - አይሁድ ሒትለር ላይ ሥልጣን አልነበራቸውም፤ እኛ ግን በጠላታችን ላይ ሥልጣን አለን፡፡ ጠላታችን ዓለምን እየገዛ ነው፤ እኛን ግን አይገዛንም፡፡ ይሁን እንጂ፣ በሚቻለው ሁሉ ይዋጋል፤ ችላ ካልነው ሊውጠን ይችላል፡፡ በዚህም ምክንያት ሐዋርያው ጳውሎስ እኔና እናንተን፣ ‹‹…ነቅታችሁ በትጋት ጸልዩ›› በማለት ይመክረናል፤ (ቈላስይስ 4፥2)፡፡

የምንነቃበት አንዱ ዋነኛ መንገድ በጸሎት አማካይነት ነው፡፡ ጸሎት ለመንፈሳዊ ነገር ዐይናችንን ስለሚከፍት፣ ከተፈጥሮአዊው ባሻገር አልፈን ማየት እንድንችልና በእውን ከመከሰቱ በፊት አደጋንና ጥቃትን ማወቅ እንድንችል ያደርገናል፡፡ ይህ እውነት ኢየሱስ ከመሰቀሉ በፊት በነበረው ምሽት በግልጽ ታይቷል፡፡

የምንነቃበት አንዱ ዋነኛ መንገድ በጸሎት አማካይነት ነው፡፡

የመጨረሻውን ራት እየበሉ እያለ ኢየሱስ ከጥቂት ጊዜ በኋላ የሚደርስበትን ከባድ ስቃይ በመንፈሱ አውቆ ነበር፡፡ በዚያ ጊዜ ምንም የሚያሰጋ ነገር አልነበረም፤ ሁሉም ሰላም ነበር፤ ግን እርሱ እየመጣ ያለውን በሚገባ ማየት ችሎ ነበር፡፡ ከራት በኋላ ደቀ መዛሙርቱን ይዞ ወደሚያዘወትረው የጸሎት ቦታ፣ ወደ ጌቴሴማኒ የአትክልት ቦታ ሄደ፡፡ ‹‹ነፍሴ እስከ ሞት ድረስ እጅግ አዝናለች፤ ከእኔ ጋር በመትጋት በዚህ ቆዩ›› በማለት ለጴጥሮስ፣ ለያዕቆብና ለዮሐንስ ነገራቸው (ማቴዎስ 26፥38)፡፡ ጌታ፣ ‹‹ከእኔ ጋር በመትጋት›› ማለቱን ልብ አድርጉ፡፡ ለትጋት ወይም ራስን ለመግዛት ከሰጠነው ትርጉም አንዱ፣ ‹‹ሊመጣ የሚችል አደጋን ወይም ችግር በጥንቃቄ መጠበቅ›› የሚል ነበር፡፡ ኢየሱስ ቀድሞውኑ እንደ ተጋ ነበር፤ ሆኖም ሊመጣ ያለውን አደጋ ማስጠንቀቂያ ምልክት ደቀመዛሙርቱ እንዳላወቁና በዚህም ምክንያት ችላ እንዳሉት ኢየሱስ በሚገባ ተረድቶ ነበር፡፡

ነፍሱ፣ ‹‹እጅግ አዝና›› እንደ ነበርና፣ በዚያም ውስጥ የሚያተጋው ዋና ምስጢር መኖሩን ኢየሱስ ተናገረ፤ ምስጢሩም ጸሎት ነው፡፡ ቀጣይና መደበኛ ጸሎት በመንፈሳዊው ዓለም እየሆነ ያለውን እንድታውቅ ነፍሳችሁን ያነቃታል፡፡ ያኔ ማስጠንቀቂያውን እንሰማለን፣ እንተረጉመዋን፣ በተገቢው

ሁኔታ እንዘጋጃለን፡፡ ጸሎት ከጠላት ቀድሞ ለመገኘት እጅግ አስፈላጊ ነገር ነው፡፡

## የማስጠንቀቂያ ምልክት

እኔና ሊዛ በተጋባን በመጀመሪያዎቹ ዓመቶች አንዳንድ ችግሮች ነበሩብን፡፡ ሁለታችንም አዳዲስ ክርስቲያኖች ነበርን፤ በዚህ ላይ ከትውልድ ትውልድ ሲደጋገሙ የኖሩ ችግሮች ነበሩብን፡፡ የሊዛ ቤተ ሰብ የፀብ፣ የፍቺና ብዙ የትዳር ጓደኞችን የመያዝ ታሪክ ነበረው፡፡ ሰይጣን በቤተ ሰቡ የዘር ሐረግ የነበረውን ምሽግ እንደ ያዘ ለዓመታት ዘልቆ ነበር፤ ስለዚህ የእኔና የሊዛ ትዳርም ላይ ብዙ ጥቃቶች ይደርሱ ነበር፡፡

በእያንዳንዱ ቀን በትንሹ አንድ አንዳንዴም እስከ ሁለት ሰዓት በጸሎት አሳልፍ ነበር፤ ከዚህም የተነሣ በመንፈሳዊው ክልል እየሆኑ ላሉ ነገሮች ንቁ እየሆንኩ መጣሁ፡፡ አልፎ አልፎ መላው እኔነቴ ውስጥ እጅግ ከባድ ሐዘን ይሰማኝ ነበር፤ ይህ ደግሞ አንድ ከባድ ችግር እየመጣ መሆኑን ለልቤ የሚናገር ማስጠንቀቂያ ነበር፡፡ ለመግለጽ ከባድ እንደሆነ አውቃሁ፤ ግን፣ የሚቀረጣጥም፣ የሚያደቅና ውስጤን የሚቃጥል ዐይነት፣ ‹‹ሐዘን›› ነበር ቢባል ትክክል ሊሆን እንደሚችል አስባለሁ፡፡

እንዲህ ያለ ነገር ሲጀምረኝ፣ መጀመሪያ ላይ ለምን እንደዚያ እንደሚሆን አይገባኝም ነበር፡፡ ሁሉም ነገር መልካም ነበር፤ ምንም ውጫዊ የአደጋ ምልክት አልነበረም፤ ነገሮች ጥሩ እየሄዱልን ነበር፡፡ በመጀመሪያዎቹ ጥቂት ጊዜዎች ያ የሐዘን ስሜት ሲወርረኝ ባለ ማወቅ ችላ ብየው ነበር፡፡ ይሁን እንጂ፣ ብዙውን ጊዜ ከጥቂት ጊዜ በኋላ ትዳራችን ላይ የገሃነም የሚመስል ጥቃት ይደርስ ነበር፡፡ በትንሹ በትልቁ እንከራከራለን፣ እንጣላለን፣ ለመፈወስ ጥቂት ቀኖች፣ ሳምንቶች አንዳንዴም ወሮች በሚወስድ ሁኔታ መጥፎ ቃላት እንነጋገራለን፡፡

በጊዜ ብዛት ይህን አጉል ልማድ ማስተዋል ጀመርኩ፤ ስለዚህም፣ ውጫዊ ሁኔታው የቱንም ያህል መልካም ቢመስልም፣ ይህ የሐዘን ስሜት ሲመጣ፣ ከአካባቢው ዘወር ብዬ ስለ ትዳራችን አጥብቄ የመጸለይን ልምድ አዳበርኩ፡፡ እውነት ለመናገር፣ ያም ሆኖ እንኳ፣ ዲያብሎስ ማጥቃቱን በቀላሉ አያቋርጥም ነበር፤ ይሁን እንጂ፣ አስቀድሞ በጸሎት አጥብቄ እቃወመው ስለ ነበር፤ ጥቃቱ ብዙም ሳይቆይ ይቆም ነበር፣ ከጥቃቱ በኋላ የሚመጣ ድቀትም አይሰማኝም ነበር፤ አንዳንዴ ቢኖር እንኳ፣ በጣም ትንሽ ነበር፡፡

በዚህ ዘመን እኔና ሊዛን ጠላት በቀላሉ ወይም ዘወትር አያጠቃንም፡፡ ጥቃት ማድረስ በሞከረ ቁጥር፣ በአፀፋው በ‹‹መንፈስ ሰይፍ›› መጠቃቱ የታከተው ይመስላል፡፡ ይህን ስል፣ በተሳሳተ መንገድ እንዳትረዱኝ እፈልጋለሁ፤ አሁንም ቢሆን እኔና ሊዛ እንደ ቀድሞ ሁሉ በንቃትና በትጋት ነው የምንኖረው፡፡ የሆነው ይሁን በሚል ዐይነት ስሜት በቸልታ አንኖርም፡፡ ዛሬም ቢሆን በዓላማ ጠላትን በጸሎት እንቃወማለን፤ በተጋባን ጊዜ መጀመሪያ ላይ እንደ ነበረው ዘወትር ጥቃት አይደርስብንም፡፡

ከዚያ ውጣ ውረድ ያገኘነው በጣም ጠቃሚ ትምህርት፣ የጠላት ጥቃት ሊመጣ እንደ ሆነ የሚጠቁሙ የማስጠንቀቂያ ምልክቶችን መረዳት ነበር፡፡ በማንኛውም የሕይወት ገጽታችን ንቁ የመሆንን አስፈላጊነት፣ ገንዘባችን፣ ጤናችን፣ ግንኙነታችንና አገልግሎችን ላይ ጥቃት ከመምጣቱ በፊት ልባችን ውስጥ የሚፈጠረውን ሐዘን ለይተን መረዳትን ተምረናል፡፡ ቅድመ ማስጠንቀቂያዎችን በተመለከተ ብዙውን ጊዜ ምንነቱን ለይቼ ማወቅ ስለማልችል መንፈስ ቅዱስ እንዲረዳኝ መጠየቅን ተምሬአለሁ፡፡ እርሱ ብዙ ጊዜ ረድቶኛል፤ እናንተንም ሊረዳችሁ ይችላል፡፡ እርሱ ረዳታችሁ ነው! ራሳችሁን ከሰጣችሁት፣ በውስጣችሁ ሆኖ እስከ መጸለይ ድረስ እንኳ ይረዳችኋል፡፡ መጽሐፍ ቅዱስ እንዲህ የሚል የተስፋ ቃል አለው፣

> እንዲሁም ደግሞ መንፈስ በድካማችን ያግዘናል፤ እንዴት መጸለይ እንደሚገባን አናውቅም፤ መንፈስ ግን በቃላት ሊገለጥ በማይችል መቃተት ለእኛ ይማልድልናል፡ ልባችንንም የሚመረምረው እርሱ የመንፈስን ሐሳብ ያውቃል፤ ምክንያቱም መንፈስ እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ ለቅዱሳን ይማልዳልና፡፡ (ሮሜ 8፥26-27)

ይህ መቃተት ከመሰቀሉ በፊት በነበረው ሌሊት፣ በአትክልት ቦታው ኢየሱስ ላይ የደረሰውን የመሰለ በጥልቅ ነፍሳችን ውስጥ የሚሰማን ሐዘን ነው፡፡ ያ ሐዘን ሲመጣ ምላሽ መስጠት አለብን፡፡ የትጋት ተቃራኒ የሆነው ስንፍናን መምረጥ እንችላለን፤ በተደጋጋሚ ችላ በማለት ወይም በውስጣችን በማመቅ ያንን ሐዘን መቆጣጠርን ልንመርጥ እንችላለን፡፡ ወይም ደግሞ በጸሎት መትጋትና ራሳችንን ለእግዚአብሔር መንፈስ ማስገዛት እንመርጣለን፡፡

የመንፈስ ቅዱስ ዓላማ በውስጣችን ሆኖ ከመቃተት አልፎ፣ ፊት ለፊታችን ያለውን ሁኔታ የምንቃወምበት ግልጽ ቃል ለእኛ መስጠት ነው፡፡ ጳውሎስ፣ ‹‹በመንፈስ (ውስጤ ባለው መንፈስ ቅዱስ) እጸልያለሁ፤ በአእምሮ (በማስተዋል) እጸልያለሁ›› ይላል (1ቆሮንቶስ 14፥15)፡፡

## ትጉና ጸልዩ

ውስጡ ስለ ነበረው ጥልቅ ሐዘን ወይም መቃተት ለደቀ መዛሙርቱ ከነገራቸው በኋላ ኢየሱስ፣ ‹‹ከእኔ ጋር በመትጋት በዚሁ ቆዩ›› ብሏቸው ነበር (ማቴዎስ 26፥38)፡፡ ከዚያም ከሦስቱ ደቀ መዛሙርት ጥቂት ፈቀቅ ብሎ ለአንድ ሰዓት ጸለየ፡፡

ተመልሶ ሲመጣ፣ ተኝተው አገኛቸው፡፡ ለመሆኑ እንዴት ሊተኙ ቻሉ? በጣም መሽቶ ስለ ነበር ይሆን? ወይም በቀን ውሎአቸው በጣም ደክሞአቸው ስለ ነበር ይሆን? ወይስ ከመጠን በላይ እስኪጠግቡ ድረስ ከመጨረሻው ራት ስለ ተመገቡ ይሆን? የሉቃስ ወንጌል የተኙበትን ምክንያት ይነግረናል፡፡ ‹‹ከጸሎትም ተነሥቶ ወደ ደቀ መዛሙርቱ መጣ፤ እነርሱም *ከሐዘን የተነሣ* ተኝተው አገኛቸው›› (22፥45)

እነርሱ ራሳቸውም ላይ ጥቃት ሊደርስ በመሆኑ፣ ኢየሱስ ላይ የደረሰው ዓይነት ጥልቅ ሐዘን ተሰምቷቸው ነበር፡፡ የመጨረሻውን ራት እየበሉ እያለ ጴጥሮስ ጌታን ከመካድ ሞትን እንደሚመርጥ በድፍረት ተናግሮ ነበር፡፡ ጴጥሮስ እስከ መጨረሻ ጸንቶ እንደሚቆም የተማመነው በራሱ ችሎታ ነበር፡፡ ሌሎች ደቀ መዛሙርትም እንዲሁ ለጌታቸው በታማኝነት እንደሚጸኑ ተናግረው ነበር፡፡ ያም ሆኖ ግን፣ ለእግዚአብሔር አባቱ ታማኝ ከመሆኑ የተነሣ እርሱ ላይ ከባድ ፈተና እንደሚመጣ ብቻ ሳይሆን፣ ለእርሱ ታማኝ ሆነው እንዳይገኙ ደቀ መዛሙቱም ላይ ከባድ ፈተና እንደሚደርስ ኢየሱስ ያውቅ ነበር፡፡

እንቅልፍ ላይ ለነበሩት ደቀ መዛሙርቱ ኢየሱስ የተናገረውን ስሙ፣

> ከዚያም ተመልሶ ወደ ደቀ መዛሙርቱ ሲመጣ ተኝተው አገኛቸው፤ ጴጥሮስንም እንዲህ አለው፤ ‹‹እናንተ ሰዎች ከእኔ ጋር ለአንድ ሰዓት እንኳ መትጋት አቃታችሁን? ወደ ፈተና እንዳትገቡ ትጉና ጸልዩ፤ መንፈስ ዝግጁ ነው፤ ሥጋ ግን ደካማ ነው፡፡›› (ማቴዎስ 26፥40-41)

እዚህም ላይ ለእግዚአብሔር በመታዘዝ ጸንቶ መቆምን ወይም ደግሞ ፍላጐቱ ቢኖር እንኳ፣ ያንን ማድረግ አለመቻልን በተመለከተ ቁልፍ የሆነ ጉዳይ አለ፡፡ በጸሎት በመትጋት ብርታት ማግኘት ይቻላል፡፡ ሐዋርያው ይሁዳ፣ ‹‹እናንተ ግን ወዳጆች ሆይ፣ እጅግ ቅዱስ በሆነው እምነታችሁ ራሳችሁን ለማነጽ ትጉ፤ በመንፈስ ቅዱስም ጸልዩ›› ይላል (ቁጥር 20)፡፡ ጸሎት ቅብጥብጥ ሥጋችንን ጸጥ ያሰኛል፤ ውስጣዊ ሰውነታችንን ያንጻል ወይም ይገነባል፡፡

ሥጋችን ደካማ ነው፤ እርሱ ሁሌም የሚፈልገው ምንም ተቃውሞ የሌለበትን መንገድ ቢሆንም፣ ብዙ ጊዜ ያ መንገድ የተሳሳተ መንገድ ነው፡፡ ሥጋችን የዚህ ዓለም ኃይላት የሚያስነሡትን ማዕበል መዋጋት አይፈልግም፡፡ በሌላ በኩል ግን ጸሎት የሥጋን ፍላጐት መግዛት እንዲቻል፣ ውስጣዊ ብርታታችን ያንጻል ወይም ይገነባል፡፡ በሕይወት ከመታከት ወይም ከመዛል ይጠብቀናል፡፡ ኢየሱስ፣ ‹‹ደቀ መዛሙርቱ ሳይታክቱ (ሳይዝሉ) ሁልጊዜ መጸለይ›› እንዳለባቸው ተናግሮአል (ሉቃስ 18፥1)፡፡ በሌላ አነጋገር የማንጸልይ ከሆነ፣ ሐዘን (መቃተት) ወደ እኛ በሚመጣ ጊዜ እንታክታለን፤ እንዝላለን ማለት ነው፡፡

በዚያ የአትክልት ቦታ ደቀ መዛሙርቱን የገጠማቸውም ይህ መታከትና ዝለት ነበር፡፡ መጸለይ ሲገባቸው ተኝተው ነበር፡፡ እያንዣበበ ለነበረው አደጋ አልነቁም፡፡ ሰነፎች እንጂ ትጉዎች አልሆኑም፡፡

በዚህ ዘመን እኔና እናንተ የመንፈስን ማስጠንቀቂያ ፀጥ የምናደርግበት ወይም የምናምቅበት ሌሎች መንገዶች አሉን - ቴሌቪዥን እንከፍታን፣ መዝሙር እንሰማለን፣ ከጓደኞቻችን እንደዋወላለን፣ የትም መድረስ በሚችለው ሞባይላችን ፌስ ቡክ እናያለን፤ የኮምፒዩተር ጨዋታ እንጫወታለን፣ ራሳችንን በሥራ እንጠምዳለን ወይም ወጣ ብለን ሥጋችንን የሚመግብ ነገር እንቀማምሳለን፡፡ መንፈስ ቅዱስ ለሚሰጠን ምሪትና ማስጠንቀቂያ የበለጠ እየደነዘዝንና ንቁ ከመሆን እየራቅን ሄደናል፡፡ ከዚህም የተነሣ መከራ ወይም ችግር ሲመጣ፣ ጸንቶ የመቆም ብርታት እናጣለን፡፡ በእግዚአብሔር ጸጋ በኩል በነጻ የሚገኘው የሚያጸና ኃይል አይኖረንም፡፡

‹‹ወደ ፈተና እንዳትገቡ ትጉና ጸልዩ›› በማለት ኢየሱስ ይቀርቡት ለነበሩ ወዳጆቹ የመከረው በዚህ ምክንያት ነበር (ማቴዎስ 26፥41)፡፡ ከእነርሱ ጥቂት ራቅ ብሎ በመሄድ ለሁለተኛ ሰዓት ጸለየ፤ ከዚያ ሲመለስ አሁንም ተኝተው አገኛቸው፡፡ በዚህ ጊዜ አልቀሰቀሳቸውም፤ ማስጠንቀቂያም አልሰጣቸውም፤ የራሳቸውን ምርጫ አድርገዋል፡፡

ብዙ ጊዜ እግዚአብሔር አንዴ ወይም ሁለቴ ያስጠነቅቀናል፤ ማስጠንቀቂያዎቹን ችላ ካልናቸው ግን በንስሐ እስክንመለስ ድረስ ዝም ይለናል፡፡ ዙሪያችንን ችግር ሲከበን ወይም ያልጠበቅነው ነገር ድንገት ሲደርስብን በመደናገጥ፣ ‹‹እግዚአብሔር ሆይ፣ ምነው?›› በማለት እንጠይቃለን፡፡ እንደ እውነቱ ከሆነ ግን፣ እርሱ አስጠንቅቆን ነበር፤ እኛ ግን ለመስማት ፈቃደኞች አልነበርንም፡፡

ኢየሱስ እንቅልፍ ላይ ከነበሩት ደቀ መዛሙርት ጥቂት ፈቀቅ ብሎ ለሦስተኛ ሰዓት ጸለየ፡፡ ጸሎቱን ጨርሶ ሲመጣ አሁንም እንደ ተኙ ነበሩ፡፡ አሳልፎ የሰጠው ይሁዳና የአይሁድ ሸንጎ ጥበቃዎች ወደ አትክልት ቦታው መጥተው ኢየሱስን ያሰሩት ያኔ ነበር፡፡

## በስኬትና በውድቀት መካከል ያለ ልዩነት

በጸሎት በመትጋቱና ንቁ ሆኖ በመገኘቱ ኢየሱስ እስከ መጨረሻው ጸና፤ የመጣበትን አገልግሎትም ፈጸመ፡፡ በሌላ በኩል ደቀ መዛሙርቱ ጸንተው ለመቆም የነበራቸውን ፍላጐት ገልጠው ነበር፤ ያን ማድረግ እንደሚችሉም አስበው ነበር፤ ሆኖም ብርታቱ አልነበራቸውም፡፡ እያንጓንጓቸው እንደሚጠቁና እንደሚወድቁ ኢየሱስ አመልክቶ ነበር፤ ‹‹በዚያን ጊዜ ደቀ መዛሙርቱ ሁሉ ጥለውት ሸሹ›› (ማቴዎስ 26÷56)፡፡ ጴጥሮስ፣ በጭራሽ አላደርገውም ቢልም የተናገረውን ነበር ያደረገው - ኢየሱስን ካደ፡፡ ጴጥሮስን በተመለከተ አንድ ጥሩ ነገር ሊባል ይችላል፡፡ ሌላው ቢቀር ለምርመራ በተወሰደ ጊዜ፣ ኢየሱስን ተከትሎ ሄዶ ነበር፡፡ ዮሐንስን ሳይጨምር፣ ሌሎቹ ደቀ መዛሙርት ግን ሕይወታቸውን ለማዳን ወዲያውኑ ከአትክልቱ ቦታ ሸሽተው ሄዱ፡፡

አማኞች መልካም ምኞታቸውን ሲናገሩና በተግባር ግን ሳያውሉት ሲቀሩ ያየነው ስንት ጊዜ ይሆን? ለምን እንደዚያ ሆነ? ምክንያቱም አትክልቱ ቦታ እንደ ነበሩት ደቀ መዛሙርት ሁሉ እነርሱም በጸሎት ባለ መትጋታቸው ነው! መንፈሳቸው ፈቃደኛ ነው፤ ሥጋቸው ግን ደካማ ነው፡፡ በሚገባ አለመታጠቃቸው ያሰቡት ፍጻሜ ላይ እንዳይደርሱ አደረጋቸው፡፡

ለመሆኑ፣ ከሐዋርያው ጴጥሮስ ሌላ፣ ‹‹ራሳችሁን አስታጥቁ›› ብሎ ለመምከር የተሻለ ሰው ማን ነው? በዚያ የመከራ ሌሊት፣ በአንደበቱ ብርቱ ነበር፤ በተግባር ግን ወድቋል፡፡ ‹‹ስምዖን፣ ስምዖን ሆይ፣ እነሆ፣ ሰይጣን እንደ ስንዴ ሊያበጥራችሁ ለመነ›› በማለት ኢየሱስ በተለይ ጴጥሮስን አስጠንቅቆት ነበር (ሉቃስ 22÷31)፡፡ ሆኖም፣ ጴጥሮስና ሌሎቹ ደቀመዛሙርት በዚያ ሌሊት ጸንተው መቆም የሚያስችላቸው ብርታት አልነበራቸውም፡፡ ስለዚህም በኃለኛው ሕይወቱ ለአንድ ሌሊት፣ ወይም ለአንድ ወቅት፣ ወይም ለጠቅላላው የሕይወት ዘመናችን መጽናት ከፈለገን፣ ራሳችንን ማስታጠቅ እንዳለብን እኔና እናንተን ያስጠነቅቃል፡፡

ራሳችንን ለውጊያ ማስታጠቅ፣ ንቃትና ትጋትን ይጠይቃል፡፡ የዚህ ዓለም ማባበል ማስተዋላችንን እንዲያደነዝዝ ወይም በሁሉም ነገር ክርስቶስን ለመምሰል ከመሰጠት እንዲያዘናጋን አንፍቀድለት፡፡ ምንጊዜም ንቁዎችና

ትጉዎች መሆን አለብን፤ እኛን መዋጥ የሚፈልገው ዲያብሎስን በጽናት ካልተዋጋን መጨረሻችን አያምርም፡፡

# 13

# ዲያብሎስን ተቃወሙት

*ራሳችሁን የምትገዙ ሁኑ፤ ንቁም፤ ጠላታችሁ ዲያብሎስ የሚውጠውን በመፈለግ እንደሚያገሣ አንበሳ ወዲያ ወዲህ ይዞራል፡፡ በእምነት ጸንታችሁ ተቃወሙት፡፡*

*1 ጴጥሮስ 5፥8-9*

አሁን በቀጥታ ውጊያውን በተመለከተ ጴጥሮስ ምክር ወደሚሰጥበት ክፍል መጥተናል፡፡ ዲያብሎስ፣ (ማንኛውንም ሰራዊቱን ጨምሮ) የሚውጠውን እንደሚፈልግ አንበሳ እንደ ሆነ ይናገራል፡፡

ግልጽ ለማድረግ ያህል አንበሳ ዲያብሎስን አይወክልም፤ ቅዱሳት መጻሕፍት ውስጥ ዲያብሎስ እባብ፣ ዘንዶ፣ ሌባ እና በሌሎችም ጥቂት ስሞች ቢጠራም፣ አንበሳ ተብሎ አያውቅም፡፡ እውነተኛው አንበሳ፣ ‹‹ከይሁዳ ነገድ የሆነው አንበሳ›› ኢየሱስ ነው (ራእይ 5፥5)፡፡ ይሁን እንጂ፣ ዲያብሎስ የሚውጠውን እየፈለገ እንደሚዞር የተራበ አንበሳ እንደ ሆነ ጴጥሮስ ያመለክታል፡፡ ዕድሉን ካገኘም እጁ የገባውን ሁሉ ያለ ምሕረት ይውጣል፡፡ እዚህ ላይ እንዳትሳሳቱ፡፡ እርሱ የተሸነፈ ጠላት ነው፤ ሆኖም በቸልታ መታየት የሌለበት፣ ምሕረት የማያውቅ ባላጋራ ነው፡፡ ምንም ርኅራኄ ወይም አዘኔታ የለውም፤ ዓላማው መግደል፣ መስረቅና ማጥፋት ነው፡፡

ሰው በላ አንበሶች ባሉበት፣ የታንዛንያ ሜዳማ ቦታዎች ሄዳችሁ ቢሆን ኖሮ፣ መሣሪያ ሳትይዙ በዚያ አካባቢ አትንቀሳቀሱም ነበር፡፡ አስተዋይ ከሆናችሁ ጥሩ ጠመንጃ ትይዛላችሁ፤ እንዴት እንደምትጠቀሙበትም ትማራላችሁ፡፡ ከታጠቃችሁ፣ ንቁና ትጉዎች ከሆናችሁ፣ ለመዋጋትም፣ ለማሸነፍም ዝግጁ ናችሁ ማለት ነው፡፡ ምንም ጉዳት አይደርስባችሁም፡፡ ጴጥሮስ አጽንዖት የሚሰጠው ለዚሁ ጉዳይ ነው፡፡

## ዲያብሎስን ተቃወሙ

ቁጥር 9 ላይ ጴጥሮስ ዲያብሎስን እንድንቃወም አጥብቆ ይመክረናል፡፡ መቃወም ለሚለው ቃል ግሪክኛው ኡቲስቴሚ (authistemi) ነው፡፡ ቴይርስ በዚህ መንገድ ይተረጉመዋል፣ ‹‹ራስን በተቃራኒ ማድረግ፣ መቋቋም፣ መቃወም፡፡›› ስትሮንግም፣ ‹‹በተቃውሞ መቆም›› የሚል ይጨምርበታል፡፡ እኔ እጅ ያለ አንድ መዝገበ ቃላት መቃወምን ‹‹በቃልም ሆነ በተግባር መከላከል›› በማለት ይተረጉመዋል፡፡ ቃሉ ታላቅ ግጭት የሚያመለክት መሆኑ የሚያጠያይቅ አይደለም፡፡

ሆኖም፣ ውጊያ ላይ ያለን እንደ መሆኑ መጠን ኢየሱስ የሰጠንን ተስፋ ቃል ስሙ፣ ‹‹እንግዲህ... በጠላትም ኃይል ሁሉ ላይ ሥልጣን ሰጥቻችኃለሁ፤ የሚጐዳችሁም አንዳች ነገር አይኖርም (ሉቃስ 10፥19)፡፡ በጣም ልብ የሚነካ አይደለም? ብርቱ በሆነ ጸጋው ከተመላለሳችሁ ምንም ነገር፣ ሌላው ቀርቶ ዲያብሎስ ራሱ እንኳ ሊጐዳችሁ እንደማይችል የእግዚአብሔር ተስፋ ቃል ያረጋግጥላችኃል! ልብ ልናደርገው የሚገባ ቃል ነው፡፡

ይሁን እንጂ፣ በተሰጣችሁ ኃይል መጠቀም ይኖርባችኃል፡፡ እንደዚያ ካላደረጋችሁ የተስፋ ቃሉ ውጤታማ አይሆንም፤ እናንተም ትጐዳላችሁ፡፡ በዚህ ምክንያት ነው ጴጥሮስ ዲያብሎስን እንድንቃወም የሚመክረን፡፡ ‹‹ከፊታችሁ ዘወር እንዲያደርገው ወደ እግዚአብሔር ጸልዩ›› አላለንም፡፡ በቀጥታ፣ በድፍረትና በዓላማ ልንቃወመው ይገባል፡፡

አዲስ ኪዳን ውስጥ በየትኛውም ክፍል፣ እግዚአብሔር ዲያብሎስን ከሕይወታችን ዘወር እንዲያደርገው እንድንጠይቅ የሚናገር ቃል የለም፡፡ እግዚአብሔር ያንን አያደርግም! እግዚአብሔርን በተመለከተ እርሱ እንደዚያ አያደርግም ማለቴ ምናልባት አንዳንዶቻችሁ ግር ሊላችሁ እንደሚችል አስባለሁ፡፡ ግን እውነት ነው፡፡ እግዚአብሔር ለሰው ልጅ በምድር ላይ ሥልጣን ሰጥቶታል፤ የገዛ ራሱን ቃል የሚቃረን ነገር አያደርግም፡፡ ኤደን ገነት ውስጥ ሰይጣን አዳምን ባሳሳተ ጊዜ እንደዚያ ያላደረገው በዚህ ምክንያት ነበር፡፡ ዲያብሎስን ለማሸነፍ ኢየሱስ የሰው ልጅ ሆኖ ወደ ምድር የመጣው በዚህ ምክንያት ነበር፡፡ የክርስቶስ አካል የሆነችው ቤተ ክርስቲያን ሰይጣንና ሰራዊቱን በቀጥታ መዋጋት ያለባት በዚህ ምክንያት ነው፡፡

በዐዋጅ ደረጃ፣ እግዚአብሔር ለኢየሱስ ሥልጣንን ሁሉ ሰጥቶታል፤ ኢየሱስ ደግሞ በተራው ለእኛ ሰጥቶናል፡፡

በዐዋጅ ደረጃ፣ እግዚአብሔር ለኢየሱስ ሥልጣንን ሁሉ ሰጥቶታል፤ ኢየሱስ ደግሞ በተራው ለእኛ ሰጥቶናል፡፡ የእርሱ አካል እንደ መሆናችን መጠን፣ እኛ መዋጋት አለብን፤ ሆኖም መጽሐፍ ቅዱስ እንደሚነግረን ውጊያው፣ ‹‹መልካም ገድል (ውጊያ) ነው›› (1ጢሞቴዎስ 6፥12 ይመ)፡፡

## ዐይነተኛ ምሳሌያችን

በእንዴት ዐይነት ሁኔታ ዲያብሎስን እንደምንዋጋ መማር ካለብን፣ ከኢየሱስ የተሻለ ከማን መማር እንችላለን? በበረሓ በነበረ ጊዜ ከተፈጸመው ሁኔታ ብዙ መማር እንችላለን፡፡

> ኢየሱስ በመንፈስ ቅዱስ ተሞልቶ ከዮርዳኖስ እንደ ተመለሰ መንፈስ ወደ በረሓ ወሰደው፤ በዚያም ዐርባ ቀን በዲያብሎስ ተፈተነ፡፡ (ሉቃስ 4፥1-2)

የዲያብሎስ ፈተና ዐርባ ቀን ሙሉ ነበር የቀጠለው፡፡ ያም ማለት ኢየሱስ አጥብቆ መዋጋት ነበረበት ማለት ነው፡፡ በጽሑፍ በሰፈረው መሠረት ኢየሱስ ከሰይጣን ጋር በመጀመሪያ የተጋፈጠው በዐርባኛው ቀን መጨረሻ ላይ ሲሆን፣ ያም የእግዚአብሔር ልጅ መሆኑን ለማሳየት በመለኮታዊ ኃይሉ እንዲጠቀም ለማነሣሣት የተደረገ ሙከራ ነበር፡፡ በዚያ ጊዜ ኢየሱስ ርቦት ነበር፤ ስለዚህም ጠላት ድንጋዩን እንጀራ እንዲያደርግ ጠየቀው፡፡ ኢየሱስ ግን፣ ‹‹ሰው ከእግዚአብሔር አፍ በሚወጣ ቃል ሁሉ እንጂ፣ በእንጀራ ብቻ አይኖርም›› በማለት በድፍረት ተቃወመው (ማቴዎስ 4፥4)፡፡

ከዚህ የምናገኘው ቢያንስ ሦስት ትምህርት አለ፡፡ ኢየሱስ ፈተናውን የተረዳውና መልስ የሰጠው ወዲያውኑ ነበር፡፡ አላሰበበትም፣ ሐሳቡን አላብላላውም፤ እንደዚያ ማድረግ ሰይጣን ያቀረበው ሐሳብ ወደ ልብ ዘልቆ እንዲገባ ዕድል መስጠት ሊሆን ይችላል፡፡ እኛም የእርሱን ምሳሌ መከተል አለብን፡፡

በሁለተኛ ደረጃ፣ ኢየሱስ በቀጥታ ለዲያብሎስ ተናገረ (ይህ በጣም አስፈላጊ ነው)፡፡ ፈታኙን ወይም ፈተናውን እንዲያስወግድለት ወደ እግዚአብሔር አባቱ አልጸለየም፡፡ ለጠላት መልስ የሰጠው፣ ‹‹በሰይጣን እንድሸነፍ የእግዚአብሔር ፈቃድ አይደለም፤ ስለዚህ በዚህ ፈተና መውደቅ የለብኝም›› በሚል ዐይነት በተዘዋዋሪ መንገድ አልነበረም፡፡ በቀጥታና ኮስተር ብሎ ነበር ለዲያብሎስ የመለሰለት፡፡ እኔና እናንተም ያንኑ ማድረግ ይኖርብናል፡፡ ‹‹ለዲያብሎስም ስፍራ አትስጡት›› የሚል ምክር ተሰጥቶናል (ኤፌሶን 4፥27)፡፡

በመጨረሻም፣ ኢየሱስ በጽሑፍ የሰፈረውን የእግዚአብሔር ቃል ተናገረ፡፡ ‹‹ተጽፎአል›› የሚለው ቃሉን አስተውሉ፡፡ ይህ በጣም አስፈላጊ የሆነው ለምንድነው? ምክንያቱም፣ የእግዚአብሔር ቃል ሰይፍ ስለ ሆነ ነው፡፡ ጳውሎስ፣ ‹‹የመንፈስንም ሰይፍ ያዙ፣ እርሱም የእግዚአብሔር ቃል ነው›› ይላል፡፡ የእግዚአብሔር ቃል ቁሳዊ *መሣሪያ* ሳይሆን፣ እጅግ ብርቱ *መንፈሳዊ መሣሪያ* ነው፡፡ ኢየሱስ ጠላትን በቀጥታ የወጋው በመንፈሳዊ *መሣሪያው* ነበር፤ ክፉኛ እንደሚጐዳ ጥርጥር የለም፡፡ ይሁን እንጂ፣ ጠላት *ሙጭጭ* ያለ በመሆኑ ተስፋ አልቆረጠም፡፡ ስለዚህም የሚያሳምም ምት በመሰንዘር ማጥቃቱን ቀጠለ፡፡

በጽሑፍ በሰፈረው ሁለተኛ መከራው ሰይጣን በአዳም ኃጢአት ለዲያብሎስ ተላልፎ የተሰጠውን የዓለምን መንግሥታት ለመያዝ አቋራጭ መንገድ አቀረበለት፡፡ ኢየሱስ ማድረግ ያለበት ወድቆ ለእርሱ መስገድ ብቻ እንደ ሆነ ነገረው፡፡ ኢየሱስ ግን፣ ‹‹ሂድ አንተ ሰይጣን፣ ለጌታ ለአምላክህ ስገድ፤ እርሱን ብቻ አምልክ ተብሎ ተጽፎአል›› በማለት መለሰ (ሉቃስ 4÷8)፡፡

ከእርሱ እንዲሄድ ኢየሱስ ለጠላት ተናገረ፡፡ ይህም እኔና እናንተ በድፍረት፣ ‹‹ሰይጣን ዘወር በል!›› ከምንለው ጋር ተመሳሳይ ነው፡፡ ከዚያም ኢየሱስ ጠላትን የበለጠ ለመጉዳት በእግዚአብሔር ቃል ተጠቀመ፡፡

> ጠላት ውጊያውን መቋቋም አቅቶት እስኪሸሽ ድረስ ፈተናው ቀጥሎ ነበር፡፡ ሉቃስ፣ ‹‹ዲያብሎስም... ሌላ አመቺ ጊዜ እስኪያገኝ ድረስ ከእርሱ ተለዩ›› ብሎ ጽፏል (4÷13)፡፡

## የተሰናከለ ፓስተር

ከጥቂት ዓመታት በፊት ኬን ብዬ የምጠራው አንድ ፓስተር ወደ ቢሮዬ መጥቶ ነበር፡፡ ኬን ጠንካራና በጣም ቆንጆ ወጣት ከመሆኑ ሌላ በጣም ጥሩ ሚስትና ልጆችም ነበሩት፡፡ አማኝ ከመሆኑ በፊት ሕገ ወጥ የዕፅ ዝውውር ውስጥ ይሳተፍ ነበር፡፡ ከዚያ ሕይወት በመውጣቱና ድነት በማግኘቱ ኬን እግዚአብሔርን አመስግኖ አይጠግብም፤ በሚያመልክበት ጊዜ ሁሉ ያለቅስ ነበር፡፡ ይህ ሰው ለኢየሱስ ያለው ጽኑ ፍቅር ልቤን ነክቶት ነበር፡፡ ኬን ለግላጋ፣ ጥሩ ባልና የሚወደድ አባት ነበር፡፡ እጅግ ብዙ የነበረው ኃጢአቱ ይቅር እንደ ተባለ ስለሚያውቅ ፍቅሩም የዚያኑ ያህል ነበር፡፡

ሆኖም፣ ለአያሌ ወሮች የዘለቀ ከባድ ውጊያ ነበረበት፤ ያንንም ለማንም ሳይነግር ለብቻው ይዞት ነበር፡፡ በመጨረሻ ጫናው ብቻውን

መቋቋም የማይችልበት ደረጃ ላይ በመድረሱ ለእኔ ሊነግረኝ ፈለገ፡፡ ወደ ቢሮዬ ሲገባ ከባድ ጭንቀት ውስጥ መሆኑ ፊቱ ላይ ይታይ ነበር፡፡

‹‹ምን ልርዳህ?›› በማለት ጠየቅሁት፡፡

ኬን ከቤተ ሰብ ታሪኩ ጥቂቱን ይነግረኝ ጀመር፡፡ በቤተ ሰቡ በተከታታይ የልብ ሕመም ይደርስ ነበር፤ ከዚህም የተነሣ የቤተ ሰቡ አባል የነበሩ ወንዶች ያለ ዕድሜያቸው ይሞቱ ነበር፡፤ ‹‹በልብ ሕመም እሞታለሁ የሚል ከባድ ፍርሃት አለብኝ፡፡ ዶክተሮች ተደጋጋሚ ምርመራ ቢያደርጉልኝም እስከ አሁን ድረስ ደኅና መሆኔን ነው የነገሩኝ፡፡ ያም ሆኖ በድንገት እሞት ይሆናል የሚል ፍርሃቴን ከአእምሮዬ ማውጣት አልቻልኩም፡፡ ከዚያ ፍርሃት ጋር እየኖርኩ ነው፤ አንዳንዴ ግን ከቁጥጥሬ ውጪ ይሆናል፡፡ እጅግ በጣም ያልበኛል፤ ልብሶቼ በላብ ይርሳሉ፡፡ ሌሊት ላይ ወይም ብቻዬን ስሆን፣ አንዳንዴም ከሰዎች ጋር እያለሁ ወይም ቤተ ክርስቲያን ውስጥ እያለሁ እንኳ ይህ ነገር ይደርስብኛል፡፡ ይህን ፍርሃት መቆጣጠር አልቻልኩም ያለ ምንም ማስጠንቀቂያ ምልክት ስለሚመጣ ከዐቅሜ በላይ ነው፡፡ አጥብቄ ጸልየአለሁ፡፡ ይህን ፍርሃት እንዲያስወግድልኝና በዚህ ከዐቅሜ በላይ በሆነ ስሜት እንዳልሸነፍ እንዲረዳኝ እግዚአብሔርን ጠይቄአለሁ›› አለ፡፡

በንግግሩ መሐል ጣልቃ የገባሁት ያኔ ነበር፡፡

‹‹ኬን፣ ምንም ውጤት ያላገኘኸው በዚያ ምክንያት ነው፡፡ ወደ እግዚአብሔር ትጸልያለህ፤ ግን፣ ኢየሱስ በበረሐ እንዳደረገው በቀጥታ ለጠላት አትናገርም፡፡ የእግዚአብሔር ቃል፣ ‘ዲያብሎስን ተቃወሙት፤ ከእናንተም ይሸሻል’ በማለት በግልጽ ነግሮናል፡፡ (ያዕቆብ 4፥7)፡፡ አንተም እንደዚያ ማድረግ አለብህ! ኢየሱስ ሰይጣንን አሸንፏል፤ ከዚያም ወደ ሰማይ ሄዶ በእግዚአብሔር ቀኝ ተቀምጧል፡፡ ከመሄዱ በፊት ግን፣ በተሸነፈ ጠላቱ ላይ የእርሱን ፈቃድ እንድንፈጽም የእርሱን ኃይልና ሥልጣን ለእኛ ሰጥቶናል፡፡ ‘መናፍስት ስለ ተገዙላች...’ በማለት ኢየሱስ ይህን ግልጽ አድርጐታል (ሉቃስ 10፥20)፡፡ ለእኛ መታዘዝ አለባቸው፡፡ በእግዚአብሔር ቃል እንድትጠቀም፣ በቀጥታ ለጠላት እንድትናገርና ለእግዚአብሔር ኪዳናዊ ተስፋ እንዲገዛ እንድታዝዘው ተነግሮሃል›› አልኩት፡፡

ያ ወዳጄ፣ ከልቡ እየሰማኝ ነበር፤ እኔም ንግግሬን ቀጠልኩ፡፡ ‹‹ኬን አንዳንዴ፣ ጠላት እኔንም ያውከኛል፤ ነገሮች ከቁጥጥር ውጪ የሆኑ ይመስለኛል፤ እንደዚያ በሚሆንበት ጊዜ ማንም ሊሰማኝ ወደማይችልበት ገለልተኛ ቦታ እሄዳለሁ፡፡ ብርቱ ጸሎት ማለት በመንፈስ፣ በነፍስና በሥጋ

ያለኝን ዐቅም ሁሉ መስጠት በመሆኑ ድምፄን ከፍ አድርጌ እጮኻለሁ፡፡ እዚህ ላይ፣ 'የሥጋ' ድርሻ ድምፄን ከፍ አድርጌ ሰይጣንን፣ ‹‹እኔ የመንፈስ ሰይፍ የሆነው የእግዚአብሔር ቃል አለኝ፤ አንተ ግን የለህም፤ ስለዚህም ተሸንፈህ እስክትሸሽ ድረስ እዋጋሃለሁ... የእግዚአብሔር ቃል... ይላል›› ማለት ሊሆን ይችላል፡፡

ስለ ፈውስ፣ ከፍርሃት ነጻ ስለ መሆን፣ ስለ መለኮታዊ ችሮታና ከመንፈሳዊ ባርነት ነጻ ስለ መውጣት፣ ከእግዚአብሔር ቃል አንዳንድ ምንባቦች እያወጣሁ ሳካፍለው ኬን እያዳመጠኝ ነበር፡፡ በጽሑፍ የሰፈረውን የተስፋ ቃል በውጊያው እንዴት እንደ መንፈሳዊ መሣሪያ እንደሚጠቀምበት አሳየሁት፡፡ በቀጥታና ጠንከር ባለ ሁኔታ ለፍርሃት መንፈስ መናገር እንዳለበት ነገርኩት፡፡ ጥቂት ጊዜ ካወራን በኃላ ጸለይኩለትና ሄደ፡፡

ከስድስት ወር በኋላ ኬን ተመልሶ መጣ፤ ፊቱ እንደ ጨፈገገ ነበር፡፡ አሁንም እንደ ከበደው ይታወቅ ነበር፡፡ ምን አዲስ ነገር እንዳለ ጠየቅሁት፤ ግን ምን ሊናገር እንደሚችል ይገባኝ ነበር፡፡

‹‹ጆን፣ አሁን ደግሞ ከምንጊዜውም ይበልጥ ብሶአል›› አለ፡፡ ‹‹ከስድስት ወር በፊት ከነበረው ይልቅ አሁን ፍርሃትን ዘወትር እየተዋጋሁ ነው፡፡ እንዲያውም ያለ ምንም ፋታ በየቀኑ ነው እየደረሰብኝ ያለው፤ ያለ ቅጥ ያልበኛል፣ ከውስጥ ጀምሮ እስከ ውጭ ድረስ ልብሴ ይርሳል፣ በራስ የመተማመን ስሜቴ ተናግቶአል፡፡ እኔ ራሴ ካለሁበት ውጊያ የተነሣ ሌሎችን ማገልገል አልቻልኩም፡፡

ከዚህም ኬን፣ ወደ ፊት ጠጋ ብሎ፣ ‹‹ጆን፣ ጸሜአለሁ፤ ጸልየአለሁ፤ እግዚአብሔር እንዲረዳኝ አጥብቄ ጠይቄአለሁ፡፡ ግን ምንም ፋታ ወይም መልስ አላገኘሁም፡፡ እንዲያውም አእምሮዬ ሊቃወስ ነው›› በማለት ነገረኝ፡፡

ከዚህ በላይ ልሰማው አልፈለግሁም፡፡ ‹‹ኬን፣ ከጥቂት ወሮች በፊት እንድታደርግ የነገርኩህን አድርገሃል? ገለል ወዳለ ቦታ ሄደህ በነገርኩህ መሠረት በቀጥታ ዲያብሎስን ተዋግተሃል? የእግዚአብሔር ቃል የሚለውን ነግረኸዋል››

‹‹እ... በእርግጥ ያንን አላደረግሁም፡፡››

እዚህ ላይ ቆጣ አልኩ፡፡ ‹‹ኬን፣ ምንም ሊሆን አይችልም፤ የመንፈስ ሰይፍ በሆነው የእግዚአብሔር ቃል በቀጥታ ጠላትን ካልተጋፈጥህ ምንም ለውጥ አይኖርም፡፡››

ራሱን ዘንበል አደረገ፤ ነገሩን ችላ ያለ መስሎኝ ነበር፡፡ ኬን በሰጠሁት ምክር ተስማምቶአል ብዬ አላሰብኩም ነበር፤ ሆኖም ሌሎች መጥተው ርዳታ ሲያገኙ ስላየ እርሱም ተመልሶ መጥቷል፡፡ የእምነት ሰው ነበር፤ እግዚአብሔር ለእርሱ ጨኸት መልስ ለመስጠት ዐቅም እንዳለውም በእርግጥ ያምን ነበር፤ ይሁን እንጂ ውጤት ባለ ማየቱ ተስፋ መቁረጥ ደረጃ ላይ ደርሶ ነበር፡፡

እንዴት እንደማስረዳው ምሳሌ እየፈለግሁ እያለ መንፈስ ቅዱስ አንድ ጥሩ ምሳሌ ሰጠኝ፡፡ ‹‹ኬን፣ የዩናይትድ ስቴትስ ፕሬዚዳንት የአገሪቱ መከላከያ ሰራዊት የበላይ አዛዥ እንደ ሆነ ይታወቃል፡፡ በቀላል አነጋገር የመከላከያው ኃይል ራስ፣ መሪና አለቃ ነው፡፡

‹‹ኢራቅ ጦር ሜዳ ስላለ አንድ የእኛ ወታደር አስብ፡፡ ጠላት ከየአቅጣጫው እየተኮሰበት ቢሆንም ወታደሩ መልሶ አይተኩስም ነበር፡፡ ግራ ገብቶትና ፈርቶ ሲርበተበት አንድ የመገናኛ ሬድዮ እጁ ውስጥ ይገባና ከኃይት ሐውስ ጋር ይገናኛል፡፡ ፕሬዚዳንቱ ቁርጥ ያለ መልስ ቢሰጠውም፣ ‹‹ክቡር ፕሬዚዳንት ከባድ ውጊያ ውስጥ ነኝ፡፡ ጠላት እየተኮሰብኝ ነው፤ ሊገድለኝ እየሞከረ ነው፡፡ ክቡር ፕሬዚዳንት፣ እባክዎን መጥተው እኔን ከመግደሉ በፊት ጠላትን ይግደሉልኝ፡፡ የማደርገው ግራ ገብቶኛል፤ ፈርቻለሁ! መጥተው እንዲረዱኝ እለምንዎታለሁ›› እያለ ወተወተ፡፡

‹‹የዚህ ሰው ሕይወት ከባድ አደጋ ላይ እንደ ሆነ ግልጽ ነው፤ ያም ሆኖ፣ ግን ፕሬዚዳንቱ ለዚህ ቅጥ ያጣ ጥያቄው ምን ዓይነት መልስ ይሰጠው ይመስልሃል?›› በማለት ኬንን ጠየቅሁት፡፡

የራሴን ጥያቄ ራሴ መመለስ ጀመርኩ፡፡ ‹‹ለምንድነው የምትጨቀጭቀኝ? በዚህ ምድር ምርጥ የሆነ ወታደራዊ ሥልጠና ሰጥቼሃለሁ፡፡ የትም የማይገኝ ምርጥ መሣሪያ ሰጥቼሃለሁ፡፡ ጠላትን እንድታጠፋ የተባበሩት የአሜሪካ መንግሥታትን ሥልጣን ሰጥቼሃለሁ፡፡ አሁንም መገናኛ ሬዲዮኑን አስቀምጠህ መልሰህ ተኩስ! ጠላትን ተጋፈጥ! የሚለው ይመስለኛል፡፡››

የኬን ዓይኖች ሲያበሩ ይታየኛል፡፡

‹‹ኬን፣ ለአንተ ሰይፍ ተሰጥቷል፤ ከአንተ ጋር የሚዋጋው ጠላት ግን ምንም የለውም፡፡ እንዲያውም፣ ትጥቅ እንዲፈታ ተደርጓል፤ ጌታ፣ ‹‹የአለቆችንና የባለ ሥልጣናትንም ማዕረግ በመግፈፍ በመስቀሉ ድል ነሥቶ በአደባባይ እያዞራቸው እንዲታዩ አደረገ›› (ቈላስይስ 2፥15)፡፡ አንተ ሕጋዊ መሣሪያ አለህ፤ ጠላት ግን ዛቻ ብቻ ነው ያለው፡፡ ያም ብቻ አይደለም፤

በኢየሱስ ስም ውስጥ ያለው ኃይልና ሥልጣንም ሁሉ ተሰጥቶሃል፡፡ ጉልበት ሁሉ ለስሙ እንደሚንበረከክ፣ አንደበት ሁሉ ጌትነቱን እንደሚመሰክር ተነግሮናል›› በማለት መናገሬን ቀጠልኩ (ፊልጵስዩስ 2፥10-11)፡፡

‹‹የእግዚአብሔር መሣሪያ ተሰጥቶሃል - የጽድቅ ጥሩር፣ የእምነት ጋሻ፣ የመዳን ራስ ቁር የመሳሰሉ መሣሪያዎች ተሰጥተውሃል፡፡ የእምነት ጋሻ ጠላት የሚወረውረውን ጥቂቱን ብቻ ሳይሆን ሁሉንም፣ ማንኛውንም ነገር ይመክታል፡፡ እግዚአብሔር በቃሉ፣ 'በአንቺ ላይ እንዲደገን የተበጀ መሣሪያ ይከሽፋል፤ የሚከስሽንም አንደበት ሁሉ ትረቺያለሽ፤ እንግዲህ የእግዚአብሔር ባሪያዎች ርስት ይህ ነው' በማለት ነግሮሃል (ኢሳይያስ 54፥17)፡፡ ጥቃቱን መቃወም ያለብህ አንተ ራስህ እንደ ሆንክ እግዚአብሔር በግልጽ ነግሮሃል፡፡ እርሱ ያንን አያደርግልህም፤ በቀጥታ ለዲያብሎስ መናገር ያለብህ አንተ ራስህ ነህ፡፡ ደጋግመህ ወደ እግዚአብሔር እየጮህኽ ነው፡፡ እንደ ፕሬዚዳንቱ ሁሉ እርሱም፣ 'መልስህ ተኩስ!' ወይም፣ 'በሰይፍ ውጋው!' እያለህ ነው፡፡››

አሁን ኬን በቀጥታ እኔን እያየ ነበር፡፡ በእኔ በኩል ከመንፈስ ቅዱስ ያገኘውን ምሳሌ እውነት ማየት ችሎ ነበር፡፡ ተስፋና እምነት ተሞልቶ ነበር ከቢሮዬ የሄደው፡፡ ከሦስት ሳምንት በኋላ ወደ ቢሮዬ ሲመጣ በደስታ እየተፍለቀለቀ ነበር፡፡ ‹‹ጆን፣ የሆነውን መስማት ይገባሃል!›› አለ፡፡

ታላቅ ዜና በመጠበቅ ወደ ፊት ዘንበል አልኩ፡፡

አንድ እሑድ ቀን፣ ‹‹ችግሩ እንደ ገና ሲጀምረኝ ወደ ቤተ ክርስቲያን እየሄድኩ ነበር›› አለ ኬን፡፡ ‹‹በየትኛውም ጊዜ በልብ ሕመም ልሞት እንደምችል የነበረኝ የፍርሃት ስሜት ወረረኝ፡፡ እንደ ተለመደው ያልበኝ ጀመር፤ ልብሴ ሁሉ ረጠበ፡፡ ሆኖም፣ ከዚያ በፊት ሁሌም አደርግ እንደ ነበረው ወደ እግዚአብሔር ከመጮኽ ይልቅ በጣም ተሰላቸሁ፡፡ የምሬን ዲያብሎስ ላይ ተቆጣሁ፡፡ ውስጤ ቁጣ ተፍለቀለቀ፤ አጠገቤ የነበረችው ሚስቴ ምንም ሳትዘጋጅ፣ በመዳፌ የመኪናውን የፊት ክፍል መታሁት፡፡ 'ሰይጣን፣ ከእንግዲህ አምርሬአለሁ፤ አሁን በአንተና በዚህ ፍርሃት ላይ እመጣለሁ!' አልኩ፡፡ ከዚያም ጮኽ ብዬና በጋለ ስሜት የእኔን ሕይወት በተመለከተ የእግዚአብሔር ቃል የሚናገረውን መጥቀስ ጀመርኩ፡፡

‹‹ጆን፣ የመኪናውን የፊት ክፍል በመዳፌ መትቼ ሰይጣን፣ ከእንግዲህ አምርሬአለሁ ስል በድንገት ልቤ ውስጥ ራእይ አየሁ፡፡ ዲያብሎስን በተጋፈጥኩበት ቅጽበት ኢየሱስን በሰማይ ዙፋን ላይ ያየሁ መሰለኝ፤ እጆቹን በመዘርጋት 'አዎን!' በማለት ሲጮኽ የሰማሁ መሰለኝ››

አለ፡፡ ከዚያም ኬን እየሳቀ፣ ‹‹ጆን፣ ሁኔታው ይህን እንድታደርግ ለረጅም ጊዜ ስጠብቅህ ነበር፤ አሁን በመጨረሻ ርምጃ በመውሰድህ ደስ ብሎኛል በማለት ኢየሱስ የተናገረኝ ያህል ነበር›› አለ፡፡

ከዚያ በኋላ ኬን ለዚያ ፍርሃት አልተሸነፈም፡፡ ፍርሃቱን ተከትሎ በሚመጣ ድብርት አልተሰቃየም፡፡ ያ ከሆነ አሁን ሃያ ዓመት ቢያልፍም፣ ይህ የተወደደ የእግዚአብሔር ሰው አሁንም ጤነኛና በሕይወት ነው፤ በደቡባዊው ዩናይትድ ስቴትስ አንድ ትልቅ ቤተ ክርስቲያን አለው፡፡ በአካልም ሆነ በመንፈሳዊ ሕይወቱ በጣም ደኅና ነው፡፡

## በጽናት መቃወም

እስቲ አሁን የጴጥሮስን ቃል የበለጠ ልብ አድርገን እንይ፣

*ራሳችሁን የምትገዙ ሁኑ ንቁም፤ ጠላታችሁ ዲያብሎስ የሚውጠውን በመፈለግ እንደሚያገሣ አንበሳ ወዲያ ወዲህ ይዞራል፡፡ በእምነት ጸንታችሁ ተቃወሙት፡፡* (1ጴጥሮስ 5፥8-9)

ምዕራፍ 1 ላይ የተመለከትነውን ታስታውሱ ከሆነ ጸንታችሁ የሚለው ቃል ተስፋ አለመቁረጥ ማለት ነው የሚያመለክተው፡፡ ጠላትን አንዴ ከተቃወምን ተመልሶ እንዳይመጣና ድጋሚ ሙከራ እንዳያደርግ ይከለክላል የሚል ተስፋ መጽሐፍ ቅዱስ አልነገረንም፡፡ ይልቁንም በተቃራኒው፣ ደግሞ ደጋግሞ ሙከራ ያደርጋል፡፡ ብዙ ክርስቲያኖች ተስፋ የሚቆርጡትና ሽንፈት የሚደርስባቸው እዚህ ላይ መሆኑን ከዓመታት ልምድ ተምሬአለሁ፡፡ ‹‹ይህ ነገር የሚሠራ አይመስለኝም›› ወይም ‹‹ለማሸነፍ የሚስፈልገው ነገር ያለኝ አይመስለኝም›› በማለት ያስባሉ፡፡ ይህ ግን ትልቅ ውሸት ነው፡፡

አንድ ሌላ ታሪክ ይህን ነጥብ ግልጽ ሊያደርግልን ይችላል፡፡ ሕፃን በነበረች ጊዜ ሊዛ የሆድ ቁርጠት ነበረባት፡፡ ይህ ሕፃናት በተለይም ከአንድ ዓመት በታች ያሉት ላይ ብዙ ጊዜ የሚደርስ ነው፡፡ በመሠረቱ ልጆች ሁሉ ያለቅሳሉ፤ የዚህ ዐይነት የሆድ ቁርጠት ያለበት ሕፃን ግን አንዳንዴ ለሰዓቶች ሊያለቅስ ይችላል፤ ያም ሆኖ ግን ሕመሙን ለማስቆም ምንም ማድረግ የምትችሉት ነገር አይኖራችሁም፡፡ ይህ ሁኔታ ለረጅም ጊዜ በየቀኑ፣ ለወሮች ሊቀጥል ይችላል፡፡ የዚህ ቁርጠት ምክንያት ምን እንደ ሆነ ዶክተሮች እስካሁን በትክክል አላወቁም፤ ሆኖም ብዙዎች በሚገባ ያልጠነከረ የስልቀጣ ሥርዐት ሊሆን እንደሚችል ያምናሉ፡፡

የመጀመሪያ ልጃችን ኤዲሰንም የሆድ ቁርጠት ነበረበት፡፡ ምክንያቱ ባልታወቀ ሁኔታ ምርር ብሎ ያለቅስ እንደ ነበር አስታውሳለሁ፡፡

ለመጀመሪያዎቹ ጥቂት ደቂቃዎች ማለቂያ የሌለው ይመስል ነበር፡፡ ጀርባውን መታ መታ እናደርግ ነበር፣ እንወዘውዘው ነበር፣ እንዘምርለት ነበር፤ ያ ሁሉ ሆኖ ግን ማልቀሱን ይቀጥል ነበር፡፡ እርሱን መርዳት ባለ መቻላችን ተስፋ ቢስነት ተሰማን፡፡ ከጥቂት ጊዜ በኋላ አቅፌው እያለ፣ በሽታው አካሉን ለቆ እንዲሄድ አዘዝኩ፡፡ በቀጥታ ለስልቀጣ ሥርዐቱ (ዳይጄሽን ሲስተም) ተናገርኩ፡፡ ከዚያም ጮኽ ብዬ እና አምርሬ በመንፈስ ጸለይኩ፤ ኤዲሰንንም ጭልጥ ያለ እንቅልፍ ወሰደው፡፡

አንድ ምሽት ሊዛ ገላ መታጠቢያ ክፍል ውስጥ ነበረች፤ እኔ ደግሞ አልጋ ላይ ነበርኩ፡፡ በድንገት ከልጆቹ መኝታ ቤት የሚያስደነግጥ ጩኸት ሰማን፡፡ ‹‹ጆን፣ የተለመደው ጉዳይ ነው!›› አለች ከገላ መታጠቢያው ክፍል፡፡

ከአልጋ ተነሥቼ ሰዓት ሳይ 6፡11 ይላል፡፡ በፍጥነት ወደ ልጆች መኝታ ክፍል ሄድኩና ኤዲሰንን በዕቅፌ ይዤ የልጄን አካል ለቆ እንዲሄድ በኢየሱስ ስም ሕመሙን አዘዝኩ፡፡ ከዚያም ኤዲሰንን እንቅልፍ እስኪወስደው ድረስ በመንፈስ ጸለይኩ፡፡ ይህ የሆነው በዐሥራ አምስት ደቂቃ ውስጥ ነበር፡፡

በሚቀጥለው ሌሊት ያንኑ አሰቃቂ ጩኸት ስንሰማ፣ ሁለታችንም አልጋ ላይ ነበርን፡፡ መጀመሪያ ወደ ሐሳቤ የመጣው - *ጸሎትህ አልሠራም! አንተ ትጸልይለታለህ እርሱን ግን ምንም አልተሻለውም፡፡ ውጤታማ አይደለህም፤ እምነት የለህም* - የሚል እንደ ነበር መቀበል እፈልጋለሁ፡፡ ሆን ብዬ ያንን ሐሳብ ከአእምሮዬ አወጣሁና፣ ስለ ጸሎት መልስ የእግዚአብሔር ቃል በሚናገረው ተካሁት፡፡

ተነሥቼ ሰዓቱን ሳይ ዛሬም 6፡11 ይላል፡፡ አጋጣሚ ነው በማለት አሰብኩ፡፡ ወደ ኤዲሰን መኝታ ክፍል ገባሁ፤ ዕቅፍ አደረግሁትና ሕመሙ ለቅቆት እንዲሄድ በኢየሱስ ስም አዘዝሁ፤ ከዚያ እንደ ገና እስኪተኛ ድረስ በመንፈስ ጸለይኩ፡፡ አሁንም ይህ ሁሉ የሆነው በዐሥራ አምስት ደቂቃ ውስጥ ነበር፡፡

በሚቀጥለው ምሽት ሊዛ ዋናው የገላ መታጠቢያ ውስጥ ነበረች፤ እኔም አልጋ ላይ ነበርኩ፡፡ ለሦስት ተከታታይ ምሽቶች ያንን ሰቅጣጭ ጩኸት ሰማን፡፡ በዚህ ጊዜ የነበረኝ ሐሳብ ትንሽ ጠንከር ያለ ነበር - *ጆን፣ ለሁለት ሳምንት ያህል ለኤዲሰን ጸልየህ ነበር፡፡ ትናንት ጸልይህ ነበር፤ ከትናንት ወዲያም ጸልየህ ነበር፡፡ ለልጅህ ምንም አልጠቀምከውም - ይህን መቀበል አለብህ፡፡ ጸሎትህ አይሠራም ማለት ነው!* አሁንም በእግዚአብሔር ቃል በመተካት ያንን ሐሳብ ተዋጋሁና እንደ ገና ከአልጋ ተነሣሁ፡፡

ዐይኔን ወደ ሰዓቱ ሳነሣ፣ ማጣራት ስለ ፈለግሁ ሁለቴ ሦስቴ ነበር ያየሁት፡፡ ለሦስት ተከታታይ ሌሊት ጩኸቱ የመጣው 6:11 ላይ ነበር፡፡ በዚህ ጊዜ በጣም ተቆጣሁ፡፡ ወደ መኝታ ቤቱ ገባሁ፤ እየተሰቃየ ያለውን ልጄን አየሁት፤ ወደ አልጋው ቀረብ ብዬ እጄን ደረቱ ላይ አደረግሁ፡፡ ዝቅ ብዬ ትንሹን ልጄን ሳየው፣ እያየሁ ያለሁት እኔ ሳልሆን በእኔ ዓይን በኩል መንፈስ ቅዱስ እያየው እንደ ሆነ ተሰማኝ፡፡

በቁጣና በታላቅ ሥልጣን፣ ‹‹አንተ ልጄን እያሰቃየህ ያለህ ክፉ የቁርጠትና የድካም መንፈስ፤ በሊዛ ቤተ ሰብ ሲተላለፍ የኖረ ይህን መርገም እሰብራለሁ፤ የቆሸሸ እጅህን ከኤድሰን ላይ አንሣ! አሁኑኑ ለቀህ ሂድ፣ ከእንግዲህ እንዳትመለስ አዝዝሃለሁ!›› በማለት ጮኽ ብዬ ጸለይኩ፡፡ ይህ ልጁን ያስደነግጠዋል ብላችሁ አስባችሁ ከሆነ፣ በተቃራኒው ነበር የሆነው፡፡ ሕፃኑ ኤዲሰን ወዲያውኑ ማልቀሱን አቆመ፤ በሚያባብል ዓይን አየኝ፤ ከዚያም ጭልጥ ያለ እንቅልፍ ወሰደው፡፡ በሆድ ቁርጠት ለማልቀስ ያ የመጨረሻ ቀን ሆነ፡፡ ከዚያ ሌሊት ጀምሮ ጤነኛና ደስተኛ ልጅ ሆኗል፡፡ ጠላት ተሸንፎአል፤ ከእንግዲህ ላይመለስ ሄዶአል፡፡

ሁለተኛው ልጃችን አውስቲን የተወለደው ከሦስት ዓመት በኋላ ነበር፡፡ ከተወለደ ጥቂት ወሮች በኋላ እርሱም ተመሳሳይ ዐይነት ምልክት ያሳይ ጀመር፡፡ አሁን ምን ማድረግ እንዳለብኝ አውቄአለሁ፤ ለሌላ ውጊያም ዝግጁ ነበርኩ፡፡ አንዴ ወይም ሁለቴ በሥልጣን ተናገርኩ፤ ሰቅጣጩ ለቅሶ ጸጥ አለ፡፡ ቁርጠቱ በጥቂት ቀኖች ውስጥ ለቀቀው፤ ከዚያ በኃላ እንደ ገና አውስቲንን አላሰቃየውም፡፡ ከጥቂት ዓመት በኋላ ሦስተኛው ልጃችን አሌክ ሲወለድ፣ ምንም የሆድ ቁርጠት አልነበረበትም፡፡ አዙሪቱ ተሰብሯል፡፡ ጠላት፣ ድጋሚ ከሞከርኩ በሰይፍ - በእግዚአብሔር ቃል ያጠቁኛል ብሎ ሲያስብ ገምቱ፡፡

የተወደዳችሁ ወገኖቼ፣ ዲያብሎስን በጽናት ተቃወሙት፡፡ በጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ በኩል በተሰጣችሁ ሥልጣን በቀጥታና ኮስተር ብላችሁ ገሥፁት፡፡ እኛ ከባርነት ነጻ ለመሆን ያለን ቆራጥነት፣ ባሪያዎቹ አድርጐን ለመዝለቅ ጠላታችን ካለው ውሳኔ መብለጥ አለበት፡፡

የሜክሲኮ ሕንዶችን ለማገልገል ሄዶ ከነበረ አንድ ታላቅ ሚሲዮናዊ የሰማሁትን ምስክርነት በፍጹም አልረሳውም፡፡ አብዛኛውን ጊዜ ይሠራ የነበረው ተራሮቹ ላይ በነበሩ ትንንሽ መንደሮች ሲሆን፣ እርሱ ካደረገው የቡድን አገልግሎት የተነሣ አንድ መንደር ውስጥ የነበረ አብዛኛው ሰው አማኝ ሆኖ ነበር፡፡ አንድ ሌሊት በመንደሩ ሰዎች ከእንቅልፉ ይቀሰቀሳል፡፡ ሰዎች በጣም ተጨንቀው ነበር፡፡ ወደ ሚሲዮኑ ቤተ ክርስቲያን ይመጡ

የነበሩ ባልና ሚስት ልጅ ገና መሞቱ ነበር፡፡ የቤተ ሰቡ አባሎች በፍጥነት መጥቶ እንዲጸልይ ሚሲዮናዊውን ጠየቁት፡፡ ወዲያውኑ ተነሥቶ ወደ ቤታቸው ሄደ፤ የሞት መንፈስ ሕፃኑን እንዲለቅ አዘዘ፡፡ በደቂቃዎች ውስጥ ሕፃኑ መሳል፣ ማስነጠስና መተንፈስ ጀመረ፡፡ ሕፃኑ ከሞት ተመለሰ! ሁሉም ደስ አላቸው! ሚሲዮናዊውም ወደ ቤት ተመልሶ የሰላም እንቅልፍ ተኛ፡፡

ከጥቂት ጊዜ በኋላ እነዚያው ሰዎች በሩን አንኳኩ፡፡ ሕፃኑ ለሁለተኛ ጊዜ ሞቶ ነበር፡፡ ሚሲዮናዊው ተነሥቶ ሄደና የሞትን መንፈስ ገሠጸ፤ ልጁም እንደ ገና ወደ ሕይወት ተመለሰ፡፡ ለዘለቄታው ትቶት እስኪሄድ ድረስ በዚያ ሌሊት ደጋግሞ ሞትን መቃወም እንደ ነበረበት ሚሲዮናዊው ተናግሮ ነበር፡፡ በኃላ ግን ልጁ በሕይወት ኖረ፣ ሚሲዮናዊው ይህን ሪፖርት ባቀረበ ጊዜ፣ ያ ልጅ መንደሩ ውስጥ ካሉ ጤነኛ ልጆች አንዱ ነበር፡፡

## አጥብቃችሁ ያዙ

ብዙ ጊዜ በጣም ጠቃሚ ነገሮች ከአማኞች ሲወሰዱ አይቻለሁ፡፡ አንዳንድ በጣም ጥሩ የሚባሉ ሰዎች እውነተኛ በረከት፣ ፈውስና ከእግዚአብሔር የተደረገ ተአምር ይቀበላሉ፤ በቀኖች፣ በሳምንቶች፣ በወሮች አንዳንዴም በዓመታት ውስጥ ተቀብለውት የነበረው ይጠፋባቸዋል፡፡ መጽሐፍ ቅዱስ፣ ‹‹መልካም የሆነውን አጥብቃች ያዙ›› በማለት የሚመክረን በዚህ ምክንያት ነው (1 ተሰሎንቄ 5፥21)፡፡ ማንኛውም አማኝ ይህን ማጤን፣ ማሰላሰልና በዚህ ምክር ጸንቶ መቆም አለበት፤ ይህን የተረዳሁት ቀደም ባለው የክርስትና ሕይወት ዘመኔ ነበር፡፡

በአብዛኛዎቹ የዐሥራዎቹ ዓመታት ዘመኔ በታችኛው ጀርባ ሕመም እሰቃይ ነበር፡፡ የአንድ ዓመት አማኝ እንደ ነበርኩ ከአንድ ጓደኛዬ ጋር አንድ ስብሰባ ተካፍዬ ነበር፡፡ ስብሰባውን ያዘጋጀችው ሴት፣ ‹‹በዚህ ስብሰባ ውስጥ በጀርባ ሕመም፣ በተለይም በታችኛው የጀርባ አካባቢ ሕመም የሚሰቃይ አንድ ሰው አለ›› በማለት ተናገረች፡፡

እየተናገረች ያለችው ስለ እኔ እንደ ሆነ ወዲያውኑ ነበር ያወቅሁት፣ ግን እየሆነ ያለው በጥቂቱም ቢሆን ግር ብሎኝ ነበር፡፡ ባሳለፍኩት ዘመን ብዙ ጊዜ ወደ ካቶሊኮች ቤተ ክርስቲያን ነበር የምሄደው፣ አንድ አገልጋይ የአንድን ሰው የግል ጉዳይ በግልጽ መናገሩ የለመድኩት አልነበረም፡፡ እተቀመጥኩበት ቦታ ቀረሁ፡፡ ሴትየዋ ከአጠገቤ ስትሄድ እፎይታ ተሰማኝ፡፡

ከዐሥር ደቂቃ በኋላ፣ ‹‹በጣም አዝናለሁ፤ ይህ ቃል አሁንም ወደ እኔ እየመጣ ነው፡፡ እዚህ ስብሰባ ውስጥ ጀርባው መፈወስ ያለበት ሰው አለ›› አለች፡፡

መቼም፣ በዚህ ሁሉ ሰው ፊት ወደዚያ አልሄድም፤ እንዲያውም፣ ከተቀመጥኩበት እንኳ አልንቀሳቀስም በማለት አሰብኩ፡፡ ይሁን እንጂ፣ በዚህ ጊዜ መንፈስ ቅዱስ በጣም እየወተወተኝ ስለ ነበር እንደ ምንም ብዬ ምላሽ ሰጠሁ፡፡ ሴትየዋና ባልዋ ሲጸልዩልኝ የጀርባ ሕመሜ ወዲያውኑ ተፈወሰ፡፡ በጣም ተገረምኩ! ይህን ያህል ዘመን ስኖር ጀርባዬ ከሕመም ነጻ ሆኖ አያውቅም ነበር፡፡ በዚያ ምሽት እግዚአብሔር አካሌ ላይ ባደረገው ነገር ከፍ ያለ የአክብሮት ፍርሃት ውስጥ ሆንኩ፡፡

ቀጥሎ በነበሩት ጥቂት ሳምንቶችም ውስጥ ጀርባዬ ደኅና ነበር፡፡ የሚገርም ነው፡፡ ከዚህ በፊት ቀጥ ብዬ ከቆምኩ ጀርባዬን በጣም ያምመኝ ስለ ነበር፣ ጥርሴን ስቦርሽም ሆነ ጢሜን ስላጭ ጐንበስ ማለት አዘወትር ነበር፡፡ አሁን ያ የለም! እግዚአብሔር ባደረገልኝ ነገር ደስተኛም አመስጋኝም ነበርኩ፡፡

ከአንድ ወር በኋላ አልጋዬ ላይ ሆኜ እንቅልፍ ሊወስደኝ ሲል፣ አንድ ነገር ክፍሌ ውስጥ ሲመጣ ተሰማኝ፡፡ ላየው ባልችልም እንኳ፣ እዚያ መኖሩ ግን በግልጽ ይታወቀኝ ነበር፡፡ በመስኮት በኩል የጨረቃ ብርሃን ወደ እኔ መኝታ ክፍል እየገባ የነበረ ቢሆንም፣ ምክንያቱን ባላወቅሁት ሁኔታ በድንገት ጨለመ፡፡ ያ ያላየሁት ነገር ክፍሌ ውስጥ ሲገባ፣ ፍርሃትም አብሮት ገባ፡፡ በድንገት ለዓመታት ሲያሰቃየኝ የነበረው የታችኛው ክፍል የጀርባ ሕመምም ጀመረኝ፡፡ *ፈውስህ ተወስዷል ያለ ስቃይ ያሳለፍከው ጊዜ አብቅቷል! በቀረው የዕድሜ ዘመንህ ሁሉ ጀርባህ ታማሚ ይሆናል* የሚል ሐሳብ በአእምሮዬ ተሰራጨ፡፡

ገና ወጣት አማኝ እያለሁ በብዛት የእግዚአብሔርን ቃል አነብ ስለ ነበር፤ ይህ የጠላት ጥቃት ሊሆን እንደሚችል በቂ ዕውቀት ነበረኝ፡፡ ጠላት የእርሱን ውሸት እንድቀበል ሊያደርገኝ እየሞከረ ነበር፤ እንደዚያ ከሆነ ደግሞ ሕመሙም ለዘለቄታው አብሮኝ ይኖራል ማለት ነው፡፡ በድንገት ከመኝታዬ ብድግ ብዬ በመነሣት ክፍሉ ውስጥ ወዲያ ወዲህ እያልኩ፣ ‹‹ሰይጣን፣ ከሳምንቶች በፊት እዚያ ስብሰባ ላይ ተፈውሻለሁ፡፡ መፈወሴን አጥብቄ እይዛለሁ! መጽሐፍ ቅዱስ - በኢየሱስ ክርስቶስ መገረፍ ቁስል እንደ ተፈወስኩ ይናገራል፡፡ ያንን የጀርባ ሕመም እንደ ገና እኔ ላይ ማምጣት አትችልም፡፡ ለዘለቄታው ተፈውሻለሁ፡፡ ስለዚህም ይህን ክፍል ለቀህ እንድትሄድ በኢየሱስ ስም አዝዝሃለሁ!›› አልኩ፡፡

ጨልሞ የነበረው ክፍል እንደ ገና በራ፡፡ ፍርሃቱና ወደ ክፍሉ ውስጥ መጥቶ እንደ ነበር የተሰማኝም ነገር ጠፋ፤ ጀማምሮኝ የነበረው የጀርባ

ሕመምም ጠፋ፡፡ ከዚያ ጊዜ ጀምሮ ያ ሕመም በጭራሽ ተሰምቶኝ አያውቅም፡፡

ኢየሱስ፣ ‹‹ማንም እንዳይወስድብህ... ያለህን አጥብቀህ ያዝ›› ብሏል (ራእይ 3፥11)፡፡ ከእግዚአብሔር የተቀበልነውን አጥብቀን በመያዝ መጽናት ይኖርብናል፡፡

ከገጠሙኝ አሳዛኝ ታሪኮች አንዱ በአንድ ምሽት እየሰበክሁ በነበረበት ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ተአምራዊ ፈውስ ተቀብሎ የነበረ ሰው ታሪክ ነው፡፡ ሕዝቡ በጣም ብዙ ስለ ነበር መጨረሻ ላይ ለሰው ሁሉ አንድ ላይ ጸለይኩ፡፡ በዚያ ሕዝብ መሐል አንድ ሰው ጐንበስ ብሎ ሲያለቅስ አየሁ፡፡ ምን እንደ ሆነ ወደ ነበረበት ቦታ ሄጄ ጠየቅሁት፡፡ ጀርባው ላይ ተደጋጋሚ ቀዶ ሕክምና ተደርጐለት እንደ ነበርና ቀሪ ሕይወት ዘመኑን ሁሉ አካለ ስንኩል ሆኖ እንደሚቀር እንደ ተነገረው ሰማሁ፡፡ ከባድ ስቃይ የነበረበት ቢሆንም፣ አሁን ግን ሙሉ በሙሉ ተፈውሶ ነበር፡፡ ከብዙ ዓመታት ወዲህ አሁን በተሰማው አዲስ ነጻነት ደስ ብሎት ከደስታ የተነሣ ነበር የሚያለቅሰው፤ አንድ ትልቅ ሰው በዚያ ዓይነት ሁኔታ ሲያልቅስ በፍጹም አይቼ አላውቅም፡፡ እጅግ በጣም ደስ ብሎታል፤ እኔም የደስታው ተካፋይ ሆንኩ፡፡

> ከእግዚአብሔር የተቀበልነውን ነገር አጥብቀን መያዝ አለብን፡፡

ይህ ከሆነ ከአንድ ዓመት ብዙ ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ ሰውየውን እንደ ገና አገኘሁት፡፡ በፊት ያየሁበት ፈገግታ አልነበረም፡፡ እንዲያውም ሊያናግረኝ የመጣው እርሱ አልነበረም፡፡ እኔ ወደ እርሱ ሄድኩና አናገርኩት፡፡ የጀርባ ሕመሙ እንደ ገና መመለሱን ነገረኝ፡፡ በዚያ ምሽት ተቀብሎ የነበረው ፈውስ እውነት መሆኑን ተጠራጥሮአል፡፡ እግዚአብሔር በዚያ ሕመም ሊያስተምረው የፈለገው ትምህርት ሊኖር ስለሚችል፣ የሕመሙ እንደ ገና መመለስ በፍጹም መጥፎ ሊሆን እንደማይችል ሊያሳምነኝ ሞከረ፡፡ የተሰጠንን አጥብቀን ስለ መያዝ ኢየሱስ የተናገረውን ላካፍለው ሞከርኩ፤ እርሱ ግን የነገርኩት ይህን ያህል ስሜት አልሰጠውም ነበር፡፡ ራሱን በተቃራኒው ነበር ያሳመነው፡፡ ጥሩ ሰው ቢሆንም፣ ጥሩ አባትና ጥሩ ባል ቢሆንም፣ እንዳለ መታደል ሆኖ፣ እርሱን ነጻ ለማድረግ ኢየሱስ ውድ ዋጋ የከፈለበትን ሸክም እስከዚህ ቀን ድረስ እንደ ተሸከመ ነው፡፡

## አለመቀበል አይቻልም

አሁን የምነግራችሁ ነገር እጅግ በጣም አስፈላጊ ነው፡፡ ካመናችሁና ከፉውን በመቃወም ከጸናችሁ ሁሌም ታሸንፋላችሁ፡፡ የተቀበላችትን አጥብቃችሁ ያዙ፤ በድፍረት የተስፉ ቃሉን በማወጅ ርምጃ ውሰዱ፣ ‹‹ዲያብሎስን ተቃወሙት፤ ከእናንተም ይሸሻል፡፡›› (ያዕቆብ 4÷7)፡፡

‹‹ይሸሻል›› የሚለውን ግሪክኛው ፌይጆ (Pheugo) ይለዋል፡፡ ‹‹ይጠፋል፤ ያመልጣል፤ ይፈረጥጣል፤ በመሸሸ ራሱን ያድናል›› ማለት ነው፡፡ እንዲያውም አንዳንዶች ፌይጆ ‹‹ደንብሮ መሸሸ›› እንደ ሆነ ሲያስተምሩ ሰምቻለሁ፡፡ ጥሩ ትርጉም ነው! የእግዚአብሔር ቃል ዲያብሎስ ምናልባት ይሸሽ ይሆናል አይደለም የሚለው፡፡ ከተቃወማችሁት እንደሚሸሽ ነው የሚናገረው፡፡ መጽሐፍ ቅዱስን መሠረት ያደረገ፣ ደፋር ተቃውሞን በጣም ይጠላል!

የእግዚአብሔርን ቃል እስከ ያዛችሁ ድረስ፣ ጠላት እናንተን እንደሚፈራ ማወቅ አለባችሁ፡፡ እናንተን ሲያይ፣ ጓደኞቻችሁ የሚያዩትን ሳይሆን ክርስቶስን ያያል፡፡ የክርስቶስ አካል ናችሁ፤ በእግዚአብሔር የተቀባችሁ ናችሁ፡፡ ሰይጣንን በደመሰሰውና መሣሪያዎቹን ሁሉ በነጠቀው በክርስቶስ መልክ ተፈጥራችኋል፡፡ ለሰይጣን ከባድ ስጋት ናችሁ፡፡ ብዙዎቻችን የሰይጣንን ኃይል በጣም አግዝፈን እናስባለን፤ የእግዚአብሔር ቃል እንደሚነግረን ግን ከእግራችን በታች ነው፤ ከክርስቶስ አካል እግሮች በታች ነው፡፡ የክርስቶስ አካል ውስጥ በጣም ትንሹ የእግር ጣት ብትሆኑ እንኳ፣ የጠላት ኃይል በክርስቶስ ካላችሁ ቦታ ወይም ማንነት በታች ነው፡፡ መጽሐፍ ቅዱስ እንዲህ ይላል፣

> አንተ የንጋት ልጅ አጥቢያ ኮከብ ሆይ እንዴት ከሰማይ ወደቅህ! አንተ ቀድሞ መንግሥታትን ያዋረድህ እንዴት ወደ ምድር ተጣልህ! በልብህ እንዲህ አልህ፣ ‘ወደ ሰማይ ዐርጋለሁ፤ ዙፋኔንም ከእግዚአብሔር ከዋክብት በላይ ከፍ አደርጋለሁ፤ በተራራው መሰብሰቢያ፣ በተቀደሰውም ተራራ ከፍታ ላይ በዙፋኔ እቀመጣሁ፤ ከደመናዎች ከፍታ በላይ ዐርጋለሁ፤ ራሴንም እንደ ልዑል አደርጋለሁ፡፡’ ነገር ግን ወደ ሲኦል፣ ወደ ጥልቁም ጉድጓድ ወርደሃል፡፡ የሚያዩህ አትኩረው እየተመለከቱህ በመገረም ስለ አንተ እንዲህ ይላሉ፣ ‹‹ያ ምድርን ያናወጠ፣ መንግሥታትን ያንቀጠቀጠ ይህ ሰው ነውን›› (ኢሳይያስ 14÷12-16)፡፡

ከታሪክ አንጻር ኢሳይያስ እየተናገረ የነበረው ስለ ባቢሎን ንጉሥ ነው፡፡ ይሁን እንጂ፣ ብዙ ጊዜ የቅዱሳት መጻሕፍት ትንቢቶች ሁለት የተለያዩ መልእክቶችና ትርጒሞች ይኖራቸዋል - አንዱ ቁሳዊ ሲሆን ሌላው መንፈሳዊ፡፡ ግለ ሰቦችን፣ ቤተ ሰቦችንና መንግሥታትን ስላወደመ ኃያል ኢሳይያስ ሲናገር፣ ያለ ጥርጥር በመንፈሳዊ ደረጃ ስለ ሰይጣን እየተናገረ መሆኑ ግልጽ ነው፡፡ እንደ ኢሳይያስ ከሆነ የእርሱና የሰራዊቱ ፍጻሜ፣ ‹‹ቀንና ሌሊት ከዘላለም እስከ ዘላለም›› ወደሚሰቃይበት ጥልቅ መጣል ይሆናል (ራእይ 20፥10)፡፡

ካመናችሁና የጨለማ ኃይላትን በመቃወም ከጸናችሁ፣ ከእግዚአብሔር ዘንድ በረከትና ነጻነት አለመቀበል አይቻልም፡፡ ይህም ገንዘብን፣ ጥበብን፣ ጤናን፣ ሥራን፣ አገልግሎትን፣ ከሁሉም በላይ ደግሞ ሌሎችን የመርዳት ችሎታን በተመለከተ ሊሆን ይችላል፡፡ በመንፈስ ሰይፍ ከተዋጋችሁ እንደ ኢየሱስ ምንጊዜም አሸናፊዎች ትሆናላችሁ፡፡

## ማስጠንቀቂያ

ይህን ምዕራፍ ከመዝጋቴ በፊት ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ስለታዘብኳቸው ሁለት ጽንፎች መናገር እፈልጋለሁ፡፡ የመጀመሪያው በእያንዳንዱ ቁጥቋጦ ውስጥ ዲያብሎስን የማየት ጽንፍ ነው፡፡ በዚህ ምድብ ውስጥ ያሉ ክርስቲያኖች በብዛት ስለ አጋንንት ስለሚያስቡ ዓይኖቻቸውን ከጌታ ላይ አንሥተዋል፡፡ ይህ በፍጹም ጤናማ አይደለም፡፡ ሁለተኛው ጽንፍ ምንም እንኳ፣ እግዚአብሔርን ቢወዱም ወደ ቢሮዬ መጥቶ እንደ ነበረው ፓስተር ኬን ጨርሶ ጠላትን ችላ ማለት ነው፡፡ በዚህ ምድብ ውስጥ ያሉ አብዛኞዎቹ ክርስቲያኖች ጠላትን ችላ ካልኩት የኋላ ኋላ እርሱም ትቶ ይሄዳል የሚል አስተሳሰብ አላቸው፡፡ ይህ ከንቱና ከእውነት የራቀ ነው፡፡ በንቃት ጠላትን እንድንቃወምና፣ የእግዚአብሔር ፈቃድ እስኪያሸንፍ ድረስ፣ እንደዚያ ማድረጋችንን እንድንቀጥል ታዝዘናል፡፡ በኢየሱስ ስም እስካልተጋፈጥነው ድረስ ለውጥ እንደማይኖር በአእምሮአችን መያዝ አለብን፡፡ ፊት ለፊት ከመቃወም አታፈግፍጉ! እንደ የመንግሥቱ ዜጎች ውጊያ ግዴታችሁ ነው፤ ለእግዚአብሔር መታዘዛችሁን የምታሳዩበትና ይህም እግዚአብሔር በጸጋው በሰጣችሁ እጅግ ታላቅ ኃይል የሚሆን ነው፡፡

መጽሐፍ ቅዱስ በመንፈሳዊ ጤናማነት እንዴት እንደምንኖር ያስተምረናል፡፡ ‹‹በፊታችን ያለውን ሩጫ በጽናት እንድንሮጥ፡፡ የእምነታችን ጀማሪና ፍጹም አድራጊ የሆነውን ኢየሱስን እንድንመለከት›› ተነግሮናል (ዕብራውያን 12፥1-2)፡፡ ዓይኖቻችንን ኢየሱስ ላይ ማድረግና

በዚያ መጽናት ጤናማ አኗኗር ነው፡፡ ሰይጣንም ሆነ የእርሱ ወገን ከሆኑት አንዱ በመንገዳችሁ ጣልቃ ሲገባ በሚገባ ተቃወሙት! ብትቃወሙት ከእናንተ ይሸሻል፡፡ ሆኖም፣ ወዲያውኑ ትኩረታችሁን ወደ ኢየሱስ መልሱ፡፡ እምነታችንን የሰጠን እርሱ ነው፤ በእምነታችን ፍጹም የሚያደርገንም እርሱ ነው፡፡

# 14

# ላቅ ያለ የመቃወም መንገድ

*በዓለም ዙሪያ ያሉት ወንድሞቻችሁ ተመሳሳይ መከራ እንደሚቀበሉ ዐውቃችሁ በእምነት ጸንታችሁ ተቃወሙት››*

*1ጴጥሮስ 5፥9*

ለምሳሌ የአንድ ሌላ አገር ጦር በወረራ አገራችሁን ይዞአል እንበል፡፡ እውነተኛ ነጻነት ማግኘት ከፈለጋችሁ ፊት ለፊት ጠላትን ከመግጠም ባለፈ፣ ጠላት ያበጃቸው ምሽጎችንም ታፈራርሳላችሁ፡፡ ብዙ ጊዜ እንዲህ ያሉ ምሽጎች በፈንጂዎችና በድንጋይ ካቦች ይታጠራሉ ወይም ደግሞ ከምድር በታች በተዘጋጀ ጉድጓድ ውስጥ ይሆናሉ፡፡

ይሁን እንጂ፣ ለማፍረስ እጅግ በጣም አስቸጋሪ ከሚሆንባችሁ ምሽጎች አንዱ በቁጥጥሩ ሥር ባደረገው ሕዝባችሁ አእምሮ ውስጥ ጠላት የሚያኖረው የተዛባ አስተሳሰብ ነው፡፡ እንዲህ ያለው ሁኔታ ስነ ልቦናዊ በመሆኑ በቀጥታ ውጊያ መቆጣጠር አይቻልም፡፡ ይሁን እንጂ፣ እንዲህ ያለውን የጦርነቱን ስውር ገጽታ ካላሸነፋችሁ፣ በቀጥታ ፊት ለፊት በመዋጋት ብቻ የምታገኙት ድል የኃላ የኃላ ዘላቂ አይሆንም፡፡

ከዚህ ምዕራፍ ለእንዲህ ዓይነቱ ተቃውሞ ራሳችንን ዝግጁ ማድረግ ስለምንችልበት ሁኔታ እንማራለን፡፡ በቀጥታ ፊት ለፊት እንደሚደረገው ውጊያ ሁሉ ይኸኛውም ጽናትን ይጠይቃል፡፡ እንደዚያ ካልሆነ ሌሎች የውጊያ ዐይነቶች ሁሉ ዘላቂ ውጤት አያስገኙም፡፡ ‹‹ራሳችሁን ለእግዚአብሔር አስገዙ፤ ዲያብሎስን ተቃወሙት ከእናንተም ይሸሻል›› በማለት ሐዋርያው ያዕቆብ ስለዚህ ውጊያ ይናገራል፡፡ ይህም ዘወትር በእግዚአብሔር በመተማመንና ለእርሱ በመታዘዝ መኖር አለብን ማለት ነው፡፡ እንደዚያ ስናደርግ የእርሱን መንገድ፣ የእርሱን ሐሳብና መርሐ በዙሪያችን ወዳለው ጠማማ ዓለም እናስተላልፋለን፡፡ ፍጹም ታዛዥነት፣ የጠላትን ምሽግ በማጥቃትና እኛም ወደ አዲስ የሥልጣንና የአገዛዝ ደረጃ ከፍ እንድንል በማድረግ ረገድ ዋነኛ የውጊያ ስልት ነው፡፡ ጳውሎስ የሚለውን ስሙ፣

> የምንኖረው በዚህ ዓለም ቢሆንም፣ የምንዋጋው በዚህ ዓለም ስልት አይደለም፡፡ ደግሞም የምንዋጋበት የጦር መሣሪያ የዚህ ዓለም መሣሪያ አይደለም፤ ይሁን እንጂ፣ ምሽግን ለመደምሰስ የሚችል መለኮታዊ ኃይል ያለው ነው፡፡ በእግዚአብሔር ዕውቀት ላይ በትዕቢት የሚነሣውን ክርክርና ከንቱ ሐሳብ ሁሉ እናፈርሳለን፤ አእምሮንም ሁሉ እየማረክን ለክርስቶስ እንዲታዘዝ እናደርጋለን፡፡ መታዘዛችሁ በተፈጸመ ጊዜ አለመታዘዝን ሁሉ ለመቅጣት ተዘጋጅተናል፡፡ (2 ቆሮንቶስ 10፥3-6)

የሰይጣን ምሽጎች የአስተሳሰብ ሂደቶች፣ የአእምሮ ዝንባሌዎች፣ አመለካከቶች፣ ዕይታዎችና የእግዚአብሔርን ዕውቀት ወይም ፈቃድ የሚቃረኑ ማናቸውም ዐይነት ስነ ልቦናዊ ግንዛቤዎች ሊሆኑ ይችላሉ፡፡ በዚህ ዝርዝር ብቻ ባይወሰንም ይህ ቅንዓትን፣ ስግብግብነትን፣ ራስ ወዳድነትን፣ ጫና ማድረግን፣ መጐምጀትን፣ ጥላቻን፣ ፀብን፣ አታላይነትና ምቀኝነትንም ይጨምራል፡፡ እነዚህ የልብና የአእምሮ ዝንባሌዎች የእግዚአብሔርን እውነት ይቃረናሉ፤ እውነተኛና የከረረ መንፈሳዊ ግጭትም ያስከትላሉ፡፡ ይሁን እንጂ፣ ጳውሎስ እንደሚለው መታዘዛችን እንዲህ ያሉትን ዐመፆች ከሥራቸው ነቅለን የምናስወግድበትን ኃይል ያስታጥቀናል፡፡

## በክርስቶስ ማደግ

ቀደም ባለው ምዕራፍ እንደ ተገለጸው አዳጋች ሁኔታዎችን በሚገባ ማስተናገድ ስንችል የሥልጣንና የኃይል ደረጃችንም ከፍ ይላል፡፡ በሌላ አነጋገር ወደ አገዛዝ ቦታ እያደግን፣ ከፍ እያልን እንመጣለን፡፡ ራስን ስለ ማስታጠቅ ጴጥሮስ ወደሚሰጠው ምክር ስንመለስ፣ እንዲህ የሚል እናነባለን፤

> እንግዲህ ክርስቶስ በሥጋው መከራን ስለ ተቀበለ እናንተም በዚሁ ዓላማ ታጥቃችሁ ተነሡ፤ ምክንያቱም በሥጋው መከራን የሚቀበል ሰው ኃጢአትን ትቶአል፡፡ ከዚህም የተነሣ ከእንግዲህ በሚቀረው ምድራዊ ሕይወት እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ እንጂ፣ እንደ ሥጋ ምኞት አንኖርም፡፡ (1 ጴጥሮስ 4፥1-2)

መከራን የሚቀበል ሰው ኃጢአትን ትቶአል፡፡ ጴጥሮስ እንዲህ ሲል ምን ማለቱ ነው? መንፈሳዊ ግብ ላይ ስለ መድረስ፣ በክርስቶስ ሙሉ ሰው ወደ መሆን ደረጃ ስለ ማደግ እየተናገረ ነው፡፡ በእግዚአብሔር መንግሥት፣ ‹‹መንፈሳዊ ጉልማሳ›› የሆነ ሰው፣ ለእግዚአብሔር ፈቃድ ለመታዘዝ ሙሉ በሙሉ የተሰጠ ይሆናል እንጂ፣ የሰዎችን ፍላጐት ለመፈጸም አይኖርም፡፡ ከእንግዲህ ምሽጉን ያፈራርስበታል እንጂ፣ ለዚህ ዓለም ሥርዐት ተፅዕኖ

አይሸነፍም፡፡ 2 ቆሮንቶስ 10፥6 ላይ ጳውሎስ፣ ‹‹መታዘዛችሁ በተፈጸመ ጊዜ አለመታዘዝን ሁሉ ለመቅጣት ተዘጋጅተናል›› በማለት ነበር ይህን ኃይል የገለጸው፡፡

የዕድሜ ደረጃችን ምንም ይሁን ምን፣ በእግዚአብሔር ቤተ ሰብ የተወለድነው እንደ ሕፃን መሆኑን ማስታወስ አለብን፡፡ ስለዚህ እንድናድግ ይጠብቅብናል፡፡ ‹‹እንድታድጉ አዲስ እንደ ተወለዱ ሕፃናት ንጹሑን መንፈሳዊ ወተት ተመኙ›› ተብለናል (1 ጴጥሮስ 2፥2)፡፡ በአካላዊ ሕይወታችን የተለያዩ የዕድገት ደረጃዎች እንዳሉ ሁሉ (ሕፃንነት፣ ልጅነት ጉልማሳነት...) በመንፈሳዊ ዕድገትም እንዲሁ ነው፡፡ ጳውሎስ፣ ‹‹ወንድሞች ሆይ፣ በክርስቶስ ገና ሕፃናት እንደ መሆናችሁ፣ እንደ ሥጋውያን እንጂ እንደ መንፈሳውያን ልናገራችሁ አልቻልሁም›› ይላል (1 ቆሮንቶስ 3፥1)፡፡ እነዚያ የቆሮንቶስ ክርስቲያኖች በዕድሜ ትልልቅ ሰዎች ሊሆኑ ይችላሉ፣ መንፈሳዊ ብስለትን በተመለከተ ግን ገና ሕፃናት ነበሩ፡፡ ለአንድ አማኝ፣ በዚያ ደረጃ ተወስኖ መቅረት በጣም አሳዛኝ ነው፡፡

በሌላ መልእክቱ ጳውሎስ ስለ ቀጣዩ መንፈሳዊ ዕድገት ደረጃ ይናገራል፤ ‹‹ከእንግዲህ... በልዩ ልዩ ዐይነት የትምህርት ነፋስ ወዲያ ወዲህ እየተንገዋለልን ሕፃናት አንሆንም›› (ኤፌሶን 4፥14)፡፡ እንደ ገና ጳውሎስ፣ ‹‹ወንድሞች ሆይ፣ በአስተሳሰባችሁ ሕፃናት አትሁኑ፤ ለክፉ ነገር ሕፃናት ሁኑ፤ በአስተሳሰባችሁ ግን ጉልማሶች ሁኑ›› በማለት ይጽፋል (1 ቆሮንቶስ 14፥20)፡፡ ሐሜትንና ክፋትን በተመለከተ ግን የጉለመስን አማኞች መሆን አለብን፡፡ አንድ ሕፃን ምላሽ የሚሰጠው መልካምም ይሁን መጥፎ፣ በተሰጠው ሥልጠና መሠረት ነው፡፡ እንዲሁም ሕፃናት ለጥቃትና ለማንኛውም ዐይነት ተፅዕኖ የተጋለጡ ናቸው፡፡ ይሁን እንጂ፣ ጉልማሶች ብዙ ጊዜ የት ወይም እንዴት እንደ ቆሙ ያውቃሉ፤ በክፉ ኃይሎች ወዲያ ወዲህ በቀላሉ አይወሰዱም፡፡ በእውነት ላይ ጸንተን መቆም እንድንችልና ውጤት ባለው መልኩ ማንኛውንም አለመታዘዝ መልሰን እንድንገፋ ወይም እንድንቀጣ በክርስቶስ እንድናድግ ተነግሮናል፡፡ ጳውሎስ እንደሚነግረን በክርስቶስ ማደግ፣ መረዳት ወይም ማስተዋልን ይጠይቃል፡፡ ያም ሆኖ ግን፣ ከዚያ ያለፈ ነገርንም ያካትታል፤ ጴጥሮስ ያንን በማንሣት ይናገራል፡፡

በመንፈሳዊ ሕይወታችን የምናድገው እንዴት ነው? ይህን ለመረዳት በመጀመሪያ አካላዊና አእምሮአዊ ዕድገትን መረዳት ይጠቅማል፡፡ አካላዊ ዕድገት የምን ውጤት ነው ገደቡስ ምንድነው? የጊዜ ውጤት ነው፤ በጊዜ የተገደበ ነው፡፡ የስድስት ወር እያለ አንድ ሜትር ርዝማኔ ያለው ሕፃን አይታችኃል? በፍጹም፤ የአንድ ጉልማሳ ቁመት እንዲኖር ከተፈለገ፣

ብዙውን ጊዜ ከዐሥራ አምስት እስከ ዐሥራ ስምንት ዓመት ይጠይቃል፡፡ አካላዊ ዕድገት በጊዜ ሂደት የሚመጣ ነው፡፡

በአንጻሩ ግን የአእምሮ ዕድገት በጊዜ የተገደበ አይደለም፡፡ በዐሥራ አራት ዓመታቸው ከሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የተመረቁና፣ ‹‹የልጅ ዐዋቂ›› የተባሉ ልጆች አውቃለሁ፡፡ ሃምሳ ዓመት የሆናቸውና ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ያላጠናቀቁ ሰዎች አውቃለሁ፡፡ ስለሆነም በአእምሮ ወይም በዕውቀት ማደግ የጊዜ ጉዳይ ሳይሆን፣ የመማር ጉዳይ ነው፡፡ በመጀመሪያ አንደኛ፣ ቀጥሎ ሁለተኛ፣ ሦስተኛ፣ አራተኛ፣ አምስተኛ… እያላችሁ መሄድ አለባችሁ፡፡ ይሁን እንጂ፣ ይህን እንደ ፍላጐታችሁ በፍጥነት ወይም በዝግታ ልታደርጉት ትችላላችሁ፡፡

ታዲያ፣ መንፈሳዊ ዕድገትና በሳልነትስ የጊዜ ውጤት ይሆን? በጊዜ ይገደብ ይሆን? ዳግም ከተወለዱ ገና አንድ ዓመት ብቻ ቢሆናቸውም፣ በክርስትና ሕይወታቸው በጣም ያደጉና የበሰሉ ሰዎች ተመልክቻለሁ፡፡ በአንጻሩም ድነትን ካገኙ ሃያ ዓመት ያለፋቸውና አሁንም እንደ ሕፃን ‹‹መንፈሳዊ ዳያፐር›› የሚደረግላቸው ክርስቲያን መሪዎቻቸውንና አማኝ ወዳጆቻቸውን የሚያስቸግሩ ሰዎችንም አውቃለሁ፡፡ ስለሆነም መንፈሳዊ ብስለት የጊዜ ውጤት አይደለም፡፡

መንፈሳዊ ዕድገትና ብስለት የመማር ውጤት ይሆን? በመማር የሚገደብ ይሆን? ፈሪሳውያን የመጀመሪያዎቹን አምስት የመጽሐፍ ቅዱስ መጻሕፍት በቃላቸው ሸምድደው ነበር፤ በቃል ከያዙትም ይጠቅሱ ነበር፤ ሆኖም፣ በዐይናቸው ፊት በሽተኞችን ቢፈውስም፣ አጋንንትን ቢያስወጣም፣ የእግዚአብሔርን ልጅ አላወቁትም፡፡ ሕይወታቸው በግብዝነት የተሞላ ነበር፤ የመሲሑን መምጣትና አገልግሎቱን በተመለከተ መንፈሳዊ ዐይኖቻቸው ታውረው ነበር፡፡

ታዲያ መንፈሳዊ ዕድገት የምን ውጤት ነው? ገደቡስ ምንድነው? መልሱ፣ የመከራ ውጤት ነው፡፡ የጴጥሮስን ቃሎች እንደ ገና ተመልከቱ፤ ‹‹በሥጋው መከራን የሚቀበል ሰው ኃጢአቱን ትቶአል›› (1 ጴጥሮስ 4፥1)፡፡ ኃጢአቱን የተወ ደግሞ የተሟላ መንፈሳዊ ብስለት ላይ ይደርሳል፡፡

እንግዲህ እዚህ ላይ ብዙ፣ ‹‹መከራ የተቀበሉ ሰዎች አውቃለሁ፤ ግን በመንፈሳዊ ሕይወታቸው ከማደግ ይልቅ አሁን መራሮች ሆነዋል›› የሚል ክርክር ሊነሣ ይችላል፡፡ አዎን፣ እንዲህ ያሉ ሰዎችን በቀላሉ ማግኘት ይቻላል፡፡ ስለዚህም ለመንፈሳዊ ብስለት ወሳኝ የሆነ አንድ ሌላ ቁልፍ መኖር አለበት፡፡ የዕብራውያን መልእክት ጸሐፊ፣ ‹‹የእግዚአብሔር ልጅ

ቢሆንም እንኳ፣ ከተቀበለው መከራ መታዘዝን ተማረ›› የሚል ፍንጭ ይሰጠናል (ዕብራውያን 5፥8)

ይህ ጥቅስ ኢየሱስ ወደ ምድር ሲመጣ ወዲያውኑ በቅጽበት ታዛዥ እንዳልሆነና ይልቁንም መታዘዝን መማር እንደ ነበረበት ይነግረናል፤ ያንንም በጥሩ ሁኔታ እንደ ፈጸመ ይነግረናል፤ እርሱ ኃጢአት ወይም ስሕተት አላደረገም፡፡ ለአሁኑ ጉዳያችን ቁልፍ የሆነው ነጥብ ኢየሱስ በመከራ ውስጥ መታዘዝን ተማረ የሚለው ነው፡፡ እንግዲህ ይህን ጥቅስ ከጴጥሮስ ቃል ጋር ስናያይዘው መንፈሳዊ ዕድገት፣ ፀሐይ በሕይወታችን ደምቃ ስታበራ፣ ሰው ሁሉ ስለ እኛ ጥሩ ነገር ሲናገርና ጥሩ አያያዝ ሲያደርግልን፣ ሁሉም ነገር በመልካም ሁኔታ በመሄድ ላይ እያለ የሚመጣ እንዳይደለ ግልጽ ያደርጋል፡፡ ይልቁንም በመከራና በፈተና መካከል ለእግዚአብሔር በመታዘዝ ስንጸና፣ በመንፈሳዊ ሕይወታችን እንደምናድግ ነው የሚነግረን፡፡ ሰዎች ክፉ ሲያደርጉብን፣ በማናውቀው ነገር ሲያሙን፣ ሲበድሉን፣ ሊጎዱን ሲሞክሩ... ወይም ሥራ ስናጣ፣ ከጠበቃ ወይም ከዶክተር ደስ የማይል ወሬ ስንሰማ ወይም፣ የሚያስፈልገንን ነገር ከየት እንደምናገኝ እርግጠኛ ባልሆንን ጊዜ፣ ለእግዚአብሔር ጥበብ ራሳችንን ስናስገዛ እናድጋለን፤ እንበረታለን፡፡

ምንም እንኳ የማይጠቅመን ቢመስለንም በችግራችን መካከል በእግዚአብሔር መተማመንን እንመርጣለን፡፡ በተቀዳሚና በመጀመሪያ ደረጃ፣ ለእግዚአብሔር ቃል በመታዘዝ የክፉውን ጥቃት እንቃወማለን፡፡ እውነተኛ መንፈሳዊ ዕድገት የሚመጣው ያኔ ነው፡፡ ይህ ደግሞ በያዕቆብ ልጅ በዮሴፍ ሕይወት ምሳሌነት በጥሩ ሁኔታ ታይቷል፡፡

## የዮሴፍ ሕልም

እግዚአብሔር ከአብርሃም ጋር ኪዳን አድርጐ ነበር፡፡ ይኸው ኪዳን ወደ ልጁ ወደ ይስሐቅ፣ ወደ የልጁ ልጅ ያዕቆብ ተሸጋግሮ ነበር፡፡ ያዕቆብም ዐሥራ ሁለት ልጆች ነበሩት፤ ዐሥራ አንደኛው ዮሴፍ ነበር፡፡ ታላላቅ ወንድሞቹ ዮሴፍን ይጠሉት ነበር፤ ምክንያቱ ምን እንደ ነበር መጽሐፍ ቅዱስ ያመለክታል፡፡ ወጣቱ ዮሴፍ መጥፎ ወሬ ያመላልስ ነበር (ዘፍጥረት 37፥2)፣ ትንሽ ጉረኛ ብጤም ነበር (ቁጥር 5)፡፡ አባታቸው ያዕቆብ ከሌሎቹ አስበልጦ ዮሴፍን ይወድ ነበር፤ ከዚህም ሌላ አባቱ የሰጠው በኅብረ ቀለማት ያጌጠ እጀ ጠባብም የበለጠ ሳያሞላቅቀው አልቀረም፡፡ እንዲህ እንዲህ ያሉ ነገሮች ዮሴፍ በወንድሞቹ እንዲጠላ አደረጉ፡፡

ግንኙነታቸው ሻክሮ በነበረበት በዚህ ጊዜ እግዚአብሔር ለዮሴፍ ሁለት ሕልሞች ሰጠው፡፡ በመጀመሪያው ሕልሙ፣ ዕርሻ ውስጥ ዐሥራ ሁለት የታሰሩ ነዶዎች አየ፡፡ የእርሱ ነዶ ቀጥ ብላ ስትቆም የወንድሞቹ ነዶዎች ግን ወደቀው ሰገዱላት፡፡ በሁለተኛው ሕልሙ፣ ዮሴፍ ፀሐይና ጨረቃ እንዲሁም ዐሥራ አንድ ከዋክብት ሲሰግዱለት አየ፡፡ ዮሴፍ በገራገርነትና በስሜት ከራሱ ትርጉም ጋር ሕልሙን ለወንድሞቹ ተናገረ፡፡ ወንድሞቹ ግን የዮሴፍን ስሜት አልተጋሩም፤ እንዲያውም የበለጠ ጠሉት፡፡

በኋላም ለአባታቸው መንጋዎች ግጦሽ ፍለጋ ዐሥሩ ወንድሞቹ ከቤት በጣም ርቀው ሄደው ነበር፡፡ ጊዜ እየረዘመ በመሄዱ እንዴት እንደ ሆኑ እንዲያይ ያዕቆብ ዮሴፍን ላከው፡፡ ታላላቅ ወንድሞቹ ወደ እነርሱ እየመጣ መሆኑን ሲያዩ፣ ‹‹ሕልመኛው ትንሹ ወንድማችን እየመጣ ነው፤ አነግሥባችኃለሁ ባዩ ያውና፡፡ እንግደለው! ያኔ ሕልሙ ምን እንደሚሆን እናያለን›› በማለት ዶለቱበት፡፡

እዚያ ውስጥ እንዲሞት በማሰብ ጉድጓድ ውስጥ ከተቱት፡፡ ከጥቂት ጊዜ በኋላ ግን ወደ ግብፅ እየሄዱ ያሉ፣ ግመሎቻቸውንና ሸቀጣ ሸቀጦችን የጫኑ እስማኤላውያን በዚያ በኩል ሲያልፉ አዩ፡፡ አራተኛው ልጅ ይሁዳ አንድ ጥሩ ነገር አሰበ፡፡ ‹‹ወንድማችንን መግደል ምንም አይጠቅመንም፡ እርሱን ለባርነት ሸጠን ገንዘብ ብናገኝ ይሻላል፡፡ በዚህ ላይ ደግሞ እርሱን በመግደል ማንም እኛን ተጠያቂ ማድረግ አይችልም›› አለ፡፡

ወንድሞቹ ሁሉ በሐሳቡ ተስማሙና ዮሴፍን በሃያ ጥሬ ብር ሸጡት፡፡ ከርስቱና ከቤተ ሰቡ ዮሴፍን ለመንቀል ያነሣሣቸው ቅናት፣ ጥላቻና መጥፎ ሐሳብ ነበር፡፡ ልብ አድርጉ፣ ይህ ሁሉ የደረሰበት በሥጋ ወንድሞቹ ነበር!

በዚህ ዘመን ያለን ብዙዎቻችን ዮሴፍ ላይ የተፈጸመውን ግፍ ማሰብ ይከብደናል፡፡ እርሱን ለባርነት መሸጥ ከመግደል ያላነሰ ጭካኔ ነበር፡፡ የአባታቸው ስም መጠሪያና የርስት ወራሾቻቸው ስለሚሆኑ በዚያ ዘመን ወንዶች ልጆችን መውለድ በጣም ጠቃሚ ነበር፡፡ የዮሴፍ ወንድሞች ይህን ክብር አሳጥተውታል፡፡ ስሙን ደምስሰዋል፤ ሙሉ በሙሉ ማንነቱን ገፍፈውታል፡፡ በዚያ ዘመን አንድ ሰው በባርነት ወደ ሌላ አገር ከተሸጠ፣ እስኪሞት ድረስ ባሪያ ሆኖ ይኖር ነበር፡፡ ሚስቱና ልጆቹም እንደ እርሱ ባሪያዎች ይሆናሉ፡፡ ዮሴፍን በተመለከተ እርሱ የሚያውቀውና ለእርሱ ውድ የነበረ ነገር ሁሉ ተወስዷል፡፡ በዕድሜ ዘመን ሁሉ ባሪያ ሆኖ መኖር፣ እጅግ ሲበዛ ከባድ ነበር፤ ሆኖም፣ ከአንድ ሀብታም ቤተ ሰብ መወለድና በገዛ ወንድሞች ክፋት የመውረስ መብትን ማጣት ደግሞ መግለጽ በማይቻል መልኩ እጅግ ከባድ ነበር! ከእንግዲህ ዮሴፍ፣ ‹‹በቁሙ የሞተ›› ያህል ነበር፡፡

የዮሴፍ ወንድሞች ያደረጉት መግለጽ በሚያዳግት ሁኔታ ከባድ ጭካኔ ነበር፡፡

ዮሴፍን የገዙ እስማኤላውያን ግብፅ ሲደርሱ፣ የፈርዖን ባለ ሥልጣን ለሆነ ጴጥፋራ ለሚባል ሰው ሸጡት፡፡ ከእንግዲህ እርሱ የጴጥፋራ ንብረት ነው፡፡ እኔና እናንተ ከተፈጸመ ሺህ ዓመታት በኋላ ታሪኩን ከመጽሐፍ ቅዱስ ማንበብ እንችላለን፤ ውጤቱ ምን እንደ ሆነም እናውቃለን፡፡ ዮሴፍ ግን የሚያነበው የዘፍጥረት መጽሐፍ አልነበረውም፡፡ በባዕድ ምድር ባርያ እንዲሆን ከመሸጡ ውጪ የወደ ፊት ሕይወቱ ምን እንደሚሆን አያውቅም፡፡ ከእንግዲህ አባቱን፣ ወዳጆቹን ወይም የትውልድ አገሩን የሚያይ አልመሰለውም፡፡ ሕልሞቹ ሲፈጸሙ የማየት ዕድል ይኖረኛል ብሎ አላሰበም ነበር፡፡ እንዴት ሊፈጸሙ ይችላሉ? በግብፅ ባሪያ ነው፤ በሕይወት እስካለ ድረስ የሌላ ሰው ንብረት በመሆኑ፣ ከእንግዲህ ግብፅን ለቅቆ መውጣት አይችልም፡፡

ግን በእምነት እንጂ፣ በማየት አንመላለስም፡፡

ዮሴፍ ጲጥፋራን ዐሥር ዓመት ሙሉ አገለገለ፡፡ በዚህ ጊዜ ውስጥ አንዴ እንኳ ከቤተ ሰቡ አልሰማም፤ ወንድሞቹ እርሱ መሞቱን ለወዳጅ ዘመዶቹ እንደሚናገሩ እርግጠኛ ነበር፡፡ በዚህ ጊዜ አባቱ በእርሱ መሞት እንዳለቀሰና ያለ እርሱ ሕይወቱን እየገፋ እንደ ሆነ እርግጠኛ ነበር፡፡ ከአባቱ ጋር እገናኛለሁ የሚል ተስፋ አልነበረውም፡፡

በጊዜ ወስጥ ዮሴፍ በጴጥፋራ የሚወደድ ሆነ፡፡ የጴጥፋራ ቤትና ንብረት በሙሉ ኃላፊ ሆነ፡፡ ሆኖም ውስጥ ውስጡን አንድ የሚያውከው ነገር ነበር፡፡ የጴጥፋራ ሚስት የምኞት ዐይኗን ጥላበት ነበር፤ ያንን በተመለከተም እፍረት የሚሰማት ዐይነት አልነበረችም፡፡ እንዲያውም ከእርሷ ጋር እንዲተኛ በየቀኑ ትወተውተው ነበር፡፡ እርሱን ለማሳሳት ብዙ ሙከራ አደረገች፡፡ ይሁን እንጂ፣ ዮሴፍ የምታደርገውን ማንኛውንም ሙከራ ተቃወመ፤ ‹‹በዚህ ቤት ላይ ከእኔ የበለጠ ኃላፊነት ያለው ማንም የለም፤ እርሱ ያልሰጠኝ ነገር ቢኖር አንቺን ብቻ ነው፤ ያውም ሚስቱ ስለሆንሽ ነው፤ ታዲያ፣ እኔ ይህን ክፉ ድርጊት ፈጽሜ እንዴት በእግዚአብሔር ፊት ኃጢአት እሠራለሁ?›› አለ (ዘፍጥረት 39፥9)፡፡ ምንም እንኳ፣ የወጣትነት ዕድሜው በተፈጸመበት ክህደት የተበላሸና ተስፋ የሌለው ቢመስልም፣ ዮሴፍ የእውነት ሰው በመሆኑ ለአምላኩ ተገዛ፤ ቁልፉ ይኸው ነበር፡፡

አንድ ቀን ቤቱ ውስጥ ዮሴፍና የጴጥፋራ ሚስት ብቻ ነበሩ፡፡ አሁንም እርሱን የማሳሳት ምኞቷ አብሯት ስለ ነበር ልብሱን ጨምድዳ በመያዝ፣ ‹‹በል አብረኸኝ ተኛ›› አለችው፡፡

እንደ ገና ዮሴፍ ተገቢ ያልሆነ ነገር ማድረግን እምቢ በማለት ከቤት ሸሽቶ ወጣ፡፡ በነገሩ በጣም የተናደደችው ሴትየዋ ነገሩን ለውጣ፣ ‹‹አስገድዶ ሊደፍረኝ ነበር!›› በማለት ጮኸች፡፡

ብዙም ሳይቆም ጴጥፋራ ዮሴፍ እንዲታሰር አደረገ፡፡ ልክ በወንድሞቹ በተሸጠ ጊዜ እንደ ሆነው ሁሉ፣ በዮሴፍ ሕይወት የነበረ ማንኛውም ጥሩ ነገር በድንገት በአንድ ቀን ብን ብሎ ጠፋ፡፡

## ውኂያ እስር ቤት ውስጥ

በአንዳንድ አገሮች ያሉ እስር ቤቶች ከፈርዖን እስር ቤት ጋር ሲወዳደሩ ምንም አይደሉም፡፡ በአሜሪካ ባሉ በርካታ እስር ቤቶች አገልግያለሁ፤ የቱንም ያህል መጥፎ ቢሆኑም፣ ከመካከለኛ ምሥራቅ እስር ቤቶች አንጻር እንደ ጥሩ ሆቴል ሊቆጠሩ ይችላሉ፡፡ በዚያ የዓለማችን ክፍል ያሉ ጥቂት ጥንታዊ እስር ቤቶችን ጎብኝቻለሁ፡፡ ብርዳማና የፀሐይ ብርሃን ጨርሶ የማያገኙ ናቸው፡፡ በአንዳንድ አገሮች እንዳሉ እስር ቤቶች የእስረኞች መሥሪያ ቦታ፣ ቴሌቪዥን፣ ምግብ ቤት፣ የሚተኙበት ፍራሽ የላቸውም፡፡

በዚያ ዘመን ውሃም ሆነ ምግብ ለእስረኞች የሚሰጠው በሕይወት ለመቆት የሚያስችላቸውን ያህል ብቻ ነበር (1 ነገሥት 22÷27 ይመ)፡፡ ከመዝሙር 105÷18 እንደምንመለከተው የዮሴፍ እግሮች በእግር ብረት ተጉድተው ነበር፤ እርሱም ብረት ማነቆ ውስጥ ገብቶ ነበር ይላል፡፡ ጴጥፋራ ዮሴፍን እስር ቤት ያስገባው እንዲሞት ነበር፡፡ ግብፃዊ ቢሆን ኖሮ የመፈታት ዕድል ማግኘት ይችል ነበር፤ ይሁን እንጂ፣ የንጉሡን ከፍተኛ ባለ ሥልጣን ሚስት አስገድዶ በመድፈር ወንጀል የተከሰሰ ከሌላ አገር የመጣ ባሪያ ስለ ሆነ ዮሴፍ ምንም ተስፋ አልነበረውም፡፡

በዚያ ቀዝቃዛና ጨለማ እስር ቤት ውስጥ ሆኖ ዮሴፍ ምን ሊያስብ እንደሚችል መገመት ትችላላችሁ? ምቹ ጊዜ የመጣለት የመሰለው ጠላት ያለ አንዳች ምሕረት አእምሮና አስተሳሰቡን ሳያጠቃ አልቀረም፡፡ በዚህ ጊዜ ዮሴፍ – *ጴጥፋራና ቤተ ሰቡን ከዐሥር ዓመት ይበልጥ በቅንነትና በታማኝነት ሳገለግል ኖሬአለሁ፡፡ ሌላው ቀርቶ ከሚስቱ እንኳ የበለጠ እኔ ለእርሱ ታማኝ ነበርኩ፡፡ ከግብረ ሥጋ ኃጢአት በየዕለቱ በመሸሽ ለእግዚአብሔርና ለምድራዊ አስተዳዳሪዬ ታማኝነቴን ጠብቄአለሁ፡፡ ታዲያ፣*

*ለዚህ ታማኝነቴ የተሰጠኝ ዋጋ ምንድነው? እስር ቤት መጣል! እንደ ማንኛውም ስሜቱ የጋለ ወንድ፣ ከዚያች ሴት ጋር በመተኛት የግብረ ሥጋ ግንኙነት የሚሰጠውን ደስታ ለምን ሳላገኝ ቀረሁ? ብቻችንን በነበርን ጊዜ ከእርሷ ጋር የግብረ ሥጋ ግንኙነት ፈጽሜ ቢሆን ኖሮ፣ ይኼኔ ማንም አያውቅም ነበር፤ እኔም እዚህ እስር ቤት አልሆንም ነበር* ብሎ ሊያስብ ይችላል፡፡

ለእንዲህ ዓይነቱ ትክክል ያልሆነ ሐሳብ ዮሴፍ አእምሮን ከፍቶ ቢሆን ኖሮ፣ *ለመሆኑ አፍቃሪና ታማኝ የሆነ አምላክ ለእርሱ ለሚታዘዙ ሰዎች የሚከፍለው ይህን ነው? እንዲያውም እርሱ ጨርሶ ታማኝ ሊሆን አይችልም፤ በእርሱ የተማመነ አገልጋዩን አዋርዷል፡፡ ሌላ ምንም በደል ሳይኖርብኝ፣ ለእርሱ በመታዘዜ ብቻ እኔ እዚህ ስሰቃይ፣ ዐመፀኛው ግን እንዲሳካለትና እንዲያሸንፍ ፈቅዷል፡፡ ታዲያ፣ ለእግዚአብሔር የመታዘዝ ጥቅሙ ምንድነው? መሪ እንደምሆን ሕልም አሳየኝ፤ እኔም በገርነት ያንን ለወንድሞቼ ነገርኩ፤ ታዲያ ባርነትና እስራት እንጂ ሌላ ምን ጠቀመኝ? እንዲያውም በታዛዥነቴ በጸናሁ መጠን፣ በዚያው ልክ የሕይወቴ ሁኔታም እየከፋ የሚሄድ ይመስላል፡፡ እግዚአብሔርን ማገልገል ዋጋ የለሽ ድካም ነው! ወደሚል ወራዳ የአስተሳሰብ ደረጃ የሚወርድበት በር ይከፈት ነበር፡፡*

በዚያ እስር ቤት ውስጥ ዮሴፍ የነበረው ነጻነት በጣም የተገደበ ነበር፤ ያም ሆኖ ግን፣ በእንደዚያ ያለ ሁኔታ ውስጥ እንኳ ቢሆን፣ ለደረሰበት ችግር የሚሰጠውን ምላሽ የመምረጥ መብት ነበረው፡፡ ታዲያ የትኛውን ይመርጥ ይሆን – ሕይወቱ በመራራነትና በቅርታ እንዲሞላ ይፈቅድ ይሆን? ንቀትና ጥላቻ ይሞላው ይሆን? የእግዚአብሔርን ቃል በመናቅ የመበቀል ሐሳብን ያስተናግድ ይሆን? የልቡን በር እያንኳኳ ላለው ጥላቻ ቦታ ይሰጥ ይሆን? ወይስ ልቡ ውስጥ እየፈሰሰ ያለውን አሉታዊ አስተሳሰብና ስሜት በጽናት ይቃወም ይሆን?

እነዚያ ተከታታይ አሳዛኝ ሁኔታዎች፣ እርሱን ለመሪነት ለማዘጋጀት እግዚአብሔር የተጠቀመባቸው መንገዶች መሆናቸውን ዮሴፍ የተረዳው ከብዙ ጊዜ በኋላ ሊሆን እንደሚችል አስባለሁ፡፡ በመከራ ውስጥ ዮሴፍ *መታዘዝን እየተማረ ነበር፡፡ የመታዘዝ ጡንቻው እየዳበረ ነበር፡፡* አሁን ባለበት ደረጃ 315 ፓውንድ ክብደት ያለው ነገር ሲሰጠው፣ ለዚያ የሚሆን ዐቅም የለኝም እያለ የሚጮኽ ሰው ይመስላል! *ታዲያ* አይዞህ በርታ፣ ጽና የሚለውን የሰማይ ድምፅ ይሰማል ወይስ ቀላሉን የመራራነትና የበቀልን *መንገድ ለመምረጥና ሰብዓዊ ፍጡርን ለማድመጥ በሸክሙ ጫና ይንበረከክ ይሆን?*

## እግዚአብሔር ሳያውቅ የሆነ ነውን?

ለዮሴፍ መከራ ዋናው ምክንያት ወንድሞቹ ነበሩ፡፡ እነርሱ ያንን ሁሉ በደል ባያደርሱበት ኖሮ እዚህ መከራ ላይ አይወድቅም ነበር፡፡ እስር ቤት ባሳለፋቸው ሁለት ዓመቶች ውስጥ፣ ወንድሞቹ ለጉዳት ባይዳርጉት ኖሮ ነገሮች ምንኛ የተለየ መልክ ሊኖራቸው ይችል እንደ ነበር ሳያስብ እንዳልቀረ እርግጠኛ ነኝ፡፡

እኛስ ብንሆን እንዲህ ያሉ ሐሳቦችን የምናስተናግደው ስንቴ ይሆን? እንዲህ ባይሆን ኖሮ፣ እንዲያ ባይሆን ኖሮ፣ የሚሉ ሐሳቦችን በሚገባ እናውቃቸዋለን፡፡

- *አለቃዬ ክፉ ባይሆን ኖሮ፣ ከሥራ መባረር ሳይሆን እንዲያውም የደረጃ ዕድገት አገኝ ነበር፡፡*
- *ባሌ እንደዚያ ባያደርግ ኖሮ፣ እዚህ የገንዘብ ችግር ውስጥ አልወድቅም ነበር፡፡*
- *ከሀብታም ቤተ ሰብ ብወለድ ኖሮ፣ ይኼኔ ታሪኬ የተለየ ይሆን ነበር፡፡*
- *አባትና እናቴ በሕፃንነቴ ባይፋቱ ኖሮ አልታመምም ነበር፡፡*

ለሚመጣው ችግር ሁሉ ሌሎችን መውቀስና በሌሎች ላይ ማማረር በጣም ቀላል ነው፡፡ ይሁን እንጂ፣ ማምለጥ የማንችለው እውነት እንዲህ ያሉ ሐሳቦች፣ የኃላ ኃላ ከባድ ጉዳት የሚያደርሱብንን ነገሮች መቋቋም እንዳንችል የእኛን የራሳችን ዐቅም የሚያዳክሙ መሆናቸው ነው፡፡ ትልቁ አደጋ ያለንበት አዳጋች ሁኔታ ሳይሆን፣ በችግራችን ጊዜ ወደ አእምሮአችን ሰርጎ የሚገባው የተሳሳተ እምነትና አስተሳሰብ ነው፡፡ በእግዚአብሔር ሉዓላዊ ዕቅድ ባለን እምነት መጽናትና፣ ከቃሉ ጋር የሚቃረን ማንኛውንም አፍራሽ አስተሳሰብ በጽናት መቃወም ይኖርብናል፡፡

በመጨረሻም - የትኛውም ሰው፣ የትኛዋም ሴት፣ የትኛውም ክፉ ነገር፣ ከእግዚአብሔር ፈቃድ ሊያወጣን እንደማይችል ማወቅ አለብን!! ፍጻሜያችን በእግዚአብሔር እንጂ በማንም ሰው እጅ ውስጥ አይደለም የሚለው እውነት ልባችን ውስጥ ጠንካራ መሠረት መያዝ አለበት፡፡ የዮሴፍ ወንድሞች እግዚአብሔር የሰጠውን ራእይ ለማጥፋት በጣም ሞክረው ነበር፡፡ እንዲያውም የተሳካላቸው መስሎአቸው ነበር፡፡ እርስ በርሳቸው፣ ‹‹ኑ እንግደለውና ከጉድጓዶቹ በአንዱ ውስጥ እንጣለው... እስቲ ሕልሞቹ (ራእዮቹ) ሲፈጸሙ እናያለን›› ተባብለው ነበር (ዘፍጥረት 37፥20)፡፡ በዓላማ

እርሱን ለማጥፋት ተነሡ፡፡ የዮሴፍ ሕልም መፈጸም የሚችልበት ማንኛውም ዕድል እንዳይኖር ማድረግ ሞከሩ፡፡

ወንድሞቹ ዮሴፍን ለባርነት መሸጣቸው እግዚአብሔር ሳያውቀው በድንገት የሆነ ነገር እንደ ሆነ ታስቡ ይሆን? ነገሩ ጨርሶ የማይታመን ቢመስል እንኳ፣ አንዳንዴ ስለ እግዚአብሔር ያለን አስተሳሰብ ከዚያ የተለየ አይደለም፡፡

## ከባዱ የዮሴፍ ፈተና

ዮሴፍ እንደ አንዳንድ ሰዎች ቢሆን ኖሮ፣ እዚያው የታሰረበት ቦታ ሆኖ ወንድሞቹን የማጥፋት ሤራ ያውጠነጥን ነበር፡፡ ከእግዚአብሔር ቃል የሚቃረኑ ነገሮችን በማሰብ ራሱን ለማጽናናት ይሞክር ነበር (ሮሜ 12፥19 ይመ)፡፡ *አንዴ ከዚህ እስር ቤት ልውጣ እንጂ፣ የእጃቸውን እንዲያገኙ አደርጋለሁ፡፡ አንድ ጥሩ ጠበቃ እይዝና ክስ መሥርቼ እነርሱም በተራቸው እንዲታሰሩ አደርጋለሁ፡፡ ...ግን፣ ለምን ብዬ ገንዘብና ጊዜዬን አባክናለሁ? ሁሉንም አስገድላቸዋለሁ፡፡ ከዚያም እነርሱ እኔ ላይ ለማድረግ እንደ ሞከሩት አሟሟታቸው በአንድ ዓይነት አደጋ የደረሰ እንዲመስል አደርጋለሁ* በማለት ያስብ ነበር፡፡

ግን፣ እንደዚያ ያለ ሐሳብ ይዞ ቢሆን ኖሮ፣ ምናልባት እግዚአብሔር ከእስር ቤት እንዲወጣ እንኳ ላያደርግ ይችል ነበር፡፡ ምክንያቱም እነርሱን ማጥፋት ከዐሥራ ሁለቱ ውስጥ ዐሥሩ የእስራኤል ነገድ አባቶችን ማጥፋት ይሆን ነበር! ያን ማድረግ የንጉሥ ዳዊት፣ ከሁሉም የበለጠ ደግሞ የኢየሱስ ክርስቶስ የዘር ሐረግ የመጣበትን የይሁዳን ነገድ ማጥፋት ይሆን ነበር፡፡ እግዚአብሔር ደግሞ ያ እንዲሆን አይፈቅድም፡፡

ዮሴፍ ከእግዚአብሔር ፈቃድ በላይ ራሳቸውን ከፍ ከፍ የሚያደርጉ ሐሳቦችን፣ ምክንያቶችን፣ ምኞቶችን በጽናት መቃወም ነበረበት፡፡ በእግዚአብሔር ተስፋ ቃል ያለውን እምነት አጥብቆ መያዝ ነበረበት፤ ምክንያቱም እምነትና ታዛዥነቱ የሚፈተንበት ከባድ ፈተና ገና እየመጣ ነበር፡፡

እርሱ እዚያ እያለ ሌሎች ሁለት ሰዎች ታስረው መጡ፡፡ አንደኛው የፈርዖን መጠጥ አሳላፊ ሲሆን፣ ሌላው ደግሞ ወጥ ቤቱ ነበር፡፡ ታዲያ፣ የዮሴፍ ፈተና ምን ይሆን? ከዐሥር በሚበልጡ ዓመታት ውስጥ እርሱ ራሱ አንዴ እንኳ በሕይወቱ የእግዚአብሔርን ታማኝነት ባለየበት ሁኔታ፣ ውስጥ ቢሆንም፣ እግዚአብሔር ታማኝ መሆኑን ለእነዚያ ሁለት ሰዎች ይነግራቸው ይሆን? ልብ አድርጉ፤ ዮሴፍ አለቃና መሪ እንደሚሆን ሕልም አይቶ የነበረ

ቢሆንም፣ የተሰጠው ተስፋ አንዱ ገጽታ እንኳ ገና አልተፈጸመም ነበር፡፡ ዮሴፍ እንደ አንዳንዶቻችን ቢሆን ኖሮ፣ ‹‹እናንተ ሰዎች ሕልም እንዳያችሁ እየነገራችሁኝ ነው፤ ከብዙ ዓመታት በፊት እኔም እንደ እናንተ ሕልም አይቼ ነበር፡፡ ግን መጨረሻዬ እዚህ እስር ቤት ውስጥ መማቀቅ ሆኖ ቀረ፡፡ ስለዚህ ሕልማችሁን ጨርሶ ብትረሱት ነው የሚሻላችሁ›› ይላቸው ነበር፡፡

የእርሱ ምላሽ ያንን የመሰለ ቢሆን ኖሮ፣ ‹‹እግዚአብሔር ታማኝ አይደለም፡፡ የሰጠውን የተስፋ ቃል መፈጸም አይችልም›› በማለት እያማረረ እዚያው እስር ቤት ውስጥ ይሞት ነበር፡፡ ወደ ታቀደለት ፍጻሜ ከሚያደርሰው መንገድ ይወጣ ነበር፤ ምክንያቱም የፈርዖንን ሕልም ለመፍታት ዮሴፍ ከእስር ቤት የወጣው ሕልም የመተርጐም ችሎታ እንዳለው መጠጥ አሳላፊው ከሁለት ዓመት በኃላ ለፈርዖን ስለ ነገረው ነበር፡፡ ያቺ ትንሽ የምትመስል አጋጣሚ፣ ዮሴፍ ከእስር ቤት ወጥቶ ከፈርዖን ቀጥሎ በመላው ግብፅ ሁለተኛው ሰው እንዲሆን አስቻለች፤ ከዘጠኝ ዓመት በኃላም ከረጅም ዓመታት በፊት ባየው ሕልም መሠረት ወንድሞቹ ወድቀው ሲሰግዱለት ለማየት አበቃች፡፡

ዮሴፍ እግዚአብሔር የሰጠው ተስፋ ሲፈጸም ለማየት ሃያ አንድ ዓመት ሙሉ ጠበቀ፡፡ ሆኖም፣ እግዚአብሔር ቃሉን ለመጠበቅ ታማኝ በመሆኑ በትክክል ተፈጽሞአል፡፡ በሦስት ዓመት ውስጥ ወይም በሦስት ወር ወይም በሦስት ሳምንት የጸሎታችንን መልስ ካላገኘን ተስፋ የምንቆርጥ ስንቶቻችን እንሆን? የእግዚአብሔር አሠራርና ጊዜ ከእኛ ጋር ሳይጣጣም ከቀረ መጥፎ ርምጃ እንወስዳለን፡፡ ሆኖም፣ ሕልማችንን የምናጨናግፍ እኛ ራሳችን እንጂ፣ እግዚአብሔር አይደለም! መጽናት አለብን፤ በእምነትና በመታዘዝ መዝለቅ አለብን፤ ለዚያ የሚያስፈልገን ኃይል የእግዚአብሔር ጸጋ ውስጥ አለ፡፡ የእግዚአብሔር ጸጋ ማንኛውም ሰው የሚቀበለው ነጻ ስጦታ ሲሆን፣ እኛ ማድረግ ያለብን በቃሉ መታመንና በእግዚአብሔር ባለን እምነት መጽናት ብቻ ነው፡፡ ተስፋ ካልቆረጥን በጊዜው እናጭዳለን፡፡

ቀደም ሲል እንዳልኩት የትኛውም ሰው ወይም የትኛውም ጋኔን እግዚአብሔር ለሕይወታችሁ ያለውን ዓላማ ማደናቀፍ አይችልም፤ በዚህ እውነት ላይ ከተመሠረታችሁ በእርሱ መንግሥት ውስጥ ማንም የማያስቆመው ኃይል ትሆናላችሁ፡፡ ይሁን እንጂ፣ ይህን በተመለከተ አንድ ማወቅ ያለባችሁ እውነት፣ ያንን ማደናቀፍ የሚችል ሰው ቢኖር–ያ ሰው እናንተ ራሳችሁ መሆናችሁን ነው!

የእስራኤልን ሕዝብ አስቡ፡፡ ከግብፅ ባርነት አውጥቶ ወደ ተስፋው ምድር እንዲያገባቸው እግዚአብሔር ሙሴን ላከው፡፡ የእርሱ ፈቃድ ከግብፅ

ከወጡ አንድ ዓመት በኃላ ምድረ ከነዓን እንዲገቡ ነበር፡፡ ሆኖም፣ ባለ ማመናቸው፣ በተሳሳተ አስተሳሰባቸው፣ በማጉረምረማቸውና በትንሽ በትልቁ ሙሴን በመውቀሳቸው፣ በታቀደው ጊዜ ወደ ቦታቸው አልገቡም፡፡ ይልቁንም፣ ከካሌብና ከኢያሱ በቀር ያ ትውልድ በሙሉ በምድረ በዳ አለቀ፡፡ በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ፣ እግዚአብሔር ታማኝ አለመሆኑን ተናግረዋል፤ እንደ እውነቱ ከሆነ ግን፣ ለእግዚአብሔር ታማኝ ያልሆኑት እነርሱ ነበሩ፡፡ በእምነትና በመታዘዝ ባለ መጽናታቸው የታሰበላቸውን አበላሹ፡፡

## የመሪ ባሕርይ

መጀመሪያ ላይ ዮሴፍ አሳባቂ፣ ጉረኛና ትዕቢተኛ ቢሆንም በዚያ አልዘለቀም፡፡ በመከራ ውስጥ መታዘዝን ተማረ፤ የተዋጣለት መሪ ሆኖ ለመገኘት የሚያስፈልገውንም ባሕርይ አዳበረ፡፡ በግብፅ አገር ሁለተኛው ታላቅና ኃያል ሰው ሆነ፡፡ ወንድሞቹ ላይ ምሬት፣ ቂም፣ ይቅር አለማለትና ጥላቻ ይዞ ቢሆን ኖሮ፣ በቀላሉ ይበቀላቸው ነበር፡፡ አገራቸው ራብ በመግባቱ ምግብ ፍለጋ ወንድሞቹ ወደ ግብፅ መጥተው ነበር፡፡ ዕድሜ ልክ እንዲታሰሩ ማድረግ፣ ማሰቃየት ወይም መግደል ይችል ነበር፡፡ ይሁን እንጂ፣ ዮሴፍ ያደረገው ተቃራኒውን ነበር፡፡ ምንም ሳያስከፍል እህልና እነርሱና ቤተ ሰቦቻቸው እንዲኖሩበት በግብፅ አገር ጥሩ የሚባለውን መሬት ሰጣቸው፡፡ ምድሪቱ የምትሰጠውን መልካም ነገር ተመገቡ፡፡ ለማይገባቸው ወንድሞቹ በግብፅ ያለውን መልካም ነገር ሁሉ ሰጣቸው፡፡ በዮሴፍ ልብ ውስጥ የክርስቶስን የመሰለ ባሕርይ ተገኝቶ ነበር፤ ምክንያቱም የረገሙትን ወንድሞቹን ባርኮአቸዋል፤ ለጠሉት መልካም አድርጎላቸዋል (ማቴዎስ 5፥44-45 ይመ)፡፡

እስቲ አሁን ደግሞ ጴጥሮስ የሚለውን እናንብብ -

> በዓለም ዙሪያ ያሉት ወንድሞቻችሁ ተመሳሳይ መከራ እንደሚቀበሉ ዐውቃችሁ በእምነት ጸንታችሁ ተቃወሙት፡፡ በክርስቶስ ወደ ዘላለም ክብሩ የጠራችሁ የጸጋ ሁሉ አምላክ ለጥቂት ጊዜ መከራ ከተቀበላችሁ በኃላ እርሱ ራሱ መልሶ ያበረታችኃል፤ አጽንቶም ያቆማችኃል፡፡ (1ጴጥሮስ 5፥9-10)

የጸጋ ሁሉ አምላክ... ይመልሳችኃል፣ ያበረታችኃል፣ ያጸናችኃል፣ ያቆማችኃል፡፡ እነዚህ ለእኔም ሆነ ለእናንተ የሚሆን ተስፋ የያዙ አራት ብርቱ ቃሎች ናቸው፡፡ ለእንዳንዱ ቃል ጀምስ ስትሮንግ የሰጠውን ትርጉም ቀጥሎ አቀርባለሁ፡፡

1. መመለስ - ‹‹መመለስ፣ ጠግኖ ማደስ፣ ማስተካከል፣ ማበጀት፡፡››
2. መጽናት - ‹‹ጽኑ ማድረግ፣ ወደሚፈለገው አቅጣጫ ማቅናት፣ መመቻቸት፣ መተከል፣ የማይነቃነቅ፡፡››
3. መበርታት - ‹‹ማረጋገጥ፣ ወይም በመንፈሳዊ ዕውቀትና ኃይል መጠንከር፡፡››
4. መቆም - ‹‹መሠረት መጣል፣ መገንባት፡፡››

እነዚህ ቃሎች ለመሪነት እያዘጋጀው እያለ፣ እግዚአብሔር በዮሴፍ ውስጥ ያደረጋቸውን ነገሮች ይገልጻሉ፡፡ ተጠገነ፣ ታደሰ፣ ከእንግዲህ አሳባቂ፣ ወይም ጉረኛ ወይም ትዕቢተኛ አይሆንም፡፡ የታቀደለት ቦታ ላይ ለመድረስ ከአእምሮ በላይ በሆነ የእግዚአብሔር ጸጋ ኃያል ሆነ፣ ከፍ አለ፡፡ ወንድሞቹን ከመርገም ይልቅ እንዲባርክ በመንፈሳዊ ሕይወት ጠነከረ፡፡ ተስፋ አስቆራጭ በሚመስል ሁኔታ ውስጥ በጽናት መታዘዙ ጥበብን፣ ድፍረትንና ትክክለኛ ባሕርይን እንዲያዳብር አደረገ፡፡

ባለፈው ምዕራፍ ከጠላት ጋር በምናደርገው ውጊያ የእግዚአብሔርን ቃል የመናገርን ጠቃሚነት ተመልክተን ነበር፡፡ ይሁን እንጂ፣ ዋናው ነገር ቃሉን ማነብነብ ሳይሆን፣ ለእግዚአብሔር ቃል በመታዘዝ መጽናት ነው፡፡ የእርሱን እውነት ማሰብ፣ መናገርና መኖር ነው፡፡ በነቢዩ ኤርምያስ ውስጥ እግዚአብሔር፣ ‹‹በምድር ላይ ለእውነት ጀግና የሆኑ የት አሉ?›› በማለት ይጠይቃል (ኤርምያስ 9፥3)፡፡ በዚህ ትውልድ ውስጥ ዮሴፍን የመሰሉ ሰዎች ይፈልጋል፡፡ በመታዘዝ ከጸናንና በድፍረት የእግዚአብሔርን ቃል ከተናገርን ብዛት ያለው የተፈጸሙ ተስፋዎችን፣ በሳል ባሕርይን፣ የበለጠ ሥልጣንን መከር እናጭዳለን፤ የጠላትን ምሽጎች እናፈርሳለን፡፡ በዙሪያችን ያሉ ሰዎችም ከእምነት ጽናታችንና ታዛዥነታችን ተጠቃሚ ይሆናሉ፡፡

እግዚአብሔር የጠራችሁ ለእንዴት ያለ ታላቅ ሕይወት ነው! በእናታችሁ ማሕፀን ከመሠራታችሁ በፊት እንኳ ለእናንተ ዕቅድ አዘጋጅቷል፡፡ እንደ ዮሴፍ ሁሉ ለታላቅነት እየጠራችሁ ነው፡፡ ጴጥሮስ በሚከተለው ሁኔታ ነው ምክሩን የሚደመድመው፣

> ይህን አጭር መልእክት… የጻፍሁላችሁ ልመክራችሁና ይህ እውነተኛ የእግዚአብሔር ጸጋ መሆኑን ልመሰክርላችሁ ብዬ ነው፡፡ (1ጴጥሮስ 5፥12)፡፡

በጽናት ለመታዘዝ የሚያስችል ኃይል የሚገኘው ከእግዚአብሔር ጸጋ ነው፡፡ ከእንግዲህ ይህን ድንቅ የእግዚአብሔር ጸጋ፣ ኃጢአትን ወደ

መሸፈንና የመንግሥተ ሰማይ መግቢያ ቲኬት ብቻ ወደ መሆን ደረጃ ዝቅ እንደማናደርገው አምናለሁ፡፡ ከዚያ እጅግ የበለጠ ነው! በእርሱ ጸጋ አማካይነት ለጌታችን ለኢየሱስ ክርስቶስ ፍጹም ክብር ራሳችንን እንለያለን፡፡

# 15

# ጽናት ያለው ጸሎት

*እውነት እላችኋለሁ፤ አብ በስሜ የምትለምኑትን ሁሉ ይሰጣችኋል፡፡*

*ዮሐንስ 16፥23*

ጽናትን አስመልክቶ የምናደርገው ውይይት በግል ከራሱ ከእግዚአብሔር ጋር የሚኖረን ግንኙነት ካልተጨመረበት የተሟላ አይሆንም፡፡ ለመሆኑ፣ ወደ እግዚአብሔር መቅረብና ከእርሱ መለመን ያለብን እንዴት ነው? ወደ እርሱ መቅረብ ያለብን በፍርሃትና በመሽቆጥቆጥ ይሆን? ምናልባት ጸሎታችን መልስ ሳያገኝ ቢቀር ተስፋ እንዳንቆርጥ ከእርሱ መለመን ያለብን ‹‹ትልልቅ ነገሮች››ን ብቻ መሆን እንዳለበት ታስባላችሁ? የጸሎታችን ትንሹ ክፍል፣ መካከለኛው ወይም አብዛኛው እጅ መልስ እንደሚያገኝ ነው መጠበቅ ያለብን?

እነዚህ ጥያቄዎች ግራ ሊያጋቡዋችሁ እንደሚችሉ አውቃለሁ፤ ይሁን እንጂ፣ ከሃያ ዓመታት በላይ ካደረግሁት የአገልግሎት ጉዞና ከብዙ መሪዎችና አማኞች ጋር ካደረግሁት ጸሎት በኋላ፣ እነዚህ ጥያቄዎች በእርግጥ የተጋነኑ አለመሆናቸው ነው የተረዳሁት፡፡ ውስጣቸው የእርግጠኝነት ጥንካሬ ወይም የጋለ ፍላጐት፣ የሌለባቸው እጅግ በጣም ብዙ ጸሎቶችን ሰምቻለሁ፡፡ ሰዎች ከመጸለይ ይልቅ ወዲያ ወዲህ የሚያዩበት፣ መጽሐፍ ቅዱስ የሚያነቡበት፣ ወይም የአምልኮ መዝሙር የሚሰሙበት፣ አያሌ የጸሎት ሰብሰባዎች ተካፍዬ አውቃለሁ፡፡ እነዚህ ክርስቲያኖች እዚያ በመገኘታቸው ብቻ እግዚአብሔር መልስ እንደሚሰጣቸው ያስቡ ይሆን ወይ? ወይም ደግሞ አጥብቆ መጸለይንና ለማንኛውም ነገር በእግዚአብሔር መተማመንን ከረጅም ጊዜ በፊት እርግፍ አድርገው የተዉ ሰዎች ይሆኑ ወይ? በማለት ብዙ ጊዜ ራሴን ጠይቄአለሁ፡፡

ብዙ ጊዜ መሪዎች ጥልቀት የሌለውና የተድበሰበሰ ጸሎት ሲጸልዩ ስሰማ ልቤ በጣም ያዝናል፡፡ የጸሎት ጥያቄዎቻቸውን ለእግዚአብሔር በሚያቀርቡበት ሁኔታ ለአንድ የመንግሥት ባለ ሥልጣን አቅርበው ቢሆን ኖሮ፣ ‹‹ለመሆኑ፣ ምን እያላችሁ ነው? ጊዜያችሁን ኮ እያባከናችሁ ነው!››

ይላቸው ነበር በማለት አስቤም አውቃለሁ፡፡ እነዚህ ክርስቲያን መሪዎች የሰዎችን ተስፋ በጣም እንዳያነሳሱና በኃላም ተስፋ እንዳይቆርጡ በማሰብ ሆን ብለው መንፈሳዊ ቃሎችን በጥንቃቄ የሚመርጡ ይመስላል፡፡ ለብዙ የዘመናችን ክርስቲያኖች፣ መንፈሳዊው ዓለም እውነታ የሌለው መሆኑን የሚያሳይ በመሆኑ በጣም አሳዛኝ ነው፡፡

## ደፋርና የጋለ ፍላጐት ያለው መሆን

‹‹ወደ ጸጋው ዙፋን በእምነት (በድፍረት)›› እንድንመጣ የአጽናፈ ዓለሙ ፈጣሪ እግዚአብሔር ጥሪ አቅርቦልናል (ዕብራውያን 4፥16)፡፡ በድፍረት ማለት በልበ ሙሉነት፣ ባለ ማወላወል፣ ባለማመንታትና በጽናት ማለት ነው፡፡ የድፍረት ተቃራኒ ደግሞ ፈሪነት፣ ማመንታትና ቅልስልስነት ነው፡፡ የሚያስፈልጋችሁን ከእርሱ መቀበል እንድትችሉ በልበ ሙሉነት፣ ባለ ማወላወልና ባለማመንታት ወደ እርሱ እንድትመጡ እግዚአብሔር የጠራችሁና የነገራችሁ መሆኑን እስቲ ረጋ ብላችሁ አስቡ፡፡ የእርሱ ፍላጐት ይኸው ነው!

ሐዋርያው ያዕቆብ፣ ‹‹የጻድቅ ሰው ጸሎት ኃይል አለው›› በማለት ይነግረናል፡፡ (ያዕቆብ 5፥16)፡፡ (ሁሉም ሊባል በሚችል መልኩ የእንግሊዝኛ መጽሐፍ ቅዱሶች ትርጉሞች - ‹‹ጸሎት›› ብቻ ሳይሆን፣ ‹‹የጋለ ጸሎት›› ነው የሚሉት)፡፡ የጋለ ማለት ከፍተኛ ፍላጐት፣ ስሜት ወይም ተነሳሽነት ማሳየት ማለት ነው፡፡ የጋለና ልባዊ የሆነ ጸሎት ውጤት የሚያስገኝ መሆኑን ነው ያዕቆብ የሚናገረው፡፡ በሌላ በኩል በማመንታና በማወላወል የሚቀርብ ጸሎት ውጤት የለውም ማለት ነው፡፡

መቼም፣ የጋለ የሚለውን ቃል ስትሰሙ፣ ጽናት ያለው የሚለውም ቃል ትዝ ሊላችሁ እንደሚችል አስባለሁ፡፡ እንደዚያ መሆንም አለበት፡፡ ያዕቆብ የታላቁ ነቢይ የኤልያስን ምሳሌ በማቅረብ ላነሣው ሐሳብ አጽንዖት ይሰጣል፡፡

> ኤልያስ እንደ እኛ ሰው ነበረ፤ ዝናብ እንዳይዘንብ አጥብቆ ጸለየ፤ በምድርም ላይ ሦስት ዓመት ተኩል ዝናብ አልዘነበም፡፡ እንደ ገናም ጸለየ፤ ዝናብም ከሰማይ ዘነበ፤ ምድርም ፍሬዋን ሰጠች፡፡ (ያዕቆብ 5፥17-18)

የሚያስፈልጉን ነገሮችንና ሌሎች ጥያቄዎቻችንን ይዘን ወደ እርሱ ስንቀርብ በልባዊ ስሜትና ጽናት እንዲሆን እግዚአብሔር እንደሚፈልግ ግልጽ ነው፡፡

ኤልያስ አጥብቆ - በጽናት ጸለየ፤ ተአምራዊ ውጤትም አገኘ፡፡ አጥብቆ የሚለው ቃል የጋለ የሚለው ተመሳሳይ ነው፡፡ ‹‹ሙሉ ትኩረትን፣ ዓላማን ወይም ጥረትን እዚያ ላይ ማድረግ፤ በሙሉ ልብ መነሣሣት›› የሚል ገለጻም ተሰጥቶታል፡፡ ውጤት ባለው ሁኔታ ስለ መጸለይ ስታስቡ የእግዚአብሔርን ቃል አጥብቃችሁ መያዝ ያለባችሁ መሆኑንስ ትረዳላችሁ? የሚያስፈልጉን ነገሮችንና ሌሎች ጥያቄዎቻችንን ይዘን ወደ እርሱ ስንቀርብ በልባዊ ስሜትና ጽናት እንዲሆን እግዚአብሔር እንደሚፈልግ ግልጽ ነው፡፡

ዝናብ እንዳይዘንብ ከጸለየ የተወሰነ ጊዜ በኋላ፣ ኤልያስ ዝናብ ተመልሶ እንዲመጣ ጸለየ፡፡ መጽሐፍ ቅዱስ ስለዚያ ሁኔታ ሲናገር፣ ‹‹ኤልያስ ወደ ቀርሜሎስ ተራራ ጫፍ ወጣ፤ ፊቱንም በጉልበቶቹ መካከል አድርጎ ወደ መሬት አቀረቀረ›› ይላል (1ነገሥት 18፥42)፡፡

አንድ ሌላ የመጽሐፍ ቅዱስ ትርጉም ደግሞ፣ ‹‹መሬት ላይ ወድቆ ጸለየ›› ይላል፡፡ በጋለ ስሜት ወደ እግዚአብሔር ሲጸልይ ይታየኛል፡፡ ተንበርክኮ ወይም ተቀምጦ ራሱን በጉልበቱ መካከል እያሳረፈና እያነሣ፣ ‹‹የአብርሃም፣ የይስሐቅና የያዕቆብ አምላክ ሆይ፣ ዝናብ እንዲመጣ የአንተ ፍላጎት መሆኑን ነግረኸኝ ነበር፡፡ ይህች ምድር ፍሬ ማፍራት እንድትችል ደመናና ዝናብ እንዲመጣ እለምንሃለሁ! ሕዝብህ እንደ ገና በመልካምነትህ ደስ ይሰኙ ዘንድ ዝናብ ከመምጣት እንዳይዘገይ እጠይቅሃለሁ!›› በማለት ጮኾ ይጸልይ ነበር፡፡ ጸሎቱ ድፍረት፣ ጽናትና ልባዊ ግለት ያለበት ነበር፡፡ ከዚያ በኃላ ኤልያስ፣ ‹‹ውጣና ወደ ባሕሩ ተመልከት›› በማለት አገልጋዩን አዘዘው (1ነገሥት 18፥43)፡፡

እስራኤል መደበኛውን ዝናብ ያገኙ በነበረበት በቀደሙት ዓመታት ዝናቡ ከሜዲትራንያን ባሕር ተነሥቶ ወደ ምዕራብ ይመጣ ነበር፡፡ አሁንም ኤልያስ አገልጋዩን ያዘዘው በዚያው አቅጣጫ ደመና መኖሩን እንዲያይ ነበር፡፡ የሚያምንበትን በተመለከተ ርምጃ ወሰደ፡፡ እኛም በእውነት የምናምን ከሆነ፣ የምናደርገው ይህንኑ ነው፡፡ የኤልያስ አገልጋይ ተመልሶ መጣና፣ ‹‹ምንም የለም›› አለው፡፡

ብዙዎቻችን እዚያ ላይ እናቆም ነበር፡፡ ‹‹ምናልባት የሰማሁት ትክክል ላይሆን ይችላል፡፡ ምናልባትም፣ በኃጢአታቸው ምክንያት እግዚአብሔር እስራኤልን መቅጣቱን አላበቃ ይሆናል፡፡ አክዓብ ሥልጣን ላይ እስካለ ድረስ መቼም፣ ቢሆን ዝናብ ሊኖር አይችልም›› እንል ነበር፡፡

በእምነት ጸንተን ከመቆም ይልቅ መጸለያችንን እናቋርጥና ከዚህም የተነሣ ከእግዚአብሔር ፈቃድ ውጪ እንሆን ነበር፡፡ ኤልያስ ግን እንደዚያ ያለ ሰው አልነበረም፡፡

ኤልያስ የእግዚአብሔርን ፈቃድ ያውቅ ነበር፤ የእግዚአብሔር ፈቃድ ደግሞ መፈጸሙ እንደማይቀር ያውቅ ነበር፡፡ ስለዚህ በድጋሚ ወደ እግዚአብሔር ጮኸ፤ በዚህ ጊዜ ጸሎቱን ስለ ሰማለት በድፍረትና በጋለ ሁኔታ፣ በእምነት እግዚአብሔርን በማመስገን ነበር የጸለየው፡፡ ወጥቶ እንዲያይ ለሁለተኛ ጊዜ አገልጋዩን አዘዘ፡፡

ጸሎትና እምነት በተግባር ካልተገለጠ በቀር፣ ከተራ ሃይማኖተኝነትና ጊዜ ከማባከን ውጪ ሌላ ምንም ማለት አይደለም፡፡ በጋለ ሁኔታ መጸለይ ማለት ልባችሁ፣ አእምሮአችሁ፣ ነፍሳችሁና አካላችሁ ለመቀበል ወስኖአል፣ በዚያም መሠረት ርምጃ ይወስዳል ማለት ነው፡፡ የምትንቀሳቀሱት እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ እንደ ሆነ ልበ ሙሉ ከመሆናችሁ የተነሣ ማንኛውም እንቅፋት የጸሎታችሁን መልስ ከመቀበል አያግዳችሁም፡፡ አካባቢዎቹና ሁኔታዎቹ ሊለወጡ እንደሚችሉና መለወጥም እንዳለባቸው በእርግጠኝነት ታውቃላችሁ፡፡

የኤልያስ አገልጋይ ተመልሶ መጣና፣ ‹‹ምንም የለም›› በማለት ነገረው፡፡ መጀመሪያው ላይ መጸለያችንን ባናቋርጥ እንኳ ሁለተኛውን ሪፖርት ስንሰማ፣ ብዙዎቻችን ተስፋ ቆርጠን መጸለያችንን እናቋርጥ ይሆናል፡፡ በዚህ ጊዜ፣ እግዚአብሔር ለዚህ ጸሎት ለምን መልስ እንደማይሰጥ አሳማኝ የመሰለንን ነገረ መለኮታዊ (ቴዎሎጂካል) ምክንያት ልንፈልግለት እንሞክራለን፡፡ ኤልያስ ግን እንደዚያ አልነበረም! እንደ ገና ወደ ሰማይ ዞሩን ፊት በጸሎት ቀረበ፤ ለሦስተኛ ጊዜ አገልጋዩን ወደ ተራራው ላከው፡፡ በዚያ ጊዜም ያገኘው መልስ ከበፊቱ የተለየ አልነበረም፡፡ ለአራተኛ፣ ለአምስተኛ፣ ለስድስተኛና ለሰባተኛ ጊዜ አገልጋዩን ላከ! (አገልጋዩ ምን ያህል የተባረከ አገልጋይ ነበር፤ በአንድ ቀን ውስጥ ሰባት ጊዜ ወደ ቀርሜሎስ ተራራ ጫፍ እንዲወጣ ሲነገረው የታዘዘውን አደረገ፡፡ የጋለ ፍላጎት የነበረው ኤልያስ ብቻ ሳይሆን፣ አገልጋዩም ጭምር ነበር!)፡፡ አገልጋዩ ለሰባተኛ ጊዜ ሄዶ ከተመለሰ በኃላ፣ ‹‹የሰው እጅ የምታህል ትንሽ ደመና ከባሕሩ እየወጣች ነው!›› የሚል ሪፖርት አቀረበ፡፡

መቼም፣ የሰው እጅ የምታህል ትንሽ ደመና ኤልያስ ላቀረበው ጸሎት መልስ የሚሆን ዝናብ አታስገኝም፡፡ ሆኖም፣ ልመናውን አቁሞ ወደ ተግባር ለመግባት ለኤልያስ ያ በቂው ነበር፡፡ ጸሎቱ እንደ ተሰማ አውቋል፡፡

ኤልያስም - ‹‹ሂድና አክዓብን ‘ዝናቡ ሳያግድህ ሠረገላህን ጭነህ ውረድ ብለህ ንገረው›› አለው፡፡ ወዲያውኑም ሰማዩ በጥቁር ደመና ተሸፈነ፤ ነፋሱ ነፈሰ፤ ከባድ ዝናብ ጣለ፡፡ (1ነገሥት 18፥44-45)፡፡

እርሱ ሰባት ጊዜ ጸለየ፤ ሰባት ጊዜ አገልጋዩን ላከ፡፡ ኤልያስ ባቀረበው ጥያቄ አላወላወለም፣ እምነቱ ጽኑ ነበር፤ መልሱን ለመቀበል ቁርጥ ያለ ውሳኔ አድርጎ ነበር፡፡ የጋለና ውጤት ስላለው ጸሎት ያዕቆብ ሲናገር፣ ስለ እንዲህ ያለው ጸሎት መናገሩ ነበር፡፡ በእምነት፣ በንግግር፣ በጽናትና በተግባር የጋለ ተነሳሽነት ነበረው፡፡

## ትንሽ ደመና እየወጣች ነው

እየወጣች ያላችው የኤልያስ ትንሽ ደመና፣ በጽኑ እምነት ከጸለይን የሚኖረንን ነገር የሚያመለክት ማረጋገጫ ነው፡፡ መንፈስ ቅዱስ ከልባችን ጋር ሆኖ ይመሰክርልናል፡፡ (ሮሜ 8፥16 ይመ)፡፡ ይህ ትንሽ ደመና ነው ሊባል ይችላል፡፡ አንዳንዴ ቃል ሊሆን ይችላል፤ አንዳንዴ ወደ ልባችን የሚለቀቅ ደስታ ሊሆን ይችላል፤ አንዳንዴ ደግሞ ከእግዚአብሔር የጠየቅነው ነገር መልስ ማግኘቱን የሚመሰክርልን ወደ ልባችን የሚመጣ ግንዛቤ ሊሆን ይችላል፡፡ ትንሿ ደመናችን ስትወጣ ካየን፣ ኤልያስ እንዳደረገው ሁሉ በዚያ መሠረት መንቀሳቀስ እንችላለን፡፡

ሚስቴ ሊዛ፣ አራተኛው ልጃችንን ለመውለድ በተቃረበችበት ጊዜ የሆነውን አስታውሳለሁ፡፡ ከምትወልድበት ቀን አምስት ቀን አልፎአት ነበር፤ ሆኖም ከዚያ በፊትም ቢሆን ከትክክለኛው ቀን አልፋ ነበር የምትወልደው፡፡ በዚህ ጊዜ ግን ሊዛ፣ አንድ ትክክል ያልሆነ ነገር እንዳለ ይገባት ነበር፡፡ ልጁ ማሕፀንዋ ውስጥ መንፈራገጥ ጀምሮ ነበር፡፡ ስለሚያሳስባት ነገር ሪፖርት ለማድረግ ወደ ዶክተሩ ደውላ ነበር፤ እርሱም፣ ‹‹ነገ ጠዋት ወደ ሆስፒታል ነይና ምጥ እንዲመጣ እናደርጋለን›› ብሏት ነበር፡፡

በሚቀጥለው ጠዋት ግን ዶክተሩ ያለ ምንም መዘግየት ቶሎ መውለድ እንዳለባት ነገራት፡፡ ማሕፀኗ እንዲፍታታ በእግራችን ጥቂት ወዲያ ወዲህ እንድንል መከረን፡፡ እኔና ሊዛ የጠዋት ጊዜውን ሁሉ በእግራችን ወዲያ ወዲህ ብንልም ምንም ውጤት አልተገኘም ነበር፡፡ እኩለ ቀን ላይ ሊዛን ስለ ደከማት ዕረፍት እንድታደርግ ወደ ሆስፒታሉ ተመለሰን፡፡ ‹‹ጆን፣ እባክህን ወጣ በልና ጸልይልኝ፡፡ ቶሎ ምጥ ካልጀመረኝ ልጁን ለማውጣት ሌላ ጠንከር ያለ ርምጃ ይወስዳሉ፤ እኔ ደግሞ እንደዚያ እንዲሆን አልፈልግም›› አለችኝ፡፡

ከሚወሰዱት ርምጃ አንዱ፣ ፒትኮሲን እን ኢፒዱራል የሚባል ክኒን መስጠት ነበር፡፡ የመጀመሪያው ልጃችንን በወለደች ጊዜ እንደዚያ አድርጋ ስለ ነበር የጀርባ ሕመም ያስከተለ ችግር ተፈጥሮ ነበር፡፡ ሌላው ችግር ደግሞ በጣም ውድ መሆኑ ነበር፡፡ አገልግሎታችን ገና ትንሽ ደረጃ ላይ ስለ ነበር የሕክምና ኢንሹራንስ አልነበረንም ነበር፡፡ ከመደበኛ ወጪያችን በላይ ምንም ገንዘብ የሌለን፣ በጣም ዝቅተኛ ገቢ ያለው ቤተ ሰብ ነበርን፡፡

ቀትር ላይ ከሆስፒታል ወጥቼ ድምፄን ወደ ሰማይ ከፍ የማደርግበት በአካባቢው ያለ አንድ ፀጥተኛ ቦታ አገኘሁ፡፡ በጋለ ሁኔታ ጸለይኩ፡፡ ከዐርባ አምስት ደቂቃ በኃላ ወደ ሊዛ ክፍል ተመለስኩ፤ ግን ምንም ለውጥ አልነበረም፡፡ አንድ ሰዓት ከእርሷ ጋር ካሳለፍኩ በኋላ ለሁለተኛ ጊዜ ለመጸለይ ወደ ውጪ ወጣሁ፡፡ በዚህ ጊዜ ወደ እግዚአብሔር የማቀርበው ልመና በጣም ጠንከር ብሎ ነበር፡፡ ቀትር አጋማሽ ላይ እንደ ገና ተመለስኩ፤ ሆኖም ምንም ለውጥ እንደሌለ ነበር ያየሁት፡፡

ሌላ አንድ ሰዓት አብረን አሳለፍን፡፡ ከተለያዩ ምክንያቶች የተነሣ የሊዛ ስጋት በጣም ከፍ ብሎ ነበር፤ ዋናው ስጋቷ የልጃችን በደኅና መወለድ ነበር፡፡ ‹‹ጆን፣ እባክህን ወጣ በልና መጸለይህን ቀጥል፡፡ በጣም ስጋት እየተሰማኝ ነው›› አለችኝ፡፡

ለሦስተኛ ጊዜ ወደዚያ ገለልተኛ የጸሎት ቦታ ሄድኩ፡፡ በዚህ ጊዜ ከበፊቱ የበለጠ ግለትና ጽኑ መሻት ነበረኝ፡፡ ጸሎቴም ጽኑና ጮኽ ያለ ነበር፤ መልስ ለመቀበል ቁርጥ ያለ ውሳኔ አድርጌ ነበር፡፡ ሊዛ ፊት ላይ ያንገበበውን ፍርሃት አይቼ ስለ ነበር እንድትጽናና እፈልጋለሁ፡፡ በቋንቋዬ እየጸለይኩ ኪዳናዊ ተስፋውን ለእግዚአብሔር አቀረብኩ፡፡ ከዚያ በኃላ ደግሞ አጥብቄ በመንፈስ ጸለይኩ፡፡

ከተወሰኑ ደቂቃዎች በኃላ፣ *ልጅህ ዛሬ ይወለዳል፤ እናቱና ልጁም ነገ በዚህ ሰዓት በሰላም እቤታቸው ይሆናሉ* የሚል ቃል ልቤ ውስጥ በግልጽ ሰማሁ፡፡ ቃል በመስጠት፣ ጸሎቴ መሰማቱን መንፈስ ቅዱስ ከልቤ ጋር አብሮ መሰከረ፡፡ ‹‹የሰው እጅ የምታህል ትንሽ ደመና›› ሰጠኝ፡፡ አሁን ርምጃ ለመውሰድ ዝግጁ ነኝ፡፡

11 ሰዓት አካባቢ ወደ ሊዛ ክፍል ተመልሼ፣ ‹‹አርደን ዛሬ ይወለዳል፤ አንቺና እርሱ ነገ በጥሩ ጤንነት እቤታችሁ ትሆናላችሁ›› በማለት ነገርኳት፡፡ እርሷም ተጽናናች፡፡ ሆኖም፣ ወዲያውኑ ለውጥ ባለ ማየታችን የተነገረን መፈጸም የሚችልበት ሁኔታ ያለ አይመስልም ነበር፡፡ የምጥ ምልክት

አይታይም ነበር፡፡ ታዲያ፣ ልጁ እንዴት ቶሎ መወለድ ይችላል? ግን ትንሿን ደመና አይቻለሁ!

ምሽቱ እያለፈ ነበር፤ ነርሶቹና ዶክተሮቹ ቀጥሎ ማድረግ ስለ ነበረባቸው ነገር እየተወያዩ ነበር፡፡ በዚህ መሐል፣ ‹‹ወደ ውጭ ወጣ ብለህ ብትጸልይስ?›› በማለት ከአንድ ጊዜ የበለጠ ጠይቃኝ ነበር፡፡

‹‹አያስፈልግም፡፡ ከዕኩለ ሌሊት በፊት ልጁ ይወለዳል›› አልኳት፡፡ ሰዓት መጥቶ ሰዓት ባለፈ ቁጥር፣ ልቤ ውስጥ በግልጽ የሰማሁትን ቃል ችላ የማለት ወይም አጥብቆ ያለ መያዝ ሐሳብ መጥቶብኝ ነበር፡፡ ይሁን እንጂ፣ እግዚአብሔር እንደ ሰማኝ እርግጠኛ ነበርኩ፤ ስለዚህም ጸንቼ ቆምኩ፡፡

በመጨረሻም፣ ከሌሊቱ 5 ሰዓት ጥቂት አልፍ ሲል ሊዛን ምጥ ጀመራት፡፡ አርደን 5፡51 ላይ ተወለደ፡፡ ከማሕፀን ሲወጣ፣ እትብቱ አንገቱ ላይ በጣም ተጠምጥሞበት ነበር፡፡ የፊቱ መልክ ከሌላው የአካሉ መልክ ምን ያህል የተለየ መሆኑን ሳይ የተሰማኝን ሀዘን አስታውሳለሁ፡፡ በመታነቅ ሂደት ላይ ነበር፡፡ ዶክተሩ በፍጥነት እትብቱን ቆረጠው፤ አርደንንም ጥብቅ ክትትል ወደሚደረግለት ቦታ በፍጥነት ወሰዱት፡፡

በሚቀጥለው ቀን ከሰዓት በኋላ 9፡30 ላይ ከሆስፒታል ወጣን፡፡ 10፡30 ላይ ሊዛና ልጇ እቤታቸው ሆኑ፡፡ እግዚአብሔር ለስለስ ባለ ድምፅ የነገረኝ አንድም ሳይቀር በትክክል ተፈጸመ፡፡

ለምኑ፣ (ጠይቁ) መለመናችሁን አታቋርጡ

‹‹ለምኑ ይሰጣችኋል፤ ፈልጉ ታገኛላችሁ፤ በር አንኳኩ ይከፈትላችኋል›› የሚለውን የኢየሱስን ቃል ብዙዎቻችን እናውቃለን፡፡ (ሉቃስ 11፥9)፡፡ ይህ የተወሰደው ከአዲሱ መደበኛ የመጽሐፍ ቅዱስ ትርጉም ሲሆን፣ አምፕሊፋይድ የተሰኘው የመጽሐፍ ቅዱስ ትርጉም ይበልጥ ግልጽ ያደርገዋል፡፡

> ለምኑ፣ መለመናችሁንም ቀጥሉ ይሰጣችኋል፣ ፈልጉ፣ መፈለጋችሁንም ቀጥሉ ታገኛላችሁ፤ አንኳኩ፣ ማንኳኳታችሁንም ቀጥሉ በሩ ይከፈትላችኋል፡፡ ለሚለምንና መለመኑን ለሚቀጥል ይሰጠዋል፤ የሚፈልግና መፈለጉን የሚቀጥል ያገኛል፤ ለሚያንኳኳና ማንኳኳቱን ለሚቀጥል በሩ ይከፈትለታል፡፡
>
> (ሉቃስ 11፥9-10)

በጽናት እንድንለምን፣ እንድንፈልግና እንድናንኳኳ ኢየሱስ እያበረታታን እንደ ሆነ ማየት እንችላለን፡፡ ግን ለምን? እግዚአብሔር የመስማት ችግር ስላለበት ነው? በፍጹም አይደለም! ጉዳዩ በእውነት ማመናችንን ይመለከታል፡፡ ለመቀበል የወሰኑና ለመቀበል ፍላጎት ያላቸው ሰዎች አውቃለሁ፡፡ በሁለቱ መካከል ሰፊ ልዩነት አለ፡፡ አንድ ሰው በእውነት ውሳኔ ካደረገ ጽኑ፣ ትጉና ደፋር ይሆናል፡፡ ባዶ እጅ መመለስን እንደ አንድ አማራጭ አይቀበልም፡፡ በሌላ በኩል አንድ ሰው ያለው ፍላጎት ብቻ ከሆነ፣ በቀላሉ ተስፋ ይቆርጣል፡፡ በእውነት የምናምን ከሆነ ግን መለመናችንን እንቀጥላለን፤ የፈለገውን ጊዜ ቢወስድም፣ በዚያው ልክ መሻታችንም ይቀጥላል፡፡ ይህን በተመለከተ ጌታ ራሱ ያስተማረውን ተመልከቱ፣

> ደቀመዛሙርቱ ሳይታክቱ ሁሉጊዜ መጸለይ እንደሚገባቸው ለማሳየት ኢየሱስ ይህን ምሳሌ ነገራቸው፤ እንዲህም አላቸው፤ በአንዲት ከተማ የሚኖር እግዚአብሔርን የማይፈራና ሰውን የማያከብር አንድ ዳኛ ነበር፡፡ በዚያችው ከተማ የምትኖር አንዲት መበለት ነበረች፤ እርሷ ከባላጋራዬ ጋር ስላለብኝ ጉዳይ ፍረድልኝ እያለች ወደ እርሱ ትመላለስ ነበር፡፡ ዳኛውም ለተወሰነ ጊዜ አልተቀበላትም ነበር፤ በኃላ ግን በልቡ እንዲህ አለ፤ ምንም እግዚአብሔርን ባልፈራ፣ ሰውንም ባላከብር፣ ይህች መበለት ስለምትጨቀጭቀኝ እፈርድላታለሁ፤ አለበለዚያ ዘወትር እየተመላለሰች ታሰለቸኛለች፡፡ ጌታም እንዲህ አለ፤ ዐመፀኛው ዳኛ ያለውን ስሙ፡፡ እግዚአብሔርስ ቀንና ሌሊት ወደ እርሱ ለሚጮኹ ምርጦቹ አይፈርድላቸውምን? ከመጠን በላይስ ችላ ይላቸዋልን? እላችኃለሁ፤ ፈጥኖ ይፈርድላቸዋል፤ ነገር ግን የሰው ልጅ በሚመጣበት ጊዜ በምድር ላይ እምነትን ያገኝ ይሆንን? (ሉቃስ 18፥1-8)

እዚህ ላይ ኢየሱስ ሳይታክቱ ማለትም፣ ሳያቋርጡ በማለት መናገሩን ልብ አድርጉ፡፡ ይህ ጥሩ ሐሳብ ብቻ ሳይሆን በጣም አስፈላጊም ነው፤ ጽናት ለእናንተ የእግዚአብሔር ፈቃድ ነው፡፡ ከሴትየዋ ታሪክ የምንመለከተው ባቀረበችው ጥያቄ ጽኑ መሆንዋንና ዐመፀኛው ዳኛ እንዲሰለች ማድረግዋን ነው፡፡ በቀላል አባባል በውትወታዋ አታከተችው፡፡ ዐመፀኛው ዳኛ እርሷ ዘወር እንድትልለት ለማድረግ ሲል ብቻ፣ የጠየቀችውን አደረገላት፡፡ በጣም የሚገርመኝ እግዚአብሔርን እንዴት መለመን እንዳለብን ለማሳየት ኢየሱስ በዚህ ምሳሌ መጠቀሙ ነው፤ ምክንያቱም፣ ‹‹ይህን ስሙ›› ብሏል፡፡ ከዚያም ሌሊትና ቀን ወደ እግዚአብሔር ስለሚጮኹ ሰዎች ሲናገር፣ ‹‹ታዲያ፣ እርሱ አይፈርድላቸውም?›› በማለት ይጠይቃል፡፡ እግዚአብሔር ዐመፀኛ

አይደለም፤ እርሱ ወዳጃችን ነው፡፡ ስለዚህም ኢየሱስ በነገረን ምሳሌ እንዳለችው ሴት ጽኑ ውሳኔ ካደረግን እግዚአብሔር የምንለምነውን ያደርግልናል፡፡

እዚህ ላይ ጥቂት ገለጻ መስጠት አስፈላጊ ነው፡፡ ይህን ምሳሌ በተሳሳተ መንገድ በመረዳት፣ አንድ ሰው በማነብነብ ወይም በመደጋገም ሌሊትና ቀን መጸለይ እንዳለበት ሊያስብ ይችላል፡፡ ኢየሱስ ግን እንዲህ እንዳናደርግ አስጠንቅቆናል፤ ‹‹ስትጸልዩ ከንቱ ቃላት በመደጋገም ጸሎታቸው የሚሰማላቸው እንደሚመስላቸው አሕዛብ ነገራችሁን አታስረዝሙ›› (ማቴዎስ 6፥7)፡፡ በተናገረው ምሳሌ ኢየሱስ ማሳየት የፈለገው፣ ስንጸልይ መደጋገምና ማነብነብ እንዳለብን አይደለም፡፡ እርሱ አጽንዖት የሰጠው ጽናትና ልበ ሙሉነት ባለው ዝንባሌ ልመናችንን በእግዚአብሔር ፊት ማቅረብ ያለብን መሆኑን ነው፡፡ ልመናችን እንደ ፈቃዱ መሆኑንና ከዚህም የተነሣ የጠየቅነውን እንደማይነሳን ልበ ሙሉዎች ሆነን ወደ እርሱ እንቀርባለን፡፡ ኤልያስ ተስፋ አስቆራጭ ነገርን አሜን ብሎ አልተቀበለም፡፡ በጸለየው መሠረት ለውጥ ለማየት ወስኖአል፡፡ ጸሎቱ እንደ ተሰማለት እስኪያውቅ ድረስ ይኸው ውሳኔው አብሮት ነበር፡፡

## አጥብቆ መፈለግና ማንኳኳት

ኢየሱስ ያስተማረን እንድንለምንና መለመናችንንም እንድንቀጥል ብቻ ሳይሆን፣ መፈለጋችንንና ማንኳኳታችንንም እንድንቀጥል ነበር፡፡ የጋለ ጸሎት በግል ክፍላችን መጸለይ ብቻ ሳይሆን፣ አጥብቆ መፈለግንና ማንኳኳትንም ይጨምራል፡፡ በሌላ አነጋገር በጸሎት የለመንነውን ወይም የጠየቅነውን እንኖረዋለን ማለት ነው፡፡ በጸሎት ውጤት እንዲገኝ ከተፈለገ፣ ይህ በጣም ወሳኝ ጉዳይ ነው፡፡

ይህን የጸሎት ገጽታ በተመለከተ ከልምዴ የማካፍላቸው አያሌ ታሪኮች አሉ፡፡ ቀጥሎ ያሉት ጥቂቶቹ የቅርብ ምሳሌዎች ናቸው፡፡

አንድ ኮንፈረንስ ላይ ንግግር ከማድረጌ በፊት፣ ሐዋይ ውስጥ ባለ ማዊ በሚባል ቦታ እኔና ሊዛ ብቻችንን ሁለት ቀን ተከል የማሳለፍ ዕድል አግኝተን ነበር፡፡ እኔና እርሷ በፀጥታ የምናርፍበት ሁኔታ ስላልነበረንና በዚህም ላይ አባቷ በቅርቡ በመሞታቸው ሐዘን ላይ ስለ ነበረች ይህ በጣም ምቹ ጊዜ ሆኖልን ነበር፡፡ ብቻችንን የምንሆንበት ሁኔታ ለመፍጠር ይህን ጊዜ በጥንቃቄ አስቤበት ነበር፡፡

ጉዞ ለማድረግ አስበን በነበረበት እያንዳንዱ ቀን የአየሩ ሁኔታ ሪፖርት ምንም ለውጥ አልነበረውም፤ ያለ ማቋረጥ ከባድ ዝናብ ይዘንብ

ነበር! ጥሩ ያልሆነ የአየር ሁኔታ ዕቅዳችንን ማጨናገፍ መቻሉ ጥርጥር አልነበረም፤ ስለዚህም ዝናብ እንዳይኖር አጥብቄ ጸለይኩ፤ እኛ በነበርንበት አካባቢ እንዳያልፍ የአየሩን ሂደት አዘዝኩ፤ የጸለይኩትን ተፈጻሚ ያደርጉ ዘንድ ለሰማይ መላእክትም ተናገርኩ፡፡

ሊዛ ግን እየደጋገመች፣ ‹‹መዝነቡ አይቀርም መዝነቡ አይቀርም›› ስትል እኔ ደግሞ፣ ‹‹ጥሩ አየር ሁኔታ ይኖረናል፡፡ ሁሉም መልካም ይሆናል›› በማለት እመልስላት ነበር፡፡ ምሽት ላይ ሐዋይ ስንደርስ የተቀበለን ጨለማና የጨፈገገ የአየር ሁኔታ ነበር፡፡ አሁንም ቢሆን ሪፖርቶቹ ዝናቡ ጨርሶ እንደማያቋርጥ ነበር የሚናገሩት፡፡ እንዲያውም ሆቴሉ ውስጥ ከነበረው ቴሌቪዥን አንድ የአየር ሁኔታ ሪፖርት ሰምቼ ነበር፡፡ በዚህ ሪፖርት መሠረት የሐዋይ ደሴቶችን ብቻ ሳይሆን የፓስፊክ ውቅያኖስን አካባቢ ጭምር የሚሸፍን ግዙፍ ደመና እየመጣ ነበር፡፡

ጠዋት የመስኮቱን መጋረጃ ገለጥ ሳደርግ፣ ድቅድቅ ጨለማና ዶፍ ዝናብ ነበር ያየሁት፡፡ በዚያ ድቅድቅ ጥቁር ደመና ውስጥ ጥቂት ክፍተት እንኳ ማየት አልቻልኩም፡፡ በእርግጥም የአየር ሁኔታ ባለ ሙያዎች እንደ ተናገሩት ነበር የሆነው፡፡ ይሁን እንጂ፣ እኔ ከጸለይኩት የሚቃረን ማንኛውንም ነገር መናገር አልፈለግሁም፡፡ ድምፄን ከፍ አድርጌ፣ ‹‹አባት ሆይ፣ ስለዚህ ውብ ፀሐያማ ቀን ተመስገን፡፡ እኔና ሚስቴ በውስጥ ልብሳችን ፀሐይን እየሞቅን ስናርፍ ማየት እፈልጋለሁ›› እል ነበር፡፡

ሊዛ በዚህ ያልተለመደ ሁኔታዬ ትስቅ ነበር፡፡ የተለያየ ነገር አንሥተን ከእርሷ ጋር ብንጨዋወትም፤ ያደረግሁትን ጸሎት በተመለከተ ግን፣ ለዋዛ ፈዛዛ ቦታ አልሰጠሁም ነበር፡፡ ቅንጣት ታህል ማፈግፈግ አልፈለግሁም፡፡ ቁርስ ወደ መመገቢያው ቦታ ሄድን፡፡ ውጪ በጣም ይዘንብ ስለ ነበር የሬስቶራንቱ ሠራተኞች ጠረጴዛዎቹን ውጪ ካለው መጠለያ ሆቴሉ ውስጥ ለማግባት ተገድደው ነበር፡፡

ቁርሳችን ከመጣ በኃላ ዝናባማውን ጥቁር ደመና መልከት አደረግሁና፣ ‹‹ጌታ ሆይ፣ ስለዚህ ምግብ ተመስገን፤ በኢየሱስ ስም የተቀደሰ ይሁን፡፡ ስለዚህ ደስ የሚል ፀሐያማ ቀን ተመስገን›› በማለት በዓላማ ጸለይኩ፡፡

ሊዛ ፈገግ አለችና በቀልድ መልክ፣ ‹‹ጆን፣ ለምን መልስ ያገኛል ብለህ የምታምነውን ጸሎት አታቀርብም?›› አለች፡፡ ነገሩ ሁለታችንንም አሳቀን፡፡ ሁሌም የሚያስቁ ቀልዶችን ጣል ማድረግ ትችልበታለች፡፡ ‹‹ፍቅሬ፣ የጸለይኩት የምሬን ነው፤ ዛሬ በጣም ጥሩ ቀን ይሆናል›› አልኳት፡፡

ቁርስ መብላት ከማብቃታችን በፊት ዝናቡ ቆመ፤ ጥቁሩ ደመና ሄደ፤ ሰማያዊ ሰማይ ታየ፤ ፀሐይዋም በድምቀት ማብራት ጀመረች፡፡ ማዊ በቆየንበት ጊዜ አንድ ጊዜ እንኳ አልዘነበም፤ እንዲያውም ፀሐይዋን የሚጋርድ ደመና እንኳ አላየንም፡፡

በኋላም ለኮንፈረንሱ ወደ ሌላው የሐዋይ ክፍል ወደ ኦሐ ሄድን፡፡ እኛ በማዊ ፀሐይማ ቀን ባሳለፍንበት ጊዜ፣ እነርሱ ጋ ግን ዶፍ ዝናብ እንደ ነበር የአካባቢው ሰዎች ነገሩን፡፡ እንዲያውም እኛ በደረቁ የኦሐ ወገን ነበርን ማለት ይቻላል፤ ሆኖም ከባዱ ዝናብ አደገኛ ቆሻሻችን ውቅያኖሱ ውስጥ እንዳይጨምር በማሰብ የባሕሩ ዳርቻ ተዘግቶ ነበር፡፡ ማዊ እያለን በጣም ጥሩ የአየር ሁኔታ እንደ ነበር ስንነግራቸው የአካባቢው ሰዎች በጣም ነበር የተገረሙት፡፡

አስደናቂው አምላካችን አጥብቄ ያቀረብኩትን ጸሎት ሰምቶ የአየሩን ሁኔታ እንደ ለወጠው ከልቤ ነው የማምነው፡፡

## መግዛት ለማይችሉ መጻሕፍት

ይህን ታሪክ ያካፈልኳችሁ እግዚአብሔር የሚሰማውና መልስ የሚሰጠው፣ ‹‹ትልልቅ ጥያቄዎችን›› ብቻ ነው የሚለውን አስተሳሰብ ስሕተት ለማሳየት ነበር፡፡ እርሱ በሕይወት ለሚገጥሙን ጥቃቅን ነገሮች እንኳ በእውነት ያስባል፡፡ እርሱ አባታችን ነው! አሁን ደግሞ እጅግ በጣም አስፈላጊ ስለ ሆነ ጉዳይ ማለትም፣ ችግረኞችን መርዳትን በተመለከተ ያቀረብኩት ጸሎት እንዴት መልስ እንዳገኘ እመሰክርላችኋለሁ፡፡

> እርሱ በሕይወት ለሚገጥሙን ጥቃቅን ነገሮች እንኳ በእውነት ያስባል፡፡

መጻሕፍቶቻችን በዓለም ላሉ አብያተ ክርስቲያናት ሁሉ የእግዚአብሔር መልእክቶች እንደ ሆኑ እኔም ሆንኩ ሊዛ ከልባችን ነው የምናምነው፡፡ ብዙ ጊዜ እንደምናገረው የእኔ ስም መጻሕፍቱ ላይ የተጻፈው መልእክቱን ለመቀበል የመጀመሪያው ሰው በመሆኔ ብቻ ነው፡፡ እንግዲህ ከዚህ አንጻር ጠንከር ያለ አደራ አለብን ማለት ነው፡፡ እነዚህን መልእክቶች በዓለም ዙሪያ ማዳረስ የምንችልበት መንገድ እንድናገኝ እኔና ሊዛ አጥብቀን የመጸለይ ኃላፊነት ነበረብን!

ይህን እየጻፍኩ ባለሁበት ጊዜ፣ መጽሐፎቼ ከስድሳ በላይ ቋንቋዎች ተተርጉመዋል፡፡ የረጅም ጊዜ ጸሎታችንም እነዚህን መጻሕፍት በማደግ ላይ ላሉ ወይም ለወንጌል ዝግ ለሆኑ አገሮች በስጦታ መልክ ለፓስተሮችና

ለመሪዎች ማዳረስ እንድንችል ነበር፡፡ እንዲያውም ከምንሸጣቸው መጻሕፍት ይልቅ በነጻ የምናድላቸው እንዲበልጡ ነው የምንፈልገው፡፡

ባለፉት ዐሥር ዓመቶች በቻይና፣ በኢራን፣ በፓኪስታን፣ በሕንድ፣ በፊጂ፣ በታንዛንያ፣ በርዋንዳ፣ በዩጋንዳና በሌሎችም አገሮች 250,000 የሚሆኑ መጻሕፍት አሰራጭተናል፡፡ በብዙ ሚሊዮን የሚቆጠሩ መጻሕፍቶቻችን ተሸጠዋል፤ ስለዚህም ከምንሸጠው ይልቅ በነጻ የምናድለው እንዲበልጥ ያለን ግብ ላይ ለመድረስ ገና ብዙ ይቀረናል፡፡

በ2011 ዓ.ም መጀመሪያ ላይ፣ የአስተዳደር ሰዎቻችን ለወደ ፊቱ ዕቅድ በሚያወጡበት ጊዜ፣ በ2010 ያደልናቸው መጻሕፍት 33,000 ብቻ መሆናቸውን ተረዳሁ፡፡ ብዙ ውይይት ካደረግን በኃላ፣ ‹‹የዚህ ዓመት ግባችን 250,000 መጻሕፍት በውጭ አገር ላሉ መሪዎች መስጠት መሆን አለበት›› በማለት ተናገርኩ፡፡

በድንገት ሁሉም ፀጥ አለ፡፡ ወዲያውኑ አንድ የሥራ ባልደረባችን፣ ‹‹ይህ በጣም የተጋነነ ይመስለኛል፡፡ ካለፈው ዓመት ጭማሪው በጣም ከፍ ያለ ነው፡፡ ተጨማሪ ድጋፍ እንዲያደርጉልኝ ይህን ግዙፍ ዕቅድ ለአጋሮቻችን መናገር አለብን፡፡ ለማንኛውም ጊዜ ያስፈልገናል፡፡ ምናልባት አሁን 100,000 ብናደርገውና በሚቀጥሉት ዓመታት ግን ከፍ እያደረግነው ብንሄድ አይሻልም?›› በማለት ተናገረ፡፡

‹‹የለም፣ እንደዚያ አይሆንም፤ በዓለም ዙሪያ ያሉ አብያተ ክርስቲያናትን መድረስ የምንችልበት ዐቅም እንዲሰጠን እግዚአብሔርን ማመን መቻል አለብን›› አልኩ፡፡ ‹‹ሁለት መቶ ሃምሳ ሺህ ይህን ያህል ትልቅ አይደለም፡፡››

ክርክሩ ተጋጋለ፡፡ እኔ ያስቀመጥኩ ግብ በጣም የተጋነነ እንደ ሆነ ለማሳየት ይህ የሥራ ባልደረባችን ተጨማሪ ምክንያቶች አቀረበ፡፡ ምክንያታዊና ለአእምሮ የማይመች ግብ መሆኑንም ተናገረ፡፡ እርግጥ ነው በእርሱ ስሌትና ምክንያታዊነት አንጻር ካየነው እርሱ ያለው ትክክል ነበር፤ ይሁን እንጂ፣ ያ ወንድም የእግዚአብሔርን ጸጋ ግምት ውስጥ አላስገባም፡፡

እኔ ግን፣ ‹‹እንደምታውቁት እነዚህን መጻሕፍት የማሰራጨት ተልዕኮ ያለው ሌላ አገልግሎት የለም፤ እግዚአብሔር በአደራ የሰጠው ለእኛ ነው፡፡ *የሰይጣን ሽንገላ፣ እንስት አንበሶቹ ይነሣሉ...* የተሰኙትንና ሌሎች መጻሕፍት መስጠት የምንችል እኛ ነን፡፡ ለዚህ ደግሞ እግዚአብሔርን የማመን ኃላፊነት አለብን፡፡ አድማሳችንን ሰፋ እናድርገው›› በማለት ይበልጥ በዐቋሜ ጸናሁ፡፡

ተቃውሞው ቀጠለ፡፡ በዚህ ጊዜ ድምፄን ከፍ አድርጌና የበለጠ ጠንከር ብዬ፣ ‹‹በፍርድ ቀን በኢየሱስ ፊት ስንቆም በጣም ትንሽ የሆነ ነገር ከእርሱ የጠየቅነው ለምን እንደ ሆነ ገለጻ እንድንሰጥ አልፈልግም፡፡ በፍርድ ቀን ፓስተሮችና ክርስቲያን መሪዎች ለመሆኑ፣ እግዚአብሔር በአደራ የሰጣችሁን መጻሕፍት ሳትሰጡን የቀራችሁት ለምንድነው? ብለው እንዲጠይቁን አልፈልግም፡፡ ሌሎች አገልግሎቶች ለዚህ ተጠያቂ አይሆኑም - ተጠያቂዎቹ እኛ ብቻ ነን!›› አልኩ፡፡

የክፍሉ ከባቢ ሁኔታ ተጋጋለ፤ ውጥረትና የግጭት ድባብ ባጠላበት ሁኔታ ስብሰባው ተጠናቀቀ፡፡ እዚህ ደረጃ በመድረሱና እኔም በእንደዚያ ባለ ግለት መናገሬ ቅር አለኝ፡፡ የሥራ ባልደረቦቻችን ቅኖችና መንፈሳዊ ሰዎች መሆናቸውን አውቃለሁ፤ እነርሱ ሁሌም ለአገልግሎታችን የሚያስቡት መልካሙን ነው፡፡ ሆኖም፣ በጥልቅ ልቦናዬ ውስጥ በፍጹም ወደ ኃላ ማፈግፈግ እንደሌለብኝ አውቅ ነበር፡፡ በማደግ ላይ ላሉ የዓለማችን አገሮች፣ ጥሩ ጥሩ መንፈሳዊ መጻሕፍቶችን የተራቡ ፓስተሮችንና አብያተ ክርስቲያናትን መርዳት በተመለከተ ክፍተቱ ውስጥ መቆም በጣም አስፈላጊ ነበር፡፡

ከጥቂት ቀኖች በኃላ የአገልግሎታችን ዋናው አስተዳዳሪ ወደ እኔ መጥቶ፣ ‹‹ጆን፣ ልብህ ውስጥ ያለውን እናደርጋለን፡፡ እዚህ ያለነው ከ' እግዚአብሔር ለአንተና ለሊዛ የሰጠውን ራእይ ለማስፈጸም ነው፡፡ ግን አሁንም 250,000 መጻሕፍት ማደል እንዳለብን ታምናለህ ወይ? በጉዳዩ በሚገባ ከጸለይክበትና የምታምንበት ከሆነ፣ በምታደርገው ሁሉ መቶ በመቶ ከአንተ ጋር ነን፡፡ ያንን ግብ ለማሳካት በትጋት እንጸልያለን ደግሞም እንሠራለን›› አለ፡፡

እንደ ገና በጉዳዩ ላይ አጥብቄ ጸለይኩ፤ አሁንም ቢሆን 250,000 መጻሕፍት በነጻ ለመስጠት የነበረኝ እምነት በቦታው እንዳለ ነበር፡፡ በቬየትናም፣ በላይቤሪያ፣ በቻይና፣ በኢራን፣ በቱርክ፣ በጋና፣ በታጂክስታን፣ በሊባኖስ፣ በበርማና በሌሎችም አገሮች ላሉ መሪዎች መጻሕፍቱን የመስጠት በሮች ተከፍተውልን ነበር፡፡ መጻሕፍቱን ማግኘት ከሚፈልጉ በጣም ብዙ ጥያቄዎች እንደሚመጡም እናውቅ ነበር፡፡ ይህን የሚያህሉ መጻሕፍት ለማሳተምና በዓለም አቀፍ ደረጃ ለማሰራጨት ከ$ 600,000 እስከ 700,000 (የአሜሪካ ዶላር) ያስፈልግ ነበር፡፡ ይህ ለእኛ በጣም ብዙ ነበር፤ ለእግዚአብሔር ግን አልነበረም፡፡

ከሁለት ሳምንት በኃላ ፍሎሪዳ አንድ ሆቴል ክፍል ውስጥ እያለሁ የሥራ ባልደረቦቻችን ስልክ ደወሉልኝ፡፡ በጣም መገረማቸውና

መደነቃቸውን ከድምፃቸው በሚያሳውቅ ሁኔታ፣ ‹‹ጆን፣ በየአገሩ ላሉ መሪዎች ለምናሳትማቸው መጻሕፍት የ$300,000 ቼክ አግኝተናል›› አሉኝ፡፡ ሆቴሉ ውስጥ እያለሁ ከደስታዬ የተነሣ ጮኽኩ፡፡

በኃላ እንደ ሰማሁት ከሠራተኞቻችን አንዱ በቴክሳስ ለሚኖር አንድ ነጋዴ (ቢዝነስማን) ስላለን ራእይ ያካፍለዋል፡፡ ሰውየውም ቼክ ይጽፋል፡፡ ባለፉት ሃያ ዓመታት ውስጥ አገልግሎታችን ከአንድ ቦታ ብቻ ያገኘው ትልቁ ስጦታ $50,000 ነበር፡፡ ይህ ግን በእርግጥ፣ ተአምር ነበር! ይህ ገንዘብ ወደ 150,000 መጻሕፍት ለማሳተም ያስችለናል፡፡ ሆኖም፣ ለ2011 ያለንን ግብ ግማሹን ብቻ ነበር ያሚላነው - ወሩ ደግሞ ገና የካቲት ላይ ነበር! የቴሌፎን ጥሪው የፈሽታ ያህል ሆነልን - ሁላችንም በጣም ተነቃቅተንና ደስ ብሎን ነበር፡፡

ስልኩን ከመዝጋቴ በፊት፣ ‹‹ወገኖቼ፣ ከሁለት ሳምንት በፊት በነበረን ስብሰባ ለምን እንደዚያ አጥብቄ እንደ ተከራከርኩ አሁን ተረዳችሁ?›› በማለት ጠየቅሁ፡፡ ስብሰባው ላይ በጣም ሲከራከረኝ የነበረው ዋናው አስተዳደሪ እየሳቀ፣ ‹‹እኔስ አንተ ሰይጣን ከፊቴ ዘውር በል!›› ትለኛለህ ብዬ ነበር አለ፡፡ ሁላችንም ሳቅን፡፡

በዚያው ቀን ቆየት ብሎ ሊዛ፣ ‹‹እግዚአብሔር ለሚቻል ነገር ብቻ እንድናምነው አይፈልግም፤ እርሱ የሚፈልገው የማይቻል ስለሚመስለውም ነገር እንድናምነው ነው፡፡ ራእያችንን አጥብቀን ባንይዝ ኖሮ፣ የ300,000 ዶላሩ ቼክ እጃችን ይገባ ነበር ብዬ አላስብም›› የሚል አስተያየት ሰጠች፡፡ በዚህ እኔም እስማማለሁ፡፡

ዓመቱ መገባደጃ ላይ ዐርባ አንድ አገሮች ውስጥ በሚኖሩ መሪዎች እጅ 250,000 መጻሕፍት ተዳረሱ፡፡ የአጋሮቻችን ድጋፍና ጸሎት፣ እንዲሁም ተሳትፎ ያደረጉ ሰዎች ያላሰለሰ ጥረት ባይኖር ኖሮ፣ ይህ ግብ እውን አይሆንም ነበር፡፡ ይህ ሰዎችን የመድረሱ ሂደት ጥቂት ቅጾች የሚያስፈልጉት ምስክርነት ይወጣው ነበር፡፡

ይህ የእኔንም ሆነ የሥራ ባልደረቦቻችንን ሁሉ እምነት በከፍተኛ ደረጃ ማሳደግ ችሎአል፡፡ ይሁን እንጂ፣ እጅግ ብዛት ያላቸው ሰዎችን ሕይወት መንካት ይቻል ዘንድ፣ በሩ እንዲከፈት አጥብቆ መለመንን፣ መፈለግንና ማንኳኳትን ጠይቋል፡፡ እግዚአብሔር፣ ‹‹እንደ ኃይሉ መጠን፣ ከምንለምነው ወይም ከምናስበው ሁሉ በላይ እጅግ አብልጦ›› ማድረግ እንደሚቻለው ምንጊዜም ማስታወስ አለብን (ኤፌሶን 3፥20)፡፡ ውሱን የሆነው ሰብዓዊ አእምሮአችን በሐሳባችንም ሆነ በእምነታችን ደረጃ እርሱን

እንዲወስነው መፍቀድ የለብንም፡፡ በእውነት ምናምን ከሆነ፣ ያለ መታከት እንለምናለን፣ እንፈልጋለን፣ የእርሱ ክብር እስኪገለጥ ድረስ ማንኳኳት እንቀጥላለን፡፡

## ምን እየጠበቃችሁ ነው?

የመንግሥቱ ዕድገትና ስፋት መጀመሪያውኑ በመንፈሳዊ ክልል ካልተረጋገጠ በተፈጥሮአዊው ክልልም እውን አይሆንም፡፡ ‹‹መልካሙን የእምነት ገድል ተጋደል፤ በመልካም መታመን የመሰከርህለትንና የተጠራህበትን የዘላለም ሕይወት አጥብቀህ ያዝ›› በማለት ጳውሎስ ጢሞቴዎስን ይመክራል (1ጢሞቴዎስ 6፥12)፡፡ የዘላለምን ሕይወት መያዝ፣ ኢየሱስ ያደረገውንና ያዘጋጀልንን አጥብቀን መያዝ ማለት ነው፤ ይህ ደግሞ በከፊል ልብ ማድረግ የሚቻል አይደለም፡፡ ልጆቹ እንዲህ ያለ ውሳኔ ማድረጋቸውን እግዚአብሔር ሲያይ፣ ያኔ እርሱም ይንቀሳቀሳል፡፡

ዕብራውያን 11፥6፣ ‹‹ያለ እምነት እግዚአብሔርን ደስ ማሰኘት አይቻልም›› በማለት ይነግረናል፤ ‹‹ምክንያቱም ወደ እግዚአብሔር የሚቀርብ ሁሉ እግዚአብሔር መኖሩንና ከልብ ለሚሹትም ዋጋ እንደሚሰጥ ማመን አለበት፡፡›› ‹‹ከልብ ለሚሹት›› እንጂ፣ አልፎ አልፎ ወይም እንዲሁ ላይ ላዩን ለሚፈልጉት እግዚአብሔር ዋጋ እንደሚሰጣቸው አይደለም የተነገረን፡፡ እርሱ አጥብቀው፣ ከልብ ወደሚፈልጉት ይቀርባል፡፡

ከዚሁ እውነት አንጻር በነቢዩ በኤርምያስ በኩል እግዚአብሔር ሲናገር፣

> ለእናንተ ያለኝን ዕቅድ እኔ ዐውቃለሁ ይላል እግዚአብሔር፤ ዕቅዱም ፍጻሜው ያማረና ተስፋ የሚሰጥ፣ እናንተንም የሚጠቅም እንጂ የሚጎዳ አይደለም፡፡ እናንተም ትጠሩኛላችሁ፤ ቀርባችሁ ወደ እኔ ትጸልያላችሁ፤ እኔም እሰማችኋለሁ፡፡ እናንተ ትፈልጉኛላችሁ፣ በፍጹም ልባችሁ ከፈለጋችሁኝ ታገኙኛላችሁ - ይላል (ኤርምያስ 29፥11-14)

እግዚአብሔር ለሕይወታችን ያለው ዕቅድ መልካም ነው፡፡ ይሁን እንጂ፣ ይህን የበዛና የተትረፈረፈ ልግስና ለመቀበል፣ ከልብ አጥብቆ መፈለግ ይጠይቃል፡፡ ይህ እውነተኛ እምነት ነው፡፡

ስለ ሴትየዋና ዐመፀኛው ዳኛ በተናገረው ምሳሌ መጨረሻ ላይ ኢየሱስ ያለውን ታስታውሳላችሁ? ‹‹የሰው ልጅ በሚመጣበት ጊዜ በምድር ላይ እምነትን ያገኝ ይሆን?›› ነበር ያለው፡፡ ምንኛ የሚገርም ጥያቄ ነው!

እርሱ ወደ እኛ ሲመጣ የሚያገኘው እንዲሁ ላይ ላዩን የሆነ፣ ከፊል ልብና ፈራ ተባ የሚል እምነትን ነው ወይስ እውነተኛ እምነትን? እርሱ እየተናገረለት ያለው እምነት አዘወትራ በመጠየቋ ዳኛውን ካታከተችው ሴት ጋር የሚመሳሰል እምነት ነው፡፡

ስለዚህ በጸሎት ወደ እግዚአብሔር ስትቀርቡ ዐይናፋር አትሁኑ፡፡ የጸሎት ጥያቄዎቻችሁ ፈራ ተባ አይበሉ፡፡ በእርሱ ኃይል ደፋሮች፣ ጠንካሮች፣ ጽኑዎችና ግልጾች ሁኑ፡፡ በእግዚአብሔር ፊት ያለን ጽናት፣ እርሱ የሚወደን አባታችን መሆኑንና በስሙ አጥብቀን የምንለምነውን የሚሰጠን መሆኑን ካለን ልበ ሙሉነት እንጂ፣ ከተስፋ መቁረጥና ጀምሮ ከመተው የሚመጣ አይደለም፡፡

ስለዚህ በጸሎት ወደ እግዚአብሔር ስትቀርቡ ዐይናፋር አትሁኑ፡፡

ምን እየጠበቃችሁ ነው? በዙሪያችሁ ትልልቅ ችግሮች አሉ፡፡ እነርሱን በተመለከተ በልበ ሙሉነት በጸሎት ወደ እግዚአብሔር ፊት እንድትቀርቡላቸው የሚፈልጉ ብዙ ሰዎች በአካባቢያችሁ አሉ፡፡ ብርሃን ሁኑላቸው! በማይናወጥ ጽናት አሁኑኑ ወደ እግዚአብሔር ቅረቡ!

# 16

# ሽልማት እንደሚቀበል ሩጡ

*ስለዚህ ሽልማቱን እንደሚቀበል ሰው ሩጡ፡፡*

*1ቆሮንቶስ 9፥24*

ከዚህ መጽሐፍ ስናነብ እንደ ነበረው እኔና እናንተ ተግዳሮት ያለበት ሩጫ ውስጥ ነን፡፡ ከላይ የተመለከትነው 1ቆሮንቶስ ላይ ያለው ክፍል ሩጫው ግላዊ መሆኑን ያሳያል፡፡ የአንተ ወይም የአንቺ የግል ሩጫ ነው፤ የእኔም የግሌ ሩጫ ነው፡፡

ውድድሩ በሚገባ እንዳንጨርስ ከሚፈልጉ ኃይላት ጋር ነው እንጂ እርስ በርሳችን አይደለም፡፡ እኔና እናንተ የምንኖረው በኃጢአት በወደቀ ዓለም ውስጥ በመሆኑ ተቃውሞ መምጣቱ የማይቀር ነው፡፡ ውድድር ሜዳ ውስጥ ነን፡፡ አንድ የመጽሐፍ ቅዱስ ትርጉም — ‹‹ሽልማት እንደሚያገኝ ሰው ሆናችሁ ሩጡ›› ይላል፡፡

በምን ዓይነት ሁኔታ ነው መሮጥ ያለብን? በጽናት መሮጥ አለብን፡፡ የዕብራውያን መልእክት ጸሐፊ፣ ‹‹…በፊታችን ያለውን ሩጫ በጽናት እንሩጥ›› ይላል (12፥1)፡፡

በሕይወቴ ሁሉ የአትሌቲክስ ወዳጅ ነኝ፤ አብዛኞቹ ጓደኞቼም አማተር ወይም ፕሮፌሽናል አትሌቶች ናቸው፡፡ ጠበቅ አድርገው የያዙት በአዳጋች ሁኔታዎች ውስጥ እንኳ በመጽናት ከባድ ልምምድ ያደርጋሉ፡፡ ጳውሎስ፣ ‹‹ለውድድር የሚዘጋጅ ማንኛውም ሰው በሁሉም ነገር ራሱን ይገዛል›› ይላል (1ቆሮንቶስ 9፥25)፡፡ አትሌቶች እንዲህ የሚያደርጉት ለምንድነው? ሐዋርያው፣ ‹‹ሽልማት ለመቀበል›› የሚል መልስ ነው የሚሰጠው፡፡

ሽልማቱ ላይ ማተኮራቸው ተነሣሽነት ይሰጣቸዋል፡፡ ሁሉ ነገራቸውን ሽልማቱ ላይ ያደረጉ ራእይና ሽልማቱን ለማግኘት ተነሣሽነት ከሌላቸው የበለጠ አዳጋች ሁኔታዎችን በመታገሥ ልምምድ ያደርጋሉ፡፡

ቁርጭምጭሚቱ ላይ ከባድ ጉዳት ቢደርስበትም፣ እስከ መጨረሻው ድረስ በጨዋታው መቀጠል እንዲፈቅድለት አጥብቆ አሠልጣኙን እየለመነ የነበረ የሖኪ ተጨዋች አይቻለሁ። ሕመም ቢኖረው እንኳ፣ አብዛኞቹ ሰዎች የማይደፍሩትን መቋቋም ችሎአል። አፍንጫው ላይ ጉዳት ቢደርስበትም፣ አሸንፎ የመገኘት ራእይ ስለ ነበረው የሕመሙ ስቃይ እየተሰማው እስከ መጨረሻው መጫወቱን የቀጠለ የእግር ኳስ ተጫዋች አይቻለሁ። በስፖርትም ይሁን በሌላ መስክ፣ በተለያየ ጊዜ ሁላችንም እንዲህ ያሉ ሁኔታዎች አይተናል። ራእይ ታላቅ ተነሣሽነት ሰጪ ነው። እንዲህ ያለውን ችግር በጽናት የሚታገሡ፣ ራእያቸውን ወይም ትኩረታቸውን ሽልማቱ ላይ ያደረጉ ናቸው።

ብርቱና አጥፊ ከሆኑ የሰይጣን ጭፍሮች ጋር በየዕለቱ እንደሚፋለም የእግዚአብሔር መንግሥት ሕዝብ፣ የምንወዳደረው ለምን እንደ ሆነ ማወቅ ይኖርብናል። ለመሆኑ የጀመርነውን ለመጨረስ ያለን ተነሣሽነት ምን ያህል ነው? ታማኝ እንደ ሆንን መዝለቅ ይህን ያህል አስፈላጊ የሆነው ለምንድነው? እንደ እግዚአብሔር ሕዝብ የግል ሕይወታችን ለዚያ ያለው አስተዋፅዖ ምንድነው? እግዚአብሔር በፊታችን ያኖረው ሩጫ ትልቁ የመንግሥቱን ስዕል በማሟላት ረገድ ይህን ያህል አስፈላጊ የሆነው ለምንድነው?

በመልካም ሁኔታ መጀመር ጥሩ ነው፤ ይሁን እንጂ፣ በእግዚአብሔር አሠራር የበለጠ ፋይዳ የሚኖረው አጨራረሳችን ነው።

የእነዚህ ጥያቄዎች መልስ ለአንድ አትሌት ወይም ለሩዋጭ ከሚሰጠው መልስ ጋር አንድ ዓይነት መሆናቸውን ጳውሎስ ይነግረናል። ሽልማት ወይም ዋጋ ለማግኘት እንደክማለን፤ ‹‹ስለዚህ ሽልማቱን እንደሚቀበል ሰው ሩጡ።›› በመጨረሻው የሕይወት ዘመኑ ሐዋርያው ዮሐንስም ከዚህ ጋር የሚመሳሰል የእግዚአብሔር ትእዛዝ አስፍሮልናል፤

> እናንተም የደከማችሁበትን ዋጋ እንዳታጡ፣ ነገር ግን ሙሉ ሽልማት እንድትቀበሉ ለራሳችሁ ተጠንቀቁ። (2 ዮሐንስ 8)

እንደሚገባ መጨረስ ባለ መቻሉ ሰሎሞን የላቀውን ሽልማት ሳይቀበል ቀርቷል። ትኩረቱን ሁሉ ግቡ ላይ አላደረገም።

በመልካም ሁኔታ መጀመር ጥሩ ነው፤ ይሁን እንጂ፣ በእግዚአብሔር አሠራር የበለጠ ፋይዳ የሚኖረው አጨራረሳችን ነው። በመልካም ሁኔታ መጨረስና ሽልማቱን መቀበል ጽናትና ትዕግሥት ይጠይቃል፤ ሁለቱም ደግሞ ከተነሣሽነት ኃይል ማግኘት አለባቸው። ስለሆነም፣ የምንደክምለት

ሽልማት ምንድነው? እንዳናጣው የተነገረንስ ዋጋ ምንድነው? የሚለውን በጣም ጠቃሚ ጥያቄ እዚህ ላይ መመርመር ተገቢ ነው፡፡

ሽልማቱን በሁለት ደረጃ ማየት ይቻላል፡፡ የመጀመሪያውን እዚህ አሁን እንመረምራለን፣ ሁለተኛውን ደግሞ፣ በቀጣዩ ምዕራፍ እንመረምራለን፡፡

## የመጀመሪያው ሽልማት

የመጀመሪያው ሽልማት ወይም ዋጋ፣ የሕይወታችን አቅጣጫ የእግዚአብሔርን መንግሥት - ማለትም ለዘላለም የምንኖርበትን መኖሪያ ከመሥራት ጋር በቀጥታ ይያያዛል፡፡[1]

እግዚአብሔር ራሱ ቤት - ማለትም በጣም የከበረ ቤት እየሠራ ነው፡፡ እዚያ ቤት ውስጥ ለመኖር በጣም በመፈለጉ የዘመናት ትኩረቱም እዚያ ላይ ነበር፡፡ በእርግጥ መኖሪያውን እዚያ ለማድረግ አጥብቆ ይፈልጋል፡፡

እኔና ሊዛ ደረጃውን የጠበቀ ቤት አሠርተን ነበር፡፡ በ1980ዎቹ መጨረሻዎቹ ዓመታት ኦርናልዶ ፍሎሪዳ እየኖርን እያለ ሮበርት የሚባል ደረጃውን የጠበቀ ቤት ሠሪ ወደ እኛ መጥቶ ነበር፡፡ ‹‹አግልግሎታችሁን በጣም ነው የምወደው›› አለኝ፤ በማያያዝም፣ ‹‹ደረጃውን የጠበቀ ቤት ልሠራላችሁ እፈልጋለሁ›› አለ፡፡ በዚያ ዘመን እንኖር የነበረው በጣም ትንሽና መጠነኛ ቤት ውስጥ ነበር፤ ምናልባትም ለቤቱ መሥሪያ ሰውየው የሚጠይቀው ገንዘብ በጣም ውድ ሊሆን እንደሚችል አሰብን፡፡ ይህንኑ ስንነግረው ሮበርት፣ ‹‹የለም፤ እኔው ራሴ ነኝ 'በእግዚአብሔር ዋጋ' የምሠራላችሁ›› አለን፡፡ በእርግጥም ከቤቱ የአንዲት ሳንቲም ጥቅም እንኳ አላገኘም ነበር፡፡

ከዚያ ቀደም ሲል እኔና ሊዛ ሁለት ቤቶች ነበሩን፡፡ ንድፋቸውን ወይም ካርታቸውን በተመለከተ ምንም ያደረግነው ነገር አልነበረም፤ ቤቱን በተመለከተም በጣም መጠነኛ በሆነ ደረጃ እንጂ፣ ይህ ነው የሚባል ውሳኔ ማድረግ አልተፈቀደልንም ነበር፡፡ ስለሆነም ደረጃውን የጠበቀ ቤት የማሠራት ውጣ ውረድ ለእኛ ፍጹም እንግዳ ነገር ነበር፡፡

1. የእግዚአብሔርን ቤት በተመለከተ ሰፋ ያለ ማብራሪያ ለማግኘት *Driven By Eternity* የተሰኘውን መጽሐፌን አንብቡ (New Yourk Faith Words, 2006)

ከጥቂት ቀን በኋላ ሮበርት ወደ ቤታችን መጥቶ እያለ አንድ ባዶ ወረቀት አውጥቶ፣ ‹‹የምትፈልጉትን ዓይነት ቤት እዚህ ላይ ሳሉ!›› በማለት በስሜት ሲነግረን የነበረውን ሁኔታ በፍጹም አልረሳውም፡፡

ግራ ተጋባን፤ እንዲህ ያለ ነገር መኖሩን ጨርሶ አናውቅም ነበር፡፡ ግን ሊዛ ስለዚህ ጉዳይ ስታስብ እንደ ነበረ ሰው ሆና መሳል ጀመረች፡፡ እኔ ትንሽ ቀርፋፋ ስለ ሆንኩና ለጥናቴ ሐሳቦች እያዘጋጀሁ ስለ ነበር አብዛኛውን ነገር የሠራችው ሚስቴ ነበረች፡፡ የአዲሱ ቤታችንን ንድፍ እኛ በምንፈልገው ሁኔታ መሥራት የመቻላችን ሐሳብ ራሱ በጣም ደስ የሚልና የሚያጓጓ ነበር፡፡

በዚያ ትልቅ ወረቀት ላይ እኛ እንደ ነገሩ የሠራነው ንድፍ ወደ አርኪቴክተሩና ዲዛይነሩ ተወስዶ ከጥቂት ቀን በኋላ ሙሉውን የቤቱን ፕላን አሳዩን፡፡ በጣም ደስ የሚል ነበር፡፡ ብዙም ሳይቆይ መሠረት ተጥሎ ሕንፃው ተጀመረ፡፡

እኔና ሚስቴ ቤቱ እየተሠራ ወደ ነበረበት ቦታ በየቀኑ እንሄድ ነበር፡፡ እንዲያውም፣ አንዳንዴ በቀን ሁለቴ እንሄድ ነበር፡፡ ቀጣዩን የሕንፃውን ገጽታ እስክናይ ድረስ በጣም ጓጉተን ነበር፡፡ ደረጃውን የጠበቀ ቤታችን ፕላን ውስጥ አዳዲስ ነገር መጨመሩና በቅርቡ እዚያ ቤት የመኖር ናፍቆታችን፣ ጥቂት ወሮች የዓመታት ያህል፣ ጥቂት ቀኖች የሳምንቶች ያህል የረዘሙብን መሰለን፡፡ እዚያ ባዶ ወረቀት ላይ የሰፈረው ንድፍ ነፍስ ሲዘራና እውን ሲሆን በዐይናችን ስናይ በጣም ተደነቅን!

እርሱ የሚፈልገው ቤት ተሠርቶ ለማየት እግዚአብሔር ያለው ፍላጐት እኛ ከነበረን ፍላጐት በጣም የበለጠ መሆኑን አምናለሁ፡፡ እንደ እኛ ለጥቂት ወሮች ሳይሆን፣ እርሱ ለዘመናት ሲጠብቅ ኖሮአል፡፡ እንዲያውም ቤቱ ተሠርቶ ለማየት እግዚአብሔር ከዓለም መፈጠር በፊት ነው ሲጠብቅ የነበረው፡፡

በዚህ ምድር ለአንዳንድ ለየት ለሚሉ ቤቶች መጠሪያ ስም እንሰጣቸዋለን፡፡ ለምሳሌ የእንግሊዟ ንግሥት ቤት ባክኒንግሃም ቤተ መንግሥት ይባላል፡፡ የአሜሪካው ፕሬዚዳንት የሚኖርበት ቤት ኃይት ሐውስ ይባላል፡፡ ቤርሙዳ ያለው የአክተር ሚካኤል ዳግላስ ቤት ሎንግላንድስ ነው፡፡ የቀድሞ ቢትል የጆርጅ ሐሪሰን ቤት ፍራየር ፓርክ ነው፡፡ የአክተር ኒኮላስ ኬጅ ቤት ሚድፎርድ ካስል ነው፡፡ ብዙዎቻችን የማናውቀው ነገር እግዚአብሔር ለዚህ ቤት ስም ማውጣት የጀመረው ከእኛ ረጅም ዘመናት በፊት ቀድሞ መሆኑን ነው፡፡ ዛሬም እንኳ እየተሠራ ያለውን ዘላለማዊ ቤቱን

ጽዮን በማለት ጠርቶታል፡፡ ይህን በተመለከተ ዘማሪው ሲጽፍ እንዲህ ይላል፣

> እግዚአብሔር ጽዮንን መርጦአታልና፤ ማደሪያውም ትሆን ዘንድ ወዶአልና እንዲህ አለ – ይህች ለዘላለም ማረፊያዬ ናት፤ ፈልጌአታለሁና በእርሷ እኖራለሁ፡፡ (መዝሙር 132÷13-14)፡፡

ይህን ቤት እግዚአብሔር እንደ ፈለገው ልብ አድርጉ፡፡ እኔና ሊዛ አዲሱ ቤታችንን በናፍቆት ስንጠብቅ እንደ ነበር ሁሉ እርሱም በናፍቆት ይጠብቃል፡፡ ይህ ጽዮን የተሰኘው ቤት በትውልዶች ዘመን ሁሉ በእግዚአብሔር ልብ ውስጥ እንደ ነበር የሚናገሩ ሌሎች የቅዱሳት መጻሕፍት ክፍሎችም አሉ፡፡ ‹‹እግዚአብሔር ጽዮንን መልሶ ይሠራታልና›› (መዝሙር 102÷16)፤ ‹‹በጽዮን የሚኖር እግዚአብሔር›› (መዝሙር 9÷11)፤ ‹‹ፍጹም ውብ ከሆነችው ከጽዮን እግዚአብሔር አበራ›› (መዝሙር 50÷2)፡፡

አንድ ቤት ስትሠሩ የምትጀምሩት ከመሠረት ነው፡፡ ኢሳይያስ፣ ‹‹እነሆ የተፈተነ ድንጋይ፣ የመሠረት ድንጋይ፣ ለጽኑ መሠረት የሚሆን የከበረ የማእዘን ድንጋይ በጽዮን አስቀምጣሁ›› ይላል (ኢሳይያስ 28÷16)፡፡ የማእዘኑ መሠረት ድንጋይ ምንድነው ወይም ደግሞ የበለጠ ትክክል ለመሆን ማን ነው? የተወደደው የእግዚአብሔር ልጅ ኢየሱስ ክርስቶስ ነው፡፡ ኢሳይያስ እንደሚነግረን ኢየሱስ ዘላለማዊ የእግዚአብሔር ቤት – ጽዮን የሚሠራባቸው ነገሮች አካል ነው፡፡ እንዲያውም የማእዘን ድንጋይ እንደ መሆኑ መጠን፣ እርሱ እጅግ በጣም አስፈላጊው ወይም ጠቃሚ ክፍል ነው፡፡

ከዚያም የእግዚአብሔር ቃል፣ ‹‹እናንተ ደግሞ... እንደ ሕያዋን ድንጋዮች መንፈሳዊ ቤት ለመሆን ትሠራላችሁ›› ይላል (1ጴጥሮስ 2÷5)፡፡ ጴጥሮስ እየተናገረለት ያለው ቤት ጽዮን እንደ ሆነ ግልጽ ነው፡፡ ኢየሱስ በምሳሌያዊ ቃል ድንጋይ ተብሏል፤ እኛም እንደዚያው ነን፡፡ እኛ ‹‹ሕያዋን ድንጋዮች›› ስንሆን እርሱ ደግሞ የማእዘን ድንጋይ ነው፡፡ ከኢየሱስ ጋር አብረው በመሆን ክርስቲያኖች እግዚአብሔር ለዘላለም የሚኖርበት ቤት መሥሪያዎች ናቸው!

> በሐዋርያትና በነቢያት መሠረት ላይ ታንጻችኃል፤ የማእዘኑ ራስ ድንጋይ ክርስቶስ ኢየሱስ ራሱ ነው፤ በእርሱ ሕንፃ ሁሉ አንድ ላይ ተገጣጥሞ በጌታ ቅዱስ ቤተ መቅደስ እንዲሆን ያድጋል፡፡ እናንተም ደግሞ እግዚአብሔር በመንፈስ የሚኖርበት ማደሪያ ትሆኑ ዘንድ አብራችሁ እየተገነባችሁ ነው፡፡ (ኤፌሶን 2÷19-22)

## ረዳት ሠራተኞች

ሕንፃው የሚሠራባቸው ነገሮች ብቻ ሳይሆን፣ አብረን የምንሠራ እንደ ሆነም ተነግሯል (1ቆሮንቶስ 3፥9 ይመለከቷል)፡፡ በዘመኑ ሕንፃ ሥራ ቋንቋ፣ ‹‹ረዳት ሠራተኞች›› ማለት ይቻላል፡፡ ረዳት ሠራተኞቹ እነማን ናቸው? ግንበኞች ለሳኞች፣ አናጢዎች፣ ኤሌክትሪሺያኖች፣ ቧንቧ ሠራተኞች ወዘተ ናቸው፡፡ ቤቱን እውን የሚደርጉት እነዚህ ሁሉ በአንድነት ሆነው ነው፡፡ ሮበርት ቤቱን በሠራልን ጊዜ፣ ቤቱ ላይ አንዲት ሚስማር እንኳ አልመታም፣ አንዲት ብሎኬት እንኳ በቦታው አላኖረም፤ አንዱን አጠና እንኳ አልቆረጠም ያንን ሁሉ የሠሩ ረዳት ሠራተኞቹ ወይም ተቋራጮቹ ናቸው፡፡

ታዲያ፣ ቤቱን የሚሠሩ ረዳቶቹ ወይም ተቋራጮቹ ከሆኑ የመሐንዲሱ ሥራ ምን ሊሆን ነው? ሦስት መልሶች አሉ፡፡ በመጀመሪያ ደረጃ፣ መሐንዲሱ የቤቱን ፕላን ይሠራል፡፡ የራሱን ቤት የሚሠራው እርሱ እንደ መሆኑ መጠን እግዚአብሔር ከረጅም ጊዜ በፊት ዋናውን ፕላን አውጥቶአል፡፡ ሐዋርያው ጳውሎስ፣ ‹‹...ዓለም ከመፈጠሩ አስቀድሞ መርጦናልና›› ይላል (ኤፌሶን 1፥4)፡፡ የዕብራውያን መልእክት ጸሐፊም፣ ‹‹ዓለም ከተፈጠረ ጀምሮ የእርሱ ሥራ ተከናውኖአል›› ይለናል (4፥3)፡፡ የእግዚአብሔር ቤት የታቀደው አዳም ከመፈጠሩ ረጅም ጊዜ በፊት ነበር፡፡ በጣም ይገርማል!

በሁለተኛ ደረጃ፣ ቤቱ የሚሠራባቸውን ነገሮች የሚወስን መሐንዲሱ ነው፡፡ ሕይወታችሁ በእግዚአብሔር የታቀደና የተመረጠ መሆኑ ደስ አይላችሁም? ‹‹በማሕፀን ሳልሠራህ ዐወቅሁህ፤ ከመወለድህ በፊት ለየሁህ›› የሚለው በዚህ ምክንያት ነው (ኤርምያስ 1፥5)፡፡ ጳውሎስም፣ ‹‹ዓለም ከመፈጠሩ አስቀድሞ በእርሱ መርጦናልና›› በማለት ይነግረናል (ኤፌሶን 1፥4)፡፡

ሦስተኛው የመሐንዲሱ ኃላፊነት ረዳት ሠራተኞቹን ወይም ተቋራጮቹን በቅደም ተከተል ማሰማራት ነው፡፡ መጀመሪያ ሕንፃው ሳይዋቀር፣ የቧንቧ ቱቦዎች ወይም የኤሌክትሪክ ሽቦዎች አይዘረጉም፡፡ ግድግዳው ሳይሠራ፣ ቀለም ቀቢው ወደ ሥራ አይገባም፡፡ ረዳት ሠራተኞቹ በቅደም ተከተሉ መሠረት የማይሠሩ ከሆነ ምስቅልቅል ነው የሚሆነው፡፡ ስለዚህም ይህ የሥራው ገጽታ በጣም አስፈላጊ ነው ማለት ነው፡፡

ብዙ ጊዜ የዘመናዊ ቤቶች ግንባታ፣ ‹‹ዋና ተቋራጭ›› የላቸውም፤ የእግዚአብሔርን ቤት በተመለከተ ግን እንደዚያ አይደለም፡፡ የእግዚአብሔር ቤት ዋናው ተቋራጭ ማን ይመስላችኋል? ልክ ናችሁ - ኢየሱስ ክርስቶስ

ነው፡፡ ገላትያ 4፥4፣ ‹‹የተወሰነው ጊዜ በደረሰ ጊዜ፣ እግዚአብሔር ልጁን ላከ›› ይላል፡፡ ጽዮን የምትሠራበት፣ ‹‹የተወሰነው ጊዜ›› በደረሰ ጊዜ ዋናው መሐንዲስ እግዚአብሔር፣ የማእዘን ራስ ድንጋይና ረዳት ሠራተኛ የሆነው ኢየሱስ ክርስቶስን ላከ፡፡

የዋና ሠራተኛነት ድርሻውን ኢየሱስ በሚገባ አጠናቅቆአል፡፡ የጀመረውን በመልካም ሁኔታ ፈጽሞአል! የመጨረሻውን ራት ከደቀመዛሙቱ ጋር በበላ ጊዜ፣ ‹‹የሰጠኸኝን ሥራ በመፈጸም በምድር አከበርሁህ›› በማለት በትሕትናና በልበ ሙሉነት ለአባቱ መናገር ችሎ ነበር (ዮሐንስ 17፥4)፡፡ እንደ ዋናው የሥራ መሪ ጽዮንን የመሥራት ዋና ድርሻውን ኢየሱስ አጠናቅቆአል፡፡

እኔና እናንተን በተመለከተስ? በእግዚአብሔር ቤት ሥራ እንደ ተሰማሩ ረዳት ሠራተኞች ስላለን ድርሻ የእግዚአብሔር ቃል ምን ይላል?

‹‹እግዚአብሔር አስቀድሞ ያዘጋጀልንን መልካም ሥራ እንድንሠራ በክርስቶስ ኢየሱስ የተፈጠርን የእግዚአብሔር እጅ ሥራዎች ነን›› ተብሎ ተነግሮናል (ኤፌሶን 2፥10)፡፡ ‹‹መልካም ሥራ›› እንድንፈጽም በክርስቶስ የተፈጠርን መሆኑን ልብ አድርጉ፡፡ በሌላ አነጋገር እኛ የተፈጠርነው ማንኛውም ዓይነት ሰው እንድንሆን ሳይሆን፣ አንዳች ቁም ነገር፣ አንዳች መልካም ነገር እንድንሠራ ነው፡፡ ይህን በጣም ልብ አድርጉ፤ ከጥቂት ዓመታት ወዲህ ይህን በተመለከተ በክርስቶስ አካል ሚዛናዊነት የሌለው ትምህርት እየተሰጠ ነው፡፡ በክርስቶስ ስላለን ማንነት ጠንከር ያለ አጽንዖት ሰጥተናል፤ በመሠረቱ ይህ ጠቃሚም አስፈላጊም ቢሆንም፣ በክርስቶስ የተፈጠርንበትን ዓላማ ችላ እንድንል እስኪያደርገን ድረስ አጽንዖት መስጠታችን ግን ትክክል አይደለም፡፡ ይህ ጉዳይ ሚዛን የጠበቀ አለመሆኑ ለሁለት ትልልቅ ችግሮች ምክንያት ሆኖአል፡፡

በመጀመሪያ ደረጃ፣ በምዕራቡ ዓለም ልፍስፍስ ቤተ ክርስቲያን እንድትገኝ አድርጎአል፡፡ አብዛኞቹ አማኞች በሳምንት አንድ ቀን ወደ ቤተ ክርስቲያን ይሄዳሉ፤ ብዙዎቹም ያን ያህል እንኳ አይሄዱም፡፡ በሥራችን ዕድገት እንድናገኝ፣ ማኅበራዊ ሕይወታችንን እንድናሻሽል ልዩ ጥረት እያደረግን ነው፡፡ መኪና መግዛት፣ የቤት ዕዳችንን መክፈል፣ ልጆቻችንን ማሳደግና፣ እነርሱን ማስተማሪያ ገንዘብ ማጠራቀም፣ ለጡረታ ዘመናችንም አንዳች ነገር ማድረግ እንፈልጋለን፡፡ እነዚህ ነገሮች በግል ለእግዚአብሔር የመሰጠት ፍጻሜ መሆን ሲኖርባቸው የተነሣሽነታችን ምክንያት ሆነውብናል፡፡ በጣም ብዙዎቻችን ማጠናቀቅ ወይም መጨረስ ያለብን ዘላለማዊ፣ ‹‹ሥራ›› ያለን የመሆኑን ሐቅ ችላ ብለናል፡፡

እስቲ ስለዚህ ጉዳይ ረጋ ብላችሁ አስቡ - መጀመሪያውኑ መንገዱን ባያውቅ ኖሮ ጳውሎስ፣ ‹‹ሩጫውን ጨርሻለሁ›› ማለት እንዴት ይችል ነበር? (2ጢሞቴዎስ 4፥7)፡፡ እስቲ ግልጽ ላድርገው፡፡ በቡድን ሆናችሁ አገር አቋራጭ ጉዞ ማድረግ ከፈለጋችሁ፣ ከጉዞው በፊት ተሳታፊዎች ሁሉ የጉዞው ካርታ ያላቸው መሆኑን ማወቅ ይኖርባችኋል፡፡ የመሮጫ መስመሩን ሳታውቁ አገር አቋራጭ ሩጫ የምታደርጉ ከሆነ፣ መጨረሻ ላይ ደክሞአችሁ ትወድቃላችሁ፤ ጉዞውን ማጠናቀቅ አለማጠናቀቃችሁን እንኳ አታውቁም፡፡ በእውነትና በትክክል ሩጫውን መጨረሳችሁን መናገር የምትችሉት የታቀደውን መንገድ የምታውቁና የምትከተሉ ከሆናችሁ ብቻ ነው፡፡ እንደ ኢየሱስ ሁሉ ጳውሎስም፣ ‹‹የሰጠኸኝን ሥራ ፈጽሜአለሁ›› ማለት ችሎአል፡፡

ትኩረታችን ሁሉ የዕለት ተዕለት ጉዳያችን ላይ ብቻ እስከ ሆነ ድረስ፣ እንዴት አድርገን ሩጫችንን መጨረስ እንችላለን? ከእርሱ ጋር ያለን ግንኙነት በሳምንት አንድ ቀን እሑድ ብቻ ከሆነ፣ እግዚአብሔር ለእኛ ያደረገውን እንዴት እናውቃለን? በየዕለቱ በትጋት እርሱን የማንፈልግ ከሆነ እንዴት አድርገን የእርሱን ዕቅድ እናውቃለን?

ሚዛኑን ያልጠበቀ አጽንዖት መስጠታችን የፈጠረው ሁለተኛ ችግር፣ ብዙ ክርስቲያኖች እውነተኛ የእግዚአብሔር ጥሪ ያላቸው፣ የሙሉ ጊዜ አገልጋዮች ብቻ ናቸው በማለት ማሰባቸው ነው፡፡ ወንድ ይሁን ሴት፣ ወጣት ይሁን ሽማግሌ፣ እያንዳንዱ ከእግዚአብሔር የተወለደ ሰው ሰማያዊ ጥሪ አለው፤ ያ ጥሪ በእግዚአብሔር ቤት ሥራ ውስጥ ታማኝ ሠራተኛ ሆኖ መገኘት ነው፡፡ ምክንያቱም፣ ‹‹እግዚአብሔር አስቀድሞ ያዘጋጀልንን መልካም ሥራ እንድንሠራ በክርስቶስ ኢየሱስ የተፈጠርን የእግዚአብሔር እጅ ሥራዎች ነን›› (ኤፌሶን 2፥10)፡፡

ጽዮንን ማለትም የእርሱን ዘላለማዊ ቤት በመሥራት ረገድ የአንድ ረዳት ሠራተኛን ድርሻ የመወጣትን መብት እግዚአብሔር ሰጥቷችኋል፡፡ ቤቱ የሚሠራው በድንጋይ፣ በእንጨት ወይም በሌላ ነገር አይደለም፡፡ በሰው እጅ ያልተሠራ፣ የንጉሥ ልጆች በሆኑ ወንዶችና ሴቶች ልጆች የተሠራ ቤት ነው፡፡ በዘመናችን እንዳሉ ብዙ ተቋራጮች በዚያ ቤት የተሟላ ፍጻሜ ውስጥ የእናንተ ሕይወት ጥሪ ስላለው አስተዋፅዎ ላታውቁ ትችላላችሁ፤ እንደ እውነቱ ከሆነ ያንን ሁሉ የሚያውቅ ዋናው መሐንዲስ ነው፡፡ አንድ ቀን ቤቱ ሲጠናቀቅና ለዘላለም ከእርሱ ጋር በምንኖርበት ጊዜ ግን ያደረግነው አስተዋፅዎ የተሟላ ትርጉም ይኖረዋል፡፡

ሮበርት ሠራተኞቹን ሲያሰማራ የፕላኑን የተወሰኑ ክፍሎችንም ለእያንዳንዳቸው ሰጥቷቸው ነበር፡፡ በትክክል እንዲያደርጉ የፈለገውን ነበር

እፊታቸው ያኖረው፡፡ ሙሉውን ፕላን የሚያውቅ - እርሱ ነው፤ እነርሱ ግን የተሰጣቸውን ድርሻ ብቻ ነው የሚውቁት፣ እንዲሠሩ የሚጠበቅባቸውም የራሳቸውን ድርሻ ብቻ ነው፡፡ ቤቱ እየተሠራ ወዳለበት ቦታ መጥተው፣ የተሰማቸውን ወይም መልካም መስሎ የታያቸውን አይሠሩም፡፡ የእነርሱ ድርሻ መሐንዲሱ አስቀድሞ ያዘጋጀውን ፕላን መከተል ነው፡፡

ለእኔ፣ ለእናንተና ኢየሱስ ክርስቶስን ጌታና አዳኝ ላደረገ ማንኛውም ሰው እግዚአብሔር አስቀድሞ የተሻለውን መንገድ አዘጋጅቶአል (ኤፌሶን 2፥10)፡፡ ቤታችንን እንደሚሠሩ ረዳት ሠራተኞች ሁሉ እያንዳንዳችንም በእግዚአብሔር ዘላለማዊ ቤት ሥራ ውስጥ ራሱን የቻለ ድርሻ አለን፡፡ አንዱ ሥራ ከሌላው የበለጠ ወይም ያነሰ በፍጹም ሊሆን አይችልም፡፡ ቤቱ እርሱ ባቀደው መልኩ በትክክል እንዲሠራ እግዚአብሔር ይፈልጋል፤ ያ ደግሞ የእያንዳንዳችንን ተሳትፎና በሚገባ ማጠናቀቅን ይጠይቃል፡፡

## የግንበኛው ሽልማት ወይም ኪሳራ

ቅዱሳት መጻሕፍት ውስጥ ብዙ ጊዜ ግንበኞች ተብለን ስለ ተጠራንበት ምክንያት አሁን በተሻለ ሁኔታ መረዳት ትችላላችሁ፡፡ ‹‹ግንበኞች የናቁት ድንጋይ እርሱ የማእዘን ራስ ሆነ›› በማለት ዘማሪው ጽፎአል (118፥22)፡፡ ቀደም ሲል እንደ ተመለከትነው ጴጥሮስ በእግዚአብሔር ቤት ሥራ ውስጥ አማኞች ሁሉ ‹‹ድንጋይ›› መሆናቸውን ከተናገረ በኋላ እንደ እግዚአብሔር ቤት ሠራተኞች ስላለብን ድርሻ ሲያመለክት፣ ‹‹…እንደ ሕያዋን ድንጋዮች መንፈሳዊ ቤት ለመሆን ትሠራላችሁ… እንግዲህ ለእናንተ ለምታምኑት ይህ ድንጋይ ክቡር ነው፤ ለማያምኑት ግን - ግንበኞች የናቁት ድንጋይ እርሱ የማእዘን ራስ ሆነ›› ይላል (1ጴጥሮስ 2፥5፣7)፡፡

ታዛገሮቹ በታማኝነትና በእውነት የእግዚአብሔርን ቤት የሚሠሩ ግንበኞች ሲሆኑ፣ የማይታዘዙ ወይም የእግዚአብሔርን ዕቅድና ፕላን የማይከተሉ ግን ከታቀደው ግብ ውጪ እንደሚሠሩ ከዚህ ጴጥሮስ ከተናገረው ቃል እንረዳለን፡፡

እንግዲህ ይህን በአእምሮአችን ከያዝን፣ ስለ ሂደቱና ሽልማት አሰጣጡ፣ ሐዋርያው ጳውሎስ የሚያቀርበውን ገለጻ ለመመርመር ተዘጋጅተናል ማለት ነው፡፡

> …እያንዳንዱም እንደ ሥራው መጠን የራሱን ሽልማት ይቀበላል፡፡ እኛ ከእግዚአብሔር ጋር አብረን የምንሠራ ነንና፡፡ …የእግዚአብሔር ሕንፃ (ጽዮን) ናችሁ፡፡ ከእግዚአብሔር በተሰጠኝ ጸጋ መጠን እንደ

አንድ ብልኅ ግንበኛ መሠረትን ጣልሁ፤ ሌላውም በላዩ ላይ ይገነባል፤ ነገር ግን እያንዳንዱ እንዴት እንደሚገነባ መጠንቀቅ አለበት፡፡ ምክንያቱም አንድ ጊዜ ከተመሠረተው መሠረት በቀር ሌላ መሠረት መጣል የሚችል ማንም የለም፤ ይህም መሠረት ኢየሱስ ክርስቶስ ነው፡፡ (1ቆሮንቶስ 3፥8-11)

በመጀመሪያው ዐረፍተ ነገር፣ እግዚአብሔር ስለ ሽልማት ወይም ዋጋ ስለ መቀበል እየተናገረ መሆኑን ማስተዋል ተገቢ ነው፡፡ የ 1ቆሮንቶስን ምንባብ ሰፋ አድርገን በምናይበት ጊዜ ይህን በአእምሮአችሁ ያዙ፡፡

ጳውሎስ መሠረቱን ጣለ፡፡ ከሁለት ሺህ ዓመታት በፊት የተጻፉ ቢሆኑም፣ በክርስቶስ እንዴት መኖር እንደሚገባን ለመረዳት ዛሬም መልእክቶቹን እንደ አስተማማኝ መሠረት እንጠቀምባቸዋለን፡፡ ፍሎሪዳ ያለውን ቤታችንን የሠሩ የመጀመሪያዎቹ ረዳት ሠራተኞች መሠረት አኑረዋል፡፡ እነርሱ መሠረቱን ከጣሉ በኃላ እዚያ ላይ የተቀሩት የሥራው ባለ ድርሻዎች የየበኩላቸውን ሥራ አኖሩ፡፡

ጳውሎስ በመቀጠል፣ ‹‹ማንም በዚህ መሠረት ላይ በወርቅ ወይም በብር፣ በከበረ ድንጋይ ወይም በዕንጨት፣ በሣር ወይም በአገዳ ቢያንጽ፣ ሥራው እንዴት እንደ ሆነ ይታያል›› ይላል (3፥12)፡፡ ወርቅ፣ ብርና የከበረ ድንጋይ ዘላማዊውን ያመለክታሉ፤ እንጨት፣ ሣርና አገዳ ግን ጊዜያዊውን ያመለክታሉ፡፡ በእያንዳንዱ የሕይወታችን ቅጽበት ለዘላለማዊው ወይም ለጊዜዊው ዓለም የማነጽ ወይም የመሥራት ምርጫ አለን፡፡ ዓላማችን ገንዘብ ማግኘት ከሆነ፣ ታዋቂ ወይም ተወዳጅ መሆን ከሆነ፣ ሰዎችን የምንረዳው ለግል ጥቅማችን ከሆነ፣ እንዲሳካልን ወይም እንዲከናወንልን የምንፈልገው ምን ያህል ጉበዝ መሆናችንን ለማሳየት ከሆነ፣ እያነጽን ወይም እየሠራን ያለነው ለጊዜያዊው ነው፡፡ ይሁን እንጂ፣ ችግር ላይ ላሉት የእግዚአብሔርን ዘላለማዊ ቃልና ልግስና በማምጣት ትኩረታችን የእግዚአብሔርን መንግሥት ማነጽ ወይም መሥራት ላይ ከሆነ ለዘላለሙ እየሠራን ነው፡፡

በመቀጠል ጳውሎስ፣ ‹‹ሥራው እንዴት እንደ ሆነ ይታያል፤ ምክንያቱም ያ ቀን ወደ ብርሃን ያመጣዋል፡፡ በእሳት ስለሚገለጥ እሳቱ የእያንዳንዱን ሰው ሥራ ምንነት ይፈትናል›› ይላል (3፥13)፡፡

ሥራችን በእሳት ይፈተናል፤ ሥራችን ብቻ ሳይሆን ከሥራችን በስተ ጀርባ ያለው ዓላማችን ምንነትም ይፈተናል (1ቆሮንቶስ 4፥5 ይመ)፡፡ እንጨት፣ ሣርና አገዳን እሳት ቢነካቸው ያቃጥላቸዋል፡፡ ያው እሳት ወርቅን፣ ብርን ወይም የከበረ ድንጋይን ቢነካቸው የበለጠ ያጠራቸዋል፤ የበለጠ

ያሳምራቸዋል እንጂ አቃጥሎ አያጠፋቸውም፡፡ በመጨረሻው የክፍያ ቀን፣ ‹‹ማንም የገነባው ሥራ ቢጸናለት ሽልማቱን ይቀበላል፤ ሥራው የተቃጠለበት ግን ሽልማት ይቀርብለታል፤ እርሱ ራሱ ግን ይድናል፤ ይሁን እንጂ፣ የሚድነው በእሳት ውስጥ በጭንቅ እንደሚያልፍ ሆኖ ነው›› (3፥14-15)፡፡

እንደ ግንበኛ የተሰጣችሁን ሥራ በመልካም ከጨረሳችሁ ሽልማት እንደምታገኙ ልብ አድርጉ! ሆኖም፣ ከእግዚአብሔር ቃል ጋር የማይጣጣም ሥራ ብትሠሩ - ዓላማችሁ ራስ ወዳድነት፣ አለመታዘዝና ትዕቢትን መሠረት ያደረገ ከሆነ - ሥራችሁ ይቃጠልባችኋል፡፡ በክርስቶስ እንደሚያምኑ ሰዎች መንግሥተ ሰማይ ትገባላችሁ፤ ዘለቄታ ላለው ሥራ የሚሰጥ ሽልማት ግን አይኖራችሁም፡፡ ለሁላችንም ጠንከር ያለ ማስጠንቀቂያ ነው!

ይህን ታላቅ ምንባብ እየመረመረን እያለ፣ አንድ ማስታወስ ያለባችሁ ነገር፣ ጳውሎስ እየተናገረ ያለው ስለ ግለ ሰብ ሳይሆን ስለ መላው ቤተ ክርስቲያን መሆኑን ነው፡፡

> እናንተ ራሳችሁ የእግዚአብሔር ቤተ መቅደስ እንደ ሆናችሁ፣ የእግዚአብሔርም መንፈስ በውስጣችሁ እንደሚኖር አታውቁምን? ማንም የእግዚአብሔርን ቤተ መቅደስ ቢያፈርስ እግዚአብሔር እርሱን ያፈርሰዋል፤ የእግዚአብሔር ቤተ መቅደስ ቅዱስ ነውና፤ ያም ቤተ መቅደስ እናንተ ናችሁ፡፡ (3፥16-18)፡፡

አሁንም ጠንከር ያለ ቃል! የእግዚአብሔርን ቤት ወይም የክርስቶስ ሙሽራ የሆነችው ቤተ ክርስቲያን ላይ በደል የሚፈጽምና ወደ ስሕተት የሚመራ ማንኛውም ሰው ልብ ውስጥ ይህ ቅዱስ ፍርሃት ማምጣት አለበት፡፡ ሌላው ቀርቶ የእግዚአብሔር ቤት በጣም ትንሽ የተባለ፣ ‹‹ሸክላ›› ላይ ወይም፣ ‹‹ከቅዱሳን ሁሉ ያነሰ›› የሚባለው ላይ እንኳ በደል መፈጸምን አስመልክቶ የተሰጠውን ይህን ጠንከር ያለ ማስጠንቀቂያ ልብ አድርጉ፡፡

## የሠራተኛው ዋጋ

ጳውሎስ፣ ‹‹ማንም ራሱን አያታልል›› በማለት ነው የሚደመድመው (3፥18)፡፡ በጣም የሚያሳዝነው አንዳንድ ክርስቲያኖች በመልካም የማይፈጽሙት፣ የራሳቸውን መከተል ሲፈልጉ ከመንገድ በመውጣታቸው ነው፡፡ ለክብሩ የሚሆነውን የእግዚአብሔርን ቤት ሥራ በመተው ጠፊ ወደ ሆነው ክብር፣ የሰዎችን ጊዜያዊ ይሁንታ ወደ መፈለግ ወይም አንድ ቀን ተቃጥሎ የሚጠፋውን የዚህ ዓለምን ሀብት ወደ ማሳደድ ዘወር ብለዋል፡፡

አትሳሳቱ! ከትኩረታችሁ አትዘናጉ! በክርስቶስ ተልዕኮ አላችሁ፡፡ የምትሠሩት ሥራ መጀመሪያውኑ እግዚአብሔር ባቀደለት መልኩ መጠናቀቅ አለበት፤ እንደዚያ ካልሆነ እናንተ እንድትሠሩ ታቅዶ የነበረውን ሌላው ይሠራዋል፡፡ ቀጥሎ ያለው ጥቅስ ይህን ወሳኝ ነጥብ ያመለክታል፡፡

> ከእግዚአብሔር በተሰጠኝ ጸጋ መጠን እንደ አንድ ብልኅ ግንበኛ መሠረትን ጣልሁ፤ ሌላውም በላዩ ላይ ይገነባል፤ ነገር ግን እያንዳንዱ እንዴት እንደሚገነባ መጠንቀቅ አለበት፡፡ ምክንያቱም አንድ ጊዜ ከተመሠረተው መሠረት በቀር ሌላ መሠረት መጣል የሚችል ማንም የለም፤ ይህም መሠረት ኢየሱስ ክርስቶስ ነው፡፡ ማንም በዚህ መሠረት ላይ በወርቅ ወይም በብር፣ በከበረ ድንጋይ ወይም በዕንጨት፣ በሣር ወይም በአገዳ ቢያንጽ፣ ሥራው እንዴት እንደ ሆነ ይታያል፤ ምክንያቱም ያ ቀን ወደ ብርሃን ያመጣዋል፡፡ በእሳት ስለሚገለጥ እሳቱ የእያንዳንዱን ሰው ሥራ ምንነት ይፈትናል፡፡ ማንም የገነባው ሥራ ቢጸናለት ሽልማቱን ይቀበላል፤ ሥራው የተቃጠለበት ግን ሽልማት ይቀርበታል፤ እርሱ ራሱ ግን ይድናል፤ ይሁን እንጂ፣ የሚድነው በእሳት ውስጥ በጭንቅ እንደሚያልፍ ሆኖ ነው፡፡ (1ቆሮንቶስ 3፥10-15)

የሠራነው ነገር በእግዚአብሔር ምርመራ መስፈርት ማለፍ ካልቻለ፣ ሥራው፣ ይቃጠልብናል፡፡ ማንኛውም ሰው ሥራው በተለይም ደግሞ ለአጽናፈ ዓለሙ ፈጣሪ የሠራው ሥራ እንዲቃጠልበት አይፈልግም!

ቤታችን እየተገነባ በነበረ ጊዜ ጥሩ ሥራ ያልሠራ አንድ ተቋራጭ ላይ የሆነው ትዝ ይለኛል፡፡ ሰውየው ሮበርት ባሳየው ፕላን መሠረት የተሰጠውን የሥራ ድርሻ አልሠራም ነበር፡፡ እኔና ሊዛ በየቀኑ ቤቱ እየተሠራ ወደ ነበረበት ቦታ እንሄድ ስለ ነበር፣ ችግሩን ለማየት የመጀመሪያዎቹ ነበርን፡፡ ዋናው የሥራ መሪውን ሮበርትን ጠርተን ችግሩን ስናሳየው በጣም ተቆጣ፡፡ ያ ሥራውን ያበላሸው ሰው መደበኛ ሠራተኛው ስላልነበር ወዲያውኑ ነበር ከሥራ ያስወጣው፡፡ ሰውየው ቤቱ አልቆ የማየት ሽልማቱን አጣ፡፡ ለሥራው ይገባው የነበረውን ክፍያ ብቻ ሳይሆን፣ በዚያ ያማረ የቤት ሥራ ተሳትፎ ባደረጉ ሰዎች መካከል የመቆጠር ዕድልንም አጥቷል፡፡

ዓይናችን እያየ ነበር ሮበርት የዚያን ሰው ሥራ ያፈረሰው፡፡ ከዚያ በኋላም፣ ልክ እርሱ ፕላኑ ላይ እንዳስቀመጠው አድርጎ ሊሠራለት የሚችል ሌላ ሠራተኛ ቀጠረ፡፡ ያ ሰው የሚገባውን ክፍያም ሆነ፣ ለዚያ ያማረ ቤት ቀና አስተዋፅዖ ማድረጉን የማወቅ ርካታም አገኘ፡፡

የእግዚአብሔርን ቤት መገንባትን በተመለከተም ይህ መርሖ እንደሚሠራ ቅዱሳት መጻሕፍት ይነግሩናል፡፡ ሥራቸው ተቀባይነት የማያገኝላቸው ሰዎች ይኖራሉ፡፡ የእነዚህ ወገኖች ሥራ ይፈርሳል፤ የዘላላማዊው ቤት አካልም አይሆንም፡፡

ይህን በሚገባ ለማየት እንዲስችላችሁ እስቲ አንድ ምሳሌ ላቅርብ፡፡ በየቀኑ ቤቱ እየተሠራ ወደ ነበረበት ቦታ እሄድ ስለ ነበር በተለያየ የሥራ ምድብ ተሰማርተው የነበሩ ሰዎች አውቀውኝ ነበር፤ ‹‹ሰባኪው›› እያሉ ነበር የሚጠሩኝ፡፡ ቤቱ እየተሠራ ወደ ነበረበት ቦታ ስሄድ፣ የአሲድ ሮክ ሙዚቃቸው ጩኸት ገና ከሩቅ ነበር የሚሰማኝ፡፡ እኔ መምጣቴን ሲያዩ ከመካከላቸው አንዱ ቶሎ ሮጥ ይልና የሙዚቃ ማጫወቻውን ይዘጋው ነበር፡፡ እኔም፣ ሌላው ቢቀር እንደ የእግዚአብሔር ሰው ማክበራቸው ፈገግ ያሰኘኝ ነበር፡፡ ከዚያ ከእነርሱ ጋር ጥቂት አወራለሁ፡፡ በጣም ከመቀራረባችን የተነሣ ከአንዳንዶቹ ጋር ስለ ትልልቅ ጉዳዮች እንኳ እንነጋገር ነበር፤ አንዳንዶቹንም በወንጌል የማገልገል ዕድል አግኝቼ ነበር፡፡

በጣም በሚያማምሩ ሕንፃ ሥራዎች ስለ ነበራቸው ድርሻ ነግረውኝ እንደ ነበረም አስታውሳለሁ፡፡ በእንዲህ ያሉ ታላላቅ ሥራዎች ስላደረጉት አስተዋፅዖ ሲናገሩ ፊታቸው ይፈካል፡፡ በእነዚህ ታላላቅ ሥራዎች መሳተፍ በመቻላቸው ያገኙትን ርካታ ማየትም ትችላላችሁ፡፡

እስቲ ይህን አንድ ርምጃ ወደ ፊት እንውሰደው፡፡ በዋሽንግተን ባለው ኃይት ሐውስ ቤተ መንግሥት ግንባታ የሥራ ድርሻ የነበራቸው ሰዎች ምን ሊሰማቸው እንደሚችል ማሰብ ትችላላችሁ? በተለያየ ምክንያት ወደ ተለያዩ የአገሪቱ ክፍሎች ሄደው የነበሩ ልጆቻቸው ወደ ቤት ሲመለሱ ስላዩዋቸው በጣም የሚያማምሩ ሕንፃዎች ሲነግሩዋቸው ማሰብ ሞከሩ፡፡ ታዲያ፣ በእነዚያ በጣም ባደነቋቸው ሕንፃዎች ግንባታ ስለ ነበረው ተሳትፎ አባት ለልጁ ሲናገር የሚሰማውን ደስታና ርካታ ማሰብ ትችላላችሁ? አባቱ በኃይት ሐውስ ሥራ ግንባታ ተሳትፎ አድርጎ የነበረ ልጅ፣ የአሜሪካ ፕሬዚዳንት የሚኖርበትን ባለ ግርማ ሞገስ ቤት ከሠሩ ሰዎች አንዱ የእገሌ አባት ናቸው ሲባል ሲሰማ ፊቱ ላይ የሚታየውን ኩራት ማሰብ ትችላላችሁ?

በእግዚአብሔር ቤት ሥራ እኛ ያለንን ድርሻ በተመለከተም ይኸው ነው! ሆኖም፣ እኛ የምንሠራው ቤት የሚፈርስ ወይም ከመቶ ዓመታት በኃላ በሌላ ሕንፃ የሚተካ አይደለም፡፡ ከዘላለም እስከ ዘላለም የመላው አጽናፈ ዓለምን ትኩረት የሚማርክ ይሆናል፡፡ እስቲ ነቢዩ ሚክያስ የሚለውን እንስማ፣

በመጨረሻው ዘመን የእግዚአብሔር ቤት መቅደስ ተራራ፣ ከተራሮች ልቆ ይታያል፤ ከኮረብቶች በላይ ከፍ ይላል፤ ሕዝቦችም ወደ እርሱ ይጐርፋሉ። ብዙ አሕዛብ መጥተው እንዲህ ይላሉ - ኑ ወደ እግዚአብሔር ተራራ፣ ወደ ያዕቆብ አምላክ ቤት እንሂድ፣ በመንገዱ እንድንሄድ መንገዱን ያስተምረናል። (ሚክያስ 4፥1-2)

የመላው አጽናፈ ዓለም ትኩረት በዚህ ቤት ዙሪያ ያጠነጥናል። መላው ፍጥረትን የሚገዛ ጥበብና ሕግ ከዚህ ቤት አስተዳደር ይመነጫል። ምናልባትም እጅግ አስደናቂው ሐቅ፣ የእግዚአብሔር ቤት ማለትም ጽዮን ዐሥር ትሪሊዮን ዓመታት በኃላ እንኳ ሥራው መጀመሪያ የተጠናቀቀበትን ጊዜ ያህል ያማረና ውብ ሆኖ መዝለቁ ሊሆን ይችላል!

አንድ እስከ ፍጻሜው በታማኝነት የዘለቀ የወንጌል አገልጋይ ነበር። ውጤት ባለው ሁኔታ ከስድሳ ዓመት በላይ ካገለገለ በኃላ፣ ያለፈው ሚሊኒየም ማብቂያ ላይ ወደሚጠብቀው ሽልማት ገባ። ይህ ሰው ከሞተ አንድ ወይም ሁለት ዓመት በኃላ በማዕከላዊ ምዕራብ ወዳለ አንድ ቤተ ክርስቲያን ለአገልግሎት ሄጄ እያለ፣ የአምልኮ መሪው እግዚአብሔር ስለ ሰጠው አንድ ግልጽ ሕልም አጫውቶኝ ነበር። በዚያ ሕልም ወደ መንግሥተ ሰማይ ተወስዶ ነበር፤ ያንን በመልካም ሁኔታ የጨረሰ አገልጋይንም እዚያ ያየዋል። አገልጋዩ ምድራዊ ባልሆነ ፈገግታ ተሞልቶ፣ ‹‹እንዲያውም እኔ ካሰብኩት እጅግ በጣም የበለጠ ነው›› በማለት ለአምልኮ መሪው ይነግረዋል። ጥቂት ደቂቃዎች ከተነጋገሩ በኃላ አገልጋዩ ዘወር ብሎ እርሱ ተሳትፎ አድርጎ የነበረበትን የእግዚአብሔር ቤት ሥራ ያሳየዋል። እጅግ ሰፊና ድንቅ ነበር። እርሱ ምድር ላይ ሆኖ ያስብ ከነበረው ይበልጥ የዚያ ሰው ታማኝት እጅግ ሰፊ ተፅዕኖ ማሳደር ችሎ ነበረ፤ የሥራው ውጤትም እፊቱ ነበር። ልክ እነዚያ ሥራ ተቋራጮች ተሳትፎ ስላደረጉበት ቤት ሥራ እንደ ነገሩኝ ሁሉ፣ እርሱም ሥራውን ማሳየት ችሎ ነበር። ምንኛ ድንቅ ሽልማት! ምንኛ ድንቅ ዋጋ!

> እኛ የምንሠራው ቤት... ከዘላለም እስከ ዘላለም የመላው አጽናፈ ዓለምን ትኩረት የሚማርክ ይሆናል።

እናንተ ተሳትፎ ያደረጋችሁበትን የእግዚአብሔር ቤት ሥራ ውጤት ለማየት ለሚመጡ ልጆቻችሁና የልጅ ልጅ ልጆቻችሁ፣ እንዲሁም እጅግ ብዛት ላላቸው ሕዝቦች ከዘላለም እስከ ዘላለም ማሳየት ስትችሉ ምን ሊሰማችሁ እንደሚችል ማሰብ ትችላላችሁ?

ያን ማሰብ ራሱ ክቡር ነው! የሚጠብቀን ምንኛ ክቡር ዋጋ ያለው ነው! ታዲያ፣ በሚገባ ለመጨረስ ምን ያህል ተነሳሽነት ይጠበቅብን ይሆን!

አሁን ደግሞ ሌላውን ገጽታ እናስብ፡፡ የጀመራችሁትን በሚገባ ባለ መጨረሳችሁ ጽዮን በሚባለው ቤት ግንባታ ሥራ ድርሻ እንደሌላችሁ ሲነገራችሁ የሚሰማችሁን ማሰብ ትችላላችሁ? ልጆቻችሁና ሌሎች ትውልዶቻችሁ የሠራችሁትን ለማየት ሲመጡ፣ የእናንተ የሥራ ድርሻ በመፍረሱና ለሌላ ታማኝ ሰው በመሰጠቱ፣ ለዘላለም የምታሳየት ሳይኖራችሁ ሲቀር የሚሰማችሁን ማሰብ ትችላላችሁ? ልክ 1ቆሮንቶስ 3 ላይ ጳውሎስ እንደ ተናገረው ምንኛ ከባድ ኪሣራ ነው!

የተከበራችሁ ወዳጆቼ፣ እናንተን በተመለከተ ያ እንዲሆን አልፈልግም፡፡ እግዚአብሔር ለእናንተ ያለው ዓላማ ያ አይደለም፡፡ በጣም የሚያሳዝነው ግን ብዙ አማኞችን በተመለከተ እንደዚያ መሆኑ ነው፡፡ ይሁን እንጂ፣ ከእነዚያ አንዱ እንዳትሆኑ አሁኑኑ መወሰን ትችላላችሁ፡፡ ዮሐንስ የሚሰጠንን ምክር በጥንቃቄ አድምጡ፤ እናንተም የደከማችሁበትን ዋጋ እንዳታጡ፣ ነገር ግን ሙሉ ሽልማት እንድትቀበሉ ለራሳችሁ ተጠንቀቁ፡፡ (2 ዮሐንስ 8)

ዘላለማዊውን የእግዚአብሔር ሥራ በመገንባት ባደረጉት ተሳትፎ፣ ልጆቹ ሁሉ ሙሉ ዋጋ መቀበል የሚችሉበትን መንገድ እግዚአብሔር አዘጋጅቶአል፡፡ ድካማችሁ በፍጹም ዋጋ አያጣም፤ አያረጅም፤ በሌላ አይተካም፡፡ በቢሊዮን በሚቆጠሩ ሰዎችና በቅዱሳን መላእክት፣ ከዘላለም እስከ ዘላለም ሲደነቅ ይኖራል፡፡

ይህ በጽናትና በታማኝነት ጌታችንን በማገልገላችን የምንቀበለው የመጀመሪያው ሽልማት ወይም ዋጋ እንጂ የመጨረሻው አይደለም፤ ሌላ የበለጠ ይኖራል፡፡ ይህን በቀጣዩ ምዕራፍ እንመለከታለን፡፡

# 17

# ወደ ንጉሡ መቅረብ

*እናንተም የደከማችሁበትን ዋጋ እንዳታጡ፣ ነገር ግን ሙሉ ሽልማት እንድትቀበሉ ለራሳችሁ ተጠንቀቁ፡፡*

*2 ዮሐንስ 1፥8*

መከራና ችግር መምጣቱ የማይቀር ነው፡፡ ትክክለኛ ማበረታቻ በጽናት ሩጫችን እንድንሮጥ ይረዳናል፤ ተነሣሽነት የሌላቸው ግን ሊሰናከሉ፣ ምናልባትም ሩጫቸውን ሊያቋርጡ እንኳ ይችላሉ፡፡ በመልካም ሁኔታ ለመጨረስ ተነሣሽነት መኖሩ እጅግ ጠቃሚ ነው፡፡

የመጀመሪያው ሽልማት ሥራችሁ በእርሱ ዘንድ ተቀባይነት ማግኘቱን በማወቅ፣ በእግዚአብሔር ቤት ሥራ የነበራችሁን ተሳትፎ ለዘላለም የመመስከር ሽልማት ነው፡፡ ሁለተኛው ሽልማት በመጠኑ ግልጽ ሲሆን፣ ለዘላለም ከኢየሱስ ጋር የሚኖረንን ቀረቤታ ይመለከታል፡፡

## ከንጉሡ ጋር የጠበቀ ቀረቤታ

በዘመናት ውስጥ ባደረግሁ ጉዞ በዓለም ዙሪያ ካሉ አማኞች ጋር በነበረኝ ግንኙነት ምዕራባውያን ክርስቲያኖች እግዚአብሔርን የሚያስቡት እንደ አንድ ሶሻሊስት ይሆን ወይ? በማለት ራሴን ጠይቄ አውቃለሁ፡፡ እርሱ ሁሉንም ሰው ዕኩል እንደሚሸልምና በሰማይም ሆነ በምድር ሁሉም ተመሳሳይ ዓይነት ሥልጣን፣ ኃላፊነትና ክብር እንደሚኖራቸው ነው ብዙ አማኞች የሚገምቱት፡፡ ምንም እንኳ የእግዚአብሔር ማዳን ለሁሉም ዕኩል ቢሆንም፣ ድነት የሥራ አስተዋፅዖዋችንን መሠረት ያደረገ ባይሆንም - በምንታዘዝበት፣ በምንጸናበትና ለቃሉ እውነተኛ በሆንንበት መጠን፣ እግዚአብሔር ለታማኝነታችን ዋጋ ይሰጣል፤ ብዙዎች ግን ገና ይህን ሐቅ አልተረዱም፡፡

በመልካም ሁኔታ ከጨረስን የምንቀበለው ዋጋ ወይም ሽልማት፣ ባለፈው ምዕራፍ ከተመለከትነው እጅግ የሚበልጥ ለዘላለም ከኢየሱስ ጋር የሚኖረን ቀረቤታ ነው፡፡ በጣም ከምንወደውና ከምናከብረው ጋር የጠበቀ ቀረቤታ ከማድረግ የሚበልጥ ምንም ነገር የለም፡፡ መጽሐፍ ቅዱስ፣ ‹‹በጉ ወደሚሄድበት ሁሉ ይከተሉታል›› በማለት የሚናገርላቸው አሸናፊዎች ስለሚኖራቸው መብት ይናገራል (ራእይ 14፥4)፡፡ ወደሚሄድበት ሁሉ ለዘላለም ኢየሱስን መከተል እንዴት ትልቅ መታደል ነው!

ይህ እውነት በወንጌሎቹም ውስጥ በግልጽ ይታያል፡፡ በኢየሱስ ምድራዊ አገልግሎት ማብቂያ አካባቢ የሁለት ደቀመዛሙርቱ እናት የሆነች ሴት ወደ እርሱ መጥታ፣ ‹‹እነዚህ ሁለት ልጆቼ በመንግሥትህ አንዱ በቀኝህ፣ አንዱ በግራህ እንዲቀመጡ ፍቀድ›› በማለት ጠይቃው ነበር (ማቴዎስ 20፥21)፡፡

እርግጥ ነው፣ ከፍተኛው የክብር ስፍራ፣ እግዚአብሔር አብ አጠገብ የሚቀመጠው ኢየሱስ ጐን መሆን ነው፡፡ ከዚያ የሚበልጥ ቦታ የለም! መጽሐፍ ቅዱስ በጣም ወደ እግዚአብሔር ዙፋን ቀረብ ብለው ስለሚያገለግሉ ሱራፌል ስለሚባሉ ኃያላን መላእክት ይናገራል (ኢሳይያስ 6፥1-6 ይመለከቷል)፡፡ ‹‹ቅዱስ፣ ቅዱስ፣ ቅዱስ እግዚአብሔር!›› እያሉ ያለ ማቋረጥ አንዳቸው ለሌላው ጮኸው ይናገራሉ፡፡ ክርስቲያኖች ከእነርሱ የተወሰደውን ቃል ይዘምራሉ፡፡ ይሁን እንጂ፣ መላእክቱ የሚዘምሩት እግዚአብሔር ደስ ለማሰኘት አይደለም፡፡ ስላዩትና ስለ ተመለከቱት ሁሉ፣ ለእርሱ ምስጋና ለመስጠት ነው የሚዘምሩት! በእያንዳንዱ ቅጽበት ሌላ ተጨማሪ የታላቅነቱ ገጽታ ይታያል፤ እነርሱ ማድረግ የሚችሉት ደግሞ፣ ‹‹ቅዱስ!›› ማለት ብቻ ነው፡፡ እንዲያውም ድምፃቸውን ከፍ አድርገው በስሜት በመጮኻቸው በቢሊዮን የሚቆጠሩ መላእክትና ቅዱሳን የነበሩበት አዳራሽ መድረክ መሠረቱ ተናውጦአል፡፡

እነዚህ ኃያላን መላእክት ስላሉበት ቦታ ቅንጣት ቅር አይላቸውም፡፡ *‹‹ዐሥር ትርሊዮን ዓመታት ሙሉ እዚህ ነበርን፡፡ አሁን ግን ሰልችቶናል፡፡ እግዚአብሔር በእኛ ቦታ ሌሎች መላእክት ለመተካት ፈቃደኛ ቢሆንና እኛ ግን የተቀረውን የመንግሥተ ሰማይ ወይም የአጽናፈ ዓለሙ ክፍል መጐብኘት ብንችል ደስ ይለን ነበር›› በማለት አያስቡም፡፡*

በፍጹም! የሰማይ መላእክት ከዚያ ውጪ የትም መኖር አይፈልጉም፡፡ በእግዚአብሔር ፊት ከመሆን፣ ትልቅነቱን ከማየትና ጥበቡን ከመስማት የበለጠ በመላው አጽናፈ ዓለም አንድ ቦታ እንኳ የለም፡፡ ቀለል ባለ ቃል ለማስቀመጥ በፍጥረታት ሁሉ ውስጥ፣ የፈጣሪን ያህል እጅግ

የሚገርም የለም፡፡ ከእርሱ ዓይን ምንም የሚሰወር ነገር እንደሌለ ማስታወስ አለብን፤ ስለሆነም ወደ እርሱ በጣም ስንቀርብ ነገሮችን ከእርሱ ዕይታ አንጻር እናያለን፡፡ ምንም እንኳ በጣም ደካማ ምሳሌ ቢሆንም፣ አልበርት አይነስታይን፣ ኒል አርምስትሮንግና አይዛክ ኒውተን አጠገብ ተቀምጣችሁ በቴሌስኮፕ ሰማያትን ስትመለከቱ አስቡ፡፡ አቤት ምንኛ ጥልቅ መረዳት ታገኙ ይሆን! ነገሮችን ከእግዚአብሔር ዕይታ አንጻር ከማየት ጋር ሲነጻጸር፣ ይህ እጅግ ዝቅ ያለ ምሳሌ እንደ ሆነ አውቃለሁ፤ ይሁን እንጂ በጥቂቱም ቢሆን ሐሳቡን እንድትገነዘቡ ይረዳችኋል፡፡

አንድ እኔ የማውቀው አገልጋይ ወደ መንግሥተ ሰማይ ተወስዶ እንደ ነበር ይናገራል፡፡ እዚያ በነበረ ጊዜ ዙፋኑ ያለበት ክፍል ውስጥ ለመግባት እጅግ ከፍ ያለ ስሜት ይሰማዋል፡፡ መንግሥተ ሰማይ ያሉት ሁሉ ይህ ዐይነቱ ስሜት ነበራቸው - የሚቻለውን ያህል ሁሉም ወደ እግዚአብሔር መቅረብ ይፈልጉ ነበር፡፡ ያ ወዳጄ ሲናገር፣ እርሱ ከሚያስበው ማንኛውም ነገር ይልቅ መንግሥተ ሰማይ የበለጠ ውብ ነው፣ ይሁን እንጂ፣ መንግሥተ ሰማይ ውስጥ ከራሱ ከጌታ የበለጠ የሚናፈቅ ውብ ነገር አልነበረም፡፡

የያዕቆብና የዮሐንስ እናት ላቀረበችው ጥያቄ ኢየሱስ ሲመልስ፣ ‹‹በቀኜና በግራዬ መቀመጥ አባቴ ላዘጋጀላቸው ነው እንጂ፣ እኔ የምፈቅደው ነገር አይደለም›› ነበር ያለው (ማቴዎስ 20፥23)፡፡ እዚህ ላይ ለመሆኑ በመንግሥተ ሰማይ የክብር ቦታ የሚባል አለ? በማለት መጠየቅ እንችላለን፡፡ ወይስ፣ ከሞላ ጐደል ኢየሱስ፣ ‹‹እናንተ፣ የክብር ቦታ አትፈልጉ፡፡ እኔ ወይም አባቴ አጠገብ መሆን ለምን ታስባላችሁ? እናንተም ሆናችሁ ልጆቻችሁ ሕይወታችሁን ለእግዚአብሔር ክብር ኑሩ፡፡ አንድ ቀን እግዚአብሔር ለማንኛውም ክርስቲያን ዕኩል የክብር ቦታ ይሰጣል›› እያለ ይሆን?

ለዚህ ጥያቄ መልስ ለመስጠት እንዲቻል፣ የሚቀጥለውን ሕይወት በተመለከተ ለኢየሱስ ቀርቦ የነበረ አንድ ሌላ ጥያቄ ማየት ይኖርብናል፡፡ አንድ ቀን ነገረ መለኮታዊ ጥያቄዎችን በማቅረብ እርሱን ግራ ማጋባት የፈለጉ ሰዱቃውያን ወደ ኢየሱስ መጥተው ነበር፡፡ ‹‹ሰባት ወንድማማቾች ነበሩ፤ ታላቅ ወንድማቸው ሚስት ቢያገባም ልጅ ሳይወልድ ሞተ፡፡ ከዚያም ሁለተኛው ወንድም አገባት፤ ግን እርሱም ልጅ ሳይወልድ ሞተ፡፡ በዚህ መልኩ ሰባቱም ወንድማማቾች ሴትዮዋን አግብተዋት ነበር፡፡ ታዲያ፣ በትንሣኤ ቀን የማንኛቸው ሚስት እንደምትሆን መልስ እንድትሰጠን እንፈልጋለን›› አሉት፡፡

ኢየሱስ የሰጠው መልስ ለሁለቱ ደቀ መዛሙት እናት ከሰጠው መልስ የተለየ ነበር፡፡ ‹‹የዚህ ዓለም ልጆች ያገባሉ፤ ይጋባሉም›› አለ፡፡

የሚመጣውን ዓለምና የሙታንን ትንሣኤ ማግኘት የሚገባቸው ግን አያገቡም፤ አይጋቡም፤ እንደ መላእክትም ስለሆኑ ከዚያ በኃላ አይሞቱም፤ የትንሣኤ ልጆች ስለ ሆኑም የእግዚአብሔር ልጆች ናቸው፡፡ (ሉቃስ 20፥35-36)

ኢየሱስ የሰዱቃውያንን ስሕተት አስተካከለ፤ በመንግሥተ ሰማይ ጋብቻ እንደማይኖር ነገራቸው፡፡ ይሁን እንጂ፣ እርሷ የጠየቀችውን በተመለከተ የያዕቆብንና የዮሐንስን እናት ተሳስተሻል አላላትም፡፡ እንዲያውም በመንግሥተ ሰማይ የክብር ቦታ እንደሚኖርና ያም ቦታ እርሱ አጠገብ መሆን እንደ ሆነ ተናግሮአል፡፡ በፍርድ ቀን እግዚአብሔር ይህን ቦታ እንደ ሽልማት ወይም እንደ ዋጋ ይሰጣል፡፡ ሌሎች የቅዱሳት መጻሕፍት ክፍሎች ደግሞ ይህ የክብር ቦታ፣ በመልካም ሁኔታ ለጨረሱ ማለትም ጽናት ላላቸው አማኞች እንደ ሽልማት ወይም እንደ ዋጋ እንደሚሰጥ ያመለክታሉ፡፡

## የመጪዎቹ ነገሮች ጥላ

ይህ እውነት በትንቢተ ሕዝቅኤልም ተነግሯል፡፡ ምንም እንኳ፣ እዚህ ላይ የብሉይ ኪዳን ካህናት ቢጠቀሱም በታላቁ የጽዮን መቅደስ ማለትም በእግዚአብሔር ዘላለማዊ ቤት፣ ሕይወት ምን እንደሚመስል የሚያመለክት ትንቢታዊ ራእይ ሕዝቅኤል ያቀርባል፡፡

በነቢዩ ሕዝቅኤል በኩል እግዚአብሔር ለሌዋውያን - ለብሉይ ኪዳን ካህናት ይናገራል፡፡ ታዲያ፣ ይህ እኛን የሚመለከተው እንዴት ነው? ሐዋርያው ዮሐንስ እንዲህ በማለት ይነግረናል፡፡

> ለወደደንና ከኃጢአታችንም በደሙ ነጻ ላወጣን፣ አምላኩንና አባቱን እንድናገለግልም መንግሥትና ካህናት ላደረገን ለእርሱ ክብርና ኃይል ከዘላለም እስከ ዘላለም ይሁን! አሜን፡፡ (ራእይ 1፥5-6)

ካህናት ለሚለው ቃል አጽንዖት መስጠቴን እዩ፡፡ ከመንፈስ የተወለዱ ክርስቲያኖች ከዘላለም እስከ ዘላለም የአምላካችን ካህናት ናቸው፡፡ ቀጥሎ ያለውን የእግዚአብሔር ቃል ስሙ፤

> እስራኤል እኔን ከመከተል በራቁ ጊዜ፣ ከእኔ የራቁትና ጣዖቶቻቸውን በመከተል የቀቅበዝበዙት ሌዋውያን (ካህናት) የኃጢአታቸውን ዕዳ ይሸከማሉ፡፡ የቤተ መቅደሱ በር ኃላፊ በመሆንና በእርሱም ውስጥ በማገልገል መቅደሴን ሊያገለግሉ ይችላሉ፡፡ (ሕዝቅኤል 44፥10-11)

በዚህ ዘመን ያለ ጣዖት አምልኮ እነዚያ እስራኤላውያን በነበሩበት ዘመን እንደ ነበረው አይደለም፤ ይሁን እንጂ፣ እንደያኔው ሁሉ ዛሬም ጣዖት ማምለክ በእግዚአብሔር ፊት በጣም ጸያፍ ነው፡፡ ‹‹መጐምጀት አምልኮተ ጣዖት›› እንደ ሆነ ተነግሮናል (ቈላስዬስ 3፥5)፡፡ ለዚህ ሕይወት ነገሮች ከመጠን በላይ ስንጓጓና ስንጐመጅ አምልኮተ ጣዖት መፈጸማችን ነው፡፡ በዚህ ዘመን ላለን ለእኛ ጣዖት ማምለክ የደረጃ ዕድገት፣ ገንዘብ፣ ንብረት፣ ማንነት፣ ተወዳጅነት፣ ደስታ፣ ዝና ወይም ምቀኝነትንና የግል ፍላጐትን ማሳካትን የመሳሰሉ ሌሎች ነገሮች ሊሆኑ ይችላሉ፡፡ እግዚአብሔርን ከምንወደው ወይም ከምንፈልገው የበለጠ የምንወደውና የምንፈልገው ነገር ሁሉ ጣዖት ነው፡፡ ኃይልና ብርታታችንን የምንሰጠው ወይም ኃይልና ብርታቱን የሚሰጠን ነገር ሁሉ ጣዖት ነው፡፡

ጣዖት አምልኮ – ምግብ መብላትን በሚመስል ነገር እንኳ ሳይቀር በማንኛውም የሕይወት ገጽታ በተግባር ሊገለጥ ይችላል፡፡ ለምግብ የሚስገበገቡ በጣም ብዙ ክርስቲያኖች አሉ፡፡ ሀዘን ሲሰማቸው ይበላሉ፤ ደስ ሲላቸውም ይበላሉ፤ የምግብነት ይዘቱ ምንም ይሁን ምን፣ የሚጣፍጥ ከሆነ ማንኛውንም ነገር ይበላሉ፡፡ ለጊዜው ጣፋጭ በመሆኑ ብቻ በመጐምጀት ሰውነታቸው ጠቃሚ ባልሆነ ምግብ እንዲበከል ያደርጋሉ፡፡ እነዚህ ሰዎች ጥቅም ላይ የዋለ ዘይት ወይም የቆሸሸ ጋዝ መኪናቸው ውስጥ አይጨምሩም፤ ወደ ሰውነታቸው የሚገባ ምግብን ጥራትና መጠን በተመለከተ ግን ምንም ጥንቃቄ አያደርጉም፡፡ ምግብ ጣዖታቸው ሆኖአል፡፡ ኃይልና ብርታትን የሚያገኙት ከሚመገቡት ምግብ ጣዕምና ሙሉ ከሆነ ሆዳቸው ስሜት በመሆኑ ለዚያ ስሜት ብርታታቸውን ይሰጡታል፡፡

ጣዖት አምልኮ አንድ ሰው ታዋቂ ለመሆን በሚኖረው ፍላጐትም ውስጥ ይታያል፡፡ በቤተ ክርስቲያን፣ በመሥሪያ ቤታቸው ወይም በማኅበረ ሰባቸው ‹‹የክብር ቦታ›› ለማግኘት ሌሎች ላይ ማንኛውንም ነገር ከማድረግ ወደ ኃላ የማይሉ ሰዎች አሉ፡፡ ሥልጣንና ታዋቂነትን ለማግኘት ያማሉ፣ የሌሎችን ስም ያጠፋሉ፣ ያታልላሉ፣ ይዋሻሉ ወይም ታማኝነታቸውን ጥያቄ ውስጥ በሚጥል ሁኔታ ይንቀሳቀሳሉ፡፡ በእንዲህ ያሉ ወራዳ ተግባሮች ቀጥተኛ ተሳትፎ ባያደርጉ እንኳ፣ ከፍ ብሎ የመታየት ፍላጐታቸውን ጣዖት ያደርጉታል፡፡ ብርታታቸውን የሚያገኙት ከታዋቂነት፣ ከማንነት፣ ከዝና ሲሆን፣ ከዚህም የተነሣ ኃይላቸውን ለዚያ ነገር ይሰጣሉ፡፡

ጣዖት አምልኮ፣ ጽናትና ታማኝነታችሁን ይነጥቃችኃል፡፡ እስከ መጨረሻው ድረስ በታማኝነት እንዳትሮጡ ጉልበታችሁን ይሰርቃችኃል፡፡

ከላይ ከትንቢተ ሕዝቅኤል በተመለከትነው ምንባብ ዘላቂ ርካታ ለማይሰጡዋቸው ነገሮች ሲሉ እርሱን መፈለግ እርግፍ አድርገው ለተዉ አማኞች እግዚአብሔር ሲናገር እንመለከታለን፡፡ እነዚህ ጣዖቶች ለጊዜው ደስ ያሰኙን ይሆናል፤ ለዘለቄታ ሕይወታችን ግን ርካታ አይሰጡንም፡፡ ጣዖት የሚያመልኩ ሰዎች ለፈጸሙት በደል ሁሉ ዋጋ እንደሚከፍሉ እግዚአብሔር ይናገራል፡፡ ሽልማታቸው ወይም ዋጋቸው ሲቃጠል በማየት ዋጋ ይከፍላሉ፡፡ በመጨረሻ እነርሱ ይድናሉ፤ ሆኖም በጣም ተጐድተው ነው የሚድኑት፡፡ የቤተ ሰቡ አባሎች ናቸው፤ ሆኖም የሚኖሩት እንደ አገልጋዮች ዝቅተኛና ጥቃቅን የቤት ወስጥ ነገሮች በመሥራት ይሆናል፡፡

እዚህና አሁን ባለንበት ሁኔታ እግዚአብሔር ለእኛም እየተናገረ መሆኑን ማስታወስ አለብን፡፡ እርሱ ለእኛ ካለው ሙላት እኔና እናንተ ጐድለን እንድንገኝ አይፈልግም፡፡ መንግሥተ ሰማይ ማሰብ ከምንችለው ማንኛውም ነገር ይበልጣል፤ በምድር ያለ ማንኛውም ነገር ከውበቱ ጋር ሊወዳደር አይችልም፡፡ ይሁን እንጂ፣ መንግሥተ ሰማይ ውስጥ ደረጃ አለ - እጅግ ከፍ ያለ ክብርና ዝቅ ያለ ክብር ያለው ቦታ አለ፡፡ በእግዚአብሔር ቤት የሚኖረን ማንኛውም ቦታ በዚህ ምድር ካለ ማንኛውም ነገር ይበልጣል፤ ይህን አስመልክቶ ዳዊት፣ ‹‹በክፉዎች ድንኳን ከመቀመጥ ይልቅ በአምላኬ ቤት ደጅ መቆም እመርጣለሁ›› ብሏል (መዝሙር 84፥10)፡፡

ዳዊት፣ ‹‹የትኛውም ቦታ ከመሆን ይልቅ በእግዚአብሔር ቤት ውስጥ ተራ አገልጋይ መሆን ይሻለኛል›› እያለ ነው፡፡ መላው አጽናፈ ዓለም ውስጥ የእግዚአብሔርን ቤት ያህል፣ ሐልዎቱ እጅግ እውን የሆነበት መኖሪያውን ያህል፣ ምንም የሚያኅጓ ቦታ የለም፡፡ ጽዮን ውስጥ ያለ የትኛውም ቦታ፣ ከማንኛውም ነገር ወይም ከየትኛውም ቦታ ይሻላል፡፡

እዚህ ላይ እግዚአብሔር ግልጽ ማድረግ የፈለገው ነጥብ ሊያመልጠን አይገባም፡፡ በጣም ስለሚወደን ከተዘጋጀልን ምርጥ ነገር ጐድለን እንዳንገኝ ማለትም በእርሱ አጠገብ የመሆንን፣ ከእርሱ ጋር አብሮ የመሥራትን፣ ለዘላለም እግዚአብሔር ራሱን የማግኘት ሽልማት በማጣት ሊደርስብን ከሚችል ሐዘን እያስጠነቀቀን ነው፡፡ አማኝ ለፍርድ በሚቀርብበት ጊዜ እንባ ይኖራል፤ ይሁን እንጂ፣ እግዚአብሔር፣ ‹‹እንባን ሁሉ ከዐይናቸው ያብሳል›› ተብለናል (ራእይ 21፥4)፡፡ ለዘላለም ሕይወት ያዘጋጀንን አጭር የሕይወት ዘመናችንን አለ አግባብ የመጠቀማችን ግንዛቤ አብሮን ይኖራል፡፡ ዘላቂነት የሌለውን ነገር ስናሳድድ ያጣነውን ሁሌም እናስታውሰዋለን፡፡ ይህ ባለፈው ምዕራፍ በስፋት ስናገርለት የነበርው ዘላለማዊ ኪሣራ ነው (1ቆሮንቶስ 3፥12-15 ይመለከቷል)፡፡

በሌላ በኩል ደግሞ እግዚአብሔር እየተናገረ ያለውን ስሙ፤ ‹‹ነገር ግን እስራኤላውያን ከመንገዴ ስተው በወጡ ጊዜ፣ የመቅደሴን ሥራ በታማኝነት ያከናወኑ የሳዶቅ ዘርና ሌዋውያን የሆኑት በፊቴ ቀርበው ያገለግሉኛል›› (ሕዝቅኤል 44÷15)፡፡

ምንም እንኳ በዚህ ጥቅስ እግዚአብሔር እየተናገረ ያለው በተለይ ለብሉይ ኪዳን ካህናት ቢሆንም፣ እነዚህ፣ ‹‹ሊመጡ ላሉ ነገሮች ጥላ›› (ቆላስያስ 2÷17) መሆናቸውና ‹‹ይህ ሁሉ ምሳሌ ይሆን ዘንድ በእነርሱ ላይ›› (1ቆሮንቶስ 10÷11) መፈጸሙ ተነግሯል፡፡ በብዙ መልኩ የብሉይ ኪዳን ነገሮች ወደ ፊት የሚመጡ ነገሮች ጥላ፣ ምሳሌና አመልካች ናቸው፡፡ *ያገለግሉኛል* የሚለውን ቃል ልብ አድርጉ፡፡ ቤቱ ውስጥ አገልጋይ መሆንና ዳዊት ለማድረግ ፈቃደኛ እንደ ሆነው ወለል ማጽዳት አንድ ነገር ነው፡፡ እግዚአብሔርን ራሱን ማገልገል ግን ፍጹም ሌላ ነገር ነው፡፡

በ1983 ዓ.ም የሙሉ ጊዜ አገልግሎት በጀመርኩበት ዘመን 8000 አባሎች የነበሩት አንድ ቤተ ክርስቲያን አባል ነበርኩ፡፡ ቤተ ክርስቲያኑ በዚያ ከተማ ብቻ ሳይሆን፣ በዓለም አቀፍ ደረጃም ቢሆን የታወቀ ነበር፡፡ በአንድ ወቅት ወደ 450 የቢሮ ሠራተኞች ነበሩን፡፡ የፓስተሩና የሚስቱ ዋና ረዳት እንድሆን ተቀጥሬ ነበር፡፡ እነርሱን ማገልገል ለእኔ ትልቅ መታደል ነበር፡፡ ቢሮዬ እነርሱ ቢሮ ጐን ስለ ነበር፣ ብዙ ጊዜ እቤታቸው የመሄድና ታላላቅ የዓለማችን አገልጋዮች ጋር አብሬ ምሳ ወይም ራት ለመብላት በመቻሌ ሌሎች አባሎች ያላገኙት ዕድል ነበረኝ፡፡ ወደ እነዚህ ታላላቅ መሪዎች ቀረብ ብዬ መቀመጥ መቻሌን ሳስብ ራሴን እንደ ዕድለኛ እቆጥረው ነበር፡፡

ሌሎች አባሎች መስማት ያልቻሉዋቸውን የጥበብ ሐሳቦች የመስማት ዕድል ነበረኝ፡፡ እስከ ዛሬ ድረስ መመሪያ የሆኑኝ አመለካከቶችን ያገኘሁት በዚያ ዘመን ነበር፡፡ የነበረኝ ቦታ ቤተ ክርስቲያኑ ውስጥ ካሉ ሥራዎች ሁሉ ይልቅ ብዙዎች የሚጓጉለት ነበር፡፡ ብዙ የቢሮ ሠራተኞች፣ ‹‹አሁን ባለህበት ቦታ በማገልገልህ በጣም ታድለሃል›› በማለት ይነግሩኝ ነበር፡፡ አንዳንዶቹም፣ ‹‹ይህን ቦታ እንዴት አገኘህ? ምን ብታደርግ ነው ይህን ቦታ ያገኘኸው?›› በማለት ይጠይቁኝ ነበር፡፡ ሌሎች ደግሞ፣ አንድ ቀን ከዚያ ቦታ ብለቅ፣ የእኔን ቦታ የሚይዘው ማን ሊሆን እንደሚችል ብዙ ጊዜ ይነጋገሩ ነበር፡፡ ቦታው በዚያ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ በጣም ምርጥ የሚባል ቦታ ከመሆኑ የተነሣ ትክክል መሆናቸውን አውቃለሁ፡፡

ከእግዚአብሔር ጋር የዚህ ዓይነት ቀረቤታ ሊኖራቸው ስለሚችል ሰዎች አስባችሁ ታውቃላችሁ? በሚመጣው ዘመን በእግዚአብሔር ሐልዎት

ውስጥ የመኖርና ወደ እርሱ የመቅረብ ዕድል የሚጐናጸፉ፣ ተግባራቸውን በሚገባ የተወጡና እስከ ፍጻሜው በትዕግሥት የሮጡ ጽናት ያላቸው አማኞች ናቸው፡፡ እነዚህ ወገኖች በክብር ቦታ ይቀመጣሉ፡፡ ሕዝቅኤል 44፥28 ላይ፣ ‹‹ርስታቸውን በተመለከተ እኔ ርስታቸው እሆናለሁ›› በማለት እግዚአብሔር እንደ ተናገረው ይሆናል፡፡

ታዲያ ከዚህ የበለጠ ሽልማት ወይም ዋጋ ሊኖር ይችል ይሆን? ከእርሱ አጠገብ የሚሆኑት፣ ሐሳቡን የሚሰሙት፣ ራእይና መረዳት የሚቀበሉት፣ አመራርንና የወደ ፊቱን በማቀድ ከእርሱ ጋር አብረው የሚሠሩት፣ በትጋት ያገለግሉትና ከእርሱ ጋር በታማኝነት የጸኑት ይሆናሉ፡፡ ከእርሱ ጋር ተቀምጠን ለዘላለም እንገዛለን፡፡ ፊት ለፊት እናገለግለዋለን፡፡ ምንኛ ድንቅ ተስፋ ነው!

በድጋሚ የጳውሎስን ምክር ስሙ፣

ለውድድር የሚዘጋጅ ማንኛውም ሰው በሁሉም ነገር ራሱን ይገዛል፤ እነርሱ ዐላፊ ጠፊ የሆነውን አክሊል ለማግኘት ይደክማሉ፤ እኛ ግን ለዘላለም የማይጠፋውን አክሊል ለማግኘት እንደክማለን፡፡ (1ቆሮንቶስ 9፥25-26)፡፡

ፕሮፌሽናል ራጮች የተዘጋጁትን ዋንጫዎችና ሜዳሊያዎች ለማግኘት ከባድ ልምምድ ያድርጋሉ፤ ይሁን እንጂ እኛ ከምንሮጥለት ጋር ሲነጻጸሩ እነዚህ ነገሮች ከምንም አይቆጠሩም! ‹‹ሸክም የሚሆንብንን ሁሉ፣ በቀላሉም ተብትቦ የሚይዘንን ኃጢአት አስወግደን በፊታችን ያለውን ሩጫ በጽናት እንሩጥ›› የሚል ምክር የተሰጠን በዚህ ምክንያት ነው (ዕብራውያን 12፥1)፡፡ አንድ ዘመናዊ ትርጉም ይህንኑ ቃል፣ ‹‹ተዘጋጁ፣ ሩጫ ጀምሩ - በፍጹም አታቋርጡ!›› በማለት አብራርቶታል፡፡ በሌላ ቦታ ደግሞ፣ ‹‹ሽልማት እንደሚቀበል ሰው ሩጡ›› ይላል (1ቆሮንቶስ 9፥24)፡፡ አሁን - ስለሚጠብቀኝ ሽልማት በመስማቴ እነዚህ ቃሎች አሁን የበለጠ ፋይዳ አግኝተዋል? በማለት ራሳችሁን ጠይቁ፡፡

የምትሰጡት መልስ ምን ሊሆን እንደሚችል አስባለሁ፡፡

# 18

# ተስፋ አትቁረጡ!

*ነገር ግን እስከ መጨረሻ የሚጸና እርሱ ይድናል፡፡*

*ማቴዎስ 10፥22*

ማንም ወይም ምንም ተስፋ እንድትቆርጡ ወይም እንድታቋርጡ ሊያስገድዳችሁ አይችልም፤ ያንን መወሰን የምትችሉ እናንተ ብቻ ናችሁ፡፡

ስለሆነም፣ በፍጹም ተስፋ አትቁረጡ፤ በፍጹም አታቋርጡ፡፡

አሸናፊዎች ከሆንን በዚህ ሕይወትም ሆነ በሚመጣው ሕይወት የምናገኘው ሽልማት ወይም ዋጋ አሁን ከሚገጥመን መከራ ወይም ችግር እጅግ የበለጠ ነው፡፡ ኢየሱስ እንደ ተናገረው፣ ‹‹እስከ መጨረሻው የሚጸና እርሱ ይድናል፡፡››

አዳኛችን በዚህ በመጨረሻዎቹ ዘመኖች ስለሚሆን አሳዛኝ ነገር አስቀድሞ ተናግሮአል፡፡ ‹‹ብዙዎች ይሰናከላሉ (ተስፋ ይቆርጣሉ/ያቋርጣሉ›› አለ (ማቴዎስ 24፥10)፡፡ ይህን እየተናገረ እያለ እንኳ በጣም ሳያዝን አልቀረም፡፡ በጣም የወደዳቸው፣ እነርሱን ለማዳን ሕይወቱን የሰጠላቸው ሰዎች አንድ ደረጃ ላይ ተስፋ ይቆርጣሉ፤ ያቋርጣሉ፡፡

እንደ እውነቱ ከሆነ እንደዚያ መሆን አልነበረበትም፤ አሳዛኝ የሚያደርገውም ይኸው ነው፡፡ ከመከራው የሚያወጣንን ብቻ ሳይሆን፣ ወደ መከራው ወይም ወደ ችግሩ ከመግባታችን በፊት ከነበረው ይልቅ ብርቱዎች፣ አስተዋዮችና የበለጠ ታማኞች ሆነን መውጣት የሚያስችለንን ኃያል ጸጋ እግዚአብሔር ሰጥቶናል፡፡ ብዙዎች ተስፋ የሚቆርጡት ወይም የሚያቋርጡት ትክክለኛ ዕይታ ስለሌላቸው ነው፡፡ እንደሚገባ ባለ መታጠቃቸው ነው፡፡

ማቋረጥ የተለያዩ መልኮች አሉት፡፡ ብዙ ጊዜ ሥረ መሠረቱ ተመሳስሎ መኖርን መፈለግ ሲሆን፣ ይህ ደግሞ የጽናት ተቃራኒ ነው፡፡

መጀመሪያው ምዕራፍ ላይ የነገርኳችሁ በራእይ ያየሁት ሰው ከወጀቡ በተቃራኒ ይቀዝፍ ነበር፡፡ ከእግዚአብሔር ጋር መመላለስ፣ በመንግሥቱ መሠረት መኖር፣ ራሳችንን መለየት፣ ከዚህ ዓለም ሥርዓት በተቃራኒ መኖርንም ያካትታል፡፡

አጥብቀን የእግዚአብሔርን መንገድ (ጥበብ) መከተል አለብን፡፡ መመሳሰል ወይም ማመቻመች ጥሩ አማራጭ አይደለም፡፡

## ክርስቲያን መሆን አስቸጋሪ ሲሆን

በሰማዕትነት ከመገደሉ በፊት የመጨረሻው ቀን አስቸጋሪ እንደሚሆን ሐዋርያው ጳውሎስ አስቀድሞ አይቶ ነበር፡፡ ‹‹በመጨረሻው ቀን ክርስቲያን መሆን በጣም ከባድ ይሆናል›› በማለት ለጢሞቴዎስ ጽፎለት ነበር (2ጢሞቴዎስ 3፥1)፡፡ ጳውሎስ በአምስት የተለያዩ ጊዜዎች ሰላሣ ዘጠኝ ጊዜ ተገርፎአል፤ ሦስት ጊዜ በዱላ ተቀጥቅጧል፤ አንድ ጊዜ በድንጋይ ተደብድቧል፤ ለዓመታት ታሥሮአል፡፡ በሄደበት ሁሉ ጥላቻና ስደት ገጥሞታል፡፡ ያም ሆኖ ግን፣ ከእርሱ ዘመን ይልቅ ይህ የእኛ ዘመን ለእግዚአብሔር ለመኖር አስቸጋሪ እንደሚሆን ነበር በትንቢት ያመለከተው! ለመሆኑ፣ በሕይወቱ ይህን የሚያህል ከባድ መከራና ስቃይ ከደረሰበት በኋላ እንዴት እንዲህ ማለት ቻለ? በመቀጠል ጳውሎስ ለጢሞቴዎስ ሲጽፍ፣

> ሰዎች ራሳቸውን የሚወዱ ይሆናሉ፤ ገንዘብን የሚወዱ፣ ትምክሕተኞች፣ ትዕቢተኞች፣ ተሳዳቢዎች፣ ለወላጆቻቸው የማይታዘዙ፣ የማያመሰግኑ፣ ቅድስና የሌላቸው፣ ፍቅር የሌላቸው፣ ለዕርቅ የማይሸነፉ፣ ሐሜተኞች፣ ራሳቸውን የማይገዙ፣ ጨካኞች፣ መልካም የሆነውን የማይወዱ፣ ከዳተኞች፣ ችኩሎች በከንቱ ትዕቢት የተወጠሩ፣ ከእግዚአብሔር ይልቅ ተድላን የሚወዱ ይሆናሉና፡፡ (2ጢሞቴዎስ 3፥2-4)

ይህን ቃል መጀመሪያ ስናነብ፣ ‹‹ምን ማለት ፈልጎ ነው? ለመሆኑ፣ እነዚህ ባሕርያት ጳውሎስ ከነበረበት ይልቅ፣ ለእኛ ዘመን የተነገሩ ናቸው ማለት እንዴት ይቻላል?›› በማለት እንጠይቅ ይሆናል፡፡ እውነት ነው፣ እነዚህ ባሕርያት ጳውሎስ በነበረበት ማኅበረ ሰብም ውስጥ ነበሩ፡፡ በዚያም ዘመን ሰዎች ራሳቸውንና ገንዘብን ይወዱ ነበር፤ ቅድስና የሌላቸውና ይቅር ማለት የማያውቁ ነበሩ፤ ዝርዝሩ ውስጥ ያሉ ነገሮች ሁሉ እነርሱም ላይ ነበሩ፡፡ እንዲያውም በበዓለ ሃምሳ ቀን ጴጥሮስ፣ ‹‹ከዚህ ጠማማ ትውልድ ራሳችሁን አድኑ›› በማለት ተናግሮ ነበር (ሐዋርያት ሥራ 2፥40)፡፡

ታዲያ፣ ጳውሎስ የተናገረው በተለይ ለእኛ ዘመን ነው ማለት እንዴት ይቻላል? በታሪክ ውስጥ ከእግዚአብሔር ጋር መመላለስ በጣም አስቸጋሪ ስለሆነ ዘመን ሲናገር እነዚህ ባሕርያት ላይ ያነጣጠረው ለምንድነው? ቀጥሎ ከምናነበው ጥቅስ መልሱን እናገኛለን፤ ‹‹ሃይማኖታዊ መልክ አላቸው፤ ኃይሉን ግን ክደዋል›› (2ጢሞቴዎስ 3፥5)፡፡

ጳውሎስ እንደሚናገረው፣ ትልቁ ችግር የሚመጣው ‹‹አማኞች›› እውነትን ሲያመቻምቹ ነው፡፡ ከሌሎች የአዲስ ኪዳን ጸሐፊዎች ጋር በአንድነት በእኛ ዘመን፣ ‹‹ዳግም የተወለዱ ክርስቲያኖች›› በማለት ራሳቸውን ከሚጠሩት ብዙዎች በእግዚአብሔር ጸጋ ጸንተው እንደማይቆሙ ሐዋርያው ያስጠነቅቃል፡፡ በጸጋ የዳኑ መሆናቸውን ደጋግመው ይናገራሉ፤ ይሁን እንጂ፣ እንደ የእግዚአብሔር መንግሥት ጽኑ ጠረኞች ልዩ ሊያደርጋቸው የሚችለውን የጸጋውን ኃይል ችላ ይላሉ፡፡

መቅዘፊያቸውን የጣሉት እንዲህ ያሉት ናቸው፡፡ ፊታቸውን ወደ ላይ አቅንተው ይሆናል፤ ግን ከዚህ ዓለም ሥርዓት ወጀብ ጋር ቁልቁል ይወርዳሉ፡፡ ቀደም ብዬ በነገርኳችሁ ራእይ እንዳየሁት አብዛኞቹ ጀልባዎች የዚህ ዓይነት ሰዎች የሞሉባቸው ነበሩ፡፡ አንድ ዓይነት ዐቋም የያዙ ሰዎች መሆናቸው ደግሞ የመሳቱን ኃይል የበለጠ ጠንካራና አሳማኝ ያደርገዋል፡፡ የእነርሱ መሳት ብቻ ሳይሆን፣ ብዙዎችንም ያሳስታሉ፤ ብዙ ቅኖችን ያሰናክላሉ፡፡ ጳውሎስ እየተናገረ ያለው እንዲህ ስላለው አዳጋች ሁኔታ ነው፡፡

ወደ ኋላ ዘወር ብዬ ታሪክን ስመለከት የጥንት ቤተ ክርስቲያን ከባዱ ውጊያ ከሕግ አክራሪነት (Legalism) ጋር የተያያዘ እንደ ነበር እረዳለሁ፡፡ ይህም በእግዚአብሔር ጸጋ ከመታመን ይልቅ፣ እንድትድኑ ከተፈለገ ሕግን መጠበቅ አለባችሁ እያለ በማስተማር አዳዲስ ክርስቲያኖች ሕግ ሥር እንዲሆኑ ያደርጋል፡፡

አሁን ግን እኛ የተለየ ውጊያ ውስጥ ነን፡፡ በዚህ ዘመን ትልቁ ጦርነት የሚገጥመን ከሕግ የለሽነት (Lawlessness) ጋር እንደ ሆነ አምናለሁ፡፡ ሕግ የለሽነት የተለወጠ ሕይወት ባይኖርም፣ መዳን እንደሚቻል ይናገራል፡፡ ክርስቲያኖች ነን እያልን ከመዳናችን በፊት ከነበረው በፍጹም ያልተለወጠ ሕይወት እየኖርን ነው፤ ግን የአንድ ክለብ አባሎች ሆነናል፤ የክለባችንን ዓርማ ለብሰናል፤ የክለባችንን ቋንቋ እንናገራለን፤ ራእዩ ውስጥ የነበሩ ብዙ ሰዎች ያሉባቸው ጀልባዎች ቁልቁል ይወርዱ እንደ ነበር ሁሉ እኛም ከማዕበሉ ጋር ቁልቁል እየወረድን ነው፡፡ በእግዚአብሔር ባለን እምነትና ለእርሱ በመታዘዝ ጽኑዎች አይደለንም፡፡

በዚህ ዘመን ትልቁ ጦርነት የሚገጥመን ከሕግ የለሽነት (Lawlessness) ጋር እንደ ሆነ አምናለሁ፡፡

በመጨረሻው ቀን፣ ‹‹ክፋት ስለሚገን የብዙዎች ፍቅር ይቀዘቅዛል›› በማለት ኢየሱስ አስጠንቅቋል (ማቴዎስ 24፥12-13)፡፡ ግን'ኮ ኢየሱስ በዚህ ምድር በነበረበትም ጊዜ ኃጢአት ገንኖ ነበር፡፡ ታዲያ፣ የእኛን ዘመን የተለየ ያደረገው ምንድነው? በጣም አስደንጋጩ እውነት፣ ኢየሱስ የተናገረው ስለ ጠቅላላው ማኅበረ ሰብ ሳይሆን፣ የእርሱ ተከታዮች መሆናቸውን ስለሚናገሩ ሰዎች መሆኑ ነው፡፡ በዘመናችን ባሉ ክርስቲያኖች መካከል ኃጢአት እንደሚበዛ ነበር የተናገረው፡፡ እንደዚያ ባይሆን ኖሮማ ንግግሩን፣ ‹‹እስከ መጨረሻ የሚጸና ግን እርሱ ይድናል›› በማለት አይደመድምም ነበር፡፡ መቼም፣ ለአንድ የማያምን ሰው፣ ‹‹ሩጫህን ከጨረስህ ትድናለህ›› አትሉትም፤ ምክንያቱም፣ እርሱ ቀድሞውኑ ሩጫው ሜዳ ውስጥ አልነበረም፡፡ ይሁን እንጂ፣ ለአንድ በእምነት ውስጥ ላለ ሰው፣ ሩጫውን ለጀመረ ሰው እንደዚያ ብትሉት ትርጉም ይሰጣል፡፡

ኢየሱስ የተጠቀመበት ቁልፍ ቃል *ትዕግሥት* ወይም *ጽናት* የሚለው ነው፡፡ ትዕግሥት ወይም ጽናት ያስፈለገበት ምክንያት ተቃውሞና፣ ዐመፅ ስለሚኖር ወይም እውነትን ለመከተል አዳጋች ስለሚሆን ነው፡፡ በመልካም ሁኔታ ለመጨረስ መጽናት ይኖርብናል፡፡

## ጊዜው ደርሷል

እንግዲህ ከዚህ አንጻር ጳውሎስ ለጢሞቴዎስ ለጻፈው ሁለተኛ መልእክት የበለጠ ትኩረት መስጠት ይኖርብናል ማለት ነው፡፡ ስለ ችግሩ ከተናገረ በኃላ ጳውሎስ መፍትሔውንም ሲሰጥ፣ ‹‹ክፉዎችና አታላዮች ግን እየሳቱና እያሳቱ በክፋትም ላይ ክፋት እየጨመሩ ይሄዳሉ፡፡ አንተ ግን በተማርኸውና በተረዳኸው ጽና›› ይላል (2ጢሞቴዎስ 3፥13-14)፡፡

ይህ እንደ ወቅቱ ሁኔታ የሚለዋወጥ ጉዳይ አይደለም፤ አስተሳሰቦች ወይም ባሕሎች ሳያግዱት ሁሌም በዘመናት ውስጥ ጸንቶ የሚኖር ነው፡፡ ጳውሎስ ለተማሪው ለጢሞቴዎስ፣ ‹‹አንተ ግን በተማርኸውና በተረዳኸው ጽና›› ማለቱን አስተውሉ፡፡ ስለሆነም መፍትሔው እውነቱን በጽናት ወይም አጥብቆ መያዝ ነው፡፡

የዓለምን መንገድ እንድንከተል ማዕበል ወይም ቅስቀሳ ቢኖርም፣ ፍጻሜው ከእውነት መንገድ መሳት ነው፡፡ በዚህም ምክንያት ጳውሎስ እንዲህ ይላል፣

*ከሕፃንነትህ ጀምረህ፣* በክርስቶስ ኢየሱስ በማመን *መዳን የሚገኝበትን* ጥበብ *ሊሰጡህ የሚችሉትን ቅዱሳት መጻሕፍትን* ዐውቀሃል፡፡ ቅዱሳት *መጻሕፍት* ሁሉ የእግዚአብሔር *መንፈስ ያለባቸው* ናቸው፤ ለማስተማር፣ *ለመገሠጽ፣* ለማቅናት፣ በጽድቅም *መንገድ ለመምከር ይጠቅማሉ፤* ይኸውም የእግዚአብሔር ሰው *ለመልካም ሥራ* ሁሉ ብቁ ሆኖ እንዲገኝ *ነው፡፡* (2 ጢሞቴዎስ 3፥15-17)

በዚህ ምንባብ ውስጥ ላሉት ሁለት ቁልፍ *ቃሎች* አጽንዖት ሰጥቻለሁ – *ከሕፃንነትህ ጀምረህ* እና *ቅዱሳት መጻሕፍትን* ለሚሉት፡፡ ቅዱሳት *መጻሕፍት* ሁሉ እስትንፋሰ *መለኮት ያለባቸው* ናቸው፡፡ *ዘመንና* ባሕልን ተሻግሮ *የሚሄድ* የእርሱ እውነት ናቸው፡፡ ሕይወታችንን ሁሉ የምናሳርፍባቸው *መሠረቶች* ናቸው፤ በመንገዳችን ሁሉ እግዚአብሔርን ደስ ማሰኘት በምንችልበት ዕውቀትና *ኃይል ያስታጥቁናል፡፡*

2 ጢሞቴዎስ *ምዕራፍ* 3 *መጨረሻ* ላይ ሲደርስ *ጳውሎስ* ስለዚህ ጉዳይ *መጻፉን ያበቃ ሊመስለን ይችላል፡፡* ይሁን እንጂ፣ እስከ 1227 *ዓ.ም* ድረስ ቤት ክርስቲያን *መጽሐፍ* ቅዱስን በምዕራፎችና በቁጥሮች አልከፋፈለችም ነበር፡፡ *ጳውሎስ* ይህን በሚጽፍበት ጊዜ ሁለተኛ ጢሞቴዎስ በምዕራፎችና በቁጥች *ያልተከፋፈለ* አንድ ወጥ መልእክት (ደብዳቤ) ነበር፡፡ እንደ እውነቱ ከሆነም ሐሳቡን ገና አልቋጨም፡፡ ጀምሮት የነበረውን በሚቀጥለው መስመር እየቀጠለ ነው፤

> በእግዚአብሔር *ፊት፣* እንዲሁም በሕያዋንና *በሙታን* ሊፈርድ ባለው በክርስቶስ ኢየሱስ *ፊት፣ መገለጡንና መንግሥቱን* በማሰብ *ይህን* ዐደራ እልሃለሁ፤ *ቃሉን* ስበክ፤ ጊዜው ቢ*መችም* ባ*ይመችም* ዝግጁ ሁን፤ በ*ታላቅ* ትዕግሥትና በማስተማር አቅና፣ *ገሥጽ፣* አበረታታም፡፡ ምክንያቱም ሰዎች ትክክለኛ የሆነውን ትምህርት የማይቀበሉበት ጊዜ *ይመጣል፤* ከዚህ ይልቅ ለገዛ ምኞቶቻቸው የሚስማማውን፣ የሚያሳክክ ጆሮአቸው ሲሰማ የሚፈልገውን እንዲነግሯቸው በዙሪያቸው ብዙ አስተማሪዎችን ይሰበስባሉ፡፡ እውነትን ከመስማት ጆሮአቸውን *ይመልሳሉ፡፡* (2 ጢሞቴዎስ 4፥1-4)

‹‹በእግዚአብሔርና በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ *ፊት* ዐደራ እልሃለሁ፡፡›› *ጳውሎስ* ለተማሪው ከዚህ የበለጠ ጠንካራ ትእዛዝ መስጠት አይችልም፡፡ *ለመሆኑ፣* ዐደራው ምንድነው? የእግዚአብሔርን *ቃል* መስበክና ማስተማር ነው፡፡ ፍልስፍና፣ ዓለማዊ *የአመራር መርሖ፣* የብልጥግና ወይም ሀብታም የመሆን ጥበብን፣ የንግግር ወይም ሰዎችን የማሳመን ወይም ለዘመኑ

የሚመቹ ሌሎች ነገሮችን ማስተማር አይደለም፡፡ ዐደራው ዘመን ተሻጋሪ ቅዱሳት መጻሕፍትን ማስተማር ነው፡፡

ቅዱሳት መጻሕፍት ሁሉ እስትንፋሰ መለኮት ያለባቸው እንደ ሆኑና ሕይወታችንን ለመምራት ጠቃሚ መሆናቸውን ጳውሎስ አስረግጦ ተናግሮአል፡፡ ከዚያም ይህንኑ እንዲሰብክና እንዲያስተምር ለጢሞቴዎስ ዐደራ ይለዋል፡፡ ለምን? ምክንያቱም፣ እየሳቱና እያሳቱ በመሄድ ያሉት ሰዎች እውነተኛውን ትምህርት (አስተምህሮ) የማይቀበሉበት ዘመን ይመጣል (ያ ጊዜ ይህ የእኛ ዘመን እንደ ሆነ አምናለሁ)፡፡ ትምህርቱ ወይም አስተምህሮው ምንድነው? እንደ እውነቱ ከሆነ ትምህርት ብቻ አይደለም፤ ይልቁንም መሠረታዊ ወይም የቅዱሳት መጻሕፍት የጀርባ አጥንት የሆነ ትምህርት ወይም አስተምህሮ ነው፡፡ ሁሉንም ነገር አገጣጥሞ የሚይዝ ትምህርት ነው፡፡

በጣም የሚያሳዝነው ግን፣ መንፈሳዊ (መጽሐፍ ቅዱሳዊ) መሠረታችን የዘመኑን አዝማሚያ ለማስተናገድ ቦታ እየለቀቀ እየሄደ መሆኑን ነው የማየው፡፡ የአንድ ትልቅ ቤተ ክርስቲያን አገልጋይ ማኅበረ ምዕመናኑ ፊት ቆሞ፣ ግብረ ሰዶማዊ መሆኑን ሲናገር ጉባኤው ቆሞ አድናቆቱን በጭብጨባ የሚገልጽበት ዘመን ላይ በመሆናችን ነገሩ ከቁጥጥር ውጪ ሆኖአል ማለት ይቻላል፡፡ ሌላው ደግሞ ይነሣና በዚህ ዘመን እግዚአብሔር አይፈውስም ሲል፣ ጉባኤው ከእግዚአብሔር ቃል ይልቅ እርሱን ያምናል፡፡ ሌላው ደግሞ ይነሣና የኃላ ኃላ ሰው ሁሉ ይድናል፤ ማንም ሰው ገሃነም ውስጥ አይጣልም የሚል ሐሳብ ያለበት መጽሐፍ ይጽፋል፤ ታላቅ ክርስቲያን መሪ ተደርጎም ይቆጠራል፡፡ ሌላው የድንግልን ልጅ መወለድና የኢየሱስ ክርስቶስን ዳግም መመለስ በተመለከተ ጥያቄ እንዳለው ቢናገርም፣ እንደ ታላቅ የክርስትና እምነት መሪ ይከበራል፡፡ ይህን የመሳሰሉ አሳዛኝ ነገሮች በ ‹‹ክርስቲያኖች›› መካከል በየዕለቱ ይሰማሉ፡፡

ምናልባትም በቅርቡ የተደረገ አንድ ጥናት ችግሩን ለመረዳት ያግዘን ይሆናል፡፡ አንድ ብሔራዊ ጥናት እንዳመለከተው፣ ‹‹ዳግም ከተወለዱ ክርስቲያኖች›› ውስጥ ፍጹማዊ ግብረ ገባዊ እውነት (absolute moral truth) መኖሩን የሚያምኑ 46 እጅ ብቻ ሆነው ተገኝተዋል፡፡ ‹‹ወንጌል አማኝ ክርስቲያኖች›› ከሚባሉት መካከል 50 እጅ ከኢየሱስ ክርስቶስ ውጪ በሌሎች መንገዶች ሰዎች መንግሥተ ሰማይ መግባት እንደሚችሉ ያምናሉ፡፡ ‹‹ዳግም ከተወለዱ ክርስቲያኖች›› መካከል ሰይጣን በእውን ያለ ኃይል መሆኑን የሚያምኑ 40 እጅ ብቻ ናቸው፡፡[1]

1. www.barna.org/transformation-article/252-barna-survey-examines-changes-in worldview-among-Christians-over-the-past-13-years

ይህ እንዴት ሊሆን ቻለ? መልሱን፣ ‹‹ትክክለኛ የሆነውን ትምህርት (አስተምህሮ) የማይቀበሉበት ጊዜ›› ይመጣል ከሚለው ጳውሎስ ለጢሞቴዎስ ከተናገረው ቃል ማግኘት ይቻላል፡፡ - በእውነት ጸንተን አልቆምንም፡፡

ብዙውን ጊዜ የምንሰማውና እኛ ራሳችንም ብንሆን የምናስተምረው አንዳች ለውጥ የማያመጣ ወንጌልን ነው፡፡ የዚህ መልእክት አንኳር ሐሳብ፣ ለእግዚአብሔር ቃል መሠረታዊ አስተምህሮ ታማኝ አለመሆን ነው፡፡ አሁን በቅርቡ የመጣ ተወዳጅ ትምህርት ደግሞ በኃጢአት ንስሐ ማድረግ እንደማይገባ የሚያስተምር ነው፡፡ ኃጢአት በእግዚአብሔር ጸጋ ስለ ተሸፈነ ከእንግዲህ በኃጢአት መጸጸት ወይም ንስሐ መግባት አስፈላጊ እንዳልሆነ በስሜት ለአያሌ አማኞች ይነገራቸዋል፡፡ ይህን ትምህርት የተቀበሉ ወንዶችና ሴቶች መልእክቱ ምን ያህል ቀላል፣ ትኩስና ነጻ የሚያወጣ መሆኑን በኩራት ሲናገሩ ሰምቼ አውቃለሁ፡፡ ቀላል፣ ትኩስና ነጻ የሚያወጣ መሆን እውነተኝነትን የሚያመለክት ከሆነ፣ ማንኛውም የሥጋን ምኞት የሚያነሣሣ ትምህርት ሁሉ እውነት ነው ማለት ነው! ክርስቲያኖች ንስሐ ማድረግ የለባቸውም የተባለው ትክክለኛ ትምህርት ከሆነ፣ በዮሐንስ ራእይ ውስጥ ከሰባቱ አብያተ ክርስቲያናት ለአምስቱ ‹‹ንስሐ ግባ›› እያለ በመናገሩ ኢየሱስ ክርስቶስ ተሳስቶአል ማለት ነው (ራእይ 2፥5፣16፤21፣22፤3፥3፣19 ይመለከቷል)፡፡

ኃጢአት ማድረግ ለሚፈልጉ ሰዎች እንዲመች ተብሎ እውነት አይሸቃቀጥም፡፡ ከሰዎች ፍላጎት፣ ምቾትና ‹‹ፖለቲካዊ ትክክለኝነት›› ጋር እንዲጣጣም ተብሎ እውነት ማፈግፈግ የለበትም፡፡ በተቃራኒው ግን የእግዚአብሔር ልጅ፣ ‹‹ወደ ሕይወት የሚያደርሰው መንገድ አስቸጋሪ ነው›› በማለት ይናገራል (ማቴዎስ 7፥14)፡፡

በአሁኑ ጊዜ ከትክክለኛው አስተምህሮ ያፈነገጡ መምህራንን ለራሳችን አሰባስበናል፡፡ እነዚህ ብልጣብልጥ ሰዎች የባሕላችንን ሞራላዊ ዝቅጠት የሚያስተናግድ ወንጌል አምጥተዋል፡፡ በዚህ ዘመን እውነት የአማኞችን ሕይወት ሲቀርጽ አይታይም፤ ይልቁንም በባሕሉ አካሄድ መሠረት እውነቱ ራሱ ይቀረጻል በዚያም መሠረት ይተረጐማል፡፡ ለምን? ምክንያቱም፣ ‹‹ከመካከላቸው ውጡ፤ ለእኔም የተለያችሁ ሁኑ›› ከሚለው ይልቅ ከዓለም ጋር ተወዳጅተን እንድንኖር የሚናገሩ ቃሎችን መስማት ፈልገናል (2ቆሮንቶስ 6፥17)፡፡

እውነትን ማመቻመች በጀመሩ ጊዜ መጀመሪያ ላይ ብዙ ክርስቲያኖች መንፈስ ቅዱስ ደስ አለመሰኘቱ ተሰምቷቸው ነበር፡፡ ይሁን እንጂ፣ ስፍር ቁጥር የሌላቸው ብዙዎች፣ በትላልቅ ጀልባዎች ከወጀቡ ጋር

እየነፈሱ ያሉት፣ የኃላ ኃላ መንፈስ ቅዱስን ያሳዝናሉ፤ ጆሮዎቻቸውን ይዘጋሉ፤ እውነትን እንዳይሰሙም ይደነቁራሉ፡፡

## የአሸናፊዎች ትውልድ

ታዲያ፣ ይህ ለምን ያስደንቀናል? በመጨረሻው ቀን ዐመፅ ወይም ክህደት እንደሚኖር ተነግሮናል (2 ተሰሎንቄ 2፥3 ይመ)፡፡

በሌላ በኩል ደግሞ፣ በዚህ ወቅት የአሸናፊዎች ትውልድ እንደሚነሣም ተነግሮናል፡፡ እነዚህ አሸናፊዎች ወንዶችና ሴቶች፣ ወጣትና ሽማግሌዎች ያለባቸው ናቸው (ሐዋርያት ሥራ 2፥17-18 ይመለከቷል)፡፡ እነዚህ ጀግኖች እውነትን በጽናት የያዙ እንደሚሆኑ ነቢያትም ሆኑ ሐዋርያት ተናግረዋል፡፡ ድቅድቁ ጨለማ የሚያመጣው ችግርና የሚፈጠረው ስሕተት ለእነዚህ ተዋጊዎች መድረክ ያዘጋጅላቸዋል፡፡ በእምነታቸውና በተግባራቸው ጽናት ለእግዚአብሔር መንግሥት ወደ ፊት ይገሠግሣሉ እንጂ፣ በፍጹም ወደ ኃላ አያፈገፍጉም፡፡ በጨለማ ውስጥ እንዳለ ብርሃን በእውነት ራሳቸውን ይለያሉ፡፡ ተመሳስሎ በመኖር ሳይሆን፣ ዳንኤል እንዳደረገው በአምላካዊ ፍርሃትና በጸጋው ብቁ የማድረግ ኃይል፣ በማንኛውም የሕይወት ገጽታቸው ልቀው ይገኛሉ፡፡

የተወደዳችሁ አንባቢዎች፣ ከእነዚህ አሸናፊዎች ወገን እንደምትሆኑ ተስፋ አደርጋለሁ፡፡ ወገባችሁን በእውነት ታጥቃችሁ፣ የጽድቅንም ጥሩር ለብሳችሁ፣ ወደዚህ ታላቅነት እንድትገቡ ጸሎቴ ነው፡፡ የእምነትን ጋሻ አንሥታችሁ፣ በፊታችሁ ያለውን ሩጫ በጽናት እንደምትሮጡ፣ እስከ መጨረሻው ተቃውሞን እንደምትዋጉ ተስፋ አደርጋለሁ፡፡ አሸናፊዎች እንድትሆኑ ተፈጥራችኃል፡፡ እጅግ ከባድ የሆነውን ተቃውሞ በትዕግሥት የተቀበለው የኢየሱስ ክርስቶስ ዘር እናንተ ውስጥ አለ፡፡ የእርሱ ብርታት በውስጣችሁ አለ! የእርሱ ባሕርይ በውስጣችሁ አለ፡፡ ተስፋ ቆርጣችሁ ወይም አቋርጣችሁ እንድትወጡ፣ ወደ ኃላ እንድታፈገፍጉ፣ እንድትሰነካከሉ ወይም ተመሳስላችሁ እንድትኖሩ አይደለም የተጠራችሁት፡፡ እጅግ ድንቅ በሆነ የእግዚአብሔር ጸጋ ተባርካችሁ ነበር፡፡

የተነሣባችሁ ችግር የቱንም ያህል ታላቅ ቢሆን፣ ወደ ቀጣዩ የአገዛዝ ደረጃ እንደሚያደርሳችሁ መወጣጫ መሰላል አድርጋችሁ ቁጠሩት፡፡ እንደ ጳውሎስ ሁሉ ከደረሰባችሁ ችግር ተማሩ፡፡

> ... በሕይወት ለመኖር እንኳ ተስፋ እስክንቆርጥ ድረስ ከዐቅማችን በላይ የሆነ ጽኑ መከራ ደርሶብን ነበር፡፡ በእርግጥም የሞት ፍርድ እንደ ተፈረደብን ይሰማን ነበር፤ ይህም የሆነው ሙታንን በሚያስነሣ በእግዚአብሔር እንድንታመን እንጂ፣ በራሳችን እንዳንታመን ነው፡፡ እርሱ እንዲህ ካለው የሞት አደጋ አድኖናል፤ ያድነናልም፤ ወደ ፊትም ደግሞ እንደሚያድነን ተስፋችንን በእርሱ ላይ ጥለናል፡፡ (2ቆሮንቶስ 1፥8-10)

እርሱም ሆነ አብረውት የነበሩት በሕይወት ማለፍ የማይችሉ እስኪመስል ድረስ ጳውሎስ ላይ ከባድ መከራ ደርሶ ነበር፡፡ በደረሰበት መከራና ተቃውሞ ጳውሎስ ላቅ ወዳለው የሥልጣንና የኃይል ደረጃ ከፍ አለ፡፡ ምንጊዜም የእግዚአብሔር ጸጋ (ኃይል) ብቁ ነው፡፡ እግዚአብሔር ከማንኛውም ከባድ ሁኔታ ውስጥ መልሶ ያወጣናል፡፡

እኛ ማድረግ ያለብን በዚያ ውስጥ መጽናት ነው፤ እምነታችንን አጥብቀን መያዝ ነው፤ ምክንያቱም በሌላው ገጽታ ታላቅ ድል አለ፤ እርካታና ዕድገት አለ፡፡ ያዕቆብ እንደሚናገረው፣ ‹‹በፈተና የሚጸና እግዚአብሔር ለሚወዱት የሰጠውን ተስፋ፣ የሕይወትን አክሊል ይቀበላል›› (ያዕቆብ 1፥12)፡፡

የእግዚአብሔር ብቁ የማድረግና የማስቻል ዐቅም አላችሁ፤ የእርሱ ባሕርይና ኃይል እናንተ ውስጥ አለ፡፡ የክርስቶስ አካል ናችሁ፡፡ የአካሉ ራስ (ኢየሱስ) አይወድቅም፤ አይሸነፍም፣ አካሉም እንደዚያ መሆን አለበት፡፡ ጳውሎስ፣ ‹‹ከየአቅጣጫው ብንገፋም አንንኰታኰትም፤ ግራ ብንጋባም ተስፋ አንቆርጥም (አናቋርጥም) በማለት ጽፎአል (2ቆሮንቶስ 4፥8)፡፡

የክርስቶስ አካል በመሆናችን ተስፋ አንቆርጥም፤ አናቋርጥም! እነዚህን ቃሎች ጳውሎስ ይደጋግማቸዋል፣ ‹‹ተስፋ አንቈርጥም፤ አናቋርጥም›› (2ቆሮንቶስ 4፥1) እንደ ገና ‹‹ተስፋ አንቆርጥም፤ አናቋርጥም›› (2ቆሮንቶስ 4፥16) እነዚህን የመሳሰሉ በርካታ ጥቅሶችን መደርደር ይቻላል፡፡ በድንቅ ሁኔታ በነገር ሁሉ እንዲሳካላችሁና እንዲከናወንላችሁ ተፈጥራችኃል

በፍጹም እግዚአብሔር ትቶኛል ብላችሁ አታስቡ፡፡ እርሱ በፍጹም እንደዚያ አያደርግም፡፡ ይህን የተስፋ ቃል አድምጡ፣ ‹‹እርሱ እስከ መጨረሻው ድረስ አጽንቶ

በፍጹም እግዚአብሔር ትቶኛል ብላችሁ አታስቡ፡፡ እርሱ በፍጹም እንደዚያ አያደርግም፡፡

ይጠብቃችኋል፡፡ ወደ ልጁ ወደ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ኅብረት የጠራችሁ እግዚአብሔር የታመነ ነው›› (1ቆሮንቶስ 1፥9)፡፡ በጣም ድንቅ ተስፋ ቃል አይደለም? ታዲያ፣ እርሱ እናንተን ካልጣላችሁና ካልተዋችሁ እናንተ ራሳችሁን የምትጥሉትና የምትተውት ለምንድነው? ጽናት ይኑራችሁ፤ ጽኑዎች ሁኑ፡፡

ለመሆኑ፣ ጽኑ መሆን የሚያስገኘው ሽልማት ምንድነው? ይህን አስመልክቶ ከእግዚአብሔር አፍ የወጣ ቃል ስሙ፣

> ድል ለሚነሣውና ሥራዬንም እስከ መጨረሻው ለሚፈጽም በአሕዛብ ላይ ሥልጣን እሰጠዋለሁ፡፡ (ራእይ 2፥26)

ምንኛ ድንቅ ሽልማት ነው! ጳውሎስ፣ ‹‹ብንጸና ከእርሱ ጋር ደግሞ እንነግሣለን›› በማለት ይህንኑ የኢየሱስ ተስፋ ቃል፣ ያጸናዋል (2ጢሞቴዎስ 2፥12)፡፡ ይህ እውን የሚሆነው በሚመጣው ዓለም ብቻ ሳይሆን፣ እዚህና አሁን ጭምር መሆኑን አትርሱ፡፡ ‹‹የእግዚአብሔርን ጸጋና የጻድቅን ስጦታ ብዛት የሚቀበሉ በአንዱ በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል በሕይወት ይነግሣሉ›› (ሮሜ 5፥17)፡፡

ስለሆነም፣ በክርስቶስ ወንድሞቼና እኅቶቼ እንድትጸኑ የሚያስችላችሁ ኃይል ተሰጥቶአችኋል፡፡ በመልካም ሁኔታ ለመጨረስ የሚያስችላችሁ የእግዚአብሔር ጸጋ አላችሁ፤ ጸጋው በፍጹም አይሸነፍም፡፡ ስለሆነም፣ ሽልማት ወይም ዋጋ ለማግኘት በእምነት ሩጡ፡፡ አንድ ዓይነት መለኮታዊ ተልዕኮ መፈጸምን፣ ቁልፍ የሆነ ስፍራ መያዝን፣ ከእግዚአብሔር መንግሥት ጋር ባላችሁ ቀረቤታ፣ አጭር ጊዜ ወይም ረጅም ጊዜ ወይም የሕይወት ዘመንን በሙሉ ለሚጠይቅ ተግባር እንድታሸንፉና እንድትገዙ ተፈጥራችኋል፡፡ ይህን አጥብቃችሁ በመያዝ የሚገኘውን የበዛና የተትረፈረፈ ሕይወት የመለማመድ መብት አላችሁ፡፡ አገዛዝ ውስጥ እንድትገቡ ትጠበቃላችሁ፡፡ ለንጉሣችሁ ክብር የተለያችሁ ትሆናላችሁ፡፡ በእርግጥ ደስ የሚል ሽልማት ወይም ዋጋ አላችሁ፡፡ ሁሌም ይህን አስታውሱ፣

እግዚአብሔር ተስፋ አድርግ

አይዞህ በርታ፤

እግዚአብሔርን ተስፋ አድርግ፡፡ (መዝሙር 27፥14)

## ተጨማሪ - ሀ

## የእግዚአብሔር ልጅ ለመሆን ጸሎት

ለመሆኑ የእግዚአብሔር ልጅ መሆን የሚቻለው እንዴት ነው? በመጀመሪያና በተቀዳሚ ደረጃ፣ ጉዳዩ ኢየሱስ ክርስቶስ ያደረገላችሁን እንጂ፣ እናንተን የሚመለከት አይደለም፡፡ ወደ ፈጣሪአችሁ ወደ እግዚአብሔር መልሶ ሊያመጣችሁ እርሱ ስለ እናንተ ሕይወቱን ሰጥቷል፡፡ ለእናንተ ዘላለማዊ ሕይወት ለመስጠት የጠየቀው ዋጋ የእርሱን መስቀል ላይ መሞት ብቻ ነበር፡፡

በማኅበረ ሰቡ ውስጥ ያላችሁ ቦታ፣ ዘራችሁ፣ ቤተ ሰባዊ መሠረታችሁ፣ ሃይማኖታችሁ ምንም ይሁን ምን፣ ወይም ደግሞ በሰዎች ዓይን የሚያስመሰግን ወይም የማያስመሰግን ሕይወት ቢኖራችሁ፣ የእግዚአብሔር ልጆች መሆን ትችላላችሁ፡፡ እርሱ ወደ ቤተ ሰቡ እንድትመጡ ይፈልጋል፣ ደግሞም ይናፍቃል፡፡ ይህ በሕይወታችሁ እውን የሚሆነው ኃጢአትን ስትክዱ፣ ከእግዚአብሔር ውጪ የምትኖሩትን ኑሮ ስትተዉና ሕይወታችሁን ለጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ጌትነት ስትሰጡ ብቻ ነው፤ እንደዚያ ካደረጋችሁ በእውነት ዳግም ትወለዳላችሁ፡፡ ከእንግዲህ የጨለማ ባሪያ አይደላችሁም፤ ዳግም የተወለዳችሁ በመሆኑ የእግዚአብሔር ወንዶችና ሴቶች ልጆች ትሆናላችሁ፡፡ መጽሐፍ ቅዱስ እንዲህ ይላል፣

> ኢየሱስ ጌታ ነው ብለህ በአፍህ ብትመሰክር፣ እግዚአብሔም ከሙታን እንዳስነሣው በልብህ ብታምን፣ ትድናለህ፤ የምትጸድቀው በልብህ አምነህ ነው፤ የምትድነውም በአፍህ መስክረህ ነውና፡፡ (ሮሜ 10÷9-10)

እንግዲህ ኢየሱስ ክርስቶስ እንደ ሞተላችሁ ካመናችሁና ለራሳችሁ መኖር ሳይሆን ሕይወታችሁን ልትሰጡት ፈቃደኛ ከሆናችሁ፣ ከልባችሁ ይህን ጸሎት ጸልዩ፤ የእግዚአብሔር ልጆችም ትሆናላችሁ

*በሰማይት የምትኖር እግዚአብሔር ሆይ፣ ኃጢአተኛ መሆኔን፣ ከአንተ የጽድቅ ሚዛን የጐደልኩ መሆኔን አምናለሁ፡፡ ለኃጢአቴ የዘላለም ፍርድ ሊፈረድብኝ ይገባ ነበር፡፡ በዚያ ሁኔታ ውስጥ ስላልተውኸኝ አመሰግንሃለሁ፤ ከድንግል ማርያም የተወለደውን፣ የእኔ ኃጢአት መስቀል ላይ ተሸክሞ የሞተው አንድ ልጅህን ኢየሱስ ክርስቶስን እንደ ላክኸው አምናለሁ፡፡ በሦስተኛው ቀን ከሞት እንደ ተነሣና ጌታዬና አዳኜ ሆኖ በአንተ ቀኝ እንደ*

*ተቀመጠ አምናለሁ፡፡ ስለዚህም ዛሬ _______ ቀን 20 ______ ዓመተ ምሕረት ሕይወቴን ሙሉ በሙሉ ለኢየሱስ ጌትነት ሰጥቻለሁ፡፡*

*ኢየሱስ ሆይ አንተ ጌታዬ፣ አዳኜና ንጉሤ መሆንህን እመሰክራለሁ፡፡ በመንፈስህ አማካይነት የእግዚአብሔር ልጅ እንድሆን እንድትለውጠኝ እለምንሃለሁ፡፡ አጥብቄ ይዤው የነበረውን የጨለማ ሥራ እክዳለሁ – እተዋለሁ፤ ከዛሬ ጀምሮ እኔ ለዘላለም እንድኖር ራስህን ለሰጠኸው ለአንተ እንጂ ለራሴ አልኖርም፡፡*

*ጌታ ሆይ፣ አመሰግንሃለሁ፤ ከእንግዲህ ሕይወቴ ሙሉ በሙሉ በአንተ እጅ ነው፤ በቃልህ በተናገርከው መሠረት አታሳፍረኝም፡፡*

አሁን ድነሃል፤ የእግዚአብሔር ልጅ ሆነሃል፡፡ በዚህ ቅጽበት መላእክት ከአንተ ጋር ደስ ይሰኛሉ! እንኳን ወደዚህ ቤተ ሰብ መጣህ! በተቻለህ መጠን በፍጥነት ሦስት ጠቃሚ ርምጃዎች እንድትወስድ እመክርሃለሁ፡፡

1. ስላደረግኸው ውሳኔ ቀድሞኑ አማኝ ለነበረ ሰው አካፍል፡፡ ጨለማን የምናሸንፍበት አንዱ መንገድ ከአንደበታችን የሚወጣ ምስክርነት ነው (ራእይ 12፥11 ይመለከቷል)፡፡

   - በwww.messengerinternational.org. በኩል Messenger International ከተባለው የአገልግሎት ድርጅታችን ጋር መገናኘት ትችላህ ከአንተ መስማት እንወዳለን፡፡

2. የእግዚአብሔርን ቃል የሚያስተምር ጥሩ ቤተ ክርስቲያን አባል ሁን፡፡ በሚኖረው የአገልግሎት ዘርፍ ተሳተፎ አድርግ፡፡ ገና አዲስ የተወለዱ ልጆችን ወላጆቻቸው፣ ‹‹ከእንግዲህ ራስህን ቻል›› አይሏቸውም፡፡ አሁን አንተ በክርስቶስ ሕፃን ነህ፤ እግዚአብሔር አባትህ ለማደግ የሚረዳህ ቤተ ሰብ ሰጥቶሃል፡፡

3. የውሃ ጥምቀት ሥርዐት ፈጽም፡፡ ምንም እንኳ አሁን የእግዚአብሔር ልጅ ብትሆንም፣ ጥምቀት በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል ሕይወትህን ለእግዚአብሔር መስጠትህን ለተፈጥሮአዊውም ሆነ ለመንፈሳዊው ዓለም በግልጥ የምትመሰክርበት ሥርዐት ነው፡፡ ኢየሱስ አዳዲስ አማኞችን፣ ‹‹በአብ፣ በወልድና በመንፈስ ቅዱስም ስም›› እንድናጠምቅ በመናገሩ፣ ታዛዥነታችንንም የምናሳይበት ተግባር ነው (ማቴዎስ 28፥19)፡፡

በክርስቶስ በጀመርከው አዲስ ሕይወት መልካሙን ሁሉ እመኝልሃለሁ፡፡ አገልግሎታችን በመደበኛነት ደረጃ ይጸልይልሃል፡፡ ከእንግዲህ በእውነት ጸንተህ መኖር ጀምር!

## ተጨማሪ - ለ

# የተለያዩ የመጽሐፍ ቅዱስ ትርጉሞች የተጠቀምኩበት ምክንያት

አንዳንዶ፣ ‹‹የተለያዩ የመጽሐፍ ቅዱስ ትርጕሞች የተጠቀምከው ለምንድነው? የአንዳንድ ጥቅሶችን የተወሰነ ክፍል ብቻ የወሰድከው ለምንድነው?›› የሚሉ ጥያቄዎች ይገጥሙኛል፡፡

1. መጀመሪያ ላይ መጽሐፍ ቅዱስ የተጻፈው በ11,000 ዕብራይስጥ፣ አረማይክና፣ ግሪክ ቃላት ነበር፡፡ አብዛኞቹ የእንግሊዝኛ ትርጉሞች ግን በግምት 6,000 ቃላት ነው የሚጠቀሙት፡፡ እንግዲህ ከዚህ አሐዝ ብቻ በመነሣት ትርጉሞቹ ውስጥ አንዳንድ ነገሮች ሊያመልጡ፣ አንዳንዶም ሊጠፉ ይችላሉ የሚል መደምደሚያ ላይ ብንደርስ አግባብ ይሆናል፡፡ በርካታ የእንግሊዝኛ ትርጉሞች መጠቀሙ፣ እግዚአብሔር ለእኛ ማስተላለፍ የሚፈልገውን መልእክት በሙላትና በጥልቀት እንድናገኝ ይረዳል፡፡

2. የምንጠቀመው በአንድ ትርጉም ብቻ ከሆነና፣ አንባቢው አንድን ጥቅስ የሚያስታውስ ከሆነ ብዙ ከመለመዱ የተነሣ ብቻ አእምሮው በቀላሉ ወደዚያ ሊወሰድ ይችላል፡፡ የተለያዩ ትርጉሞች መጠቀሙ ግን እንዲህ የመሆኑን ዕድል ይቀንሳል፤ የአንባቢው ትኩረት ቅዱስ ቃሉ ላይ ብቻ እንዲሆን ይረዳል፡፡

3. መጽሐፎቼን በምጽፍበት ጊዜ አጽንዖት መስጠት የፈለግሁትን ሐሳብ በተሻለ ሁኔታ ሊያሳይልኝ የሚችለው የትኛው እንደ ሆነ ለመወሰን፣ በትንሹ ከአምስት እስከ ስምንት የተለያዩ ትርጕሞች፣ የተመረጡ የቅዱሳት መጻሕፍትን ክፍሎች በጥንቃቄ አነባለሁ፡፡ የምጠቀመው ትርጕሞችን ሳይሆን ፍቺ የሚሰጡ መጻሕፍትን ከሆነ እየተጠቀምኩበት ያለው ፍቺ ሐሳብ ዕውቅናና ተቀባይነት ካለው ትርጉም ያፈነገጠ እንዳይሆን አረጋግጣለሁ፡፡

4. አንዳንዴ ሙሉውን ጥቅስ የማልወስድበት ምክንያት መጽሐፍ ቅዱስ ምዕራፎችና ቁጥሮች እንዲኖሩት የተደረገው በ1227 ዓ.ም በመሆኑ ነው፡፡ መጀመሪያ ላይ መጽሐፍ ቅዱስ በምዕራፎችና በቁጥሮች ተከፋፍሎ አልነበረም የተጻፈው፡፡ ከወንጌሎቹ መመልከት እንደሚቻለው ብዙ ጊዜ ኢየሱስ ከብሉይ ኪዳን ጥቅሶች የተወሰኑ ጥቅሶችን ብቻ ነበር የተጠቀመው፡፡

## ለማስታወስና ለውይይት

1. ከአጀማመራችን ይልቅ አፈጻጸማችን የበለጠ አስፈላጊ መሆኑን ትስማማላችሁ ወይስ አትስማሙም? መልሳችሁን አብራሩ፡፡
2. ‹‹ጽናት ያለው መንፈስን›› እንዴት ትገልጹታላችሁ?
3. የእግዚአብሔር ጸጋ ትርጉም ምንድነው ትላላችሁ? ይህን መጽሐፍ በማንበባችሁ ስለ ጸጋ ያላችሁ ግንዛቤ ያደገው እንዴት ነው?
4. ክርስቲያኖች፣ ‹‹በሕይወት መግዛት›› ያለባቸው የመሆኑ እውነት፣ ለእናንተ ያለው አንድምታ ምንድነው (ሮሜ 5፥17.... ይመለከቷል)? ይህ እውነት ቤተ ሰባችሁ ላይ፣ ሥራችሁ ላይ፣ ለማንኛውም የሕይወት ተግዳሮቶች የምትሰጡት ምላሽ ላይ ያመጣው ለውጥ ምንድነው?
5. ብዙ ክርስቲያኖች ሕይወት ላይ እየነገሡ አይደለም፡፡ እንዲህ የሆነው ለምን ይመስላችኋል?
6. አማኝ በሕይወት በሚገጥሙ ተግዳሮቶች መግዛት እንዲችል የሚረዱ አንዳንድ መሠረታዊ ዝንባሌዎችና ተግባሮች ምንድናቸው?
7. የሰይጣን ዓላማና ዕቅድ ምንድነው (ዮሐንስ 10፥10 ይመልከቷል)? ባለፉት ጥቂት ሳምንቶች ሰይጣን በሕይወታችሁ፣ ‹‹መስረቅ፣ ማጥፋትና መግደል›› ሲፈጽም ያያችሁት እንዴት ነበር፡፡
8. ኢየሱስ በዚህ ዓለም እስካለን ድረስ መከራ እንደሚኖርና እርሱ ግን፣ ‹‹ዓለምን አሸንፌዋለሁ›› በማለት ነግሮናል (ዮሐንስ 16፥33)፡፡ ይህ አሸናፊዎችና ድል አድራጊዎች እንድንሆን የሚረዳን እንዴት ነው?
9. ትዕቢተኛ ሰው የሚያሳያቸው አንዳንድ ባሕርያት ምንድናቸው? ትሑት የሆነ ሰው ባሕርያትስ ምንድናቸው?
10. ሐዋርያው ጴጥሮስ፣ ‹‹ትሕትናን ልበሱ›› በማለት የኢየሱስ ተከታዮችን ይመክራል (1ጴጥሮስ 5፥5)፡፡ ተግባር ላይ ሊውል በሚችል መልኩ ምን ማለቱ ይመስላችኋል?
11. ዲያብሎስን ለመቃወም የምንጠቀምባቸው አንዳንድ መንገዶች ምንድናቸው?
12. መከራ ወይም ችግር በክርስቲያን ሕይወት ውስጥ ይህን ያህል ጠቃሚ እውነታ የሆነው ለምንድነው?

13. ጽኑ በሆነ ክርስቲያን ሕይወት ውስጥ ጸሎት ያለው ድርሻ ምንድነው?

14. ‹‹አጥብቆ›› መጸለይን እንዴት ትገልጹታላችሁ?

15. በመንግሥተ ሰማይ የተለያየ ዓይነትና የተለያየ ደረጃ ያለው ሽልማት የሚኖረው ለምንድነው?

16. ከዚህ መጽሐፍ የተመለከታችኋቸው ዐቢይ ሐሳቦችን ስታስታውሱ ከእግዚአብሔር ጋር ስትመላለሱ መንፈስ ቅዱስ፣ ‹‹ጽናት ያለውን መንፈስ›› ለማዳበር እንዲጨምርላችሁ የምትፈልጉት ምንድነው?

## ተስፋ እንዳትቆርጥ የሚያስፈልግህ ኀይል

# ጽናት

አሁን እጅህ ያለው መጽሐፍ፣ ጽናትን አስመልክቶ ጆን ቢቨሬ ካዘጋጀው ትምህርት አንዱ ነው፡፡ ይህን መጽሐፍ ማንበብ፣ ተያይዞ ካለው DVD እና ከኢንተርኔት መውሰድ በሚቻለው አጋዥ የትምህርት መሣሪያዎች መጠቀም፣ የዚህን ብርቱና ሕይወት ለዋጭ ተከታታይ ትምህርት ማንኛውንም ክፍል ማጥናት ያስችልሃል፡፡ ትምህርቱን በሚገባ ማጥናት የክርስትና ጉዞህን ያጐለብታል፤ የበለጠ እግዚአብሔርን እንድታገለግልም በጐ ተፅዕኖ ያሳድርብሃል፡፡




ሙሉው ትምህርት የሚከተሉት አካትቶአል -

- <u>ጽናት ዋናው መጽሐፍ</u>
  ከጠቅላላው ትምህርት ታትሞ የሚገኘው ይኸኛው ብቻ ነው፡፡ የመጽሐፉ ኤሌክትሮኒክ ቅጂ አጋዥ ዲስኩ ውስጥ በebook እና በPDF ይገኛል፡፡

- <u>ጽናት አጋዥ ዲስክ</u>
  ይህ አብዛኞቹ ትምህርቶች በዲጂታል የሚገኙበት ተያይዞ ያለው ዲስክ ነው፡፡

- <u>ጽናት መልስ መስጫ መጽሐፍና የጥናት መመሪያ</u>
  ይኸኛውም ዲስኩ ውስጥ በebook እና በPdf ይገኛል፡፡

- <u>ጽናት መጽሐፍ በድምፅ</u>
  ጽናት ዋናው መጽሐፍ የያዛቸው 18 ምዕራፎች በmp3 በአማርኛ የሚነበቡበት ነው፡፡

- <u>ጽናት የቪድዮ ክፍለ ትምህርት</u>
  ለዓይነት የሚሆኑ ጽናት ክፍለ ትምህርቶች በዚህ ዲስክ ውስጥ ይገኛሉ፡፡ 12 የቪዲዮ ክፍለ ትምህርቶችን ከኦንላይን በነጻ መውሰድ ይቻላል፡፡

- <u>ጽናት ክፍለ ትምህርት በድምፅ</u>
  12 የድምፅ ክፍለ ትምህርቶች በሙሉ በmp3 የሚገኙበት ነው፡፡

- <u>እንስት አንበሶቹ ይነሣሉ</u>
  ዲስኩ ውስጥ በebook እና በPdf ይገኛል፡፡

## ተስፋ እንዳትቆርጥ የሚያስፈልግህ ኀይል

# ጽናት

### ጽናት ክፍለ ትምህርት ስላካተታቸው ነገሮች ተጨማሪ መረጃ

mp3 የድምፅ ፋይሎች - እነዚህን በድምፅ ማጫወቻ፣ በስማርት ፎን ወይም በኮምፒዩተር መውሰድ ይቻላል፡፡

Pdf ዲጂታል ፋይሎች - በታብሌት ወይም በኮምፒዩተር መውሰድ ይቻላል፡፡ በቀላሉ ሊነበቡ፣ ሊታተሙና ሊባዙ ይችላሉ፡፡ ከጽሑፉ ኮፒ ማድረግና መለጠፍ ትችላላችሁ፡፡

Ebook - የታተመ መጽሐፍ በዲጂታል የሚገኝበት ነው፡፡ በታብሌት/ፓድ፣ በኮምፒዩተር ወይም ስማርት ፎን መጫንና ማንበብ ይቻላል፡፡

አጋዥ ዲቪዲ - በተለያየ ምክንያት ዲቪዲውን በቪዲዮ ማጫወቻ መክፈት ካልቻላችሁ፣ ኮምፒዩተራችሁ ላይ መጫንና ተራ በተራ ፋይሎቹን መክፈት ሞክሩ፡፡ አሁንም ችግር ከገጠማችሁ ስለ ኮምፒዩተር ለሚያውቅ ሰው ንገሩና እንዲረዳችሁ ጠይቁት፤ ከዚያም ለጥናታችሁ ተጠቀሙባቸው፡፡

እነዚህ ክፍለ ትምህርቶች ሁሉ ለእናንተ የተሰጡ ናቸው፡፡ ይህን ዲስክ ኮፒ ለማድረግ፣ ጽሑፎችን ወይም ሌሎች ነገሮችን ኮፒ ለማድረግና ከእነዚህ ፋይሎች ማንኛውንም ለወዳጆቻችሁ ኢ-ሜይል ለማድረግ፣ ጠቃሚ የመሰሏዋችሁ ነገሮችን በወርድ ዶኩሜንት ኮፒ ለማድረግና ፔስት አድርጋችሁ ትምህርቶቹን ለቤተ ክርስቲያናችሁ ለመላክ፣ ሌሎች እንዲጠቀሙባቸው በኢንተርኔት ለመጫን ነጻነት ይሰማችሁ፡፡ የእግዚአብሔርን ቃል ትክክለኛ ትምህርትና ኀይል ያለው የክርስትና ሕይወትን ለሚራቡ ሁሉ እነዚህን አጋዥ ምንጮች አካፍሉ፡፡

እነዚህንና ሌሎች የጆንና የሊዛ ቢቨሬ ትምህርቶች

ከwww.MessengerInternational.org

www.Cloudlibrary.org መውሰድ ትችላላችሁ




ይህ ዲስክ ከጆን ቢቨሬ በግል ለእናንተ የተሰጠ ነው፡፡ ይህን ብርቱ ትምህርት በስፋት ለማጥናትና ለሌሎችም ለማካፈል የሚረዱዋችሁ ትምህርቶች ለማግኘት በር ይከፍትላችኋል፡፡ የዚህን ካሪኩለም የትኛውንም ክፍል እንድታከፋፍሉና እንድታሰራጩ ትበረታታላችሁ፡፡ ፋይሎችን ለሌሎች ኢሜል ማድረግ፣ ለተማሪዎች ማካፈል፣ በኢንተርኔት መጫንና ማተም ወይም ቅጂዎችን ማባዛት ትችላላችሁ፡፡ በተለይም በየትኛውም ቦታ ያሉ ክርስቲያን አማኞችን ሁሉ ለማነቃቃትና ለማበረታታት ተዘጋጅቷል፡፡

እነዚህና ሌሎች የጆንና የሊዛ ቢቨሬ ትምህርቶች (በቋንቋችሁ የሚገኙ ከሆነ)

ከ www.MessengerInternational.org
www.CloudLibrary.org መጫን ትችላላችሁ

በብዙ ቋንቋዎች የተዘጋጁ ተጨማሪ ጽሑፎችን ለመመልከት በYoutube.com እና Yuku.com እና በሌሎች ማኅበራዊ ሳይቶች መጫን ይቻላል፡፡

«ለታላቅ ድል እንድንበቃ ሊያጠነክረን ይጠቀምበታል እንጂ እግዚአ ብሔር ችግርን አይፈጥርም፤ ማሸነፍ የምንችልበትንም ኃይል ሳይሰጠን በፍጽም አይመራንም»

ጆን ቢቨሬ - ጽናት

## በሚገባ ለመጨረስ የሚያስፈልገውን ሁሉ አግኝተሃል!

ክርስቲያኖች እንዲሁ፣ «ውልብ ብለው» እንዲያልፉ አልተፈጠሩም። ከአስቸጋሪ ሁኔታዎች በላይ ከፍ እንድትልና ታላቅነትን እንድታሳይ ተፈጥረሃል! በዚህ አነቃቂ መጽሐፍ ተነባቢው ጸሐፊ ጆን ቢቨሬ በሚገባ ለመጨረስ የሚያስችለው ምን እንደ ሆነ ይገልጻል። ከኑሮ ዘዴ ባለፈ መልኩ፣ "ጽናት" የተሰኘው፣ ይህ መጽሐፍ ከሐዋርያው ጳውሎስ ጋር፣ «በችግሮቼ ደስ ይለኛል» ማለት የሚያስችል አዲስ የአእምሮ ዝንባሌ ያቀርብልናል። መጽሐፍ ቅዱስን መሠረት ያደረጉት እውነቶቹ በየትኛውም የሕይወት ዘመንህ እንድትለመልም ያዘጋጁሃል።

## የጽናት ተመክሮን ተካፈል!



ጆን ቢቨሬ ከፍተኛ ተነባቢነት ያላቸው መጻሕፍት ደራሲና ተወዳጅ የኮንፈረንስ ተናጋሪ ነው። እንደ እርሱ የተዋጣለት ደራሲ የሆነች ባለቤቱ ሊዛና እርሱ፤ በ1990 ጆን ቢቨሬ ሚኒስትሪስ የተሰኘ አገልግሎት መሥርተዋል።
በ214 አገሮች የሚሰራጨው ሜሴንጀር የተባለው ሳምንታዊ የቴሌቭዥን ፕሮግራማቸውን ጨምሮ ባለ ብዙ ገጽታዎች የሆነው አገልግሎት ዓለም ዓቀፍ ሽፋን ያለው ወደ መሆን አድጓል። ቢቨሬ Breaking Intimidation, The Fear of the Lord እና Undercover የተሰኙትን ጨምሮ በርካታ መጻሕፍት ጽፏል።

የዚህ ጽናት የተሰኘው መጽሐፍ ማጥኛ ዲቪዲ ተካትቶአል፡፡



www.CloudLibrary.org
www.MessengerInternational.org
ከተሰኘው ድረ ገጽ እነዚህንና ሌሎች ጽሑፎችን መጫን ይቻላል።

Messenger International
MessengerInternational.org

ይህ መጽሐፍ የደራሲው ስጦታ ነው አይሸጥም።

በፌስቡክ እና በቲዊተር ጆን ቢቨርን ተከታተሉ